# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 16

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች ለፍ/ቤቶች፣ ለሕግ ባለሙያዎች፣ ለሕግ ትምህርት ቤቶችና በአጠቃላይ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ጥረታችን ቀጥሏል፡፡

በዚህ ቅጽ 16 በ2006 ዓ.ም.የተሰጡ ውሣኔዎችን በድረ ገጻችን አስቀምጠናል፤ ታትሞም በቅርቡ ይሠራጫል ቅጽ 15 የታተመው ሐምሌ 2006 ዓ.ም. በመሆኑ የዚህ የአሁኑ ዕትም ውሣኔዎች በአንፃራዊነት ቶሎ ማሠራጨት ተችሏል፡፡ ከዚህ ባነሰ አጭር ጊዜያት ውስጥ ውሣኔዎችን አሣትሞ ለማሠራጨት ብርቱ ጥረት እያደረግን ሲሆን የዚህን ዕትምና የቀደሙትን ቅጾች ውሣኔዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረ ገጽ (www.fsc.gov.et) ማግኘት እንደሚቻል እያስታወስኩ በውሣኔዎቹ ጥራትም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ገንቢ አስተያየቶች እና ትችቶች ለሥራችን መሻሻል ስለሚያግዙን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን በአክብሮት እገልጻለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ ክፍሌ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

# በ2006 ዓ.ም. የሰበር ችሎት
# የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ወሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የፍትሐ ብሔር ህግ ሥነ-ሥርዓት** | | | | | **1** |
| 1. | አንድ ክስ እንደቀረበ የሚቆጠረው ክስ የቀረበበት ጽሁፍ በፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ስለመሆኑ፡- የመስቀለኛ ይግባኝ ክርክር ስለሚመራበት የህግ አግባብ፣<br>በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚቀርብን መስቀለኛ ይግባኝን በተመለከተ በህግ በግልፅ የተቀመጠ ድንጋጌ ባለመኖሩ ምክንያት በመደበኛነት የተቀመጡት የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው ስለመሆኑ፣መልስ ሠጪው ወገን የሚያቀርበው ይግባኝ ማመልከቻ ግልባጭ ለይግባኝ እንዲደርስ ሊደረግ የሚቻለው ይግባኙ ያልተሰረዘ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 213(1) ፣337 ፣338 ፣ 340(2) | 92043 | ቱሌን ዩኒቨርሲቲ አሲስታንስ ፕሮግራም ኢትዮጵያ<br><br>እና<br>ዶ/ር ዮዲት አብርሃም | መጋቢት 22/2006 | 2 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 58(ሀ)፣63 | 91493 | አቶ አየለ ሚናሞ<br>እና<br>አቶ አሰፋ ባዩ | ሰኔ 03/2006 | 6 |
| 3. | በአንድ ክርክር ችሎት በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ በሌላ ችሎት ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ውሳኔ ተሠጥቶ ከሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የተላለፈውን ውሳኔ በአግባቡ በማጤን በጭብጥነት ሊይዘው ስለሚችልበት አግባብ፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.247 እና 248 | 94293 | ሸዋ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ አሸብር አበበ | ሚያዝያ 9/2006 | 10 |
| 4. | ከጭብጥ አያያዝ ጋር በተገናኘ በአንድ ወገን ተቆጥሮ የቀረበን ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በሚል ወይም ህጋዊ ተቀባይነት ባለው ሌላ ምክንያት መሰማት አይገባውም የሚል ግልፅ ትእዛዝ ሳይሰጥበት የክርክሩ ጭብጥ በአንደኛው ወገን ማስረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ መደረጉ ተገቢ የክርክር አመራር ስርዓት ስለአለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 255፣257፣258፣259 | 95026 | አቶ ዮናስ በቀለ<br>እና<br>አቶ ብርሃኑ ኩምሳ | መጋቢት 8/2006 | 14 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ክስ በሚሰማበት ወቅት የቀረ ከሳሽ ፍ/ቤቱን በበቂ ሁኔታ የቀረበትን እክል ካስረዳ ፍ/ቤቱ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ሊያደርግ የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(2) | 97555 | ወ/ሮ ሳኒያ ከድር<br>እና<br>የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ | ሐምሌ 14/2006 | 17 |
| 6 | ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ላይ ግራ ቀኙ መልስ እንዲሰጡበት ሳይደረግ እና የመከላከያ መልሳቸውን ሳያቀርቡ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ ፍርድ መስጠት ተገቢ ስላለመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)(ሠ)(መ)፣91(1) | 95620 | በቂርቆስ ክ/ከተማ የወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ፤ አለቃ ከድር አህመድ(አራት ሰዎች) | ግንቦት 07/2006 | 20 |
| 7 | በተከራካሪ ወገኖች በአንድ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የእርማት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔ ያረፈበት ነጥብ ላይ ብቻ ስለመሆኑ፣ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 | 95649 | ወ/ሮ ኢትዮጵያ ንጉሴ<br>እና<br>አዲስ ጡብ ማምረቻ ድርጅት | ሚያዝያ 6/2006 | 25 |
| 8 | በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.1851 | 90361 | እነ ወ/ሮ አለዊያ ዑመር (ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ሐሺም ሁሴን | የካቲት 26/2006 | 28 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የመቃወም አቤቱታ የሚመራው በመደበኛው የክርክር አመራር ሰርዓት ስለመሆኑ፡-<br>- የመቃወም አቤቱታን የሚሰማው ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.<br>222፣223፣234፣358፣359፣360(1) እና(2) | 86398 | ወ/ሮ አሰለፉች ይመር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስመረት ተወልደ(ሶስት ሰዎች) | ሐምሌ 28/2006. | 33 |
| 10 | አንድ ክስ ሲቀርብ በክስ ማመልከቻው ላይ መገለፅ ከሚገባቸው ነገሮች መካከል አንዱ የክሱ ምክንያት እና ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችና እነዚሁ የተፈጠሩበት ጊዜና ስፍራ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ80(2)፣213(1)፣216(1)፣222 (1)(ረ) | 91329 | ወ/ሮ አስመረት ኃ/ሚካኤል<br>እና<br>እነ አቶ ተስፋዬ ጥላሁን (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 24/2006 | 39 |
| 11. | የማይገባውን ክፍያ የከፈለ ሰው ገንዘቡን ከከፈለበት ቀን አንሥቶ ሕጋዊ ወለድ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው፣ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው እምነትን በሚያጓድል ሁኔታ ክፍያውን ተቀብሎት በሆነ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2164(2) | 91643 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ<br>እና<br>ካኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ጥር 15/2006 | 43 |
| 12 | በህብረት ሥራ ማህበራትና በአባሎቻቸው ወይም በቀድሞ አባላቸው ወይም በህብረት ስራ ማህበር አባላት ወይም የቀድሞ አባላትና በማህበሩ | 91745 | አቶ ዳዊት አበበ<br>እና<br>አንድነት ቁጥር 4 የጋራ | የካቲት 12/2006 | 46 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የሽምግልና ጉባኤው ውሳኔ ሳይሰጥበት ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ዳኝነት ለማየትና ለመወሰን የማይችሉ ስለመሆኑ፣የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37፣ አንቀጽ 79(1) እና አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 | | መኖሪያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች) | | |
| 13 | በውሳኔ በተቋጨ የክስ መዝገብ ላይ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31 | 93171 | ወ/ሮ ሴቴ ከበደ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስናቁ ፋንታዬ (ሦስት ሰዎች) | ግንቦት 8/2006 | 50 |
| 14 | በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሚጋችነት ሊቀርቡ ስለሚችሉበት ስርዓት፣ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ አለመገኘት የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 57፣ 58(1)፣ 60፣61፣62፣ 63 እና 197(1) | 94302 | ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ<br>እና<br>ፋርማ ብርብር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ሚያዝያ 7/2006 | 53 |
| 15 | በአንድ ክርክር ሂደት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን የፌዴራል የሚያደርገው የነበረ ሁኖ እያለ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ስልጣን ሳይኖረው ስረ ነገሩን አስተናግዶ ዳኝነት ከሰጠ | 95033 | አቶ ስንታየሁ ተፈሪ<br>እና<br>ወ/ሮ ማርታ በቀለ | መጋቢት 25/2006 | 57 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በኋላ ይኼው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሠጠውን ዳኝነት ተቀብሎ ከወጣ በኋላ በሌሎች ጉዳዩን የፌዴራል ሊያደርጉ በማይችሉ ተከራካሪ ወገኞች መካከል የተሰጠው ውሳኔ ከመነሻውም የፌዴራል ጉዳይ ነው ብሎ መወሰን አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43(1)፣ አዋጅ ቁ.25/88 | | | | |
| 16 | በክርክር ወቅት ጣልቃ ልግባ የሚለው ወገን በተከራካሪ ወገኖች መካከል ባለው ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ባይሆን በምን አግባብና መልኩ  መብቱንና ጥቅሙን የሚጎዳ መሆኑንና አዲስ ክስ በማቅረብ ለማስቀረት የማይቻል መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41(2) | 95934 | አቶ አስፋው ንዳ<br>እና<br>ወ/ሮ እየሩሳሌም አየነ (ሁለት ሰዎች) | ግንበት<br>18/2006 | 62 |
| 17 | ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ የመጀመሪያውን ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድን ካሻሻለው ወይም የለወጠው እንደሆነ በትችቱ ላይ ለይግባኝ ባዩ የሚገባውን ዳኝነት ዘርዝሮ መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182(1)፣348(1) | 92903 | ወ/ሮ ስላስ ረዳ<br>እና<br>ወ/ሮ ለተሚካኤል ገ/ሐዋሪያት(ሁለት ሰዎች) | ሚያዝያ<br>24/2006 | 66 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የንግድ ህግ** | | | | **70** |
| 18 | ለቼኩ መሰጠት መሰረት የሆነውን ውል እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለውን ህግ ሳይመለከቱና በተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ፍሬ ነገሩን ሳያጣሩ የሚሰጥ ዳኝነት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 90434 | ሉሃናአንጂነሪግኮንስትራክ ሽንኃ.የተ.የግልማህበር<br>እና<br>ማክሮጠቅላላስራተቋራጭኃ .የተ.የግልማህበር | ሰኔ 06/2006 | 71 |
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | **77** |
| 19 | አንድ ሠራተኛ በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሠረት በአሰሪ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታን አለመወጣቱ ስለሚያስከትለው ውጤት፣ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 13(2)፣13(7) | 90570 | አቶ ፍፁም አስታጥቀ ወኪል<br>እና<br>የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት | ጥር 27/2006 | 78 |
| 20 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚፈጠር የስራ ግንኙነትን መነሻ በማድረግ ሰራተኛው በሕግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ፡- አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) | 92410 | ቻይና ሀይ ዌይ ግሩፐ ሊሚትድ<br>እና<br>አቶ ውብሸት እንግዳው | ጥር 29/2006 | 82 |
| 21 | የመድን ዋስትና የገባ የመንግስት የልማት ድርጅት በአንድ ሰራተኛው ላይ ለደረሰ የአካል ጉዳት ተጠያቂ የማይሆነው የተገባው የመድህን | | አቶ ምህረት አለነ ገረመው | ሐምሌ 29/2006 | 86 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሽፋን በአዋጁ የተጠበቀውን መጠን የሚሽፈን ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>በአዋጁ ስሌት ለአነሰ መጠን ያህል የመድህን ሽፋን አሰሪው ተጠያቂ ስለመሆኑ፣<br>በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1)፣ አንቀጽ 109(3) ,134(1) | 97512 | እና<br>የኢትዩጵያ ቱሪስት<br>ንግድ ስራ ድርጅት | | |
| 22 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደርግ የቅጥር ውሉ ላይ በግልፅ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ካልተስማሙ በስተቀር አሰሪው የሙከራ ጊዜ ነው ብሎ በሚያስበው ጊዜ ውስጥ የሰራተኛውን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የማይችል ስለመሆኑ፡- አዋጅ 377/1996 አንቀፅ 11(3) | 98052 | በርሄ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ<br>ተቋራጭ<br>እና<br>አቶ ገመቹ አዱኛ | ሐምሌ 14/2006 | 92 |
| 23 | የአዋጅ ቁጥር 377/96 የተፈፃሚነት ወሰን በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚቋቋም በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም፤ በአዋጁ በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ሕግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 3 | 92152 | ግርማ ደሳለኝ<br>እና<br>ወጣቶች ገነት የመጀመሪያ<br>ደረጃ ት/ቤት | የካቲት 11/2006 | 95 |
| 24 | የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6ወር ጊዜ ውስጥ | 96458 | ኢትዮጵያ የርቀት<br>ትምህርት ኮሌጅ | ሐምሌ 29/2006 | 98 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፣<br>የጳጉሜ ቀናት በይርጋ ቀናት የማይካተቱ ስመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4)፣የፍ/ሕ/ቁ. 1860(3) | | እና<br>ዶ/ር ደሣለኝ ተመስገን | | |
| 25 | ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ በአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ አሰሪው ለሰራተኛው መክፈል የሚገባውን ሒሳብ ካልከፈለ ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ ለሰራተኛው እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ደሞዙን ያህል አሰሪው እንዲከፍለው ሰራተኛው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በመጠየቅ ሊያስወስን የሚችል ስለመሆኑ-<br>አዋጅ ቁ.377/ 1996 አንቀፅ 38 | 98724 | ሙኒሽ ካፌ ድርጅት(ሙኒሽ ጀርመን ቤከር እና ካፌ)<br>እና<br>አቶ ዳዊት ፀጋው | ሐምሌ 14/2006 | 101 |
| 26 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ያለ የሥራ ግንኙነት በተቋረጠ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የክፍያ ጥያቄ ያለበት አካል መብቱን ካልጠየቀ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣ በተጨማሪነት ስድስት ወር ከሞላው(ካለፈው) በኃላ የሁለቱ የስራ ግንኙነት ቢቀጥል እንኳን አስቀድሞ የታገደውን የስንብት ክፍያ ጥያቄን ከአዋጁ ድንጋጌ ይዘት አኳያ | 92302 | አቶ ርፅሶም እምባፍራሽ<br>እና<br>ኢትዮ ቴሌኮም | ጥር 26/05/06 | 105 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የይርጋ ጊዜን ሊያቋርጥ የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>አዋጅ 377 አንቀፅ 162(3)፣162(4) | | | | |
| 27 | አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ በሚደርስበት የጤንነት ችግር ምክንያት አሰሪው የአንድ ወር የህመም ፍቃድ ሰጥቶት ነገር ግን በተሠጠው ጊዜ ውስጥ ከህመሙ ማገገም ካልቻለ ተጨማሪ የህመም ፍቃድ ከግማሽ ደመወዙ ጋር እንዲያገኝ ሊደረግ የሚችል ስለመሆኑ፡-<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 85(1)፣86(2) | 99026 | አቶ አብርሃም ታደለ<br>እና<br>ጥቁር አባይ ትራንስፖርት ኃላ/የግል/ማህበር | ሐምሌ 17/2006 | 108 |
| 28 | የሥራ ውሉ ሊጠናቀቅ የአንድ ወር ጊዜ ብቻ የቀረው በሆነ ጊዜ አሰሪው የስራ ውሉ ከሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ከ1ወር በፊት የሥራ ውሉን ያቋረጠ እንደሆነ ሊከፍል የሚገባው የ1 ወር ደመወዝ ብቻ እንጂ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፤<br>አዋጅ ቁጥር377/96 አንቀፅ 43(4)(ሀ)፣36 | 95392 | የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት<br>እና<br>አቶ ሽመልስ አለሞ | ግንቦት 06/2006 | 112 |
| 29 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ የውል ግንኙነት ተዋዋይ ወገኖች የገቡትን ግዴታ በቅንነት ይፈፅማሉ ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ፣ በአሰሪውና ሰራተኛው መካከል በሚደረግ | 92423 | የሺሐረግ ታደሰ<br>እና | ጥር 16/2006 | 116 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሥልጠናና የት/ት ውል መሰረት አሰሪው የሚጠበቅበትን ድጋፍ ለሰራተኛው የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1732፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 83 (3)፣ አንቀፅ 84 | | የአምቦ ማዕድን ውሃ አ/ማ | | |
| 30 | አንድ የስራ ውል በሰራተኛው አነሳሽነት እንደነገሩ አግባብ በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 31 እና 32 | 93511 | አቶ ደረሰ ወርቁ<br>እና<br>በርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ | የካቲት 24/2006 | 121 |
| 31 | በፍትሐ ብሔር ክርክር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር ማስረዳት እንደሚጠበቅበት እና በአንፃሩም ግዴታ ፍርስ ነው ወይም ተለውጧል የሚለው ወገንም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>ሠራተኛው በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ላልሰራው ስራ ደሞዝ ስለሚጠይቅበት አግባብ፣<br>በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 54(1)፣54(2)<br>በፍ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና(2) | 93532 | አቶ በኃይሉ ደቦጭ አንበሴ<br>እና<br>ኢትዮጵያ ገብራት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ጥር 12/2006 | 125 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 32 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ የስራ ግንኙነት የተነሳ ለተወሰነ ጊዜ ለፕሮጀክት ስራ መደብ የተቀጠረ ሠራተኛ ከአንድ የፕሮጀክት ወደ ሌላ የፕሮጅክት ስራ አዘዋውሮ ማሰራት በአሰሪውና ሰራተኛው መካከል ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ግንኙነት ተፈጥሯል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ. 377/96 አንቀፅ 30፣ አንቀፅ 10 | 93813 | ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር<br>እና<br>ባዩ ጠበቃ አደም ታደለ | የካቲት 13/2006 | 130 |
| 33 | አንድ ሰራተኛ ሲከፈለው የነበረው የደሞዝ መጠን ከፍተኛ መሆን የሥራ ስንብት ክፍያን ከመጠየቅ የሚያግደው ስላለመሆኑ፣<br>አዋጅ 377/1996 አንቀጽ 39 እና አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2(2)(ሸ) | 93828 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ<br>እና<br>ካፒቴን እንድሪያስ ጀምሬ | የካቲት 11/2006 | 135 |
| 34 | አንድ ሰራተኛ የሥራ ውሉ በሚቋረጥበት ጊዜ በስሙ የሚቀመጠው የፕሮቪደንት ፈንድ ለእዳ ማስቻያ ሊሆን የሚችለው ሰራተኛው ዕዳ እንዳለበት ያመነ እንደመሆኑ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 59(1) | 95451 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ መርዓዊ መስፍን | ሚያዝያ 06/2006 | 139 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 35 | አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊት በመፈፀሙ ምክንያት ያገኘው ጥቅም ባይኖርም፣ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ባያደርስም ወንጀልነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ስለመሆኑ፣<br>የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) | 95522 | የኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መሃል ሜዳ ደንበኞች አገልግሎት ፅ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሙሉጌታ ወ/ጊዩርጊስ | መጋቢት 08/2006 | 143 |
| 36 | በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በተነሳ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበው ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሆነ ጉዳዩ በተነሳበት ክልል የሰበር ችሎት የተደራጀ እስከሆነ ድረስ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ እና ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ ሳይረጋገጥ በቀጥታ ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣<br>በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6)፣ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1)፣ | 94102 | ኢትዮቴሌኮም ደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ሪጅን<br>እና<br>ወ/ሮ ሳባ መንገሻ | ሚያዚያ 21/2006 | 147 |
| 37 | በሥራ ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወስድ የሚገባ ስላለመሆኑ፣ | 94839 | መተሃራ ስኳር ፋብሪካ<br>እና<br>ጥበቡ እሸቱ (139 ሰዎች) | መጋቢት 22/2006 | 150 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50፣ 51 እና 80 ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 14 እና 15፣አዋጅ ቁ.25/88አንቀፅ5 | | | | |
| 38 | በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በሠራተኛ ዕድገት ዝውውርና ሥልጠና በሚመለከት አሠሪው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በፍርድ ሊታዩና ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች ስለመሆናቸው፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 37፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138፣142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና ከአንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ | 94889 | ወ/ሮ አልማዝ ባዛ እና የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን | መጋቢት 23/2006 | 156 |
| 39 | የሥራ መሪ መብቱን ለማስከበር የሚችልበት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1846 | 94931 | ወ/ሮጥሩወርቅ መንግስቴ እና የተገጣጣሚ ህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት | የካቲት 14/2006 | 162 |
| 40 | የጡረታ እድሜያችን ሳይደርስ በጡረታ እንድንወጣ ተደርጐ የስራ ውላችን ከህግ ወጪ ተቋርጧል በማለት የሚቀርብ ክስን መደበኛ ፍ/ቤት ስንብቱ በህግ አግባብ የተደረገ መሆን አለመሆኑን የማጣራትና የመመርመር ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 23-27 (1)(ተ) እና 30፣40 አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) | 98099 | እነ ወ/ሮ ደንቄ ከዳ (ሀያ ሰዎች) እና የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክስዮን ማህበር | ሰኔ 19/2006 | 165 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | **170** |
| 41 | የጉዳት ካሳ አከፋፈልን በተመለከተ በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን ለፍርድ ቤቱ የተተወ ስለመሆኑ፣<br>በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ተቀጣሪ የሆነ ግለሰብ የአካል ጉዳት በሚደርስበት ወቅት የጉዳት ካሳው አሰላሉ የጡረታ መውጫ እድሜውን መሰረት ቢያደርግ ተገቢ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154፣2090፣2091፣2095<br>አዋጅ.ቁ715/2003 | 92040 | አቶ ጥምቀቱ ጋመነ<br>እና<br>ወ/ት ታገሰች ዮሐንስ | ሚያዚያ 09/2006 | 171 |
| 42 | አንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ ለደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>በፍ/ሕ/ቁ 2162፣2164(1) | 93104 | ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር<br>እና<br>አቶ ደስታ ጁላ ቤካሎ | ሚያዚያ 20/2006 | 177 |
| 43 | ከሳሽ የጠየቀውን የካሳ ገንዘብ ተከሳሽ በግልጽ አለመካዱ የካሳውን መጠን ሙሉ ወይም በከፊል እንዳመነ የማያስቆጥር ስለመሆኑ፤<br>ሰዎች አንድ ሆነው በአንድ ጉዳይ ካሳ እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ሀላፊ | 94181 | አቶ ሽኩር ጀማል<br>እና<br>ወ/ሪት ኤደን ነጋሽ | ግንቦት 18/2006 | 181 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንደሆኑና ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነው በዋና አድራጊው እና በተባባሪዎች መካከል ልዩነት የሚደረግ ስለመሆኑ፤<br>በፍ/ህ/ቁ 2155/1/ እና /2/<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 83 | | | | |
| | **ቤተሰብ** | | | **184** | |
| 44 | የቀለብ ገንዘብ መጠን ስለሚወሰንበት አግባብ፣ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2 | 98552 | ሚ/ር አደም ሐሚድ<br>እና<br>ወ/ሮ ሐናእ አብዱልቃድር | ሐምሌ 4/2006 | 185 |
| 45 | ይርጋ በተመለከተ የሚቀርብ መቃወሚያ ከመልስ ጋር መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 234(1)(ሐ) እና 244(2)(ሠ) | 85815 | አቶ ኢብራሀም መሀመድ ኑር<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ጀሚላመሐመድ (አራት ሰዎች) | ሐምሌ 17/2006 | 189 |
| 46 | በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መመዘኛ የሚያሟላ አቤቱታ አቅራቢ (ፍርድ ተቃዋሚ) የሚቃወመው ፍርድ በይግባኝ ያልተሻረ (ዋጋ ያለው) እና ያልተፈፀመ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ | 93987 | እነ አቶ ዳንኤል ወንዳፈራ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስናቀች ቦጋለ (አራት ሰዎች) | ሐምሌ 18/2006 | 193 |
| 47 | የውርስ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ በውርስ ህጉ የተመለከቱትን የውርስ ንብረት ክፍፍልን | 94322 | ወ/ሮ አልማዝ በቀለ | ሐምሌ | 198 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚገዙትን ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና አላማ የተከተለና ያገናዘበ መሆን ስላለበት፣ የፍ/ህ/ቁ 1079፣1082፣1083፣1086 ፣1087(2)፣1092፣1093 | | እና<br>አቶ ገዛኸኝ በቀለ | 17/2006 | |
| 48 | በህግ ፊት የሚፀና ስጦታ ለማድረግ ሰጪው ስጦታ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑ፤የባልና የሚስት የጋራ በሆነ ንብረት ላይ አንደኛው ተጋቢ ብቻውን የሚያደርገው ስጦታ ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ፣ | 90959 | ተክለፃድቅ ኤካ<br>እና<br>እነ አቶ መላኩ ፍሬው(2 ሰዎች) | ግንቦት 063/2006 | 204 |
| | **ንብረት** | | | | **208** |
| 49 | ትዳር ያለው አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ በሞት በተለየ ጊዜ የተከራይነት መብቱ ለሌላኛው ተጋቢ ሊተላለፍ የሚችለው አግባብነት ባለው መመሪያ ስለመሆኑ፣ | 93346 | እነ ወ/ሮ ብርሃን ደሳለኝ(2 ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ብርትኳን ዮሐንስ | ግንቦት 21/2006 | 209 |
| 50 | አንድ ሰው በድልድል ያገኘውን መሬት ሌላ ሰው ሊወስድበት የሚገባው በሕጉ የተመለከቱ ምክንያቶች ሲኖሩ ብቻ ስለመሆኑ፣ የት/ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀጽ 31፣5፣12፣14 | 95538 | አብርሃ ሕሉፍ ገሰሰው<br>እና<br>ወ/ሮ ትበርህ | ግንቦት 07/2006 | 212 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እና 22<br>ደንብ ቁ. 48/2000 “ን”<br>በደንብ ቁጥር 48/2000 14፣15፣16<br>አዋጅ ቁጥር 456/1997<br>በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሰት አንቀጽ 37፣40(3) እና 79 | | ገብረሕይወት | | |
| 51 | ሁከት ፈጥረሀል ተብሎ የተከሰሰ ሰው ሁከት ፈጥረሀል በተባለበት ነገር ላይ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ካለው ሁከት ፈጠረ ሊባል ስላለመቻሉ፣<br>የፍ/ህ/ቁ 1149(3) | 94869 | አቶ ሙሳ ደገፈ<br>እና<br>አቶ ጥላሁን ደስታ | ሰኔ 19/2006 | 216 |
| 52 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሠው ባለማቋረጥ ለ 15 ዓመታት ግብር በስሙ መክፈሉ ከተረጋገጠ የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ህ/ቁ 1168(1) | 89148 | አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም<br>እና<br>ወ/ሮ አስመረት መኮንን | ሰኔ 3/2006 | 220 |
| 53 | ጉዳዩ ከይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ከሰነዶች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ በፍርድ ሊወሰን የሚችል አይደለም ሊባል ስላለመቻሉ፤<br>እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካርታ ወይም ሌሎች ሰነዶች ተወስደውብኛል | 97464 | ወ/ሮ ዘይነብ ጀማል<br>እና<br>እነ የቦሌ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ | ሰኔ 04/2006 | 225 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተብሎ ክስ በሚቀርብበት ጊዜ የተወሰዱበት አግባብ ህጋዊ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊጣራ የሚችል ጉዳይ ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 37(1)፣<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.4 | | አስተዳደር ጽ/ቤት(ሁለት ሰዎች) | | |
| | **ውል** | | | | **229** |
| 54 | አንድ ፍርድ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች /መብቶች ስለመሆኑ፣<br>በህግ አግባብ መብቱን ባስተላለፈ ንብረት ላይ የቀድሞ ባለቤት በድጋሚ ሽያጭ የሚፈጽምበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 | 92290 | ወ/ሪት ጦቢያው መኮንን<br>እና<br>እነ አቶ እርቁ ጎዳ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 14/2006 | 230 |
| 55 | የዋስትና ግዴታ ግልፅ መሆን ያለበት ስለመሆኑ ኃላፊነቱም ግዴታ ከተገባለት እዳ ወሰን ለማለፍ እንደማይችል እና እንዲሁም ይህ ለአፈፃፀሙ ግዴታ የተገባለት የእዳ መጠን ወይም የገንዘብ ልክ በዋስትና ውሉ ካልተገለፀ ዋስትናው ፈራሽ ስለመሆኑ፣ | 94837 | አቶ ልዑል ዘወዴ<br>እና<br>አጀመራ የወርቅ ግብይት ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሚያዝያ 22/2006 | 235 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ከዚህ በተጨማሪ ገና ለወደፊት ሊደርስ ለሚችል ግዴታ አፈፃፀምም ዋስ ለመሆን እንደሚችል ነገር ግን በግልፅ ለምን ያህል እዳ ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል በግልፅ በውሉ ላይ መስፈር ያለበት ስለመሆኑ፣<br>ፍ/ብ/ህ/ቁ 1922(2)(3)፣ 1925(1) | | | | |
| 56 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በተመለከተ መንግስት ካለበት ኃላፊነት የተነሳ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውል እንዲዋዋሉ እና መዝገብ እንዲያደራጁ የተወሰነ አካልን ባላደረገበት ጊዜና ቦታ በአካባቢው የሚፈፀሙ ልማዳዊ አሰራሮችን ህጋዊ መሰረት የላቸውም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>ከፍ/ሕ/ቁ. 3364 | 98079 | የቀይ አፈር ገዳሞች<br>እና<br>አቶ ኤርሚያስ ገሠሠ | ሰኔ 18/2006. | 239 |
| | **ወንጀል** | | | | **243** |
| 57 | በወንጀል ጉዳይ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ያስገኘው ሕግ በፍርዱ ውስጥ መገለጽ እንደሚገባውና የጥፋተኝነት ውሳኔው የሚሰጥበት ድንጋጌ መፈጸሙ ከተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር ጋር በጥንቃቄ መነጻጸር የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>ወ/መ/ሕ/ስ/ስቁ. 149 | 94070 | እነ አቶ ወልዱ<br>ገ/አብዝጊ(ስድስትሰዎች)<br>እና<br>የትግራይ ክልል ዐ/ሕግ | ሚያዝያ 22/2006 | 244 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 58 | አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ በሌለበት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ጥፋተኛ የተባለው ሰው ቀርቦ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስነሳት ሳይሆን በዋናው ጉዳይ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ከጠየቀ በኃላ በሌለሁበት የተሰጠው ውሳኔ ይነሳልኝ ብሎ ቢያመለክት በፊት የጠየቀው ይግባኝ በህጉ ላይ የተቀመጠውን የ30 ቀን የጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ስለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.198 | 95875 | እነ አቶ አዳሙ ዘለቀ(3 ሰዎች)<br>እና<br>የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ | ሰኔ 17/2006 | 250 |
| 59 | በተለያየ ጊዜና መዝገቦች የተለያዩ ቅጣቶች በአንድ ተከሳሽ ላይ በሚወሰንበት ጊዜ ተከሳሹ ይጣመርልኝ ብሎ በሚጠይቅበት ጊዜ ተደምረው የሚፈፀሙ ሲሆን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን እንደገና በድጋሚ የሚታዩበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አንቀፅ 186(3)፣184(1)፣ 108(1) | 96503 | አቶ መኮንን ወለላው ካሳ<br>እና<br>የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ | ሰኔ 19/2006 | 255 |
| 60 | ከውል ግንኙነት ጋር በተያያዘ በህገ ወጥ መንገድ መብትን ማስከበር የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አንቀፅ 436(ለ) | 98647 | አቶ ፅጋቡ ወላይ ገብሩ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ዐቃቤ ሕግ | ሰኔ 02/2006 | 260 |
| 61 | አንድ ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሣኔ | 94227 | አቶ ገ/መድህን ኃ/ማርያም | ግንቦት | 266 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ በመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያ ለተከሳሹ ያለመድረስ ጉዳይ ስለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሕ/ሥ/ ሥ/ቁ. 199(ሀ) | | እና<br>ትግራይ ክልል ዐ/ህግ | 05/2006 | |
| 62 | አንድ በወንጀል ድርጊት ቅጣት የተጣለበትን ተከሳሽ ቅጣቱ እንዳይፈፀም ፍርድ ቤቱ ለማድረግ የሚችለው ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ፣ እንዲፈፅም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ፣ በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ ስለመሆኑ፣<br>ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈጻፀም መተማመኛ ዋስትና የሚጠይቅ ስለመሆኑ፣<br>አንቀጽ 197/1/ እና/2/ | 94404 | የደቡብ ብሔር በሔረሰቦች ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል አቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ መኩሪያ ቡሎ | መጋቢት 09/2006 | 270 |
| 63 | የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ይልቅ የተሻሻለው | 95438 | አቶ ሰለሞን ደሣለኝ<br>እና | ግንቦት 07/2006 | 275 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መመሪያ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው የተሻሻለው መመሪያ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ የወንጀል ህግ አተረጓጓም መርሆን መከተል ያለበት ስለመሆኑ፣<br>ወንጀል ህጉ ቁ 6 | | የደቡብ ክልል ዐ/ህግ | | |
| 64 | አንድ ተከሳሽ በክስ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል ሲል በመዝገብ ካሰፈረ በኃላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/አ 134(1) | 96954 | ዘፈኑ ወልደ ትንሣኤ<br>አብርሃ እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ህግ | ሚያዚያ 24/<br>2006 | 279 |
| 65 | አንድ ሰው በአንድ አይነት የወንጀል አሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈጸመው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27(1)፣60(ሀ) (ሐ) እና 598(1) | 96078 | ረዳት ሳጂን አህመድ ለገሰ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | መጋቢት<br>11/2006 | 282 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የዳኝነት ስልጣን** | | | | | **288** |
| 66 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን እና ፍሬ ጉዳይን የማጣራት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የአ.አ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42(2) | 93220 | ግርማ አያሌው ዋልታንጉስ<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት | መጋቢት 8/2006 | 289 |
| 67 | በመንግስት በጀት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚፈጠሩትን የመብት ጥያቄዎች መመራት ያለበት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሆን አለበት፡፡<br>-በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 (2)(ሠ) ፣ አዋጅ 515/1999 አንቀጽ 3<br>በአዋጅ 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 214/2003 እና 210/2003 | 93358 | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማርች ፕሮጀክት<br>እና<br>እነ ቤተልሔም ሽፈራ (ሶስት ሰዎች) | መጋቢት 26/2006 | 293 |
| 68 | ከከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት በሚቀርብበት ጊዜ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ፣ | 96216 | አቶ ተክለብርሃን ዘገየ እና<br>እና | ሐምሌ 29/2006 | 297 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በአንድ ክስ ውስጥ ብዙ አቤቱታዎች ቀርበው ከነዚሁ በከፊል ዋናውን ክስ የሚመለከቱ በከፊል ደግሞ ዋናውን ክስ መነሻ አድርገው ቅርንጫፍ ነገሮችን የሚመለከቱ በሆነ ጊዜ የፍርድ ቤቱ ስልጣን የሚወሰነው ከፍተኛ ግምት ያለውን አቤቱታ መሰረት አድርጎ በመከተል ስለመሆኑ፣ መመሪያ ቁጥር 4/2004<br>አዋጅ ቁጥር 361/1995 ፣ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 17(2) | | አቶ ሸምሰዲን አክመል<br>(አራት ሰዎች) | | |
| 69 | ከጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን ከዛም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በየደረጃው ሳያቀርብ በቀጥታ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይለት የሚጠይቅበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89(2) እና ንዑስ አንቀፅ 3(ሐ)፣ አንቀፅ 89(2)(3)(ሐ) ፣(5) እና (6) | 97372 | ማም ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር<br>እና<br>እነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን(ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 29/2006 | 302 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| ጉምሩክ | | | | | 307 |
| 70 | በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ እንደተከፈለ የሚቆጠርበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>ቀረጥና ታክሱን የማስከፈል ስልጣን በህገ መንግስቱ ተለይቶ የተቀመጠ ስለመሆኑ፣<br>የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 96(1) አዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 6(8)፣9 እና 10፣ ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(6)፣(2(11)፣2(17) እና 91 ፣15(1)፣ 82 (1ሀ))((ለ)) | 97409 | የኢትዮጲያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>እነ ጋርዊች ዋንግ(ሶስት ሰዎች) | ግንቦት 09/2006 | 308 |
| 71 | አንድ የግብር ውሳኔ በግምት ስለሚወሰንበት አግባብ<br>የግብር ህግ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 69 | 88446 | ሙሉ አሚን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ግንቦት 22/2006 | 315 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 72 | ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበት ዕቃ ህጋዊ የግምሩክ ስርዓት ካልተፈፀመበት ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ ከተያዘ እና ከተወረሰ በህጋዊ መንገድ ዕቃው ሲገባ የተከፈለው ቀረጥ(tax) እንዲመለስለት የዕቃው ባለቤት የሚጠይቅበት የህግ ስርዓት ስላለመኖሩ፣<br>አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 104(3) | 92537 | አዞግሎባልኃ/የተ/የግልማህ በር<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን | ግንቦት 21/2006 | 320 |
| **አፈጻጸም** | | | | | 322 |
| 73 | በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያድርግ መልኩ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ ስላለመኖሩ፣<br>የአስተዳደር አካል በባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ ፍጹም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስላለመሆኑ፣<br>ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378፣ 392<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 | 91622 | ወ/ሮ አፍሪካ ታደሰ-<br>እና<br>ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ-ታልፏል<br>የጎባ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት | መጋቢት 12/2006 | 323 |
| 74 | አንድ ንብረት ወይም ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ሊቆረጥ የሚችለው ከተቻለ በስምምነት ይህ ካልተቻለ ደግሞ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት ስለመሆኑ፣ | 94571 | እነ ወ/ሮ የልፍኝ መኮንን (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ዘርሁን መኮንን | ሐምሌ 1/2006 | 329 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| 75 | ለፍርድ ማስፈጸሚያ የቀረበን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመጀመሪያ የሐራጅ ሽያጭ የሚቀርብበትን የዋጋ ግምትን አስመልክቶ የተነሳ ክርክር መፍትሄ ስለሚያገኝበት አግባብ፤<br>ፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 423(2)(ሀ) | 92035 | ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ. ዓድዋ ቅርንጫፍ<br>እናእነ አቶ ሐጎስ ተስፋይ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 24/2006 | 333 |
| 76 | አንድ የፍርድ ባለገንዘብ በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ በህግ፣በውል ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የቀደምትነት መብት ካላቋቋመ በቀር ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ጋር ደረጃቸው(መብታቸው) እኩል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ ስሌት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደውን ገንዘብ እንዲከፍሉ ማድረጉ የህግ መሰረት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ስ/ስህ/ቁ 403<br>የፍ/ህ/ቁ 3043፣3044፣3045፣2825 | 97206 | አቶ አማረ መልካሙ<br>እና<br>አቶ ካሴብ ህሉፍ | ሐምሌ 28/2006 | 337 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **342** |
| 77 | አግባብ ባለው የዩኒቨርስቲ አካል በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቅሬታ ሲኖራቸው የይግባኝ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፤<br>ይግባኙን የማስተናገድ ስልጣን የፌደራል | 101271 | መ/ር ግዛቸው ጥሪት<br>እና<br>ወሎ ዩኒቨርሲቲ | ሐምሌ 30/2006 | 343 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን | ገፅ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍ/ቤት ስለመሆኑ፣ | | | | |
| 78 | አንድ ሰው የፖሊስ ቅጥር ፎርም የሚል ስያሜ የያዘ ሰነድ ስለሞላ ወይም በቅጥር ፎርሙ በሕጉ አግባብ የሚገኙት ማዕረጎች ተሰጥተውት የጥቅማ ጥቅሙ ተጋሪ መሆኑ ብቻ ጉዳዩን በፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲዳኝ ማድረግ ተገቢ ስላለመሆኑ፡- <br>አዋጅ ቁ.720/2004 አንቀፅ 2(1) <br>የፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.268/2005 አንቀፅ 3፣4፣5፣6(1) እና 7 | 99367 | ዶ/ር ሕሊና ፍቅሬ <br>እና <br>የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል | ሐምሌ 29/2006 | 351 |

# የፍትሐብሔር

# ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 92043

መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ቱሌን ዩኒቨርሲቲ አሲስታንስ ፕሮግራም ኢትዮጵያ - ጠበቃ ሰማው ንጋቱቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ዶ/ር ዮዲት አብርሃም -ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የይርጋ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ06/08/2004 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ20/01/2001 ዓ.ም ጀምሮ በሰው ኃይል ከፍተኛ አማካሪነት የስራ መደብ በተከሳሽ ድርጅት ሲያገለግሉ ቆይተው የስራ ውላቸውን በራሳቸው ፈቃድ ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምረው ማቋረጣቸውን እና ተከሳሽ ድርጅት የተለያዩ ክፍያዎችን ሊከፍላቸው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ያልተከፈላቸው የአራት ወር ደመወዝ፣የዓመት ዕረፍት ክፍያ፣የተጠራቀመ ፕሮፌደንት ፈንድ እና ክፍያ የዘገየበት ታስቦ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ተከሳሽ ድርጅት በ17/09/2004 ዓ.ም በሰጠው መልስ የይርጋ መቃወሚያ እና የፍሬ ጉዳይ መልስ ያቀረበ ሲሆን የይርጋ መቃወሚያው ይዘትም ከከሳሽ ጋር የነበረው በየጊዜው የሚታደስ የስራ ውል ለመጨረሻ ጊዜ ለሶስት ወር የተራዘመው በ22/07/2003 ዓ.ም በመሆኑ የከሳሽ የስራ ውል የተቋረጠው ከሳሽ እንደሚሉት ከ13/02/2004 ዓ.ምሳይሆን ከ23/10/2003 ዓ.ምጀምሮ መሆኑን እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 06/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ ከዘጠኝ ወር በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊዘጋ ይገባል የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ እና የመቃወሚያ ክርክሩን ከመረመረ በኃላ በግራ ቀኙ መካከል በ21/01/2001 ዓ.ምበተደረገው የመጀመሪያ ውል ላይ የስምምነቱ ጊዜ የሚራዘመው ሁለቱም ወገኖች በጊዜው ርዝማኔ ላይ በጽሁፍ በሚያደርጉት ስምምነት እንደሆነ መገለጹን፣ተከሳሽ በ22/07/2003 ዓ.ም ፃፍኩ የሚለው የማራዘሚያ ደብዳቤ ከሳሽ ያልተስማሙበት እና ማብራሪያም የጠየቁበት መሆኑን፣በዚህም ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል የውል ማራዘሚያ ስምምነት አለ ሊባል የማይችል መሆኑን እና ከሳሽ ስራቸውን መቀጠል በመፈለጋቸው ከ23/10/2003 ዓ.ምበኃላም ስራ ላይ መቆየታቸውን ተከሳሽ ድርጅት ክሱ በተሰማበት ወቅት ያመነ መሆኑን ገልጾ የከሳሽ የስራ ውል የተቋረጠው ከሳሽ እንደሚለው በ23/10/2003 ዓ.ምጀምሮ ሳይሆን ከ13/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን፣የስራ ውሉ የተቋረጠው ከ23/10/2003 ዓ.ምጀምሮ ነው በማለት ተከሳሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያጣ ቢሆንም ከሳሽ የስራ ውላቸውን ካቋረጡበት ከ13/02/2004 ዓ.ምጀምሮ ፍ/ቤት ቀርበው ፋይል እስካስከፈቱበት 17/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ከአራት ቀን በመሆኑ እና በዚህም ሁኔታ ክሱ የቀረበው ይርጋው ከሞላ ከአራት ቀናት በኃላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቶታል፡፡

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የስር ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 213(1) ድንጋጌ መሰረት አንድ ክስ እንደቀረበ የሚቆጠረው ክስ የቀረበበት ጽሁፍ በፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ በመሆኑ እና የክስ ማመልከቻው ለሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ ምልክት የተደረገበት በ12/08/2004 ዓ.ምሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ፋይሉ የተከፈተበትን 16/08/2004 ዓ.ምክስ የቀረበበት ቀን አድርጎ መውሰዱ ተገቢ እንዳልሆነ ገልጾ የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ13/02/2004 ዓ.ምጀምሮ ክስ እስከቀረበበት 12/08/2004 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ስድስት ወር ያልሞላው በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም ሲል ብይኑን ሽሮ የስር ፍ/ቤት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት በመመለስ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት አቅርቦት የነበረውን መስቀለኛ ይግባኝ ደግሞ በተመሳሳይ ቀን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ አሰናብቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እና መስቀለኛ ይግባኙን በትዕዛዝ በመዝጋት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ባቀረበው መስቀልኛ ይግባኝ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሳይሰማ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 337 መሰረት የመዝጋቱን አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ

መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ የይግባኝ ክርክር መልስ ሰጪ የሆነው ወገን በቀጥታ ይግባኝ ያላቀረበ ቢሆንም እንኳ ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ይግባኝ ባዩ ባቀረበው የይግባኝ ክርክር በመልስ ሰጪነት ከሚያቀርበው ክርክር ጋር በፍርዱ ቅር የተሰኘበትን ጉዳይ በማቅረብ በይግባኝ ባይነትም ለመከራከር እንደሚችል እና በዚህ ሁኔታ የቀረበውን ይግባኝ መልስ ሰጪው ለይግባኝ ባይ ያደረሰ ስለመሆኑ መተማመኛ ካላቀረበ ማመልከቻው በመልስ ሰጪው ኪሳራ ተገልብጦ ለይግባኝ ባዩ እንዲደርስ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340(1) እና (2) ተመልክቷል፡፡በመሰረቱ አንድ ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ ይግባኙ የተመሰረተው በስር ፍ/ቤት የመዝገብ ግልባጭ ላይ ብቻ ከሆነ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ባዩን ከሰማ በኃላ መልስ ሰጪን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን ዘግቶ ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ እና መ/ሰጪው ወገን የሚጠራው ይግባኙ ባልተሰረዘ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እና 338 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

መስቀለኛ ይግባኝ ስለሚስተናገድበት ስርዓት በሕጉ በተለየ ሁኔታ በግልጽ የተመለከተ ነገር እስከሌለ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 እና 338 ድንጋጌዎች የተመለከተው የክርክር አመራር ስርዓት ለመስቀለኛ ይግባኝም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት የሚኖረው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.340(2) በተመለከተው መሰረት መልስ ሰጪው ወገን የሚያቀርበው የይግባኝ ማመልከቻ ግልባጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.338 መሰረት ለይግባኝ ባዩ እንዲደርስ ሊደረግ የሚችለው ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ.337 መሰረት ያልተሰረዘ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡በመሆኑም መልስ ሰጪው ወገን ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ከተሰማ በኃላ የሌላኛውን ወገን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት እንዲሰረዝ በማድረግ የሚሰጥ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 340(2) የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት የሚቃረን ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ከአመልካች ክርክር አንጻር ጉድለት የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት አቅርቦት በነበረው ይግባኝ ላይ የሌላኛውን ወገን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ መስቀልኛ ይግባኙን በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ በማሰናበት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 78241 በ23/05/2005 ዓ.ም ሰጥቶ የነበረውን ብይን ሽሮ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስላልሆነ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት እና ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341(1) መሰረት ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለስ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 132623 በ06/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጪነት አቅርቦት የነበረውን ይግባኝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ በማሰናበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 132623 በ06/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 78241 የተያዘው ክርክር ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ04/03/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ገ

የሰ/መ/ቁ. 91493

ሰኔ 03 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ አየለ ሚናሞ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አሰፋ ባዩ -ተወካይ አቶ ዘርይሁን ሞገስ - ቀረቡ፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ ተጠሪ ተወካይ በጠበቃቸው አማካኝነት ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአሁን አመልካች ተጠሪው በሌለበት የንብረት ግምት ክስ አቅርበው በመ/ቁ/06973 በቀን 15/01/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብር 95,067. ተጠሪው እንዲከፍላቸው በማስወሰን የተጠሪን ይዞታ በስማቸው ማዛወራቸውን ሚያዚያ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ተጠሪ ባቀረቡት ክርክር መነሻ አመልካቹ ውሳኔውን በማስረጃነት አያይዘው በማቅረባቸው የተረዱ ስለሆነ እና ውሳኔውም መብታቸውን የሚያሳጣ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78(2) መሰረት ውሳኔው ተነስቶ ተወካዩ ወደ ጉዳዩ ገብቼ እንድከራከር ይታዘዝልኝ ብለዋል፡፡

ለአመልካችም የተጠሪው ተወካይ አቤቱታ እንዲደርሳቸው በተደረገው መሰረት ቀርበው በ06/10/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ባቀረቡት መቃወሚያ፡-ተጠሪው ለተወካዩ የሰጡት ውክልና በፍ/ሕ/ቁ/2205 መሰረት ንብረት እንዲያስተዳድሩ የተሰጠ እንጂ ተጠሪውን ወክለው በፍርድ ቤት ቆመው ለመከራከር የሚያስችላቸው ባለመሆኑ ውክልናው ተቀባይነት የለውም ሲሉ በመከራከራቸው ተወካዩም ለመቃወሚያው በሰጡት መልስ፡- ቀደም ሲል እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ በዚሁ የውክልና ማስረጃ ከአመልካች ጋር ስንከራከር ስለነበረ መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ ወደ ጉዳዩ ገብቼ እንድከራከር ይታዘዝልኝ ብለዋል፡፡

የወንዶ ገነት ወረዳ ፍርድ ቤትም፡-በ01/12/2004 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን፡- አመልካች ቀደም ሲል ክሱን ሲያቀርቡ የተጠሪው አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤት ቁጥሩ 171 በሚል በገለጹት መሰረት መጥሪያውን በአድራሻቸው ማድረስ ሲገባቸው ሳያደርሱ መጥሪያው ወደ ሌላ አድራሻ እንዲላክ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደረጉ ስለሆነ

ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2) መሰረት ተነስቶ የተጠሪው ተወካይ ወደ ጉዳዩ ገብተው ሊከራከሩ ይገባል ሲል በይኗል፡፡

ከዚህ ብይን በኋላ የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ፡- በዋናው ጉዳይ ላይ ተጠሪው በሌሉበት ክርክር ተካሂዶ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የአፈጻጸም ክስ አቅርቤ ተጠሪው በሌሉበት ፍርዱ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ተሰጥቶ ቤቱን እና ቦታውን ተረክቤ ወደ ስሜ ተዛውሮ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶኝ ጉዳዩ ተጠናቆ ሳለ በፍርድ በተጠናቀቀ ጉዳይ ክርክሩ ሊቀጥል አይገባም፣ለተጠሪው ተወካይ ተጠሪው ውክልና የሰጡት በ1996 ዓ.ም ሲሆን ክሱ በቀረበ ጊዜም ተጠሪው ቀርበው እንዲከራከሩ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ መቅረብ ስላልቻሉ በሕይወት መኖራቸውን ስለምጠራጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.65(1) መሰረት ራሳቸው እንዲቀርቡ ይታዘዝልኝ ሲሉ በመከራከራቸው የተጠሪው ተወካይም በጉዳዩ ለመከራከር የሚያስችለኝ ሙሉ ውክልና እያለኝ ዋናውን ባለጉዳይ ማቅረብ አስፈላጊ ስላልሆነ አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ሲሉ መልስ በመስጠታቸው ፍርድ ቤቱም 01/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ብይን፡- ከመዝገቡ ማጣራት እንደተቻለው ተጠሪው ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ እንደገና እንዲከራከሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2) መሰረት የተፈቀደላቸው ሆኖ ሳለ የፍርድ ባለመብቱ (የአሁን አመልካች) እንደገና መቃወሚያ ማቅረባቸው ተገቢ ባለመሆኑ ተጠሪው በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/78(2) በተፈቀደላቸው መሰረት በተወካያቸው በዋናው ጉዳይ መከራከር ይችላሉ ሲል አመልካች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አደርጓል፡፡

አመልካችም በዚሁ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገን ካከራከረ በኋላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ብይን ያጸናው ሲሆን ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠ/ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሥር ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም ሲል አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ ሲጠቃለል፡- የተጠሪው ተወካይ ጠበቃ በንብረት ግምት ላይ ተጠሪው በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 78(1) መሰረት አቤቱታ አቅርበው መዝገቡ ከአመልካች በኩል የሚቀርበውን መልስ ለመቀበል እና የቃል ክርክር ለማድረግ በተቀጠረበት ቀን የተጠሪ ተወካይ በመቅረባቸው የውክልናው ማስረጃ በወካዩና በተወካዩ መካከል የዝምድና ትስስር ሳይኖር የተሰጠ መሆኑን፤እንዲሁም የውክልና ማስረጃው በፍ/ሕ/ቁ/2205(2) መሰረት ተወካዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር በሚያስችል መልኩ የተሰጠ ባለመሆኑ ተወካዩ ተጠሪውን ወክለው ለመከራከር የሚያስችል ውክልና ማስረጃ የላቸውም በሚል ክርክር ከማቅረብም ሌላ ዋናው ባለጉዳይ በህይወት መኖር አለመኖራቸውን ስለምጠራጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 50(1) መሰረት ቀርበው

እንዲከራከሩ እንዲታዘዝ በሚል ላቀረብኩት ክርክር የወረዳው ፍርድ ቤት የውክልና ማስረጃው ተወካዩ ክርክር ለማድረግ የሚያስችላቸው መሆን ስላለመሆኑ በዝምታ በማለፍ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.58(2) መሰረት በማንሳት ክርክሩ እንዲቀጥል መበየኑና በይግባኝ እና በሰበር በየደረጃው ያሉ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ማጽናታቸው ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የተጠሪው ተወካይ በሰጡት መልስ፡- በውክልናው ማስረጃው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የተጠሪን ንብረት በተመለከተ ክስ እንዳቀርብ፣መልስ እንድሰጥ እና ክርክር ለማድረግ በግልጽ ሥልጣን የተሰጠኝ በመሆኑ፤ እንዲሁም በዚሁ የውክልና ማስረጃም ተጠሪውን በመወከል ያሰጠሁትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረቡት ክስ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረጉት ክርክሮች አንድም ቀን የውክልና ማስረጃውን በመቃወም ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር አሁን ግን ማስረጃው ተቀባይነት የለውም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ተገቢ ባለመሆኑ የሰበር አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግባቸው ይገባል ብለዋል፡፡

አመልካችም ለተጠሪው የመልስ መልስ ከማቅረባቸውም ሌላ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የተጠሪው ተወካይ የያዙት የውክልና ማስረጃ ክርክሩን ለማድረግ የሚያስችላቸው አይደለም ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች በማለፍ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ በማንሳት ተወካዩ ክርክሩን እንዲቀጥሉ ብይን የሰጡት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ባለጉዳዩ ራሱ ቀርቦ እንዲከራከር ፍርድ ቤቱ ካላዘዘ ወይም ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ህግ ከሌለ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሰው ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት እና በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57 ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው ለተወካዩ በሰጡት ውክልና ሥልጣን መሰረት ተወካዩ ክርክር ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም በዚህ ችሎት የቃል ክርክር በተደረገበት ወቅት በወካዩና በተወካዩ መካከል ዝምድና መኖሩን ወይም አለመኖሩ ተወካዩ እንዲገልጹ ተጠይቀው ወካዩ የአክስታቸው ልጅ እንደሆኑ የገለጹ በመሆኑ የአክስታቸውን ልጅ በመወከል ክርክር ለማቅረብም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ58(ሀ) መብት የሚሰጣቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በተጠሪውና በተወካዩ መካከል ያለው የዝምድና ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58(ሀ) የዋናው ባለጉዳይ ተወካይ ሆኖ ለመከራከር ከተቀመጠው የዝምድና

ደረጃ ውጪ ሆኖ በመገኘቱ የውክልናው ማስረጃው በዚህ ድንጋጌ መሰረት የተገኘ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ እንዲሁም ተወካዩ የውክልና ማስረጃ በፍ/ሕ/ቁ205 መሰረት የተሰጠ ስለመሆኑ ጠቅሰው የሚከራከሩ ቢሆንም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የተሰጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ውክልናው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ58(ሀ) የተዘረዘረውን የዝምድና ደረጃ ተከትሎ የተሰጠ ለመሆኑ ስላላረጋገጡ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 63 መሰረት መስፈርቱን አሟልተው በጠበቃነት የሚከራከሩ ስለመሆኑ በግልጽ ሳያመለክቱ በውክልና ማስረጃው ላይ የፍ/ህ/ቁ205 በመጠቀሱ ብቻ ማስረጃው ተጠሪውን ተክቶ ለመከራከር ብቁ የሚያደርጋቸው አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ተወካዩ ቀደም ሲል በይዞታ መብት ላይ ክርክር ሲደረግ ዋናው ባለጉዳይ በመወከል እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስከራከር እንደነበር አመልካች እያወቁ በዝምታ ቆይተው አሁን ውክልናውን ሊቃወሙ አይገባም ያሉትም ቢሆን አመልካች ውክልናው ህጋዊ አለመሆኑን በመረዳት በንብረት ግምት ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ተጠሪው በተወካያቸው አማካኝነት ክርክር በማቅረባቸው ያነሱት የክርክር ጭብጥ መሆኑ መቃወሚያውን ከማቅረብ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪው ለተወካዩ የሰጡትን ውክልና ማስረጃ በመቃወም ያቀረቡትን ክርክር ተቀብለው ዋናው ባለጉዳይ ወይም ትክክለኛ ተወካይ ቀርቦ ክርክሩን እንዲቀጥል ማድረግ ሲገባቸው የውክልና ማስረጃው ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምሩ በማለፍ ክርክሩ እንዲቀጥል ብይን የሰጡት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የወንዶ ገነት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/6973 በቀን 01/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ብይን፣የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/27806 በቀን 05/06/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ፣እና የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 59120 በቀን 27/09/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪው ለተወካያቸው የሰጡት ውክልና ተወካዩ ተጠሪውን ተክተው ለመከራከር የሚያስችላቸው አይደለም ብለናል፡፡ ይህ ውሳኔ ዋናው ባለጉዳይ ወይም ህጋዊ ወኪላቸው ወይም ጠበቃቸው ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር የሚያስቀር አይሆንም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 94293

ሚያዝያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሸዋ ንግድና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ አሸብር አበበ፡- ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ለፌዴራሉ መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ፡-አመልካች ለ1ወር ከህግ ውጭ ከስራ አግዶኝ ካቆየኝ በኃላ ወደ ስራ እንዲመልሰኝ በተደጋጋሚ ብጠይቀውም ለመመለስ ፍቃደኛ ባለመሆን የስራ ውሌን ከህግ ውጭ ስላቋረጠ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች ይፈፅምላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ የአመልካች ድርጅትን ስም፤የስራ አስኪያጁን ፊርማና የድርጅቱን ማህተም አስመስለው ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት አዘጋጅተው በመገልገል የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት ፈፅመዋል በሚል በመጠርጠሩ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ ለ1ወር ከስራ ታግደው የነበረ ቢሆንም ምርመራው ባለመጠናቀቁ ፖሊስ ጉዳዩን አጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ተጠሪ ለጊዜው መደበኛ ስራውን እንዲቀጥል ቢነገረውም ፍቃደኛ ባለመሆኑና በዚህም መሠረት በስራ ገበታው ላይ በመደዳው ከ5 የስራ ቀናት በላይ ባለመገኘቱና በፈፀሙት የማጭበርበር ድርጊት የስራ ውላቸው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27(1)(ለ)(ሐ) መሠረት በህጉ አግባብ መቋረጡን በመግለፅ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመርያ ደረጃ የተመለከተው የፌደራሉ መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና የአመልካችን ምስክሮች ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ክርክሩ ከተጀመረ በኃላ በፈፀሙት የማጭበርበር ድርጊት በወንጀል ችሎቱ ጉዳዩ ታይቶ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ መሆኑን አመልካች ገልፀው መዝገቡ ቀርቦ እንዲታይላቸው ያመለከቱትን በተመለከተ ቀደም

ሲል ጉዳዩን ሲመለከቱት በነበሩት ዳኛ በጭብጥነት የተያዘው ተጠሪ ከስራ ታግደው ከቆዩ በኃላ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ ነበሩ ወይስ አልነበሩም? የሚለው ነጥብ ብቻ በመሆኑና ክርክሩም የቀጠለው በዚሁ ነጥብ ላይ በመሆኑ በወንጀል ጥፋተኛ የመሆናቸው ጉዳይ የወንጀሉን መዝገብ በማስቀረብ ሊመረመር አይችልም በማለት ካለፈ በኃላ ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ እምቢተኛ ሆነው ከ 5 የስራቀናት በላይ ስለመቅረታቸው የአመልካች ማስረጃ ስላላስረዳ የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ አመልካች የ6ወር ደመወዝ የካሳ ክፍያ የ2ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የስራ ስንብትና የዓመት ረፍት ጊዜ ወደ ገንዘብ ተለውጦ በድምሩ ብር 13,296.33 የገቢ ግብር ቀንሶ ለተጠሪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔም በፌዴራሉ ከፍተኛ/ፍ/ቤት በይግባኝ ታይቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሠረት ፀንቷል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን መሠረታዊ የቅሬታ ነጥቦችም የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በፈፀሙት የማጭበርበር ወንጀል ድርጊት ጭምር መሆኑን አመልካች ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ማለትም የፅሑፍ መልስ ሲሰጥ ጀምሮ ክርክሩ ቀርቦ እያለ የስር ፍ/ቤቱ ግን ይሄንን በጭብጥነት ሳይዝ ማለፉ ስለጭብጥ አያያዝና አመሠራረት አስመልክቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.247 እና 248 የተደነገገውን የሚጥስ ነው፡፡ተጠሪ የአመልካችን ድርጅት ማህተምና የስራአስኪያጁን ቲተር የሚመስል ሀሰተኛ ማህተም በራሳቸው ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት የተዘጋጀውን በመገልገል በፈፀመው ወንጀል ድርጊት ተከሶ እና ጉዳዩም ተጣርቶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በስራ ክርክር ችሎት በክርክር ላይ እያለን የተጠሪ ስራ ውል ከተቋረጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ የተደረገበት ውሳኔ ቀርቦ ታይቶ እና ጉዳዩ ከዚህ አንፃር በጭብጥነት ተይዞና ተመርምሮ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መስጠት ሲገባዉ ታልፎ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.247 እና 248 ድንጋጌዎች አኳያ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ውሳኔዎቹ ተሽረው የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህግ አግባብ ስለሆነ የካሳ ክፍያና ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ይወስንልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱም ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡበትን የወንጀል መዝገብ በትዕዛዝ አስቀርቦ እና አቤቱታውንም ከወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ ጋር በማገናዘብ መርምሮ የግራ ቀኙን የክርክር ሂደት አመልካች ስለስንብቱ ጉዳይ ተጠሪ በፈፀመው ድርጊት በወንጀል ተከሶ ክርክሩ ተጠናቆ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቷል፣ ይህ የወንጀል ችሎትጥፋተኝነት ውሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ስለሆነ ይታይልን በሚል አመልካች ላቀረበው ክርክር የስር ፍ/ቤት ከጭብጥ ውጭ ነው በሚል መታለፉ ስነ-ስርዓታዊ ነው?ወይስ አይደለም?የሚለውን ማየት እንዲቻል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም አመልካች ተጠሪን ከስር ለማሰናበት በምክንያትነት የጠቀሰው የአንድ ወር እግዱ ጊዜ ካበቃ በኃላ ተጠሪ ወደ ስራቸው ለመመለስ ፍቃደኛ ባለመሆን በተከታታይ ከ5 የስራ ቀናት በላይ በስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸውና እንዲሁም የድርጅቱን ማህተም እና የስራአስኪያጁን ቲተር አስመስሎ ሐሰተኛ የስራ ልምድ ሰርተው ወይም አሰርተው በመጠቀም በፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ምክንያት ነው በሚል መሆኑንና እነዚህን ምክንያቶችም ለክሱ መልሱን ሲሰጥ ጀምሮ ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን ለማሳየት በመከላከያነት አንስቶ መከራከሩን የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ተጠሪ ለስራ ስንብቱ ምክንያት ከሆነው ጋር በተያያዘ በፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ተከሰው በወንጀል ችሎት ጥፋተኛ ስለተባሉ እና ይህ የወንጀል ችሎት ጥፋተኝነት ውሳኔም ለጉዳዩ አግባብነት ስላለው ቀርቦ ይታይልን በማለት አመልካች ፍ/ቤቱን በክርክሩ ሂደት መጠየቁንም ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ በጭብጥነት የተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ ነበሩ?ወይስ አይደለም?የሚል እንጂ የተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ መሆን ጉዳይ አይደለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው አልፏል፡፡ይሁን እንጂ ይህ በወንጀል ችሎቱ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትውሳኔ አመልካች ስር ፍ/ቤት ካቀረበው መከራከሪያ ነጥብ አኳያ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ አስቀርቦ ሳይመለከት እና ጉዳዩንም ከወንጀሉ ጥፋተኝነት ውሳኔ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኃላ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ነበረበት፡፡

በመሠረቱ ተጠሪ የአመልካችን ማህተም እና እንዲሁም የድርጅቱን ስራ አስኪያጅ ቲተር አስመስሎ ሐሰተኛ የስራ ልምድ አሰርተው እና ይሄንኑ ሐሰተኛ ሰነድም ሌላ ቦታ ለስራ መወዳደሪያነት አለአግባብ በመጠቀም በፈጸሙት ወንጀል ድርጊት ተከሰው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ድንጋጌን በመተላለፍ በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው መቀጣቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ትዕዛዝ ቀርቦ ከዚህ መዝገብ ጋር እንዲያያዝ የተደረገው የወንጀል መዝገብም ይሄንኑን ያስገነዝባል፡፡

ይህ የተጠሪ ጥፋትም በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) ስር እንደተመለከተው በስራ ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም የሚለውን የሚያሟላከመሆኑም በላይ በአዋጁ አንቀጽ 27(1)(መ) ስር እንደተመለከተውም ተጠሪ የማይገባ ብልፅግና በመሻት የአመልካች ንብረት በሆነው ማህተም በድርጅቱ ስራአስኪያጅ ቲተር እና በድርጅቱ ስም አላአግባብ መጠቀም

ድርጊት እና ጥፋትመፈፀሙን የሚያሳይ ሲሆን አመልካቹ ከዚህ ምክንያት ጋር በተያያዘ በተጠሪ ላይ የወሰደው የስንብት እርምጃም ከእነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች አኳያ ህጋዊ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው ከህግ አግባብነት ውጭ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ከዚህ በላይ በተገለፁት ምክንያቶች መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.72453 በ29/8/05ዓ.ምየሰጠው ፍርድ እና የፌዴራሉ ከ/ፍ/ቤትበኮ/መ/ቁ.135773 በ23/11/05ዓ.ም. ይህንኑን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1)መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ ስራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ የ6ወር የካሳ ክፍያ፤የስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል አይገባም ብለናል፡፡
4. ነገር ግን የስር ፍ/ቤቶች የዓመት ረፍት ፍቃድንና ምስክር ወረቀትን አስመልክቶ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
5. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- ከስር ፍ/ቤት የቀረበው የወንጀል መዝገብ ይመለስ፡፡
- በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው የአፈፃፀም እግድም ተነስቷል፡፡ይፃፍ
- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/

የሰ/መ/ቁ. 95026

መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ዮናስ በቀለ-ከጠበቃ አያሌው ካሳዬ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ብርሃኑ ኩምሳ- ቀርበዋል

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍርድ

ጉዳዩ ከስራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዘ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ እና አመልካች እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን ያደረጉትን ክርክር የመረመረው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተከሳሽን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ የስራ ውሉን ያቋረጡት አላግባብ በመሆኑ ሕገወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች በድምሩ ብር 23,139 ከብር 200 ኪሳራ ጋር ለከሳሽእንዲከፍሉ የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን እኛም በሰበር ክርክሩ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብ የስር ፍ/ቤቶች የስራ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ውሳኔ የሰጡት ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በግራ ቀኙ ማስረጃ እና በተገቢው ስነ-ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ካደረጉ በኋላ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ መሆኑን በመገንዘብ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪ በ28/06/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ01/04/1994 ዓ.ም ጀምሮ ከተከሳሽ ጋር የቅጥር ውል ፈጽመው በካሸርነት እና በአስተናጋጅነት

ስራ ሲያገለግሉ እንደቆዩ እና ተከሳሽ በ26/06/2003 ዓ.ም የስራ ውላቸውን በሕገወጥ መንገድ እንዳቋረጡባቸው የሚገልጽ ሆኖ ሕገወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ29/07/2003 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከከሳሹ ጋር የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ የደላላነት ስራ በጋራ ሲሰሩ የነበረ ከመሆኑ ውጪ በቅጥር ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያልነበራቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠውበግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውል አለ ወይስ የለም? የሚል ጭብጥ ይዞ ሲሆን ከሳሽ ምስክሮቻቸውን አቅርበው እንዲያሰሙ ካደረገ በኋላ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካች በስር ፍ/ቤት ምስክሮችን ቆጥረው የነበረ መሆኑን በሰበር አቤቱታቸው ላይ የገለጹ እና ይህም በተጠሪው ያልተስተባበለ ሲሆን አመልካች ምስክሮችን ቆጥረው የነበረ ስለመሆኑም ሆነ ምስክሮቹን ሳይሰማ ስለቀረበት ምክንያት ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ የገለጸው ነገር የለም፡፡የአመልካች ምስክሮች ሳይሰሙ የቀሩት አመልካች በተያዘላቸው ቀጠሮ ሳያቀርቧቸው ስለቀሩ ስለመሆኑ ተጠሪ በመልሳቸው የገለጹ ቢሆንም ይህ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያረጋግጥም፡፡በመሰረቱ ከግራ ቀኙ የክርክር አቋም አንጻር ፍ/ቤቱ ለክርክሩ አወሳሰን የያዘው ጭብጥ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246-248 ድንጋጌዎች አንጻር ትክክለኛ ቢሆንም በሌላኛው ወገን የተቆጠረው ማስረጃ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በሚል ወይም ሕጋዊ ተቀባይነት ባለው ሌላ ምክንያት መሰማት አይገባውም የሚል ግልጽ ትዕዛዝ ሳይሰጥበት የክርክሩ ጭብጥ በአንደኛው ወገን ማስረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ መደረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.255፣257፣258፣259 እና ሌሎችም ድንጋጌዎች አንጻር ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች በግራ ቀኙ ማስረጃ እና በተገቢው ስነ-ስርዓታዊ አግባብ እንዲጣሩ ሳያደርጉ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠው እና በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የስራ ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ሕገወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች በድምሩ ብር 23,139 ከብር 200 ኪሳራ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትበመ.ቁ.40456 በ05/09/2005 ዓ.ምተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 134431 በ14/02/2006 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአመልካች የተቆጠሩትን ምስክሮች በመስማት እናየቀረበ ወይም የተቆጠረ ካለም የጽሁፍ ማስረጃ ጭምር በመመርመር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 3(1) በተመለከተው መሰረት በግራ ቀኙ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት መኖር አለመኖሩን አጣርቶ እና መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት ጉዳዩ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 97555

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳኒያ ከድር ጠበቃ ዘካርያስ መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኮሪያ ዘማቾች ቤተሰቦች ሽመናና ስጋጃ ስራ ጠበቃቀረቡ

***መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ይዘቱም በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ክስ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንደማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ቀርቤተራዬን እየጠበቅኩ ስሜ የተጠራ መስሎኝ በሌላ ሰው መዝገብ ችሎት ገብቼ  የእኔ ያልሆነው መዝገብ ሲዘጋ የእኔ መስሎኝ በመሄድ የእኔ መዝገብ ሲጠራ ባለመቅረቤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይህ የሆነው ባለመስማትና ባለማሰብ በጥፋቴ ስለሆነ የተዘጋው መዝገብ ይንቀሳቀስልኝ በማለት ሲሆን ተጠሪዎችም የአመልካች ጥያቄ ደርሶአቸው በሰጡት መልስ(ሀሳብ)አመልካች በራሳቸው ጥፋት መዝገቡ መዘጋቱን ስለገለፀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ እንደዚህ አይነቱን ጥፋት ይቅርታ የሚያደርግበት አግባብ ስለማይኖር መዝገቡን ለማስከፈት በቂ ምክንያት አይሆንም በቸልተኝነታቸው በመሆኑ ሊንቀሳቀስ አይገባም ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥህቁ.74(2)አንጻር ለመመርመር ከላይ አመልካች ባለመቅረባቸው ምክንያት ነው ብለው የሰጡትን ሀሳብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጋችን በቂ የሆነ እክል ምክንያት ትርጉም ባይሰጠውም አመልካችን ከችሎት መቅረብ ያገደው ምክንያት በቂ እክል ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት መዝገቡ ሊቀሳቀስ አይገባም በማለት ጥያቄው ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ የቀረበለትን መዝገብ በ22-4-2006 በዋለው ችሎት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡በአቤቱታቸውም ላይ የሥር ውሣኔዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን ቁጥር 74(2)አላማ ያላገናዘበ ትርጉም የተሰጠው ስለሆነና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል ሲሉ ጠይቋል፡፡

በዚህም የሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው አመልካች የሌላ ሰው ሥም ሲጠራ በስህተት ወደ ችሎት ገብተው መዝገባቸው የተዘጋ መስሏቸው መሄዳቸው በቂ እክል ምክንያት ነው?አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡

በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንግዲህ አመልካች በዚህ ጉዳይ የሚሉት በፍ/ቤቱ ቅጥር ጊቢ መጥቼ ተራዬን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ በስህተት የሌላሰው መዝገብ በተጠራበት ወደ ችሎት ገብቼ መዝገቡ የተዘጋ መስሎኝ መሄዴ በጉዳዩ መሣሣቴና ያለማሰቤን ይገልፃልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስልኝ ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው እንደዚህ ያለው ስህተት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጋችን እንደበቂ ምክንያት ሊቆጠር የሚገባው ነው አላለም ስለዚህ ሊንቀሳቀስላቸው አይገባም የሚል ነው፡፡የሥር ፍ/ቤቶችም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰሙ በኃላ አመልካች በንቃት መከታተል ነበረባቸው ጥፋት መሆኑን እራሳቸውም አምኗልና መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት በብይን ዘግቶታል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ሲመረምረው አመልካች ቀጠሮአቸውን አውቀው ወደ ፍ/ቤት ጊቢ መጥተው መሄዳቸው ተጠሪ በፅሑፍ ከሰጡት መልስም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የተቀበሉት እውነታ ነው ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች በስም ስህተትና ባለማስተዋል ችሎት ገብቶ መዝገባቸው የተዘጋ መስሏዋቸው መሄድ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው ጉዳያቸውን ትተው የሄዱ ናቸው ወደ ሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ እንደሚሉትም አመልካች ጉዳዩን ለመጎተትና ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ እያዩ ሄዱ የሚለው ክርክርም ከግምትነት በዘለለ የተረጋገጠም አይደለም፡፡በመሆኑም ችሎቱ ይህን አባባል አልተቀበለውም፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74(2)ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማም የአመልካችን አይነት ተከራካሪ ወገን ለመገደብ ተብሎ የተቀረፀ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻልበት ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

በመሆኑም አመልካች ለመዝገቡ መዘጋት እንደምክንያት ያቀረቡዋቸው ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.(74(2)ሥር እንደበቂ የእክል ምክንያት ሊቆጠር አይችልም ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ማጣቱ መሠረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርዓታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ብይንና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስላቸው ያቀረቡት ምክንያት በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ቁ.74(2) መሠረት በቂ ነው ብለናል፡፡
3. መዝገቡ እንደገና ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ ከቆመበት ይቀጥል ብለን ጉዳዩን ለስር ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ይፃፍ፡፡
4. የግራ ቀኙ ውጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ 95620

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- በቂርቆስ ክ/ከተማ የወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-

1. ፲ አለቃ ከድር አህመድ } ቀረቡ
2. ወታደር ምትኩ ጀማል
3. ፲ አለቃ ነጋሽ አሰፋ } አልቀረቡም
4. ፲ አለቃ ሳሙኤል በቀለ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁን የሰበር ተጠሪዎች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሾች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ፡- ታህሳስ 01 ቀን 1996 ዓ/ም ከተከሳሽ ጋር ባደረግነው የአጭር ጊዜ የሊዝ ውል 128 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ 4 ክፍል የንግድ ቤቶችን በግል ገንዘባችን ሰርተን ስንጠቀምበት የቆየን ቢሆንም ቦታው ለሸራተን ሆቴል ማስፋፊያ ምክንያት እንዲፈርስ ተወስኖ ቤቶቹን ተከሳሽ ያስፈረሰ ቢሆንም ፍራሹን ለከሳሾች መስጠት ሲገባው ከሌሎች ከፈረሱት የመንግስት ቤቶች ጋር ተሸጧል በሚል ስለከለከለን ለቤቶቹ መሥሪያ የዋሉትን ቁሳቁሶች ዋጋ እና ቤቶቹን ለሰሩት ባለሙያዎች የተከፈለውን የእጅ ዋጋ በድምሩ ብር 130,000.00 ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልን ሲሉ የንብረቶቹን ዝርዝር እና ግምታቸውን በማስፈር ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከማቅረቡም ሌላ በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥቷል፡፡ የመቃወሚያ ነጥቦቹም፡- በከሳሾች እና ተከሳሽ መካከል

በተደረገው የሊዝ ውል አንቀጽ 12 በውሉ ትርጉምና አፈጻጸም ዙሪያ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በስምምነት ሊፈቱ እንደሚገባ፤ካልተቻለም በሽምግልና ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶ እንደሚጠናቀቅ ስለተስማማን ከሳሾች በቀጥታ ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡትን ክስ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን የለውም፣የሊዝ ውሉ ጊዜው የተጠናቀቀ በመሆኑ ቀሪ የሆነውን ውል መሰረት አድርገው ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም የሚሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው መልስ፡-በሊዝ ውሉ አንቀጽ 6(4) መሰረት ከሳሾች ቦታው ለልማት ተፈልጎ እንዲነሱ በሚጠይቁበት ጊዜ ለግል ሥራቸው ለገነቧቸው ግንባታዎች ወጪም ሆነ ካሳ ሊጠይቁ እንደማይችሉ የተደነገገ በመሆኑና ቦታውም ለልማት መፈለጉን ባልካዱበት ሁኔታ ያቀረቡት የንብረት ግምት ክስ አግባብነት የለውም ሲል ከመከራከሩም በተጨማሪ ከሳሾች ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው ጠይቀው በኮንቴይነር ኢንተርፕራዝ እንዲደራጁ ከተደረገ በኋላ የተሰጣቸውን የንግድ ማከናወኛ ቦታ ለ3ኛ ወገን አስተላልፈው በመገኘታቸው በመመሪያው መሰረት እንዲነጠቁ ተደርጓል፤ ብር 130,000.00 ለንብረታቸው ግምት እንዲከፈላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም ንግድ ቤቱ ሲሰራ የተሰራበት ዕቃ የወጪ ዝርዝር በማስረጃ አስደግፈው ካለማቅረባቸውም ሌላ ተከሳሽም ንብረቱን በምን ያህል ዋጋ እንደሸጠ የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም ከሳሾች ክሳቸውን በዝርዝር ማስረጃ አስደግፈው ስላላቀረቡ ውድቅ ሊደረግባቸው ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ያቀረባቸውን የመቃወሚያ ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ፍርድ፡- በከሳሾች እና ተከሳሽ መካከል ታህሳስ 01 ቀን 1996 ዓ/ም በተደረገው የአጭር ጊዜ የሊዝ ውል አንቀጽ 6.4 ውል ሰጪ ቦታውን ለሌላ ልማት ፈልጎት ውል ተቀባዩ እንዲለቅ ሲጠየቅ ውል ተቀባዩ ለግል ሥራው ይጠቅመኛል ብሎ ለገነባቸው ቤቶች ወጪም ሆነ ኪሳራ ሊጠይቅ እንደማይችል የተገለጸ ቢሆንም በአንቀጹ የሰፈረው ሁኔታ ከሳሾች ቦታውን ሲለቁ ለግንባታ የተጠቀሙባቸውን ንብረቶች የመጠየቅ እና ከተከለከሉም ግምታቸውን ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይደለም፣ተከሳሽም የከሳሾችን ቤቶች ስለማፍረሱ እና የቤቶቹን ፍራሽ አካላት መሸጡን በማመኑ ተከሳሾች በክሳቸው ለጠቀሷቸው ንብረቶች ግምታቸውን የማይከፍልበት ምክንያት አይኖርም ሲል ከሳሾች እንዲከፈላቸው ክስ ካቀረቡት የብር 130,000.00 የንብረት ግምት ውስጥ ብር 31,620.00 በመቀነስ ቀሪውን ብር 73,780.00 ፍርዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ተከሳሹም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከራቸው በኋላ በሰጠው ፍርድ፡-የሥር ፍርድ ቤት የተሻሻለ ክስ እንዲቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ መልስ ሰጪዎች ግምቱን በተመለከተ ዘርዝረው እንዲያቀርቡ ከሚገልጽ በስተቀር ሌላ የተለየ ይዘት

የለውም፣ይግባኝ ባይም ቀደም ሲል የቀረበው ክስ ግልጽ ባለመሆኑ ለመከላከል የሚያስችል አይደለም በማለት በዝርዝር እንዲቀርብ አለመጠየቁ በወቅቱ በቂና ለመከላከል የሚያስችል መሆኑን አምኖ መቀበሉን ስለሚያሳይ በተሻሻለው ክስ መልስ አልሰጠሁም ሲል ያቀረበው ቅሬታ መሰረታዊ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፣እንዲሁም ይግባኝ ባዩ በሥር ፍርድ ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ተገቢ ነው የሚላቸውን ክርክሮች በማቅረቡ ክርክሩን ለሥር ፍርድ ቤት መመለስ መልስ ሰጪዎችን ለመጉላላት ከሚዳርግ በስተቀር ጠቀሜታ የለውም ብሏል፡፡ በሌላ በኩል ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በተመለከተም ከብር 130.000.00 ውስጥ ብር 73,780 ይግባኝ ባዩ እንዲከፍል መወሰኑ ፍትህን የሚያጓድል አይደለም ሲል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ አጽንቷል፡፡

አመልካችም በሥር ፍርድ ቤቶች ፍርድ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት የጠቀሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም፡- ለአመልካች የደረሰው ክስ በ03/02/2005 ዓ/ም የተጻፈ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በራሱ አነሳሽነት አመልካችን ሳይጠራ ክሱ እንዲሻሻል በማዘዝ በ15/04/2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንድሰጥበት ሳያደርግ እና የመከላከያ መልሴን ሳላቀርብ ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ ፍርድ መስጠቱም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ማጽናቱ ፍርድ ቤቶቹ መሰረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ህግ ጥሰት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው፤ለአመልካች የተሻሻለው ክስ ቢደርስ ኖሮ በቀረበው የንብረት ግምት ዝርዝር እና ማስረጃ ዝርዝር አንጻር አመልካችም ንግድ ቤቶቹ ከመፍረሳቸው በፊት በባለሙያ የተሰራውን ግምት እና ቤቶቹ ሲፈርሱ የነበሩትን እማኞች በማቅረብ ማስተባበል የምችል ሆኖ ሳለ ክርክሩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ማድረጉ ጠቀሜታ የለውም ሲል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍርዱ ያሰፈረው ያለአግባብ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ፡- በመጀመሪያው ክስ በጥቅል ቀርቦ የነበረው የንብረት ግምት ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በቀረበው ክስ በዝርዝር ከመቅረቡ ውጪ የተሻሻለው ክስ በመጀመሪያ ከቀረበው ክስ የፍሬ ነገር ልዩነት የለውም፡፡ የተሻሻለውና በዝርዝር የቀረበው ክስ ለአመልካች ቢደርስ ኖሮ አመልካቹ ምናልባት እንደገና ግምቱን ከመቃወም በስተቀር አስቀድሞ የንግድ ቤቶቹን ማፍረሱን በማመኑ ክዶ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በመሆኑም ለአመልካች የተሻሻለው ክስ ቢደርሰውም እንኳን ውሳኔውን የሚያስለውጥ ክርክር ማቅረብ በማይችልበት ሁኔታ የመከላከል መብቴ አልተከበረም ሲል ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሊደረግበት የሚገባ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ተጠሪዎች ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጡት አግባብነት ያላቸውን የፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ጠብቀው ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍርዱ መግቢያ ላይ የአሁን ተጠሪዎች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ የተሻሻለ ክስ ማቅረባቸውን የገለጸ ሲሆን አመልካችም ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በአማራጭ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ ማቅረቡን መዝግቧል፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጠውም ይህንኑ የተሻሻለውን ክስ እና አመልካች ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም ያቀረበውን መልስ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም በተሻሻለው የተጠሪዎች ክስ ላይ አመልካች መልስ ስለመስጠቱ የፍርድ ቤቱ ፍርድ አያመላክትም፡፡ ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም አመልካች የሰጠው መልስ ለመጀመሪያው ክስ እንጂ ለተሻሻለው ክስ አለመሆኑን በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ከተደረገው ክርክር እና ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከሰጠው ፍርድ መረዳት ከመቻሉም ሌላ በዚህ በሰበር ደረጃም በተደረገው ክርክር ተጠሪዎች አመልካች ለተሻሻለው ክስ መልስ አለመስጠቱን በማመን ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሻሻለው ክስ ላይ አመልካች የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ያላደረገው ምክንያት ግልጽ ባይሆንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ለተሻሻለው ክስ አመልካች መልስ አለመስጠቱን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች በተሻሻለው ክስ መልስ እንዲሰጥበት ማድረጉ የሚያመጣ ለውጥ አይኖረውም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪዎች አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ግምቱን በተመለከተ በዝርዝር ማቅረባቸውን ከሚያሳይ በስተቀር ከመጀመሪያው ክስ የተለየ ይዘት ያለው ካለመሆኑም ሌላ አመልካችም ግምቱ ተገቢ እንዳልሆነ በመጀመሪያው ክስ ተከራክሯል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ መጀመሪያ በቀረበው ክስ ንብረቶቹ የሚያወጡት ዋጋ ግምት እና ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች በዝርዝር አለመቅረባቸው ተረጋግጦ ክሱ ተሻሽሎ የንብረቶቹ ዝርዝር ከነግምታቸው እና የተለያዩ ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎች ተለይተው በዝርዝር እንዲቀርቡ እስከተደረገ አመልካችም የተሻሻለው ክስ ደርሶት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1)(ሠ) በተነገረው መሰረት የማያምናቸውን የንብረቶቹን ግምት እና ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችም ካሉ በግልጽ እና በዝርዝር በመካድ እንዲከራከር፣ እንዲሁም በዚሁ የህግ ቁጥር በፊደል (መ) መሰረት የበኩሉን ማስረጃዎች በማቅረብ እንዲያስተባብል ዕድል መስጠት በድንጋጌው የተመለከተው መብቱ እንዲከበርለት የሚያደርግ ከመሆኑም ሌላ ትዕዛዙን የሰጠው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91(1) መሰረት ክሱ እንዲሻሻል በራሱ አነሳሽነት ሲያዝ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ይረዳል በሚል የያዘውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርስ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም በተሻሻለው የተጠሪዎች ክስ ላይ አመልካች መልስ ሳይሰጥበት እና የበኩሉን የማስተባበያ ማስረጃዎችን ሳያቀርብ የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ፍርድ የሰጡት ከዚህ በላይ

የተጠቀሱትን ደንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ፍርዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ የተደነገገውን የክርክር አመራር ሥርዓት መሰረት በማድረግ የተሰጠ አለመሆኑን ስለሚያሳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ስንል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 02230 በቀን 19/07/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/135414 በቀን 23/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. ተጠሪዎች ታህሳስ 15 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ለአመልካች ደርሶት አመልካችም የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመስማት በጉዳዩ ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የበኩሉን ፍርድ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ለቂርቆስ ምድብ ችሎት ትዕዛዝ ይጻፍ፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 95649

ሚያዝያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኢትዮጵያ ንጉሴ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አዲስ ጡብ ማምረቻ ድርጅት - ጠበቃ ምናለ ዓለሙ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ በአሰሪው የተወሰደበትየስራ ስንብት እርምጃ ሕገወጥነት በፍርድ ተረጋገጦ ወደስራው እንዲመለስ ለተወሰነለት ሰራተኛ ውዝፍ ደመወዝ መከፈል የሚገባው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) የተመለከተውን ድንጋጌ አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ተጠሪው የወሰደውን የስንብት እርምጃ በመቃወም አመልካች ባቀረቡት ክስ ሳቢያ ጉዳዩን የተመለከተው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ እንደሆነ መረጋገጡን ገልጾ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ በመ/ቁ.74375 በ02/08/2005 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪው ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኃላ በመጨረሻ ግንበመ.ቁ.133025 በ02/11/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/.ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ ማሰናበቱን፣ከዚህ በኂላ አመልካች ጉዳዩ በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው በመጀመሪያው የስረ-ነገር መዝገብ ላይ በ26/02/2006ዓ.ምበተጻፈ ማመልከቻ ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ፍ/ቤቱም ጥያቄው መቅረብ የሚገባው ለይ/ሰሚው ፍ/ቤት እንደሆነ ገልጾ በ29/02/2006 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን፣ቀጥሎም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ባፀናበት ወቅት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስንላቸው ያለፈው በስህተት በመሆኑ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.208መሰረት እንዲታረምላቸውበ18/03/2006ዓ.ምበተጻፈ ማመልከቻ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን፣ፍ/ቤቱም አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት በ26/03/2006 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱን እና አመልካች አቤቱታ ያቀረቡትም ሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች በመጨረሻ የሰጧቸው ሁለት ትዕዛዞች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮበዚህ ጉዳይ አመልካች ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ ስለፀና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት ውዝፍ ደመወዝእንዲከፈላቸው የዳኝነት ጥያቄያቸውን በግልጽ አቅርበው እያለ በአቤቱታው ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ተጠቅሷል በሚል አቤቱታው በሙሉ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቿ መሰረታዊ የክርክር ነጥብ ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 133025 በ02/11/2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ዘግቶ ያሰናበተው አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኋላ በመሆኑ በመ/ደ/ፍ/ቤት ከተወሰነልኝ የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ በተጨማሪ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት ሌላ የስድስት ወራት ውዝፍ ደመወዝ ሊወስንልኝ ይገባ ነበር የሚል መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡እንደተባለው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው በ02/08/2005 ዓ.ም ሲሆን ይ/ሰሚው ከ/ፍ/ቤት ደግሞ አፈጻጸሙን አግዶ ካቆየ በኋላ ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው በ02/11/2005 ዓ.ም በመሆኑ አፈጻጸሙ ለሶስት ወራት ያህል ታግዶ ቆይቷል፡፡ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ ያሰናበተው አፈጻጸሙን ለሶስት ወራት አግዶ ካቆየ በኋላ በመሆኑ ይግባኙን በሰረዘበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) በተመለከተው መሰረት ተጨማሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊወስንልኝ ሲገባው በዝምታ ያለፈብኝ አላግባብ ነው የሚሉ ከሆነ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ተጨማሪ ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስን ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበት በ02/11/2005 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ ላይ አመልካች ስርዓቱን ጠብቀው የሰበር አቤቱታቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸው የነበረ ሆኖ እያለ ይህንን አላደረጉም፡፡ይልቁንም የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክተው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ ካሰናበተ ከአራት ወር ከሶስት ሳምንት በኋላ አመልካች የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲታረምላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌን በመጥቀስ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረባቸውን ነው፡፡በመሰረቱ አንድ ፍ/ቤት በሰጠው ፍርድ ወይም ትዕዛዝ ውስጥ ውሳኔ ሊያሳርፍበት ይገባው የነበረውን መብት አላግባብ አልፎብኛል የሚል ተከራካሪ ወገን አላግባብ ታለፈብኝ የሚለውን መብት ማስከበር የሚችለው በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ቀጥሎ ላለው የፍ/ቤት እርከን ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ በማቅረብ ከሚሆን

በስተቀር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌን ጠቅሶ ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረብ አይደለም።የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ድንጋጌ ለተያዘው ዓይነት ክርክር አግባብነት/ተፈጻሚነት/ የሌለው ስለመሆኑም ከድንጋጌው አነጋገር በግልጽ መገንዘብ ይቻላል።

ሲጠቃለል አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል።

**<u>ውሳኔ</u>**

1. ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ባጸናበት ወቅት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 43(5) መሰረት የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ሳይወስንልኝ ያለፈው በስህተት በመሆኑ ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ይታረምልኝ በማለት አመልካች በ18/03/2006 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ያቀረቡትን ጥያቄ የመረመረው የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት ነጥብ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ሊታረም የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት በመ.ቁ. 133025 በ26/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 90361

የካቲት 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች-፡ ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶለሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1.ወ/ሮ አለዊያ ዑመር

2. አቶ አህመድ ሁሴን

3 .ወ/ሮ ኑር ሁሴን

4. ወ/ት አስማ ሁሴን

5. አቶ ሙህሲን ሁሴን

6. ወ/ት አይዳ ሁሴን

ተጠሪ፡- አቶ ሐሺም ሁሴን

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ዕዳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ተከሳሾች በነበሩት የአሁኖቹ አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ17/10/2003 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት የነበሩት እና የቀሪዎቹ ተከሳሾች አባት የሆኑት አቶ ሁሴን አህመድ በ28/09/1992 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ተከሳሾቹ የሚስትነት እና የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸውን፣ሟች እና ሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲበኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የብርጭቆ ፋብሪካ በሽርክና ሲያቋቁሙ ከሳሽ ፋብሪካውን እንዲያስተዳድሩ ተስማምተው የነበረ መሆኑን፣ከሳሽም ከሶስት ዓመታት ያለምንም ስራና ክፍያ ሲጉላሉ መቆየታቸውን፣የፕሮጀክቱን ስራ ተግባራዊ ለማድረግ በሂደት ላይ እያሉ ሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲ በገዛ ፈቃዳቸው ራሳቸውን ከፕሮጀክቱ ያገለሉ መሆኑን፣ከሳሽ ያለምንም ስራና ክፍያ ለቆዩባቸውሶስት ዓመታት ክፍያና ካሳ

የሚውል ብር 400,000 በሼህ አህመድ ሁሴን አል አሙዲ በስህተት ለሟች እንዲከፈል መደረጉን እና ሟችም ክፍያው የተከፈላቸው በስህተት መሆኑን አምነው በ10/05/1985 ዓ.ም በተጻፈ መተማመኛ በእማኞች ፊት አረጋግጠው እያለ ይህንን ክፍያ ሳይፈጽሙ በሞት መለየታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሾቹ የአውራሻቸው የሆነውን ይህንኑ ዕዳ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሾቹ በበኩላቸው በ14/11/2003 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ከ18 ዓመት በላይ የሚሆነው በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽ የሟች ባለቤት፣ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ወራሾች ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን፣ሟች በ10/05/1985 ዓ.ም ሰጡ በተባለው መተማመኛ ላይ ያለው ፊርማ የሟች አለመሆኑን፣2ኛ ተከሳሽ ዕዳውን አምነው የተቀበሉበት ነው በተባለው በ09/12/2001 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማም የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን እና ውርሱ ሳይጣራ እና የውርስ ክፍያው ሳይፈጸም ወራሾች በሟች ዕዳ ሊጠየቁ የማይገባ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም ፊርማዎቹ በተካዱት ሁለቱ ሰነዶች ላይ የተመለከቱት ፊርማዎች ተመርምረው ውጤቱ እንዲገለጽ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በሟች ተሰጠ የተባለው መተማመኛ በአረብኛ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ በመሆኑ መመርመር እንዳልተቻለ የተገለጸ ሲሆን በ2ኛ ተከሳሽ የተሰጠ ነው በተባለው መተማመኛ ላይ ያለው ፊርማ ግን በ2ኛ ተከሳሽ የተፈረመ መሆኑ ተረጋግጦ ቀርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር ከመረመረ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ የሟች ባለቤት፣ ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ወራሾች መሆናቸውን እንዳረጋገጡ፣ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም.ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 17/10/2003 ዓ.ም ድረስ ከ18 ዓመት በላይ ያለፈው ቢሆንም 2ኛ ተከሳሽ በ09/12/2001 ዓ.ም በሰጡት መተማመኛ ሟች በሰጡት ማስረጃ መሰረት ብር 400,000 ፋብሪካው ከተሸጠ በኋላ የሚከፈል መሆኑን በማረጋገጥ መተማመኛ የሰጡ በመሆኑ እና ተከሳሾቹ በሰነዱ ላይ የተመለከተው ፊርማ የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን ክደው የነበረ ቢሆንም ፊርማው የ2ኛ ተከሳሽ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ በ2ኛ ተከሳሽ የተሰጠው የዕዳ ማረጋገጫ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1851(ሀ) መሰረት ይርጋውን የሚያቋርጥ እንደሆነ እና ተከሳሾቹ በወረሱት የገንዘብ መጠን የሟችን ዕዳ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው በመግለጽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወለድ እና ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሾቹ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተከሳሾቹ በስር ፍ/ቤት ለክሱ በሰጡት መልስ 2ኛ ተከሳሽ ዕዳውን አምነው የተቀበሉበት ነው በተባለው በ09/12/2001 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማም የ2ኛ ተከሳሽ አለመሆኑን ክደው ከመከራከር ውጪ 2ኛ ተከሳሽ የሰጠው መተማመኛ ሌሎች ተከሳሾችን አይመለከትም በሚል

ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ በይግባኝ ክርክር ደረጃ 2ኛ ተከሳሽ የሰጠው መተማመኛ ሌሎች ተከሳሾችን አይመለከትም በሚል ያቀረቡት ክርክር በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች ለሟች ዕዳ የአንድነት ባለዕዳዎች ናቸው የሚባል ቢሆን እንኳ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም. ብቻውን በግሉ ሰጠ የተባለው የባለዕዳነት መተማመኛ የተቀሩትን ባለዕዳዎች ሁኔታ ሊያከብድ የሚችል መሆን አለመሆኑን ከፍ/ሕ/ቁ.1906 አንፃር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሳ ስለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን እና የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረውም ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1845 እና 1846 ላይ ተመልክቷል፡፡አመልካቾቹ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሚከራከሩትም ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም.ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 17/10/2003 ዓ.ም.ድረስ ከ18 ዓመት በላይ አልፎታል በማለት ሲሆን የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህን የይርጋ መቃወሚያ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት በ2ኛ ተከሳሽ በ09/12/2001 ዓ.ም. የተሰጠው የዕዳ ማረጋገጫ በፍ/ሕ/ቁ. 1851(ሀ) መሰረት ይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ በሕግ ተለይቶ የተወሰነ የይርጋ ጊዜ የመቋረጥ እና ያለመቋረጥ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ ሊነሳ የሚችለው የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል የተባለው ምክንያት የተከሰተው የይርጋው ጊዜ ከመሙላቱ በፊት በሆነ ጊዜ እንጂ የይርጋው ጊዜ የሞላ ወይም ያለፈ በሆነ ጊዜ ጭምር አይደለም፡፡በተያዘው ጉዳይ ሟች መተማመኛ ሰጡ ከተባለበት ከ10/05/1985 ዓ.ም. ጀምሮ 2ኛ አመልካች መተማመኛ ሰጡ እስከተባለበት 09/12/2001 ዓ.ም.ድረስ 16 ዓመት ያለፈ በመሆኑ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ከተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚበልጥ በመሆኑ 2ኛ አመልካች ሰጡት የተባለው መተማመኛ የይርጋውን መቆጠር የሚያቋርጥ ነው በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተያዘውን አቋም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚች በሰጡት ማስረጃ መሰረት ብር 400,000 ፋብሪካው ከተሸጠ በኋላ የሚከፈል መሆኑን በማረጋገጥ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም. መተማመኛ የሰጡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡በመሰረቱ የይርጋ ተጠቃሚ የሆነ ሰው የሞላውን ይርጋ ለመተው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1856(1) የተመለከተ በመሆኑ አመልካቾቹ ሚች በ10/05/1985 ዓ.ም.ከሰጡት መተማመኛ አንጻር ሞልቶ የነበረውን ይርጋ በመተው አዲስ የመተማመኛ ሰነድ የሰጡ መሆኑ የተረጋገጠ እስከሆነ ድረስ ይህ በ2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም የተሰጠው መተማመኛ ይርጋን የሚያቋርጥ ሳይሆን አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ የሚያመለክት በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ሊወሰን የሚገባው የይርጋ ጊዜውን ከ09/12/2001 ዓ.ም. በመቁጠር ነው፡፡ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ይርጋው አልፏል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

አመልካቾቹ አጥብቀው የሚከራከሩበት ሌላኛው ነጥብ 2ኛ አመልካች በ09/12/2001 ዓ.ም.መተማመኛ የሰጡት በራሳቸው ስም እንጂ በሌሎች አመልካቾች ስም ጭምር አይደለም የሚል ነው፡፡በመሰረቱ አመልካቾቹ ከስር ጀምሮ የሚከራከሩት በአንድነት ሲሆን በከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደተገለጸው በሰነዱ ላይ የተመለከተው ፊርማ የ2ኛ ተከሳሽ አይደለም ከማለት በስተቀር ይህን የክርክር ነጥብ በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት አንስተው አልተከራከሩበትም፡፡በመጀመሪያ ደረጃ ያልተነሳውን ክርክርና ያልቀረበውን አዲስ ነገር በይግባኝ ደረጃ መቀበል የማይቻል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329(1) ስር የተመለከተ በመሆኑ ይህ የክርክር ነጥብ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛ አመልካች ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ስለሌሎች አመልካቾች የውክልና ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ እና በ09/12/2001 ዓ.ም መተማመኛውን በፈረሙ ማግስት በግልግል ዳኞች ጉባኤ ዘንድ ቀርበው ስለሁሉም አመልካቾች የዕርቅ ሰነድ የፈረሙ ስለመሆኑ ተጠሪ በመልሳቸው ላቀረቡት ክርክር አመልካቾች ያቀረቡት የማስተባበያ ክርክር አለመኖሩን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ይህም 2ኛ አመልካች መተማመኛውን የፈረሙት በራሳቸው ስም ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አመልካቾች ስም መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ 2ኛ አመልካች መተማመኛውን የፈረሙት በራሳቸው ስም ብቻ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር የሕግ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 185840 በ28/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 125077 በ25/06/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ.86398

ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልች፡- ወ/ሮ አሰለፈች ይመር - ጠበቃ ችርነት ወርዶፋ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ አስመረት ተወልደ
2. አቶ ብርሃኔ ተወልደ
3. አቶ ናትናኤል ተወልደ

ጠበቃ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻ ወይም የትዳር ሁኔታ መኖር አለመኖርን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን የመቃወሚያ ክርክር በመቀበል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የአቶ ተወልደ ገብሩ ሕጋዊ ሚስት ናቸው፤ብርክቲ ተወልደ፣ሲሳያስ ተወልደ፣ዳንኤል ተወልደ እና ሄለን ተወልደ ደግሞ ከዚሁ ጋብቻ የተወለዱ የአቶ ተወልደ ገብሩ ልጆችና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው በማለት ቀደም ሲል በ22/03/1993 ዓ.ም. ሰጥቶት የነበረውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) ድንጋጌ መሰረት አሻሽሎ የአመልካችን ሚስትነት የሚመለከተውን የውሳኔ ክፍል በመሰረዝ እና የተወላጆቹን ልጅነት እና ወራሽነት የሚመለከተውን የውሳኔ ክፍል ግን በማጽናት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 17 በቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 1972 ሲኖሩ ቆይተው በ12/03/1991 ዓ.ም በሞትመለየታቸውን በመግለጽ አመልካች ሚስትነታቸው እና የአራቱ ልጆች ወራሽነት እንዲሁም አመልካች ለሁለቱ ልጆች

ሞግዚት መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በ29/03/1991 ዓ.ም አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ለዚህ አቤቱታቸውም አራት ምስክሮችን መቁጠራቸውን እና ሚስትነታቸውን የሚያረጋግጥ ከወረዳ 2 ቀበሌ 11 ጽ/ቤት በቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ የተመዘገቡበትና ሌሎችም ማስረጃዎች በትዕዛዝ እንዲቀርቡላቸው መጠየቃቸውን፣በሌላ በኩል አቶ መስፍን ተወልደ፣ወ/ሮ ይህደጎ ተወልደ እና ወ/ሮ ፍሬ ወይኒ ተወልደ የተባሉ ሰዎች የሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ልጆች መሆናቸውን ገልጸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጣልቃ ገብነት ለመከራከር ጠይቀው በተፈቀደላቸው መሰረት በ23/11/1991 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ሟች በአድራሻቸው ይኖሩ የነበሩት ከሕጋዊ ባለቤታቸው ከወ/ሮ አክበረት አስገዶም ጋር መሆኑን፣ሟች ከአመልካች ጋር አመልካች በጠቀሱት አድራሻ ኖረው የማያውቁ መሆኑን፣አመልካች ሚስት ስለመሆናቸው የቀረበ የጽሁፍ ማስረጃ አለመኖሩን፣ሌሎች አመልካቾችም በጋብቻ ውስጥ ስላልተወለዱ ልጅነታቸውን አረጋግጠው መቅረብ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በመግለጽ መከራከራቸውን፣ለዚህ የጣልቃ ገቦች ክርክር አመልካቿ በ11/04/1992 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ሟች ከወ/ሮ አክበረት አስገዶም ጋር የነበራቸው ጋብቻ በስምምነት የፈረሰ መሆኑን፣የጋብቻ ሁኔታ መኖሩን በምስክሮች ማስረዳት የሚቻል መሆኑን፣ተወላጆቹም የተወለዱት በጋብቻ ውስጥ በመሆኑ ወራሽነታቸው ሊረጋገጥ የሚገባው መሆኑን በመግለጽ መልስ መስጠታቸውን፣ፍ/ቤቱም በሁለቱም ወገኖች አራት አራት ምስክሮችን ከሰማ በኃላ የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በምስክሮች ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 700(1) የተመለከተ መሆኑን እና በአንጻሩ የባልና ሚስትነት ሁኔታ አለመኖሩንም በምስክሮች ማስተባበል የሚቻል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 700(2) ተደንግጎ እንደሚገኝ፣ሟች እና አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 17 በቀበሌ 20 በቤት ቁጥር 1972 ውስጥ ከ20 ዓመት በላይ በባልና ሚስትነት የኖሩ፣አራት ልጆችን የወለዱ እና እሰከ ሟች ሞት ድረስ ያልተለያዩ መሆኑ በአመልካች ምስክሮች እንደተረጋገጠ፣ በማስረጃነት በትዕዛዝ የቀረበው በዞን 5 የወረዳ 2 ቀበሌ 11 መስተዳድር ጽ/ቤት የስራ አስፈጻሚ አባላት ያስተላለፉት ውሳኔም ሟች የአመልካች ባለቤት መሆናቸውን የሚገልጽ እንደሆነ፣ጣልቃ ገቦች ያሰሟቸው ምስክሮች በአመልካች ማስረጃ የተመሰከረውን ፍሬ ነገር የሚያስተባብል እንዳልሆነ በዝርዝር ገልጾ የጣልቃ ገቦችን ክርክር ውድቅ በማድረግ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 699 መሰረት የአመልካችን ሚስትነት እና የሌሎችን አመልካቾች ልጅነት እና ወራሽነት በማረጋገጥ በ22/03/1993 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን የውሳኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአሁኖቹ ተጠሪዎች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ውሳኔ ላይ ሲሆን በ28/08/2000 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ይዘትም ባጭሩ፡-ባለቤታቸው ወ/ሮ አክበረት አስገዶም ከሞቱበት ከ1973 ዓ.ም. ጀምሮ

ሟች አቶ ተወልደ ገብሩ እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ ሌላ ጋብቻ ያልመሰረቱ መሆኑን፣አመልካች ውሳኔ ያሰጡትም ጋብቻው በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሀይማኖት ወይም በባህል መሰረት የተፈጸመ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ሳይኖር መሆኑን እና ሌሎች አመልካቾችም በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ አለመሆኑን የሚገልጽ ሆኖ የሚስትነት እና የልጅነት ውሳኔው እንዲሰረዝ የተጠየቀበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም በመቃወም አቤቱታው ላይ አመልካቿ መልስ እንዲሰጡበት ካደረገ እና የመቃወም አመልካቾችን ምስክሮች ከሰማ በኃላ

1. አመልካች ወ/ሮ አሰለፈች ይመር የሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ሚስት ናቸው ወይስ አይደሉም?
2. ከወ/ሮ አሰለፈች ይመር የተወለዱት አመልካቾች የሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ልጆች ናቸው ወይስ አይደሉም?

የሚሉ ጭብጦችን መስርቶ አጠቃላይ ክርክሩን በመመርመር **የመጀመሪያውን ጭብጥ** በተመለከተ አመልካቿ ሚስትነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ጋብቻቸው የተፈጸመው በየትኛው ስርዓት መሰረት እንደሆነ እንዳልገለጹ፣አመልካች ቀደም ሲል ያሰሟቸው ምስክሮችም አመልካች ከአቶ ተወልደ ገብሩ ጋር ሲኖሩ ነበር ከማለት ውጪ ጋብቻ የነበራቸው ስለመሆኑም ሆነ ጋብቻው በየትኛው ስርዓት መሰረት እንደተፈጸመ የገለጹት ነገር እንደሌለ፣የመቃወም አመልካቾቹ ምስክሮች በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም በአንደኛቸው ባህል መሰረት የተፈጸመ ጋብቻ አለመኖሩን ወይም ጋብቻ አለመመስረቱን በተመሳሳይ ሁኔታ እንደገለጹ እና የጋብቻ ሁኔታ አለ የሚል ድምዳሜ በመያዝ ውሳኔ የተሰጠውም ባልተነሳ ጉዳይ ወይም ባልተጠየቀ ዳኝነት በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይገባ ገልጾ የሚስትነት ውሳኔውን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በመሰረዝ እና **ሁለተኛውን ጭብጥ** በተመለከተ ግን አራቱ አመልካቾች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ እንደቻለ እና ሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ በነበሩበት መረዳጃ ዕድር መሙያ ቅጽ ላይም ልጆች በሚለው ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው እንደተገኙ ገልጾ ብርክቲ ተወልደ፣ሲሳያስ ተወልደ፣ዳንኤል ተወልደ እና ሄለን ተወልደ ከሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ የተወለዱ ልጆች ናቸው በሚል ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በማጽናት ውሳኔ ሰጥቶአል።

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሚስትነት ውሳኔው መሰረዙን በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በአጣሪው ችሎት በተያዘው ጭብጥ እና ቀጥሎም በአጣሪው ችሎት ከተያዘው ጭብጥ

አገላለጽ ጋር ተያይዞ ተጠሪዎቹ ተጨማሪ ክርክር ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል ይህ አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት በ22/01/2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ ወደ ተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመገባቱ በፊት አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠው በሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በቅድሚያ እልባት ማግኘት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በፍርድ ቤት የሚደረግ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 1 የተመለከተ ሲሆን ተከራካሪ ወገኖች ወደ ክርክር የሚገቡትም በከሳሽነት፣ በተከሳሽነት፣ በጣልቃ ገብነት፣ በተቃዋሚነት፣ በተተኪነት በመቃወሚያ አቅራቢነት፣ በመቃወም ተጠሪነት እና በመሳሰሉ በሕጉ በተመለከቱ ሁኔታዎች ሊሆን እንደሚችል አግባብነት ካላቸው የስነ- ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡በእነዚህ የሕግ አግባቦች ከሚደረጉት የክርክር ዓይነቶች መካከል አንዱ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የተሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል በማለት አስቀድሞ ለአንድ ወገን የተሰጠውን ውሳኔ ለማሰረዝ የመቃወም አመልካች በሆነው ወገን እና አስቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ተጠቃሚ በሆነው የመቃወም ተጠሪ በሚባለው ወገን መካከል የሚደረግ ክርክር ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ ክርክር የሚቀርብበት እና የሚመራበት ስርዓት እንዲሁም የዚህ ዓይነቱን ክርክር የሚሰማው ፍርድ ቤት ስላለው ስልጣን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ከቁጥር 358 እስከ 360 የተመለከተ ሲሆን በተለይም የመቃወም አቤቱታው መቅረብ የሚገባው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 222 እና 223 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ እና የማስረጃ መግለጫ የሚቀርብበትን ስርዓት መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጎአል፡፡የመቃወም አቤቱታው እና የማስረጃው ቅጂ የመቃወም ተጠሪ ለሆነው ወገን እንዲደርስ መደረግ የሚገባው መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር የመቃወም ተጠሪው የጽሁፍ መልስ እና የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚገባው በእነዚህ ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ የተጻፈ ባይሆንም የመቃወም ተጠሪ የሆነው ወገን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 234 ድንጋጌ መሰረት ለቀረበበት የመቃወም አቤቱታ ያለውን የመከላከያ መልስ እና ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ስለመሆኑ ከቁጥር 360(1) እና (2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡በተለይም የመቃወሚያው ክርክር የሚሰማው የመጀመሪያው ክርክር በተሠማበት ስነ ስርዓት መሰረት ስለመሆኑ በቁጥር 360(2) የተመለከተው አስገዳጅ ድንጋጌ በቀጥታ የቀረበ ክስ እና ክርክር የሚስተናገድበትን ስርዓት በተመለከተ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱት መሰረታዊ ድንጋጌዎች የመቃወሚያ ክርክርን በማስተናገድ ረገድም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ሊደረጉ የሚገባቸው መሆኑን በግልጽ

የሚያስገነዝብ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው  የክርክር አመራር ስርዓት ዓይነተኛ ዓላማ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች እኩል ዕድል እንዲኖራቸው እና በተለይም የመቃወም አመልካች የሆነው ወገን የክርክሩ ተካፋይ ባልነበረበት ጊዜ የቀረበውን የመቃወም ተጠሪ ወገን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ በመስቀልኛ ጥያቄ እና በማስተባበያ ክርክር ጭምር የመፈተን ዕድል እንዲያገኝ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል፡፡በመጀመሪያ ደረጃ የሚደረግ የፍትሐብሔር ክርክር ከሚመራባቸው መሰረታዊ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መካከል ደግሞ የመጀመሪያ ክስ ሲከፈት ስለሚፈጸም ስነ ስርዓት እንዲሁም ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር በአራተኛ መጽሀፍ በምዕራፍ ሁለት እንደቅደም ተከተላቸው ከቁጥር 241 እስከ 256 እና ከቁጥር 257 እስከ 271 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረበ አንድ የመቃወም ክርክር በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲመራ ለማድረግ ተከራካሪ ወገኖች በተለይ ደግሞ ክርክሩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመቃወም አመልካቾች በመቃወሚያቸን መሰረት ያስረዱልናል ያሏቸውን ምስክሮች አቅርበው ያሰሙ ሲሆን የመቃወም ተጠሪዋ ግን በቀድሞው ክርክር ጊዜ ካሰሙት በስተቀር የመቃወም አቤቱታው ከቀረበ በኋላ ያሰሙት ምስክር አለመኖሩን ወይም በሌላ አነጋገር በቀድሞው ክርክር ጊዜ አሰምተዋቸው የነበሩትን ምስክሮች በድጋሚ አቅርበው የመቃወም አመልካቾች ባሉበት ያላሰሙ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች ቀደም ሲል ያሰጡት የሚስትነት ውሳኔ ሊነሳ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት  የመቃወም አመልካቾች ብቻ ሳይሆን የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ጭምር ቀርበው እንዲሰሙ ማድረግ ሲገባው የመቃወም ተጠሪዋ ባሉበት የተሰሙትን የመቃወም አመልካቾች ምስክሮች ቃል ቀደም ሲል የመቃወም አመልካቾች በሌሉበት ከተሰማው የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ቃል ጋር በማነጻጸር የአመልካቿ ሚስትነት በተጠሪዎቹ ማስረጃ ተስተባብሏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ እና ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት አድርጎ የሚስትነት ውሳኔውን በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የክርክር አመራር ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመውን  ይህንን ስነ ስርዓታዊ ግድፈት ማረም ሲገባው ውሳኔውን ያጸናው በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም የአመልካች የሚስትነት ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የመቃወም ተጠሪዋ ምስክሮች ቀርበው የመቃወም አመልካቾች ባሉበት እንዲሰሙ ሊደረግ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ያልተሰጠ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 117112 በ01/02/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 99599 በ14/12/2004 ዓ.ም በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ከአመልካቿ የተወለዱት አራት ልጆች ከሟች አቶ ተወልደ ገብሩ ባራኪ የተወለዱ ልጆች ናቸው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የአመልካችን የሚስትነት ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 360(2) መሰረት በመሰረዝ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. የመቃወም ተጠሪዋ ቀደም ሲል ያሰሟቸውን ምስክሮች፣እነዚህ ምስክሮች ሊቀርቡ የማይችሉበት በቂና አሳማኝ ምክንያት ካለም የመቃወም ተጠሪዋ የሚቆጥሯቸውን ተለዋጭ ምስክሮች አስቀርቦ የመቃወም አመልካቾች ባሉበት ከሰማ እና የጽሁፍ ማስረጃም ካለ የመቃወም አመልካቾች አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ አመልካች ቀደም ሲል ያሰጡት የሚስትነት ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ መሰረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.91329

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስመረት ኃ/ሚካኤል ጠበቃ ጌትነት የሻነህ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ተስፋዬ ጥላሁን

2. ወ/ሮ መቅደስ ፈቃደ

3. አቶ ደረጀ ተስፋዬ

1ኛ ተጠሪ እና ስለ ሶስቱም ተጠሪዎች ጠበቃ ወንዳውክ አየለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አላግባብ የተያዘ ነው የተባለን ቤት በፍርድ ኃይል ከማስለቀቅ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካች እና ተጠሪዎች ጉዳዩ በተጀመረበት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ በ16/03/2003 ዓ.ም.አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከሳሽ ከአቶ ዘርዓይ ሐጎስ ጋር በ16/05/2002 ዓ.ምባህላዊ ጋብቻ ፈጽመው በ04/02/2003 ዓ.ምጋብቻውን በማስመዝገብ ማስረጃ የተሰጣቸው መሆኑን፣ በ18/05/1998 ዓ.ም በተጻፈ የኮንዶሚኒየም ቤት ሽያጭ ውል በቦሌ ክ/ከተማ በቀበሌ 01 ውስጥ በብሎክ 2 የሚገኝ ቁጥሩ ቢ.አር.አር.ቢ.2-1/05 የሆነ ቤት ከቦሌ ክ/ከተማ ለአቶ ዘርዓይ ሐጎስ የተላለፈ መሆኑን፣ ከሳሽ እና ባለቤታቸው ይህንኑ ቤት በ16/05/2002 ዓ.ም በተጻፈ የጋብቻ ውል የጋራ ያደረጉት መሆኑን፣ ይህንን ቤት በተመለከተ ባለቤታቸው ለ1ኛ ተከሳሽ በ25/12/2002 ዓ.ምየተጻፈ የውክልና ስልጣን ሰጥተው የነበረ ቢሆንም የውክልና ስልጣኑን ከ24/01/2003 ዓ.ም ጀምሮ የሻሩ መሆኑን እና ተከሳሾቹ ምንም መብት

ሳይኖራቸው ተከራዮችን በማስወጣት ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይዘው የሚገኙ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እና ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ኪራዩን እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በበኩላቸው በ12/04/2003 ዓ.ም.በተዘጋጀ ማመልከቻ ከሳሽ የአቶ ዘርዓይ ሐጎስ ባለቤት ስላልሆኑ ቤቱን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም የሚል መቃወሚያ ካስቀደሙ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጡት መልስ ክስ ያስነሳውን ቤት አቶ ዘርዓይ ሐጎስ በ25/12/2002 ዓ.ም. በተጻፈ ውል በብር 345,000 ለ1ኛ ተከሳሽ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑን፣ ለዋስትና ይሆን ዘንድም አቶ ዘርዓይ ሐጎስ የብር 345,000 ብድር ውል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ለ1ኛ ተከሳሽ የፈረሙ መሆኑን፣ የብድር ውሉን የፈረሙትም ትዳር እንደሌላቸው ከሚመለከተው ክፍል ማረጋገጫ በማቅረብ መሆኑን፣ ይህ በተደረገበት ጊዜም ከሳሽ የአቶ ዘርዓይ ሐጎስ የአክስት ልጅ እንደሆኑ በመግለጽ አብረዋቸው የነበሩ መሆኑን፣1ኛ ተከሳሽ ከአቶ ዘርዓይ ሐጎስ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት የቤቱን ጠቅላላ እዳ ከፍለው ከክፍለ ከተማው ጋር የሽያጭ ውል ያደረጉ መሆኑን እና ቤቱን የተላለፈባቸው በሽያጭ ውል በመሆኑ የውክልና ስልጣኑ የተሻረ የመሆን አለመሆን ጉዳይየሚያስከትለው ውጤት አለመኖሩን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው ቤቱን ያልያዙና ተከራዮችንም ያላስወጡ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን በ16/06/2003 ዓ.ም. በብይን አልፎ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ቤቱን ይዘው የሚገኙት ከሳሽ እንደሚሉት ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው በሕገወጥ መንገድ ሳይሆን በአቶ ዘርዓይ ሐጎስ እና በ1ኛ ተከሳሽ መካከል በተደረገ የሽያጭ ውል መሰረት እንደሆነ መረጋገጡን፣ የሽያጭ ውል መኖሩ በከሳሽም ያልተካደ መሆኑን፣ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ ቤቱን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ መብት የሚኖራቸው የሽያጭ ውሉን ከማስፈረስ አንጻር ከሚሆን በስተቀር ተከሳሾቹ ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ቤቱን በሕገወጥ መንገድ ይዘዋል በማለት እንዳልሆነ እና ከሳሽ የውል ይፍረስልኝ ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚል ጭብጥ መስርቶ በመዝገቡ ማከራከርና ውሳኔ መስጠት ስነ ስርዓታዊ አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ተጠሪዎች በሕገ ወጥ መንገድ መያዛቸውን በገለጹበት እና የኮንዶሚኒየም ቤቶችን ከአምስት ዓመት በፊት ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ

የማይቻል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 19/1997 በተደነገገበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የያዙት በሽያጭ ውል በመሆኑ የሽያጭ ውሉን የማስፈረስ ክስ ካልቀረበ በስተቀር በዚህ ክስ የውሉ ሕጋዊነት ሊመረመር አይችልም በሚል አመልካች በሚስትነታቸው ያቀረቡትን የቤት ይልቀቁልኝ ጥያቄ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በአመልካቾች በሕገ ወጥ መንገድ ተይዞአል በሚል አመልካች ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ያደረገው ቤቱ በተከሳሾቹ የተያዘው ከሳሽ እንደሚሉት በሕገ ወጥ መንገድ ሳይሆን በሽያጭ ውል መነሻ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ከሳሽ ቤቱ የተያዘው በውል መሆኑን እያወቁ በሕገወጥ መንገድ እንደተያዘ አድርገው ክስ ማቅረባቸው ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ማናቸውም ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ሁሉ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን በሚገባ መርምሮ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችለው በዚያው ነገር ሌላ አከራካሪ ጉዳይ በማያስከትል ሁኔታ ግልጽ በሆነ አጻጻፍ መቅረብ እንዳለበት፣ በክስ ማመልከቻ ላይ መገለጽ ከሚገባቸው ነገሮች መካከልም አንዱ የክሱ ምክንያት እና ለክሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችና እነዚሁ የተፈጠሩበት ጊዜና ስፍራ እንደሆነ የክስ አቀራረብን ከሚመለከቱ የፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ 80(2)፣213(1)፣216(1)፣222(1)(ረ) እና ሌሎችም ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓላማም የፍትሐብሄር ጉዳዮችን በተመለከተ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩት የግንኙነት ዓይነቶች፣ እንዲሁም እነዚህ ግንኙነቶች የሚገዙባቸው የህግ ድንጋጌዎች፣ ግንኙነቶቹን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች የሚመሩበት ስርዓትም ሆነ የተለያዩ ግንኙነቶችን አስመልክቶ ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡት የክርክር ነጥቦች የተለያዩ በመሆናቸው ምክንያት እንደየግንኙነቱ እና ክርክሩ ዓይነትና ሁኔታ ለፍ/ቤት የሚቀርቡትን ክርክሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ እና በተገቢው ስነ ስርዓታዊ አግባብ መርቶ እልባት ለመስጠት ማስቻል እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አቶ ዘርዓይ ሐጎስ በ25/12/2002 ዓ.ም. በተጻፈ ውል በብር 345,000 ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉ መሆኑ በአመልካች እንዳልተካደ እና ቤቱ በተጠሪዎች እጅ የገባው እና ይዘው የሚገኙት በዚሁ ውል ምክንያት እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በዚህ ሁኔታ በውል በተላለፈው ቤት ላይ መብት አለኝ የሚሉ ከሆነ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሰረት በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ማስከበር የሚችሉት ውሉን ከማስፈረስ አንፃር ከሚሆን በቀር በተጠሪዎች

በውል የተያዘውን ቤት በሕገወጥ መንገድ እንደተያዘ አድርገው ክስ ለማቅረብ የሚችሉበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ  አይኖርም፡፡ ቤቱ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ነው ማለት እና ቤቱ የተያዘበት ውል የሕጉን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ አይደለም ማለት ደግሞ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አመልካች ይህንኑ ተገንዝበው በፌ/ከ/ፍ/ቤት የውል ይፍረስልኝ ክስ አቅርበው በክርክር ላይ የሚገኙ ስለመሆኑ ተጠሪዎች የመዝገብ ቁጥሩን ጭምር ጠቅሰው ላቀረቡት ክርክርም አመልካች ያቀረቡት ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ያቀረቡት ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. አመልካች ያቀረቡት ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት የተከተለ ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 69748 በ11/09/2003 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 111732 በ23/04/2005 ዓ.ም. በፍርድ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የውል ይፍረስልኝ ክስ ለማቅረብ ያላቸው መብት በዚህ ውሳኔ አልተነካም፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/ዘቢ

የሰ/መ/ቁ. 91643

ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፦አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነገረ-ፈጅ
ፅጌ መለሰ ቀረቡ

ተጠሪ:- ካኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ሀጎስ አብርሃ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ።**

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 126221 ግንቦት 12 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበው ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ተጠሪ ከሳሽ አመልካችተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ተጠሪ በመኪና አስመጭነት የሚሠራ ነጋዴ መሆኑን ገልፆ፣ ከውጭ ያስመጣኋቸው አሥር ትራክተሮች የሚገዛኝ በማጣቴ በንብረትነት በማስመዝገብ በግል ልገለገልባቸው ስለፈለግሁ የባለሀብትነት ስም ለማዛወር 422,604.22 /አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም/ ለተከሳሽ (አመልካች) በ3-10-2003 ዓ.ም ከፍያለሁ፡፡ ከሳሽ ይህንን ገንዘብ ከከፈልኩ በኋላ ትራክተሮቹን ጌትስ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገዝቶኛል፡፡ ተከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲመልስ ብጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከነወለዱ እንደዚሁም ወጭና ኪሣራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ገንዘቡን

ከመመለሳችን በፊት የኢኮኖሚና ገንዘብ ሚኒስትር አስተያየት መጠየቅ ያለብን በመሆኑ ጠይቀናል ገንዘቡንም ለመመለስ በሂደት ላይ ስንሆን፣ ወጭና ኪሣራ ግን ልንከፍል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ከሳሽ በክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ ተከሳሽ ከሳሽን ለክርክርና ለወጭ ያልጋበዘ በመሆኑ፣ ወለድ ወጭና ኪሣራ ለከሳሽ ሊከፍል አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. ተጠሪ ወለድ ወጭና ኪሣራ የሥር ፍርድ ቤት አይገባህም ማለቱን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ተጠሪን ስምንት ወራት ያህል ገንዘቡን አልመለሰለትም፡፡ ስለዚህ አመልካች ወለድ፣ ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብና የጠበቃ አበል የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካች ተጠሪ የጠየቀውን ወለድ ፣ የዳኝነት ገንዘብ ፣ ይክፈል ፡፡ የጠበቃ አበል ተጠሪ ከጠየቀው ብር 44,000 ግማሹን ብር 22,000 /ሃያ ሁለት ሺ ብር/ ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የወጭና ኪሣራ ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ራሱ አገልግሎት ለማግኘት ገንዘቡን በፈቃዱ ከፍሎ አገልግሎት ለመስጠት በሂደት ላይ እያለን፣አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ከዚያም የመንግሥት የፋይናንስ አሠራር በመጠበቅ ልንመልስለት በሂደት ላይ በነበርንበት ወቅት፣ ወለድ፣ወጭና ኪሣራ እንድንከፍለው ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ አመልካች ገንዘቡን በወቅቱ ያልመለሰ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከዋናው ገንዘብ በተጨማሪ ወለድ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች የከፈለው ገዥ ያጡ መኪናዎች በስሙ ለማዛዋር በማሰብ እንደሆነ ከክስ ማመልከቻው ተገልጿል፡፡ ተጠሪ ገንዘቡን ከከፈለ በኋላ መኪናዎቹ (ትራክተሮች) በመሸጣቸው፣ የመኪናዎቹ ስመሀብት በስሙ ለማዛወር ጠይቆት የነበረው አገልግሎት እንዲቋረጥና አገልግሎቱን ለማግኘት ለአመልካች የከፈለው ገንዘብ እንዲ መለስለት እንደጠየቀ፣ ግራቀኙ በበታች ፍርድ ቤቶች እና በሰበር ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡ ይህም የተጠሪ ጥያቄ ልከፍል የማይገባኝን ገንዘብ የከፈልኩ ስለሆነ ሊመለስልኝ ይገባል የሚል እንደሆነና

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በማድረግ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ገንዘቡን የተቀበለው ተጠሪ የጠየቀውን አገልግሎት ለመሥጠት የግድ መከፈል የነበረበት ክፍያ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ገንዘቡን የተቀበለው እምነትን የሚያጓድል ተግባራትን በመፈፀም አይደለም፡፡ የማይገባውን ክፍያ የከፈለ ሰው ገንዘቡን ከከፈለበት ቀን አንሥቶ ሕጋዊ ወለድ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው፣ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው እምነትን በሚያጓድል ሁኔታ ክፍያውን ተቀብሎት በሆነ ጊዜ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2164 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች ይዘት መሠረታዊ ዓላማና ተግባርና ተፈፃሚነት በአግባቡ ሣያገናዝብ፣ አመልካች ብር 38,034 (ሰላሣ ስምንት ሺ ሰላሣ አራት ብር) ወለድ ለተጠሪ መክፈል አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. ተጠሪ ገንዘቡ እንዲመለስለት ከጠየቀ በኋላ አመልካች ወዲያውኑ ባለመመለሱ፣ ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የዳኝነት ገንዘብ፣ ለጠበቃ አበልና ለቴምብር ቀረጥ ወጭ ያደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህንን ወጭ አመልካች እንዲሸፍን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 462 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ወለድ እንዲከፍል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰነው የውሣኔ ክፍል ብቻ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ወለድ ብር 38,034/ሰላሣ ስምንት ሺ ሰላሣ አራት ብር/ እንዲከፍል የሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 7,076 /ሰባት ሺ ሰባ ስድስት ብር/ ለቴምብር ቀረጥ የከፈለውን ብር 275 /ሁለት መቶ ሰባ አምስት ብር/ እና የጠበቃ አበል 22,000/ሃያ ሁለት ሺ ብር/ እንዲከፍል በማለት የሰጠው የውሣኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገብ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 91745

የካቲት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዳዊት አበበ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1. አንድነት ቁጥር 4 የጋራ መኖሪያ ቤት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

2. አቶ ካሚል ጀማል - አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች፣ አመልካች በመጀመሪያ ክርክሩን ለሽማግሌ ዳኞች ያላቀረበ በመሆኑ፣ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለንም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች የአንደኛው ተጠሪ አባል የነበረ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኖ ወርሃዊ መዋጮ መክፈል አቋርጠሀል በማለት አላግባብ ከአባልነት ያሰናበተኝ ስለሆነ የማህበር አባልነት መብቴ እንዳይሰረዝ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት በስር ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎች ተከሳሽ ሆነው የአመልካች ክስ በግልግል መታየት ያለበትና ለፍ/ቤት መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡
2. የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ጉዳዩን ለሽማግሌ ዳኞች ከሚያቀርብ ወይም ለሽማግሌ ዳኞች ቀርቦም ከሆነ ውጤቱን ጠብቆ በሕጉ መሰረት ይግባኝ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ከሚያቀርብ በስተቀር በቀጥታ ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በመጀመሪያ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች ሐምሌ 5 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች የክስ ምክንያት ያላግባብ ከማህበር አባልነቴ ተሰናበትኩ የሚል በመሆኑ በፍርድ ቤት የሚታይ እንጂ በሽማግሌ ዳኞች የሚታይ አይደለም፡፡ ክስ ከማቅረቤ በፊት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት አመልክቼ አመልካች አንድ፣ ተጠሪዎች አንድ የሽማግሌ ዳኛ ከመረጥን በኋላ ተጠሪዎች ሰብሳቢ ዳኛ መርጠዋል፡፡ ሰብሳቢው ዳኛም አድሏዊነት የሚታይበት በመሆኑ እንዲቀየር በማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት አመልክቼ ዳኛ መቀየር የማይችሉ መሆኑን ማህበራት ማደራጃ ስለገለፀልኝ ክስ ለፍርድ ቤት አቅርቤያለሁ፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 70922 መጋቢት 10 ቀን 2004 በሰጠው ውሳኔ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን የሰጠውን ውሳኔ ወደጎን በመተው የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጡት ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

4. ተጠሪዎች የስር ፍርድ ቤት ይህ ሰበር ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 73 የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራ ቀኛችንን ክርክር በመመርመር ውሳኔ እንዲሰጥበት በወሰነው መሰረት ተጠሪዎች ጉዳዩ በመጀመሪያ መታየት ያለበት በሽማግሌ ዳኞች ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 147/91 ድንጋጌዎች በመጥቀስ ያቀረብነውን መቃወሚያ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ተከራክረዋል፡፡አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ መጀመሪያ መቅረብ ያለበት ለሽማግሌ ዳኞች ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች የአንደኛው ተጠሪ አባል እንደነበርና ሁለተኛ ተጠሪ የማህበሩ ሊቀመንበር ሆኖ ሲሰራ ወርሃዊ ክፍያ አልከፈልክም በማለት ከአባልነት እንዲሰናበት አላግባብ በሌላ ሰው እንዲተካ ያደረገ በመሆኑ የማህበሩ አባል ሆኜ እንድቀጥል ይደረግልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔና በሰበር ከቀረበው ክርክር ተገንዝበናል፡፡ ይህም የሚያሳየው ክርክሩ የተነሳው በህብረት ሥራ ማህበሩና አላግባብ የማህበር አባልነት መብቴ ተቋርጧል በሚለው የቀድሞው የማህበሩ አባል በሆነው አሁን ግን አባልነቱ በአንደኛ ተጠሪ በመሰረዙ በአባልነት መጠቀስ ያለበት ወይም የሌለበት ስለመሆኑ ከፍሬ ጉዳይና ከህግ አንፃር ተመዝኖ ውሳኔ ሊሰጥበት ከሚገባው በአመልካች መካከል መሆኑን ነው፡፡ በአንድ ማህበር አቋም ስለ ስራው አካሄድ ወይም ስለስራው አፈፃፀም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወይም

በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ስም ክርክር የሚያቀርቡ ሰዎች በማህበሩና በማህበሩ አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ ለሽማግሌ ዳኞች ቀርቦ መታየት እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 147/96 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል። አመልካች አንደኛ ተጠሪ አላግባብ ከአባልነት ሰርዞኛል ከማለቱም በተጨማሪ የማህበሩ አመራር የሆነውን ሁለተኛ ተጠሪም ላይ ክስ አቅርቧል።

7. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 37 ተደንግጓል። የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተግባራዊ ተፈፃሚነትም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 37 ድንጋጌዎች ውጤታማነት በሚያጎለብትና በሚያጠናክር መንገድ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ሲታይ በህብረት ሥራ ማህበራትና በአባሎቻቸው ወይም በቀድሞ አባላቸው ወይም በህብረት ስራ ማህበር አባላት ወይም የቀድሞ አባላትና በማህበሩ አመራር መካከል የሚነሳ ክርክር በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው የሽምግልና ጉባኤ ነው። ከዚህ አንፃር ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 ሥልጣን ለተሰጠው ለሽምግልና የዳኝነት አካል ሳይቀርብ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው ዳኝነት ለማየትና ለመወሰን የማይችሉ መሆኑን የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 37፣ አንቀጽ 79(1) እና የአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 ድንጋጌዎች በማየት መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር አመልካች ጉዳዩ በቀጥታ በፍርድ ቤት ሊታይ ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

8. ሌላው አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 70922 መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ነው። ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 70922 ያየው መሰረታዊ ጭብጥ ተካሳሾች የቃል ክርክር በሚያሰሙበት ቀን ከሳሽ የነበረው (አመልካች) ባለመቅረቡና ተከሳሾች (ተጠሪዎች) በመካዳቸው መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ አመልካች በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት እንዲከፈት ሲጠይቅ በቀነ ቀጠሮው ያልቀረብከው በቂ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመስጣቸው ይህ ሰበር ችሎት ከሳሽ (አመልካች) በቀነ ቀጠሮው ያልቀረበው በበቂ ምክንያት በመሆኑ መዝገቡ ተከፍቶ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት የመለሰበት ነው። ጉዳዩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341(1) የተመለሰ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች (አመልካቾች) ያቀረቡትን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በመመርመር የሰጠው ብይን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244(1) ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው። የሥር ፍርድ ቤት ብይኑን የሰጠውም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር

መዝገብ ቁጥር 70922 የሰጠውን ውሳኔ ይዘትና ሕጋዊ ውጤት መሰረት በማድረግ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና መከራከሪያ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡

9. አመልካች የሽማግሌ ዳኞች በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በኩል ተሰይሞ የነበረ መሆኑንና ሰብሳቢው ዳኛ አድሏዊ በመሆኑ ለፍርድ ቤት ክስ አቀረብኩ የሚለው መከራከሪያ ህግን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡ የሽማግሌ ዳኞች ከተሰየሙ በኋላ አንድ ዳኛ እንዲለወጥ ማድረግ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከተከራከሪዎች አንደኛው ዳኛው እንዲለወጥ የሚጠይቅበትን ምክንያት በመዘርዘር በመጀመሪያ የሽማግሌ ዳኞቹ ፣የሽማግሌ ዳኞቹ እንቢተኛ ከሆኑ ለፍርድ ቤት ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3340 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3342 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ህጉን በመከተል ጥያቄያቸውን ሳያቀርቡ ክሱን በቀጥታ ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ የአመልካችን መከራከሪያ አልተቀበለውም፡፡

ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጉዳይ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49 መሰረት በተቋቋመ የሽማግሌ ዳኞች ቀርቦ ውሳኔ ማግኘት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
4. ይህ ውሳኔ አመልካች የሽማግሌ ዳኞች እንዲቋቋምለት ጥያቄውን ለሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ወይም ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 93171

ግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ወ/ሮ ሴቴ ከበደ - ተወካይ ወርቁ ከበደ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ አስናቁ ፋንታዬ - ተወካይ መኩሪያ መኮንን ቀረቡ

2. አቶ ጣፋጭ ተሾመ- መብታቸው ታልፏል

3.የጉባ ላፍቶ ወረዳ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

<u>**ፍርድ**</u>

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ጋር በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00951 ያላቸው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31 መሠረት ወደ ሀከፋ ወረዳ ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ያቀረቡትን የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት አመልካች አቤቱታውን ያቀረቡት ቁጥር 00951 የሆነው መዝገብ በውሣኔ ከተቋጨ በኂላ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 መሠረት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ የቀረበ ጥያቄም በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ እንዲሁም የክስ ይዛወርልኝ ጥይቄው በበቂ ምክንያት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ዳግም ዳኝነት እንዲታይ መዝገቡ ተከፍቶ በ22/05/2004 ዓ.ም. ትዕዛዝ መስጠቱ በተመለከተበት ሁኔታ ተጠሪዎች ለክስ ይዛወርልኝ አቤቱታው በሰጡት መልስ በወረዳው ፍ/ቤት የተከፈተ መዝገብ የለም በማለት የሰጡትን መልስ ተከትሎ የአመልካች አቤቱታ ሳይስተናገድ የተከፈተ መዝገብ የለም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ መብታቸው ከታለፈው 2ኛ ተጠሪ በስተቀር ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር

ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ ወረዳ ፍ/ቤት በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ ወደ ሌላ ወረዳ ፍ/ቤት ተዛውሮ እንዲታይ አንደኛው ወገን ሲያመለክት ተገቢ ምክንያቶች መኖራቸው ተረጋግጦ በክስ ይዛወርልኝ አቤቱታው እንደየሁኔታው አግባብነት ያለው ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 31 ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ለማቅረብ ጉዳዩ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆን ይኖርበታል፡፡በተያዘው ጉዳይ የዞኑ ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ላለመቀበል የሰጠው ዋነኛ ምክንያት ግራ ቀኙ በጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ክርክር ሲያደርጉበት የነበረው ቁጥሩ 00951 የሆነው መዝገብ በውሳኔ የተቋጨ መሆኑ እና መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 6 ድንጋጌ መሰረትም ሆነ በሌላ ምክንያት ያልተንቀሳቀሰ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ ተችሏል የሚል ሲሆን አመልካች ለክስ ይዛወርልኝ አቤቱታቸው በቂ ምክንያት አላቀረቡም የሚለው ነጥብበተጨማሪ ምክንያትነት በውሳኔው ይዘት ውስጥ የተገለጸ ከመሆኑ ውጪ ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔ ክፍል ውስጥ ያልተጠቀሰ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡የጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤትየቀረበለትን የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ለማየት መዝገቡ እንዲንቀሳቀስበ22/05/2004 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጥቷል መባሉን በተመለከተ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ተሰጠ የተባለውን ትዕዛዝ አመልካች በዞኑ ከ/ፍ/ቤት ስለማቅረባቸው የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታውን የተመለከተው የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት ተፈጻሚነት ባለው የውሳኔው ክፍል ላይ እንደገለጸው ጥያቄውን ሳይቀበል የቀረው የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በስር ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት በመሆኑ በመሰረቱ ይህ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔ አመልካች መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ የተደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታቸውን በሌላ መዝገብ እንደ አዲስ ከማቅረብ የሚከለክላቸው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በስር ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት በዞኑ ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበው በወረዳው ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ፋይል ባልተከፈተበት ወይም የቀድሞው መዝገብ ቁጥር 00951 ባልተንቀሳቀሰበት ሁኔታ ስለሆነ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም በማለት የሰሜን ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06041 በ12/03/2005 ዓ.ም. የሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 01-00728 በ17/10/2005 ዓ.ም.በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ውድቅ የተደረገው የወረዳው ፍ/ቤት መዝገብ መንቀሳቀሱን የሚያረጋግጥ ትዕዛዝ አያይዘው ባለማቅረባቸው በመሆኑ፡ቀደም ሲል ያቀረቡት አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ ተቀባይነት ማጣቱ የመዝገቡን መንቀሳቀስ የሚያረጋጥ ማስረጃ በማያያዝ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄያቸውን በሌላ መዝገብ በድጋሚ ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበቡ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 94302

ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ አንተነህ ድንበሩ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ፋርማ ብርብር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ወንድወሰን ተ/ማርያም ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሟጋችነት ሊቀርቡ የሚችሉበትን ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ክርክሩ በተጀመረበት በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበሩት በአቶ ብርሃኑ አማረ(በአሁኑ አመልካች) ላይ የመሰረተው ክስ በሌሉበት ተሰምቶ በተከሳሹ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን፣ተከሳሹም ክሱ በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው በተገቢው ስርዓት እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ክርክሩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት አቤቱታ ማቅረባቸውን፣አቤቱታውን ያቀረቡትም ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ሕንፃ ስራ ተቋራጭ በሚል ስም መሆኑን፣ከሳሹም የአቤቱታው ግልባጭ ደርሶት በሰጠው መልስ ክሱን ያቀረበውም ሆነ ውሳኔ ያሰጠው በአቶ ብርሃኑ አማረ ላይ እንጂ በብርሃኑ አማረ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ላይ ባለመሆኑ ከከሳሹ ጋር የውል ግንኙነት በሌለው እና ውሳኔ ባልተሰጠበት ድርጅት ነገረ ፈጅ አማካይነት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት መከራከሩን፣ፍ/ቤቱም ወደአቤቱታው ፍሬ ጉዳይ ሳይገባ የአቤቱታ አቀራረቡን ስነስርዓታዊነት ከመረመረ በኋላ ተከሳሹ ግለሰብ ነጋዴ መሆናቸውን፣ከተከሳሹ ስም ቀጥሎ የተመለከተው ሐረግም የሚያመለክተው ተከሳሹ በሕግ መሰረት የተቋቋመ ድርጅት መሆኑን ሳይሆን የግለሰብ ነጋዴውን የንግድ ስም መሆኑን፣ነገረ ፈጅ መወከል የሚችለው በሕግ አግባብ የተቋቋመ ድርጅት እንጂ ግለሰብ(የተፈጥሮ ሰው) አለመሆኑን ገልጾ ተከሳሽ የሕጉን መመዘኛ

ሳያሟሉ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መመለሱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት አቤቱታ የቀረበው አመልካችን ወክሎ ለመከራከር በሚችል ሰው አይደለም መባሉ የመዝገብ መዘጋት ውጤትን የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት የተዘጋጀ አቤቱታ ፈርመው በማቅረብ ስለአመልካቹ ሆነው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢነት ያለው ነው ወይስአይደለም?
2. ተገቢነት ያለው ነው ከተባለ መስፈርቱን አለማሟላታቸው የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምን ሊሆን ይገባል?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ጭብጦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪ ክሱን የመሰረተው እና ውሳኔ ያሰጠው የአመልካቹን ስም ብርሃኑ አማረ ገብረአብ ብሎ በመግለጽ ሲሆን አመልካች ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ስማቸውን የገለጹት ብርሃኑ አማረ ጠቅላላ የህንፃ ስራ ተቋራጭ በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ከአመልካቹ ስም ቀጥሎ "ጠቅላላ የህንፃ ስራ ተቋራጭ" በሚል የተመለከተው ሐረግ የተሞላው የአመልካቹን የንግድ ስራ ዘርፍ ወይም የንግድ ስም ለማመልከት ታስቦ ከመሆኑ ውጪ አመልካቹ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ተቋም መሆኑን ለማመላከት እንዳልሆነ በግራ ቀኙ ያልተካደ ጉዳይ ስለመሆኑ ከክርክራቸው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ቀጥሎ መታየት የሚገባው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት የአመልካቹ ነገረ ፈጅ ሆነው የቀረቡት ሰው በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር በተሟጋችነት ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዎች በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በመሰረቱ በማናቸውም ፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከራከር ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ወይም በፍ/ቤቱ የተሰጠ የተለየ ትዕዛዝ የሌለ በሆነ ጊዜ ባለጉዳዩ ራሱ

ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት፣በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.57 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ሕግ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አበል ሳይሰጣቸው ስለሌላ ሰው ሆነው በወኪልነት ወይም በነገረ ፈጅነት አቤቱታ ለማቅረብ፣ለመከራከር፣ለመሟገት እና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉት የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት ወይም አያት ስለመሆናቸው በቁጥር 58(1) ስር ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ ስለአመልካቹ በመሆን በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ሰው ከዋናው ባለጉዳይ ጋር በቁጥር 58(1) ከተመለከተው የዝምድና ግንኙነት መካከል አንዱን የሚያሟሉ ስለመሆኑ ወይም ዋናው ባለጉዳይ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር ከተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች መካከል በአንዱ የሚሸፈኑ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር ካለመኖሩም በላይ የውክልና ሰነዱም ይህንን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ሰው በክርክሩ ለመቀጠል የሚችሉበት ስነ-ስርዓታዊ አግባብ አይኖርም፡፡በመሆኑም ስለአመልካቹ ሆነው በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ከዋናው ባለጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 63 ድንጋጌ መሰረት በተገቢው ባለስልጣን ዘንድ ተረጋግጦ የተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መኖሩ ተረጋግጧል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት እንዲችሉ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 197(1) በተመለከተው መሰረት ተለዋጭ ትዕዛዝ እና ቀጠሮ መስጠት ይገባው የነበረ ከመሆኑ ውጪ አመልካች ሙሉ በሙሉ አቤቱታ እንዳላቀረቡ ወይም ጉዳዩን እንዳልተከታተሉ በመውሰድ መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበቱ የስነስርዓት ሕጉን አጠቃላይ ዓላማ እና መርህ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ትዕዛዝ በከፊል መሰረታዊ ሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ-ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም ሲል መዝገቡን ዘግቶ በማሰናበት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤትበመ.ቁ.100727 በ21/10/2005 ዓ.ምየሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.149227 በ26/11/2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተመለከተው ውሳኔ ውስጥ ስለአመልካቹ ሆነው የቀረቡት ተወካይ በአመልካቹ ስም በፍ/ቤት በተሟጋችነት ለመቆም በስነ-ስርዓት ሕጉ የሚጠየቀውን መስፈርት የሚያሟሉ ስላልሆኑ አመልካቹን ወክለው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ መዝገቡን ዘግቶ በማሰናበት የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. አመልካች ክርክሩን ራሳቸው ወይም በጠበቃ ወይም መስፈርቱን በሚያሟላ ተወካይ አማካይነት መከታተልና መምራት እንዲችሉ ፍ/ቤቱ ተለዋጭ ትዕዛዝ እና ቀጠሮ በመስጠት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሰረት ከቀረበለት አቤቱታ ጋር ተያይዞ የግራቀኙን ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሰረት ለፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌ/የመ/ደ/ ፍ/ቤት ይላክ፡፡
6. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 95033

መጋቢት 25 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ስንታየሁ ተፈሪ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ማርታ በቀለ - ጠበቃ ሽመልስ መንግስቱ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩየፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 43 ድንጋጌ መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን የፌዴራል የሚያደርገው የነበረ ሁኖ እያለ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ስልጣን ሳይኖረው ስረ ነገሩን አስተናግዶ ዳኝነት ከሰጠ በኂላ ይኼው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሠጠውን ዳኝነት ተቀብሎ ከወጣ በኂላ በሌሎች ጉዳዩን የፌዴራል ሊያደርጉ በማይችሉ ተከራካሪ ወገኞች መካከል የተሰጠው ውሳኔ ከመነሻውም የፌዴራል ጉዳይ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኗ ተጠሪ ላይ በጨኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም፡-የተጠሪ መኪና በአካላቸው ላይ ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪ በድምሩ ብር 269,266.44(ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) የአካል ጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ተጠሪም ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የጉዳት ካሳ መጠን ጥያቄው ተገቢነት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ከመከራከራቸውም በተጨማሪ በተጠሪ ላይ ጉዳት አደረሰ የተባለው መኪናቸው የመድን ሽፋን ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ያለው መሆኑን ጠቅሰው ይኼው አካል ወደ ክርክሩ እንዲገባ ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ከዚህም በኂላ ፍርድ ቤቱ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ክርክሩን ከመራ በኂላ ተጠሪንና ኡንሹራንስ ድርጅቱን ለክሱ ኃላፊ

አድርጎ ኢንሹራንስ ድርጅቱ የውል ግዴታ ስላለበትየሞራል ካሳን ጨምሮ ለአመልካች ብር 98,750.00 እንዲከፍል፣ተጠሪ ደግሞ ብር 12,460.00 እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ ግራ ቀኙ ቅር በመሰኘት በየፊናቸው ይግባኛቸውን ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ለአመልካች የጉዳት ካሳ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ ነው በማለት ከደመደመ በኋላ የጉዳት ካሳ መጠኑን በተመለከተ ግን የሥር ፍርድ ቤት ስህተት መፈፀሙን ገልፆ ለአመልካች ሊከፈል የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 143,016.44(አንድ መቶ አርባ ሶስት ሺህ አስራ ስድስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) መሆኑን ለይቶ ከወሰነ በኋላ መድን ሰጪ ድርጅት ሊጠየቅ የሚገባው ግን በመድን ውሉ መሰረት ነው በማለት ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ) ብቻ ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር ብቻ ከተከራከሩ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ዳኝነት ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ከዚህ በኋላ ደግሞ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ከአሁኑ አመልካች ጋር ብቻ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በወረዳው ፍርድ ቤት በጣልቃ ገብነት ገብቶ የተከራከረ ሲሆን ይህም ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርገውና የወረዳው ፍርድ ቤት ደግሞ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑ ውሳኔው ከመነሻውም ሕጋዊ አይደለም በሚል ምክንያት ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ባልቀረበበት ሁኔታ ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ ከመነሻውም በወረዳው ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አልነበረም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ለአመልካች የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ አላማ ያገናዘበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በይግባኝ ደረጃ በነበረው ክርክር የተሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ ከክርክሩ ውጪ መሆኑ መረጋገጡን፣አመልካችና ተጠሪ በክልሉ ነዋሪ ሁነው የክሱ መሰረትም የጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ ከእሱ ጋር ኃላፊነት ሊወስድ ወይም ሊካፈል የሚችል ሦስተኛ ወገን ወደ ክርክሩ እንዲገባለት እንዲታዘዝ ማመልከት እንደሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43(1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥያቄ መነሻ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተደረገ ተከራካሪ ወገን በክርክሩ ውስጥ ሊያነሳ የሚችለው የኃላፊነት እና የኃላፊነት መጠን አስመልክቶ የክርክሩ ዘንግ ከተከሳሽ፣ ከከሳሽ ወይንስ ከሁለቱም ወገን ጋር ሊሆን ይገባል? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በሁለት አቅጣጫ ምላሽ ሊያገኝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም የጣልቃ ገብ ኃላፊነት ምንጭ ውል ወይንስ ሕግ የሚለው በመሠረታዊ ሕግ ድንጋጌዎች የሚወሰን መሆኑ እና በሌላ በኩልም የክርክሩ አቀራረብ እና ይዘት በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተደነገገው አግባብ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ጉዳይ በወረዳው ፍርድ ቤት አዋሽ ኢንሹራንስ ጣልቃገብ ሁኖ የተከራከረ ሲሆን ጣልቃ ገብነት በፍትሓብሔር ስነስርዓት ሕጉአግባብ የተፈቀደ አንዱ የክርክሩ ተሳታፊ የሚሆንበትና ራሱን የቻለ መሰረታዊ አላማ ያለው፣ በስነ-ስርዓት ሕጉ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በ1958ቱ ፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ሕግ ወደ ክርክሩ ሊገባ የሚችልበት ስርዓት የተለያየ ቢሆንም ይህ ስርዓት አገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራል ስርዓትና በዚሁ ስርዓት ከተዘረጋው የፍርድቤቶች አደራጃጀት ጋር ተጣጥሞ በመታየት ስራ ላይ ሊውል የሚገባው መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም አንድን ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ብሎ ለመለየት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተቀመጠው መስፈርት ታይቶ የጉዳዩን የመዳኘት የስረነገር ስልጣንም ከዚሁ አንጻር መለየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 ስር አንድን ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች ተገልጸዋል፡፡ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ በፌዴራል መንግስት የተቋቋመና የተመዘገበ የልማት ድርጅት ሲሆን በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረነገረ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑ እና እስከ ብር 500,000 ግምት ያለው የገንዘብ ክርክር የማየት ስልጣን ደግሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 5(6) እና በአንቀጽ 14 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(4) እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት በአንቀጽ 75(3) በተመለከተው የስልጣን ውክልና መሰረት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ በክልሉ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ስለሆነም ከመነሻው ሲታይ በእርግጥ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን አልተሰጠውም፡፡እንዲሁም የሥረ ነገረ የስልጣን ጥያቄ በማናቸውም የክርክር ደረጃ የሚነሳና ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት ጭምር ማየት

የሚችለው ጉዳይ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡በመሆኑም የጩኮ የወረዳው ፍ/ቤት የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ወደ ክርክሩ መግባቱ ጉዳዩን ከስረ ነገር ስልጣኑ ውጪ የሚያደርገው መሆኑን ተገንዝቦ ክሱ ጣልቃ ገቡን ባካተተ ሁኔታ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቀርብ ዘንድ ጉዳዩን ዘግቶ ማሰናበት ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በማየት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ያልነበረ ሲሆን የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ቢሆን ጉዳዩን ከዚህ አንፃር በመመልከት በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር ይገባው ነበር፡፡ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ ለማድረግ በሕጉ መስኪያ የተቀመጠው ተከራካሪ ወገን በይግባኝ ደረጃ የክርክሩ ተሳታፊ የነበረ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ ረገድ በወረዳው ፍርድ ቤት የተፈጸመውን ስህተት ሳያርም መቅረቱ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ))የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ይሁን እንጂ አንድን ክርክር የፌዴራል ብሎ ለመውሰድ ያስችል የነበረው የአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ተቀብሎ በስርዓቱ መሰረት ክርክሩን በበላይ ፍርድ ቤቶች ያልቀጠለ ከመሆኑም በላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያደረባቸው የአሁኗ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርቡ በመልስ ሰጪነት የሰየሙት የአሁኑን አመልካች ብቻ ነው፡፡ተጠሪ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸው ተቀባይነት ሲያጣም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠሪነት የሰየሙት የአሁኑን አመልካች ብቻ እንጂ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያን ጭምር አይደለም፡፡ስለዚህ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነበረው የክርክር ደረጃ ጉዳዩ የፌዴራል መሆኑን የሚያስገነዝብ ተከራካሪ ወገን የነበረ ሲሆን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ በነበሩት የክርክሩ ሂደቶች ግን ይህ አካል ተሳታፊ አይደለም፡፡ይህም የሚያሳየው ጉዳዩን የፌዴራል ለማድረግ ይችል የነበረው የሕግ ምክንያት ቀሪ የሆነ መሆኑንና በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሚደረገው ክርክር ደግሞ በባሕርይው የፌዴራል ጉዳይ ለመሆን የሚያስችል የሕግ ምክንያት የሌለው መሆኑን ነው፡፡

የክርክሩ ሂደት የሚያስገነዝበው ከላይ የተገለጸውን ሁኔታ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ እልባት ማግኘት ያለበት ከስነ ስርዓት ሕጉ አላማ ጋር ተዛምዶና ታይቶ ሊሆን ይገባል፡፡የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ ዓላማ ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ ተገቢውን እልባት እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡በተለይም የሥነ - ሥርዓት ድንጋጌዎችን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እና በክርክሩ አመራር በህጉ በግልፅ ያልተሸፈኑትን ነገር ግን ፍ/ቤቱ በእራሱ በመሰለው እንዲወስን፣ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በሚያስችል አኳኋን በተደነገገ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ ከትክክለኛው ትርጉም ለመድረስና የተሰጠውንም ሥልጣን (Discretionary power) በአግባቡ ለመጠቀም ይህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ጉዳዩን ማየቱ ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይታመናል፡፡እንደሚታወቀው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረታዊ መብቶችንና ግዴታዎችን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል መሣሪያ በመሆኑ ይህንኑ ሂደት ውጤት እንዳይኖረው

የሚያደርግ የስነ ስርዓት ሕግ አተገባበር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው በተከራካሪ ወገን ማንነት የተነሳ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው ለማለት የሚቻልበት የሕግ ምክንያት ባለበት ሁኔታ ጉዳዩን ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት አይቶ ዳኝነት ከሰጠና በይግባኝ የክርክር ሂደትም ይኼው ሳይታረም ቀርቶ ጉዳዩን የፌዴራል ነው ብሎ ለማለት የሚያስችል ተከራካሪ ወገን በፍሬ ጉዳዩ የተሰጠውን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቀበል ከክርክሩ ውጪ ከሆነ እንዲሁም ክርክሩ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ ለማድረግ በማያስችሉ ተከራካሪ ወገኖች መካከል ከቀጠለ ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለው የስነ ስርዓት ሕግ ጥያቄን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ም" ሆነ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ግልጽ ምላሽ የማይሰጡበት በመሆኑ ምላሽ ማግኘት ያለበት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ መሰረታዊ አላማ አንፃር ሁኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ቀሪ የሆነውን የሕግ ምክንያት በመያዝ ጉዳዩ ከመነሻውም ስልጣን በሌለው ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው በማለት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተሰጠውን ዳኝነት መሻሩ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉን መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ መሻር እና በዋናው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አይቶ የመጨረሻ ዳኝነት እንዲሰጥበት ማድረጉ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ውሣኔ**</u>

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59864 ጥቅምት 29 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 59864 በመቀጠል ተጠሪ ለአመልካች ካሳ እንዲከፍሉ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪናኪሣራግራቀኙይቻቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.95934

ቀን 18/09/2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ አስፋው ንዳ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ እየሩሳሌም አየነው - ከጠበቃ እንዷለም በዕወቀቱ - ቀረቡ

2. አቶ መከተ ሲሳይ - ከጠበቃ ጌታው ተስፋዬ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ የሚስተናገድበትን የህግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ የቤት ባለቤትነት መፋለም ክስ ያቀረቡባቸው ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ተወካይነት ጠበቃ ተወክሎላቸው ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካችና ወ/ሮ ፀሐይ ቸበራ የተባሉ ግለሰብ ወደ ክርክሩ ለመግባት እንዲፈቀድላቸው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኑ ተጠሪዎች በጣልቃ እንግባ ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች የተከሳሽ ወኪል ሁነው ጠበቃ ወክለው ስለ ተከሳሹ ጥቅም ሁነው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው የስነ ስርዓት ህጉን አላማ ያልተከተለ መሆኑን ገልጸው የተቃወሟቸው ሲሆን ወ/ሮ ፀሐይ ቸበራ የተባሉትን ግለሰብ ደግሞ ለጣልቃ ልግባ ጥያቄአቸው ተገቢው ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የስር ተከሳሽ የሆኑት የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት አቶ ጌታሁን ተስፋዬ የተባሉትን ጠበቃ ወክለው ጠበቃው ቁጥሩ 3936 የሆነ ቤት የተከሳሽ የግል ቤት ሁኖ ቤቱን ተከሳሹ ለአሁኑ አመልካች የሸጡላቸውና ሰነዶቹም ቦታውን ለሚያስተዳድረው መሬት አስተዳደር ተመላሽ ሆኖ ቤቱን የአሁኑ አመልካች በእጃቸው

አድርገውና ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ አውጥተው የሚገለገሉበት መሆኑን በመጥቀስ የከሳሽ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከራቸውን፣የጣልቃገብነት ጥያቄው የአመልካቹ መብትና ጥቅም የሚነካበትን የህግ አግባብ የማያሳይ መሆኑን እንዲሁም አመልካች በተከሳሽነትም ሆነ በጣልቃ ገብነት በአንድ ጊዜ የሚከራከሩበት አግባብ የሌለ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የወ/ሮ ፀሐይ ቸበራ ጥያቄ ደግሞ በማስረጃ ያልተደገፈ ነው በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ አልተቀበላቸውም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች የተከሳሽ ወኪል መሆናቸው ስለወኪላቸው ጥቅምና ስለራሳቸው መብትና ጥቅም የሚያቀርቡትን ክርክር የማያግዳቸው ሁኖ እያለ ጉዳዩ በማስረጃ ሳይጣራ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም የተባለው ከህግ አግባብ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ከወኪላቸውና ለራሳቸው መብትና ጥቅም በአንድ ጊዜ ሊከራከሩ የሚችሉበት የህግ አግባብ የሌለ መሆኑን፣ አመልካች አለኝ የሚሉት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርም በሚመለከተው የአስተዳደር አካል ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ/ም የመከነ መሆኑን ዘርዝረውና ጥያቄያቸው ከስነ ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ ውጪ መሆኑን ጠቅሰው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው የሚነቀፍበት የህግ አግባብ የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካችን ደግፈው መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም ለሁለቱም ተጠሪዎች መልስ የመልስ መልሳቸውን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቷል፡፡

በመሰረቱ ጣልቃ ገብነት አንድ በፍትሃ ብሔር ክርክር ተካፋይ ያልነበረ ሰው የክርክሩ ተካፋይ የሚሆንበትና መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር ተገቢውን ክርክር እንዲያቀርብ በህጉ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሰው ወደ ክርከሩ የሚገባው በተከሳሽ ጠያቂነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊሆን እንደሚችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ በዚህ ድንጋጌ እንደተመለከተው ሌሎች ወገኖች በሚከራከሩበት ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሶስተኛ ወገን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር እንዲፈቀድለት ሊከራከር ይችላል፡፡ ሆኖም የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ለመሆን ሌሎች ስዎች በሚከራከሩበት ጉዳይ

የሚሰጠው ውሳኔ በቀጥታ መብቱንና ጥቅሙን የሚነካ መሆኑን የማስረዳት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ በሌላ አገላለፅ ጣልቃ ልግባ ጥያቄ ተቀባይነት እንዲኖረው ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ሰው መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ በቀጥታ የሚፈጸም መሆኑንና ሌላ አዲስ ክስ በማቅረብ ለማስቀረት የማይቻል መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ጣልቃ ገብ ልሁን በሚል ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ውሳኔው በቀጥታ መብቱንና ጥቅሙን የማይጎዳ ከሆነ እና አዲስ ክስ በማቅረብ ማስቀረት የሚቻልበት ሁኔታ ያለው ከሆነ ጥያቄው በህግ ፊት ተቀባይነት የሚያገኝበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን ነው፡፡

ጣልቃ ልግባ የሚለው ወገን በተከራካሪ ወገኖች መካከል ባለው ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ መብቱን በምን አግባብና መልኩ ሊነካ እንደሚችል ማሳየት እንደአለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41(2) ድንጋጌ ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካቹ ዝርዝር ምክንያቱን በማስፈር ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡ የጣልቃ ገብነቱ አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባውም ጊዜ ለማራዘም፣ ክርክሩን ለማጓተት ሊሆን እንደማይገባውም ከተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የስር ተከሳሽ ወኪል ሁነው ስለተከሳሹ ጥቅምና መብት ጠበቃ ወክለው ቤቱ የተከሳሹ የግል ቤትና ለአሁኑ አመልካች የተላለፈ መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ለራሳቸው ጥቅምና መብት ደግሞ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ አመልካች ስለተከሳሹ የወከሏቸው ጠበቃ ቤቱ የስር ተከሳሽ የግል ቤት መሆኑን ጠቅሰው ክርክር ከማቅረባቸው ውጪ ቤቱ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ነው ቢባል እንኳን በአመልካች እጅ የገባበት ሁኔታ ከስር ተከሳሽ ጋር ያደረጉትን ሽያጭ ህጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት ምክንያት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41(2) በተመለከተው አግባብ ዘርዝረው አላቀረቡም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በስር ከሳሽ እና ተከሳሽ መካከል በሚደረገው ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ ተከሳሽን የሚጠቅም ከሆነ የአሁኑን አመልካች ሊጎዳ ይችላል ተብሎ ሚታሰብበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ከስር ከሳሽ መብትና ጥቅም በተለየ ሁኔታ መብትና ጥቅማቸው ሊከበር የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩን ዘርዝረው የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸውን ስለማቅረባቸው የክርክሩ ሂደት አያሳይምና፡፡ አመልካች የመብታቸው ምንጭ የስር ተከሳሽ መሆናቸውን፤ የወኪላቸውን መብትና ጥቅም ከራሳቸው መብትና ጥቅም ጋር አዛምደው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ማቅረባቸው ክርክሩን ለማጓተት ነው ተብሎ ከሚታሰብ ውጪ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይደለም፡፡ እንዲህ አይነት የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ደግሞ የጣልቃ ልግባ አቤቱታዎች የሚስተናገዱበትን ስርዓት ከዘረጋው ስነ ስርዓታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከፍትሐብሔር ስርዓት ህጉ መሰረታዊ አላማ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ተከሳሽ ለነበሩት ግልሰብ ወኪል ሁነው ጠበቃ ወክለው ጠበቃውም አከራካሪው ቤት የስር ተከሳሽና ለአመልካች የተላለፈ መሆኑን ጠቅሰው ሲከራከሩ ቆይተው ለአመልካች መብትና ጥቅም ማስከበር ሲባል ነው በማለት የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ማቅረባቸው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 41 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻለ ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.74380 ሚያዝያ 22 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቀ.137867 ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

በ23/04/2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.92903

ሚያዝያ 24 ቀን፺.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ስላስ ረዳ - ጠበቃ ጠጅነሽ ሰይፉ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ለተሚካኤል ገ/ሐዋሪያት
2. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ
} አልቀረቡም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ከንግድ መደብር ኪራይ ጋር ተያይዞ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የሰበር አመልካች ከሳሽ ሆነው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ አመልካች በ14/06/2005 ዓ/ም በተፃፈ ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ፡- አመልካች ለንግድ ቤትነት ለመገልገል ከ 2ኛ ተጠሪ ተከራይተው በነበረው ቤት ላይ የፀጉር ስራ ንግድ ፈቃድ በማውጣትና ለስራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮችንም ካሟላ በኂላ የንግድ ድርጅቱን ከነፈቃዱና ሙሉ እቃው ለ1ኛ ተጠሪ በወር ብር 4,000 ኪራይ ያካራዩ መሆኑን ጠቅሰው ሆኖም ግን 1ኛ ተጠሪ ከህግ አግባብ ውጭ በንግድ ድርጅቴ ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል አቋቁሜያለሁ በማለት ድርጅቴን ለማስረከብ ፈቃደኛ ስላልሆነ ተጠሪዎች ከህግ ውጭ በድርጅቴ ላይ ያደረጉት ኪራይ ውል ፈርሶ 1ኛ ተጠሪ ድርጅቱን ከነ ሙሉ እቃው ለአመልካች እንዲያስረክብ እንዲወሰንላቸው እና እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ከመስከረም 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያልተከፈለ የድርጅቱን ውዝፍ ኪራይ ገንዘብ ብር 24,000 መከፈል ከነበረበት ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ጉዳይን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይተው የነበረውን ንግድ ቤት በኪራይ ውሉ በገቡት ግዴታ መሰረት አስቀድመው አከራይን (2ኛ ተጠሪን) ሳያሳውቁ ለ1ኛ ተጠሪ አሳልፈው ማከራየታቸው የኪራይ ውሉን ስምምነት የጣሱ ስለሆነ እና 2ኛ ተጠሪም ይሄንኑ ተከትሎ ከአመልካች ጋር የነበረውን የቤቱን ኪራይ ውል አቋርጦ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ማከራየቱ መብቱና ተገቢ ስለሆነ ይህ በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው ኪራይ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ አልተቀበልኩም በማለት ጥያቄውን ወድቅ በማድረግ አልፏል፡፡ የንግድ መደብሩን ኪራይ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ የሚገደዱት ኪራይ በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው ኪራይ ውል እስከተቋረጠበት (28/02/2004 ዓ/ም) ድረስ ያለው ኪራይ ብቻ ስለሆነ በዚህ መሰረት የመስከረምና ጥቅምት ወር 2004 ዓ/ም የ2 ወራት ኪራይ ክፍያ ብር 8,000 ውሳኔ ከተሰጠበት ከ 15/06/04 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታዋን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አሳልፈው ለ1ኛ ተጠሪ ያከራዩት ንግድ ቤቱን ሳይሆን ንግድ መደብር መሆኑን ከገለፀ በኋላ የንግድ መደብሩን ደግሞ በንግድ ህጉ ቁ.145(1) እና ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ.31264 አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የአከራዩን ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ ማከራየት ስለሚችልና በዚህም መሰረት አመልካች ንግድ ድርጅቱን 2ኛ ተጠሪ ሳያሳውቁ ለ1ኛ ተጠሪ ማከራየታቸው ህጉን መሰረት ተደረጎ እንጂ ህጉን ያልተከተለ አድራጎት ባለመሆኑ በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የቤቱ ኪራይ ውል መቋረጡ በአግባቡ ስላልሆነ ውሉ ፀንቶ ሊቀጥል ይገባል በማለት ከወሰነ በኋላ በሌላ በኩል ግን በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው የኪራይ ውል ህጋዊ ባለመሆኑ ሊፈርስ ይገባል በማለትና እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ንግድ ድርጅቱን ቀድሞ በተረከበበት ሁኔታ መልሰው ለአመልካች ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ በከፊል በመቃወም ሲሆን ቅሬታ ነጥቡም ባጭሩ፡- 1ኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በወር ብር 4000 ተከራይተው የነበሩ መሆኑን ሳይክዱና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም በበኩሉ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር 1ኛ ተጠሪ ንግድ ድርጅቱን ከነ እቃው ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ከወሰነ በኋላ ኪራዩን በተመለከተ ግን ውሳኔ ሳይሰጥበት በዝምታ ማለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ውሳኔው ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም ተመርምሮ አመልካች 1ኛ ተጠሪ የተከራዩትን የንግድ ድርጅት ኪራይ ይክፈሉኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በዝምታ

የመታለፋን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙም ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው በጉዳዩ ላይ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የንግድ ድርጅቱን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ስር ፍ/ቤት እንዲከፍላቸው ዳኝነት የጠየቁት ብር 24,000 ብቻ መሆኑን ፤ ከዚህ ውስጥም የመስከረምና ጥቅምት 2004 ዓ/ም የ2 ወራት የድርጅቱ ኪራይ ብር 8,000 በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለአመልካች መወሰኑን፤ የድርጅቱ ኪራይ መጠንም በወር ብር 4,000 መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪም የኪራይ መጠኑ ብር 4,000 አለመሆኑን ክዶ አለመከራከሩን፤ አመልካችም የስር ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይከፈላቸው ከቀረው የድርጅቱ ኪራይ ክፍያን ጨምሮ አለኝ ያሉትን ቅሬታቸውን በሙሉ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን የንግድ መደብሩን ልረከብ ጥያቄን አስመልክቶ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ክፍል ለውጦ አመልካች ድርጅቱን እንዲረከቡ በማለት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ሆኖም ግን ለአመልካች ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ወድቅ ተደርጎ የታለፈውን ኪራይ በተመለከተ ምንም አይነት ዳኝነት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ሳይሰጥበት በዝምታ መታለፉን ነው፡፡

በመሰረቱ በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል ተደርጎ የነበረው የድርጅቱ ኪራይ ውል ህጋዊና ተገቢ ነው በማለት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ተወስኗል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተጠሪዎች መካከል በቤቱ ላይ የተደረገው ኪራይ ውልም ህገ-ወጥ ነው ተብሎ እንዲፈርስ ከመደረጉም በላይ 1ኛ ተጠሪም ድርጅቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ጭምር ተወስኗል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በድርጅቱ ኪራይ ውል መሰረት እንዲከፍሉ የተጠየቁትን ቀሪ የድርጅቱን ኪራይ ክፍያ በተመለከተ ሊከፍሉ የማይገባበትን ህጋዊ የሆነ ክርክር ባላቀረብበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ቀሪው ኪራይ ለአመልካች እንዲከፈል ሳይወስን በዝምታ ማለፉ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182(1) እና 348(1) ድንጋጌዎች ይዘት አኳያ የውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላገኘን ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.128192 በ30/10/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች ስር ፍ/ቤት እንዲከፈላቸው ዳኝነት ከጠየቁት ብር 24,000 የድርጅቱ ኪራይ ውስጥ የመሰከረምና ጥቅምት 2004 ዓ/ም ብር 8,000 በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተወሰነላቸው ሲሆን ቀሪው ብር 16,000ም ሊከፈላቸው የማይገባበት በቂና ህጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ይሄው ገንዘብ ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ከ 24/08/06 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡

3. የሰበር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

- ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና እንዲሁም ፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በትዕዛዝ የቀረቡት መዝገቦች ይመለሱ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
- በተሻሻለው ውሳኔ መሰረት ይፈፀም ዘንድ የውሳኔ ግልባጩ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

# የንግድ ህግ

የሰ/መ/ቁ 90434

ሰኔ 06 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሪታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሉሃና አንጂነሪግ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ፍሬው ካሳሁን ቀረበ

ተጠሪ፡- ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ኃ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ሰለሞን በዳኔ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረው በተጠሪ ከሣሽነት አመልካች በቼክ ቁጥር C-1469751 ብር 462,518.04 እንዲከፈለው ከሰጠ በኃላ ክፍያው እንዳይፈጸም አመልካቹ ለባንኩ ትእዛዝ ሰጥቶ እንዲታገድ ከመደረጉም በላይ ገንዘቡን አመልካቹ ሊከፍል ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ገንዘቡ በአመልካች እንዲከፈለው ይወሰን ዘንድ በተፋጠነ ስነ ስርዓት በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡

አመልካች እንዲከላከል ተፈቅዶለት ባቀረበው መልስም ቼኩ በተጠሪ እጅ ሊገባ የቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈፀመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት መሰረት አድርጎ ለሚፈጸመው ቅድመ ክፍያ ለዋስትና የተሰጠ መሆኑን ፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የስራ ውል ስምምነት ሲፈጸም አስቀድሞ እዳ አለብኝ ተብሎ የሚሰጥም ሆነ የሚገባ የውል ስምምነት የሌለ መሆኑን ፣ ቼኩ በተጠሪ እጅ የገባው ለተባለው አላማ ስለሆነ ተጠሪ እንዲፈጸምለት ለባንኩም ሆነ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄው ከማቅረቡ በፊት በውሉ አግባብ አመልካች ያልተወጣውን ግዴታ አረጋግጦ መሆን ሲገባው በቀጥታ በቼኩ ላይ የተገለጸውን ክፍያ እንዲፈጸምለት የዳኝነት ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ፣ ቼኩ የተሰጠው ለተባለው ዓላማ ወይም በተጠሪና በአመልካች መካከል በነበረው የግል ግንኙነት ከሆነ ደግሞ ቼኩ እንደቀረበ የሚከፈል ሰነድ ሳይሆን ተራ ሰነድ መሆኑን ፣ አመልካች ወደ ስራው ገብቶ ስራውን እያከናወነ እያለ ያልታሰበ ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ

በመድረሱ ንብረቶች በመጎዳታቸው ምክንያት ለተጠሪ ቅድመ ሁኔታዎችን ሰጥቶ ስራውን በወቅቱ ለማቋረጥ መገደዱን ፣ ነገር ግን ተጠሪ ባለመስማማት ውሉን በራሱ ጊዜ ማቋረጡን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ለክሱ ኃላፊ ያደረገው ሲሆን የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተም በክሱ ላይ የገለጸውንና ሌሎች ወጪዎችን እንዲሁም የኮሚሽን ክፍያ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች ቼክ ለኮንስትራክሽን ስራ ለመያዣነት የተሰጠ መሆኑን ሳይገነዘቡና የተሰራ ስራ ስለመኖሩ እንዲሁም ተጠሪም ለተሰራው ስራ ከስራው ባለቤት ክፍያ መውሰዱ እየታወቀ ይህንኑ አልፈው አመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የኮንስትራክሽን ስራ ሁኔታ ሳይጣራ ቼኩ ለተጠሪ ለክፍያ መቅረብ አልነበረበትም በማለት ያቀረበው ክርክር ታልፎ በበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያው እንዲፈጸም የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ በዚህ አግባብ ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ቼክ የንግድ ወረቀት ከሚባሉ አንዱ ሲሆን እንደቀረበ የሚከፈል ፣ በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለው ትእዛዝ የሚሰጥበት ፣ ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ህ/ቁ.732፣827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ በቼክ ገንዘብ ለመክፈል አውጭው በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተቀመጠ የቼኩን ዋጋ አጣርቶ የሚከፈል ፣ በቂ ስንቅ /ገንዘብ/ ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑም እርግጠኛ መሆን እንዳለበት የን/ህ/ቁ. 830(2) ድንጋጌ ያስቀምጣል፡፡ ይህንኑ በህግ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ የቀረ አውጪ በቼኩ ላይ የተጻፈውን ገንዘብ /እዳ/ ለአምጪው እንዲከፍል የሚገደድ ስለመሆኑ የህጉ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ዕዳ ከፋዩ /አውጪው/ ግዴታውን እንዲወጣ የማይገደደው በህጉ የተቀመጡትን መቃሚያዎች /መከራከሪያ ነጥቦችን/ በአግባቡ ሲያስረዳ ነው፡፡ በህጉ እዳ ከፋዩ በአምጪው ላይ ሊያቀርብ ይችላል ተብለው የተቀመጡት መቃወሚያዎች በን/ህ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ እነዚህም፡- በሁለቱ

የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ ፣ በሰነድ አጻጻፍ ፎርምና በሰነዱ ላይ በተጻፉ ቃሎች ፣ እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሰራ ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ስልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎችን ባለመሟላታቸው የሚነሱ መቃወሚያዎችና አምጭው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው መሆን ስለመሆናቸው የሚያሳዩ እንደሆነ ህጉ አስቀምጧል፡፡

እንግዲህ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል እንደመሆኑ መጠን አውጪው ለቼኩ መውጣት ምክንያት የሆነውን ነገር የማስረዳት እና የማስተባበል ሸክም ያለበት ስለመሆኑ ከህጉ ቅርፅ ፣ ይዘትና መንፈስ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በቼኩ የተጻፈውን ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም የሚለው አውጪው ከላይ በን/ህ/ቁጥር 717 ስር የተመለከተቱትን ሁኔታዎች በበቂ እና አሳማኝ መንገድ ማስረዳት ግዴታውን ሲወጣ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኮንስትራክሽን ስራን በተመለከተ ውል መኖሩ አልተካደም፡፡ ቼኩም ለዚህ ምክንያት የተሰጠ መሆኑን አመልካች ክርክርና ማስረጃ ያቀረበበት ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች በውሉ መሰረት የሰራው ስራ መኖር፣ የስራው መጠን ምን ያህል እንደሆነና በዚሁ ስራ መነሻ ተጠሪ ከስራው ባለቤት ክፍያ ያገኘ መሆን ያለመሆኑ በዚሁ መዝገብ ክርክር ተደርጎ በማስረጃ የማይነጥርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

የአመልካች እና የተጠሪ ግንኙነት የተመሰረተው በመሃከላቸው በተደረገው የግንባታ ውል ላይ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል ክርክር ቀርቦ በተጠሪ እስካልተካደ ድረስ ተጠሪ በተፋጠነ ስነ ስርዓት ታይቶ ይወሰንለት ዘንድ ላቀረበው ክስ መሰረት ያደረገው ቼክ ቁጥር C-1469751 በግንባታ ውሉ መነሻ የተሰጠ ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት መብቱ በሌላ መዝገብ ሳይሆን በዚህ መዝገብ የማይታይበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች  እነዚህን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ክሱን ይከላከል ዘንድ እንዲፈቀድለት ያቀረበው ጥያቄ ፍ/ቤቱ ከተቀበለው በኃላ የመከላከያ መልሱንና እና ማስረጃዎችን ሊታይለት ይገባል እንጂ በክሱ ቼክ በመጠቀሱ ብቻ ጉዳዩ ቼክን በሚመለከቱ የንግድ ህግ ድንጋጌዎች አንጻር ብቻ በማየት በቼኩ የተመለከተው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፈል ለመወሰን የሚያስገድድ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች አጥብቆ የተከራከረው ቼኩ ለተጠሪ የተሰጠው አመልካች በኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ስምምነት መሰረት በውሉ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ፣ በውሉ ለተመለከተው የቅድሚያ ክፍያ በተወሰነ መጠን በመውሰዱ ለዚሁ ለመያዣነት እንዲሆን ነው የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት ነው፡፡ ለዚህ የአመልካች ክርክር ግራ ቀኙ መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም ተፈረመ የተባለው የግንባታ የውል ስምምነት ቀርቦ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት ቀርቦ ይዘቱና መንፈሱ ሊታይና የቼኩን መሰጠት ምክንያት ማጣራት የሚያስችል ነው፡፡ ተጠሪ ቼኩ የተሰጠው በቼክነቱ

እንዲከፈል እንጂ ሁኔታ ላይ /ከአመልካች የውል ግዴታ መወጣት ጋር እየታየ የሚከፈል አይደለም/ የተመሰረተው አይደለም የሚል ክርክር በማንሳት በአመልካች በኩል እንዲፈጸም በውሉ የተቀመጠውን ግዴታ አመልካቹ ያለመወጣቱን እንዲያስረዳ አልተደረገም፡፡ የአመልካች ክርክር የግንባታ ውል ስምምነቱ እና የሲቪል ስራ ፕሮጀክቶች ግንባታ መደበኛ ሁኔታዎች /fidic/ ጋርም ተዛምዶ የማይታይበት ምክንያት የሌለ ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከእነዚህ ሁኔታዎች አንጻር ያጣሩት አግባብ ያለመኖሩን ከክርክር ሂደት ተገንዝበናል፡፡

በንግድ ህግ ቁ.717/1/ እንደተመለከተው ዕዳ ከፋዩ ሰነዱን /ቼኩን/ በያዘው ሰው ላይ በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱት ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይም ከላይ እንደተገለፀው የግንባታ ውሉ የአመልካች እና የተጠሪ የግል ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡

የግንባታ ውል ስምምነት ደግሞ ሁለቱም ወገኖች በውሉ ያገኙትን መብት እና ከውሉ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ የያዘ ሰነድ ስለሆነ የገንዘብ ክፍያ የሚጠይቀው ተዋዋይ ወገን ገንዘቡን ያገኘ ዘንድ የበኩሉን ግዴታ ሊወጣ ይገባል፡፡ ግራ ቀኙ በውሉ ያላቸው ግዴታ ታይቶና ግዴታውን የተወጣ ወገን መኖር ያለመኖሩ በማስረጃ ከነጠረ በኃላ የቼኩ ክፍያ እልባት ይገባል እንጂ ይኼው ታልፎ ተጠሪ ቼክን መሰረት አድርጎ ክስ በማቅረቡ ብቻ የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ሳይመዘን ውድቅ የሚሆንበትን አግባብ የን/ህ/ቁጥር 717፣732፣827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አያሳይም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ለቼኩ መሰጠት መሰረት የሆነውን ውል እና ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት ያለውን ህግ ሳይመለከቱና በተገቢው የክርክር አመራር ስርዓት ፍሬ ነገሩን ሳያጣሩ ዳኝነት መስጠታቸው ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡፡

አመልካች ለመከላከል ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ በኂላ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን ግንኙነት እና ቼኩ የተወሰደበትን ምክንያት መሰረት አድርጎ ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሆኖ ለገንዘብ ጥያቄው ኃላፊ መባሉ የአመልካች ማስረጃዎችን የስር ፍርድ ቤት ሳይሰማና የሰነድ ማስረጃዎችንም በሕጉ አግባብ ዝርዝር ምክንያት ሳይሰጥ ታልፎ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሕግ አግባብ የቀረበን ክርክርና የተቆጠረ ማስረጃ ደግሞ ያለ ሕጋዊ ምክንያት ሳይሰማና ሳይመዘን በዝምታ የሚታለፍበት፣ አግባብነት የሌለው ሕግ ተጠቅሶ ውድቅ የሚሆንበት፣ የሰነድ ማስረጃው ቀርቦ ደግሞ ይዘቱ ሳይታይ በደፈናው ውድቅ የሚደረግበት የማስረጃ አቀባበል እና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትና ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች አግባብነት ባላቸውና በሕጉ አግባብ በተቆጠሩ የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነትም ከሚመለከታቸው አካላት በሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው መንገድ ሳይጣሩ ዳኝነት መስጠት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የማይቀበለው ጉዳይ ሲሆን የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ

የሚሰጥ ዳኝነት ደግሞ በውጤቱ የተከራከሪ ወገኖችን የመደመጥ መብት እጅጉን የሚጎዳ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ሲጠቃለልም፡-

1. በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈጸመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት ስለ አከራካሪው ቼክ የሚያሳየው ነጥብ ምን እንደሆነ፣
2. ቼኩ ከዚሁ ውል በመነጨ ስምምነት ለተጠሪ በአመልካች የተሰጠ ከሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል መስከረም 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈፀመ የኮንስትራክሽን ንዑስ ስራ ተቋራጭነት ውል ስምምነት መሰረት አመልካች የሰራው ስራ መኖር ያለመኖር፣
3. ውሉ የተቋረጠበት ምክንያትና ውሉን ያቋረጠው ወገን የትኛው እንደሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምን እንደሆነ፣
4. ተጠሪ በአመልካች በተሰራው ንዑስ የኮንስትራክሽን ስራ ከስራው ባለቤት ያገኘው ክፍያ መኖር ያለመኖሩና ካለም የክፍያው መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ ሌሎች ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በአመልካች በተቆጠሩት ማስረጃዎች፣ ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 136 በሚመድባቸው ባለሙያዎች (በተለይ በአመልካች የተሰራው ስራ መኖር ያለመኖርና ተሰርቶ ከሆነም የስራው ዋጋ መጠን)፣ አመልካች ጉዳዩን ያስረዳሉ በማለት ያቀረቧቸው ሰነዶች ትክክለኛ መሆናቸውን፣ ይዘታቸው ምንን እንደሚገልጽና ለጉዳዩ ያላቸውን የማስረጃነት ዋጋ በዝርዝር በመመልከት አስፈላጊ ሲሆን ሌሎች ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ፍርድ ቤቱ ራሱ በማስቀረብ ጭምር ጉዳዩን በተገቢው መንገድ አጣርቶና የፍሬ ነገሩን ክርክር አሟልቶ፣ በሕጉ የተመለከተውን የፍርድ አፃፃፍ ስርዓት በመከተል ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ስነ ስርዓታዊ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 200800 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 117557 ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 200800 ክርክሩን እንዲቀጥል በማድረግ በፍርድ ሐተታው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ብቻ የአመልካችን ማስረጃዎችን በመስማትና በተገቢው መንገድ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በሚያስቀርባቸው ማስረጃዎች ጭምር በማጣራት ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

# አሰሪና ሰራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 90570

ጥር 27 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የአቶ ፍፁም አስታጥቄ ወኪል አቶ ታምራት አስታጥቄ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የተቀናጀ የቤተሰብ አገልግሎት ድርጅት የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስራ ክርክር ችሎት በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ በአመልካች የቀረበው የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- ከሣሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በፕሮጄክት አስተባባሪነት የስራ መደብ ላይ በ1/3/2001 ዓ.ም ተቀጥረው እያገለገሉ ሳሉ ተከሳሹ ድርጅት ያለአግባብ የስራ ውላቸውን ያቋረጡ መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈፀምላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ተከሳሹም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስ የስራ ውሉ በተከሳሽ አነሳሽነት ሊቋረጥ የቻለው በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ሆነው ድጋፍ የሚደረግላቸውንና በወሲብ ጥቃት ምክንያት ለስነ-ልቦና ቀውስ የተጋለጡ ህፃናትን ከሳሽ ያለተከሳሽ ድርጅት እውቅናና ፈቃድ በእንግዶች እንዲጉበኙ፣ እንዲጨፍሩ እና ፎቶግራፍ በእንግዶች እንዲነሱ በማድረጉና ይህ ድርጊትም ከከሳሹ የስራ ሙያ ውጭ ከመሆኑም በላይ የድርጅቱን የስራ ደንብም የጣሰ በመሆኑ ስንብቱ ህጉን ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ ለከሳሹ የሚፈፀም ክፍያ የለም ሲሉ በመከራከር መልሱን ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ቃል ሰምቶ ጉዳዩንም ከቀረበው ማስረጃ እና ህጉ ጋር አገናዝቦ ተመልክቶ መመርመሩን ከገለፀ በኋላ ምንም እንኳ ጉብኝቱን ያለተከሳሹ እውቅና የፈቀዱ ስለመሆኑ እና እንዲሁም እነኝህ የወሲባዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑት ህፃናትን ያለጥንቃቄ እንዲጉበኙ ማድረግ፣

ከእንግዶቹ ጋር እንዲጨፍሩ ማድረግ እና ፎቶ ግራፍ እንዲነሱ ማድረግ በህፃናቱ ስነ-ልቦና ጤንነት ጋር በተያያዘ ችግር የሚፈጥርባቸው ስለመሆኑ በባለሙያ ምስክርነት ቃል ጭምር የተረጋገጠ ቢሆንም ሆኖም ግን ከሳሹ ጉብኝቱን የፈቀዱት ህፃናቱ ከእንግዶቹ ጋር እንዲጨፍሩና ፎቶግራፍ እንዲነሱ ጭምር ስለመሆኑ ባለመረጋገጡ እና እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ ድርጊቱን በህፃናቱ ህይወት ላይ ጉዳት እንዲከተል ሆነ ብሎ የፈፀመው ነው ለማለት ስለማይቻል እና በአጠቃላይ የከሳሽ ስራ ውል የተቋረጠው በህጉ መሠረት ባለመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ የካሳ ክፍያ ብር 33,030 /ሠላሳ ሦስት ሺህ ሠላሳ ብር/፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 11,010/አሥራ አንድ ሺህ አሥር ብር/ እና ከወጪና ኪሳራ ብር 400/አራት መቶ ብር/ ጋር ተከሳሹ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ከድርጅቱ እውቅና ውጭ የወሲብ ተጠቂ የሆኑት ህፃናት በእንግዶች እንዲጐበኙ ማድረጉ መረጋገጡን በመግለፅና ይህ በአመልካች የተፈፀመው ድርጊትም በድርጅቱ የተቀመጠውን የአሰራር ደንብ መጣስ ብቻ ሳይሆን ሙያው የሚጠይቀውን ልዩ ጥንቃቄንም አለማድረጉን የሚያስረዳ በመሆኑ እና ጥፋቱም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሠ) ስር የሚያስጠይቅ ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ይሄንኑ ባለመገንዘብ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት መወሰኑ አለአግባብ ነው ሲል የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1/ መሠረት በመሻር ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይፅናልኝ የሚል ይዘት ያለው አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል  በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የግራ ቀኙን የሰበር ፅሑፍ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የተጠሪ ድርጅት ከተቋቋመበት ዋና ዋና አላማዎች መካከል አንዱ እነዚሁኑ የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸውን ህፃናት መንከባከብ እና በጥቃቱ ምክንያት ከደረሰባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ እንዲድኑ እርዳታ ማድረግ መሆኑን፣ አመልካችም ይሄንኑ አላማ ለማስፈፀም ተቀጥሮ እነዚሁ ህፃናት ተጠልለው የሚገኙበት ማዕከል ኘሮጀክት አስተባባሪ መሆኑን፣ በዚህም መሠረት

የህፃናቱን ጤንነት ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብ ከስነ-ልቦና ቀውሱ እንዲያገግሙ የበኩሉን ሚና መወጣት ሚስጥራቸውን መጠበቅ እና እንዲጠበቅ ወይም እንዳይጋለጥ ለማድረግ በስራ ውሉ እና በድርጅቱ አሰራር ስርዓት መሠረት ከፍተኛ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን፣ ሆኖም ግን አመልካች ከተጠሪ ድርጅት እውቅናና ፈቃድ ውጭ ህፃናቱ ያለጥንቃቄ በእንግዶች እንዲጐበኙ፣ እንዲጨፍሩ እና በእንግዶቹ ፎቶግራፍ እንዲነሱ ማድረጉን በሰውና ሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን፣ ይህ ድርጊትም የህፃናቱ ሚስጥር እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑንና ሚስጥራቸው በተጋለጠ ቁጥር ደግሞ በወሲብ ጥቃቱ ምክንያት የደረሰባቸውን የስነ-ልቦና ቀውስ በማባባስ ከፍተኛ የጤንነት ችግር ውስጥ እንዲገቡና የወደፊት ማህበራዊ ህይወታቸውም እንዲጐዳ የሚያደርግ ስለመሆኑ በተጠሪ ድርጅት በኩል ተቆጥረው በስር ፍ/ቤት ቀርበው በተሰሙት የባለሙያዎች ምስክርነት ቃል መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሠራተኛ ደግሞ በስራ ውሉ እና በስራ ደንቡ መሠረት በአሰሪ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመፈፀም ግዴታ እንዳለበት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 13(2) ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የዚሁኑ አዋጅ ድንጋጌዎችን፣ የህብረት ስምምነትን፣ የስራ ደንብ እና በህግ መሠረት የሚተላለፉ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታም እንዳለበት በንዑስ አንቀጽ 7 ስር ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች እነዚህ የወሲብ ተጠቂ የሆኑትን ህፃናት ጤንነት የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ ከደረሰባቸው የስነ-ልቦና ቀውስ እንዲድኑ የበኩሉን እገዛ ማድረግ፣ ሚስጥራቸውንም የመጠበቅ እና እንዳይጋለጥ የማድረግ ግዴታ የተጣለበት ሆኖ ሳለ ያለድርጅቱ ፈቃድና እውቅና ውጭ ህፃናቱ ጥንቃቄ በጐደለ ሁኔታ በውጭ እንግዶች እንዲጐበኙ እና ፎቶግራፍም በእንግዶች እንዲነሱ በመፍቀድ ሚስጥራቸው እንዲጋለጥ ማድረጉ በአዋጁ አንቀጽ 13(2) እና 13(7) መሠረት በስራ ውሉ እና በድርጅቱ የአሠራር ስርዓት መሠረት እንዲፈፀም የተጣለበትን ግዴታ አለመወጣቱንና መጣሱን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ድርጊትም በመካከላቸው የተደረገውን የስራ ውሉን መሠረታዊ ስምምነት የሚጥስ በመሆኑ ተጠሪም ይህንኑ መነሻ በማድረግ የስራ ውሉን ማቋረጡ የአዋጁን አንቀጽ 13(2) እና 13(7) ድንጋጌዎች ይዘት፣ አላማ እና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንም፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ለጉዳዩ በቀጥታ አግባብነት የሌለውን የአዋጁን አንቀጽ 27(1)(ሠ) ድንጋጌን ጠቅሶ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሊስተካከልና ሊታረም የሚገባ ቢሆንም ሆኖም ግን በውጤት ደረጃ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የበታች ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሽሮ በሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 95631 በ11/3/2005 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 129923 በ20/07/2005 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት በተለወጠ ምክንያት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. የሰበር ወጪና ኪሳራን ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፣

ዘ/ቢ

የሰ/መ/ቁ. 92410

ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ቻይና ሀይ ዌይ ግሩፕ ሊሚትድ- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-አቶ ውብሸት እንግዳው - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ30/08/2002 ዓ.ም.ጀምሮ እስከ 15/02/2005 ዓ.ም. ድረስ በወር የተጣራ ደመወዝ ብር 25,000 እያገኙ ሲሰሩ ቆይተው የስራ ውላቸው ሲቋረጥ ደመወዝ እና የስራ ስንብት ክፍያ የተፈጸመላቸው ቢሆንም የዓመት ዕረፍት፣የሳምንት ዕረፍት እና የሕዝብ በዓላት ክፍያ ያልተፈጸመላቸው በመሆኑ ይኸው ክፍያ ታስቦ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ባቀረበው የመቃወሚያና የፍሬነገር መልስ ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ከሳሽ የስራ ውላቸውን በፈቃዳቸው ባቋረጡበት ጊዜ የሚገባቸውን ክፍያ በሙሉ ተሳስበው የተቀበሉ መሆኑን፣አሁን ጥያቄ ያቀረበባቸውን ክፍያዎች በወቅቱ መጠየቅ የሚችሉ ሆኖ እያለ ክፍያዎችን በመከፋፈል አሁን ያቀረቡት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.216 መሰረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣የዓመት ዕረፍታቸውን የተጠቀሙ መሆኑን፣የሳምንት ዕረፍት እና የሕዝብ በዓላት ክፍያ የየትኛው ዓመት እንደሆነና እና በማን ትዕዛዝ እንደሰሩ በክሳቸው ለይተው ያልገለጹ መሆኑን፣በሳምንት ዕረፍት እና በሕዝብ በዓላት ጊዜ ስራ የሚሰራ ከሆነ ክፍያ የሚፈጸመው ከየወሩ ደመወዝ ጋር ተጨምሮ በዚያው በተሰራበት ወር በመሆኑ ያልተከፈላቸው ክፍያ የሌለ መሆኑን፣ከሳሽ ቀደም ሲል ከተፈጸመላቸው ውጪ ከአሰሪው የሚጠይቁት ሌላ ክፍያ አለመኖሩን በማረጋገጥ ስምምነት ከፈረሙ በኋላ አሁን

ያቀረቡት የተጨማሪ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የዳኝነት ጥያቄ ከቀረበበት ክፍያ ውስጥ በይርጋ ቀሪ የሚደረገውን መጠን በመለየት፣በቀሪው መጠን ላይ በተከሳሽ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ባለመቀበል እና ሰራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) መሰረት ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ ከተከሳሽ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ስራው የመንገድ ስራ በመሆኑ ቻይናውያን የፕሮጀክቱ ኃላፊዎች በሚሰጡት የቃል ትዕዛዝ መሰረት ስራው ከሳምንት እስከ ሳምንት ይሰራ የነበረ መሆኑ እና የዓመት ዕረፍትም የሚጠየቀው በጽሁፍ መሆኑ በከሳሽ ምስክሮች መረጋገጡን እና በአንፃሩ ከሳሽ በትርፍ ሰዓት እና በበዓላት ቀናት ስላለመስራታቸው ወይም ለስራው ክፍያ የተፈጸመላቸው ስለመሆኑ እንዲሁም ከሳሽ የዓመት ዕረፍት የወሰዱ ስለመሆኑ የተከሳሽ ምስክሮች ማስረዳት እንዳልቻሉ ገልጾ የ13 ቀናት የሳምንት ዕረፍት እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 21,663 እና የ29 ቀናት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 24,167 በድምሩ ብር 45,830 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሳሽ ድርጅት ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው በመቅረቱ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው ከአመልካች የሚጠይቀው ቀሪ ክፍያ አለመኖሩን ተስማምቶ የፈረመ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በዚህ ረገድ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ ለተጠሪው ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈለው የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቹ የፈረሙት ስምምነት ስራቸውን በለቀቁበት ጊዜ ቀሪ የደመወዝ ክፍያ፣ የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ በድምሩ ብር 60,000 የተከፈላቸው መሆኑ እና ከዚህ በኋላ በአሰሪው ላይ የሚያቀርቡት ሌላ የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ የተገለጸበት ነው፡፡የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው ተዋዋይ ወገኖች የስራ ውላቸውን በስምምነት ማቋረጥ እንደሚችሉ እና ሆኖም ግን ሰራተኛው በሕግ የተሰጠውን መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት የህግ ውጤት እንደማይኖረው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመጥቀስ ነው፡፡የትርፍ ሰዓት፣የበዓላት ቀናት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ ደግሞ ለሰራተኛው በሕግ የተጠበቁ መብቶች ስለመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 68(1)፣75(1) እና 77(5) ድንጋጌዎች ላይ

ተመልክቶአል፡፡በመሰረቱ ተጠሪው የፈረሙት ስምምነት ቀሪ የደመወዝ ክፍያ፣ የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ በድምሩ ብር 60,000 የተከፈላቸው መሆኑን የሚገልጽ ከመሆኑ ውጪ የትርፍ ሰዓት፣የሕዝብ በዓላት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያዎችን ጨምሮ ከአሰሪው የሚገባቸውን ክፍያዎች በሙሉ የተቀበሉ ስለመሆኑ ወይም እነዚህን ክፍያዎች ለመጠየቅ የሚያስችልየስራ ሁኔታ ያልነበረ ስለመሆኑ የተገለፀበት አይደለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ ከአመልካች የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ግን ለተጠሪው የተወሰነው የዓመት ዕረፍት ክፍያ መጠን የግራ ቀኙን ክርክር እና የአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 77(1) የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑ መመርመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ በስራው ላይ የቆዩት ከ30/08/2002 ዓ.ም.ጀምሮ እስከ 15/02/2005 ዓ.ም. ድረስ መሆኑን በክስ ማመልከቻቸው ላይ የገለጹ ሲሆን ይህ ጊዜም 2 ዓመት ከ 6 ወር ከ15 ቀን ነው፡፡በመሰረቱ ከሰራተኛ የሚሰጠው የዓመት ዕረፍት ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት 14 ቀን መሆኑ እና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ አገልግሎት በ14 ቀን ላይ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአገልግሎት ዓመት 1 የስራ ቀን እየታከለ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 77(1) (ሀ) እና(ለ) ስር ተመልክቷል፡፡አመልካች በዚህ ረገድ በግልጽ ላቀረበው ክርክር ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላይ በዝምታ ከማለፍ በስተቀር የሰጡት ማስተባበያ የለም፡፡በመሆኑም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት ክፍያ የ15 ቀን ተኩል ሆኖ እያለ በ29 ቀን ታስቦ እንዲከፈል መደረጉ ከግራ ቀኙ ክርክር እና በሕጉ ከተመለከተው ውጪ ሆኖ በመገኘቱ በዚህ መጠን ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 82043 በ11/10/2003 ዓ.ም. የሰጠው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.135827 በ18/11/2005ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ሰራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 25(1) መሰረት ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑን በመግለጽና በዚህ ረገድ ከአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የሳምንት ዕረፍት፣የሕዝብ በዓላት እና የዓመት

ዕረፍት ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ስ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

3. ከላይ በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ለተጠሪው የሚከፈለው የዓመት ዕረፍት ክፍያ መጠን የ29 ቀን ነው በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የዓመት ዕረፍት ክፍያ የ15 ቀን ተኩል ነው በማለት ወስነናል፡፡
5. ለተጠሪው ሊከፈል የሚገባው የሳምንት ዕረፍት፣የትርፍ ሰዓት እና የዓመት ዕረፍት ክፍያ በድምሩ ብር 34,579.68(ሰላሳ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ከስድሳ ስምንት ሳንቲም) ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ነው በማለት ወስነናል፡፡
6. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.84794 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ29/11/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
7. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
8. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
9. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 97512

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ምህረት አለነ ገረመው - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት - ነ/ፈጅ ፈለቀ ካሣሁን ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት የቀረበውን የአካሉ ጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡-አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በጋራዥ ኃላፊነት የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው በወር ብር 3,460.00(ሶስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ ብር) እየተከፈላቸው ሲሰሩ የኮድ ቁጥሩ 3-08573 በሆነው የተጠሪ ድርጅት ተሽከርካሪ ለስራ እየተጓዙ ሚያዚያ 05 ቀን 2003 ዓ/ም በደረሰው የመኪና አደጋ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱንና በሕክምናም በአካላቸው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን የተረጋገጠ መሆኑን፣በደረሰው የአካል ጉዳት መጠን መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባው ብር 171,600.00 (አንድ መቶ ሰባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ብር) ሁኖ እያለ ተጠሪ ድርጅት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ባለው የኢንሹራንስ ውል መሰረት ከፍተኛው የመድን ሽፋን ብር 120,000.00 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ብር) መሰረት ተደርጎና ከጉዳት መጠኑ ጋር ተሰልቶ ብር 36,000.00 (ሰላሳ ስድስት ሺህ ብር) ከሕግና ከድርጅቱ ህብረት ስምምነት ውጪ ከፍሎ ቀሪውን ያልከፈላቸው መሆኑን ጠቅሰው ብር 171,600.00 እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡- አመልካች የድርጅቱ ሰራተኛ በስራ ላይ እያሉ በአካላቸው ላይ ጉዳት መድረሱን ሳይክድ የአካል ጉዳት ካሳ ለአመልካች የተከፈለው ድርጅቱ ባለው የመድን ሽፋን መሆኑን፤ የመድን ሽፋን ላላቸው የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሰራተኞች በስራ ላይ ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሳ የሚከፈለው በመድን ፖሊሲው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) ድንጋጌ መጠቀሱን ገልጾ አመልካች በዚሁ አግባብ ብር 36,000.00 የተከፈላቸው

በመሆኑ ቀሪ የሚከፈላቸው የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ የለም ሲል ተከራክሯል፡፡የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከተጠሪ ድርጅት ጋር ያለውን የመድን ፖሊሲውን እንዲያቀርብለት አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ብር 36,000.00 የተከፈላቸው በመድን ፖሊሲው መሰረት በመሆኑና በዚህ አግባብ የአካል ጉዳት ካሳ የተከፈለው ሰራተኛ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 109(1) መሰረት አሰሪውን ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ድምዳሜ የአመልካችን ቀሪ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን ውድቅ አድርጎ ወስኖታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በአመልካች ላይ በስራ ላይ ለደረሰው የ30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት በአዋጁ ሊከፍል የሚገባው የካሳ መጠን ብር 62,280.00(ስልሳ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ሁኖ እያለ አመልካች ተጠሪ ብር 36,000.00 በመድን ፖሊሲው መሰረት ተከፍሏል በማለት ቀሪውን ብር 26,280.00 ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(3(ሀ)) እና ስራ ላይ ያለውን የድርጅቱን የህብረት ስምምነት አንቀጽ 25(2) ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ ይገባል ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት የድርጅቱ ነገረ ፈጅ ቀርበው በጽሑፍ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡በመልሳቸው ላይም ለአመልካች የአካል ጉዳት ካሳ የተከፈለው በሕጉ አግባብ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡እንደመረመርነውም አመልካች በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያት የተከፈለው ካሳ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(3(ሀ)) መሰረት የተሰላ አይደለም በማለት ያቀረበው ክስ የስር ፍርድ ቤቶች ከኢንሹራንስ የጉዳት ካሳ አከፋፈል አንጻር ብቻ በማየት ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ የአካል ጉዳቱ በስራ ላይ መድረሱና የጉዳቱ መጠንም 30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት መሆኑን ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነጥብ መሆኑን፣ግራ ቀኙን የሚያከራክረው የካሳው መጠን መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ አመልካች በአካላቸው የደረሰውን የጉዳት መጠን መሰረት በማድረግ ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁትና የካሳውን መጠን ለማስላት መሰረት ያደረጉት በአካላቸው ደረሰ የተባለውን

30% ጉዳት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 96(1) መሰረት በስራ ቦታ ላይ ለሚደርስ የአካል ጉዳት የካሳ መጠን የሚሰላበት አግባብን ሕጉ በአንቀፅ 109(3) ደንግጎ እናገኛለን፡፡በዚህም መሰረት በሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት ከሆነ የሰራተኛው የአመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው ውጤት እንዲሁም ሰራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ከዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት መጠን በታች ከሆነ ከአካል ጉዳት ደረጃው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንደሚከፈለው የተጠቀሰው ድንጋጌ ይገልፃል፡፡በአመልካች ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት መሆኑን (30%) የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

በአንድ ሠራተኛ ላይ የሚደርሱት የጉዳት መጠን ደረጃዎች፡-ጊዜያዊ የአካል ጉዳት፣ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት፣ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት እና ሞት መሆናቸው በሕጉ ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ ይህን ደረጃ በመመሪያ በጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ የሚያወጣው የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር መሆኑና ደረጃውን የሚያወጣውም ለዘላቂ ከፊል እና ሙሉ የአካል ጉዳት ብቻ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 102(1) ስር ተመለክቷል፡፡ በጊዜያዊ የአካል ጉዳት ሠራተኛው ቀድሞ የነበረውን የመሥራት ችሎታ መልሶ ስለሚያገኝ፤ ሞትም ቢሆን የጉዳቱ መጠን በራሱ የተገለጠ በመሆኑ ሚኒስትሩ ለእነዚህ ጉዳቶች ደረጃን የማይወሰን መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ሚኒስትሩ ደረጃቸውን ለሚወስንላቸው ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል ጉዳቶች ግን የጉዳቶቹ መጠን ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ጉዳቱ በደረሰ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ በተቻለ መጠን የጉዳቱን መጠን መወሰን ከሚኖርበት የህክምና ቦርድ ማስረጃ ማግኘት እንደሚያስፈልግ የአዋጁ አንቀጽ 102 (2) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለውም አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ ጉዳት ሲደርስበትና ጉዳቱ ዘላቂ ሁኖ ጉዳቱ ያስከተለው የመስራት ኃይል ቅነሳ በተገቢው ባለሙያ ተረጋግጦ በደረሰው የጉዳት መጠን ሰራተኛው እንዲካስ ማድረግ የሕጉ ፍላጎት መሆኑን ነው፡፡የአዋጁ አንቀጽ 109(3(ሀ) ድንጋጌ ሲታይም ከስራ ላይ ለሚመጣ ጉዳት ምክንያት ዘላቂና ሙሉ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ ሊያገኘው የሚችለው ከፍተኛው ክፍያ የሰራተኛው የአመት ደመወዝ በአምስት ተባዝቶ የሚገኘው የብር መጠን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ይሁን እንጂ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ከሆነ ሰራተኛው ሊያገኝ የሚገባው የካሳ ክፍያ መጠን በሰራተኛው አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ደረጃ መሰረት አድርጎ የሚሰላ መሆኑን የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡

ሕጉ የካሳ መጠኑ የሚሰላበትን አግባብ ከመደንገጉም በተጨማሪም ሰራተኛው የአካል ጉዳት ክፍያ ተከፋይ የማይሆንባቸው አጋጣሚዎችም እንዳሉ ያሳያል፡፡ይኼውም፡ አንድ ሰራተኛ ሲሰራ የነበረው በመንግስት የልማት ድርጅት ሁኖ በመንግስት የጡረታ ሕግ የታቀፈ ከሆነ ወይም አሰሪው በገባለት የመድህን ዋስትና ተጠቃሚ ከሆነ በዘላቂ የአካል ጉዳት ክፍያ እንደማያገኝ

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 109(1) ስር የደነገገ ሲሆን የዚህ የድንጋጌው መሰረታዊ አላማም ሰራተኛው በደረሰበት ከባድ የአካልጉዳት ምክንያት ከጡረታ ከወጣ ወዲያውኑ በመንግስት የጡረታ ክፍያ ስርዓት የሚታቀፍ በመሆኑ ከአንድ ምንጭ ሁለት ጊዜ የመካስ ሁኔታ እንዳይኖር ለመከላከል ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡እንዲሁም አንድ አሰሪ ለሰራተኞቹ በስራ ላይ ለሚደርስ አደጋ ዋስትና ገብቶላቸው የነበረ መሆኑና በፖሊሲው መሰረት ስለደረሰበት ጉዳት ሰራተኛው የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ አሰሪው የጉዳት ካሳ ለመክፈል የሚገደድበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያስረዳል፡፡ይሁን እንጂ ይህ የህጉ መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ሰራተኛው ተገቢውን ካሳ በደረሰው የአካል ጉዳት መጠን አንፃር እየታዬ ሊያገኝ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም ቀጥሎ መታየት ያለበት ቁልፍ ጥያቄ ሰራተኛው በሕጉ የተጠበቀለትን የካሳ መጠን አሰሪው በመድን ፖሊሲው ሙሉ በሙሉ ሳይሸፈን እንዲቀር አድርጎ ቢገኝ የመድን ፖሊሲው መኖሩ ብቻውን ሰራተኛው በመድን ፖሊሲው ስሌት መሰረት ተሰልቶ የሚመጣውን ካሳ ብቻ ተከፍሎ እንዲሄድ ያስገድደዋል? ወይስ አያስገድደውም? የሚለው ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይም "በሕብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የመንግስት ድርጅቶች ሰራተኞች የሚሰጠው የጉዳት ካሳ አሰሪው በገባበት የመድህ ዋስትና ወይም በመንግስት የጡረታ ሕግ መሰረት ይሆናል፡፡ድርጅቱ መድህን ያልገባ ከሆነ በመንግስት የጡረታ ሕግ ለሚሸፈኑ ሰራተኞች የመንግስት የጡረታ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡"በሚል የተቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት የሚቻለው አንድ ሰራተኛ በመንግስት የጡረታ ሕግ የታቀፈ ከሆነ ወይም አሰሪው በገባለት የመድህን ዋስትና ተጠቃሚ ከሆነ የጉዳት ካሳውን አሰሪው እንዲከፍል የማይገደድ መሆኑን ነው፡፡ይህ ድምዳሜ የሚያዘው ግን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3) ስር የተመለከተውን የካሳ ስሌት መሰረት አድርጎ የኢንሹራንስ ሽፋኑ ለሰራተኛው ካሳውን ለመክፈል የሚያስችል ሁኖ ሲገኝ ነው፡፡ይህ ካልሆነ ሰራተኛው በስራው ላይ ለደረሰበት ካሳ ተገቢውንና በሕጉ የተቀመጠለትን ካሳ አግኝቷል ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ከዚህ ውጪ አሰሪው የገባው የኢንሹራንስ ሽፋን ሰራተኛው በሕጉ በተመለከተው ስሌት መሰረት የሚያገኘውን የአካል ጉዳት ካሳ የሚቀንስ መሆኑ ቢረጋገጥም አሰሪው የመድን ሽፋን በመግባቱ ብቻ የጉዳት ካሳውን እንዲከፍል አይጠበቅበትም ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(1) መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅት ለሰራተኞቹ የገባው የአካል ጉዳት ዋስትና ሽፋን መኖሩ ድርጅቱን ተጠያቂ የማያደርገው ድርጅቱ ሰራተኛው በአዋጁ አንቀጽ 109(3) በተመለከተው ስሌት መሰረት ሊያገኝ የሚገባውን የአካል ጉዳት ለማስገኘት የሚያስችል የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንጂ

በሕጉ ጥበቃ ከተደረገው የካሳ መጠን ያነሰ የሚያስገኝ የመድን ሽፋን ገብቶ በተገኘ ጊዜም ጭምር አይደለም፡፡ድርጅቱ በሕጉ ከተመለከተው የካሳ መጠን ያነሰ የኢንሹራንስ ሽፋን ገብቶ ሲገኝ ለቀሪው የጉዳት ካሳ ኃላፊነቱን የማይወስድበት ምክንያት የለም፡፡ግራ ቀኙ ለክርክራቸው መሰረት ያደረጉት የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 25(2) ሲታይም በድርጅቱ ስራ ምክንያት አደጋ ለደረሰበት ሰራተኛ ድርጅቱ በገባው የኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረት ያሳክማል፣ደመወዙንም ይከፍላል፣ሆኖም መስራት የማይችል ከሆነ ስራው ላይ ባለው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስለዚህ ጉዳይ የተደነገጉትን እና በጡረታ አዋጅ መሰረት መብቱ ይጠበቅለታል በሚል የሚያስቀምጥ ከመሆኑ ውጪ በስራ ላይ ለደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ የሚከፍልበትን ስሌትና የአሰሪውን ከኃላፊነት ነጻ የሚሆንበትን አግባብ የማያስቀምጥ ሁኖ አግኝተናል፡፡ከሁሉም በላይ የሕጉ የጉዳት ካሳና ኃላፊነት ድንጋጌዎች የዝቅተኛ የስራ ሁኔታዎች (minimum labour conditions) አካል ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ በመሆኑና ሕጉም የሚያስቀምጠው ዝቅተኛውን ጥበቃ ሁኖ በሕጉ ከተቀመጠው ሁኔታ በላይ ግን በህብረት ስምምነት ወይም በውል ሊወሰኑ የሚችሉ መብትና ጥቅሞች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚታመኑ ሁኖ ሕጉ ካስቀመጠው ዝቅተኛው ሁኔታ በሕብረት ስምምነት መቀነስ የማይቻል መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 134(1) በግልጽ የተቀመጠ ከመሆኑ ጋር ሁሉ ተዳምሮ ሲታይ ተጠሪ የሕብረት ስምምነቱን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበትን ህጋዊ አግባብ አላገኘንም፡፡

ከላይ ከተመለከቱት የሕግ ማእቀፎች አንፃር የአመልካችን ጥያቄ ስንመለከተው አመልካች 30% ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ተጠሪም ማስተባበያ ክርክር ያቀረበበት ጉዳይ አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 109(3(ሀ)) በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት ሊከፍል የሚገባው ካሳ የወር ደመወዛቸው × በአስራ ሁለት ወራት × አምስት አመታት × የመስራት ኃይል ቅነሳ ተባዝቶ የሚመጣው የገንዘብ መጠን ነው፡፡በዚህ የሕጉ ስሌት መሰረት ለአመልካች ሊከፍል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ መጠን፡ 3460.00×12×5×30%×=62,280.00 ሁኖ አግኝተናል፡፡ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ተጠሪ ድርጅት በገባው የመድን ሽፋን መሰረት ብር 36,000.00 በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 109(1) መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል የማይገደድበት ሁኖ ቀሪውን ብር 26,280.00 (ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ግን ከሕጉ ስሌት ማስቀረት የሚችልበት ምክንያት ስላልተገኘ ለአመልካች ሊከፍል የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የቀሪ የአካል ጉዳት ካሳ ክፍያ ጥያቄን ውድቅ ያደረጉት ተጠሪ በሕጉ አግባብ ሙሉ በሙሉ የመድን ሽፋን የገባላቸው መሆኑን የመድን

ድርጅቱም በስሌት መሰረት የከፈላቸው መሆኑን ሳያረጋገጡ በመሆኑ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 82946 ሐምሌ 24 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 136063 ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ/ም በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች ላይ ለደረሰው የአካል ጉዳት በሕጉ ስሌት መሰረት የሚከፈላቸው የካሳ መጠን በኢንሹራንስ ሽፋን ሙሉ በሙሉ ያልተከፈላቸው በመሆኑ ቀሪውን ብር 26,280.00 (ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር) ለአመልካች ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስነናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 98052

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-በርሄ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ስዩም ረጋሳ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ገመቹ አዱኛ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ30/08/2005 ዓ.ም.አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ16/07/2005 ዓ.ም. ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በጀማሪ ነገረ ፈጅነት የስራ መደብ ላይ ተቀጥረው አንድ ወር ከ15 ቀናት የሰሩ መሆኑን፣የ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ እንዲኖር የተደረገ ስምምነት ሳይኖር ተከሳሽ ድርጅት የስራ አፈጻጸምህ ዝቅተኛ ነው፣ሰዓት አክብረህ ስራ አትገባም የሚል እና መሰል ምክንያቶችን በመዘርዘር የስራ ውላቸውን አላግባብ እንዳቋረጠ የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ ድርጅት ከሕገወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን እንዲፈጽምላቸው እና ቅጥሩም ቋሚ ቅጥር ነው ተብሎ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ13/10/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ከሳሽ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ መሆኑን፣በዚህ የሙከራ ጊዜ ውስጥ በፍ/ቤት ቀጠሮ በጊዜ ሳይቀርቡ ቀርተው መዝገቦች እንዲዘጉ በማድረግ፣በሰዓት ስራ ባለመግባት እና የመሳሰሉ ጥፋቶችን ከመፈጸማቸውም በላይ ማስጠንቀቂያ እና መልሶችን ራሳቸውን ችለው የማዘጋጀት ውስንነት የታየባቸው መሆኑን እና ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ እንዲሰናበቱ የተደረገውም የሙከራ ጊዜአቸው ባለማጠናቀቁ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሮአል፡፡

ፍ/ቤቱም የተከሳሽን ምስክሮች ከሰማ እና ከሳሽ ፈርመው ተቀብለዋል በተባለው ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ መሆኑን በሚገልጸው ደብዳቤ ላይ የተመለከተው እና በከሳሽ የተካደው

ፊርማ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ከሳሽ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ መሆኑን በሚገልጸው ደብዳቤ ላይ የተመለከተው እና በከሳሽ የተካደው ፊርማ የከሳሽ መሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ የተረጋገጠ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 11(3) በተመለከተው መሰረት ግራ ቀኙ በ16/07/2005 ዓ.ም. ባደረጉት የቅጥር ውል ላይ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ስለመስማማታቸው ውሉ የማያመለክት መሆኑን፣ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ግራ ቀኙ ስለመስማማታቸው በውሉ እስካላረጋገጡ ድረስ ቅጥሩ የተፈጸመው ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ የሚገልጸውን ደብዳቤ ከሳሽ ፈርመው መቀበላቸው ብቻውን ከሳሽ በዚህ የውል ሁኔታ ስለመስማማታቸው የሚያረጋግጥ አለመሆኑን፣የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ግራ ቀኙ በውሉ ያልተስማሙ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከሳሽ በተከሳሽ የተጠቀሱትን ድክመቶች አሳይተው ቢሆን እንኳ ተከሳሽ የከሳሽን የስራ ውል ማቋረጥ ይገባው የነበረው በማስጠንቀቂያ ሆኖ ሳለ ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ ስንብቱ የተከናወነው ከሕግ አግባብ ውጪ እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ተከሳሽ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 2,500፣የስራ ስንብት ክፍያ ብር 273.97 እና የካሳ ክፍያ ብር 15,000 በድምሩ ብር 17,773.97(አስራ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሶስት ከዘጠና ሰባት) የገቢ ግብር ቀንሶ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ሰሚው ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የቅጥር ውሉ በተደረገበት በዚያው ቀን ተጠሪ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ የሚገልጸውን ደብዳቤ ፈርመው መቀበላቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ለሙከራ ጊዜ መቀጠራቸው የተገለጸበት ደብዳቤ በአመልካች ብቻ የተዘጋጀ ነው ተብሎ የአመልካች ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል።

በዚህም መሰረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛ ለስራው ተስማሚ አለመሆኑ ሲረጋገጥ አሰሪው የስራ ስንብት እና የካሳ ክፍያ ለመክፈል ሳይገደድ የሰራተኛውን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 11(5) በግልጽ የተመለከተ ሆኖ እያለ እና ተጠሪውም ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆኑ በቅጥሩ ዕለት በአድራሻቸው የተጻፈውን ደብዳቤ ፈርመው በመቀበል ያረጋገጡ ሆኖ እያለ አሰሪው ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ውሉን ያቋረጠው አላግባብ ስለሆነ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እንዲፈጽም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ አይደለም በማለት መሆኑን ተገንዝበናል።እንደተባለው

ተገቢ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛን በሙከራ ጊዜው ውስጥ አሰሪው ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ አዋጁ የሚደነግግ ቢሆንም የአዋጁ አንቀጽ 11(5) ድንጋጌ ተፈጻሚ ከመደረጉ አስቀድሞ ግን ተዋዋዮቹ የሙከራ ጊዜ እንዲኖር በቅጥር ውላቸው የተስማሙ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት የአዋጁ አንቀጽ 11(3) በግልጽ ያመለክታል፡፡በተያዘው ጉዳይ የቅጥር ውሉ የተደረገውም ሆነ ተጠሪው የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ ስለመሆኑ አመልካች ለተጠሪው በደብዳቤ የገለጸው በተመሳሳይ ቀን ነው፡፡ተጠሪ የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ የመሆን አለመሆኑ ጉዳይ ደግሞ መረጋገጥ ያለበት በአዋጁ አንቀጽ 11(3) መሰረት በቅጥር ውሉ እንጂ አመልካች በተናጠል ለተጠሪው በሚሰጠው ማስታወቂያ ባለመሆኑ ተጠሪው የሙከራ ጊዜውን የቅጥር ሁኔታ በውሉ ላይ በግልጽ የተቀበሉ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአመልካች የተጻፈላቸውን የቅጥር ደብዳቤ ፈርመው የተቀበሉ መሆኑ መረጋገጡ ብቻ የሙከራ ጊዜውን የቅጥር ሁኔታ ተስማምተው ተቀብለዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ  የተቀጠሩት ለ45 ቀናት የሙከራ ጊዜ በመሆኑ እና የተሰናበቱትም በስራ ላይ የተለያዩ ድክመቶችን በማሳየታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ለተጠሪው ተገቢ ክፍያዎችን እንዲፈጽም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 83708 በ21/02/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 139206 በ06/06/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 86397 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ10/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 92152

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ደሳለኝ – ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወጣቶች ገነት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ ቤት – ነ/ፈጅ አንዋር ሙስጠፋ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት ያላግባብ ከሥራ የተሰናበቱ ስለመሆኑ ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁት ዳኝነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሚታይ አይደለም ተብሎ ውድቅ በመደረጉ ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት በጥበቃ ሠራተኛነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ እንዳሉ ከሕግ ውጪ ተሰናብቼአለሁ በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱ ተጠሪን ጠርቶ ባለመቅረቡ በሌለበት አይቶና ጉዳዩን አጣርቶ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት የወሰነ ሲሆን፤ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ ትምህርት ቤት ከሕዝብ ትምህርት ቤትነት ወደ መንግሥት ከመዛወሩ በፊት ለሰሩባቸው ጊዜያት ተገቢ ክፍያ እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሆኖ እያለ፤ ትምህርት ቤቱ ወደ መንግሥት ከተዛወረ በኋላ ሥራ ባልሰሩበት ሁኔታ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አይታይም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታቸውም ተመርምሮ አመልካች ቀደም ሲል ተጠሪ ከሕዝብ ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት ሳይቀየር በማገልገል ላይ እያሉ ያላግባብ መሰናበታቸውን ገልፀው በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት

የቀረበው ክስ ተጠሪ በአሁኑ ወቅት የመንግሥት እንጂ፣ የሕዝብ ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መመሪያ እንዲቀርብ ተደርጎ አመልካችም አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡
ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ ተቋሙ የሕዝብ የነበረ መሆኑን፤ ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ወደ መንግሥት የተዛወረ መሆኑን ፤ አመልካች ስንብቱ ተከናውኗል በማለት ክስ የመሰረቱት ደግሞ መስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሕዝብ ጥያቄና ፍላጎት ከሕዝብ ይዞታነት ወደ መንግሥት ይዞታነት የሚዛወሩ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ሽግግር ለማስፈፀም የተዘጋጀው መመሪያ ደግሞ ተፈፃሚነቱ ከሰኔ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን ነው፡፡
ወደ ሕጉ ስንመጣ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የራሱ የሆነ የተፈጻሚነት ወሰን ያለው ስለመሆኑ አንቀጽ 3 የሚደነግግ ሲሆን፤ ይህ ድንጋጌ በአዋጁ የሚገዙትና የማይገዙትን የሥራ ግንኙነቶችን ይዞ ይገኛል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 3(1) በንዑስ አንቀጽ 2 ስር በስተቀር የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም በቅጥር ላይ የተመሰረተው ግንኙነት በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች የማይፈጸሙባቸው መሆኑን በአንድ መልኩ ከዚህ ድንጋጌ ስንረዳ በሌላ መልኩ ደግሞ ከነዚህ ውጭ ባሉ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚፈጠሩ ማንኛውም ግንኙነት ላይ አዋጁ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው እንረዳለን፡፡ የአንቀጹ ሁለተኛው ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ ደግሞ ግንኙነታቸው በቅጥር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም በዝርዝር በሚያስቀምጣቸው የሥራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ የማይፈጸም መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ እነዚህም ለአስተዳደግ ሲባል፣ ከሕመም ለመዳን፣ ወይም እንደገና ለመቋቋም፣ የትምህርትና ለሥልጠና (የሙያ መልመጃ ትምህርትን ሳይጨምር ) የሚደረጉ የሥራ ውሎችን፣ የሥራ መሪን፣ ለትርፍ በሚካሔድ ሥራ ላይ ያልተመሰረተ የግል አገልግሎት ቅጥርን፣ በልዩ ሕግ የሚተዳደሩ እንደ የጦር ኃይል ባልደረቦችን፣ የመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞችን፣ ዳኞችን፣ ዐቃቤ ሕጐችን፣ ፖሊሶችን እና ሌሎችንም እንዲሁም በራሱ የንግድ ሥራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰራ ሥራ የሚያከናውን ተዋዋይ ያለበት ግንኙነቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም አዋጁ እነዚህ ግንኙነቶች ላይ የማይፈጸም መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም በአጭሩ ሲገለጽ አዋጁ በአጠቃላይ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚቋቋም በቅጥር ላይ

የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም፤ በአዋጁ በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ሕግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ተጠሪ ተቋም ወደ መንግሥት ከሐምሌ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሲዛወር ከተጠሪ ጋር የሥራ ግንኙነት እንዳልነበራቸው የሚገልጹ ቢሆንም፤ መመሪያው ተፈጻሚ የሆነው ግን ከሰኔ 01 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ፤ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሚታይበት ምክንያት የለም፡፡ መመሪያው ወደኋላ ሂዶ እንዲሰራ ሊደረግ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት አመልካች የሚያቀርቡት ክርክርም ሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ውስጥ ሥራ ላይ ያልነበሩ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አላገኘነም፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባልቀረበበት ሁኔታ የሥልጣን ጉዳይ አንስቶና በተገቢው ማስረጃ በማጣራት ዳኝነት መስጠቱም ተካራካሪ ወገን ባይቀርብም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነትም የስረ ነገር ሥልጣን ጥያቄን ማንሳት የሚችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9(1) እና 231(1)(ለ) ድንጋጌዎች የምንረዳው በመሆኑ፤ በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርቡት ቅሬታም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(2) እና በአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 መሠረት በመደበኛው ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የሚታይ ባለመሆኑ፤ የበታች ፍርድ ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80282 የካቲት 21 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132323 ሰኔ 18 ቀን 2005 ዓ.ም በውሣኔ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚገዛ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ሥልጣን ባለው አካል ጥያቄያቸውን ከማቅረብ ይህ ውሣኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.

የሰ/መ/ቁ. 96458

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ኢትዮጵያ የርቀት ትምህርት ኮሌጅ አልቀረበም

ተጠሪ፡- ዶ/ር ደሣለኝ ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ከሣሹ(የአሁን ተጠሪ)ባቀረበው ክስ ታህሳስ 19/2005 ባቀረበው ክስ አመልካች ሰኔ 22/2004 በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ያሰናበተኝ በመሆኑ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ይክፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ተከሣሽ (አመልካች)ባቀረበው መልስ የተጠሪ ጥያቄ በ6 ወር የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 162(4) የሥራ ውሉ ለመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርቡት ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ደንግጓል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪም ያቀረቡት ክስ የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ሰኔ 22-2004 ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ 6 ወር ያለፈው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የክስ አቤቱታቸው በጊዜ ለማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያትም በቂና አሣማኝ አይደለም፡፡በመሆኑም ጥያቄው በይርጋ ይታገዳል በማለት ተወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የከፍተኛ ፍ/ቤትም ውል ከተቋረጠ በኂላ የሚቀርቡ ክፍያዎች ከ6ወር በኂላ መቅረብ እንደሌለበት ቢደነግግም የፍትሀብሄር ሕጋችን በአንቀጽ 1860(3) ጳጉሜን እንደወር የማትቆጠር በመሆኗ የአመልካች ጥያቄ ከ22-10-2004 እስከ ታህሳስ 19-2005 በመቅረቡ 6ወር ስላልሞላው በይርጋ ሊታገድ አይገባም በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት ብይን በመሻር በዋና ጉዳይ፤ በፍሬ ነገሩ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.341(1)መሠረት መልሶታል፡፡

ለሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህን ለማረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታም ተጠሪ ሰኔ 22/2004 የሥራ ውላቸው መቋረጡን ጠቅሰው ታህሳስ 19/2005 ያቀረቡትን የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 162(4)መሠረት 6 ወር ካለፈ በኋላ ነው ብሎውድቅ የተደረገውን ጉዳይ የፌደራሉ የይግባኝ ሰሚ (ከፍተኛው) ፍ/ቤት በፍትሀብሔር ህጋችን ቁጥር 1860(3) ጳጉሜ እንደወር አትቆጠርም በማለት የሰበር ውሣኔን መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቋል፡፡ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ አቅርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍትሐብሔሩን ህግ ቁጥር 1860(3) ጠቅሶ ጳጉሜ እንደወር አትቆጠርም የክሱ ጊዜ 6ወር አልሞላውም ብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት እንደ ጭብጥ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም እንዳየነው አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ ያቀረቡት ከውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ያቀረቡት ጥያቄ ጳጉሜ እንደወር ስለማትቆጠር 6ወር አልሞላም ተብሎ የይርጋ መቃወሚያው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉና በፍሬ ነገሩ እንድንከራከር መደረጉ በአግባቡ አይደለም የሚል ነው፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪ የሆነው የህግ ጥያቄ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4)የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል የሚለው ድንጋጌ "ጳጉሜን ያካትታል ወይስ አያካትትም?በሚል ነጥብ ነው፡፡እንግዲህ ይርጋ ማለት የመብት ጥያቄ ጊዜ በማለፉ ቀሪ የሚሆንበት ነው ባንፃሩ መብት ላልነበረው የሚያጐናፅፍ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ አይቋረጥም የተባለበት ምክንያት የፍትሐብሔር ህጋችን አንቀፅ 1860(3)ጳጉሜን እንደወር ስለማይቆጥር እና የአሰሪና ሰራተኛ ህጉም "ወር"ን መሠረት አድርጐ ስለተደነገገ ነው፡፡

ጳጉሜ እንደ አስራ ሦስተኛ ወር የማትቆጠር መሆኑ ከታወቀና የሀገራችን የአንድ አመት ጊዜ 12 ወራቶች ከሆኑ ከዚህ አቆጣጠር ውጭ ያሉት ቀናት በግራ ቀኙ መሀከል መብትም ሆነ ግዴታ ሊፈጥር አይገባም፡፡ጳጉሜ ተጠሪ ሥራም ላይ ቢሆኑ የሚሰጣቸው ጥቅም ወይም በመብት ደረጃ የሚጠይቁትም ክፍያ የለም፡፡እንግዲህ እንደወር የማይቆጠረው "ጊዜ" ለቀረበው ከውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የሚነሣው የክፍያ ጥያቄ ጳጉሜ ተሰልቶ የተጠሪን መብት ሊያጣብብ አይገባውም፡፡

ባጠቃላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያውን ደረጃ ፍ/ቤት ብይን ሽሮ የተጠሪ ጥያቄ የ6ወር ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም በማለትወደ ሥር ፍ/ቤት መዝገቡን መመለሱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 4/8/05 በመ.ቁ.07615 የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 16/12/2005 በመ.ቁ.133056 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የግራ ቀኙ በፍሬ ነገር ደረጃ ክርክራቸው ይቀጥሉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.341(1) መመለሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ. 98724

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ሙኒሽ ካፌ ድርጅት(ሙኒሽ ጀርመን ቤከር እና ካፌ) ጠበቃ ወርቁ ፉንታሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዳዊት ፀጋው - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ15/05/2005 ዓ.ም.አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ ከ24/01/2004 ዓ.ም.ጀምሮ በብር 900 የወር ደመወዝ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በባሬስታ የስራ መደብ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ከ30/04/2005 ዓ.ም. ጀምሮ የስራ ውላቸውን አላግባብ እንዳቋረጠ የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ ድርጅት ከሕገ ወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙትን እና ሌሎች ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ16/07/2005 ዓ.ም. በሰጠው መልስ ተከሳሽ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው ከ03/05/2005 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ዋናው መ/ቤት ተዛውረው እንዲሰሩ በ01/05/2005 በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጾላቸው እያለ በተዛወሩበት ቦታ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ በስራ ላይ ባለመገኘታቸው በሕጉ አግባብ መሆኑን ገልጾ ከዓመት ፈቃድ ክፍያ ብር 519 ውጪ ከሳሽ ጥያቄ ያቀረቡባቸው ሕገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸው የክፍያ ዓይነቶች ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ከሳሽ እንዲሰናበቱ የተደረገው በተዛወሩበት ቦታ በመደዳው ከአምስት የስራ ቀናት በላይ ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት እንደሆነ በማስረጃ በመረጋገጡ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸሙላቸው አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣

ሊከፈላቸው የሚገባው የ17.5 ቀን የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 525.00 ብቻ መሆኑን፣ተከሳሽ ተገቢውን የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ ለከሳሽ መስጠት የሚገባው መሆኑን፣ከሳሽ ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የጠየቁ ቢሆንም በእጃቸው የሚገኙ ንብረቶች ካሉ አስረክበው ክሊራንስ ከያዙ በኋላ ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጠይቀው የዘገየ ክፍያ ስለመኖሩ ስላላስረዱ ጥያቄአቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የተከሳሽን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ጭምር ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በከሳሽ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አሻሽሎ ሌላውን የውሳኔ ክፍል ሲያጸና ክፍያ የዘገየበትን እና የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትን በተመለከተ ግን ውሳኔውን ሽሮ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት የዓመት ዕረፍት ክፍያውን ተከሳሽ በሰባት ቀናት ውስጥ መክፈል የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ከሳሽ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያውን ለመክፈል አዘጋጅቶ ከሳሽ በራሱ ጥፋት ሳይወስድ ያዘገየ ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ እንዳልተከራከረ ገልጾ በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት ተከሳሽ ድርጅት ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት እና ለተከሳሽ ተጠብቆ የነበረውን የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመሰረዝ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስራ ውል ሲቋረጥ ለሰራተኛ ሊከፈል የሚገባው ክፍያ ዘገየ የሚባልበትን እና ዘገየ ለተባለ ክፍያ እስከ ሶስት ወር ደመወዝ የሚደርስ ክፍያ እንዲፈጸም የሚወሰንበትን አግባብ ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ከአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር በአንቀጽ 36 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ አሰሪው ለሰራተኛው መከፈል የሚገባውን ሂሳብ ካልከፈለ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ለሰራተኛው እስከ ሶስት ወር ለመድረስ የሚችል ደመወዙን ያህል አሰሪው እንዲከፍለው የስራ ክርክር ችሎት ሊወስን እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 38 የተመለከተ ሲሆን ክፍያውን በአዋጁ አንቀጽ 36 በተመለከተው የሰባት የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ መክፈል ያልተቻለው ከአሰሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት በተለይም በአንቀጽ 36 እንደተገለጸው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም

የሚፈለግበትን ማንኛውንም ሂሳብ የማወራረድ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት ሆኖ ከተገኘ አሰሪው በአንቀጽ 38 የተጠቀሰውን ክፍያ የመክፈል ግዴታ የሌለበት መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ክፍያ አዘግይቷል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የዓመት ዕረፍት ክፍያውን በሰባት ቀናት ውስጥ መክፈል የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያውን ለመክፈል አዘጋጅቶ ተጠሪ በራሱ ጥፋት ሳይወስድ ያዘገየ ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፎ አልተከራከረም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው በግልጽ ስለመጠየቃቸው ፍ/ቤቱ በውሳኔው ላይ አስፍሯል፡፡አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በተጠሪው የተጠየቁ ሌሎች መብቶችን እና የክፍያ ዓይነቶችን ክዶ የተከራከረ ሲሆን የዓመት ዕረፍት ክፍያውን በተመለከተ ግን በክፍያው መጠን ላይ ከመከራከር ውጪ ይህ ክፍያ የማይገባቸው ስለመሆኑ እና ይህ በአሰሪው የታመነው የክፍያ ዓይነትም በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ለሰራተኛው ሳይከፈል የቀረው ሰራተኛው ከአሰሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማንኛውንም ሂሳብ የማወራረድ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት በተጠሪ የተጠየቀውን ቅጣት የመክፈል ግዴታ የሌለበት ስለመሆኑ ገልጾ ያቀረበው ክርክር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ተጠሪው የሚፈለግበትን ንብረት የማስረከብ እና ሂሳብ የማወራረድ ግዴታ አልተወጣም የሚለውን የክርክር ነጥብ አመልካች በሰበር ደረጃ ከማቅረቡ በቀር በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ቢሆን የዚህ ዓይነት ክርክር አቅርቦ የነበረ ስለመሆኑም መዝገቡ አያመለክትም፡፡የታመነውን ክፍያ ያዘገየሁት ተጠሪው የበኩሉን ግዴታ ባለመወጣቱ ነው በሚል አመልካች በሁለቱ የስር ፍ/ቤቶች አንስቶ ያልተከራከረበትን ነጥብ ደግሞ በሰበር ደረጃ በመከራከሪያነት ማንሳቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329(1) ድንጋጌ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡አመልካች በዚህ ነጥብ ላይ በስር ፍ/ቤቶች ያቀረበው መከራከሪያ የለም በማለት ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን ክርክርም አመልካች አላስተባበለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ክፍያ ላዘገየበት በአዋጁ አንቀጽ 38 መሰረት የሶስት ወር ደመወዝ ለተጠሪው በቅጣት መልክ እንዲከፍል በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ  መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 07894 በ11/11/2005 ዓ.ም. የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 136017 በ10/06/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 92302

ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ርዕሶም እምባፍራሽ – ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ኢትዮ ቴሌኮም – ነ/ፈጅ አቶ ፈቃዱ ኃይሌ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን፣ ክርክሩም የተጀመረው የስር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ፍሬ ነገርም ባጭሩ፡- በተጠሪ ድርጅት ውስጥ ከ27/1/1973 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/03/1991 ዓ.ም ስሠራ ከቆየሁኝ በኋላ በስህተት በመሰናበቴ በ5/07/1997 ዓ.ም ወደ ሥራ እንድመለስ ተደርጐ እስከ ሐምሌ 6 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 4,955 ደመወዝ እየተከፈለኝ ለ24 ዓመታት ከ6 ወር ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ ተጠሪ የሥራ ውሌን ያለአግባብ ስላቋረጠ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲፈጸምለት እንዲወሰንለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ቀርቦ ለክሱ በሰጠው መልስ ከ27/1/1973 ዓ.ም እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ያለው የሥራ ስንብት ክፍያ በይርጋ የታገደ መሆኑን፤ ይህ መቃወሚያው የሚታለፍ ከሆነም እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ያለው የሥራ ስንብት የተከፈላቸው መሆኑን፣ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 16/10/2003 ዓ.ም ያለውን የሥራ ስንብት ክፍያ ደግሞ አመልካች እንዲወስዱ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ ስለቀሩ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የሌለው መሆኑንና ከሥራ የተሰናበቱትም በሕጉ አግባብ በተፈፀመ ቅነሳ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ይወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር እስከ 30/3/1991 ዓ.ም ድረስ ያለው የስንብት ክፍያ በይርጋ የሚታገድ መሆኑንና የሥራ ውሉም ሊቋረጥ የቻለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28/1/ (ሐ) መሠረት

በተፈጸመ ቅነሳ ምክንያት መሆኑን ጠቅሶ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ ከ5/7/1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለው የሥራ ስንብቱ ክፍያ ብር 13,763.88፣ በሠራተኞች ቅነሳ ጊዜ በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40(3) መሠረት ሊከፈል የሚገባ ክፍያ ብር 9,910፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 9,910፣ አመልካች ሥራ ሠርቶ ያልተከፈለው የ13 ቀናት ደሞዝ ብር 2,147.16 እና የ71 ቀናት የዓመት እረፍት ክፍያ ብር 11,726.83 በድምሩ ብር 47,457 ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ በአመልካች ይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የበታች ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት በማጽናት ወስኗል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይህንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ሲሆን፤ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች የሥራ ውሉ አላግባብ ተቋርጧል በማለት አቤቱታ ሲያቀርብ ቆይቶ በመጨረሻ ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑ ተረጋግጦ በ5/7/1997 ዓ.ም ወደ ቀድሞው ሥራው እንዲመለስ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 164(3) መሠረት የይርጋውን ጊዜ ማቋረጡ እየታወቀ፤ አመልካች ወደ ሥራ ለመመለስ እየተከራከረ በነበረበት ሁኔታ የስንብት ክፍያ በወቅቱ አልወሰደም ተብሎ ከ1973 –1991 ዓ.ም ያለው የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን፣ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን፤ እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ብቻ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሠራተኛውም ሆነ በአሠሪው የሚቀርብ ማናቸውም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ በአዋጅ አንቀጽ 162(4) ስር ተደንግጐ ይገኛል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች የሥራ ውል ከ30/03/1991 ዓ.ም ጀምሮ ለ6 ዓመት ከ3 ወር ተቋርጦ የቆየ ስለመሆኑ ግራቀኙን ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የሥራ ውሉም በወቅቱ ሊቋረጥ የቻለው በመንግሥት ውሣኔ መነሻነት ነው ከሚባል በቀር በተጠሪ ጥፋት ምክንያት ስለመሆኑ ወይም ያለአግባብ በተጠሪ የተቋረጠ መሆኑን አመልካች አላስረዳም፡፡ የሆነ ሆኖ የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት እለት ከ30/3/1991 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ጊዜ ውስጥ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄው ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካቹ በ5/7/1997 ዓ.ም እንደገና በመንግሥት መመሪያ ወደሥራ እንዲመለስ መደረጉም

አስቀድሞ በይርጋ የታገደውን የስንብት ክፍያ ጥያቄን (ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1991 ዓ.ም ያለውን የስንብት ክፍያ) ከአዋጁ አንቀጽ 164(3) ድንጋጌ ይዘት አኳያ የይርጋ ጊዜን ሊያቋርጥ የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም እንደድንጋጌው አነጋገር ተጠሪ የአመልካችን መብት በጽሑፍ አውቆለት ወይም በከፊል በራሱ የፈፀመለት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አመልካች አላስረዳም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከ30/3/1991 ዓ.ም በፊት ያለው የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ በአዋጁ መሠረት በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ እና አግባብነት ያላቸው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24120 በ18/6/2005 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 132709 በ25/10/05 ዓ.ም እንዲፀና የተደረገበት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ

የሰ/መ/ቁ. 99026

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ አብርሃም ታደለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጥቁር አባይ ትራንስፖርት ኃላ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረብም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139116 ታህሳስ 4 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ቀርቦ፤ተከሳሽ (ተጠሪ) ከህግ አግባብ ውጭ የስራ ውሌን በማቋረጥ ከስራ ያሰናበተኝ በመሆኑ፤ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ አመልካች ለአንድ ወር በህክምና ላይ ከቆየበኂላ ወደ ስራ ባለመመለሱ የካቲት 21 ቀን 2005 ዓ/ም ማስታወቂያ አውጥተናል፡፡ከዚያም ከሳሽ ሪፖርት ካደረጉ በኂላ ቀላል ስራ ካልተሰጠኝ የሹፌርነት ስራ አልሠራም በማለት ለከሳሽ በማሳወቃቸው ከስራ በመቅረታቸው ከስራ የተሰናበት ስለሆነ ስንብቱ በህግ አግባብ የተደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ በስራ ላይ እያለ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ታክሞ በተሰጠው ማስረጃ ጉዳቱ መኪና ማሽከርከር እንደማይከለክለው ተገልጿል፡፡ሆኖም ከሳሽ በህዳር ወር 2005 ዓ/ም መኪና ጅቡቲ ይዞ ከሄደ በኋላ ባደረበት ህመም ምክንያት መኪናውን ለመመለስ ባለመቻሉ መኪናው ሌላ ሹፌር ሄዶ እንዲያመጣ የተደረገ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ድርጅት የህክምና ተቋም የሆነው ከሳሽ በአከርካሪ ዲስክና በእጅ ላይ ከባድ ጉዳት የደረሰበት ስለሆነ ቀለል ያለ ስራ ላይ እንዲመደቡ የሚገልፅ ማስረጃ ሰጥቷቸዋል፡፡ የደጃዝማች ባልቻ የሰጠው ማስረጃም ይህንኑ የተከሳሹን የጤንነት ችግር የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ከሳሽ በህመም ላይ መሆናቸውንና ጤንነታቸው ስላልተሻሻለ ህክምና በመከታተል ላይ ያሉ መሆናቸውን ተከሳሽ እያወቀ ቀላል ስራ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ከስራ ያሰናበተ መሆኑን የሚያሳይ ሰለሆነ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተከሳሽ ለከሳሽ የካሳ ክፍያና የሁለት ወር የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጪ (አመልካች) የይግባኝ ባይ ድርጅት ጥር 29 ቀን 2005 ዓ.ም የህክምና ማስረጃ ከሰጣቸው በኋላ ለሶስት ሳምንታት ያህል ለአሰሪያቸው (ይግባኝ ባይ)ሳያቀርቡና ስራ ሳይገቡ ቆይተው፤የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ/ም የህክምና ማስረጃውን አቅርበዋል፡፡ይህም መልስ ሰጪ የተሰጣቸው የህክምና ፍቃድ ካለቀ በኋላ ለሃያ አንድ ቀናት ከስራ ቦታ የቀረ መሆኑን ስለሚያሳይ ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጭ የሰራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከደረሰብኝ የጤንነት ችግር እንዳላገገምኩ፤ለተጠሪ አሳውቄዋለሁ፡፡አንድ የጤንነት ችግርና ህመም ያጋጠመው ሰራተኛ ፤አሰሪው ከስራ ከማሰናበቱ በፊት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር377/96 አንቀጽ 86 ነው፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን ለጤነኛ ሰራተኞች ተፈፃሚነት ያለውን እና በእኔ ጉዳይ አግባብነት የሌለውን አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በመጥቀስ የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አመልካች የህክምና ፍቃዱ ካለቀ በኋላ ሃያ ቀናቶች ወደ ስራ ቦታው ያልመጣ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ከስራ ያሰናበተው በሕግ አግባብ ነው፡፡ በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በስራ ላይ ጉዳት የደረሰበት መሆኑንና በዚህ ምክንያት የጤና ችግር ስለገጠመው የአንድ ወር የህመም ፈቃድ በአሰሪው(ተጠሪ) ተሰጥቶት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ አመልካች የተሰጠው የሕመም ፈቃድ እንዳበቃ ወደ ስራ ቦታ ባለመምጣቱ ተጠሪ ማስታወቂያ ማውጣቱንና አመልካችም ማስታወቂያው በወጣበት ቀን ማግስት ከስራ ቦታ በመገኘት ከህመሙ እንዳላገገመ ገልፆ፣ አመልካች ይሰራው የነበረውን የአሽከርካሪነት ስራ ለመስራት የማይችል በመሆኑ ቀላል ስራ ላይ እንዲመደብ በመግለፅ የተጠሪ የጤና ተቋም የሰጠውን ማስረጃ እንዳቀረበ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ፣ አመልካችን እንደማንኛው ጤነኛ ሰራተኛ በመቅጠር የተሰጠህ የህመም ፈቃድ ካለቀ በኋላ በተከታታይ አምስት ቀናት በስራ ቦታ አልተገኘህም በሚል ምክንያት የሚያባርርበት የሕግ መሰረት የለውም፡፡

አመልካች የደረሰበት ጉዳት መኪና ማሽከርከር የማይከለክለው መሆኑ በዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል በተሰጠ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በማለት ሲሆን፣ አመልካች ጅቡቲ እያሽከረከረ የወሰደውን መኪና መመለስ ባለመቻሉ ምክንያት ሌላ ሹፌር ተመድቦ መኪናውን ከጅቡቲ ያመጣ መሆኑ፣ አመልካችም የህመም ፈቃድ የተሰጠው መሆኑና አመልካች ያጋጠመው የአከርካሪ ዲስክ እና እጅ ላይ በመሆኑ መኪና ማሽከርከር እንደማይችል ተጠሪ በኃላፊነት የሚያስተዳድረው ክሊኒክ ጭምር በማረጋገጥ ማስረጃ እንደሰጠ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ፣ አመልካች ከሙሉ ደመወዝ ጋር የተሰጠውን የአንድ ወር የህመም ፈቃድ ጨርሶ ከህመሙ አገግሞ ስራ ቦታ መገኘት ካልቻለ፣ ተጠሪ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 85 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ተጨማሪ የህመም ፈቃድ መስጠትና በአንቀፅ 86 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ግማሽ ደመወዙን በመክፈል ተጠሪ ከህመሙ እንዲያገግም የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት ሲገባው፣ የአመልካችንየስራ ውል መሰረዙ አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ መሰረት ያላደረገ ሕገ ወጥ ተግባር ነው፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት፣ በስራ ላይ የደረሰበትን አደጋ አሰሪው አውቆ የአንድ ወር የህመም ፈቃድ የሰጠው ሰራተኛ ከህመሙ አገግሞ ስራ ቦታ ላይ ሳይገኝ በሚቀርበት ሁኔታ ተፈፃሚነት ያላቸው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 85 እና አንቀፅ 86 ድንጋጌዎች መሆናቸውን ሳያገናዝብ፣ አመልካችን እንደማናቸውም ጤነኛ ሰራተኛ በመቁጠር፣ የሕመም ፈቃድ ካለቀ በኂላ በተከታታይ ከአምስት ቀን በላይ ስለቀረ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና

መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን የስራ ውል ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139116 ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ምየሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09329 ሐምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 95392

ግንቦት 06 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

አሊ መሀመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የእንግሊዝ ሕፃናት አድን ድርጅት ጠበቃ አቶ አይሸሽም መድፉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሽመልስ አለሙ አልቀረቡም

መዝገብን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአሳይታ ወረዳ ፍርድ ቤትና የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ጊዜው ከመድረሱ በፊት መቋረጡ የሚያስከትለውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1.የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ተጠሪ አመልካች በጊዜያዊነት የቀጠረው መሆኑንና የስራ ውሉም የሚጠናቀቀው ነሀሴ 25 ቀን 2004 ዓ.ም መሆኑን ገልፆ፤ የሥራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሳይደርስና በቂ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ ተከሳሽ (አመልካች)የሥራ ውሉን ያቋረጠው ስለሆነ የ6 ወር ደመወዝ የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣የአል,ጋ፣አበልና እና ሌሎች ወጪዎች ሊከፈሉኝ ይገባል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡አመልካች የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል መሆኑንና የሥራ ወሉን ያቋረጠውም ማስጠንቀቂያ በመስጠት መሆኑን ግልፆ፤ ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ከሳሽ (ተጠሪ)ያቀረበው የጥቅማ ጥቅም እና ሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች የአስራ ሁለት ቀናት

ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራ ውሉን ያቋረጠና የሥራ ውሉን ያቋረጠው በውሉ የተገለፀው ጊዜ ማለትም ነሀሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ከመድረሱ በፊት በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ የስድስት ወር ደመወዝ ፣የካሳ ክፍያ፣የሶስት ወር ደመወዝ ክፍያ ለዘገየበት፣የማስጠንቀቂያ ክፍያና ሌሎች የጥቅማ ጥቅምና አበል ክፍያዎች በድምሩ ብር 107,823.73 (አንድ መቶ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰባ ሶስት ሳንቲም) አመልካች ለተከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ስጥቷል ።

2.አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል።የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል።አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ሀምሌ 25 ቀን 2004 ዓ.ም ነው። ከዚህ በፊት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጽፈናል።እንዲሁም ክፍያዎችን ፈጽመናል። በሌላ በኩል በማስረጃ ያልተረጋገጠ የአበልና እና የአልጋ ክፍያ ተወስኖብናል ስለዚህ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል ሆኖ እያለ ተጠሪ ከጠየቀው በላይ ገንዘብ በላይ እንድንከፍል የተሰጠው  ውሳኔ መስረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል።ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው ከህግ ውጭና የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች የመልስ መልስ አላቀረበም።

3.ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ለሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከህግ ውጭ  ያሰናበተው ስለሆነ የስድስር ወር ደመወዝ የካሳ፡ ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች እንዲከፍል በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ?የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

4. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪን ለተወሰነ ጊዜ የቀጠረው መሆኑንና የሥራ ውሉ የሚጠናቀቀው ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም እንደነበር፣ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ገልጿል። አመልካች በስራ ውሉ የተገለፀው ጊዜ ሣይደርስና በቂ ምክንያት ሣይኖረው ሀምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የተጠሪን የሥራ ውል የአስራ ሁለት ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ያቋረጠው መሆኑን የወረዳው ፍርድ ቤት አረጋግጧል።ስለሆነም አመልካች ከነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በፊት ውሉን ለማቋረጥ የሚያስገድደው ምክንያት ወይም በተጠሪ በኩል ያልተፈፀመ ጥፋት ሣይኖርና ለተጠሪ

የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠው የስራ ውሉን ማቋረጡ ከሕግ ውጭ ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5. አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል በውሉ የተገለፀው ጊዜ ከመድረሱ በፊት ያለበቂ ምክንያት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሣይሰጥ አቋርጧል ከተባለ ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈል የሚገባው ክፍያ ምን መሆን አለበት የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ የተጠሪ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ጊዜ የቀረው አንድ ወር ብቻ እንደነበረ ከግራ ቀኙ ክርክርና የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ይህ ከሆነ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(4)/ሀ መሠረት እንዲከፍል የሚገደደው ውሉ እስከ ሚቋረጥበት ድረስ ያለውና ተጠሪ ያቀረቡት የአንድ ወር ደመወዝ ማለትም ብር 8052.73/ስምንት ሺ ሃምሣ ሁለት ብር ከሰባ ሶስት ሣንቲም/ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ውሉ ነሐሴ 24 ቀን 2004 ዓ.ም የሚጠናቀቅ መሆኑን ሣያገናዝቡ የበታች ፍርድ ቤቶች የስድስት ወር ደመወዝ ካሣ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. አመልካች የተጠሪ የሥራ ውል ከሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ ከአንድ ወር በፊት የሥራ ውሉን አቋርጧል፡፡በዚህ ሁኔታ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው የአንድ ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንጂ የሶስት ወር ደመወዝ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እንዲከፍል የሚገደድበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ክፍያ ለዘገየበት በማለት የሶስት ወር ደመወዝ አመልካች እንዲከፍል የወሰነው የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ሀምሌ 24 ቀን 2004 ዓ.ም በፊት ክፍያ ከፍለህ አላጠናቀክም በማለት ነው፡፡ ሆኖም አሠሪው ክፍያ እንዲከፍል የሚገደደው የሥራ ውሉ ከተቋረጠ በሰባት ቀናት ውስጥ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 36 የተደነገገ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ክፍያ ለዘገየበት በማለት አመልካች ለተጠሪ የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

7.የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ በመስክ ሥራ በሚቆይበት ወቅት የሚከፍለው የአልጋ ክፍያ ብር 6417( ስድስት ሺ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር)እንደዚሁም የሃያ ቀን የውሎ አበል ብር 2970 (ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የክፍያ ውሳኔ በማሻሻል ፤አመልካች ለተጠሪ የአንድ ወር ደመወዝ የካሣ ክፍያ ፤የአንድ ወር ደመወዝ

የማስጠንቀቂያ ክፍያ እና ለአልጋ ክፍያና የውሎ አበል በጠቅላላው በድምሩ ብር 25,492.16 /ሃያ አምስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም /ሊከፍል ይገባዋል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1.የአፋር ክልል አሳኢታ ወረዳ ፍርድ ቤትና የአወስራሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2. የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 107,823 .73 (አንድ መቶ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰባሶስት ሣንቲም) እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

3.አመልካች ለተጠሪ ብር 25,492.16 /ሃያ አምስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከአሥራ ስድስት ሣንቲም) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

4.በዚህ ፍርድ ቤት በ 23/04/2006 ዓ.ም  የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡

5.በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 92423

ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ የሺሐረግ ታደሰ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአምቦ ማዕድን ውሃ አ/ማ አልቀረበም፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130114 ግንቦት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያዘው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ተቀጥሬ በተለያየ የሥራ መደብ አገልግያለሁ፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ እየሠራሁበት ባለው የፋይናሻል ኮንትሮል የሥራ መደብ ከአዲስ አበባ ወደ ሰንቀሌ ተዛውሬ እንድሠራ ደብዳቤ ፅፎልኛል፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ፈቃድና ተከሳሽ ጋር ውል ተዋውዬ በደቡብ አፍሪካ ዩኒቨርሲቲ ስከታተለው የነበረው የማስተርስ ትምህርት የመመረቂያ ጽሑፍ መስከረም 2003 ዓ.ም በፊት እንዳስረክብ ዩኒቨርሲቲው ያዘዘ መሆኑን ገልጩ ትምህርቴን ለሶስት ወር ዝውውሩን እንዲያዘገይልኝ ጠይቀው ተከሳሽ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ የመጀመሪያውን አማራጭ እንቢተኛ ከሆነ የዓመት ረፍቴ እንዲሰጠኝና ትምህርቴን እንዳጠናቅቅ በፅሑፍ ጠይቄለሁ፡፡ ከሳሽ ያልተጠቀምኩበት አንድ መቶ ሃያ ቀናት ረፍት አለኝ፡፡ ተከሳሽ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ላቀረብኩት ጥያቄ መልስ ባለመስጠቱ ዝምታው ጥያቄውን እንደተቀበለው በመውሰድ ትምህርቴን በመከታተል ላይ እያለሁ ከአምስት

ቀናት በላይ ከሥራ ቀርተሻል በማለት ትምህርት ስጀምር የተዋዋለውን ውል የሚቃረን ህገ ወጥ እርምጃ የወሰደ በመሆኑ ደመወዜን ከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡

2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቦ በብይን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የመከላከያ መልሱን በተመለከተ አመልካች ትምህርቷን እስክታጠናቅቅ ዝውውሩ እንዲዘገይላት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ተገልፆላታል፡፡ የዓመት ፈቃድ በተመለከተ፣ ከሳሽ ፈቃድ የምትወጣበት ጊዜ በዕቅድ የተያዘው እንደአውሮፖዊያን አቆጣጠር በዲሴንበር 2010 ሆኖ እያለ፣ ከዚያ በፊት የዓመት እረፍት እንዲሰጣት ያቀረበችው ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት፣ ከሥራዋ ለአምስት ቀንየቀረች በመሆኑ፣ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የመመረቂያ ፅሑፏን ለማጠናቀቅ የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በፅሑፍ ጥያቄ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ /ተከሳሽ/ ምላሽ ሣይሰጥ የቀረ መሆኑን በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ የተከሳሽን ዝምታ የዓመት ፈቃድ ጥያቄውን እንደተቀበለው በመቁጠር ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ከሥራ ቦታ ሣትገኝ መቅረቷ ያለ ምክንያት እንደቀረች የሚያስቆጥራት አይደለም፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ከህግ ውጭ በመሆኑ የስድስት ወር ደመወዟን ከፍሎ ወደ ሥራ ይመልሳት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት፣ ከሥራ ቦታ ያልተገኘች መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ የሥራ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

4. አመልካች ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ትምህርት የጨረስኩት ተጠሪ ጋር ውል ተዋውዬ ትምህርቴን ተከታትዬ ባላጠናቅቅ ለትምህርት ያወጣውን ወጭ ለመክፈል ተስማምቼ ነው፡፡ አመልካች የዓመት ፈቃድ እንዲሰጠኝ ስጠይቅ የመመረቂያ ፅሑፍ እንዳጠናቅቅ ዩኒቨርሲቲው ያስቀመጠውን ቀነ ገደብ በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠሪ ለጥያቄው መልስ ሣይሰጥ ዝም ማለቱ እንደተቀበለው መቁጠር እንደ ጥፋት ሊያዝብኝ የሚገባ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሰበር እንዲታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ የዓመት ፈቃድ የሚሰጥበት ሥርዓት ሣይሟላና በግልፅ ፈቃድ ሣይሰጣት ወደ ተዛወረችበት ቦታ ያልሄደች በመሆኑ፣ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27/1/ለ መሠረት ከሥራ መሰናበቷ ህጋዊ ነው በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበታት በህግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በዚህ መዝገብ የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችን መሠረታዊ ባህሪና ይዘት እንደዚሁም በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነትና አንፃራዊ ግዴታ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ፈቃድ ሰጥቶና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የድጋፍ ደብዳቤ ፅፎላት፣ ከተጠሪ ጋር ውል ተዋውላ የማስተርስ ትምህርት ስትከታተል እንደነበርና፣ ተጠሪ አመልካችን ከአዲስ አበባ ወደ ስንቀሌ ሲያዛውራት፣ አመልካች የመመረቂያ ፅሑፏን ለዩንቨርሲቲው የምታስረክብበት የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ ጋር ተገጣጣሚነት እንዳለው በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በተጠሪ ፈቃድና ስምምነት የጀመረችው ትምህርት እስክታጠናቅቅ ዝውውሩ እንዲዘገይላት ተጠሪ ጠይቃ ተጠሪ ጥያቄዋን የማይቀበለው መሆኑን እንዳሳወቃት ተረጋግጧል፡፡

7. በተጠሪ ድጋፍና ፈቃድ ለሶስት ዓመት ያህል ስትከታተለው የነበረው የማስተርስ ትምህርት ለማጠናቀቅ ለተጠሪ ያቀረበችው የመጀመሪያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘው አመልካች፣ ዩንቨርስቲው ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ የመመረቂያ ፅሑፏን ለማቅረብና ትምህርቷን ለማጠናቀቅ እንድትችል ተጠሪ ያልተጠቀመችበትን የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣት በፅሑፍ ጠይቃለች፡፡ ተጠሪ በዚህ አመልካች ላቀረበችው የዓመት ፈቃድ ጥያቄ በግልፅ አሉታዊ ምላሽ እንዳልሰጠ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም ያለበት አመልካችና ተጠሪ በሥራ ውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ብቻ ሣይሆን የአመልካችን የማስተርስ ትምህርት በተመለከተ፣ ከተጠሪ የሚፈለገውን ድጋፍ፣ ትብብርና እርዳታ አመልካች ትምህርቷን ስትከታተልና ትምህርቷን ተከታትላ ካጠናቀቀች በኋላ ያለባትን ግዴታና ኃላፊነት የሚወሰን ሌላ ልዩና ተጨማሪ የውል ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ተጠሪ ክዶ አልተከራከረም፡፡ በአንፃሩ አመልካች የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ዕውቅና በሰጠውና ከተጠሪ ጋር ባደረገችው ውል መሠረት ትምህርቷን ስትከታተል የቆየች መሆኑ ግራቀኙ በበታች ፍርድ ቤቶች እና ግራቀኙ በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር ለመረዳት ችለናል፡፡

8. አመልካች የዓመት ፈቃድ ተሰጥቷት፣ በተጠሪ ድጋፍ ስትከታተለው የነበረውን የማስተርስ ትምህርት ለማጠናቀቅ በፅሑፍና በግልፅ ላቀረበችው ጥያቄ ተጠሪ በግልፅ የሰጠው አሉታዊ መልስ አለመኖሩ፣ ከላይ ከገለፅነው አመልካችና ተጠሪ መካከል ስለአመልካች የማስተርስ ትምህርት ከተደረገው ልዩና ተጨማሪ ውል አንፃር መታየት

የሚገባው ነው። ተጠሪ አመልካች ለደቡብ አፍሪካ ዩንቨርስቲ ከፍተኛ ክፍያ እየተከፈለ ስትከታተል የቆየችውና የማስተርስ ትምህርቷን በአግባቡ እንድታጠናቅቅ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ እና ትብብር ያደርጋል፣ አመልካችም ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የምታቀርበውን ጥያቄ በቅንነት በመመልከት ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል። ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ በመተማመንና በቅንነት ውሉን ይፈፅማሉ ተብለው ሊገመቱና በዚሁ መንገድ ትርጉም ሊሰጥ እንደሚገባው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1732 ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የተጠሪን ግልፅ የሆነ አሉታዊ ምላሽ ለመስጠት፣ አመልካች ጥያቄዎን እንደተቀበላት በመቁጠር ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የግድ አስፈላጊ የሆነውን የመመረቂያ ፅሑፍ የማዘጋጀት፣ በሥራ ገበታዋ ላይ ሣትገኝ መቅረቷ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ1/ለ/ መሠረት ያለበቂ ምክንያት ከሥራ ቦታ እንደቀረች የሚያስቆጥር ሆኖ አላገኘነውም።

9. በአንፃሩ አመልካች ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ያልተጠቀመችበት የዓመት ፈቃድ እንዲሰጣትና፣ የዓመት ፈቃዷን የምትፈልገው ዩኒቨርሲቲው ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ የመመረቂያ ፅሑፏን አጠናቅቃ ለማስረከብ እንደሆነ በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 84 መሠረት ለተጠሪ አሳውቃለች። ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረገው የሥልጠናና የትምህርት ውል መሠረት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት የትምህርት ፈቃድ በመስጠት አመልካች ትምህርቷን እንድታጠናቅቅ የመደገፍ ግዴታ አለበት። አመልካች ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ልዩ ፈቃድ ተጠሪ እንዲሰጣት ሣይሆን የዓመት ፈቃዷን በመጠቀም ትምህርቷን ለማጠናቀቅ ላቀረበችው ጥያቄ ግልፅ ምላሽ ሣይሰጥ አመልካች ከስራ ገበታዋ አልተገኘችም በማለት የሥራ ውሉን ማቋረጡ፣ ከላይ የገለፅናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚቃረንና የሕግ መሠረት የሌለው ተግባር ነው። በሌላ በኩል በዚህ መዝገብ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የአሠሪና ሠራተኛ እና የትምህርትና ሥልጠና ውል ግንኙነትና አመልካች ከሥራ የቀረችበት ምክንያትና ሁኔታ ተጠሪ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የወሰደው እርምጃ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 37778፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 37402 እና በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሰጠባቸው ጉዳዮች የተለየ በመሆኑ፣ ተጠሪ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም። በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል።

ውሣኔ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 130114 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበታት ከሕግ ውጭ ነው በማለት በመዝገብ ቁጥር 57393 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
- ተጠሪ የአንድ ዓመት ደመወዝ በመክፈል አመልካችን ወደ ሥራ ሊመልሳት ይገባል በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡
- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 93511

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ደረሰ ወርቄ ቀረቡ፤

ተጠሪ፡- በርሔ ሐጎስ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ጠበቃ ነገሠ ጋሹ ቀረቡ፤

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በቶንጎ-ቤጊ-ጊዳሚ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ከ10/02/2003 ዓ.ም ጀምሮ በክሊኒካል ነርስ የስራ መደብ በወር ብር 2,346.00 ደመወዝ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበረ፣ ኘሮጀክቱ በመጠናቀቁ ተከሳሽ ድርጅት ሌሎች ሰራተኞችን በሙሉ ወደ ሌላ ቦታ ሲያዛውር ከሳሽን በባዶ ካምኘ ማስቀመጡ አግባብ እንዳልሆነ በመግለጽ ከሳሽ በ17/08/2004 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ለድርጅቱ በማሳወቃቸው ድርጅቱ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንደሰጣቸው፣ ከሳሽ ማስጠንቀቂያውን በመቃወም የጽሁፍ ምላሽ በመስጠታቸው ተከሳሽ ድርጅት በ17/09/2004 ዓ.ም የስራ ውላቸውን እንዳቋረጠባቸው የሚገልጽ ሆኖ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ ተከሳሽ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽምላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ13/10/2004 ዓ.ም በተዘጋጀ መልስ የቶንጎ-ቤጊ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ስራ ተጠናቆ ሰራተኞች ወደ ጊዳሚ-ሙጊ የመንገድ ስራ ኘሮጀክት ሲዛወሩ ከሳሽም አብረው የተዛወሩ መሆኑን፣ በወቅቱ ከሳሽ ዝውውሩን ተቀብለው ጊዳሚ-ሙጊ በሚገኘው የተከሳሽ ድርጅት ካምኘ ውስጥ ስራ ጀምረው የነበረ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በዚህን ጊዜ ክሊኒኩን እየዘጉ ሌላ ቦታ በመዋላቸው አደጋና ጉዳት ለሚደርስባቸው ሰራተኞች የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ የሚሰጥ ባለሙያ ጠፍቶ የነበረ መሆኑን፣ ከሳሽ ለከፊሉ ሰራተኛ ህክምና በመስጠት እና ለከፊሉ

ደግሞ በመከልከል በአንድ ድርጅት ሰራተኞች መካከል ልዩነትን እና መከፋፈልን የፈጠሩ መሆኑን፣ በመጨረሻም ከሳሽ ወደ ዋናው መስሪያ ቤት እንዲላኩ እና ከፕሮጀክቱም እንዲሰናበቱ በጠየቁት መሰረት የፕሮጀክቱን ክሊኒክ ከዘጉበት እና ስራ አልሰራም ብለው ካቆሙበት ከ12/08/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የተከሳሽን አንድ ምስክር ከሰማ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ በ29/08/2004 ዓ.ም የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ በመቃወም ለተከሳሽ ድርጅት በ01/09/2004 ዓ.ም የጻፉት ደብዳቤ ድርጅቱ "...መጀመሪያ ወደ ቀጠረኝ መስሪያ ቤት መላክ ይህ የማይሆን ከሆነ ማሰናበት ይችላል፡፡" የሚል አባባል ያዘለ ቢሆንም የደብዳቤው አጠቃላይ ይዘት ከሳሽ መሰናበት ስለምፈልግ አሰናብቱኝ ማለታቸውን የሚያመለክት አይደለም በማለት ይህንን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ተከሳሽ ድርጅት የወሰደው የስንብት እርምጃ ሕገወጥ ነው፤ በመሆኑም ሕገወጥ የስራ ስንብት እርምጃ የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍልና የምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በስር ተከሳሽ አቅራቢነት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ ፕሮጀክቱ በመጠናቀቁ ተከሳሽ ድርጅት ሌሎች ሰራተኞችን በሙሉ ወደ ሌላ ቦታ ሲያዛውር እኔን በባዶ ካምፕ አስቀምጦኛል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የፕሮጀክቱ ስራ አለመጠናቀቁን ራሳቸው በ20/06/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ መግለጻቸውን፣ በቅጥር ውላቸው ተራ ቁጥር 15 በተመለከተው መሰረት ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን አዛውሮ የማሰራት መብት ያለው ሆኖ እያለ ከሳሽ በ17/08/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ አዲስ ድርድር እስካላደረግን ድረስ በሰራተኛው ላይ ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ አይደለሁም በማለት መግለጻቸው ክሊኒኩን ዘግተው ያለስራ የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እንደነበረ በተከሳሽ ድርጅት የቀረበውን ክርክር የሚያጠናክር መሆኑን፣ በመጨረሻም ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ ማኔጅመንቱ ጥያቄዬን የመመለስ ብቃት የለውም፣ ወደቀጠረኝ መ/ቤት መመለስ አለብኝ፣ ይህ ካልሆነ ልሰናበት ይገባል በማለት መግለጻቸው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከራሳቸው በቀረበ ጥያቄ መሰረት እንደሆነ የሚያመለክት መሆኑን ገልጾ የስንብቱን ሕገወጥነት በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሲሽር የ43 ቀን ደመወዝ፣ የትርፍ ሰዓት ማካካሻ አበል፣ የጉዞ አበል እና ክፍያ ለዘገየበት የተወሰነውን ገንዘብ በተመለከተ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ የጻፉትን ደብዳቤ ይዘት መሰረት በማድረግ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በአግባቡ የሰጠውን ውሳኔ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ደብዳቤውን በአግባቡ ሳይተረጉም የሰጠው ውሳኔ ከሕግ ውጪ ነው

በማለት አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የይ/ሰሚው ፍ/ቤት ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተቋቋመ አንድ የስራ ውል በሰራተኛው አነሳሽነት እንደነገሩ አግባብ በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ 31 እና 32 ስር ተመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የሚከራከረውም አመልካችን ከስራ ያሰናበትኩት በእነዚሁ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል ነው በማለት መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ የጻፉት ደብዳቤ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የስራ ውል ለማቋረጥ ተነሳስተው በአዋጁ አንቀጽ 31 ወይም 32 በተመለከተው መሰረት የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መወሰናቸውን የገለጹበት ሳይሆን በ29/08/2004 ዓ.ም የተሰጣቸውን የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመቃወም ለድርጅቱ ምላሽ የሰጡበት መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች በዚሁ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ በጻፉት ደብዳቤ ላይ ተጠሪ ድርጅት በአመልካች ደብዳቤ ላይ የተጠየቀውን ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን መፍትሔ እንዲሰጣቸው፣ ይህን የማያደርግ ከሆነ ግን ማሰናበት እንደሚችል የገለጹት ሀሳብም ቢሆን ተጠሪ ሌሎች መፍትሔዎችን መስጠቱን ትቶ ማሰናበቱን የሚመርጥ ከሆነ የማሰናበት እርምጃውን ከሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ጋር መቀበል እንደሚገባው መጠየቃቸውን የሚጠቁም ነው ከሚባል በቀር በራሳቸው አነሳሽነት የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መፈለጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል በይ/ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንደሰፈረው አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የተጠሪን ጥቅም የሚጎዱ የተለያዩ ድርጊቶችን ይፈጽሙ የነበረ ስለመሆኑ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የተለያዩ የክርክር ነጥቦችን ያቀረበ መሆኑን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም በመሰረቱ ተጠሪ አመልካችን ከስራ ያሰናበተው በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ በጻፉት ደብዳቤ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ ጠይቀዋል በማለት እንጂ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ የሚያስችል ጥፋት ፈጽመዋል በማለት ባለመሆኑ አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የፈጸሙት ጥፋት መኖር አለመኖሩ እና ካለም መጠኑ እና የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት በዚህ መዝገብ በተያዘው ክርክር ላይ ሊመረመር የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ከሳሽ በ01/09/2004 ዓ.ም ለተከሳሽ በጻፉት ደብዳቤ ማኔጅመንቱ ጥያቄዬን የመመለስ ብቃት የለውም፣ ወደቀጠረኝ መ/ቤት መመለስ አለብኝ፣ ይህ ካልሆነ ልሰናበት ይገባል በማለት

መግለጻቸው የስራ ውሉ የተቋረጠው ከራሳቸው በቀረበ ጥያቄ መሰረት እንደሆነ የሚያመለክት ነው በማለት ለደረሰበት ድምዳሜ አመልካች በስራው ላይ በነበሩበት ጊዜ የተጠሪን ጥቅም የሚጎዱ የተለያዩ ድርጊቶችን ይፈጽሙ ነበር የመባሉን ጉዳይ በተጨማሪ ምክንያትነት በመቀበል በውሳኔው ላይ ማስፈሩ ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት የተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በ01/09/2004 ዓ.ም ለተጠሪ የጻፉት ደብዳቤ የስራ ውላቸውን ለማቋረጥ መፈለጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው በማለት ይ/ሰሚው ፌ/ከ/ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ይህንኑ ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ሽሮ የስራ ስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የደብዳቤውን እና የግራ ቀኙን አጠቃላይ የክርክር ይዘት ያላገናዘበ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት በመ/ቁ 78899 በ29/08/2005 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 135599 በ26/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስራ ስንብት እርምጃው ሕገወጥ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽም እና የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 78899 በ29/08/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዘ/ቢ

የሰ/መ/ቁ. 93532

ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-አቶ በኃይሉ ደቦጭ አንበሴ......... ጠበቃ ገ/እግዚአብሄር ኪዳኔ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ኢትዮጵያ ገብራት ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተወካይ አቶ ግርማ ሙለታ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ20/05/2003 ዓ.ም.ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት በወር በብር 1,400 ደመወዝ ተቀጥረው በመስራት ላይ እያሉ ተከሳሽ ድርጅት ከ13/02/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ካለክፍያ እና ካለስራ እንዳስቀመጣቸው የሚገልጽ ሆኖተከሳሽ ድርጅት የሰሩበትን የ4 ወር ደመወዝ እና ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነ ደግሞ የ4ወር ውዝፍ ደመወዝ፣የስራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የዓመት ዕረፍት ክፍያ እና ክፍያ ለዘገየበት ተገቢውን ክፍያ እንዲፈጽም ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሳሽን ደመወዝም ሆነ ስራ እንዳልከለከላቸው፣ከሳሽ የነሐሴ እና የመስከረም ደመወዝ ሳይቀበሉ የቀሩት ከጂቡቲ ዕቃ ጭነው ወደ ክልል ከተሞች ስለሚያዘዋውሩ በዚህ ሳቢያ በተፈጠረው ክፍተት እና በኋላም የሚፈለግባቸውን የ180 ሊትር ነዳጅ ጉድለት ገቢ እንዲያደርጉ በ14/02/2004 ዓ.ም. በተጻፈ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ስላልነበሩ እንደሆነ፣ከሳሽ የያዙት ተሽከርካሪ ችግር እንዳለበት በ12/11/2004 ዓ.ም.ባመለከቱት መሰረት ተሽከርካሪው ለጥገና ሲቆም ከሳሽ ጥገናውን መከታተል ሲገባቸው ትተው ወደ ቤታቸው እንደሄዱ፣ከሳሽ ከ14/02/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በራሳቸው ምክንያት ከስራ የቀሩ ስለሆነ ላልሰሩት ስራ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው፣ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከስራ ባላሰናበተበት ሁኔታ የስንብት እና ተያያዥ ክፍያዎችን ለመክፈል እንደማይገደድ እና ከሳሽ የነሐሴ እና የመስከረም ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ከፈለጉ ስራ ሊቀጥሉ እንደሚችሉ በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ከሰማ በኋላ ሁለቱም ወገኖች ምስክሮቻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ በሰጠው ቀጠሮ ተከሳሽ በትዕዛዙ መሰረት ባለመፈጸሙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 199(1) መሰረት መብቱን በማለፍ በከሳሽ በኩል የቀረቡትን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ከዚህ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ የስራ ውሉ ተቋርጦብኛል በማለት ያቀረቡት ክስ ባለመኖሩ የስራ ስንብት እና ተያያዥ ክፍያዎች እንዲፈጸሙላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ስነ ስርዓታዊ አግባብ እንደሌለው፣ከሳሽ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም. ወደ ድርጅቱ ግቢ እንዳይገቡ በድርጅቱ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸውን በምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም የጥበቃ ሰራተኞቹ ክልከላውን የፈጸሙት ማን በሚባል ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ ከሳሽ እንዳላስረዱ በዝርዝር ገልጾ ተከሳሽ ድርጅት የነሐሴ እና የመስከረም ወር እንዲሁም ከሳሽ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን ባስረዱት መሰረት ከጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም. ደመወዝ ውስጥ እስከ ማስጠንቀቂያው ቀን ማለትም እስከ ጥቅምት 21 ቀን ድረስ ያለውን ደመወዝ ከፍሎ ለከሳሽ ስራ እና የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ወደስራ ገበታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸው እና የስርፍ/ቤት የስራ ውሉ ያልተቋረጠ መሆኑን በማረጋገጥ ለከሳሽ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው መወሰኑ በተረጋገጠበት፣ነገር ግን አሰሪው በተግባር የስራ ስምሪት ባልሰጠበት ሁኔታ አመልካች ስራቸውን ተገደው ካቆሙበት ጊዜ ጀምሮ የተቋረጠባቸው ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡትን የመብት ጥያቄ የስር ፍ/ቤቶች ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 54(2) አንፃር ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በፍትሐብሔር ክርክር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ሰው የግዴታውን መኖር ማስረዳት እንደሚጠበቅበት እና በአንፃሩም ግዴታ ፍርስ ነው ወይም ተለውጧል የሚለው ወገንም ይህንኑ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና(2) ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ አንፃር አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት ወደ ተጠሪ ግቢ ማለትም ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም. በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች ስለተከለከሉ መሆኑን በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አቅርበው ባሰሟቸው ምስክሮች ማስረዳታቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዚህ ረገድ ከአመልካች ለቀረበው የክርክር ነጥብ ተጠሪ በሰበር መልሱ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም፡፡

አመልካች ከ14/02/2004 ዓ.ምጀምሮ ከስራ የቀሩት በራሳቸው ምክንያት በመሆኑ ላልሰሩበት ጊዜ ደመወዝ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከማለት በስተቀር አመልካች ከ14/02/2004 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ የቀሩት በርግጥም በራሳቸው ምክንያት ስለመሆኑ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ አለመኖሩን እና ይልቁንም ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ በተሰጠው ቀጠሮ ባለመቅረቡ መብቱ የታለፈ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ ተጠሪ በሕግ የተጣለበትን ክርክሩን በማስረጃ የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ለማለት የሚቻል አይደለም።

የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ወደ ተጠሪ ግቢ ማለትም ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ ጥቅምት 15 እና 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ በተጠሪ ክልከላ ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው የተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል።ይሁን እንጂ ክልከላውን የፈጸሙት የጥበቃ ሰራተኞች የተጠሪ ሰራተኞች መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ስራቸውን የሚያከናውኑት ከአሰሪ በሚሰጣቸው ትዕዛዝ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ የክልከላ ድርጊቱን የፈጸሙት ከተጠሪ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት እንደሆነ ይገመታል።ትዕዛዙን የሰጣቸው የተጠሪ የስራ ኃላፊ የሚያውቁት ትዕዛዙን የሰጡት የስራ ኃላፊ እና የተቀበሉት የጥበቃ ሰራተኞች ከመሆናቸው ውጪ አመልካች የትዕዛዝ ሰጪውን የስራ ኃላፊ ማንነት ሊያውቁ የሚችሉበት መንገድም ሆነ እንዲያስረዱ የሚገደዱበት የሕግ አግባብ የለም።

ወደ ስራ እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች መከልከላቸውን ማስረዳታቸው ብቻ በቂ ሲሆን ይህንን ማስረዳታቸው ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በስር ፍ/ቤቶችም ቢሆን ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው።ተጠሪም ቢሆን የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላ ተግባሩን የፈጸሙት ከተጠሪ የስራ ኃላፊዎች የተሰጣቸው ትዕዛዝ ሳይኖር ነው በሚል ያቀረበው ክርክር የለም። በመሆኑም የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ወደ ተጠሪ ግቢ እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ ከዚሁ ድምዳሜው ጋር በሚቃረን ሁኔታ የተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

በመሰረቱ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 54(1) ስር በመርህ ደረጃ የተደነገገ ቢሆንም ሰራተኛው ለስራ ዝግጁ ሆኖ እያለ ለስራው የሚያስፈልገው መሣሪያ እና ጥሬ ዕቃ ሳይቀርብለት በመቅረቱ ወይም በሰራተኛው ጉድለት

ባልሆነ ምክንያት ሳይሰራ ቢውልም ደመወዙን የማግኘት መብት እንደሚኖረው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ(2) ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት በተጠሪው ክልከላ ምክንያት እንጂ የራሳቸው በሆነ ጉድለት ምክንያት አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የክልከላው ተግባር ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 54(2) ድንጋጌ መሰረት ደመወዛቸውን እንዲያጡ ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸውን ተቀብሎ እያለ የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት ማን በሚባል የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለትበክልከላው ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 68705 በ15/01/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በ12/02/2005 ዓ.ም. የተነበበው እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 129978 በ18/10/2005 በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ አመልካች ወደ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ በተጠሪ የጥበቃ ሰራተኞች እንደተከለከሉ ማስረዳታቸው በስር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ያገኘ ሆኖ እያለ የጥበቃ ሰራተኞቹ የክልከላውን ድርጊት የፈጸሙት በየትኛው የስራ ኃላፊ ትዕዛዝ እንደሆነ አመልካች አላስረዱም በማለት በክልከላው ምክንያት በስራ ገበታቸው ላይ መገኘትና መስራት ላልቻሉባቸው ጊዜያት ያለው ደመወዝ ታስቦ እንዲከፈላቸው አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. አመልካች በስራ ገበታቸው ላይ ለመገኘት ያልቻሉት በተጠሪው ክልከላ ምክንያት እንጂ የራሳቸው በሆነ ጉድለት ምክንያት እንዳልሆነ የተረጋገጠ በመሆኑ ከጥቅምት 22 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ማለትም እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ደመወዝ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 54(2) መሰረት ለአመልካች የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት ወስነናል፡፡

4. ከላይ በተ.ቁ. 2 ስር ከተገለጸው ውጪ ያለው የስር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
5. ተጠሪ ለቀጣዩ የስራ ስምሪት እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች በተወሰነው መሰረት ከሚያስፈጽሙ በቀር በስራ ስምሪት ረገድ በዚህ ችሎት የሚሰጥ ውሳኔ አይኖርም፡፡
6. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ወ/ከ

የሰ/መ/ቁ. 93813

የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ዛምራ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር /ጠበቃ ማሞ ካሳ ቀረቡ/

ተጠሪ፡- ሙሉጌታ አምባዬ /ጠበቃ አምዶም ታደለ ቀረቡ/

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ20/07/2005 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ ከሳሽ ከ18/12/2003 ዓ.ም ጀምሮ በተከሳሽ ድርጅት ብር 4,000 የወር ደመወዝ እየተከፈላቸው በጄኔራል ፎርማንነት ተቀጥረው እስከ 15/07/2005 ዓ.ም ድረስ ሲሰሩ እንደነበረ ተከሳሽ ድርጅት በ11/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ስራው አልቋል በሚል ምክንያት ከ15/07/2005 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውላቸው መቋረጡን እንደገለፀላቸው ይሁን እንጂ ተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ቦታዎች ኮንትራት የያዛቸው ስራዎች እንዳሉት ሲሰሩበት የነበረው የትግራይ ክልል ምክር ቤት ህንፃም እንዳልተጠናቀቀ፤ ርክክብም እንዳልተፈፀመ እና ስራው ባለማለቁ ከ70 በላይ ሰራተኞች በስራ ላይ እንደሚገኙ የተገለፀበት ሆኖ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ህገ ወጥ የስራ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች እና የበዓላት ቀናት ክፍያ ተከሳሹ እንዲፈፅምላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ ከሳሽ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ስራ እየተገባደደና ለርክክብ እየተዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት በአዋጁ አንቀፅ 30(1) እና (2) መሰረት በአግባቡ መሆኑን እና ሲሰናበቱ ተገቢ ክፍያዎች የተፈፀሙላቸው መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ተከሳሽ ሲሰራው ከነበረው የጎንደር ዩኒቨርስቲ ተዛውሬ ወደ መቐሌ ፕሮጀክት የመጣሁ ስለሆነ ቋሚ ሰራተኛ ነኝ በማለት ከሳሽ የተከራከሩ ቢሆንም ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት

ተዛውረው እንዲመጡ የተደረገው የጎንደር ፕሮጀክት አልቆ ወደ መቐሌ ፕሮጀክት በመዛወራቸው ሳይሆን ስራ በማበላሸታቸው ጥፋቱ እንዳይደገም በማስጠንቀቂያ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ሰራተኛ ነኝ በማለት ከሳሽ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፣ ከሳሽ የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀፅ 10 መሰረት ለተወሰነ ስራ እንደሆነ ፣የተሰናበቱትም የፕሮጀክቱ የስራ መጠን ወደ መጠናቀቅ በመቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ በማለቁ መሆኑ በግራ ቀኙ ምስክሮች የተገለጸ በመሆኑ ምክንያት ስንብቱ ህጋዊ መሆኑን ገልፆ ክሱን ውድቅ በማድረግ የ18 ቀናት የበዓላት ቀናት ክፍያ ብር 4,799.99 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በውሳኔው ቅር በመሰኘት በስር ከሳሽ ጠያቂነት በቀረበለት ይግባኝ መነሻ የመቐሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የአዋጁ አንቀፅ 30 ተፈፃሚነት የሚኖረው አናጢዎችን ግንበኞችን ለሳኞችን እና የመሳሰሉትን የጉልበት ሰራተኞች በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበረበት የጄኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞች በተመለከተ ጭምር አለመሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ማሰራት የማይችልበት ምክንያትመኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ህገ ወጥ በመሆኑ ተከሳሽ ድርጅት ህገ ወጥ ስንብት የሚያስከትላቸውን ክፍያዎች ለከሳሽ እንዲፈጽም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አስቀድሞ የጉንደር ዩንቨርሲቲ ህንፃ ኘሮጀክት እስከሚጠናቀቅ ብቻ ተቀጥሮ ሲሰራ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ወደ ትግራይ ክልል ምክር ቤት ሕንፃ ኘሮጀክት ተዛውሮ እየሰራ እያለ መሰናበቱ ሕገወጥ ነው በማለት ላቀረበው ክስ ስንብቱ የተደረገው የሕንፃው ስራ እየተጠናቀቀ በመሆኑ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤቶች ሳይታይ ታልፎ አመልካች ዝውውር መፈፀሙ ተጠሪን ላልተወሰነ ጊዜ እንደቀጠረው ያስቆጥራል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት ቀደም ሲል እንደተገለፀው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ከሳሽ የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ለተወሰነ ስራ መሆኑን

የተሰናበቱትም የኘሮጀክቱ የስራ መጠን ወደመጠናቀቅ በመቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ በማለቁ መሆኑን በማስረጃ በማረጋገጥ መሆኑን እና የኘሮጀክቱ የስራ መጠን ወደመጠናቀቅ መቃረቡና በከሳሽ ሲሰራ የነበረው ስራ ማለቁ ደግሞ በከሳሽ ምስክሮች ጭምር የተገለፀ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይ/ሰሚው የመቐሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት ይህንን የወረዳ ፍ/ቤት ሽሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው የአዋጁ አንቀጽ 30 ተፈፃሚነት የሚኖረው የጉልበት ስራተኞችን በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበረበት የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞችን በተመለከተ ጭምር አለመሆኑን እና ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጐንደር ኘሮጀክት ወደ መቀሌ ኘሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደሌላኛው ኘሮጀክትም አዛውሮ ማሰራት የማይችልበት ምክንያት መኖሩን እስካላስረዳ ድረስ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ አመልካች ተጠሪን ከጎንደር ወደ መቐሌ ፕሮጀክት ያዛወረው የጎንደር ፕሮጀክት በማለቁ ሳይሆን ተጠሪ ይሰሩበት በነበረው የጎንደር ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት በማሳየታቸው ከመሆኑ ውጪ የጎንደር ፕሮጀክት በማለቁ ምክንያት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ተጠሪ ወደ መቀሌ ፕሮጀክት እንዲዛወሩ የተደረገው ይሰሩበት በነበረው የጎንደር ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት በማሳየታቸው ስለመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት የዝውውር ደብዳቤውን ጠቅሶ በውሳኔው ላይ በግልጽ አስፍሯል፡፡

ይ/ሰሚው ፍ/ቤት በበኩሉ ይህንኑ ደብዳቤ በመጥቀስ አመልካች ተጠሪን ከጎንደር ወደ መቀሌ ፕሮጀክት አዛውሮ ሲያሰራ ነበር ከማለት በስተቀር የዝውውሩ ምክንያት በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጸው ስላለመሆኑ የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን ለመሻር መነሻ ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ የዝውውሩ ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ዝውውሩን አስመልክቶ በወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተገለጸው ፍሬ ነገር ተቀባይነት የሚያጣበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር ይጠበቅበታል፡፡ በመሰረቱ በተቀጠረበት ፕሮጀክት ላይ የስራ አፈጻጸም ግድፈት የፈጸመን ሰራተኛ አሰሪው ሌላ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ወደ ሌላ ፕሮጀክት ማዛወሩ ሰራተኛውን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የዝውውሩን ምክንያት ሳይጠቅስ ተከሳሽ ድርጅት ከሳሽን ከጎንደር ፕሮጀክት ወደ መቀሌ ፕሮጀክት አዛውሮ የማሰራቱን ሁኔታ ብቻ ነጥሎ ለውሳኔው ምክንያት ማድረጉ ተገቢውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የአዋጁ አንቀጽ 30 ተፈጻሚነት የሚኖረው የጉልበት ሰራተኞችን በተመለከተ እንጂ ከሳሹ በነበሩበት የጀኔራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተመደቡትን ዓይነት ሰራተኞች በተመለከተ ጭምር አይደለም በማለት ይ/ሰሚው የደረሰበትን ድምዳሜ በተመለከተ በመሰረቱ የጀኔራል

ፎርማን የስራ መደብ ከአመልካች ድርጅት አስተዳደራዊ ስራዎች ጋር የሚገናኝ ሳይሆን በቀጥታ በኮንስትራክሽን ወይም ከግንባታ ስራ ጋር የተያዘ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ተጠሪም ተሰማርተው የነበሩት በቢሮ ወይም በአስተዳደራዊ ስራዎች ላይ ሳይሆን በቀጥታ በፕሮጀክት ወይም በግንባታ ስራዎች ላይ ስለመሆኑ ያላስተባበሉት እና በክስ ማመልከቻቸውም ላይ የገለጹት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀጽ 30 በተመለከተው መሠረት የሚከናወን ቅነሣ የጉልበት ሰራተኞችን እንጂ እንደአሁኑ ተጠሪ ዓይነት በጀነራል ፎርማን የስራ መደብ ላይ የተቀጠሩትን ሰራተኞች የሚመለከት አይደለም በማለት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ የአዋጁን ድንጋጌ ይዘትም ሆነ በክርክሩ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች የተሰማራበት የኮንስትራክሽን ስራ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ አንዱ ፕሮጀክት ሲያልቅ ተጠሪን ወደ ሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ሊያሰራው ይገባል በማለት በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘውን አቋም በተመለከተ እንደተባለው አመልካች የተሰማራው በኮንስትራክሽን ስራ ላይ መሆኑ እና ስራውም ቀጣይነት ያለው መሆኑ የሚታወቅ እና በአመልካችም ያልተስተባበለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች እንደማንኛውም የኮንስትራክሽን ድርጅት ስራውን የሚያከናውነው በፕሮጀክቶች በመከፋፈል ነው፡፡ ፕሮጀክቶቹን በውድድር የሚያገኛቸው እንጂ እራሱ ፈጥሮ የሚያከናውናቸው አለመሆኑም የሚታወቅ ነው፡፡ ይህም አመልካቹ የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶቹ የሚጀምርበትን ጊዜ የሚወስነው በራሱ ሣይሆን በሚገባበት የውል ግዴታ መሠረት መሆኑን እና በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶች ሊኖሩት የሚችሉ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም ለአንድ ፕሮጀክት የተቀጠረ ሰራተኛን ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ወደ ሌላ ፕሮጀክት አዛውሮ ለማሰራት በኮንስትራክሽን የሰራ ዘርፍ በተሰማራ አሰሪ ላይ በሕግ የተጣለ ግዴታ አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማዛወር ቢኖርበት እንኳ ማዛወር የሚችለው በሌላኛው ፕሮጀክት ውስጥ በተመሣሣይ የሰራ መደብ ክፍት ቦታ በተገኘ ጊዜ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ይ/ሰሚው ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ፕሮጀክት አዛውሮ ሊያሰራው ይችል ነበር ከማለት በስተቀር በሌላኛው ፕሮጀክት የተጠሪ የሰራ መደብ ክፍት ስለመሆኑ እንኳ አላረጋገጠም፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ ድርጅት ከሣሽን ከጉንደር ፕሮጀክት ወደ መቐሌ ፕሮጀክት አዛውሮ እንዳሰራው ሁሉ ወደ ሌላኛው ፕሮጀክት አዛውሮ ማሰራት የማይችልበት ምክንያት መኖርን አላሰረዳም በማለት ይ/ሰሚው ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለል ይ/ሰሚው የመቀሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ለመሻር የሚያስችል በቂ የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት ሳይኖር በማስረጃ በተረጋገጠው መሰረት የህግ አግባብ የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

# ው ሳ ኔ

1. በመቀሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09635 በ06/09/2005 ዓ.ም የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የመቀሌ ከተማ ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13289 በ27/12/205 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ የ18 ቀናት የበዓላት ቀናት ክፍያ ብር 4,799.99 (አራት ሺ ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ ዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም) ከ10% የጠበቃ አበል ጋር ተከሻሽ ለከሳሽ እንዲከፍል የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09635 በ06/09/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 348 (1)መሠረት ፀንቷል፡፡
3. የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10104 የተያዘው አፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ27/01/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ል/ተ

የሰ/መ/ቁ. 93828

የካቲት 11 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ – ጠበቃ አውላቸው ደሣለኝ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ካፒቴን እንድሪያስ ጀምሬ – ጠበቃ ዶ/ር ያሬድ ለገሠ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡን ከሰ/መ/ቁጥር 91872 ጋር አጣምረን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 እና ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 494/1998 መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን ሕጋዊ አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፤ ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ናቸው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከመጋቢት 10 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በአውሮፕላን አብራሪነት የሥራ መደብ ተቀጥረው በወር ያልተጣራ ብር 91,623.60 እየተከፈላቸው ሲሰሩ ቆይተው የአንድ ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥተው የሥራ ውላቸውን ያቋረጡና ንብረቶቹን ያስረከቡ ቢሆንም አመልካች ድርጅት ሕጋዊ ክፍያዎችን ያልፈፀመላቸው መሆኑን ጠቅሰው ክፍያዎቹ እንዲከፈሏቸው እና የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ አመልካችን በገበያ ውድድር ለመጣል በሚታገሉት ድርጅቶች ተጠቂ በመሆን ሥራቸውን የለቀቁ መሆኑን፤ ይህ ደግሞ አመልካች አብራሪዎችን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለማሰልጠን ከሚያስብበት መሰረታዊ ዓላማና ከአጠቃላይ የአገር ጥቅምና ደህንነት ጋር የማይሄድ መሆኑን፤ እንዲሁም ለአመልካች ድርጅት ሕልውና አደገኛ መሆኑን ዘርዝሮ የተጠሪን የማስጠንቀቂያ መስጠትን እና ሥራ መልቀቅን ሕጋዊነት የተቃወመ ሲሆን፤ ክፍያዎችን በተመለከተም ክፍያ ለዘገዬበት ጊዜ የሶስት ወር ደመወዝ የሚከፍልበት አግባብ ያለመኖሩን፣ የዓመት ፈቃድ ደግሞ በይርጋ የታገደ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ያላቸው የዓመት እረፍት ቀናት ብዛት በጥቅሉ 64 ብቻ

መሆናቸውን፤ የሥራ ስንብት ክፍያም ተጠሪ ከሚሰሩበት ለየት ያለ የሥራ ሁኔታ ሊያገኙ ከነበረው ከፍተኛ ገቢ፣ ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር እና ሥራቸው በዓለም አቀፍ ዘርፍ ሳይቀር ካለው ተፈላጊነት አንፃር እንደሕጉ መንፈስ አሰሪው ሊሞላው የሚገባው ክፍተት አለ የሚያስብል ካለመሆኑ አንፃር ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ የስንብት ክፍያን በተመለከተ ተጠሪ እንደሚገባቸውና መጠኑም ብር 253,846.49 ክፍያ ለዘገዬበትም ሊከፈል የሚገባ ክፍያ ደግሞ የአንድ ወር ተኩል ደመወዝ ብር 144,935.40 የስልሳ አራት ቀናት የዓመት ፈቃድ ወደ ብር ሲቀየር ብር 206,129.92 በድምሩ ብር 604,911.81(ስድስት መቶ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ አሥራ አንድ ብር ከሰማንያ አንድ ሣንቲም) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካችም ሆነ ተጠሪ በከፊል ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የአመልካች ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 የተሰረዘ ሲሆን፤ በተጠሪ ይግባኝ ላይ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ለሥራ ስንብቱ መሠረት ያደረገው ስሌት ተገቢ ያለመሆኑን፣ ወጪና ኪሣራን በተመለከተም በስር ፍርድ ቤት የተወሰነበት አግባብ ሕጋዊ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ደምድሞ የሥራ ስንብቱ በጠቅላላው ብር 517,673.70 እንዲሆን፡፡ ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ደግሞ የተጠሪ ዝርዝር የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በእነዚህ ነጥቦች ብቻ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ 93,828ክፍያ እንዲከፈል መደረጉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2(ሽ) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ፤ እንዲሁም ስለድንጋጌዎች ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ውጪ ነው ሲል፤ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈል መወሰኑ ስለሥራ ስንብት ክፍያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን፤ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን፣ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በወር ያልተጣራ ብር 91,623.60 ወርሃዊ ደመወዝ ሲከፈላቸው እንደነበር፤ ከቅጥር ጊዜው ጀምሮ ሥራውን እስከለቀቁበት ጊዜ ድረስ ያለው አገልግሎታቸውም ከአሥራ ሰባት ዓመታት በላይ መሆኑንና ሥራውንም በገዛ ፍቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን ነው፡፡ ወደ ሕጉ ስንመጣ ቢያንስ አምስት ዓመት በአሠሪው ዘንድ የሥራ አገልግሎት ኖሮት በሕመም ወይም በሞት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ፤ ወይም ሥራው ላይ የሚያስቆይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ ከሥራ የተገለለ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሸ)ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ሲሆን፣ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የማያገኝበት አግባብ በሕጉ እንደተመለከተው ሠራተኛው ሥራው ላይ የሚያስቆይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ ለአሠሪው የውል ግዴታ ያለበት ከሆነ ነው፡፡ ሕጉ የአገልግሎት ዘመኑ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ ሠራተኛው ግዴታውን ሳይወጣ የሥራ ስንብት ክፍያ መጠየቅ የማይችል መሆኑን በግልጽ ከሚያሳይ በስተቀር አንድ ሠራተኛ ከፍተኛ ደመወዝ ሲከፈል የነበረ ከሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ አይገባውም በሚል ያስቀመጠው መለኪያ የለም፡፡ ሕጉ ግልጽ ከሆነ ደግሞ ሕጉን እንዳለ ከመተግበር ውጪ ትርጉም የሚሰጥበት አግባብ አይኖርም፡፡ አመልካች ድርጅት ከሠራተኞቹ ጋር ያለው ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሆኑ ግልጽ እስከ ሆነ ድረስ በአዋጁ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን ከአዋጁ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79(3) እና በሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለዳኝነት አሰጣጥ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 88739 የሥልጠና ግዴታ ያለበት ሠራተኛ ግዴታውን ሳይወጣ የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀባይነት እንደማይሰጠው፤ በሰ/መ/ቁጥር 35197 እና 37048 ደግሞ ስለሥራ ስንብት ክፍያ የሰጣቸው አስገዳጅ የሕግ ትርጉሞች የሥራ ስንብት ክፍያና የፕሮቪደንት ፈንድ አንድ ላይ ሊከፈሉ የሚችሉበት አግባብ መኖር ያለመኖሩን ለማየት ይቻል ዘንድ የሁለቱን ክፍያዎች መሠረታዊ ዓላማ መመሳሰል ከማመላከቱ ውጪ የሠራተኛውን የደመወዝ መጠን ከፍተኛነት ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን አግባብ በተመለከተ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠ ባለመሆኑ በመዛግብቱ የተሰጠው ትርጉም ተጠሪ ከሥልጠና ጋር በተያያዘ ለአመልካች ግዴታ ያለባቸው ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለመሆናቸው ያልተረጋገጠ በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያላቸው አይደሉም፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን የደመወዝ መጠን ከፍተኛነት መሠረት አድርጎ ያቀረበው ቅሬታም ሆነ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ለማስቀረብ የጠቀሳቸው መዛግብት ውስጥ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ምክንያቶች ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ እንዳያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉ

ሁነው ያላገኘን በመሆኑ፤ በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ይገባቸዋል ተብሎ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81288 የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም የተወሰነውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132873 ሰኔ 11 ቀን 2005 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የሥራ ስንብት ክፍያ መጠኑን በተመለከተም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81288 የካቲት 28 ቀን 2005 ዓ.ም ተወስኖ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 132873 ሐምሌ 02 ቀን 2005 ተሻሽሎ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ በወጪና ኪሣራ ላይ የተጠሪን የወጪና ኪሣራ ዝርዝር በመጠበቅ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ክፍያ ለዘገየበትና ለዓመት ፈቃድ ክፍያ ደግሞ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሙሉ በሙሉ የፀናው የውሣኔ ክፍል በዚህ ችሎትም አልተነካም፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

ሐምሌ 18 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ይጻፍ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ.

የሰ/መ/ቁ 95451

ሚያዝያ 06 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር-ሠናይት ፋሲካ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መርዓዊ መስፍን

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ክሱም፡- በተከሳሽ አክሲዮን ማህበር ከህዳር 8 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ እያገለገልኩ ሳለሁ ተከሳሽ ሚያዚያ 13 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የህመም ዕረፍት ሳይሰጥህ ተሰጥቶኛል በሚል ለ10 ተከታታይ ቀናት ከሥራ ቀርተሃል በሚል ከሥራ አግዶኝ ለ32 ቀናት ያህል ከቆየ በኋላ ከሥራ ማሰናበቱን ስላስታወቀኝ ወደ ሥራ እንዲመልስ ካልሆነም በስሜ የተጠራቀመውን የጉድለት መጠባበቂያ ገንዘብ እና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ የህመም ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ማስረጃ ቢያቀርቡም ማስረጃውን ሰጥቷል የተባለው የሕክምና ተቋም ለከሳሽ የህመም ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑን የገልጸ ሲሆን፤ ከዚሁ ማስረጃ ውጪ ለ15 ቀናትም ከሥራ ለቀረቡት አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ባለማቅረባቸው በህጋዊ መንገድ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፤ ወደ ሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄም ቢሆን ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡ በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን በተመለከተም፡- ስንብቱ ህጋዊ በመሆኑ የስንብትክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣እና ካሳ ሊከፈላቸው አይገባም፤የዓመት ፈቃዳቸውንም ተጠቅመው ስለጨረሱ በገንዘብ ተለውጦ የሚከፈላቸው የለም፣የፕሮቪደንት ፈንድም የአገልግሎት ዘመናቸው ከ5 ዓመት በታች በመሆኑ ሊከፈላቸው የማይገባ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ ያለባቸውን ዕዳ የማይሸፍን በመሆኑ የሚከፈል ገንዘብ አይኖርም፤የጉድለት ማሚያ ገንዘብም ቢሆን ለግል ጥቅም የሚከፈል ገንዘብ

ካለመሆኑም በላይ ቀደም ሲል ከሚሰሩበት ከገንዘብ ቤት ክፍል ወጥተው በሌላ ክፍል እየሰሩ ከሥራ የተሰናበቱ ስለሆነ ገንዘቡን የመጠየቅ መብት የላቸውም ሲል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በሰጠው ፍርድ፡- ከሳሽ ከሥራ የቀሩት የህመም ፈቃድ ሳይኖራቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ እና ከሥራ ለቀሩበትም በቂ ምክንያት ባለማቅረባቸው ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ ከጠየቋቸው ክፍያዎች ውስጥም፡- ተከሳሽ የሥራ ውሉን ያቋረጠው ለከሳሽ ማስጠንቀቂያ ሊያሰጥ በሚችል ምክንያት ባለመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈላቸው አይገባም፤የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈላቸው የጠየቁትም ቢሆን ያልወሰዱትን የዓመት ፈቃድ በግልጽ ለይተው ባለመጠየቃቸው ተቀባይነት የለውም ሲል ውድቅ ያደረገባቸው ሲሆን የጉድለት ማሚያ ገንዘብ ብር 2,141 በተመለከተም፡- ገንዘቡ ከሒሳብ ሥራ ጋር በተገናኘ ለሚከሰት ጉድለት የሚውል ሆኖ ሳለ ተከሳሽ ከከሳሽ የሚፈለግባቸው ዕዳዎች ናቸው በማለት የጠቀሳቸው ከዓመት ፈቃድ እና ከትምህርት ወጪ ጋር የተያያዙ ዕዳዎች ለጉድለት ማሚያ ከሚጠራቀም ገንዘብ ዓላማ አንጻር ዕዳዎች ናቸው ተብለው ስለማይወሰዱ እና ከሳሽም ከሒሳብ ወይም ከገንዘብ ሥራ ጋር በተያያዘ ያጎደሉት ገንዘብ ስለመኖሩ ተከሳሽ ባለማስረዳቱ ይህንኑ የጉድለት ሚሚያ ገንዘብ ለከሳሽ ሊከፍል ይገደዳል ብሏል፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን በተመለከተም ደግሞ ከሳሽ ልዩ ልዩ ዕዳዎች አለባቸው በሚል ተከሳሽ የፕሮቪደንት ፈንዱን መክፈል እንደማይገባው ቢከራከርም ከሳሽ ዕዳ ካለባቸው ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ ውጪ ይህንኑ ገንዘብ በማቻቻያነት ሊይዝ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ ከሳሽ የሥራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በማለት ተከሳሽ እንዲከፍሏቸው  የጠየቋቸውን ሌሎች ክፍያዎች ግን ስንብቱ የተደረገው በህጋዊ መንገድ ስለሆነ ተቀባይነት የላቸውም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

ተከሳሽም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

አመልካችም በሰበር አቤቱታው በዋናነት ያቀረበው ቅሬታ ነጥብ፡- ተጠሪው ያገለገሉት ከ5 ዓመት በታች በመሆኑ ያላቸው የፕሮቪደንት ፈንድ ራሳቸው ያጠራቀሙት ብር 4,828.03 ሲሆን ከአመልካች ባንክ የተበደሩት ገንዘብ፣ባንኩ በስማቸው በቅድሚያ የከፈለላቸው የዓባይ ግድብ ገንዘብ፣ መወሰድ ከሚገባቸው በላይ የወሰዱት ዓመት ፈቃድ በጥሬ ገንዘብ ተመላሽ መሆን ያለበት ፣ለትምህርት የተከፈለላቸው ገንዘብ በድምሩ ብር 12,397.54 እየተፈለገባቸው ሳለ እና ተጠሪውም አለባቸው ስለተባሉት ዕዳዎች መኖር እና አለመኖር በተመለከተ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ባላቀረቡበት እንዲሁም ስለዕዳዎቹ በመካከላችን መካካድ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ጊዜ አንስተው የፕሮቪደንት ፈንድ ለዕዳው በማቻቻያነት ሊያዝ አይገባም ያሉት

እና የጉድለት መጠባበቂያ ገንዘብም ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የወሰኑት ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ተጠሪው ለሰበር አቤቱታው የበኩላቸውን መልስ እንዲሰጡበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለማቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- የጉድለት ሚሚያውን ገንዘብ አመልካች ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የሥር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት የሚነቀፍበት ምክንያት አለው? ወይስ የለውም?
- ፍርድ ቤቶቹ ከተጠሪው ላይ የሚፈለግባቸው ዕዳ ካለ አመልካች ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በስተቀር በተጠሪው ስም የተጠራቀመውን የፕሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ አመልካች በራሱ ውሳኔ ለዕዳው ማቻቻያነት ሊያደርገው አይችልም በሚል የወሰኑት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች የጉድለት ማሚያ ገንዘብ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ሚያዚያ 24 ቀን 2005 ዓ/ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጻፈው ማብራሪያ በባንኩ የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም መመሪያ መሰረት ለጉድለት ማሚያተብሎ ለገንዘብ ከፋይና ገንዘብ ተቀባይ ሠራተኛ በሠራተኛው ስም የሚጠራቀም ገንዘብ መኖሩን፣ ገንዘቡም ለሠራተኛው የሚከፈለው ሠራተኛው ከቦታው ተነስቶ በስሙ ምንም ዓይነት ዕዳ አለመኖሩ ከተረጋገጠ ከ 6 ወር በኋላ እንደሆነ በመግለጹ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ ማብራሪያ እና በግራ ቀኙ በኩል በዚሁ ነጥብ ላይ የተደረጉትን ክርክሮች በመመርመር አመልካች በተጠሪው ላይ ይፈለግባቸዋል ሲል ከዘረዘራቸው የትምህርት፣ያለአግባብ ወስደዋል የተባሉት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፍሉ ይገባል የሚለውን እና ለዓባይ ግድብ በተጠሪው ስም የተከፈለና ተጠሪው እንዲተኩ የሚፈለግባቸውን ዕዳዎች የጉድለት ማሚያ ገንዘብ ከሚጠራቀምበት ዓላማ አንጻር በመመርመር የተጠቀሱት ዕዳዎች ተጠሪው ከሚሰሩበት የገንዘብ ከፋይ ወይም ገንዘብ ተቀባይ ሥራ ጋር ተያይዞ ከሚመጣው ዕዳ የሚለይ በመሆኑ እንደጉድለት ማሚያ ዕዳ ተደርጎ አይወሰድም፣ እንዲሁም አመልካች ከሂሳብ ወይም ከገንዘብ ሥራ ጋር በተያያዘ ተጠሪው የገንዘብ ጉድለት ዕዳ ያለባቸው ስለመሆኑ አላስረዳም በሚል ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበት ድምዳሜ የግራ ቀኙ ወገኖች ካደረጉት ክርክር እና አመልካች ለሥር የመ/ደ/ ፍርድ ቤት ከላከው ማብራሪያ ላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶቹ በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-ተጠሪው የተለያዩ ዕዳዎች ያሉባቸው ስለሆነ የተጠራቀመላቸውን የፕሮቪደንት ፈንድ የመክፈል ግዴታ የለብኝም ሲል አመልካች መከራከሩን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ከሚያመላክት በስተቀር አመልካች ከተጠሪው የሚፈለጉ ዕዳዎች ናቸው በሚል የዘረዘሯቸውን በመካድ ዕዳ የለብኝም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ሠራተኛው ያለበትን ዕዳ እስካልካደ ድረስም ደግሞ አሠሪው በሠራተኛው ስም የተጠራቀመውን የፕሮቪደንት ፈንድ ለዕዳው መክፈያ እንዲሆን የማድረግ መብት ያለው ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰበር መ/ቁ/71507 በቀን 10/07/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ዕዳዎቹን በግልጽ ክደው ባልተከራከሩበት ሁኔታ አመልካች በተጠሪው ላይ ክስ አቅርቦ ዕዳዎቹን እንዲከፈሉ ከሚያስወስን በስተቀር የፕሮቪደንት ፈንዱን ለዕዳው ማቻቻያ ሊያደረግ አይችልም ሲሉ የሰጡት የፍርድ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በማግኘታችን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/06040 በቀን 01/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/135717 በቀን 03/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. ፍርድ ቤቶቹ አመልካች በተጠሪው ላይ ክስ አቅርቦ ከሚያስወስን በስተቀር በተጠሪ ስም የተጠራቀመውን ፕሮቪደንት ፈንድ በተጠሪው ላይ ለሚፈለግባቸው ዕዳ ማቻቻያ ሊያደርገው አይችልም ሲሉ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
3. የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህጋዊ መንገድ ነው ሲሉ ፍርድ ቤቶቹ ከፕሮቪደንት ፈንድ ውጪ ያሉትን ሌሎች ክፍያዎችን በተመለከተ የሰጡትን የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348 (1) መሰረት አጽንተናል፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል ብለናል፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 95522

መጋቢት 08 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን መሃል ሜዳ ደንበኞች አገልግሎት ጽ/ቤት -ነ/ፈጅ ተስፋዬ አያሌው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-አቶ ሙሉጌታ ወ/ጊዩርጊስ - ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሓል ሜዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪ የክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል ግንኙነት ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ጠቅሰው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው ጋር አያይዘው መገኘታቸው በተደረገው መጣራት ተረጋግጦና የድርጅቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጠሪን ተገቢ ነው ያለውን ቅጣት በመቅጣት ወደ ስራ እንዲመለሱ ቢወሰንም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የኮሚቴውን ውሳኔ ሽረው አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ መወሰናቸውን፣ውሳኔውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) እና በድርጅቱ የህብረት ስምምነት አባሪ ቁጥር 4 አንቀጽ 2 ቁጥር 2.3 መሰረት ተጠሪ የማጭበርበር ወይም የማታለል ድርጊት መፈፀማቸው በመረጋገጡ የተሰጠ በመሆኑ ሕጋዊ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማሰረጃ መርምሮ የአመልካች መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ የኮሚቴውን ውሳኔ በደብዳቤ መሻራቸው ስለውሳኔ በሕጉ የተሰጠውን ትርጉም ያላገናዘበና ሕጋዊ ያለመሆኑን፣ተጠሪ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው ተያይዞ የተገኘባቸው መሆኑ ቢረጋገጥም የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የድርጊቱን ክብደትና ቅለት ያላገናዘበ ነው በማለት እርምጃውን ሕገ ወጥ ነው ብሎ ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው

እንዲመለሱ ወይም በአማራጭ ካሳ ተከፍሏቸው ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ውሳኔ የውሳኔ አጻጻፍ ስርዓትን የተከተለ አይደለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የበላይ ኃላፊው በዲሲፒሊን ኮሜቴ ውሳኔ ላይ ያላቸውን ሥልጣን ያላገናዘበ በመሆኑ የማይቀበለው መሆኑን ጠቅሶ ካለፈ በኂላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ውጤት በተመለከተ ግን ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው አያይዘው ከመገኘታቸው ውጪ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አመልካች ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ ያለመኖሩን ገልፆ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አቅርበው በማህደራቸው አያይዘው መገኘታቸው ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያገኙት ጥቅም የለም ሲል የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ሲል የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ ያለግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ እንዲታይ በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪ ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወይም ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት ተጠሪ ከማህደራቸው የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው የተገኙ መሆኑን ተጠሪን ከስራ አግዷቸው በተገቢው መንገድ አጣርቶ ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን፣የዲሲፒሊኑን ጉዳይ ሲመለከት የቆየው የድርጅቱ ኮሚቴም ጉዳዩን አጣርቶ ተጠሪን የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት፣የአንድ አመት የደረጃ እድገትና የዝወውር ቅጣት አሳልፎ ተጠሪው ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል የሰጠው ውሳኔ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ውድቅ ተደርጎ አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ መደረጉን፣ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ውል በሕግ አግባብ ሊቋረጥ ችሏል በማለት አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው አይይዘው የማጭበርበር ወይም የማታለል ድርጊት ለመፈጸም የሞከሩ መሆኑ በሚገባ በማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት መሆኑን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለድርጊቱ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ በተሳሳተ

የትምህርት ማስረጃ ከማህደራቸው ከማያያዛቸው ውጪ በማስረጃው ያገኙት ጥቅም የለም በሚል ምክንያት መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ ከተገለፀው የፍርድ ቤቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በግል ማህደራቸው የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ አያይዘው መገኘታቸው በሁሉም ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ሁኖ በዚህ ማስረጃ ተጠሪ ጥቅም አግኝተዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ግን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግልጽ አንስቶ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሲል የወሰነ መሆኑን ነው፡፡ይሁን እንጂ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር በሙከራ ደረጃ መቅረቱ የድርጊቱን ወንጀል መሆን ቀሪ የማያደርገው ሲሆን ጥቅም ማግኘት ወይም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ ተግባሩ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የግድ መሟላት ያለባቸው ፍሬ ነገሮች መሆናቸውን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ ይዘት አያሳይም፡፡በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አልተረጋገጠም የሚለውን ምክንያት የያዘው ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ በመመዘኛነት ያላስቀመጠው ነጥብ በመሆኑ ሕጋዊ አይደለም፡፡አመልካች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት አለው በማለት የሚጠቅሰው የድርጅቱ የሕብረት ስምምነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለተጠሪ የተሻለ ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑም አልተረጋገጠም፡፡ይልቁንም የህብረት ስምምነቱ አባሪ ቁጥር 4 አንቀጽ ቁጥር 2.3 ስር አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ፈጽሞ ሲገኝ የማይገባውን ጥቅም እንዲመልስ ተደርጎ እንዲሰናበት እንደሚደረግ እንጂ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ጥቅም ካላስገኘ ስንብት እንደማይከናወን በግልጽ ያለማስቀመጡን ከክርክሩ ሂደት የተረዳን ሲሆን ተጠሪም በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ማናቸውም ሰራተኛ የማጭበርበር ወይም የማታለል ሙከራ መፈፀሙ ከተረጋገጠ ድርጊቱ ሕገ ወጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 27(1(ሐ)) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በአንቀጽ 27(1(ሐ)) ስር የተመለከቱትን ሕገ ወጥ ድርጊቶችን መፈፀም ደግሞ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም ተጠሪ የተሳሳተ የትምህርት ማስረጃ በማህደራቸው አያይዘው መገኘታቸው በበታች ፍርድ ቤቶች በተደረገው የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና የተረጋገጠ ሁኖ እያለ በዚሁ በሕጉ ያልተመለከተውን መመዘኛ፤ በተሳሳተ ማስረጃ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም የለም ተብሎ የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ መባሉ በሕጋዊ ምክንያት ያልተደገፈ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት በአዋጁ አንቀፅ 27(1(ሐ)) ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በዚህም ምክንያት የበታች

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1(ሐ)) ድንጋጌን የጣሰ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በመሃል ሜዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0114277 መስከረም 03 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0112585 ህዳር 20 ቀን 2006 ዓ/ም ምክንያቱ በከፊል ተለውጦ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ 94102

ሚያዚያ 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ኢትዮ ቴሌኮም ደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ሪጅን -አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሳባ መንገሻ- አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሆኖ በአሁን የሰበር ተጠሪ ከሳሽነት የተጀመረው በጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ከሳሽ አሻሽለው ባቀረቡት ክስ፡- በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ29/02/1999 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥሬ እየሰራሁ የቆየሁ ቢሆንም በራሴ ፍላጎት የሥራ ውሌን ለማቋረጥ በ22/10/2004 ዓ/ም የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለተከሳሽ የሰጠሁ ሲሆን ተከሳሽ ድርጅትም ማስጠንቀቂያውን በጻፍኩበት ቀን የሥራ ውሌን በማቋረጡ በእጄ ያሉትን ንብረቶች ባስረክብም መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ በመሆኑም የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣በ2004 ዓ/ም የሥራ ዘመን ለቋሚ ሠራተኞች የከፈለውን ቦነስ የ2 ወር ደመወዝ፣የማስጠንቀቂያውን የአንድ ወር ጊዜ ሳይጠብቅ የሥራ መልቀቂያ በመስጠቱ በወሩ መክፈል የነበረበትን ደመወዝ፣የስንብት ክፍያ፣ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደመወዝ፣የ56 ቀናት የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ፣ በድምሩ ብር 24,594 እንዲከፍል ይወሰንልኝ ብለዋል፡፡

ተከሳሹም ለክሱ የበኩሉን መልስ ከሰጠ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመመርመር ከሳሽ ከጠየቋቸው ክፍያዎች ውስጥ የተወሰኑትን ውድቅ በማድረግ በድምሩ ብር 12,593.74 ተከሳሽ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን በሥር ተከሳሽ ድርጅት ይግባኝ ጠያቂነት ጉዳዩን የመረመረው የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ሲል በማጽናቱ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት አቅርቧል፡፡

ተጠሪዋም ለሰበር አቤቱታው የበኩላቸውን መልስ የሰጡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተገቢውን ደረጃ ጠብቆ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ ይዘን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን በቀጥታ ለዚህ ችሎት ያቀረበው የጅማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማጽናቱ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በሚቀርብ በግል የሥራ ክርክር ጉዳይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 139(1) የተደነገገ ሲሆን ከአንቀጹ መረዳት የሚቻለውም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ ቢሰጥ እንኳን እንደሌሎች የፍትሃብሄር ጉዳዮች ለቀጣይ የይግባኝ ክርክር የማይቀርብ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንቀጹ በዚህ መልክ መጠቀሱ ጉዳዩን በሰበር ችሎት ከመታየት የሚያስቀር አይደለም፡፡

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እንደመሆኑ መጠን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ የተሰጠውን ሥልጣን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ የማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ለ) ከተደነገገው መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(ሐ)፣ እንዲሁም የክልሉን ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 26(1)(ሠ) በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ ጉዳዩ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በሰበር እንዲታይለት አመልካች አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያቀርብ በቀጥታ ለዚህ ችሎት ያቀረበበትን ምክንያት በአቤቱታው በግልጽ ባያሰፍርም አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ አካል በመሆኑ እና በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሡ ክርክሮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6) በመደንገጉ፤ እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ማየት የሚችለው ጉዳዩ የክልል በሆነ ጊዜ ብቻ ነው ከሚል ድምዳሜ በመነሳት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ጉዳዩን ይህ ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ/ 95298 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር መመርመር የሚገባ ነው፡፡ ችሎቱ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ በሰጠው

ፍርድ፡- በፌዴራል መንግስቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች እና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(6) የተደነገገ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን በተመለከተ በክልሎች ውስጥ የሚነሱ የግል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የተሰጠው ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 138(1) በመደንገጉ እና ድንጋጌውም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተደነገገውን ዓይነት ተከራካሪ አካላትን ማንነት ግንዛቤ ውስጥ ካለማስገባቱም ሌላ ድንጋጌው የተካተተበት አዋጅ ቁጥር 377/1996 የወጣው፤ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመሆኑ አንጻር የአሠሪና እና ሠራተኛ ጉዳይ ክርክር የተለየ ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ህግ አውጪው ማናቸውም በክልሎች ውስጥ የሚነሳ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች (አካላት) ላይ ተመስርቶ ጉዳዩ የክልል እና የፌዴራል መሆኑ ከግምት ውስጥ ሳይገባ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደንገጉን እንደሚያሳይ፤ አንድ ጉዳይ የተነሳው በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በተነሳበት ክልል የሰበር ችሎት የተደራጀ እስከሆነ ድረስ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ እና ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ ሳይረጋገጥ በቀጥታ ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት እንደማይኖር አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይም ምንም እንኳን አመልካች የፌዴራል መንግስት አካል ቢሆንም ከዚህ በላይ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የሰበር አቤቱታውን ለፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረቡ አስቀድሞ ጉዳዩ በተጀመረበት ክልል ላለው ለኦሮሚያ ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረብ ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ተገቢውን ደረጃ ጠብቆ የቀረበ አይደለም ስንል ውድቅ አድርገናል፡፡
2. ይህ ውሳኔ መብቱን የሚጠይቅ ወገን በህጉ መሰረት አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረብ የሚያግደው አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 94839

መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- መተሃራ ስኳር ፋብሪካ – ነ/ፈጅ አሉላ ድንቂሳ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ለራሳቸውና ለሌሎች ወኪል ጥበቡ እሸቱ ቀረቡ፡፡

1. አቶ ሳሙኤል ሰላሙ
2. ብርሃኑ ሃ/ማርያም
3. ወርቁ ጎበዜ
4. ሚቲዎስ ማሴቦ
5. ጀጃል ሽሪፍ
6. ጌታቸው እሸቱ
7. ተካ ባዲ
8. ወልዴ አሸቦ
9. ጀማል አደም
10. ፍራንሶ ዮሐንስ
11. ታገሰ አቦዬ
12. አየለ ጥላሁን
13. አህመድ ሃሰን ሁሴን
14. መሐመድ ሁሴን
15. ወልዴ ኦሎሮ
16. መለሰ እሸቱ
17. ሰለሞን ገብሬ
18. ሥራውብዙ ኦብሬ
19. ሽጉጤ ሌጀሶ
20. ምትኩ ነራሞ
21. ቀቀባ ጉተማ
22. መሐመድ ሽሪፍ
23. ጅባ አብደላ
24. ዳንኤል ደንታሞ
25. ቦሩ ፈንታሌ
26. አለማየሁ ጌታሁን
27. ሙሉጌታ በቀለ
28. ሳሙኤል ጌታ
29. መኮንን አስፋው
30. መሐመድ ሰይድ
31. አውላቸው ታደሰ
32. ጴጥሮስ አቡየ
33. ጥበቡ እሸቱ
34. ገናሞ ዱአና
35. ኤልሶ አንቀሞ
36. ጀማል ኡመር
37. አርፍጮ ሄኢሶ
38. አጋፋሪ ጀንባጋ
39. ማህፋመ ታሰው
40. ተካ ባቴቦ
41. ለማንጎ ሐይሌ
42. አባቴ ዓለሙ
43. ተሰማ መርካኖ
44. ሐዋኖ አረዳ
45. ግርማ ጥላሁን
46. ተሰማ ቱሉ
47. ተስፋዬ አቡቶ
48. መሃጉ ላቴቦ
49. ጥላሁን አለሙ
50. ፀጋ በቀለ
51. ማዴቦ ሻንካ
52. ማዴቦ ሻንካ
53. ቀለመወርቅ በላይ
54. መካሻ ወርቁ
55. ሁሴን መሐመድ
56. አሽሮ አዋኖ
57. አዲፀሬ ዳንጎሬ
58. ሐይሉ መርጊያ
59. ፍቃዱ ማሙዬ
60. ተስፋዬ ማዴቦ
61. ባቴ አነቦ

62. ታደሰ ገብሬ
63. ሰልበሳ ደጋሞ
64. አሊ ሀሰን
65. አያኖ አንቺ
66. ፍቅሬ ደሳለኝ
67. አሊ ወሌ
68. ታደሰ ጅራ
69. ይዘንጋው አየለ
70. ስምኦን ሃቢብ
71. አብርሃም ጅማ
72. አለሙ አፌቦ
73. ሙላቱ ፈለቀ
74. አሰፋ አሼቦ
75. የኗላእሸት ደሳለኝ
76. ተፈራ ማጴቦ
77. በቀለ ተፈራ
78. ተስፋዬ ሰላሙ
79. አሰፋ አድማሱ
80. አሊ ሰይድ ጸጋው
81. ድሪባ ዱባለ
82. ኢብሮ ሲራጅ
83. አለሙ ሰላቶ
84. ደሣለኝ ሰርካሞ
85. ሉባንጎ አላሮ
86. አድየስ አሸቦ
87. ተስፋዬ አሸቦ
88. አርቦዬ ወየሳ
89. ይገዙ ግምቶ
90. ከተማው አነሰኝ
91. ቶማስ ደንቃጎ
92. ጴጥሮስ አቡዬ
93. የርማኮ ጀኖሬ
94. አደም ዋዩ
95. አየለ ደገፋ
96. ንጉሤ በሻ
97. ሲሳይ አሰፋ
98. ሐሰን ሙኼ
99. ካሣ ኃይሌ
100. ማቴዎስ ጌቻሞ
101. አሸነ ተፈራ
102. አይረዲን መሐመድ
103. ሃይሉ ወልዴ
104. ከበደ መልኬ
105. እሸቱ ቡሽራ
106. ተከተል አናሞ
107. አምባው መኳንንት
108. መስቀሉ አበራ
109. ተሾመ ቲራሞ
110. ተስፋዬ ካሳ
111. ሃይሌ ሞሎሮ
112. እንድሪስ መሐመድ
113. አበበ በላይ
114. ሽምሱ ጀማል
115. ዘውዴ ደንታሞ
116. ተፈራ ሽመልስ
117. ግርማ አብዬ
118. ተሾመ ጃርሶ
119. ግርማ አብዬ
120. በልዳ ታደሰ
121. ጸጋዬ ታደሰ
122. ቦልጠና ወልዴ
123. ባዩ ክብረት
124. ወ/ሮ ፀሐይ ዋቆ
125. ሃይሉ ወልደየስ
126. ማቲዎስ ቡርቃ
127. አናሞ ላልንጎ
128. አበራ ይዘንጋው
129. ምህረቱ ይርዳው
130. ዳዲ ቱፋ
131. ደምሴ ግዶቦ
132. ረጋሳ ወልዴ
133. ታደሰ የሉች
134. ይመር አበበ
135. አሰፋ ጄዳ
136. አስቻለው ገረመው
137. ጥላሁን ጉልላት
138. ለማ ሀሰን
139. አሰፋ ረዲ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሠረት አድርጎ የቀረበን የሥራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን፤ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በምስራቅ ኦሮሚያ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪዎች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር መስርተው የነበረውን የሥራ ውል አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌን በሚቃረን ሁኔታ ከሥራ የተቀነሱ መሆኑን ጠቅሰው እርምጃው ሕገወጥ ነው ተብሎ ወደ ሥራ እንዲመልሳቸው ወይም ሕጋዊ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ፣ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም የግል የሥራ ክርክር በመሆኑ በቦርዱ ሊታይ እንደማይገባ፤ ክሱም በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳ ሲሆን፣ በፍሬ ነገር ደረጃም ተገቢ ነው ያለውን የክርክር ነጥብ አንስቷል፡፡ ቦርዱም ጉዳዩን መርምሮ የአንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች ክስ ጥቅምት 09 ቀን 2005 ዓ.ም የተመሠረተ መሆኑን ጠቅሶና ጥያቄውም ከሥራ ያላግባብ ስለተቀነስን ወደ ሥራ ይመልሰን የሚል በመሆኑ፤ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንደአለው፣ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ሐምሌ 25 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀረበው የአሥራ አራት ሰዎች ክስ ጋር ተቀላቅሎ የሥራ ውሉ የካቲት 01 ቀን 2004 ዓ.ም ከተቋረጠ በኋላ መቅረቡ ተቀባይነት እንደሌለውና ክሱም በይርጋ የታገደ መሆኑን፤ የ14 ሰዎች ክስ ግን ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም መቅረቡንና ጊዜውን የጠበቀ ቢሆንም ጥያቄው በክፍያ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በቦርዱ ሥልጣን ስር እንደማይወድቅና የመደበኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች በዚህ የቦርዱ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎች ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች ሠራተኞችን የሚነካ ነው፡፡ ይህም የወል የሥራ ክርክር ያደርገዋል፡፡ ይርጋም ቢሆንም ክሱ መጀመሪያ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ሊታሰብ የሚገባውና ጊዜውም ያላለፈ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የቦርዱን ብይን ሽሮ ቦርዱ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ነው፡፡ በይርጋው የሚታገድ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን፤ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የታዘዘ ሲሆን፣ ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፤ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በቅድሚያ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ለመታየት የመጨረሻ ፍርድ አግኝቷል? ወይስ አላገኘም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት በፌዴራል መንግሥት አካል ቢሆንም ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተመሰረተውን የቅጥር ውል መነሻ ያደረገ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች መዋቅሩን መሠረት በማድረግ የዳኝነቱም ሥልጣን በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት መካከል እንደተከፋፈለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 50 እና 51 ሥር ተመልክቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 80 «የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን» በሚል ርዕስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የተደነገገ ሲሆን፣ የክልል ፍ/ቤቶች በሕገ - መንግሥቱ የተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት፤ እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸውም መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሠረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶች ሥልጣን የሚኖራቸው በሕገ-መንግሥቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አግባብ ብቻ ነው፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሠረት የፍርድ ቤቶች ሥልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (Subject matter) የሥልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ -ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በሕግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የሥረ - ነገር ሥልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግሥታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጐች ያስረዳሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ን" ያወጣው የፌዴራል መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ክርክሮች

የሚመሩበትን ሥርዓት የዘረጋውን አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከየካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም ሥራ ላይ ያዋለ ሲሆን፤ በዚህ አዋጅ የሥራ ክርክር ሥልጣን ድልድል የተደረገው የግል የሥራ ክርክርና የወል የሥራ ክርክር የሚሉትን ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ የተከራካሪ ወገንን ማንነትን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ አይደለም፡፡ በመሆኑም ክርክሮቹ ክልል የተነሱ ቢሆንም ጉዳዩን የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም አግባብነት ያላቸው የቋሚ ወይም ጊዚያዊ ቦርዶች ሊመለከቱ እንደሚችሉ አድርጎ ሕጉን ሕግ አውጪው አውጥቷል፡፡ ይህ አዋጅ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመውጣቱም በላይ ለሥራ ክርክር ጉዳዮች ልዩ ሕግ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ለሥራ ክርክሮች ከሕገ መንግሥቱ በመለስ ባሉት ማናቸውም ሕጎች የበላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስረዱን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሥራ ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ሥልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወስድ የሚገባው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ደግሞ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ሳይመለከቱ የሥራ ክርክር ለዚህ ችሎት የሚቀርብበት አግባብ የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነው፡፡

በዚህም መሠረት አንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ለመስተናገድ ይችል ዘንድ፣ በፍ/ቤቶች ወይም ክርክሮችን አይተው ለመወሰን ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በተዋረድ ታይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ እንደሚገባው ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10(3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የምንችለው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ክርክሩ የተጀመረውና በመጀመሪያ ውሣኔ የተሰጠበት በምስራቅ ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ታይቶ የቦርዱ ውሣኔ ከመሻሩ ውጪ ጉዳዩ የተነሳው ከክልሉ በሚገኝ ቦርድ እንደመሆኑ መጠን በተሻሻለው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64/2/ሐ/ እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 26(1)(ሠ) ድንጋጌ መሠረት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን መዝገቡ አያመላክትም፡፡ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችልበት ሌላ ሕጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ በዚህም ሁኔታ ጉዳዩ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሣኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ፣ ይህ ችሎት በተመሳሳይ የሥነ ሥርዓት ጥያቄ በሰ/መ/ቁጥር 95298 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት፤ይህ ጉዳይ በዚህ ችሎት ለመታየት ብቁ አይደለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በአመልካች ላይ ክስ የቀረበው አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሠረት በማድረግ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡት የሥራ ክርክሮች የሚመሩትም በዚሁ አዋጅ በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያልታየ ውሣኔን ይህ ችሎት የሚያስተናግድበት አግባብ የለም ብለናል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩን ለክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሕጉ አግባብ የማቅረብ መብቱን ይህ ውሣኔ ቀሪ አያደርገውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዘ.በ.

የሰ/መ/ቁ.94889

መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ባዛ - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ፍፁም አዲስ ቀረበ፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የደረጃ እድገት አላግባብና ከሕግ ውጭ ተከልክያለሁ በማለት የቀረበውን ጥያቄ የሚያመለክት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ በመስከረም 1 ቀን 2005 ዓ.ም የደረጃ እድገት ማሰታወቂያ አውጥቷል፡፡ ተከሳሽ በማስታወቂያው የማኔጅመንት የመጀሪያ ዲግሪና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ለዕድገት መወዳደር እንደሚችሉ ገልጿል፡፡ እኔም በማኔጅመንት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪና አሥር አመት የሥራ ልምድ ያለኝ በመሆኑ ለእድገት ለመወዳደር ተመዝግቤ የተሰጠውን ፈተና አልፌና ተወዳድሬ በአንደኝነት አልፌአለሁ፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ያለምንም በቂ ምክንያት የተወዳደርኩበትን የሥራ መደብና እድገት እንዳላገኝ ያደረገኝ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በፍርድ መብቴን እንዲያስከብርልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ ክስ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ አመልካች የተወዳደረችበትን እድገት አለማግኘቷ ተገቢ ነው፡፡ የዕድገት ማስታወቂያው የወጣው ሥራ አስኪያጅ ሣያውቀውና ሣይፈርምበት ነው፡፡ የእድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ

ሀሳብ ሥራ አስኪያጅ አልተቀበለውም በመሆኑም የከሳሽ ክርክር የህግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ውድቅ አድርጐታል፡፡ የከሳሽን የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ ከሳሽ ተከሳሽ ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት መስፈርቱን በማሟላት ከሌሎች ሁለት ተወዳዳሪዎች ጋር በድርጅቱ የተሰጠውን ፈተና ተፈትና ሌሎቹን ተወዳዳሪዎች በመብለጥ ያለፈች መሆኑ በእድገት ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ በግልፅ ሠፍሯል፡፡ ከሳሽ በፈተናውና ሌሎች መስፈርቶችን በማሟላት የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሥራ መደብ መመደብ የምትችል መሆኑ ቢረጋገጥም የተከሳሽ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቂና ቀጥተኛ የስራ ልምድና ብቃት ያለው ሰው ስላልተገኘና የእድገት ውድድሩም አራት ወራት ያህል እንደፈጀ በመግለጽ የእድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ውድቅ ያደረገው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግና የህብረት ስምምነቱን በሚቃረን መንገድ በመሆኑ ተወዳድራ ባለፈችበት የሥራ መደብ እንዲመድባት በማለት ወስኗል፡፡ ከሳሽ በህግ መሠረት የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግላት የጠየቀችውን ጥያቄም በአግባቡ በማጣራት የደመወዝ ማስተካከያ እንዲያደርግላትና ጥቅማጥቅም እንዲያከብርላት በማለት ወስኗል፡፡

3. ተጠሪ ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ተጠሪ /አመልካች /ተወዳድራ ያለፈችበት እድገት በድርጅቱ ሥራ አስኪያጅነት ያልፀደቀ በመሆኑ ተጠሪ የደረጃ እድገቱ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ክስ ለማቅረብ አትችልም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

4. አመልካች 06/03/2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ሠራተኞችን ለማወዳደር አስቀድሞ ያወጣውንና በዕድገት ማስታወቂያው የዝርዝር መስፈርት ሳያገናዝብ ያለበቂ ምክንያት የዕድገት ኮሚቴው በተሰጠው መሥፈርት መሠረት አወዳድሮ ያቀረበለትን ውጤት ውድቅ ማድረጉ በፍርድ ታይቶ ሊታረም የሚገባው ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት እንደማይታይ አድርጐ የሰጠው ትርጉምና ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የክልሉ መንግስት ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ሊያደርግልኝ የሚገባውን የደመወዝ ማስተካከያ የነፈገኝ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ

በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክታለች ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ 22-04-2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የዕድገት ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ተፈፃሚ የሚሆነው በሥራ አስኪያጁ ሲፀድቅ ነው፡፡ ይህም በሕብረት ስምምነቱ የተገለፀ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የእድገት ውድድሩን ያልተቀበለው በመሆኑ ከሳሽ እድገት ይሰጠኝ በማለት መጠየቅ አትችልም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?የሚውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለእድገት የተወዳደረችበት የሪከርድና ማህደር ሱፐርቫይዘር የሥራ መደብ በእድገት ለመወዳደር በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ የሚያስፈልግ መሆኑ ተጠሪ ከመስከረም 30 ቀን 2005 ዓ.ም ባወጣው የእድገት ማስታወቂያ ሰነድ የተገለፀ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪና የአስር አመት የስራ ልምድ ያላት በመሆኑ በእድገት ውድድር ተመዝግባ ከሌሎች ሁለት ሰራተኞች ጋር ተፈትና ብልጫ ያለው ውጤት በማግኘቷ እድገቱ እንዲሰጣት የተጠሪ ድርጅት የእድገት ኮሚቴ ቃለጉባኤ በማረጋገጥ የውሳኔ ሀሳብ ለድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀረበ በመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡

7. የድርጅቱ ዕድገት ኮሚቴ ቃለጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ የደረሰው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ "ውድድሩ ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ያለውና ብቃት ያለው ሰው ያላስገኘና ጊዜውም ከአራት ወር በላይ ስለሆነው ውድቅ ቢሆን የተሻለ ነው" የሚል ይዘትም ያለው ውሳኔ በመስጠት አመልካች የተወዳደረበትንና ያለፈችበትን እድገት እንዳታገኝ ያደረጋት መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤትቶች ውሳኔ ተረድተናል፡፡ አመልካች በዳኝነት ታይቶ እንዲታረምላት የምትጠይቀው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የእድገት ኮሚቴው አወዳድሮ ያቀረበውን ውጤትና የውሳኔ ሀሳብ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት የሕግ መሠረት የሌለው ነው በማለት ነው፡፡

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አመልካች በውድድሩ ያገኘችው ውጤትና የእድገት ኮሚቴው ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በድርጅቱ ያልፀደቀ በመሆኑ፣ ለተወዳደረችበት የሥራ መደብ አልፋለች ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች ሥራ አስኪያጅ ያላፀደቀውን የእድገት ውድድር ውጤት መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ አይደለም በሚል ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ውሳኔ፣ አንድ ድርጅት ለእድገት

ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት ተወዳድሮ በውጤቱ የእድገት ማስታወቂያ የወጣበትን የሥራ መደብ መመደብ የሚገባው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ፣ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ በቂና ምክንያታዊ ባልሆነ ማናቸውም ምክንያት የሠራተኛውን ውጤት አልቀበልም በማለት ቢወስን ፍርድ ቤቶች የሥራ አስኪያጁ ውሳኔ የህግ መሠረት ያለው በቂና ምክንያታዊ መሆኑን የመመርመርና ሥራ አስኪያጁ ስህተት ሠርቶም ከሆነ በፍርድ የማረም ስልጣን የላቸውም የሚል አንድምታዎች ትርጉም ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህም የአንድ ድርጅት የእድገት ኮሚቴ፣ የእድገት አሰጣጥ ደንብና ሥርዓት በመከተል ለእድገት ለመወዳደር ያቀረቡትን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ለመመዘን ድርጅቱ ያስቀመጣቸውን የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ በውድድሩ ከፍተኛ ውጤት ያመጣውን ሰራተኛ በመለየት፣የቀረበለትን የእድገት ውድድር ውጤትና የውሳኔ ሀሳብ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ውድቅ ቢያደርገው ሠራተኛው ጉዳዩን በፍርድ እንዲታይለት ለመጠየቅና ክስ ለማቅረብ ይቻላል ወይስ አይቻልም? ፍርድ ቤቱስ ይህንን ጉዳይ በዳኝነት በማየት አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን የሕግ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው፡፡

9. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በሠራተኛ ዕድገት ዝውውርና ሥልጠና በሚመለከት አሠሪው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በፍርድ ሊታዩና ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች እንደሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና ከአንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ ድንጋጌዎች ይዘትና ይህ ሰበር ችሎት ስለ ግል የሥራ ክርክርና ስለ ወል የሥራ ክርክር፣ የክልልም ሆነ የፌዴራል የሥራ ክርክር ችሎቶች የግል የሥራ ክርክሮችን በዳኝነት አይተው የመወሰን ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በማስፋፋት በስር መዝገብ ቁጥር 18180 ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም ለመረዳት ይቻላል፡፡
10. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሥራ አስኪያጁ የእድገት ውድድሩን ውጤት ያልተቀበለው ያለበቂ ምክንያትና ከሕግ ውጭ ነው በማለት በሥር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የዳኝነት ጥያቄ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 138፣አንቀጽ 142 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ/ እና አንቀጽ 147 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ እንዲሁም ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 18180 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በመቀበል አመልካች የእድገት ውድድሩን ውጤት አልቀበልም፣ አመልካች ተወዳድሯ ባለፈችበት የሥራ መደብ አልመድብም የሚልበትን ምክንያትና ማስረጃ እንዲያቀርብ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ከላይ የተገለፁትን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሠረት ሠራተኛው ያለህጋዊ በቂ ምክንያት አሠሪው በዘፈቀደ

እድገት ሲከለክለው በፍርድ እንዲታይለት የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብቱን የሚያስከብር ትክክለኛ የዳኝነት አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

11. የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ፡ የዕድገት ኮሚቴው ያቀረበውን የሠራተኞችን የዕድገት ውድድር ውጤት ውድቅ ያደረገው፣ ኮሚቴው ሠራተኞችን ያወዳደረው የእድገት አሰጣጥ ደንብና ሥርዓትን ሣይከተል /ወይም / በመጣስ ነው፡፡ ወይም ኮሚቴው የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሥራ መደብ ሠራተኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዕውቀትና ክህሎት ለመመዘን ድርጅቱ ያወጣቸውን የብቃት መመዘኛ መስፈርቶች ሣይከተልና ሣያሟላ ነው፡፡ በሚል ምክንያት እንዳልሆነ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው በግልፅ ያሰፈረው የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ የውሳኔ ሀሳብ ለመረዳት ችለናል፡፡

12. በአንፃሩ የተጠሪ ሥራ አስኪያጅ፣ አመልካች የተወዳደረችበት የሪከርድና ማህደር ሱፐርቫይዘርነት የሥራ መደብ የሚያስፈልገው በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪና ዜሮ አመት የሥራ ልምድ መሆኑ ተገልፆ የእድገት ማስታወቂያው እንዲወጣ ያደረገና ውድድሩም በዚሁ መሠረት የተከናወነ ሆኖ እያለ በውድድሩ ቀጥተኛ የሥራ ልምድ ያለው ሠራተኛ አልተገኘም በማለት በመጀመሪያ በመወዳደሪያነት ያላስቀመጠውን መስፈርት ጠቅሶ የአመልካችን እድገትም በቂና ህጋዊ ምክንያት ሣይኖረው አልቀበልም በማለታቸው ጉዳዩን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

13. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የእድገት ማስታወቂያ ለወጣበት የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ መሆኑን ተጠሪ በማስታወቂያው የገለፀና አመልካችም በተጠሪ የተጠየቀውን ትምህርት ዝግጅት /በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ/ ያላትና መስፈርቱን ያሟላች ሆኖ እያለና፣ በተጠሪ አመልካች ዕውቀት ክህሎት ለመመዘን የራሱን ፈተና አውጥቶ አመልካች ከሌሎች ሁለት ሠራተኞች ጋር ተወዳድራ ማለፏ ተረጋግጦ እያለ፣ ሥራ አስኪያጁ ውድድሩ " ብቃት ያለው ሰው "አላገኘንም በማለት በውሳኔው መግለፁ፣ ተጠሪ ራሱ ያወጣቸው የብቃት መመዘኛዎችና የትምህርት ዝግጅት ለሚላቸው አመልካች እድገቱን ላለመስጠት ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት እንቢተኛ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ የሥር ፍርድ ቤትና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የእድገት ውድድሩን ለማከናወን የእድገት ማስታወቂያው ከወጣ በኂላ ያለፉትን አራት ወራት እድገቱን በውድድሩ አሸናፊ ለሆነችው አመልካች ላለመስጠት እንደምክንያት ማቅረቡ፣ የሕግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

14. በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካች ለዕድገት ተወዳድራ ያለፈችበት የሥራ መደብ ላይ ላለመመደብና እድገቱን ላለመስጠት በሥራ አስኪያጁ በኩል ያቀረባቸው ምክንያቶች

በበቂ ምክንያት የተደገፈና የህግ መሠረት ያላቸው አይደሉም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የእድገት ማስታወቂያ ሲያወጣ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶችና መመዘኛዎች የሚጥሱ ናቸው፡፡ አሠሪው የሠራተኞችን ብሔረሰብ ፣ፆታ፣ሀይማኖት፣ፓለቲካ አመለካከትና ሌላም ሁኔታ መሠረት በማድረግ ልዩነት ማድረግ የማይፈቅድለት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ/2/ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ተጠሪ ሴት በመሆኗ ምክንያት ተጠሪ እድገቱን እንዳልሰጣት በመግለጽ የምትከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ እድገቱን ለአመልካች ያልሰጣት ሴት በመሆኗ ምክንያት ሣይሆን በሌሎች ተጨባጭና አሳማኝ ምክንያቶች መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነቱን ያልተወጣ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸውም ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

15. በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ከላይ የጠቀሳቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና መሠረታዊ ዓላማ ሣያገናዝብ፣የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ተወዳድራ ብልጫ ያለው ውጤት በማምጣት ልታገኝ የሚገባውን እድገት የሥራ መደብ፣ ሊሰጣት ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59766 ጥቅምት 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የደረጃ እድገቱን በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ አመልካችን በእድገት ማስታወቂያ መሠረት ተወዳድራ ባለፈችበት የሥራ መደብ ሊመድባት እና የስራ መደቡ የሚያስገኘውን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. አመልካች የጠየቀችው ውዝፍ የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄ በዚህ ሰበር ችሎት በጭብጥነት ያልተያዘ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 94931

የካቲት 14 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ጥሩወርቅ መንግስቴ - ጠበቃ አቶ ስዩም አዳሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የተገጣጣሚ ህንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት - ጠበቃ አቶ መንግስቱ ኃይሉ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ክርክሩን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ፍሬ-ነገርም ባጭሩ፡- ከሳሽ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ በግዥ አቅርቦት እና ሽያጭ መመሪያ የሥራ ኃላፊነት ላይ ተመድበው በመስራት ላይ እንዳሉ ባላወቁትና ባልተረዱበት ሁኔታ የስራ ውላቸው ያለቅድመ ማስጠንቀቂያ ከ24/05/2004 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ ለመሆኑ በ25/05/2004 ዓ/ም የተፃፈ ደብዳቤ በ3/6/2004 ዓ/ም የደረሳቸው መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ሲሆን የስር ተከሳሽ የሆነው የአሁኑ ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ፡- ከሳሽ ሊከፍሉን ይገባል በማለት ያቀረቡት የተለያዩ ክፍያዎች ጥያቄ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 መሰረት የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት 30/11/2004 ዓ/ም ያለው ጊዜ ከ6 ወር በላይ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በበኩሉ የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ከድርጅቱ የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንቡ አኳያ አገናዝቦ መመርመሩን ከገለጹ በኋላ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በ24/05/04 ዓ/ም ስለመሆኑ በስር ከሳሽ ያልተካደ መሆኑን፣ ክሱ ደግሞ የቀረበው በ30/11/04 ዓ/ም መሆኑን ከመዝገቡ መገንዘቡንና የተከሳሽ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37(3) መሰረት አንድ የሥራ መሪ የስራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ካላቀረበ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ መሆኑን ካሰፈረ በኋላ ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት

የስራ ውሉ ከተቋረጠ ከ6 ወር በኂላ ነው የሚል ድምዳሜ ሀሳብ ላይ ከደረሰ በኂላ ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(2)(ሠ) እና 245(2) መሰረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት መዝገቡን በብይን ዘግቷል፡፡ በአሁኗ አመልካች ይግባኝ አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ይግባኙን ከመረመረ በኂላ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ብይንና ትዕዛዝ በመቃወም ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ አመልካች የደረሰው በ3/6/2004 ዓ/ም መሆኑ እየታወቀ እና ከዚህ ቀን ጀምሮ ክሱ በስር ፍ/ቤት እስከቀረበበት ሐምሌ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ 6 ወር የማይሞላ መሆኑ እየታወቀ ክሱ በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ እና ጉዳዩ ወደ ስር ፍ/ቤት ተመልሶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በፅሁፍ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡
የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በስር ፍ/ቤቶች በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡
እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው አመልካች የሚከራከሩት የይርጋ ጊዜው መቆጠር ሊጀምር የሚገባው የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን የስራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ ከደረሰኝ ከ3/6/2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆን አለበት በሚል ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ የሥራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤ ለአመልካች የደረሰው በ3/6/2004 ዓ/ም መሆኑን ሳይክድ ሆኖም ግን በተጠሪ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌ መሰረት አንድ የሥራ መሪ የመብቱን ጥያቄ ለማቅረብ ከሚችልበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ጊዜ ድረስ ጥያቄውን ካላቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል በሚል ስለሚደነግግ እና አመልካችም ከዚህ አኳያ አሉኝ የሚሉትን መብት ለማቅረብ የሚችሉት የስራ ውሉ ከተቋረጠበት ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ በግልጽ በተደነገገበት ሁኔታ አመልካች የሥራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ መሆን አለበት በሚል ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በሚል የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ ማለትም የመብቱ ጥያቄ ስለሚቀርብበት የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያለው ይሄው በተጠሪ ድርጅት የስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተመለከተው የ6 ወራት የጊዜ ገደብ ስለመሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ሆኖም ግን የይርጋ

አቆጣጠሩን መነሻ ጊዜ በተመለከተ ተጠሪም በበኩሉ ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ ይሄንኑን መነሻ በማድረግ ክርክሩን እንዳቀረበው የፍ/ብ/ህ/ቁ፣ 1846 ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይም አግባብነት ያለው ስለመሆኑ የሚታመን ነው፡፡ ይህ የተጠቀሰው ድንጋጌም "የይርጋ መነሻ ጊዜ" በሚል ርዕስ የተሰየመ ሲሆን የድንጋጌው ሙሉ ይዘትም የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሰራበት ጀምሮ ነው የሚል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምረውም በመጀመሪያ ደረጃ የአመልካች ስራ ውል የተቋረጠው ከ24/05/04 ዓ/ም ጀምሮ ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የስራ ውሉ መቋረጫ ደብዳቤም ለአመልካች የደረሰው በ3/06/2004 ዓ/ም ስለመሆኑም እንዲሁ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ እና ከ3/06/2004 ዓ/ም በፊትም አመልካች የስራ ውሉን አስቀድሞ የተቋረጠ መሆኑን በሌላ አግባብ ታውቆ ነበር በሚል ከተጠሪ የቀረበ ክርክር በሌለበት ሁኔታ ደግሞ አመልካች የስራ ውሉ መቋረጡን መነሻ በማድረግ መብቷን የማስከበር እንቅስቃሴ ልትጀምር የምትችለው የስራ ውሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ ከደረሳት እለት ጀምሮ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ከ3/6/2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ክሱ ለስር ፍ/ቤት እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ (ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ/ም) ያለው ሲቆጠር ደግሞ 6 ወር ያላለፈ በመሆኑ በተጠሪ ድርጅት የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌ መሰረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይንና ይሄንኑን ብይን በማፅናት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1846ና የተጠሪ ድርጅት ስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 37 ድንጋጌን ይዘት፣ መንፈስና አላማን ያላገናዘበ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 32077 በ21/07/05 ዓ/ም የሰጠው ብይንና ይሄንኑን በማፅናት የፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 137495 በ11/02/06 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የኮ/መ/ቁ 32077 የሆነውን በማንቀሳቀስና ግራ ቀኙን አስቀርቦ ክርክሩ ከቆመበት ጀምሮ በማከራከር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/

የሰ/መ/ቁ. 98099
ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ ደንቂ ኦዳ
2. አቶ በኃይሉ ዘለቀ
3. አቶ ነጋሽ ባልቻ
4. አቶ ዩሐንስ ኦፊቾ
5. አቶ ገመዳ በጅጋ
6. አቶ ገላዬ ገመቹ
7. ወ/ሮ በቀለች ያኢ
8. አቶ በላይ ገላ
9. አቶ ግዛው ታፈሰ
10. አቶ አበራ በየነ
11. ወ/ሮ ፈለቀች እሸቴ
12. ወ/ሮ ጌጤ በቀለ
13. ወ/ሮ እጅጋየሁ ኃይሌ
14. ወ/ሮ ትምህርተ ወልዴ
15. ወ/ሮ መሬማ ሁሴን
16. አቶ መሀመድ ዳምጠው
17. ወ/ሮ ማናለ ዘውዴ
18. ወ/ሮ የኔነሽ ኃይሉ
19. አቶ ሃብታሙ አበበ
20. አቶ ብርሃኑ ድረስ
21. ወ/ሮ የሺወርቅ ገ/ሚካኤል
22. ወ/ሮ ሳባ ጥሩነህ
23. ወ/ሮ ወይንሸት ወንድሙ
24. ወ/ሮ ሶፊያ መሀመድ
25. አቶ አድማሱ ያለው
26. ወ/ሮ ቀጸላ ታመነ
27. አቶ ሐሰን መሀመድ
28. ወ/ሮ እናኑ ወልደየስ
29. አቶ ተሸመ ተ/ፃዲቅ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ፐልፕ እና ወረቀት አክሲዮን ማህበር-ነገረ ፈጅ ጂብሪል አልቃድር ቀረ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996"ን" መሰረት አድርጎ የቀረበን የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ በተጠሪ ላይ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካቾች የክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ከተጠሪ ጋር መስርተው የነበረውን የስራ ውል የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌን መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የጡረታ መብት እንዲጠበቅላቸው መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ/ም ወስኗል በሚል ምክንያት ለአመልካቾች የስራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የሰጣቸው መሆኑን፣እድሜአቸው ስልሳ አመት ሳይሞላ በጡረታ እንዲሰናበቱ መደረጉ ከሕግ ውጪ መሆኑን ጠቅሰው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌ መሰረት በሚንኒስትሮች ምክር ቤት በተወሰነው መሰረት የጡረታ መብት ተጠብቆላቸው የተሰናበቱ ስለሆነና በዚህ አግባብ የተሰናበተ ሰራተኛ ደግሞ የስራ ስንብትም ሆነ ካሳ የሚከፈልበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሠጠውን ውሳኔ እንዲቀርብ አድርጎ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች በጡረታ እንዲወጡ መደረጉ መረጋገጡንና በጡረታ የወጡት ሰራተኞች ደግሞ የሚተዳደሩት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት መሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን ለማየት ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት የተሰረዘባቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግን ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ የጡረታ እድሜ ሳይደርስ ጡረታ እንድንወጣ ተደርጓል የሚል በመሆኑና ይህም በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ያለመሆኑን ከጠቀሰ በኃላ የአመልካቾች ጉዳይ እድሜ ስላልደረሰ በጡረታ መውጣት አይገባንም የሚል በመሆኑ በፍርድ ቤት የሚታይ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ብይን ውጤቱን አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የአመልካቾች የክስ ይዘት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ጡረታ እድሜ ደርሷል የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ለሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ የሚከፈሉት ክፍያዎች እንዲከፈሉ ይወሰንልን ዳኝነት የሚጠይቅ ሁኖ ሳለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በፍርድ ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሊዳኝ የሚችል አይደለም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ክስ የመሰረቱት የሥራ ውሉ በዕድሜ ምክንያት እንዲቋረጥ መደረጉ ከሕግ ውጪ ስለሆነ ለሕገ ወጥ የሥራ ስንብት የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲከፍሉ ይወሰንልን በሚል መሆኑን፣ተጠሪ ደግሞ አመልካቾች መሰናበታቸውን ሳይክድ ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ በዚህ ረገድ ማስረጃ አቅርቦ መከራከሩን ነው፡፡ስለዚህ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር በጭብጥነት ተይዞ ዳኝነት የሚፈልገው ጉዳይ ስንብቱ ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የሥራ ስንብት የሚደረግባቸው ምክንያቶች ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን ስንብቱ አከራካሪ ሁኖ ሲገኝም ዳኝነት የሚሰጡ አካላት የትኞቹ እንደሆኑ አዋጁ ያሳያል፡፡በአዋጁ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን አከራክሮ ለመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚመለከቷቸው የክርክር አይነቶች ተገልጸዋል፡፡ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የአሠሪና ሠራተኛን ክርክር በቀጥታ ሲቀርብላቸው ወይም ደግሞ በይግባኝ ሲመጣላቸው ለማስተናገድ እንደሚችሉ የአዋጁ አንቀፅ 138 እና 139 ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡መደበኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ለማየት ሥልጣን የሚኖረው ግል የሥራ ክርክሮችን ሲሆን የግል የሥራ ክርክር የሚባለው በአዋጁ አንቀጽ 138 (1) ላይየተገለፁት እናተመሣሣይውጤት ያላቸውክርክሮች ናቸው፡፡ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ሊታዩ የሚችሉት ጉዳዮች ደግሞ ቦርዱ ያያቸውን ጉዳዮች፣ በሥልጣን ላይ የሚቀርብን መቃወሚያ፣ የማህበር ምዝገባን ክልከላ፣ ሚኒስቴሩ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ያለን ቅሬታ፣ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው በሰጠው ውሳኔ ላይ፣ ሚኒስቴሩ እገዳንና የማህበር ስረዛን በተመለከተ በሰጠው ውሳኔ ላይ ስለመሆኑ አዋጁ ያሳያል፡፡

ጉዳዩ የግል የስራ ክርክር ወይም የወል የስራ ክርክር መሆኑን መሰረት አድርጎ የሚለይበት የሕግ አግባብና በዚህ ረገድ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣንን መወሰን እንደተጠበቀ ሁኖ የስራ ውሉ የተቋረጠው በበቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑ ጉዳዩን ለመዳኘት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት ስልጣን በተሰጠው አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሌሎች ሕጎችም የስራ ውል መቋረጥን ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን በዝርዝር ደንግገው ሊያስቀምጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ከውሉ መቋረጥ ጋር ተያይዞ ክርክር ከተነሳ ይህንኑ ጉዳይ የሚዳኘው አካል ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ነገር መኖር ያለመኖሩን መመርመርን የግድ የሚለው ይሆናል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23፣ ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ። በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው ተነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል። በአዋጁ አንቀጽ 24 እንደተመለከተው ውሉ በሕግ የሚቋረጥበት ምክንያቶች በአብዛኛው ከሁለቱም ወገን ቁጥጥር ውጭ ያሉ ሲሆን የስራ ውል ሁለቱም ፈቃደኝነት የሚገቡበት እንደመሆኑ ሁሉ ሁለቱም በፈቃደኛነት ከተስማሙ ውሉን ሊያቋርጡ የሚችሉበት ሁኔታም በአንቀጽ 25 ስር ሰፍሮ ይገኛል ። ስለዚህ ከላይ በተገለጹት ቁጥሮች በተደነገጉት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈጸም የስራ ውል መቋረጥ ሕጋዊ የስራ ውል መቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል መቋረጥ በሕገ ወጥነት የሚፈረጁ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 42 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል። በዚህም ላይ በመመስረት የሚያስከትሉት ውጤቶች የሚለያዩ በመሆኑ በተናጥል የሚያስከትሉትን ውጤት ከሕጉ አግባብ በማየት ዳኝነትን መስጠት ይጠይቃል።

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከት የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው፣የጡረታ እድሜያችን ሳይደርስ በጡረታ እንድንወጣ ተደርጎ ውሉ ተቋርጧል የሚል ነው።አመልካች ደግሞ በሕጉ አግባብ የሥራ ውሉ መቋረጡን ጠቅሶ የስንብት እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል።ከዚህ መረዳት የሚቻለው የተጠሪ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት የቀረበ ሁኖ አመልካቾች ደግሞ እድሜያቸው ለጡረታ ስለመድረሱ ሳይክዱ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት የስራ ውል የሚቋረጠው የሠራተኛው የአገልግሎት ዘመን 25 አመት ያላነሰና እድሜው ከሃምሳ አመት ያላነሰ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ህልውና በማክተሙ፣ የሰው ኃይል ብዛቱ ከሚፈልገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከሥራ እንዲሰናበት ከተደረገና አገልግሎቱ ከ25 ዓመት ያላነሰና ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ ሆኖ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን ነው በሚል ነው።ይህም ስንብቱ ከህግ ውጪ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ክርክራቸውን ማቅረባቸውን የሚሳይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ስንብቱ በሕግ አግባብ የተደረገ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመር የሚያግደው አይደለም።ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) ድንጋጌ አግባብ አመልካቾች በጡረታ እንዲገለሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስወሰኑ የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም።በዚህ ረገድ አመልካቾች በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት የመልስ መልስ ይዘት ሲታይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጉዳዩ መወሰኑን አምነው ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ አሳስቶ ያስወሰነ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ውሳኔው የለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የለም።በመሆኑም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰናበታቸው ከተረጋገጠ ይኼው ውሳኔ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት እስካልተለወጠ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት

ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት የሚከራከሩበት አግባብ የለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ጥያቄ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ የስራ ስንብት ነው በሚል የቀረበና ውጤቱም በአዋጁ አንቀጽ 39 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ እንዲታይ የቀረበ መሆኑን በማገናዘብ ጉዳዩ የመደበኛ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የሚታይ ነው በማለት ክርክሩን ማየት ሲገባቸው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ይሁን እንጂ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት ከስራ የተሰናበቱና የጡረታ መብታቸውም ተከብሮ አበሉን በመቀበል ላይ እንደሚገኙ በተጠሪ በኩል የቀረበውን ክርክር ግልጽ ማስተባበያ ያላቀረቡና በዚህ ረገድ ስልጣን ባለው አካል የተሰጠው ውሳኔም በስርዓቱ መሰረት ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ የሆነበት አግባብ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ በመሆኑ የተጠሪ እርምጃ ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው እና በውጤቱ ላይ ክርክር እንዲካሄድ ማድረግ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ በዚህ ችሎት በዚህ ረገድ ድምዳሜ መያዙ ተገቢ ሁኖአል፡፡በመሆኑም አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) መሰረት በተሰጠ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብትም ተጠቃሚ መሆናቸው ያልተካደ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው ከውጤት አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሁኖ አልተገኘም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 66514 ሀምሌ 11 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 16522 ነሀሴ 09 ቀን 2005 በትዕዛዝ፣በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 173499 ታህሳስ 14 ቀን 2006 ዓ/ም ምክንያቱ ተለውጦ በፍርድ የፀናው ብይን በውጤት ደረጃ ሲታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(7) አግባብ ተሰናብተው የእድሜ ልክ የጡረታ መብት ተከፋይ መሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ የተጠሪ እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ሊባል የሚችል አይደለም ብለናል፡፡በዚህም ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35(1(ሀ) እና 44፣40(1) እና (2)፣36 እና 38 እንዲሁም 43(3) እና 44(4) ድንጋጌዎች አግባብ የጠየቋቸው የክፍያ አይነቶች ሊከፈሏቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

# ከውል ውጭ

# ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 92040

ሚያዚያ 09 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-አቶ ጥምቀቱ ጋመነ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-ወ/ት ታገሰች ዮሐንስ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጪ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገን የጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በአቶ ቢኒያም አሚቲ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ተጠሪ በገንዘብ ያዥነት ሥራ ተቀጥረው የተጣራ ብር 1717.054 በወር እየተከፈላቸው እንደሚሰሩ፣ነሐሴ 15 ቀን 2003 ዓ/ም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሰሌዳ ቁጥሩ 1-16423 አ.አ የሆነውና ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች የሆነ ሚኒባስ በአቶ ቢኒያም አሚቲ ይሽከረከር እንደነበርና ያለበቂ ጥንቃቄ እየተሽከረከረ ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት ሲገባው ይህንን ባለማድረግ በወቅቱ የዜብራ መንገድ ከቀኝ ወደ ግራ መንገዱን በማቋረጥ ላይ የነበሩትን ተጠሪን በመኪናው የፊት ለፊት አካል ገጭቶ በመጣል የግራ እጅ የላይኛው ክንድ አጥንት እንዲሰበር፣የቀኝ ትከሻ እንቅስቃሴ እንዲገደብ፣ሶስት ጥርሶች እንዲወልቁ የግራ እግር ቅልጥማቸው እንዲሰነጠቅ በማድረግ በአጠቃላይ የ30% ቋሚ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት መሆኑን፣ጉዳቱ ሲደርስ እድሜአቸው 28 አመት ሁኖ ወደፊት ተጨማሪ 40 አመታት ለመኖር እንደሚችሉ ገልፀው በወር እየሰሩ እስከ አርባ አመታት ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ገንዘብ አስልተውና የሞራልና የህክምና ወጪ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን ደምረው በጠቅላላው ብር 269,344.50(ሁለት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ አርባ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም በተጠሪ ላይ የደረሰው ጉዳት ወደፊት ሰርተው ለመኖር የማይከለክላቸው እንዲሁም ደመወዛቸው ተብሎ የቀረበውም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ጉዳዩን መርምሮ አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ በማድረግ የኃላፊነት መጠኑን ደግሞ ተጠሪ በወር ብር 1717.50 እንደሚያገኙ መረጋገጡን፣ተጠሪ የደረሰባቸው የአካል ጉዳትም 30% መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ለወደፊትም አርባ አመት ሊኖሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪ በወር ያገኙ የነበሩትን የተጣራ ገቢ በብር 1717.50(አንድ ሺህ ሰባት መቶ አስራ ሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) በአርባ አመት ሲሰላ ብር 247,320.00 (ሁለት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሃያ ብር) እንደሚመጣ፣ከዚህም በተጨማሪ በጉዳቱ ምክንያት ለህክምና የወጣው ወጪ መጠኑ ብር 13,024.00፣የሞራል ካሳ ብር 1000.00፣የትራንስፖርት ወጪ ብር 1000.00 መሆኑን ገልፆ በድምሩ ብር 261,544.00(ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ አርባ አራት ብር) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ የተጠሪ የተጣራ ወርሃዊ ደመወዝ ብር 1617.50 መሆኑ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ የአካል ጉዳት መጠኑን በማሻሻል ብር 232,848.00 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ስምንት ብር) እንዲሆን አድርጎ ሌሎች ክፍያዎችን ግን ተቀብሎ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ተቀብሎ ዳኝነት ሰጥቷል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘቱም ባጭሩ፡-ተጠሪ በጉዳቱ ምክንያት የተቋረጠባቸው ገቢ ሳይኖር የጉዳት ካሳ ይገባቸዋል ተብሎ መወሰኑም ሆነ የጉዳት ካሳ ስሌቱ እንዲሁም ካሳው በቀለብ መልክ እንዲከፈል መደረግ ሲገባው በአንድ ጊዜ እንዲከፈላቸው መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም ይህ ችሎት እንዲመለከተው የተያዘው ጭብጥ፡-በተጠሪ ላይ ደርሷል ከተባለ የ30% የአካል ጉዳት አኳያ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው የካሳ መጠን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 አንፃር ለመመርመር ሲባል ነው፡፡በዚህም መሰረት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ ተብለው መወሰኑ ላይ ሳይሆን የካሳ ስሌቱን በተመለከተ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት የተገነዘብነው ተጠሪ ስራቸው ገንዘብ ያዥ ሲሆኑ ከጉዳቱ በሁዋላ ለዚህ ስራ ብቁ አይደሉም ባይባልም 30% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ

ማስረጃ ከሕክምና ቦርድ መቅረቡንና በዚህ ስራ ሲያገኙ የነበረው ያልተቋረጠ ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ ነጥቦች መሆኑን ነው።የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳቱ ምክንያት ወደፊት ተጠሪ የሚቀርባቸውን ገቢና ከጉዳቱ ጋር ተያይዘው የወጡትን ወጪዎች በመለየት የካሣ መጠኑንም መወሰናቸውን ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል።

በመሰረቱ ካሳ የሚከፈለው ጉዳት መኖሩ ሲረጋገጥ ሲሆን የካሳ አተማመን ፣መጠንና አከፋፈልን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090፣2091፣2092፣2095 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተቀመጠ ሲሆን ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም ካሳው በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ጋር መመጣጠን ያለበት መሆኑን ነው።የበታች ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የካሳ መጠን ላይ ይግባኝ የሌለው መሆኑ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 ስር የተመለከተ ሲሆን ይግባኙ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2153 ስር ተገልጿል።

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች በኩል የቀረበውን ቅሬታና በሰበር ችሎቱ የሕግ ትርጉም ያስፈልገዋል ተብሎ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ መሰረት ስናደርግ በካሳ አተማመኑ ላይ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ሳይገቡ በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ስለመሠጠቱ የሚያሳይ ነገር ያለ ሁኖ አልተገኘም።

ተጠሪ አካላቸው በሕገ መንግስቱም ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን ካሳው ሲወሰንም ይህንኑና ጉዳቱ በአመልካች የወደፊት ኑሮ ላይ ሊያስከትለው የሚችለው አጠቃላይ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል እንጂ ተጠሪ 30%(ሰላሳ ከመቶ) ጉዳት ቢደርስባቸውም ይሰሩ የነበሩትን ስራ ላለመስራት ወይም ሌላ ስራ ላለመስራት እንቅፋት አይሆንባቸውም፣እንዲያውም ስራውን በመስራት ላይ የሚገኙ በመሆኑ የተቋረጠባቸው ገቢ የለም በሚል ምክንያት ብቻ ካሳው ሊቀነስ ይገባል፣ወይም ጭራሹን አይገባቸውም ሊባል የሚችል አይደለም።

ከውል ውጪ ኃላፊነትን በተመለከተ የሚገዙት የፍትሐብሔር ሕጋችን ድንጋጌዎች መንፈስ የጉዳትን ጠቅላላ ባህርይና የካሣ ልክ አተማመን ሁኔታዎችን ያስገነዝቡናል። በዚህም መሠረት ጉዳት በሰው ጥቅም ላይ ችግር የሚያደርስ መሆኑን፣ ይህም ጥቅም ማቴሪያላዊ /በሰው አካል ወይም ንብረት የደረሠ/ ወይም ሞራላዊ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። የተጎዳ ሰው ደግሞ መካስ እንዳለበት ያስረዳሉ። የካሣውን አተማመን በተመለከተም መጠኑ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሁኖ መመዘን ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 ድንጋጌ ያሣያል።የጉዳት ካሣ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ ሲመዘንም በተጎጂው ላይ በእርግጠኝነት መድረሱ የታወቀ /actual damage/ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/future damage/ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ የሚል መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091/1/ እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል። በእነዚህድንጋጌዎች የጉዳት ካሣ ሊተመን የሚገባ መሆኑን ሕጉ በግልጽ

ከማስቀመጡም በተጨማሪ የአተማመኑ ሥርዓትም እንደጉዳቱ ዓይነትና ማስረጃ አቀራረብ ውስብስብነት ሊለያይ የሚችል መሆኑን የሕጉ መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በዚህም መሠረት የጉዳት ካሣ መጠን አጥጋቢና በቂ ማስረጃን ወይም ርትዕን መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን የካሣ አከፋፈሉን ልክ በሚደነግገው የሕጉ ክፍል የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ በሌላ በኩል የካሣ አተማመን ሥርዓት ጠቅላላ የመስራት አቅም /General utility/ ሣይሆን ልዩ ጠቀሜታ/specific utility/ መርህን ቢከተል ፍትሐዊነት ያለው አሠራር መሆኑ ይታመናል፡፡ይህም አሠራር በተጨባጭ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነማወቅአስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የካሣውን ልክ ያላግባብ ከማጋነንና ከመቀነስ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡በመሆኑም ጉዳት መድረሱ በማስረጃ ከተረጋገጠና ጉዳቱም በተጎጂው የወደፊት ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለመሆኑ ከተረጋገጠ ካሣ መወሰን ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች መንፈስ አኳያ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ በሕጉ ዳኞች በተሰጠው ሥልጣን ወይም በጉዳዩ ላይ በቀረበው ማስረጃ መሠረት በመተመን ለተጎጂው መፍረድ የሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መኖሩን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2101 እና 2102 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ጉዳቱ መድረሱ እየታወቀ የአሁንና የወደፊት ቁሣዊ ጉዳት /material damage/ ስለመኖሩ ተጎጂው አላስረዳም ተብሎ የመካስ መብት ማጣት ከአጠቃላይ ከውል ውጪ ኃላፊነትን ከሚገዛው ሕግ አላማ ጋር አንድ ላይ የሚሄድ አይሆንም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ንብረትነቱ የአመልካች በሆነው መኪና በዜብራ መንገድ ላይ በማቋረጥ ላይ በነበሩበት ጊዜ የመኪናው አሽከርካሪ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት በመኪናው ተገጭተው በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው ጉዳት መድረሱን፣በዚህ ጉዳትም በአካላቸው ላይ 30%(ሰላሳ ከመቶ) ጉዳት መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳቱ ወደፊት ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑም የተገለፀ ነገር የለም፡፡በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች ካሳ የማይከፍሉበት ምክንያት የለም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የካሳ መጠኑን በተመለከተ የተጠሪ ወርሃዊ ደመወዝ በተገቢው ማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ፍሬ ነገሩን የማጣራት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ተቀጥረው ሲሰሩ በወር ያገኙ የነበረውን የተጣራ የደመወዝ መጠን በማስረጃ ያረጋገጡት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ የተጠሪ እድሜ 28 አመት መሆኑን በማስረጃ አረጋግጠው ከተቀበሉ በኋላ ተጠሪ ወደፊት ሊኖሩ የሚችሉት አርባ አመት መሆኑን ግን በበቂ ምክንያትና ማስረጃ አስደግፈው የተቀበሉት መሆኑን ውሳኔው አያሳይም፡፡አንድ ሰው ወደፊት የሚኖርበትን የእድሜ መጠን በመግለጹ ብቻ ይሄው በተጎጂው የተገለፀው የእድሜ መጠን ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ የጉዳት ካሳ የሚሰላበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ በመሆኑም ወደፊት

ለመኖር የሚገለፀው እድሜ በአጠቃላይ የአገሪቱን በተለይ ደግሞ የአካባቢውንና ተጨባጭ ሁኔታና በዚህ ረገድ የሚመለከተው አካል ያስቀመጠው ጥናታዊ መነሻ ካለ ይህንኑ መሰረት ማድረግ ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወደ ፊት በሕይወት ልኖር እችላለሁ በማለት ያቀረቡት የእድሜ መጠን በአጠቃላይ የአገሪቱን ወይም በተለይ የሚኖሩበትን አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ወይም የሚመለከተው አካል ይፋ ያደረገውን ጥናት መሰረት ያደረገ መሆኑን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በመሆኑም ተጠሪ አርባ አመት ወደፊት ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ መያዝ የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት የእድሜ መጠን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከተባለ ደግሞ ምክንያታዊ የሆነ እድሜ መያዝ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ተጠሪ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ሰራተኛ እንደመሆናቸው መጠን በስራው ላይ ሊቆዩ የሚችሉት ስልሳ አመት መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ከዚህ አመት በላይ በቅጥር ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ሊያገኙ የሚችሉት ገቢ ሊቋረጥ ወይም ሊቀንስ ይችላል ብሎ ለመውሰድ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የወደፊት እድሜ አርባ አመት ነው በማለት ካሳውን ከዚህ ጊዜ አንጻር በመመልከት ማስላታቸው ሊገምቱት የሚገባቸውን የነገሩን አጋጣሚ ሁኔታ ያላግባብ በመያዝ ወይም ትክክለኛውን መንገድ ትተው ያላግባብ የሆነውን ያገማመት መንገድ መያዛቸውን የሚያሳይ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2253(ሀ) ድንጋጌ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ የጣሰ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህ አይነት ሁኔታ በሚወሰነው የካሳ መጠን ደግሞ ይግባኝ ማቅረብ እንዲሁም በሰበር ማሳረም የሚቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2152 እና 2153 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡እንዲሁም አመልካች ተጠሪ ወደፊት የሚኖሩበትን እድሜ አስመልክቶ በግልጽ ክርክር አላቀረቡበትም ቢባል እንኳን ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ክፍያ ይገባኛል የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በፍርድ ቤቶቹ ጉዳዩ ከመታየት ሕጉ የማይከለክል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 83 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ነጥብ ነው፡፡ ስለሆነም በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰላው የካሳ መጠን በውጤት ደረጃ ሲታይ ከላይ የተመለከቱትን የካሳ አተማመን መንገዶችን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና ጉልሕ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት የጉዳት ካሳ አከፋፈሉ በቀለብ መልክ በየወሩ ሊሆን ሲገባ በአንድ ጊዜ እንዲከፈል መደረጉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2154 ድንጋጌ ሲታይ የጉዳት ካሳ አከፋፈል በአንድ ጊዜ ሊሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን በአቀራረፁና ይዘቱ ለፍርድ ቤቱ ፈቃድ የሠጠ ከመሆኑ አንፃር የካሣው አከፋፈል በጡረታ መልክ ሊሆን ይገባል የሚለው የአመልካች ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ክፍያው በአንድ ጊዜ ሊሆን እንደሚችልና ለፍርድ ቤቱ የተተወ ስልጣን

መሆኑንም ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 67225 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በካሳ ስሌት ደረጃ ሲታይ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 69127 ጥር 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 131954 ሐምሌ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለጉዳቱ ከመኪናው አሽከርካሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ መጠን ግን መታሰብ ያለበት ተጠሪ ወደፊት ስልሳ አመት እስከሚሞላቸው ድረስ ሊኖሩ ይችላሉ ተብሎ ሊሆን ስለሚገባው ጉዳቱ ሲደርስ ተጠሪ የነበራቸውን እድሜ (28 አመት) መነሻ በማድረግ ወደፊት የሚቀራቸው 32 አመት መሰረት ተደርጎ ሊሰሳ ይገባል ብለናል፡፡በዚህም መሰረት የተጠሪ የተጣራ ወርሃዊ ገቢ ብር 1617 መሆኑ ስለተረጋገጠ ይኼው ገንዘብ በአስራ ሁለት ወራት እና በሰላሳ ሁለት አመታት ሲባዛ የሚመጣው ውጤት (1617×12×32×30%=186,278.40) አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰምንት ብር ከአርባ ሳንቲም) ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የአካል ጉዳት ካሳ ነው ብለናል፡፡ሌሎች የክፍያ አይነቶችን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አልተነካም፡፡ተጠሪ የዳኝነት መክፈል ያለባቸው በዚህ ችሎት በተወሰነው የካሣ መጠን ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በመዝገቡ ነሐሴ 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ. 93104

ሚያዚያ 2 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር - ነ/ፈጅ ግርማ ሞገስ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ደስታ ጁላ ቤካሎ - ጠበቃ አንዱዓለም በእውቀቱ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያላግባብ ለውጭ አገር ጉዞ የተከፈለ የመጓጓዣ ወጪና አበል ይመለስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች የክስ ይዘትም፡-ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት የአንድ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆናቸው ለስራቸው ጠቃሚ የስራ ልምድ ገብይተው እንዲመለሱ አመልካች ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ወደ አውስትራሊያ አገር ልኳቸው የተላኩበትን ትምህርት አጠናቅቀው ሃላፊነታቸውን መወጣት ሲገባቸው ከተላኩበት አገር ሳይመለሱ መቅረታቸውን ገልፆ ለአበል፣ለስልጠናና ለአውሮፕላን መጓጓዣ የተከፈላቸውን ብር 180,574.94 (አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ አምስት መቶ ሰባ አራት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም) ከእነ ወለዱ እንዲመልሱ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ በጠበቃቸው አማካኝነት ለክሱ በሰጡት መልስ ወደ ውጪ አገር የተላኩት ለስራ ጉብኝት እንጂ ለትምህርት አለመሆኑ ጠቅሰው ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ ለመመለስ ከሕግም ሆነ ከውል የመነጨ ግዴታ የለብኝም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱ እየጠየቀ ያለው ያላግባብ ስለመበልጸግ የተጠቀሱትን ድንጌዎችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ በቃል ክርክር ጊዜ ግልጽ ያደረገ ቢሆንም ተጠሪ ያላግባብ ተገልግሏል በማለት አመልካች ከመግለጽ ውጪ ያገኘው ጥቅም ስለመኖሩ አላስረዳም በሚል ምክንያት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ የአመልካችን ክስ በከፊል ውድቅ አድርጎታል፡፡እንዲሁም የተጠሪ ጠበቃ ተጠሪ በአገር ውስጥ እያለ ለአበል ወስደው ያላወራረዱት

ብር 832.00 (ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት ብር) መኖሩን ያመኑ በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ በከፊል ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ውስጥ የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ ለስራው ጠቃሚ የሆነ ትምህርታዊ እውቀት ገብይተው እንደሚመለሱ ወደ አውስትራሊያ አገር ሲላኩ ለአበል ለስልጠናና ለአውሮፕላን መጓጓዣ አመልካች ብር 180,574.94 ከፍሎላቸው ከሄዱና ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው በቀሰሙት ሙያ ለአገራቸው አገልግሎት መስጠትና ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲገባቸው በዚያው ሳይመለሱ መቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ ጥቅም ስለማግኘታቸው አልተረጋገጠም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደረጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ አመልካች ተጠሪው ለመንግስት ስራ እንዲረዳቸው ከውጪ አገር ልምድ ቀስመው እንዲመጡ ወጪ አውጥቶ ከላካቸው በኋላ ወደ አገራቸው ሳይመለሱ መቅረታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ያገኙት ጥቅም ስለመኖሩ አልተረጋገጠም ተብሎ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተው ተጠሪ ለመንግስት የስራ ጉዳይ ወደ ውጪ አገር ሂደው በዚያው ስለቀሩ ለጉዞና ለስልጠና የወጣ ወጪ ሊመለስልኝ ይገባል በሚል ሲሆን ተጠሪ በአመልካች የስራ ምክንያትና ወጪ ወደ ውጪ አገር መሄዳቸውን ሳይክዱለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩት የተገኘ ጥቅም የለም፣ወደ ውጪ አገር የሄዱበትን ስራ ሰርተው ተገቢውን ሪፖርት አጠናቅረው ለአመልካች መስሪያ ቤት አስረክበዋል በሚሉ ምክንያቶች መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱአንድ ሰው የሌላውን ሰው የሥራ ድካም ወይም በሌላው ሰው ሀብት በመገልገል በቂ ባልሆነ ምክንያት ጥቅም ያገኘ እንደሆነ አላግባብ ባገኘው ጥቅም መጠን ለባለሀብቱ ወይም በጉልበቱ የደከመው ሰው የመመለስና የመካስ ግዴታ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር

2162 በመሠረታዊ መርህነት ተደንግጓል፡፡የዚህ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ሲታይ የሚከፈለው የካሳ መጠን የሚወሰነው ተከሳሹ ያገኘው ጥቅምና ከሳሹ የደረሰበት ኪሳራ ተመዛዝነው በመታየት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ለከሳሹ የሚወሰንለት ካሳ ተከሳሹ ካገኘው ጥቅምም ሆነ ከሳሹ ከደረሰበት ኪሳራ ሊበልጥ እንደማይገባ ሕጉ ያሳያል፡፡ሕጉ ተከሳሹ የሚያገኘው ጥቅም በንብረት ላይ የተቋቋመ ግዙፍ መብት ወይም ከአንድ ሰው ላይ የሚጠየቅ መብት ሊሆን እንደሚችል፣እንዲሁም ተከሳሹ የነበረበት እዳ ተሰርዞለት ወይም ግዴታው ቀርቶለት ወይም ኪሳራ ሳይደርስበት ቀርቶ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳል፡፡ስለሆነም በተከሳሹ በኩል የተገኘው ጥቅም መኖር ብቻ ሳይሆን የተገኘው ጥቅም የሕሊና እርካታን የሚያስገኝና በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን አለበት፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት በነበራቸው ኃላፊነት አበልና የአውሮፕላን ትራንስፖርት የስልጠና ወጪ ተከፍሎላቸው ወደ ውጪ አገር መሄዳቸውና በስራ ምክንያት ሂደው ሳይመለሱ መቅረታቸው ግራ ቀኙን ያላከራከሩ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ ተጠሪ የአመልካችን ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት የሚከራከሩትና የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ጥቅም ማግኘታቸው አልተረጋገጠም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ወደ ውጪ አገር ለመሄድ ለትራንስፖትም ሆነ ለተለየዩ ጉዳዮች የገንዘብ ወጪ የሚያስፈልግ መሆኑ ግልጽ ሲሆን ተጠሪ ወደ ውጪ አገር ሲሄዱ አመልካች ገንዘብ ማውጣቱ ተረጋግጧል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛ ባይሆኑና ለስራ ምክንያት ወደ ውጪ አገር የማይሄዱ ቢሆኑ ኑሮ ለአውሮፕላን ትራንስፖርትና ተያያዥ ወጪዎችን መሸፈን የሚገባቸው ተጠሪ ራሳቸው መሆኑን ነው፡፡እንዲህ ከሆነ ተጠሪ ጥቅም አላገኙም ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡ምክንያቱም በአመልካች መስሪያ ቤት በነበራቸው የስራ ግንኙነት ወደ ውጪ የተላኩት አስፈላጊውን ልምድ ቀስመው አመልካችን ያገለግላሉ በሚል ሀሳብ ሲሆን ይኼው የአመልካች ሃሳብ ተጠሪ ከሄዱበት ባለመመለሳቸው ውጤት ሳይገኝ መቅረቱን የክርክሩ ሂደትና ይዘት ያሳያልና፡፡አመልካች ኪሳራ የደረሰበት፣ተጠሪ ደግሞ በአመልካች መስሪያ ቤት የተመቻቸላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም በአመልካች ወጪ ወደ ውጪ አገር ሄደው የቀሩ በመሆኑ ለአውሮፕላን ትራንስፖርትና ለስልጠና በተከፈለው ገንዘብ መጠን ጥቅም አላገኙም ሊባል የሚችልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸውን የስራ ግንኙነት፣ወደ ውጪ ሊሄዱ የቻሉበትን ምክንያትና አንድ ሰው ወደ ውጪ ሲሄድ ደግሞ የግድ ወጪ የሚያስፈልገው መሆኑንና ተጠሪ በራሳቸው ወደ ውጪ ቢሄዱ ኑሮ የራሳቸውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይችሉ የነበረ መሆኑን፣አመልካች ተጠሪ ከተላኩበት ተመልሰው ሊያገለግሉ ይችላሉ በሚል ሙሉ እምነት ወጪውን አውጥቶ ልኳቸው ተጠሪ ያለመመለሳቸውተጠሪ በአመልካች መስሪያ ቤት ገንዘብ በመገልገል ጥቅም ማግኘታቸውን

የሚያረጋግጥ እና ይህም ጥቅም በገንዘብ ሊተመን የሚችል ሁኖ እያለ አመልካች ተጠሪ ጥቅም ማግኘቱን አላስረዳም በማለት የሰጡት ውሳኔ የክርክሩን ይዘትና ባህርይ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ጋር ያላገናዘበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሣኔ የክርክሩን ይዘት፣ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2164 /1/ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሠረት ያላደረገ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአውሮፕላንና የስልጠና ወጪን አስመልክቶ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80127 ሚያዚያ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137281 ሐምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ብር 179,742.94 (አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሁለት ብር ከዘጠና አራት ሳንቲም) ከዛሬ ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ 9%(ዘጠኝ ከመቶ) ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. ለአበል ወሰዱ በተባለው ብር 832.00 የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*

*ሃ/ወ*

የሰ/መ/ቁ.94181

ግንቦት 18/2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አደነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሽኩር ጀማል - ጠበቃ አቶ ሳሙኤል ደመቀ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሪት ኤደን ነጋሽ ጠበቃ አቶ ተስፋዬ ወረደ - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በስርቆት ወንጀል ለተወሰደ ንብረት ግምት የቀረበን የአንድነት ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረባቸው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችና ቢኒያም ታደስ ግምቱ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የሚሆን ንብረት ሰርቀው የወሰዱ መሆኑ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06338 ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ/ም በወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውን አርጋግጦ ውሳኔ ስጥቷል፡፡ አመልካች ለሱቅ የምከፍለው ኪራይና ዕቃዎች በመስረቃቸው የደረስብኝ ኪሳራ ብር 20,000 (ሃያ ሺ በር) ጨምርው እንዲከፍሉ ይወስንልኝ በማለት ክስ ያቀረበች ሲሆን በቢኒያም ታደስ ላይ ያቀረበችው ክስ እንዲቋረጥ አመልክታ ክሱ ተቋርጧል፡፡ አመልካች ንብረቶች ባለሀብት ከሳሽ መሆኗና የንብረቶቹ ግምት በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተከርክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በስርቆት ወንጀል ለተወሰዱት የተጠሪ ንብረቶችና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ አመልካች የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት ብር 85,000 (ሰማኒያ አምስት ሺ ብር) እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

2. አመልካች መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተሰረቁ የተባሉት ንብረቶች የተገዙበት ደረሰኝ አልቀረበም፡፡ በክርክሩ የግዴታ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወገን ተጠሪ ክሱ እንዲቋረጥ ጠይቃ እንዲቋረጥ አድርጋለች፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የዕቃውን ዋጋና የደረሰባትን ኪሳራ ሳታስረዳና በክስ የጠየቀችውን ገንዘብ በሙሉ አመልካች የመክፍል ኃላፊነት አለበት መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ታረምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የወንጀል ተካፋይ የነበረው ሰው አድራሻ አፈላልጌ ላገኘው አልቻልኩም፡፡ ዕቃው ተጭኖ የተወሰደው ከአመልካች ቤት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በስርቆት ለተወሰደው ንብረት ግምት የአንድነትና በነጣላ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ ውሳኔው ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ተጠሪ ክስ ያቀርበችበትን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. ጉዳዩን እንደመርመርነው  አመልካችና የፍትብሔር ክስ በከሳሽ ጠያቂነት የተቋረጠበት ቢኒያም ታደሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1)ሀ እና አንቀጽ 665 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ግምታቸው ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የሚሆኑ ንብረቶች ሰርቀው የወሰዱ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06338 ነሐሴ 7 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝብናል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች የንብረቶቹ ዋጋ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2035 እና የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2091 ድንጋጌን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

5. አመልካችና የወንጀል ስራ ተካፋይ የነበረው ቢኒያም የስርቁት ተጠሪ የንግድ ስራ የምታከናውንባቸውን ዕቃዎች እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ዕቃዎቹ በመሰረቃቸውና የንግድ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን ባለመቻሏ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ኪሳራ የደረሰባት መሆኗን ገልጻለች፡፡ ተጠሪ ይህንን ያህል ኪሳራ የደርሰባት ስለመሆኑ የማሰረዳት ግዴታ እንዳለበት በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 የማስረዳት ግዴታ ያለባት ቢሆንም፣ ይህንን ለማስረዳት በስር ፍርድ ቤት ያቀረበችው ማስረጃ ስለመኖሩ በውሳኔው አልገለፀም፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ብር 20,000 (ሃያ ሺ በር) የጉዳት ካሳ እንዲከፍል የወሰነው አመልካች ክሱን በግልጽ ክዶ መልስ አልሰጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ ሆኖም የካሳን ልክ በተመለከተ፣ ከሳሽ

የጠየቀውን የካሳ ገንዘብ ተካሳሽ በግልጽ አለመካዱ የካሳውን መጠን በሙሉ ወይም በከፊል እንዳመነ እንደማያስቆጥረው በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር ስናየው ተጠሪ በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 መሰረት በማስረጃ ያላረጋገጠችውን የጉዳት ካሳ ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) አመልካች ክዶ አልተከራከርም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ድንጋጌ ይዘት ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

6. አመልካች በስርቆት ወንጀሉ የተወሰዱ ንብረቶች ግምት እኔ ብቻ የመክፍል ኃላፊነት አለብህ መባሌ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የስርቆት ወንጀሉ ሙሉ ተካፋይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ ሰው ህግን በመጣስ በሌላ ሰው ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2035 ተደንግጓል፡፡ ሆነ ብሎ ሰዎች አንድ ሆነው በአንድ ጉዳይ ካሳ እንዲከፍሉ የተገደዱ እንደሆነ በአንድነት እያንዳንዳቸው ኃላፊ እንደሆኑና ለበደሉ ተግባር አነሳሽ በሆነውና በዋና አድራጊው እና በተባባሪዎች መካከል ልዩነት እንደማይደረግበት በፍትብሔር ህግ ቁጥር 2155 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ አመልካች በስርቆት ወንጀሉ ተካፋይ የሆነው ሁለት ሰዎች ሆነን እያለን እኔ የንብረቱ ሙሉ ዋጋ እንድከፍል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረበው ክርክር ከላይ የገለጽናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የጠየቀችውን ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) አመልካች እንዲከፍል የሰጠው የውሳኔ ክፍል ብቻ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተሰረቁትን የተጠሪ ንብረቶች ዋጋ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺ ብር) የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪ የጠየቀችውን ብር 20,000 (ሃያ ሺ ብር) ካሳ ይክፈል በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል የፍትብሔር ህግ ቁጥር 2141 እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.83 ድንጋጌዎች የሚጥስ በመሆኑ ተሽሯል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 98552

ሐምሌ 4 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-ሚ/ር አደም ሐሚድ - ጠበቃ አቶ ኪዳነማርያም ሃጉስ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡-ወ/ሮ ሐናእ አብዱልቃድር - ጠበቃ ደበበ መንግስቱ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡንመርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137912 ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ከህፃን ልጅ ማሣደጊያ የሚቆረጥ ገንዘብ መጠን የሚመለከት ክርክር ነውጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ /ከሳሽ/ ከተከሳሽ /አመልካች/ጋር የነበራት ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ገልፃ ከሳሽና ተከሳሽ በጋብቻ ስንኖር ህፃን ሁዳ አደም የተባለች ልጅ ወልደናል፡፡ ህፃኗ አንድ ዓመት ከአስር ወሯ ነው፡፡ ስለዚህ ለህፃኗ ማሳደጊያ የሚሆን በወር ብር 94,927 /ዘጠና አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሰባት ብር /ተከሳሽ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው ከሳሽ የጠየቀችውን ገንዘብ ተከሳሽ በየወሩ ለህፃኗ ማሳደጊያ ለመክፈል አልችልም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ ከሳሽ ተከሳሽ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው መሆኑን በመግለጽ ስለተከራከሩ የሥር ፍርድ ቤት የተከሳሹን ገቢ ለማረጋገጥ የተለያዩ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጠይቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ /ተጠሪ ህፃኗን ለማሳደግ የሚያስፈልጋት የትምህርትና ሌሎች ወጪዎች በሰንጠረዥ

መልክ አዘጋጅታ ያቀረበችውን የወጭ ዝርዝር ተመልክቶ ተከሳሽ ለሕፃኗ ማሳደጊያ በወር ብር 50,000 /ሃምሳ ሺ.ህ ብር / እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

2. በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይግባኝ ባይ /አመልካች / ለህፃኗ ማሳደጊያ በወር 12,000 /አስራ ሁለት ሺ. ብር / እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ የኑሮ ደረጃ አንድ ህፃን ለማሳደግ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነውን ከሚፈለገው መጠን በላይ ነው፡፡ የአመልካች ትክክለኛ ገቢ አልተረጋገጠም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ብር 12,000/ አስራ ሁለት ሺ.ህ ብር/ እንዲከፍል የወሰነው ውሳኔውን ከሰጠበት ታህሳስ 4 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ማለት ከሐምሌ 19 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ለህፃን ማሳደግያ ብር 50,000 /ሃምሳ ሺ.ህ ብር / እንዲከፍል የሰጠውን ውሳኔ ሳያሻሽለው አልፎታል፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ በሰበር አቤቱታው ሚያዚያ 20 ቀን 2006 ዓ.ም ፅፎ ያቀረባቸው መልስ የህፃን ማሳደጊያ ገንዘብ የጠየቅሁት ለህፃኗ የትምህርት ቤት የትራንስፓርት የአልባሣት የቀለብና ሌሎች ወጪዎችን በመዘርዘር ነው፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገቢ በዓመት ያገኝ መሆኑ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በላከው መረጃ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከኢትዮጵያ ውጭ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኙ የተለያዩ የንግድ ድርጅቶች እና የአክሲዮን ድርሻ ያለው ነው፡፡ አመልካች ከሌላ የወለዳቸውን ልጆቹን ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እየከፈለ እያሳደገ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካች ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካች ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለህፃን ማሳደጊያ አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው በሕግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም ? የሚውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሣስሮ በነበረበት ወቅት ለወለዳት ህፃን ሁዳ አደም ለማሣደግ የሚያስፈልገውን ወጪ የመጋራትና የመሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑ አላከራከረም አመልካችንና ተጠሪ የሚያከራክረው አመልካች ለህፃኗ አስተዳደግ ሊከፍለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን የሚወስነው እንደባለ ጉዳዩ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልምድ የሚስማማውን በመከተል በቀለብ ተቀባዩ

ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደ ሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑትን ወጭዎች የሚሸፍን መሆን እንደሚገባው በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመውና የአክሲዮን ባለድርሻ ከሆኑበት የንግድ ድርጅት በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ በዓመት የሚያገኙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

6. ይህም በመሆኑ ህፃኗን ለማሳደግ የሚያስፈልግ፣ የምግብ፣ የመኖሪያ፣ የጤና አጠባበቅና የትምህርት ወጭ ሲታሰብ፣ አንድ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ቤተሰብ፣ ህፃን ልጁን በጥሩ ሁኔታ ለመመገብ፤ በጥሩ መኖሪያ አካባቢ ለማኖርና ጤናው ለመጠበቅ እንዲሁም ጥሩ ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጭ መሠረት በማድረግ ሊወሰን ይገባዋል፡፡ ይህም ማለት አመልካች ለህፃኗ ማሳደጊያ የሚከፍለው ገንዘብ ገቢያቸው ስለማይፈቅድላቸው በህፃን አስተዳዳር አስፈላጊ የሆኑ የምግብ አይነቶች ንጥረ ነገሮች በተሟላ ሁኔታ ሣያቀርቡ፣ ህፃን ልጆቻቸው በየወቅቱ የጤና ክትትልና ምርመራ ሣያደርጉ ምቹና ፅዳት በጐደለው የመኖሪያ ቤት ውስጥ ህፃን ልጃቸው ለማኖርና ለማሣደግ ሁኔታው ያስገደዳቸዉን ወላጆች ለህፃን ልጆቻቸው የሚያወጡትን ዝቅተኛ ገንዘብ መሠረት በማድረግ ሊወሰን አይገባውም ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ህፃኗን ለማሣደግ ከብር 2000 በላይ አስፈላጊ አይደለም በማለት ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

7. የአመልካች ከፍተኛ ገቢ ያለው መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ገቢውን በተመለከተ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር በሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 20 ለዚህ ችሎት የተሰጠውን ሥልጣን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነውን የቀለብ ገንዘብ ህፃኗን መዋለ ህፃናት ለማስገባትና ለማማላለስ ህፃኗን ለጤና ምቹ የሆነ መኖሪያ ቤት ውስጥ ለማኖር ሕፃኗ የተሟላ ምግብ ፣ አልባሳትና መጫወቻ እንዲኖራት ለማድረግ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ ስለመሆኑ አመልካች የማስረዳት ግዴታውን አልተወጣም፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ ሁኔታ አንድ ህፃን ለማሳደግ ከብር 2000 በላይ አስፈላጊ እንደልሆነ በጥቅል አገላለፅ ተከራክሯል፡፡ ይህም አመልካቹ የህፃኗ አስተዳደግ ስስታዊ ሣይሆን ዝቅተኛ ገቢ ስላላቸው የልጆቻቸውን መሠረታዊ ፍላጉት የማያሟሉና የልጆችቻውን ፍላጐት ገድበው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት መንገድ እንዲሆንለት የሚያከራክር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የአመልካች መከራከሪያ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 197 እና አንቀጽ

202 ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተበቀልውም፡፡ በዚህ ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች ለህፃኗ አስተዳደግ እንዲከፍል የወሰነው የቀለብ ገንዘብ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 85815

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ኢብራሂም መሐመድ ኑር - ጠበቃ አሽናፊ ወጁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪዎች፡-

1. ወ/ሮ ጀሚላ መሐመድ ኑር
2. አቶ ሰይድ መሐመድ ኑር
3. ወ/ሮ ነጃት መሐመድ ኑር
4. ወ/ሮ ሐያት መሐመድ ኑር

የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት የአሁኖቹ ተጠሪዎች የሚች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ እንዲቀርብ ከተደረገ በኃላ በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርት አሻሽሎ በማጽናት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ተጠሪዎቹ የሚች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን ሲሉ በወ/ሮ ባህሯ አብዱ፣በአሁኑ አመልካች እና በአቶ ጀማል መሐመድ ኑር ላይ በ18/08/2002 ዓ.ም. የተጻፈ አቤቱታ ማቅረባቸውን፣1ኛ እና 3ኛተጠሪ የነበሩት ወገኖች ውርሱ ቢጣራ ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው የሚች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ አስቀድሞ በሸሪዓ ፍ/ቤት በውሳኔ ያለቀ በመሆኑ በድጋሚ የውርስ ይጣራልን አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬ ጉዳዩ ረገድም መልስ ሰጥተው መከራከራቸውን፣ፍ/ቤቱም

በ12/02/2003 ዓ.ም. በሰጠው ውሳኔ አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥብ ውድቅ አድርጎ በማለፍ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ይቀርብ ዘንድ አጣሪ እንዲመደብ ማድረጉን፣የማጣራቱ ሂደት መጀመሩን ተከትሎ አመልካች የውርስ ይጣራልን አቤቱታው በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ለአጣሪው ማቅረባቸውን፣አጣሪውም የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ መቅረብ የሚገባው ለፍርድ ቤቱ እንጂ ለአጣሪው አለመሆኑን በመግለጽ የማጣራቱን ሂደት አጠናቆ የወራሾችን ማንነት እና የውርሱን ሀብት በመለየት በ10/06/2003 ዓ.ም. የተጻፈ ሪፖርት ማቅረቡን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ሪፖርቱን አሻሽሎ ማጽደቁን፣አመልካች በአጣሪው ሪፖርት ላይ ካቀረቡት አስተያየት መካከል የውርስ ይጣራልን አቤቱታው በይርጋ የሚታገድ ነው የሚል ነጥብ የሚገኝበት መሆኑን፣ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ አመልካች ይህንን የመቃወሚያ ነጥብ ማቅረብ ይገባቸው የነበረው ለውርስ ይጣራልን አቤቱታው የመከላከያ መልስ በሰጡበት ጊዜ እንጂ ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኂላ አይደለም በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ሳይቀበለው መቅረቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪው ሪፖርት ተሻሽሎ የጸደቀበትን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የታየው ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊታይ አይገባውም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ እና የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ በተያዘው ጭብጥ መሰረት በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት በይርጋ በታገደ ጉዳይ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኃላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ስረ ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ክርክር

ለማቅረብ እንደማይችሉ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 5(1) ስር የተደነገገ ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ በተከሳሽ ወገን ሊቀርቡ ከሚችሉ የመቃወሚያ ነጥቦች ውስጥ የሚካተት ስለመሆኑ፣ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣እንዲሁም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ባለጉዳዮችን ማሰናበት የሚገባው ስለመሆኑ እንደቅደም ተከተሉ በዚሁ ሕግ በቁጥር 244(2)(ለ)፣244(1) እና 245(2) ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎቹ የሟች አባታችን የአቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ይጣራልን በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ላቀረቡት አቤቱታ አመልካች በሰጡት የመከላከያ መልስ የሟች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ አስቀድሞ በክልል 14 መስተዳድር በ2ኛ ናዒባ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 1952/88 ታይቶ በ25/11/1988 ዓ.ም. እልባት ያገኘ በመሆኑ በድጋሚ የክርክር ምክንያት ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በዚህ የመቃወሚያ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ እንደተባለው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በሟች አቶ መሐመድ ኑር ኢብራሂም ውርስ ጉዳይ ውሳኔ መስጠቱን ተቀብሎ ነገር ግን የሸሪዓ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሰጠው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34(5) እና የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 4(2) እና 5(1) መሰረት የአሁኖቹ ተጠሪዎች በሸሪዓ ፍርድ ቤት ቀርበው ለመዳኘት ፈቃደኞች መሆናቸውን ካረጋገጡ በኂላ ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት እንደማያረጋግጥ ገልጾ የአሁኑ አመልካች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በ12/02/2003 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ውድቅ በማድረግ ውርሱ እንዲጣራ መወሰኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በመዝገብ ቁጥር 102345 በ27/03/2004 ዓ.ም.በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱን እና ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታም በመዝገብ ቁጥር 77308 በ24/08/2004 ዓ.ም. በአጣሪ ችሎት ተቀባይነት ማጣቱን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡አመልካች ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ የሰበር አጣሪ ችሎትን ጨምሮ በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች አስቀድሞ ተቀባይነት ያጣ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ የመቃወሚያ ነጥቡ ውድቅ የተደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ሊታይ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በማለት አመልካች በዚህ ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የይርጋ መቃወሚያ በመከራከሪያነት ለማቅረብ ለተከሳሽ ወገን ከተሰጡት መብቶች ውስጥ የሚካተት ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መቃወሚያ መቅረብ የሚገባውም ተከሳሽ ወገን ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልሱን በሚያቀርብበት ጊዜ በመከላከያ መልሱ ውስጥ በማካተት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 234(1)(ሐ) እና 244(2)(ሠ) ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡በዚህ ሁኔታ መቅረብ ከሚገባቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ሳይቀርቡ የቀሩት ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክሉ እስካልሆነ ድረስ ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተዋቸው የሚቆጠሩ ስለመሆኑም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 244(3) ድንጋጌ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ሳይቀበል የቀረው እና ይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ቅሬታ ውድቅ ያደረገው ውርሱ እንዲጣራ ለቀረበባቸው ክስ መልስ በሰጡበት ጊዜ የይርጋ መቃወሚያ ሳያቀርቡ ቀርተው መቃወሚያውን በውርስ አጣሪው ዘንድ እና ቀጥሎም ውርሱ ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበ በኂላ በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ በተጠየቁበት ጊዜ ቀደም ሲል ያላነሱትን የይርጋ መቃወሚያ ማንሳታቸው ስነ ስርዓታዊ አለመሆኑን በመግለጽ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡የይርጋ መቃወሚያውን ለክሱ በሰጡት የመከላከያ መልስ አካተው ያላቀረቡ ስለመሆኑ ደግሞ አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም ላይ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ለክሱ በሰጡት የመከላከያ መልስ የይርጋ መቃወሚያ እንዳላቀረቡ የተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ከጊዜ በኂላ ያቀረቡትን የይርጋ መቃወሚያ አለመቀበላቸው ሊነቀፍ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 169123 በ06/09/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 126004 በ26/03/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ቁጥሩ 1952/88 የሆነው የሸሪዓ ፍርድ ቤት መዝገብ ተመላሽ ይደረግ፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.93987

ሐምሌ 18 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች:-** 1. አቶ ዳንኤል ወንዳፈራ
2. አቶ ቴዎድሮስ ወንዳፈራ } ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ:-** 1.ወ/ሮ አስናቀች ቦጋለ
2.ማቆያ ቦጋለ
3.ስንቅነሽ ቦጋለ } የቀረበ የለም፡፡
4.ፋኖሴ ቦጋለ ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የተደነገጉትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ የቀረበ የፍርድ መቃወሚያን የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች አቶ ቦጋለ ታደሰ ጥቅምት 09 ቀን 1990 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኃላ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያፈሩት በበቆጂ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ በ147.4 ካ.ሜትር ቦታ የሰፈረውን አራት ክፍል ቤት የውርስ ድርሻ ይገባናል የሚለው የአመልካቾችና የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጥያቄ ነው፡፡ ሁሉም ተጠሪዎች የሟች አቶ ቦጋለ ታደሰ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ደግሞ የተጠሪዎች እህት የሆኑትና የሟቹ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የነበሩት የወ/ሮ ደመቀች ቦጋለ ልጆች ሁነው እናታቸውን ተክተው አያታቸውን አቶ ቦጋለ ታደሰን ለመውረስ ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን መዝገቡ

ያሳያል፡፡ አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የሌሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሚቹን ውርስ ንብረት እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት የሚያገኙትን መብት የሚነካ ነው በማለት የአሁኑ አመልካቾች ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በወረዳው ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጎ በበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት ማጣቱ ያላግባብ ነው የሚለው አቤቱታ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት የተጠቁስት ተጠሪዎች 4ኛ ተጠሪን በመክሰስ የሚች አቶ ቦጋለ ታደሰን የውርስ ንብረት እንዲካፈሉ በሌሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ እናታችን ወ/ሮ ደመቀች ቦጋለን በመተካት ልናገኝ የሚገባንን ድርሻ ያስቀረ ነው በማለት ፍርድ ለመቃወም አቤቱታቸውን ነሐሴ 17 ቀን 2004 ዓ/ም ፅፈው ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤትም የአሁኑ ተጠሪዎች በአመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጡበት አድርጎ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የአመልካቾችን የፍርድ መቃወሚያ ደግፈው አመልካቾች የእናታቸውን ድርሻ ቢያገኙ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን የአሁኗ 4ኛ ተጠሪ ግን በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠውና ለፍርድ መቃወሚያ መሰረት የሆነው ፍርድ በተጠሪዋ ይግባኝ ባይነት ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመ/ቁጥር 38439 ነሀሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም በተሰጠው ፍርድ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ የመጨረሻ ፍርድ ማግኘቱን ገልጸው መቃወሚያው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው ተከራክረዋል፡፡

የፍርድ መቃወሚያውን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የሌሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤትም 4ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ በመቀበል በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በተሻረ ውሳኔ የፍርድ መቃወሚያውን ለማስተናገድ ስልጣን የሌለው መሆኑን ጠቅሶ የአመልካቾችን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245(2) ድንጋጌን ጠቅሶ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በመ/ቁጥር 39725 ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተዘግቶባቸዋል፡፡እንዲሁም አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በመ/ቁጥር 158733 በሆነው ሐምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች በሰጡት ብይን ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ ሁኖባቸዋል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38439 ነሀሴ 18 ቀን 2004 ዓ/ም ለፍርድ መቃወሚያ የሆነውን ፍርድ የሻረበት ፍርድ በክልሉ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 151765 በሆነው ህዳር 29 ቀን 2005 ዓ/ም ተሽሮ በጉዳዩ ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጸንቶ እያለ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ የለም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው፣ የውርስ ንብረት ድርሻ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያጣውም አከራካሪውን ንብረት በእጃቸው አስገብተው ለብዙ አመታት ከተጠሪዎች ጋር እኩል ሲጠቀሙበት የነበረ ሁኖ እያለ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ብይን ሕጉን መሰረት ያላደረገ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡በዚህም መሰረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ያሉት ተጠሪዎች አመልካቾችን ደግፈው የሚከራከሩ ሲሆን 4ኛ ተጠሪ ግን አመልካቾች አለን የሚሉት ውሳኔ በተጠሪዋ አቤት ባይነት፣ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ተጠሪነት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲታይ ቆይቶ በዚህ ችሎት ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት የተጠቀሱት ተጠሪዎች የውርስ ንብረት ይገባናል ጥያቄ በሕጉ አግባብ በተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ያልቀረበ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነው ተብሎ በመ/ቁጥር 158019 መስከረም 13 ቀን 2006 ዓ/ም የተወሰነ ሲሆን በውጤቱም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 151765 ጥቅምት 29 ቀን 2002 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የሻረ መሆኑን ገልፀው አመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርቡት ፍርድ የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር ሲባል የተያዘው ጭብጥ የአመልካቾች መቃወሚያ ጉዳዩ ተፈፅሟል ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ሲሆን እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር በማየት ጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት የሚቻል መሆኑን ያለመሆኑን መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአሁኗ 4ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡት የውርስ ንብረት ይገባናል ክርክር በመጨረሻ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ የከሳሾች ክስ በሶስት አመት የይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ተብሎ በመ/ቁጥር 158019 በሆነው መስከረም 13 ቀን 2006 ዓ/ም ውሳኔ ያገኘ ሲሆን በዚህም ውሳኔ መሰረት በወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠና የአመልካቾችን መብት ይነካል የተባለ ውሳኔ ጭምር የተሻረ መሆኑን ውሳኔው የሚያሳይ መሆኑን፣ከዚህም በኋላ በዚህ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአሁኑ 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አመልካች፣4ኛ ተጠሪ ደግሞ ተጠሪ ሁነው ተሰይመው ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር አቤቱታ የሥር ከሳሾች አቅርበውበት አጣሪ ችሎት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 158019 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት በመ/ቁጥር 94954 በሆነው ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የመጨረሻ ትዕዛዝ የሠጠበት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

ወደ ሕጉ ስንመጣም በመሰረቱ አንድ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራበት ሥርዓት የሚገዛው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርኣት ሕጋችንና በክልሎች ስራ ላይ ባሉት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሆኑ እሙን ነው፡፡የ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ሕጋችን ከያዛቸው ስርዓቶች መካከል በፍርድ ላይ የሚቀርበው ተቃውሞ እና በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርበው ጣልቃ ገብነትን የሚገዙት ድንጋጌዎች ይገኙበታል፡፡እነዚህ አቤቱታዎችን የሚገዙት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 418 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አንድ የክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባው ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ እና ውሳኔውም ያረፈው በአንድ የክርክሩ ምክንያት በሆነ ንብረት ላይ ሁኖ ይህንኑ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገንን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ከተረጋገጠ ፍርዱ ይኸው ወገን ባለበት እንዲታይና በሕግና በማስረጃ የተደገፈ ሁኖ ሲገኝ እንዲነሳለት የሚደነግግ ነው፡፡አቤቱታው የሚቀርብበት ሥርዓትም በቁጥር 359 ስር በተመለከተው መንገድ መሆን እንደአለበት የተቀመጠ ሲሆን ይህ ድንጋጌ የመቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በክስ አመሰራረት አይነት ሁኖ ማስረጃ ዝርዝር ሁሉ ይህንኑ ስርዓት ማሟላት እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘቱና መንፈሱ ሲታይ ክርክሩ መኖሩን ከጅምሩ እያወቀ ውጤቱን በመጠበቅ ከፍርዱ በኂላ የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርበውን ወገን አቤቱታውን በመቀበል ለማስተናገድ አስፈላጊ ያለመሆኑን ሁሉ ያስገነዝባል፡፡ ይህም የክርክር አቀራረብ በቅን ልቦና የተመሰረተ ሁኖ በአነስተኛ ወጪ፣ ጉልበትና አጭር ጊዜ ፍትሐዊነት ያለውን ውሳኔ ለመስጠት የሚቻልበት አግባብ እንዲኖር እና ሕግ አውጪ ከፈለገበት አላማ ጋር መጣጣም ያለበት መሆኑም የሚታመን ነው፡፡ እንግዲህ አቤቱታውን የሚያቀርበው ወገን የቅን ልቦና ተከራካሪ ሁኖ መሰረታዊ መብቱን ማስከበር የሚችልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ እንዲኖር ሕግ አውጪ የፈለገ ሲሆን ይህንኑ መመዘኛ የሚያሟላ አቤቱታ አቅራቢ የሚቃወመው ፍርድ ዋጋ ያለው፣ያልተፈፀመ መሆን እንደአለበትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘት ያስረዳል፡፡በሌላ አገላለፅ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ያልተሻረና አፈጻጸሙም ያልተጠናቀቀ ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ ያሳያል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት የምናገኘውን መብት የነካ ነው የሚሉት ፍርድ በመጨረሻ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሻረ ከመሆኑም በላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት

ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ የፍርድ መቃወሚያ የሚቀርብበት ፍርድ በወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ አለ ለማለት የሚቻልበት ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ዋጋ ያለው ፍርድ በወረዳው ፍርድ ቤት የሌለ መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ በወረዳው ፍርድ ቤት የሚስተናገድበት አግባብ የለም፡፡ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውጤቱ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በሌሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17198 ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39725 ታህሳስ 05 ቀን 2005 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 158733 ሀምሌ 23 ቀን 2005 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን ውጤቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የፍርድ መቃወሚያ ያቀረቡበት ፍርድ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተሽሮ የመጨረሻ እልባት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም ያገኘ በመሆኑ አቤቱታቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 94322

ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ በቀለ - ወኪል ቅጅነህ ለማ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ገዛኸኝ በቀለ - ከጠበቃ በጅጋ ሶሬቻ ጋር ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ስለውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ፣ተከሳሽ ደግሞ የአሁኗ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪ ታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ ሲሆን ወላጅ አባታቸው አቶ በቀለ ባልቻ ከዚህ አለም በሞት ህዳር 20 ቀን 2003 ዓ/ም መለያታቸውንና በህይወት በነበሩት ጊዜ በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 07 ውስጥ በካርታ ቁጥር 7/17/1 የሚታወቀውንና ቁጥሩ 290 የሆነው መኖሪያ ቤት ያፈሩ ቢሆንም ተጠሪንና አመልካችን ጨምሮ ስድስት ሕጋዊ ወራሾች እያሉ የአሁኗ አመልካች ብቸኛ ወራሽ በመምሰል ቤቱን ይዘው እንደሚገኙና የቤቱ ግምት 80,000.00 (ሰማንያ ሺ.ህ) መሆኑን ጠቅሰው ከቤቱ ግምት የተጠሪ ድርሻ የሆነውን ብር 13,000.00 (አስራ ሶስት ሺ.ህ) ድርሻቸውን እንዲያገኙ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም፡- ክሱ በአስር አመት ይርጋ እንደሚታገድ፣ተጠሪ ድርሻዬ ይገባኛል ከማለት ውጪ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን፣ወ/ሮ ጽጌ የሚች ልጅ ያለመሆናቸውንና እልፍነሽ፣ዝናሽ፣እና ፀሐይ ከተባሉት የሚች ወራሾች ጋር ፍርድ ቤት ቀርበው ስምምነት ማድረጋቸውን፣ በአከራካሪው ቤት ላይ በሚች ስም የባለቤትነት ደብተር የወጣው ተጠሪ ማዘጋጃ ቤቱን በማሳሳት መሆኑን፣ቤቱ ያለበት የቦታ ስፋትም 200 ካ/ሜትር ሳይሆን 400 ካ.ሜትር ሁኖ አከራካሪውን ቤት አባታቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅት ሕዳር 27 ቀን 1985 ዓ/ም ከሃያ አመት በፊት ሰጥተዋቸው የሚቹ ወራሾችም ይኼው ተነግሯቸው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን፣በቤቱ ላይ መብራት፣ስልክና ውሃ በስማቸው ማስገባታቸውንና ከሃያ አመት በላይ ሲጠቀሙበት ለነበሩት ንብረት ተጠሪ ወራሽ ነኝ በማለት ክስ ማቅረባቸው

ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችንም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮችን ውድቅ አድርጎ አመልካች ለተጠሪ ድርሻቸውን ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺህ) እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡አመልካች ለተጠሪ ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺህ) እንዲከፍሉ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የውርስ ቤቱን የገበያ ዋጋን መሰረት ያደረገውን ድርሻ እንጂ በክሱ ጊዜ የተጠቀሰውን ግምት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡የአሁኗ በዚሁ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤቱ የግሌ ነው የሚል ክርክር አቅርበው የነበሩ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር መስቀልኛ ይግባኝ የቀረበበት ባለመሆኑ ስነስርዓታዊ አይደለም ሲል አልፎታል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች ይግባኛቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-አከራካሪውን ቤት በ1985 ዓ/ም ከወላጅ አባታቸው ያገኙትና ከሃያ አመታት በላይ ሲጠቀሙበት የቆየ ሁኖ እያለ ተጠሪ ድርሻቸውን በገበያ ዋጋ እንዲወስዱ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም አከራካሪው ቤት በሚች አውራሽ ፈቃድ ለመሰራቱ በፅሑፍ ሰነድ በቀረበበት የበታች ፍርድ ቤቶች ለአመልካች ስለሚከፈለው ግምት ያለመወሰናቸው እንዲሁም ተጠሪን ሳይጨምር ሌሎች አራት ወራሾች ቀደም ሲል ውርሱ ሲጣራ ድርሻቸውን ለአመልካች መልቀቃቸው በስር ፍርድ ቤቶች ታልፎ የተጠሪ ድርሻ የቤቱ ግማሽ ነው ተብሎ መባሉና የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን አስቀርተው የተጠሪን ድርሻ ይክፈሉ በማለት የወሰነው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ተጠሪ በሰጡት መልስም አመልካች በቤቱ ላይ አለኝ የሚሉትን መብት በተመለከተ ስርዓቱን ጠብቀው ይግባኝ ያላቀረበበት መሆኑን ጠቅሰው ቤቱ የግሌ ነው በማለት የሚያቀርቡት ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አከራካሪውን ቤት የሚች በቀለ ባልቻ የውርስ ንብረት ነው በማለት ተጠሪ በልጅነታቸው ድርሻቸው በተጠሪ እንዲሰጣቸው ክስ አቅርበው አመልካች ቤቱ

የግሌ ነው የሚል ክርክር አቅርበው በወረዳው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ካጡ በኋላ ፍርድ ቤቱ ለክሱ መሰረት ከሆነው የቤቱ ግምት ከብር 80,000.00(ሰማንያ ሺ.ህ) ውስጥ ለስድስት ወራሾች እኩል ሲካፈል የሚመጣው ውጤት ብር 13,000.00(አስራ ሶስት ሺ.ህ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ መወሰኑን፣በዚህ ውሳኔ በከፊል ያልተስማሙት የአሁኑ ተጠሪ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ድርሻዬን ላገኝ ይገባል በማለት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ያገኙ መሆኑን፣አመልካች በስርዓቱ መሰረት ቤቱ የግሌ ነው የሚለውን ይግባኝ ከወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያላቀረቡ መሆኑንና ባሁኑ የክርክር ደረጃ ደግሞ ቤቱ የግሌ ነው የሚለውን ክርክር አጥብቀው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በየርከኑ ባሉት ፍርድ ቤቶች የሚታየው ክርክር የሚመራው በስነ ስርዓት ህጉ በተዘረጋው ስርዓት መሆኑ ይታወቃል፡፡ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅሬታ ያለበት ወገን ቅሬታውን በይግባኝ ወይም በመስቀለኛ ይግባኝ ለማሳየት የሚችል ስነ ስርዓት ሕጉ ያሳያል፡፡እነዚህ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓቶች የየራሳቸው ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ሲሆን በማን ሊቀርቡ እንደሚገባም ስነ ስርዓት ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ይግባኝ ማለት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ፍርድ ቅሬታ ያለበት ወገን ይህንኑ ቅሬታውን በህጉ ስልጣን በተሰጠው የበላይ ፍ/ቤት አቅርቦ በማሣየት በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ እንዲሻሻል እንዲለወጥ፣ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ እንዲሆን ዳኘነት የሚጠየቅበት ሥርአት ነው፡፡ ይግባኝ ለተከራካሪ ወገኖች የተሰጠ መብት ቢሆንም ገደብ የለሽ ግን አይደለም፡፡ በሌላ አገላለጽ በማናቸውም ፍርድ ወይም ትእዛዝ ላይ ሁሉ ይግባኝ ለማለት የማይቻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም በግልጽ በሕግ ሊመለከት ይችላል፡፡ ለዚህ ዓይነት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 ስር የተመለከተው ድንጋጌ በዋቢነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በመሆኑም በአንድ ፍርድ ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ መለኪያው ሊሆን የሚገባው በተሰጠው ፍርድ ወይም ትእዛዝ ተከራካሪ ወገን መብት የሚጐዳ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠ ውሣኔ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካ አሊያም ግዴታው ከፍ እንዲል የተደረገ ወገን የይግባኝ መብት ይኖረዋል፡፡ የይግባኝ ዓይነቱም ቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ(cross-appeal) ሊሆን ይችላል፡፡ የይግባኝ ዓይነቱ ቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚቀርበው ፍርዱ የይግባኝ አቅራቢውን መብት በሚጐዳው መልክየሚነካ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ከተከራካሪ ወገኖች የቀረቡለትን ሁሉንም የክርክር ነጥቦች መሰረት ያላደረገ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ጠቃሚ ሁኖ ከተገኘ ለውሣኔው መሰረት ይሆን ነበር የሚባል ምክንያት ብቻ በመያዝ ይግባኝ ሊል ይገባል ማለት የይግባኝ ሥርአትን መሰረታዊ ዓላማና መመዘኛውን እንዲሁም የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ ሥርአትን ዓላማ ያገናዘበ አይሆንም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመከራከሪያ ነጥቡን ያቀረበ እና ከመከራከሪያ ነጥቦቹ መካከል በአንዱም እንኳ ቢሆን በውሣኔው

ውጤት ተጠቃሚ የሆነ ወገን በስር ፍ/ቤት ለውሣኔው መሰረት ባልሆነው መከራከሪያ ነጥብ ብቻ ቀጥታ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ሣያቀርብ መከራከሪያ ነጥቡን በበላይ ፍ/ቤት በመልሱ እስከአቀረበ ድረስ ተቀባይነት አያገኝም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ቤቱ የውርስ ንብረት አይደለም፤የግሌ ነው የሚል ክርክር ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ለተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቁት የአሁኑ ተጠሪ ሁነው አመልካች ቤቱ የግል ተብሎ መወሰን ሲገባ መታለፉ ያለግባብ ነው በማለት ቀጥተኛ ይግባኝ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ይግባኝ አላቀረቡም፡፡እንዲህ ሳያደርጉ ቤቱ የግሌ ነው በማለት በይግባኝ መልሳቸው ላይ ክርክር ማቅረባቸው ተቀባይነት የሚያገኙበት አግባብ የለም፡፡ምክንያቱም ከመሰረቱ በወረዳው ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ተጠቃሚ የነበሩ ስለመሆኑ ውሳኔው አያሳይም፡፡ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ተቃውሞ በመቀበል አመልካች ቤቱ የግሌ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክርና የዚህ ሰበር ሰሚ አጣሪ ችሎትም በዚህ ረገድ የያዘው ጭብጥ የክርክሩን ሂደት ያላገናዘበ እና ስነ ስርዓታዊ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ነጥብ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ መወሰኑ የውርስ ንብረት ሊከፋፈል የሚገባበትን የክፍፍል ስርዓት ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡በመሰረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር የሚከናወንበትን መንገድ የፍትሐብሔር ሕጋችን ግልጽ ድንጋጌዎችን ይዞ እናገኛለን፡፡ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ ወራሾች ያልተስማሙ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳው የክፍያ ሐሳብ እንዲፀድቅ ለዳኞች ቀርቦ በሚጸድቀው አግባብ ሊከናወን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡ ሕጉ የመከፋፈሉ አፈፃፀም ደንብንም በቁጥር 1082 አስቀምጧል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረት ክፍያው የሚፈፀመው ሟቹ በፃፈው የኑዛዜ ቃል እንደሆነ፣ ስለክፍያው አፈፃፀም የተፃፈ ኑዛዜ ቃል ከሌለ ደግሞ በሕጉ በተዘረጋ ስርዓት መሰረት መደረግ እንዳለበት ያሣያል፡፡ የክፍፍሉ ደንብ በሕጉ የሚከናወንበትን አግባብ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች በቁጥር 1083 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ ቁጥር 1086 ሲሆን ይህ ድንጋጌ የውርስ ንብረት የሚከፋፈልበትን መርህ የሚያስቀምጥ ሲሆን ዝርዝር ይዘቱ ሲታይም ክፍያው በመሰረቱ የሚደረገው እያንዳንዱ ወራሽ ከውርሱ ውስጥ ንብረት እየተሰጠው በአይነት ስለመሆኑና በአይነት የተመደቡት ድርሻዎች ትክክል ያልሆኑ እንደሆነ ተጨማሪ ገንዘብ በመስጠት እንደሚስተካከሉ የሚገልጽ ነው፡፡ የድርሻዎቹን አመዳደብ ስርዓትም በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ ወራሽ በሚሰጠው የጎላ ጠቀሜታ ምርኩዝ ተደርጎ ሊከናወን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1087/2/ ድንጋጌ ስር በግልጽ ሰፍሯል፡፡ስለውርስ ንብረት ክፍፍል የሚደነግጉት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ክፍፍሉ በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ቀዳሚ የክፍፍል ሥርዓት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም

በጨረታ የውርስ ንብረት በመሸጥ ወራሾች እንዲከፋፈሉ የሚደረገው ሕጉ በአስገዳጅነት ያስቀመጠው በአይነት የማከፋፈል መንገድ የማይቻል መሆኑና በሕጉ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡የውርስ ንብረት ወራሾች በአይነት እንዲከፋፈሉ ማድረግ ቅድሚያ የሚፈጸም የክፍፍል ስርዓት ስለመሆኑ ሕጉ ከአስቀመጠ ደግሞ ከወራሾቹ አንዱ ወይም ሌላው ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ በመፈለጉ ብቻ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ ሊደረግ አይገባም፡፡ሕጉ ለውርስ ንብረት ክፍፍል በአይነት የመከፋፈል ስርዓት በቅድሚያ እንዲከናወን ወይም መርህ ሁኖ እንዲቀመጥ የፈለገውም ሕብረተሰቡ ለውርስ ንብረት የሚሰጠውን የተለየ ቦታ ግምት ውስጥ አስገብቶ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የውርስ ንብረት በሐራጅ የመሸጥ ስርዓት ተግባራዊ የሚሆንበትን አግባብ ሕጉ በቁጥር 1092 ድንጋጌ ከአስቀመጠው ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የውርስ ሀብት ውስጥ ከፍ ያለ ጉዳት ሳይደርስባቸው ሊከፈሉ የማይችሉ ንብረቶች ያሉ እንደሆነና ከወራሾቹ መካከል ይህን የማይከፈል ሀብት ሊወስድ የሚገባው የትኛው እንደሆነ በስምምነት ለመወሰን ያልቻሉ ከሆነ ስለመሆኑ ድንጋጌው ያሳያል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ቀጣይ ስለመሆኑ የሚያስገነዝበው ቁጥር 1093 ድንጋጌ ሲታይም ከወራሾቹ መካከል አንደኛው ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሽያጩ በወራሾች መካከል በሐራጅ ሊደረግ እንደሚገባ፣ በወራሾች መካከል ስምምነት ከታጣም በሐራጅ ጨረታ ውስጥ ባዕድ ሰዎች እንዲገቡ ሊደረግ እንደሚገባ እንደ የቅደም ተከተላቸው በንዑስ ቁጥር አንድና በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌዎች ስር አስቀምጧል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የውርስ ንብረት ክፍፍል ስርዓት በሕጉ የተመለከቱትን መንገዶች በመጠበቅ ሊከናወን ሊገባ ስለመሆኑና በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ንብረቱ ከወራሾቹ እጅ በቀላሉ እንዲወጣ የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የውርስ ሀብት በጨረታ እንዲሸጥ ሊደረግ የሚገባው በፍ/ሕ/ቁጥር 1093 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የበላይ ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በጨረታ እንዲሸጥ የወሰኑት ከላይ የተመለከቱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን ተከትለው ያለመሆኑን፣የወረዳው ፍርድ ቤትም ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲያገኙ ያደረገው የገበያ ዋጋን መሰረት ባደረገ መልኩ ያለመሆኑን ከውሳኔዎቹ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች የውርስ ንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡ክፍፍሉ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት ስንመለከተውም ተጠሪ ቤቱ በአይነት ሊካፈል የሚችል መሆኑን ጠቅሰው የክፍፍሉ ስርዓትም በውርስ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲከናወን ዳኝነት ያለመጠየቃቸውን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤቱን እንዲያስቀሩ በወረዳው ፍርድ ቤትም ተወስኖላቸው የነበረ ሲሆን ቤቱ በጨረታ ሊሸጥ ይገባል ተብሎ ከተሰጠው ውሳኔም ስርዓቱም ጠብቀው በመከራከር ላይ የሚገኙ መሆኑንና

የጠየቁት ከፍተኛው ዳኝነትም ቤቱ የግሌ ሊባል ይገባል የሚል መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል፡፡በመሆኑምቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ወራሾች ድርሻቸውን እንዲከፋፈሉ ከማድረግ ይልቅ የቤቱን የገበያ ዋጋ መሰረት በአደረገ መልኩ ከአመልካች ውጪ ያሉት የሟቹ ወራሾች እንዲሰጣቸውና አመልካች ቤቱን እንዲያስቀሩ መወሰኑ በውርስ ህጉ የተመለከቱትን የውርስ ንብረት ክፍፍልን የሚገዙትን ድንጋጌዎችን ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም የሟች አቶ በቀለ ባልቻ ንብረት የሆነውን አከራካሪውን ቤት ወራሾች እንዲከፋፈሉ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም የአከፋፈል ሥርዓት ግን በውርስ ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ያልተከተለ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 30082 የካቲት 06 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 33562 ሚያዝያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 161567 ሰኔ 04 ቀን 2005 ዓ/ም ፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 164191 መስከረም 21 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የሟች አቶ በቀለ ባልቻ ንብረት የሆነውና በቢሾፍቱ ከተማ ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኘው፣በካርታ ቁጥር 7/17/1 ቁጥሩ 290 የሚታወቀው ቤት የውርስ ቤት ነው ተብሎ አመልካችንና ተጠሪን ጨምሮ ለስድስት ወራሾች እንዲከፋፈል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ክፍፍሉን በተመለከተ ግን የቤቱ የገበያ ዋጋ ከታወቀ በኂላ የተጠሪንም ሆነ የሌሎች ወራሾችን ድርሻ አመልካች ከፍለው ቤቱን በአይነት እንዲያስቀሩ፣ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ግን በጨረታ ተሸጦ ሁሉም ወራሾች ድርሻ ገንዘባቸውን እኩል እንዲከፋፈሉ በማለት ወስነናል፡፡ የአዳአ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ችሎት ውሳኔ እንዲያስፈጽም በማለት የውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

### ትእዛዝ

ጥቅምት19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 90959

ግንቦት 06 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተክለ ዓዲቅ ኤካ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ. አቶ መላኩ ፍሬው
2ኛ. ወ/ሮ በየነች ታደሰ } የቀረበ የለም

***መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡***

***ፍ ር ድ***

ጉዳዩ የስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካች ላይ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም፡-ተጠሪዎችና ሌሎች ልጆች የሟች ፍሬው ቦጋለ ኤካ እና የወ/ሮ አበራሽ ዳደና ልጆች መሆናቸውና እነዚህ ወላጆቻቸው ተከታትለው ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን፣ በህይወት በነበሩበት ጊዜም በሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ ስም ቦታ ተመርተው በሶዶ ከተማ ቤት መስራታቸውን፣ ይህንኑ ቤት የአሁኑ አመልካች ጥር 28 ቀን 2001 ዓ/ም በስጦታ ከሟቹ እንደአገኙና በሰነዱ ላይ የሟች ወ/ሮ አበራሽ ደደና ፊርማ በማስመሰል ጽፈው በሶዶ ከተማ ፍትህና ጸጥታ ጽ/ቤት በማስመዝገብ አስጸድቀው መገኘታቸውንና ይህም በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ስጦታ መደረጉንና ተወላጆችን የነቀለ መሆኑን እንደሚያሳይና የሰጪው ተግባር ሕገወጥ መሆኑን ዘርዝረው ስጦታው እንዲፈርስ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም፡- ክሱ በይርጋ እንደሚታገድና ስጦታውም በሕጉ አግባብ የተደረገና ስመ ሃብቱም ለስጦታ ተቀባዩ ዙሮ የሚገኝ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በአሁኑ አመልካች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብ ውድቅ አድርጎና ፍሬ ነገሩን መርምሮ ስጦታው ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት

ይግባኙን ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የስጦታ ውሉ በሕጉ አግባብ የተደረገና ስመ ሃብቱም ለስጦታ ተቀባዩ የዞረ ሁኖ እያለ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ጭብጥ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ ሁኖ አግኝቶታል፡፡
ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት የሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ እና የወ/ሮ አበራሽ ዳደና ወራሾች መሆናቸውን ጠቅሰውና ሟቾች በጋብቻ ተሳስረው በነበሩበት ጊዜ በጋራ ያፈሩትን ቤት ሕጋዊ ባልሆነ የስጦታ ውል አመልካች መብት አለኝ በማለት ይዘው እንደሚገኙና ሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ መብት ሳይኖራቸው በሚስታቸው ድርሻ ስጦታ ከሕግ ውጪ ያደረጉ ከመሆኑም በላይ ከድርሻቸው ተወላጆችን መንቀላቸውን በመግለፅ ዘርዝረው  የስጦታው ውሉ እንዲፈርስ ይወሰንልን በሚል መሆኑን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በበኩላቸው ለተጠሪዎች ክርክር በሰጡት መልስ ከተጋቢዎች መካከል አንዱ ሲሞት በሕይወት የቀረው ተጋቢ በጋራ ንብረት ላይ ሙሉ መብት እንዳለውና በስጦታ ለሚፈልገው ሰው ቢያስተላልፍ በሕግ ክልከላ እንዳልተደረገበት እንዲሁም ስጦታው በሟቹ ሙሉ ፈቃድ ሕጉን ተከትሎ የተፈፀመ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት መከራከራቸውን ተረድተናል፡፡ይህ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ ለስጦታ ውል አደራረግ አግባብነት ያላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምሮአል፡፡ በዚህም መሰረት ሟች አቶ ፍሬው ቦጋለ ያደረጉት ስጦታ በባልና ሚስት የጋራ ሃብት በሆነው ቤት ላይ የተደረገ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ስጦታው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው? የሚለው የሕግ ነጥብ አስመልክቶ ሕጉ የሚለውን መመልከት ለውሣኔ አስፈላጊ ሆኖም አግኝቶታል፡፡
ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው ተጠሪዎች ለስጦታው መፍረስ እንደ አንድ ምክንያት የጠቀሱት ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሁኖ እያለ ባል ብቻ አደረጉ በተባለው ስጦታ ለአሁኑ አመልካች እንዲሰጥ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አመልካች በዚህ ረገድ በስር

ፍርድ ቤቶች ባቀረቡት ክርክር ከተጋቢዎች አንዱ በህይወት ከቀረ የጋራ ንብረት መብትን ጠቅልሎ ስለሚወስድ ስጦታ ማድረግ በሕግ ክልከላ አልተደረገም የሚል እንጂ ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አይደለም በማለት ክደው ያለመከራከራቸውን ተረድተናል፡፡ስለሆነም አከራካሪው ንብረት የባልና ሚስት የጋራ ንብረት መሆኑ በአመልካች በስርዓቱ መሰረት ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበት በመሆኑ በዚህ ሰበር ደረጃ አመልካች ቤቱ የጋብቻ ውጤት ስለመሆኑ ተጣርቶ አልተወሰነም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ ስጦታ ሕጋዊ መሆን ያለመሆን ነጥብ ስንመለስም፡- በመሰረቱ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ ስጦታ ያደረገ እንደሆነ ስጦታው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በፍትሃ ብሔር ሕጉ ስለስጦታ በሚደነግጉ ከቁጥር 2427 እና ተከታይ ድንጌዎች በግልጽ ምላሽ ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2427 ስለ ሥጦታ ትርጉም ሲያስቀምጥም ስጦታ አንድ ወገን ተዋዋይ ማለት ሰጪው፣ተቀባይ ተብሎ ለሚጠራው ለሌላ ሰው ችሮታ በማድረግ አሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ውል መሆኑን እንደሚያሳይ፣በዚህ ትርጉም ውስጥም“ከንብረቶቹ” የሚለው ቃል ስጦታ በሚደረገው ንብረት ላይ ስጦታ ሰጪው የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን የሚጠቁም ከመሆኑም በላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2451 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ስጦታ የሚደረገው ስጦታው በተደረገበት ቀን የሰጪው ገንዘብ ከሆነ ንብረት ላይ ብቻ መሆኑን መደንገጉም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደረጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የስጦታ ውል ያደረገ እንደሆነ የተሰጠው ስጦታ ዋጋ የማይኖረው መሆኑን ነው፡፡ስለሆነም በሕግ ፊት የሚፀና ስጦታ ለማድረግ ሰጪው ስጦታ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ስጦታው በሚስት ድርሻም ጭምር የተደረገ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስጦታውን ፈራሽ የሚያደርግ ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ ስጦታው በሚስት ድርሻ ሕጋዊ ውጤት አያስከትልም ከተባለ በባል ድርሻ ወይም በስጦታ አድራጊ ድርሻ ላይ ያለው ውጤት ነው፡፡ተጠሪዎች ስጦታው በዚህ ረገድ ሊፈርስ ይገባል በማለት ከሚከራከሩባቸው ምክንያቶች አንዱ ሟች በህመም ውስጥ እንደነበሩ ገልፀው አመልካች የሟቹን መንፈስ ልልነትና አቅመ ደካማነቱን በመጠቀም ስጦታ አድራጊ ሕጻን የሆኑተወላጆቹን ያላግባብ ከውርስ ንብረቱ ላይ እንዲነቀሉ አድርገዋል በሚል ነው፡፡አመልካች ተጠሪዎችም ሆኑ ሌሎች የሟቹ ሕጋዊ ወራሾች ሌላ የውርስ ንብረት ያላቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያቀረቡት ክርክርም የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ስጦታው ተፈፃሚነቱ ሟቹ ከሞቱ በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2428 እና 2438 ድንጋጌዎች አግባብ በውርስ ሕጉ ተወላጆቹን በተመለከተ በኑዛዜ ለመንቀል የሚቻል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑ ይታመናል፡፡ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት

ስጦታው ተወላጆቹን የውርስ ንብረት እንዳያገኙ የሚከለክል፣ከቅን ልቦና ውጪ የተደረገ መሆኑን ሟቹ የነበሩበትን የጤና ሁኔታ፣ስጦታው ከተደረገ በኂላ ሟቹ እስከ ሚያዝያ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ብቻ የቆዩ መሆኑን ሁሉ ከክርክሩ ፍሬ ነገር ደምድሞ ስጦታውን ፈራሽ ነው ሲል መወሰኑን የውሳኔው ይዘት የሚያስገነዝብ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶ በዚህ ረገድ የደመደመውንና ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የተቀበለውን ይህንኑ የፍሬ ነገር ሁኔታ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ተለይቶ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ሲታይ ለመለወጥ የሚያስችል መሰረታዊ የሆነ ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ስጦታው ከቅን ልቦና ውጪ የተደረገ ነው እስከተባለ ድረስ በስጦታ አድራጊው ድርሻ ጭምር ፈራሽ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት ያለመኖሩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2438(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ተገንዝበናል፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ነጥብ ስጦታውን መነሻ በማድረግ የቤቱ ስመሃብቱ ወደ አመልካች ዞሮ እያለ የተጠሪዎች ክርክር ተቀባይነት ማግኘቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአስተዳደር አካል የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የባለቤትነት ግምት መነሻ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ሲሆን ይህ ግምት ግን ደምዳሚ ያለመሆኑን የዚሁ ድንጋጌ ተከታይ የሆነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡በመሆኑም ስመ ሃብቱ የዞረበት መነሻ ያላግባብ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የባለቤትነት ደብተር የያዘ ሰው በፍርድ ቤት ሊከሰስ አይገባም የሚባልበት የሕግ አግባብ ስለሌለ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታም ተቀባይነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡በአጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ስጦታው ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20819 ሰኔ 06 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00064 የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በ28/05/2001 ዓ/ም በሟች ፍሬው ቦጋለ ኤካ ተደረገ የተባለው ስጦታ ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 93346

ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-**

1. ወ/ሮ ብርሃን ደሳለኝ
2. ወ/ሮ የሺ ቸኮል

ከጠበቃ አገኘሁ ዓይናለም ጋር ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ብርትኳን ዮሐንስ - ቀረቡ፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኖቹ ተጠሪዎች እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ በነበረው እና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልሆነው በኮ/ቀ/ክ/ከተማ የወረዳ 14 ኮንስትራክሽን እና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡በ02/08/2005 ዓ.ም. አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-የከሳሽ ባለቤት የነበሩት ፶ አለቃ ከበደ ሬባ በኮ/ቀ/ክ/ከተማ በወረዳ 14 የሚገኘውን ቁጥሩ 512 የሆነውን ቤት እስከሞቱበት የካቲት 2 ቀን 2005 ዓ.ም. ድረስ ከመንግስት ተከራይተው ይኖሩበት እንደነበረ፣ሟች በሕይወት እያሉ ቤት አፈላልገው እስኪያገኙ ድረስ በማለት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾችን ለጊዜው አስጠግተዋቸው እንደነበረ፣ተከሳሾቹ ቤት አፈላልገው እንዲወጡ ቢጠየቁ ፈቃደኞች ሳይሆኑ እንደቀሩ እና 3ኛ ተከሳሽም አስገድዶ ሊያስወጣቸው ፈቃደኛ እንዳልሆነ የሚገልጽ ሆኖ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ እና 3ኛ ተከሳሽም እንዲያስለቅቅ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በ14/08/2005 ዓ.ም. በጋራ በሰጡት መልስ ከቤቱ ውስጥ ከሟች አንዳንድ ክፍሎችን በመከራየት በቤቱ መኖር የጀመሩት 1ኛ ተከሳሽ ከመስከረም 1991 ዓ.ም.፣ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ከሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም. ጀምረው መሆኑን፣ከሳሽ ከሟች ባለቤታቸው ጋር በቤቱ የኖሩት ከ19/08/2003 ዓ.ም.ጀምሮ እስከ 02/06/2005 ዓ.ም.ድረስ ለ22 ወራት በመሆኑ

ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በ21/08/2005ዓ.ም. በሰጠው መልስ በከሳሽ ላይ የፈጸመው ድርጊት አለመኖሩን በመግለጽ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ በመመሪያ ቁጥር 2/2003 መሰረት ትዳር ያለው አንድ የመንግስት ቤት ተከራይ በሞት ሲለይ የተከራይነት መብቱ ለሌላኛው ተጋቢ ሊተላለፍ የሚችለው ተጋቢው ለሁለት ዓመት በቤቱ መኖሩ በተረጋገጠ ጊዜ በመሆኑ እና ከሳሽም እስከ ባለቤታቸው ሞት ድረስ በቤቱ የኖሩበት ጊዜ ከሁለት ዓመት በታች በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡በውሳኔው ቅር በመሰኘት ከሳሽ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የከተማው ይ/ሰሚ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ በመመሪያው የተቀመጠው የሁለት ዓመት ጊዜ መሰላት የሚገባው ተከራዩ እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ብቻ ሳይሆን ክርክሩ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ መሆኑን፣ጊዜው በዚህ አግባብ ሲቆጠር ደግሞ ከሳሽ በቤቱ የኖሩት ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑን እና የአሁኖቹ አመልካቾች በቤቱ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችል መብት የሌላቸው መሆኑን ገልጾ የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር ተጠሪዎቹ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የከተማው ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት አቤቱታቸውን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካቾቹ ክርክር ባስነሳው የቀበሌ ቤት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው ለ14 እና ለ11 ዓመታት መኖራቸው በተረጋገጠበት እና በቀጣይም በሚመለከተው አካል በኩል የተከራይነት መብት አግኝተው የኪራይ ውል በተዋዋሉበት ሁኔታ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ለውሳኔው የሰጠው ምክንያት በመመሪያው የተመለከተውን የጊዜ አቆጣጠር ስርዓት እና የአሁኖቹ አመልካቾች በቤቱ ውስጥ ለመቆየት የሚያስችል መብት የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ የሰጠው በ26/11/2005 ዓ.ም.ሲሆን ሰበር ችሎቱም አቤቱታውን ዘግቶ ያሰናበተው በ04/13/2005 ዓ.ም. ነው፡፡በሌላ በኩል ግን በክርክሩ ላይ ሶስቱም ፍ/ቤቶች ውሳኔ ከሰጡ በኂላ ጉዳዩ የሚመለከተው የኮ/ክ/ከተማ ወረዳ 14 ኮንስትራክሽን እና ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ሁለቱም አመልካቾች ለሚኖሩባቸው ክፍሎች ከሁለቱም አመልካቾች ጋር የኪራይ ውል መዋዋሉን እና ኪራይም ማስከፈል መጀመሩን አመልካቾቹ በሰበር አቤቱታቸው ላይ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዋም ቢሆን አስተዳደሩ ከአመልካቾቹ ጋር የኪራይ ውል የተዋዋለው አላግባብ ነው ከማለት ውጪ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ማስተባበያ የለም፡፡ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት አመልካቾቹ

ለጊዜው በጥገኝነት የገቡ በመሆኑ በቤቱ ክፍሎች የመኖር መብት የላቸውም በማለት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የኪራይ ውል ገብተው የተከራይነት መብት ያገኙ በመሆኑ አስተዳደሩ ከተጠሪዎች ጋር ውል የገባው ከሕግ ውጪ ነው የሚሉ ከሆነ አስተዳሩን በሕግ መጠየቅ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ አመልካቾቹ በቤቱ የመቆየት መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጭብጥ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የአ/አበባ ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች አመልካቾች ክርክር ባስነሳው የቤቱ ክፍሎች ለመቆየት የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጡት አመልካቾቹ የተከራይነት መብት ከማግኘታቸው በፊት ሲሆን ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ ግን አመልካቾቹ በያዟቸው የቤቱ ክፍሎች ለመቆየት የሚያስችል የኪራይ ውል ተጠቃሚ መሆናቸው በመረጋገጡ የስር ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች  ውሳኔ ሊሻር እና በአንጻሩ የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሊጸና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31918 በ27/10/2005 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የከተማው ፍ/ቤቶች ይ/ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ. 20461 በ26/11/2005 ዓ.ም.በመ.ቁ. 20659 በ04/13/2005 ዓ.ም. የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የተጠሪዋን ክስ ውድቅ በማድረግ የአ/አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 31918 በ27/10/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.95538

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አብርሃ ሕሉፍ ገሰሰው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትበርህ ገብረሕይወት የቀረበ የለም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ በእርሻ መሬት ላይ የቀረበውን የይገባኛል ክስ መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በመሬት ዳኝነት ሰጪ ጣቢያ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት ተጠሪ ሲሆኑ አመልካችን የከሰሱት በእርሻ መሬት ደልዳዮች (አከፋፋዮች) ተሸንሽኖ የተሰጠንን 50X25 ሜትር የሆነ መሬት ይልቀቁልኝ በማለት ነው፡፡በዚህ መሠረትም የእርሻ መሬቱን ተገደው እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ መሬቱን ከተጠሪ ቀድመው የተደለደሉትና በቋሚ ተክሎች አልምተው በመጠቀም ላይ የሚገኙት መሆኑንና ለተጠሪ የተሰጠበት አግባብም ሕጋዊ ያለመሆኑን በመቃወም ለሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ጥያቄ አቅርበው መሬት ሸንሻኙ ክፍል ሳይቀበላቸው የቀረ መሆኑን ጠቅሰው መሬቱን እንድለቅ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት የለም፤ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የመሬት ዳኝነት ጣቢያ ተከሣሽ (የአሁን አመልካች) መሬቱ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም ቀድሞ ለአሁኑ አመልካች የተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የቀይ ተኽሊ ወረዳ ፍርድ ቤትም የመሬት ዳኝነት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡ በመጨረሻም ተጠሪ ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቷል፡፡የሰበር ችሎቱም ተጠሪ መሬቱን በድልድል ያገኙት መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካች ቅሬታ ማቅረብና ጉዳያቸው መታየት ያለበት በአስተዳደሩ እንጂ በፍርድ ቤት ሊሆን አይገባም

በሚል ምክንያት የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-አከራካሪውን መሬት በሕጉ አግባብ ከተጠሪ ቀድሞ ከተሰጣቸው በኋላ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለተጠሪ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ክርክር ያስነሳው መሬት በመጀመሪያ ለአመልካች ከተሰጠ በኋላ እንደገና ለአሁኑ ተጠሪ ከተሰጠ በድጋሚ በላዩ ላይ ደርቦ ለሰጠው አካል ጥያቄው ከሚቀርብ በቀር በዳኝነት ሊታይ የሚችል ጉዳት አይደለም የሚለውን መሰረት በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ለማየት ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው መሬት ቀደም ሲል የተሰጠው ለአመልካች እንደሆነ እና በሱ ይዞታ ሥር ስለመቆየቱ እንዳላከራከረ ከሥር ጀምሮ ከተደረገ ክርክር እና ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የመሬት ዳኝነት ጣቢያ በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች መሬቱ ሊወሰድበት አይገባም (አይችልም) የሚል መደምደሚያ ላይ የተደረሰው መሬቱ በህጉ አግባብ ለአመልካች ጥር 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተሰጠበት ሁኔታ ከሕግ ውጪ ለአሁኑ ተጠሪ ተደርቦ ነሐሴ 20 ቀን 2002ዓ.ም መስጠቱ ያለአግባብ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሁለቱም የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሻረው አመልካች የመሬት አስተዳዳሪዎች ይዞታዬን ወስደው ለሌላ ሰጥተውብኛል ካለ ማመልከት ያለበት በየደረጃው ለሚገኙ የአስተዳደር አካላት ነው ፤ ከዚህ ባለፈ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት የሚታይ አይደለም በማለት እንደሆነ ከውሣኔው ተገንዝበናል፡፡

እንደምናየው ጉዳዩ በፍ/ቤት እንዲዳኝ ክስ ያቀረቡት ተጠሪ ናቸው፡፡ አመልካች መሬቱን የምለቅበት አግባብ የለም የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን በመከላከያነትም የሕግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦችን አንስቷል ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የመሬት ዳኝነት ጣቢያ ፍ/ቤት እንደመሆኑ የግራ ቀኝ ወገኖቹን ክርክር ከሰማ በኋላ መሬቱ ለአሁኗ ተጠሪ መለቀቅ የለበትም ብሎ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፍ/ቤት የተሰጠ እንደመሆኑ በውሳኔው ያልተስማሙት ተጠሪ ይግባኙን ማቅረብ ያለባቸው በደረጃው ለተዋቀረው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ነው፡፡ አከራካሪው ጭብጥ ተጠሪ መሬቱን የተሰጡበት በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚል በመሆኑ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ የሰሙት ፍ/ቤቶች ጭብጡን ከቀረበው የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር

አንፃር በማየት የየበኩላቸውን ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ጥር 8 ቀን 2002 ዓ/ም ለአመልካች የተሰጠው መሬት ነሐሴ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ለተጠሪ ሊሰጥ የቻለው በምን ሕጋዊ ምክንያት እንደሆነ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ድልድሉ ተገቢ ያለመሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ድምዳሜ ያሳያል፡፡

እነዚህ የዳኝነት አካላት መሬቱ ለተጠሪ የተደለደለ ከሕግ ውጪ ነው የሚል ምክንያት የሰጡት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 136/2000 አንቀጽ 31 "ን" በዋቢነት በመጥቀስ ነው፡፡ በበኩላችንም አዋጁንና ለማስፈፀም የወጣው የተሻሻለው የትግራይ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ደንብ ቁ. 48/2000 "ን" ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተመልክተናል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 5፣12፣14፣22 በመሬት የመጠቀም መብት የሚል ድንጋጌ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታው ወይም አሰራሩም በተጠቃሽ ድንጋጌዎች ስር በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በደንብ ቁጥር 48/2000 14፣15፣16 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ስር የገጠር መሬት መብት የሚገኝባቸውን መንገዶች የተዘረዘረ ሲሆን ከአንቀጽ 27 እስከ 29 ድረስም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የቦረቦር መሬት የማግኘት መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ በድልድል ያገኘውን መሬት አንድ ሰው ሊወስድበት የሚገባው በሕጉ የተመለከቱ ምክንያቶች ሲኖሩ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ለአመልካች የተሰጠው ይዞታ ለተጠሪ ተደርቦ የተሰጠበት አግባብ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡

የትግራይ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በውሳኔው እንዳመለከተው የገጠር መሬትን የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው በየደረጃው ለተዋቀሩ የአስተዳደር አካላት ቢሆንም እነዚህ አካላት የተሰጣቸውን ሥልጣን መተግበር ያለባቸው በአዋጁ እና በደንቡ በግልጽ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደ ተገለፀው አመልካች የእርሻ መሬቱን አለቅም ያለው በአዋጁ እና በደንቡ የተጠበቀለትን መብት መሠረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ ክስ የመሠረቱበት ደግሞ ይህ በሕግ የተጠበቀለትን የአመልካች መብት በፍ/ቤት ውሳኔ ቀሪ እንዲሆንና መሬቱ እንዲለቀቅላቸው ነው፡፡ ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚሰጡት ሕግን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ደግሞ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 79(3) ከተቀመጠው ድንጋጌ እና የዳኝነት አመራር ስርዓትን በሚመለከት ከወጡት ህጎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የመሬት ዳኝነቱና የወረዳው ፍ/ቤት ለአመልካች የተሰጠው ድልድል ቀሪ የሚሆንበት አግባብ የለም በማለት  የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በዳኝነት እንደማይታይ አድርጐ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሱትን የክልሉን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎችን አዋጅ ቁጥር 456/1997 ስር የተረጋገጠውን የእርሻ መሬት ይዞታ መብትን እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣40(3) እና 79 ስር የተቀመጡትን

ድንጋጌዎችንና በዚህ ረገድ በክልሉ  ሕገ መንግስትም የሰፈሩትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 60917 ነሐሴ 25 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሳንታ ገለበዳ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ግንቦት 07 ቀን 2005 ተሰጥቶ በቀይሕ ተክሊ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01471 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች የእርሻ መሬቱን እንዲለቅ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ. 94869

ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- አቶ ሙሳ ደገፌ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን ደስታ /ጠበቃ ሽመልስ ከፍያለሁ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርደ ተሰጥቷል**

ፍርድ

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን አሌሊቱ ወረዳ ፍ/ቤት የሰበር አመልካች ከሳሽ በመሆን ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ መነሻነት ነው፡፡

አመልካች ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ ለስር ፍ/ቤት በቀረበው ክስ አቤቱታ፡-በ1993 ዓ/ም ከአቶ ደስታ አያኔ እና ወ/ሮ ሸዋዬ ቡልቻ በልዋጭ ባገኘሁት ይዞታ ላይ ባህር ዛፍ ተክዬ በእጄ ያለውን ተጠሪ በ27/01/2000 ዓ/ም እንዳልጠቀምበት በመከልከል ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከቱ እንዲቆም ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪም በበኩል ቀርቦ በሰጠው መልስ፡- ይህ ክርክር የቀረበበት ይዞታም ሆነ ባህር ዛፍ የአባቱ መሆኑን፤ተጠሪም ወራሽ በመሆን ይዞታው የተላለፈለት መሆኑንና ይህ በውርስ ያገኘው ይዞታ ደግሞ እንዳይነካበት መከልከሉ መብት እንጂ ሁከት ሊባል እንደማይችል ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የፈጠረውን ሁከት እንዲያቆም በማለትውሳኔ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ቅሬታውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኂላ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ ከተጠሪ አባት በልዋጭ አግኝቸበታለሁ በማለት የጠቀሰው የውል ስምምነት

ሰነድ (በ17/7/1993 ዓ.ም የተደረገ) ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ አባት አቶ ደስታ አያሌ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ ውጤቱ ከታወቀ በኂላ በጉዳዩ ላይ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሶ ለወረዳ ፍ/ቤቱ ልኳል፡፡

የወረዳ ፍ/ቤቱም በበኩሉ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ በፎሬንሲክ ሳይንስ እንዲመረመር ካደረገ በኂላ ፊርማው የተጠሪ አባት መሆን አለመሆኑን ለመለየት አልተቻለም በሚል የተገለፀለትን የምርመራ ውጤት ጭምር መሠረት አድርጎ ጉዳዩን መመርመሩን ከገለፀ በኂላ አመልካች ክርክር የቀረበበትን ይዞታ በልዋጭ አግኝቸበታለሁ በማለት የሚከራከረው ውል ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ አባት ፊርማ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ላይ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካችም በበኩሉ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ቅሬታውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደረጃውን ጠብቆ ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም ደረጃ ቅሬታው ተቀባይነት አላገኘም ሆኖም ግን ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የቀረበበት ይዞታ ማን እጅ እንደነበር ማን ግብር ሲገብርበት እንደነበር በይዞታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር የተሰጠው ለማን እንደሆነ እና ተጠሪ ይዞታውን ሁከት ፈጥሮ መያዝ አለመያዙ በግራ ቀኙ የሰው ምስክሮች እና እንዲሁም ከሚመለከታቸው አስተዳደር አካላትም ተጠይቆ ተገቢ ማጣሪያ ከተደረገ በኂላ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ክርክሩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት በድጋሚ ወደ ወረዳ ፍ/ቤቱ መልሶታል፡፡ የወረዳ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ጉዳዩ በተመራለት መሰረት በግራ ቀኙ ምስክሮች እና እንዲሁም የክፍሉ ቀበሌ አስተዳደር እና የወረዳውን አካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ስለ ጉዳዩ ጠይቆ ካጣራ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በይዞታው ላይ የተከለውን ባህርዛፍ እንዳይጠቀምበት በተጠሪ የተፈጸመበት መሰናክል ሁከት አይደለም ሊባል የሚቻል ስለላልሆነ ተጠሪ ሁከቱን አቁሞ አመልካች ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ያለውን መብት እንዲጠቀምበት በማለት ወስኗል፡፡፡

በተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ጉዳዩን መርምሮ ቅሬታው ተቀባይነት የለውም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ ቀጥሎ 2ኛ ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማቸው በኂላ ጉዳዩን መርምሮ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩን ቀጥሎ በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማቸው በኂላ ይህ ክርክር የቀረበበት ይዞታ ወደ ተጠሪ ተመልሶ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃም ተሰጥቶት ግብርም እየገበረበት በእጁ ባለው መሬት ላይ ተጠሪ ሁከት ፈጥሯል ለማለት የሚቻል ስላልሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፡፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ የክልሉ ሰበር ችሎት ተጠሪ ሁከት ፈጥሯል ማለት አይችልም ወደሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሳኔዎች መሻሩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ታየቶ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነየህግስህተትተፈፅሞበታል ለማለት ይቻላል? ወይስአይቻልም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውይህ ለክርክሩ መነሻየሆነው ይዞታና ኋላም ባህር ዛፍ ተተክሎበታል የተባለው ይዞታነቱ በመጀመሪያ የተጠሪ አባት የአቶ ደስታ አያኔ የነበረ ስለመሆኑከ1993 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ግን በአመልካች ስም ግብር እየተገበረበት በእርሳቸው ይዞታ ስር መቆየቱን፣ መሬቱ በአመልካች ይዞታ ስር በቆየበት ጊዜ ባህር ዛፍ በአመልካች የተተከለበት መሆኑን፣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በ1998 ዓ.ም በአመልካች ስም ተሰጥቶ የነበረመሆኑን፣ሆኖም ግን ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ተጠሪ ከአባቴ አቶ ደሰታ አያኔ በውርስ ሊተላለፍልኝ የሚገባ የውርስ ሀብት ነው በማለት እናቱ ወ/ሮ ሸዋዬ ቡልቻን በ1999 ዓ.ም ከሶ በ12/9/99 ዓ.ም ማስፈረዱን፣ በፍርዱ መሠረትም ይዞታውን በፍርድ አፈፃፀም ትዕዛዝ በ2001 ዓ.ም ውስጥ መቀበሉን ይሄንኑ ተከትሎምከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የይዞታው ግብር በተጠሪ ስም መገበሩንና እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በስሙ የሰጠው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ መረጋገጡንና እንዲሁም በዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ደረጃም ግራ ቀኙ ካደረጉት የጽሑፍ ክርክር ይዞታው በውርስ ለተጠሪ ይገባል ተብሎ በተሰጠው ፍርድ መሠረት ተጠሪ ይዞታውን በአፈፃፀም ለመረከብ በስር ፍ/ቤት አስከፍቶ በነበረው አፈፃፀም መዝገብ ላይ አመልካች በመቃወሚያ አቅራቢነት ጣልቃ ገብቶ በጉዳዩ ላይ ሲከራከሩበት ከቆዩ በኋላ እና በስተመጨረሻ የአመልካች የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሠረቱ ይዞታው የተወሰደበት ወይም በይዞታው ላይ ሁከት የተነሣበት ሰው የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሣው ሁከት እንዲወገድለት እንዲሁም ስለደረሰበት ጉዳት ኪሣራ እንዲሰጠው ለመጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 1149 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሣሹ ለፈፀመው ድርጊት የሚፈቀድ መብት እንዳለው ማስረዳት ከቻለ በክሱ ኃላፊ ሊሆን እንደማይገባ እንዲሁ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የሕጉ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች በ1993 ዓ.ም በልዋጭ ባገኘሁት እና በይዞታዬ ስር በቆየ መሬት ላይ የተከልኩትን ባህርዛፍ ተጠሪ እንዳልጠቀምበት በማድረግ በ27/1/2000 ዓ.ም ሁከት ስለፈጠረብኝ ሁከቱ እንዲቆም የሚል ዳኝነት ሊሰጠኝ ይገባል በሚል የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ክርክር ያስነሣው መሬት የአባቱ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ ሆኖም ግን ይዞታውን በውርስ ስላገኘሁ እና ይህም በፍርድ ተረጋግጦ በኋላም በፍ/ቤት ትእዛዝ በአፈፃፀም የተረከብኩት ይዞታ ስለሆነ ድርጊቱ ሁከት ሊባል አይችልም በሚል የሚከራከር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በ1993 ዓ/ም በልዋጭ አግኝቼ በኂላም ባህርዛፍ ተክየበታለሁ የሚለውን ይዞታ በውርስ ለተጠሪ ይገባል ተብሎ በወረዳ ፍ/ቤቱ በ12/9/99 ዓ/ም ውሳኔ መሰጠቱ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሁከት ተፈጥሯል በተባለበት ጊዜ ይዞታው በፍ/ቤት አፈፃፀም ትዕዛዝ በተጠሪ እጅ ባይገባም ተጠሪ በፍ/ቤት ውሳኔ የይዞታው ባለመብት ሆኗል፡፡ እንዲሁም ሁከት ተፈጥሯል ከተባለበት ጊዜ በኂላ ቢሆንም ተጠሪ በፍርዱ መሰረት ይዞታውንም በአፈፃፀም እጁ አስገብቶ እና የይዞታ ማረጋገጫም በስሙ ተሰጥቶ እስከ አሁን ግብር በስሙ እየገበረበትና እየተጠቀመበት ያለ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ስለሆነም ሁከት ተፈጥሯል በተባለበት ጊዜም ቢሆን ተጠሪ አስቀድሞ በይዞታው ላይ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ስለነበረው ይህ በተጠሪ ተፈፅሟል የተባለው ድርጊት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1149(3) ድንጋጌ ይዘት አኳያ ተገናዝቦ ሲታይ ይሄንኑ በፍርድ የተረጋገጠለትን መብት ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን ከሚያሳይ በቀር ሁከት ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ በተጠሪ እጅ ገብቶ ባለበት ሁኔታ ሁከት አለ ማለት አይቻልም በማለት በውጤት ደረጃ በሰጠው ፍርድ ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 149158 በ27/12/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ችሎት በውጤት ደረጃ ሁከት የለም ሲል የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 89148

ሰኔ 3 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-አቶ ክፍሉ ገ/ማርያም - ጠበቃ አቶ መለሰ ጉርሙ ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ አስመረት መኮንን - ጠበቃ ጎሳዬ ጉርሙ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በቦረና ዞን በቡሌ ሆራ ወረዳ ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ላይ በ24/06/2002 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡2ኛ ተከሳሽ የነበረው የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ያልሆነው የከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ነው፡፡የክሱም ይዘት ባጭሩ፡-ከሳሽ በቡሌ ሆራ ከተማ ከአባታቸው ከአቶ ገ/ማርያም ዳኜ በውርስ የተላለፈላቸው 900 ካ.ሜ ይዞታ ያለው ቤት እንዳላቸው፣1ኛ ተከሳሽ በዚሁ ቤት በዝምድና መልክ በከሳሽ ፈቃድ ገብተው ሲኖሩ ከሳሽ በማያውቁት ሁኔታ የቤቱን የባለቤትነት ስም ወደራሳቸው አዛውረው እንደተገኙ፣ከሳሽ ይህ መፈጸሙን ያወቁት በ15/06/2002 ዓ.ም እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ 2ኛ ተከሳሽ አላግባብ የፈጸመውን የስም ዝውውር ሰርዞ ወደነበረበት እንዲመልስ እና 1ኛ ተከሳሽም ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

1ኛ ተከሳሽ በ08/08/2002 ዓ.ም በሰጡት የተሻሻለ መልስ አባታቸው በ1972 ዓ.ም ከሞቱ ከ30 ዓመት በኋላ ከሳሽ ያቀረቡት የውርስ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄ በይርጋ እንደሚታገድ፣በቤቱ የገቡት ከሳሽ እንደሚሉት በዝምድና መልክ ወይም በጥገኝነት ሳይሆን ከልጃቸው ዳኜ ክፍሉ ጋር በ1994 ዓ.ም ጋብቻ በመፈጸማቸው እንደሆነ፣በጋብቻውም ሁለት ልጆችን እንደወለዱ፣ዳኜ ክፍሉ በ1996 ዓ.ም በሞት እንደተለየ፣ከሳሽ ቤቱን ከእናታቸው እና ከወንድሞቻቸው መግዛታቸውን (ድርሻ መክፈላቸውን) ገልጸው ልጃቸው ጋብቻ ከመፈጸሙ አስቀድሞ በ1981 ዓ.ም በስጦታ

እንደሰጡት፣ስጦታውን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ የከተማው አስተዳደር ቁጥሩ 489/1981 በሆነ እና በ04/03/1981 በወጣ ማስታወቂያ ጥሪ አድርጎ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ ስሙን ወደ ሚች ዳኜ ክፍሉ እንዳዛወረ፣ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግብሩ ሲከፈል የነበረው በሚች ስም፣እርሱ ከሞተ በኂላ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽ ስም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው ሚች ልጃቸው እና 1ኛ ተከሳሽ እንጂ ከሳሽ እንዳልሆኑ በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ክሱ በተሰማበት ጊዜም ከጋብቻቸው በኂላ ሰባት ክፍል ቤቶችን ከሚች ባለቤታቸው ጋር መስራታቸውን በመግለጽ አስመዝግበዋል፡፡2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ በ30/06/2002 ዓ.ም በሰጠው መልስ ቤቱ ቀደም ሲል ጀምሮ በሚች ዳኜ ክፍሉ ስም ተመዝግቦ የነበረ መሆኑን እና ስሙን ወደ 1ኛ ተከሳሽ ስም ሊያዛውር የቻለው 1ኛ ተከሳሽ የሚች ልጆችን ወራሽነት እና የራሷን ሚስትነት በመ.ቁ. 84/96 በ07/04/1996 ዓ.ም በማረጋገጥ ከቡሌ ሆራ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበችው ማስረጃ መሰረት መሆኑን ገልጾ ፍ/ቤቱ እንዲያሰናብተው ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኂላ አጠቃላይ ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ ክስ ያስነሳውን ቤት ለልጃቸው ዳኜ ክፍሉ በስጦታ በመስጠታቸው የከተማው አስተዳደር ቁጥሩ 489/1981 የሆነ እና በ04/03/1981 የወጣ ማስታወቂያ አውጥቶ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ በስጦታ ውሉ መሰረት የቤቱ የባለቤትነት ስም ወደ ዳኜ ክፍሉ ተዛውሯል ከማለት ውጪ ከ1ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2444፣881፣882 እና 883 ድንጋጌዎች መሰረት የሕጉን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ የስጦታ ውል በማስረጃነት ያላቀረቡ በመሆኑ ስጦታን አስመልክቶ የቀረበው ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፣የቤቱ ግብር ለ15 ዓመታት ሳያቋርጥ የተከፈለ ባለመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ በመከራከሪያነት ያቀረቡት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168 ድንጋጌ ለክርክሩ ተፈጻሚነት እንደሌለው እና የከሳሽ የወራሽነት መብትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1000(2) መሰረት በይርጋ የሚታገድ እንዳልሆነ ገልጾ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ እና 2ኛ ተከሳሽም የባለቤትነት ስሙን በከሳሽ ስም እንዲመዘግብ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በ1ኛ ተከሳሽ ጠያቂነት ይግባኙን የተመለከተው የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ቤቱ በስጦታ የተላለፈ መሆኑን ስልጣን ያለው የከተማው አስተዳደር ማረጋገጡን፣ግብሩም በሚች ዳኜ ክፍሉ እና ከእርሱ ሞት በኂላ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽ ስም በአጠቃላይ ከ1988 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የተከፈለ መሆኑን፣እነዚህ ማስረጃዎች ሀሰተኛ ስለመሆናቸው ከሳሽ አሳማኝ እና ተጨባጭ ክርክር አቅርበው ማስተባበል አለመቻላቸውን እና የከሳሽ የወራሽነት መብትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000(1) መሰረት በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ገልጾ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን በመሻር 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ከሳሽ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የከሳሽ የክስ ነጥብ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን አላግባብ ወደ ራሷ ስም አዛውራለች የሚል እንጂ

የወራሽነት ክርክር ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000(1) የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ለክርክሩ አግባብነት እንደሌለው ጭምር በመግለጽ የዞኑን ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ይርጋን አስመልክቶ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የያዘው አቋም የሚነቀፍ አለመሆኑን ገልጾ ነገር ግን ሟች ዳኜ ክፍሉ ቤቱን በስጦታ አግኝቷል ወይስ አላገኝም? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ሟች ዳኜ ክፍሉ እና እርሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ በአጠቃላይ ከ1988 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የቤቱን ግብር ለ15 ዓመታት በተከታታይ ወይም ሳይቋረጥ የከፈሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት የቤቱ ባለቤት እንደሚሆኑ ገልጾ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ በመሻር የዞኑን ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለሟች ልጃቸው ዳኜ ክፍሉ በስጦታ እንዳልሰጡ በሚከራከሩበት እና የቤቱ ግብር ለ15 ዓመታት ተከፍሏል ለተባለውም የተከፈለው በተከታታይና ሳይቆራረጥ አለመሆኑን እና በክርክር ላይ የነበሩበትን ጊዜ(ዓመት) ጭምር ያካተተ መሆኑን በሚከራከሩበት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168(1) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ክስ ያስነሳውን ቤት ከእናታቸው እና ከወንድሞቻቸው መግዛታቸውን (ድርሻ መክፈላቸውን) ገልጸው ልጃቸው ጋብቻ ከመፈጸሙ አስቀድሞ በ1981 ዓ.ም በስጦታ አስተላልፈውለታል በማለት ተጠሪዋ የተከራከሩ ቢሆንም ስጦታውን የሚቃወም ካለ እንዲቀርብ የከተማው አስተዳደር በቁጥር 489/1981 በ04/03/1981 ያወጣውን ማስታወቂያ ከማቅረብ ውጪ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የስጦታ ውል ስለመኖሩ ተጠሪዋ የስጦታ ውሉን በማስረጃነት በማቅረብ ማስረዳት አለመቻላቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ ሽሮ የከ/ፍ/ቤት ውሳኔን በውጤት ደረጃ ለማጽናት የቻለው ግብሩ ለ15 ዓመታት በተከታታይ የተከፈለ መሆኑ ሟች ባለቤቷን እና ተጠሪዋን የቤቱ ባለቤት ያደርጋቸዋል በማለት ነው፡፡በ1988 ዓ.ም የተቀረጠው የግብር ካርኒ ግብሩ የተከፈለው ለ1988 ዓ.ም ብቻ ሳይሆን ከ1988 ዓ.ም በፊት ለነበሩት ሶስት ዓመታት ጭምር እንደሆነ ከግራ ቀኙ የሰበር ክርክር መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የቤቱ ግብር በሟች ባለቤቷ እና በተጠሪዋ ስም

የተከፈለው ክርክሩ የተጀመረበትን 2002 ዓ.ም ሳይጨምር ከ15 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ግብሩ ለ15 ዓመታት ተከፍሏል የተባለው ግራ ቀኙ ክርክር የጀመሩበትን ዓመት ጭምር በመቁጠር ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር በግራ ቀኙ ክርክር የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ግብሩ ለ15 ዓመታት ተከፍሏል ቢባል እንኳ የተከፈለው በተከታታይ ወይም ሳይቋረጥ ባለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168 ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ በተመለከተ እንደተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ (ባለይዞታ) የሆነ ሰው የዚሁ ንብረት ባለቤት መሆን የሚችለው ግብሩን ባለማቋረጥ 15 ዓመት በስሙ ከከፈለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1168(1) በግልጽ ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግብሩ በሟች እና በተጠሪዋ ስም የተከፈለው ከ15 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ ቢሆንም የተከፈለው ግን ለእያንዳንዱ ዓመት በተናጠል ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ ዓመታትን አጠቃሎ በአንድ ደረሰኝ በመክፈል ጭምር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች የሚከራከሩትም የሁለት ወይም የሶስት ዓመታት ግብር ተጠቃሎ የተከፈለባቸው ደረሰኞች ተቀባይነት ያገኙት አላግባብ ነው በማለት ነው፡፡በመሰረቱ ባለይዞታው የንብረቱ ባለቤት መሆን የሚችለው ግብሩን ለ15 ዓመታት  ባለማቋረጥ ከከፈለ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ ስውር ወይም አሻሚ በሆነ መንገድ የተደረገ ይዞታ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው እንደማይገባ እና በአንጻሩ ባለይዞታው ግብሩን በተከታታይ የከፈለው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው በማመን እንዲሁም በሌሎች ዘንድም የዚህኑ ዓይነት ግምት ለማሳደር በሚያስችል ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ግብሩ በሟች እና በኋላም በተጠሪ በተከታታይ ሲከፈል የነበረው ቤቱ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በሟች እጅ፣እርሱ ከሞተበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በተጠሪ እጅ መሆኑ በተረጋገጠበት እና በከተማው አስተዳደርም ቤቱ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ተመዝግቦ የሚታወቀው በሟች እና ከእርሱ ሞት በኋላ ደግሞ በተጠሪ ስም መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑ ይዞታው አሻሚ ወይም ስውር ነበር ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ይህ ሁሉ ሲደረግ አመልካች ይኖሩ የነበረው በዚያው ከተማ እና ቀበሌ ክልል ውስጥ ስለመሆኑ በክርክሩ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ቤቱ በተጠሪ ስም መመዝገቡን እና ግብር መከፈሉን ያወቁት በ15/06/2002 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡በክርክሩ እንደተረጋገጠው የአመልካች አባት አቶ ገ/ማርያም ዳኜ በ1972 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ አመልካች የቤቱን ግብር በስማቸው የከፈሉት ከ1972 ዓ.ም እስከ 1975 ዓ.ም ድረስ ብቻ መሆኑም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የይግባኝ ሰሚውን ችሎት ውሳኔ በመሻር ሟች ዳኜ ክፍሉ እና ተጠሪ የቤቱን ግብር ለ15 ዓመታት ሳያቋርጥ የከፈሉ በመሆኑ እና ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1168 መሰረት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት የሚያስገኝላቸው በመሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው ለአመልካች ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 129921 በ20/05/2005 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 97464

ሰኔ 04 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘይነብ ጀማል አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1.የቦሌ ክፍለ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ጽ/ቤት አልቀረበም

2. አብዱልወሃብ መሐመድ አልቀረበም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኗ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኖቹ ተጠሪዎች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ከሳሽ ነሐሴ 12 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡት ክስ፡- በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ መጋቢት 19 ቀን 1993 ዓ/ም በወጣው 10ኛ ዙር የመኖሪያ ቤት የሊዝ ዕጣ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ክልል ውስጥ የመለያ ቁጥሩ BKB-17-B56 የሆነ 160 ካሬ ሜትር ቦታ ደርሶኝ ጥቅምት 17 ቀን 1995 ዓ/ም ለ99 ዓመት የሚቆይ የሊዝ ውል ፈጽሜ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠኝ ሲሆን በቦታው ብር 90,000.00 የሚያወጣ ግንባታ በማከናወን የፕላን ስምምነት እንዲሰጠኝ ለ1ኛ ተከሳሽ ሳመለክት የ1ኛ ተከሳሽ ባለሙያ የሆኑት 2ኛ ተከሳሽ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዬን እና ሌሎች ሰነዶቼን (ዶክመንቶቼን) ከተቀበሉኝ በኋላ የከለከሉኝ በመሆኑ ተከሳሾቹ የፈጠሩት ሁከት ተወግዶ የተቀበሉትን የቦታውን ካርታ እና ሰነዶቹን እንዲመልሱ፣የግንባታ ማከናወኛ ፈቃድም 1ኛ ተከሳሽ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም፡-ከሳሽ ያቀረቡትን ክስ ከመረመረ በኋላ በሰጠው ትዕዛዝ የከሳሽ ጥያቄ ይዞታን የሚመለከት ሳይሆን በ2ኛ ተከሳሽ የተወሰዱባቸው ሰነዶች እንዲመለሱላቸው እንዲወሰን የሚል በመሆኑ ጥያቄያቸው በአስተዳደሩ በኩል ደረጃውን ጠብቆ መፍትሔ የሚያገኝ እንጂ በሁከት ይወገድልኝ ቀርቦ በፍርድ ቤት እልባት የሚያገኝ ባለመሆኑ

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም ሲል የክሱን መዝገብ ዘግቷል፡፡

ከሳሽም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/337 መሰረት በመዝጋት በማሰናበቱ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸውም በዋናነት የጠቀሱት የቅሬታ ነጥብ፡- 1ኛ ተጠሪ የፓላን ስምምነት እንዲሰጠኝ በሚል ባቀረብኩት አቤቱታ መነሻ በእጄ የሚገኙትን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና ሌሎች ሰነዶችን 2ኛ ተጠሪ ነጥቀውኝ ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አመልካችም በመሥሪያ ቤት ውስጥ በጉልበት ከ2ኛ ተጠሪ ለመቀበል ስለማልችል ያለኝ አማራጭ በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች የሁከት ተግባር በመሬት ይዞታ ብቻ እንደሚፈጸም በመቁጠር ተጠሪዎቹ የፈጸሙት ሰነዶችን የመንጠቅ ተግባር በሁከት እንደማይጠቃለል በመቁጠር ሥልጣን የለንም ሲሉ ክሴን ውድቅ ያደረጉት ያለአግባብ ነው የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ባለመስጠታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት የባለይዞታነት መብት በሌላቸው ጉዳይ ላይ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣በሌላ በኩል የባለይዞታነት መብት ለማረጋገጥ የሚቻለው ለዚሁ ሲባል ከሚመለከተው መንግስት አካል በህጋዊ መንገድ የተሰጠ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማቅረብ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚቀርቡ ሰነዶችን በተመለከተ ግን በመመርመር መፍትሔ ሊሰጥ የሚችለው የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት እንጂ ፍርድ ቤት ባለመሆኑ እና ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይታያል ቢባል የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ካርታ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ውሳኔ ስለሚሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም ሲሉ የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረጉት የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ብሏል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለሰጠው መልስ አመልካችም የበኩላቸውን የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

- አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ? ወይስ አይደለም?
- ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ቢባል የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን አላቸው ? ወይስ የላቸውም ? የሚሉትን ጭብጦች ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ማንኛውም ሰው (የተፈጥሮም ሆነ በህግ የሰውነት መብት ያለው ድርጅት) በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (justiciable matter) ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ከመደንገጉም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 4 በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በስተቀር የፍትሃብሔር ጉዳዮች ለመደበኛው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ስለመሆናቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም በቀጥታ ወይም በግልጽ በወጡ ወይም በሚወጡ ህጎች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጪ በህግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት ተለይቶ የተሰጣቸውን ፍትሃብሔር ጉዳዮች ተቀብለው የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረትም አንድ ጉዳይ በፍርድ ቤት ወይም በሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ተቀብሎ አከራክሮ ውሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለው ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በክሳቸው የፐላን ስምምነት እንዲሰጣቸው በሚል በእጃቸው የነበረውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እና የተለያዩ ሰነዶችን (ዶክመንቶችን) ከጻፉት አቤቱታ ጋር በማያያዝ የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ መስጠታቸውን 2ኛ ተጠሪም ካርታውን እና ሌሎች ሰነዶችን ከተቀበሉ በኂላ ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመጥቀስ እንዲመለስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን ከክሱ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ተጠሪዎችም ይዞታ ማረጋገጫ ካርታውን እና ሌሎች ሰነዶችን ከአመልካቿ የተቀበሉ መሆን አለመሆናቸውን፤ከተቀበሉ ደግሞ ለመመለስ እንቢተኛ የሆኑበት ህጋዊ ምክንያት ካላቸው ማስረዳት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህ ደግሞ ውሳኔ ሊያገኝ የሚችለው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ እንጂ ፍርድ ቤቶቹ በሰጡት ትዕዛዝ እንዳሰፈሩት በአስተዳደር መስሪያ ቤቱ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ከይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ከሰነዶች ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ ተጠሪዎቹ ካርታውን እና ሠነዶቹን ወስደው ከሆነ የወሰዱበት አግባብ ህጋዊ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊጣራ የሚችል ጉዳይ ሆኖ ባለበት ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል አይደለም ሲሉ መደበኛ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን እንደሌለው በመቁጠር በሰጡት ትዕዛዝ ላይ ያሰፈሩት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች በክሳቸው የመሬት ይዞታውን ያገኙት በወጣው የሊዝ ጨረታ በመሳተፍ ዕጣው ደርሷቸው መሆኑን፤ በዚሁ የመሬት ይዞታ ላይ የሊዝ ውል መግባታቸውን የገለጹ ሲሆን ይህ ችሎትም በሰበር መ/ቁ/ 77175 ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ፍርድ የሊዝ ውሎች አስተዳደራዊ ውሎች ተብለው እንደሚወሰዱና በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(መ)

የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም የከተማው አስተዳደር በባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮችን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን በየደረጃው ያዩት የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አመልካች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በህጉ ለመዳኘት ከተሰጣቸው የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን ውጪ ሆኖ ሳለ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/9(1)፣ 231(1)(ለ) መሰረት የክስ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በሚል መመለስ ሲገባቸው ተቀብለው መመርመራቸው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎች እና ይህ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 77175 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ቢሆንም በውጤት ደረጃ ግን ፍርድ ቤቶቹ የአመልካችን የክስ አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 198320 በቀን 28/09/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/140656 በቀን 10/03/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ ምክንያቱን ሳንቀበል በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 348(1) መሰረት አጽንተናል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊወሰን የሚችል ነው ብለናል፡፡
3. የሥር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ ተቀብለው የመረመሩት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን በሌላቸው ጉዳይ በመሆኑ ተገቢነት የሌለው ቢሆንም የክስ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጋቸው በውጤት ደረጃ ሲታይ የሚነቀፍበት ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡
4. ይህ ውሳኔ መብቱን የሚጠይቅ ወገን ሥልጣን ላለው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችለውን ክስ የሚያግድ አይሆንም ብለናል፡፡
5. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 92290

ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- ወ/ሪት ጦቢያው መኮንን -ጠበቃ ዘውዴ ሚናስ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. አቶ እርቁ ጎዳ-ጠበቃ ውቤ ጓዴ ቀረቡ

2. አቶ የኔአየሁ ተስፋዬ- ቀርበዋል

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ፍርድ ቤት እግድ የሠጠበት የማይንቀሳቀስ ንብረት እግዱ ተጥሶ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት በተደረገ ሽያጭ ውል መብት በሌላቸው ሰዎች ለሶስተኛ ወገን ንብረቱ ተላልፎ ሲገኝ ያለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻና ይዘትም የሚከተለው ነው፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ወርቅ ያልሆነውን እቃ ወርቅ ነው በማለት በተቀነባበረ የማታለል ዘዴ ብር 700,000.00 (ሰባት መቶ ሺህ) ተወስዶባቸው ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ መስርተው ይህንኑ ብር 2ኛ ተጠሪ እንዲከፍላቸው ተወስኖላቸው ይህንኑ ገንዘብ ለማስከፈል በኮ/መ/ቁጥር 124978 በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደፍርዱ እንዲፈፅምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው አሁን ለክርክሩ መሰረት በሆነውና በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘውና ቁጥሩ 711/3 በሆነው ቤት ላይ ሐራጅ ወጥቶ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረት ፍርድ ቤቱ እግድ ተሰጥቶበት የነበረ መሆኑን ተገንዝቦ የሐራጅ ማስታወቂያውን አውጥቶ አፈጻጸሙን በመምራት ላይ እንዳለ የአሁኗ አመልካች ቤቱን ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ከእግድ ትዕዛዙ በፊት የገዛሁት ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት ሐራጁን ለማስቆም የተቃውሞ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልኩ በቀረበው የአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስም፡-የተቃውሞ ምክንያትና ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 711/3 የሆነውን መኖሪያ ቤት

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ከአቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙትና ስመ ሀብቱንም ለማዞር እንቅስቃሴ ላይ የነበሩና 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የባለቤታቸው መሆኑን በፍርድ ቤት ችሎት ፊት ገልጸው እግድ የተሰጠበትና ለሚመለከታቸው አካላትም እግዱ የተላለፈ ሁኖ እያለ የወ/ሮ ማስተዋል መኮንን እህት የሆኑት የአሁኗ አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው አፈጻፀሙን ለማሰናከል ነው በሚል የአመልካችን አቤቱታ ተቃውመዋል፡፡2ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ባገኙት ውክልና መሰረት ለአሁኗ አመልካች በውልና ማስረጃ የሸጡ መሆናቸውን ስለማመናቸው የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ቤቱን ገዛሁ የሚሉት በቤቱ ላይ በሽያጭ ምክንያት መብት ቀሪ የሆነባቸው ሰዎች ውክልና ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ሰጥተው በመሆኑና ይህ ደግሞ ሕጋዊ ጥበቃ የማይደረግለትና ጥያቄው በአጠቃላይ ከቅን ልቦና ውጪ የቀረበ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል በሚል ምክንያት የሀራጅ መቃወሚያ አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ ቤቱ ለ2ኛ ተጠሪ እዳ ማስፈጸሚያነት ሊሆን ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበውም ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች መቃወሚያ የቤተሰቦቻቸውን ጥቅም ለመከላከል የቀረበ እንጂ ሕጋዊ ገዥ ሁነው በቤቱ ላይ ያቋቋሙትን መብት ለመከላከል የቀረበ አይደለም በሚል ምክንያት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አመልካች 1ኛ ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ በመ/ቁጥር 99833 በሆነው ተስማምተው እግዱ በተነሳበት ሁኔታ እና በሕግ አግባብ የገዙት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በማስረጃ ባልተደገፈ ምክንያትና ከዳኝነት አካሄድ ውጪ ተቃውሞው የቤተሰብን ጥቅም ለመከላከል የቀረበ ነው ተብሎ በግምት ተቀባይነት ማጣቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪዎች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአከራካሪው ቤት ላይ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ እና የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ/ም የሽያጭ ውል ማድረጋቸውና በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ እና እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ መካከል በመ/ቁጥር 99833 በተሰጠው ዋና ክርክር በመ/ቁጥር 118241 በነበረው የብር 840,000.00 የፍርድ አፈጻጸም ክርክር ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥና ለእዳው መክፈያ እንዲውል ታዝዞ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ይህንኑ በመቃወም ቤቱን ከሽያጭ ለማዳን ሲባል ቀደም ሲል ከገዙበት ብር 880,000.00 (ስምንት መቶ ሰማንያ ሺህ) ብር 240,000.00(ሁለት መቶ አርባ ሺህ) በመጨመር ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ/ም ተጨማሪ የቤት ሽያጭ ውል ማድረጋቸው በውል ሰነዶች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት መቀበሉን፣ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ በሆኑበት መዝገብ ላይ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሁነው በጠበቃቸው አማካኝነት 2ኛ ተጠሪ ያላቸውን ንብረት በቃላ መሃላ ስር ሁነው እንዲገልጹላቸው አፈፃጸሙን ለያዘው ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልክተው 2ኛ ተጠሪ ባለቤቱ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ከአቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙት በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኝና ቁጥሩ 711/3 የሆነ ቤት መኖሩን በመግለጻቸው ምክንያት የፍርድ ባለመብት ይኼው ቤት እንዲታገድላቸው ቃለ መሃላ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም የእግድ ትዕዛዝ ማስተላለፉን፣ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ለእዳ መክፈያ እንዲውል ፍርድ ቤቱ ማዘዙን፣የአሁኗ አመልካች ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በተፈረመና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በተመዘገበ የቤት የሽያጭ ውል የአቶ ፍቅረስላሴ አየለና የወ/ሮ ትብይን ታደሰ ወኪል ከሆኑት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገዝቼአለሁ በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ላይ በመ/ቁጥር 99833 በሆነው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስፈርደው በነበሩት መዝገብ አከራካሪውን ቤት ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም አሳግደው የነበረ ሲሆን ይህ እግድ ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም የተነሳው የአሁኑ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል ብር 600,000.00 (ስድስት መቶ ሺህ) ለእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ እዳ መክፈያነት እንዲሆንና ቤቱ እንዳይሸጥ ለማስቆም በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 118241 መክፈላቸውና ሰኔ 14 ቀን 2004 ዓ/ም መመዝገቡ መረጋገጡን የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99833 ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም ከመዘገበው ላይ ዋናውን መዝገብ በመመልከት ተረድተናል፡፡

በመሰረቱ በፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ሂደት ረቺ የሚሆነው ወገን ለፍርድ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲያስችለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ደግሞ ሊከበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ፍርድ ደግሞ ሊፈጸም የሚገባው በፍርድ ባለእዳውና በሕግ አግባብ እንዳይያዙ ከሚጠቀሱት ንብረቶች/መብቶች ውጪ ባሉት የፍርድ ባለእዳ ንብረቶች/መብቶች ስለመሆኑ በቁጥር 378 እና ተከታዮቹ ከተመለከቱት የፍትሐ ብሔር

ስነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው በሕግ አግባብ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ የሚችለው መብትም በሕግ አግባብ ገደብ ያልተደረገበትንና ያለውን መሆኑ እሙን ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በቤቱ ላይ ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ስምምነት ጭምር የተነሳ ቢሆንም እኚህ ተጠሪ ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ባስከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ ንብረት ሊያፈላልጉ ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ/ም በጠበቃቸው አማካኝነት አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ በመሃላ ስር ሁነው ንብረቶቻቸውን እንዲያሳውቁ ጠይቀው ተጠሪው አከራካሪውን ቤት ባለቤታቸው የገዙት መሆኑን በማረጋገጣቸው ሐምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም በቤቱ ላይ ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡አመልካች ቤቱን ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ገዛሁ የሚሉት በዚሁ ቀን ሲሆን ለውልና ማስረጃ የሀምሌ 04 ቀን 2004 ዓ/ም እግድ ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብበት ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ይህ መሆኑ ግን አመልካች አለኝ የሚሉትን ግዥ ሕጋዊ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡ሽያጩ ሲከናወን  የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ሲሆኑ በዚሁ ሰፊው መብታቸው ደግሞ በሕግ ያልተገደቡ መብቶቻቸውን መጠቀም የሚችሉ እኚህ ሰው ሴት ስለመሆናቸው ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1204፣1184 እና 1185 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 ድንጋጌ መሰረት ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊቆጠር እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ወ/ሮ ማስተዋል ቤቱን ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ የገዙት መሆኑን በመግለጽ በፍርድ ቤት ቀርበው የቤቱ ስመ ሃብት የተመዘገበላቸው እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለም የወ/ሮ ማስተዋልን ሕጋዊ ገዥ መሆናቸውን ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው የተቀበሉ በመሆኑ የቤቱ ስመ ሃብት በወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ያለመገኘቱ በቤቱ ላይ ህጋዊ መብት የላቸውም ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የቤቱ ሕጋዊ ባለሃብት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ሁነው እያለ እነ አቶ ፍቅረስላሴ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጡ ውክልና መስጠታቸው በሌላቸው መብት ላይ በመሆኑ በሕግ ፊት ዋጋ የሚሰጠው አይደለም፡፡2ኛ ተጠሪ በእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ወኪልነታቸው በሕግ አግባብ ሊያስተላለፉ የሚችሉት ለሰዎቹ ሕግ ጥበቃ ሊያደርግላቸው የሚችለውን መብት ብቻ ነው፡፡አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ያልተደረገለትን መብት ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ መብት የለውምና፡፡በዚህ መንገድ መብቱ የተላለፈለት ሰውም በሕግ ጥበቃ ሊደረግለት አይገባም፡፡

ሌላው አመልካች ሽያጩ ሕጋዊ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ውሉ ሕግ ስልጣን በሰጠው አካል ፊት የተረጋገጠ ነው በሚል ነው፡፡በእርግጥ ውልና ማስረጃ በዚህ ረገድ ሕጉ ስልጣን የሰጠው አካል መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 334/1995 የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በውልና ማስረጃ

ጽ/ቤትም በሕግ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫየሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመዘጋጀታቸው በፊትም ሰነድ አረጋጋጩ ንብረቱ በመያዥነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ መሆኑን ሊያረጋገጥ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 15(2) ድንጋጌ በኃይለ ቃል አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በውልና ማስረጃ በተረጋገጠ ውል ቢሆንም የቤቱ ስመ ሃብት ከእነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ወደ ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ባለመዞሩ ምክንያት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ከያዙት ግለሰብ ሽያጩን አግኝተዋል ለማለት የሚያስችል ሁኔታ የሌለ መሆኑን በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 99833 እና 118241 የተሰጡ ትእዛዛት የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በአጠቃላይ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአከራካሪው ቤት ሕጋዊ ባለቤት የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ማስተዋል መኮንን መሆናቸውንና እነ አቶ ፍቅረስላሴ አየለ ደግሞ በቤቱ ላይ የነበራቸውን መብት ለወ/ሮ ማስተዋል መኮንን በሽያጭ ማስተላለፋቸውን ፍርድ ቤት ቀርበው ከአረጋገጡ በኋላ ለወ/ሮ ማስተዋል መኮንን ባለቤት ለሆኑት ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዲሸጡ ውክልና መስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ የሠጡት ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 124976 መጋቢት 09 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 88605 ሰኔ 27 ቀን 2005 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/16 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 711/3 የሆነውን መኖሪያ ቤት ላይ የአመልካች አይደለም ተብሎ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ እንዲቀጥል መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በሽያጩ ተግባር የደረሰባቸው ጉዳት ካለ የሚመለከተውን አካል በመክሰስ መብታቸውን ከማስከበር ይህ ውሣኔ አይገድብም ብለናል፡፡
4. ቁጥር 99833 የሆነው የስ/ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 94837

ሚያዝያ22ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ልዑል ዘወዴ - ጠበቃ አቶ ትዕዛዙ አበበ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አጀመራ የወርቅ ግብይት ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የዋስትና ግዴታ ውል ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ባአሁኑ አመልካችና የዚህ ሰበር ክርክር ተካፋይ ባልሆነውና የስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ገ/ኪዳን በርሄ በተባለ ግለሰብ ላይ በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአኙዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቤቱታ፡- የስር 1ኛ ተከሳሽ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በወርቅ ገዥነትና ተቆጣጣሪነት ሲሰራ በነበረበት ጊዜ ለወርቅ ግዥ ከማህበሩ ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ ብር 57,406 አጉድሎ በመገኘቱ እና በዚህም ምክንያት ተከሳሹ ገንዘቡን ለማህበሩ ከከፈለ በኃላ ስራውን እንዲያቆም ተብሎ የነበር ቢሆንም ሆኖም ግን በመካከላቸው በቀን 25/12/2004 ዓ.ም በተደረገው ስምምነት መሰረት ተከሳሹ የጎደለውን ገንዘብ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማህበሩ መልሶ ለመክፈልና ለወደ ፊቱም ስራውን በታማኝነት ለመስራት ተስማምተዋል፡፡ በተስማማው መሰረት ግዴታውን የማይወጣ ከሆነና በዚህ ምክንያት ለሚመጣው ኃላፊነትም የአሁኑ አመልካችን በዋስነት አቅረበዋል፡፡ ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ የስር ተከሳሹ አሁንም በድጋሚ ከማህበሩ ብር 80,000 በቀን 10/2/2005 ዓ.ም ከወሰደ በኂላ መጀመሪያ አጉድሎ ካልተከፈለው ጋር በድምሩ ብር 124,995 በገባው ግዴታ መሰረት ስላልከፈለ ይሄንኑ ገንዘብ ከዋሱ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሹም ቀረቦ በሰጠው መልስ፡- እዳው መኖሩን አምኖ ነገር ግን ከማህበሩ ያልተከፈለው ኮሚሽን ስላለ ሂሳቡ ተሰልቶ ከታወቀ በኃላ እዳው እንዲከፈል ይታዘዝልኝ የሚል

ይዘት ያለው መከራካሪያ ማቅረቡን የውሳኔ ግልባጩ ያሳያል እንዲሁም የአሁኑ አመልካችም ቀረቦ በሰጠው መልስ፡- ለብር 57,406 ተራ የሆነ ዋስትና ግዴታ መግባቱን አምኖ ሆኖም ግን ዋና ባለ እዳ እያለ ለዚህም ቢሆን ልጠየቅ እንደማይገባና ለብር 80,000 ደግሞ ከመጀመሪያውም የዋስትና ግዴታ አለመግባቱን ጠቅሶ መከራከሩን የስር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአኙዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን ተከራከሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኃላ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1776 በዋቢነት ጠቅሶ ሁለቱም የስር ተከሳሾች በተጠሪ ጥያቄ መሰረት ገንዘቡን ይክፈሉ በማለት ወስኖባቸዋል፡፡ በስር ተከሳሾች አመልካችነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች አስቀርቦ ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ቀጥሎም በአሁን አመልካች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ የተመለከተው የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ አቤቱታውን መርምሮ የሰበር ቅሬታው ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አሁን በአመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በሰር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የሰበር ቅሬታውም በዋናነት አመልካች የዋሰትና ግዴታውን የፈረመው ለብር 57,406 እዳ ብቻ ሆኖ ሣለ የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 ድንጋጌን በሚጥስ መልኩ የዋስትና ግዴታ ከተገባበት እዳ መጠን በላይ ለሆነ ገንዘብና ለብር 124,995 አመልካችን ተጠያቂ ማድረጋቸው ተገቢ ካለመሆኑም በላይ አመልካች የገባው የዋስትና ግዴታ አይነትም ተራ ዋሰትና ከመሆኑም አኳያ ዋናው ባለእዳ እዳውን መክፈል የማይችል መሆኑ ሣይረጋገጥ አመልካች ዋሰትና የተገባበትን ገንዘብ እንዲከፍል በስር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1934 ድንጋጌ አኳያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ስህተቱ ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች የዋስትና ግዴታ ከገባው ብር 57,406 በተጨማሪ ዋናው ባለእዳ ከዋሰትና ውሉ በኂላ ላጕደለው ገንዘብ ብር 80,000 ኃላፊ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1922 እና 1924/1/ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጕ ተጠሪም ቀርቦ በቀረበው አቤቱታ ላይ በጽሑፍ መልሱን ሰጥቷል መሠረታዊ ይዘቱም በአመልካች አስቀድሞ የተገባው የዋስትና ግዴታ ዋናው ባለእዳ በኃላ ላይ ላጕደላው ብር 80,000 ጭምር በፍ/ብ/ህ/ቁ.1925(1) ድንጋጌ መሠረት በዋሱ ላይ ኃላፊነትን የሚያስከትል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጕ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጠረ መሠረታዊ የሆነ

የህግ ስህተት የለም በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አመልካችም በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመ/መልሱን ሰጥቶበታል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የዋስትና ግዴታ ግልፅ መሆን እንዳለበት እና ኃላፊነቱም ግዴታ ከተገባለት እዳ ወሰን ለማለፍ እንደማይችል እና እንዲሁም ይህ ለአፈፃፀሙ ግዴታ የተገባለት የእዳ መጠን ወይም የገንዘብ ልክ በዋስትና ውሉ ካልተገለፀ ዋስትናው ፈራሽ እንደሚሆን ከፍ/ብ/ህ/ቁ1922(2)(3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ደግሞ ዋናው ባለእዳ የሆኑት አቶ ገ/ኪዳን በርሔ ያጉደሉትን ገንዘብ ብር 57,406 በተቀመጠው ቀን ገደብ መሠረት ለተጠሪ ካልከፈሉ የአሁኑ አመልካች ተያዥ ወይም ዋስ ሆኖ ገንዘቡን ለተጠሪ ለመክፈል በመስማማት የዋስን ግዴታ በቀን 25/12/2004 ዓ.ም በተፃፈ ውል መግባቱን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ተችሏል ፡፡

ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በገባው ዋስትና ውል (በ25/12/2004 ዓ/ም በተፈረመው ሰነድ) ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ብር 57,406 ብቻ መሆኑን እንጂ ከዚህ ውጭ ዋስትና የተገባለት ሌላ የገንዘብ መጠን በዋስትና ውሉ ላይ አልተገለፀም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በግልፅ ለተጠቀሰው ገንዘብ ብር 57,406 ብቻ ካልሆነ ከዚህ ውጭ በዋስትና ውሉ ላይ ላልተመለከተው እና በኋላ ላይ ዋናው ባለዕዳ ከተጠሪ ማህበር በቀን 10/2/2005 ዓ/ም ወስዶ አጉድሏል ለተባለው ብር 80,000 አመልካች በዋስትና ውሉ መሰረት በኃላፊነት ሊጠየቅ እንደማይችል ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በእርግጥ ገና ለወደፊት ሊደርስ ለሚችል ግዴታ አፈፃፀምም ዋስ ለመሆን እንደሚቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ስር የተመለከተ ቢሆንም እንኳ ይህም ከዋስትና ውል ፎርም ጋር በተያያዘ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት ሊያሟላ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ለወደፊቱ ለሚመጣ ግዴታም ለሚገባ የዋስትና ውል ለምን ያህል እዳ መጠን ወይም ገንዘብ ልክ እንደተገባ በውሉ ካልተገለፀ ዋሱንም ያለአግባብ ሊጐዳ የሚችል ከመሆኑም በላይ ይህ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ድንጋጌም ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922(3) ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ በአመልካች የተፈረመው የዋስትና ውል ከብር 57,406 በስተቀር ገና ወደፊት ዋናው ባለእዳ ሊያጐድል የሚችለውን እዳንም ጭምር ሊያካትት ይችላል ቢባልም እንኳን ለምን ያህል እዳ መጠን ወይም የገንዘብ ልክ እንደሆነ በውሉ ስላልተገለፀ ተጠሪ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1925(1) ድንጋጌን በምክንያትነት ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር ከዚህ በላይ በተገለፀው

ምክንያት ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነም በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካችን በዋስትና ውሉ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ መጠን ብር 57,406 ወሰን በማለፍ ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1922 ድንጋጌ ይዘት አኳያ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች ዋናው ባለ እዳ እዳውን መክፈል የማይችል መሆኑ ሳይረጋገጥ በእኔ ላይ በስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1934 ድንጋጌን ያገናዘበ አይደለም በማለት ያቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ይህ ክርክር እንደአግባብነቱ በአፈፃፀም ጊዜ የሚታይ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ባለገንዘቡ አስቀድሞ የዋናውን ባለእዳ ንብረት ለማፈላለግ እና በእሱ ላይ ክርክሩን ለመቀጠል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1936(1) ስር እንደተመለከተው የሚያስፈልገውን ወጭ አስቀድሞ ለባለገንዘቡ መስጠቱ ባልተገለፀበት ሁኔታ ክርክሩ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአኙዋሃ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 0068/2005 በቀን 14/10/05 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01482/05 በ17/11/05 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 00300/05 በ6/2/06 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በገባው ዋስትና ግዴታ መሠረት ሊጠየቅ የሚገባው ለብር 57,406 (ሃምሳ ሰባት ሺህ አራት መቶ ስድስት ብር) ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡ አመልካች ከዚህ በላይ ላለው የዋናው ባለዕዳ ዕዳ በኃላፊነት ሊጠየቅ አይችልም ብለናል፡፡
3. አመልካች የገባው የዋስትና ግዴታ ዓይነት ተራ ዋስትና በመሆኑ አመልካች ይሄንን የተጠቀሰውን ገንዘብ (57,406) ብር ለመክፈል የሚገደደው ዋናው ባለዕዳ መክፈል ካልቻለ ብቻ ነው ብለናል፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## <u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

- በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን የአፈፃፀም እግድ ተነስቷል፡፡ መነሳቱም ተገልፆ አፈፃፀሙን ለያዘው ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
- የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሻሻሉን እንዲያውቁ የውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 98079

ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-የቀይ አፈር ገዳሞች አቶ ማሙዮ አበራፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ኤርሚያስ ገሠሠ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለተጠሪ በውርስ የተላለፈ ነው የተባለን እና በአመልካች አላግባብ የተያዘ ነው የተባለን ይዞታ በፍርድ ኃይል ለማስመለስ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በራሳቸው እና በሁለት ሕጻናት ወንድሞቻቸው ስም በአሁኑ አመልካች ላይ በደቡብ ወሎ ዞን በጀማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሳቸውም ይዘት ባጭሩ፡- ከከሳሽ ወላጆች በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን 600 ካ.ሜ የቦታ ይዞታ በላዩ ላይ ካለው የሳር ቤት እና የባህር ዛፍ አትክልት ጋር ተከሳሽ አላግባብ ይዞ እንደሚገኝ የሚገልጽ ሆኖ ይኸው ንብረት እንዲመለስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩሉ ከይርጋ መቃወሚያ በተጨማሪ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ክስ ያስነሳውን ይዞታ የያዘው ከሳሽ እንደሚሉት በሕገወጥ መንገድ ሳይሆን የከሳሽ ወላጆች የወሰዱትን የብድር ገንዘብ መመለስ ባለመቻላቸው ክስ ያስነሳውን ይዞታ ከባህርዛፉ እና ሳር ቤቱ ጋር በሽያጭ ውል ለተከሳሽ በማስተላለፋቸው ምክንያት መሆኑን፣ተከሳሽ ሳር ቤቱን በቆርቆሮ ለውጦ ይዞታውንም ወደ ራሱ አዛውሮ በመጠቀም ላይ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ መከራከሩን እና ፍ/ቤቱ የተከሳሽን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ መዝገቡን በብይን ዘግቶ የነበረ ቢሆንም ብይኑ በከ/ፍ/ቤት ተሽሮ በፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ የተመለሰለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩ በተመለሰለት መሰረት በከሳሽ ወላጆች እና በተከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? ሟቾች ለአውራሾች የሚያስተላልፉት መብት አላቸው ወይስ

የላቸውም? የሚሉ ጭብጦችን መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ ከሳሽ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ዘንድ የተደረገ እስካልሆነ ድረስ ሕጋዊ አይደለም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የከሳሽ ወላጆች ብድሩን ለመክፈል ባለመቻላቸው ክስ ያስነሳውን ይዞታ በ1985 ዓ.ም በተደረገ እና በደጎሎ ከተማ በቀበሌ 01 አስተዳደር በተመዘገበ ውል ለተከሳሽ ያስተላለፉ እና ተከሳሽም ይዞታውን ተረክቦ ይዞ የሚገኘው ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ መሆኑ፣ የከተማው መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮም የይዞታው ሕጋዊ ባለቤት ተከሳሽ መሆኑ ታውቆግብሩን በስሙ መክፈል የጀመረ መሆኑ፣ ውሉ በተደረገበት ጊዜ በደጎሎ ከተማ ውስጥ ማዘጋጃ ቤትም ሆነ ውል የሚያዋውል ሌላ አካል ያልነበረ መሆኑ፣ ተዋዋዮቹም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ውሉን በቀበሌው አስተዳደር ለማስመዝገብ ስለመስማማታቸው በውሉ ላይ ገልጸው የተስማሙ መሆኑ፣ የከሳሽ ወላጆችም ይህንኑ አውቀው በሞት እስከተለዩበት 1995 ዓ.ም ድረስ በዚህ ይዞታ ላይ ያቀረቡት የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ፣ ማዘጋጃ ቤቱ በአዲስ መልክ በተደራጀበት በ1997 ዓ.ም ከሳሽ በይዞታው ላይ ግብር መክፈል ጀምሬአለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ግብሩ የተከፈለው ለአከራካሪው ይዞታ መሆኑን የግብር ሰነዱ የማያመለክት መሆኑ በክርክሩ መረጋገጡን በዝርዝር በመግለጽ ለከሳሾች በውርስ የሚተላለፍላቸው ንብረት የለም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ የቀረበለትን ይግባኝ ዘግቶ ያሰናበተ ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሉ በስር ከሳሽ የተካደ መሆኑን፣የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አለመሆኑን፣ውሉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት በመሆኑ በፍ.ሕ.ቁ. 1723 በተመለከው መሰረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ የተደረገ ስላልሆነ እንደረቂቅ የሚቆጠር መሆኑን፣በ15/02/1985 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ውል ረቂቅ ብቻ ነው የሚባል ከሆነ ደግሞ ግራ ቀኙ በፍ.ሕ.ቁ.1815 መሰረት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ መደረግ የሚገባው መሆኑን በዝርዝር ገልጾ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የስር ከሳሽ በ15/02/1985 ዓ.ም. ተደረገ በተባለው ውል ላይ መጠኑ የተመለከተውን ገንዘብ ብር 3,500 (ሶስት ሺህ አምስት መቶ) ለተከሳሽ እንዲመልሱ እና በአንፃሩ ተከሳሽም ይዞታውን ለከሳሽ እንዲመልስ እንዲሁም ቦታውን ለማልማት ያወጣውን ወጪ ክስ መስርቶ እንዲጠይቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታና ንብረት ከተጠሪ ወላጆች በ1985 ዓ.ም በውል ተረክቦ እና በስሙ አዛውሮ ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑ እና የተጠሪ አውራሾችም ይህንኑ ተቀብለው በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩ

በተረጋገጠበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ችሎት ውሉ አልተመዘገበም በሚል አውራሾች አሳልፈው የሰጡት መብት ለወራሾች ሊተላለፍ ይገባል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠሪ ወላጆች ከአመልካች በብድር የወሰዱትን ገንዘብ መመለስ ባለመቻላቸው ከአመልካች ጋር በ15/02/1985 ዓ.ም በተደረገ ውል ክስ ያስነሳውን ይዞታ በሽያጭ ለአመልካች ማሳተላለፋቸው እና ማስረከባቸው፣ውሉም ግራ ቀኙ በተስማሙበት መሰረት በቀበሌው ጽ/ቤት ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ማድረጋቸው፣ ይህንን ያደረጉትም ማዘጋጃ ቤትም ሆነ ውል የሚያዋውል ተቋም በወቅቱ በከተማው ውስጥ ስላልነበረ መሆኑ፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታው የሚገኘው በአመልካች እጅ መሆኑ እና የተጠሪ ወላጆች በሕይወት እስከነበሩበት 1995 ዓ.ም ድረስ በውል ባስረከቡት ይዞታ ላይ ያነሱት የይገባኛል ጥያቄ አለመኖሩ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ ተጠሪ ክስ ያቀረቡትም ክስ ያስነሳውን ይዞታ አመልካች አላግባብ ይዞ እንደሚገኝ በመግለጽ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክስ ያስነሳውን ይዞታ አመልካች አንድም ጊዜ እንዳልያዘ እና በቁጥጥሩ ስር እንዳላደረገ በመግለጽ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት የክርክር ነጥብ የስር ክሳቸውን እና በመዝገቡ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የክልሉ ሰበር ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለመሻር የቻለበት ዓቢይ ምክንያት የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አይደለም የሚል ነው፡፡እንደተባለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች በጽሁፍ እና በፍርድ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ ያለባቸው ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) የተመለከተ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደርም ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል አለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሰረቱ የፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ያደረጉት በነፃ ፈቃዳቸው መሆኑን፣ ሻጩ በሚያስተላልፈው ንብረት ላይ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሙሉ መብት ያለው መሆኑን እና መሰል የውል አደራረግ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በሕጉ የተመለከተውን ፎርም እና ስርዓት አሟልቶ የተደረገ ከመሆን በተጨማሪ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መፃፍ (መግባት) ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1568(ሀ)፣2878 እና በሌሎችም ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ

ውሉ በተደረገበት ጊዜ እና ቦታ ውሎችን ለማዋዋል የሚችል የመንግስት ተቋምም ሆነ የተደራጀ የርስት መዝገብ ያልነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ተዋዋይ ወገኖችም ይህንኑ ተገንዝበው ውላቸውን በወቅቱ ውሎችን ተቀብሎ ይመዘግብ ለነበረው የቀበሌ አስተዳደር በማቅረብ አስመዝግበዋል፡፡ የተጠሪ ወላጆችም በፍ/ሕ/ቁ. 2879 መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ፈጽመዋል፡፡ አመልካችም ከሽያጩ ጊዜ ጀምሮ ንብረቱን በመረከብና በማልማት ላለፉት 18 ዓመታት ሲጠቀምበት ቆይቷል፡፡ የተጠሪ ወላጆች በዚህ ሁኔታ ውሉን ካደረጉበትና ንብረቱን ካስረከቡበት ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በሞት እስከተለዩበት 1995 ዓ.ም ድረስ ባሉት አስር ዓመታት ውሉንም ሆነ ንብረቱን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳያቀርቡ የቀሩት ንብረታቸውን ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በሽያጭ ማስተላለፋቸውን በመቀበል ነው፡፡ በመሰረቱ መንግስት ባለበት ኃላፊነት መሰረት የርስት መዝገብ እንዲደራጅ ባላደረገበት ጊዜ እና ቦታ በተዋዋይ ወገኖች እና በአካባቢው ባሉ የመንግስት (የቀበሌ) አስተዳደር አካላት የሚፈጸሙ የዚህ ዓይነቶቹ ልማዳዊ አሰራሮች ሕጋዊ መሰረት የላቸውም ለማለት የሚቻልበት አግባብ አለመኖሩን ከፍ/ሕ/ቁ.3364 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት የቀበሌ አስተዳደር ውል ለማዋዋል በሕግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም አይደለም የሚለውን ነጥብ ብቻ ነጥሎ በመውሰድ ውሉ ረቂቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው በአግባቡ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሉ ረቂቅ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ በጅማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 90/2003 በ07/02/2004 ዓ.ም.ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 7588 በ16/02/2004 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 26285 በ03/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪን ክስ ውድቅ በማድረግ በጀማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 690/2003 በ07/02/2004 ዓ.ም ተሰጥቶ በደቡብ ወሎ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.7588 በ16/02/2004 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 94070

ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡-

1. አቶ ወልዱ ገ/አብዝጊ
2. አቶ ጉዕሽ ገ/ስላሴ ተስፋዬ
3. አቶ በላይ ገ/ስላሴ ተስፋዬ
4. አቶ ገ/ኪዳን ገ/ስላሴ ተስፋዬ
5. አቶ ብርሃን ገ/ስላሴ ተስፋዬ
6. ቄስ ገ/መድህን ተስፋዬ መረሳ

} ጠበቃ አብርሃም ገ/ወልድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዐ/ሕግ - ተወልደ በርሔ በ V.c.ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች ክሱ በቀረበበት በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ማዕከላዊ ዞን በአብይ ዓዲ ከ/ፍ/ቤት እንደቅደም ተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ፣4ኛ፣5ኛእና 6ኛ ተከሳሽ የነበሩ ናቸው፡፡

ተጠሪ በ06/02/2005 ዓ.ም. አሻሽሎ ያቀረበባቸው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 539(1)(ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ15/09/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ሲሆን በኦምበራ መጠቃ ንዑስ ወረዳ ልዩ ስሙ ሳልኅል በሚባል ቦታ በግፍ ሰው ለመግደል አስበውና አቅደው ከበታች መሬት በኩል ስራ በመስራት ላይ በነበሩት ሰዎች ላይ የድንጋይ ናዳ እያወረዱ ሲያደናቅፉ ከቆዩ በኃላ በጉዳዩ ላይ ለመግባባት ከታች በኩል የነበሩት ሰዎች መጥተው ሲያናግሯቸው ምን አመጣችሁ? በሚል ምክንያት ሟች ነጋሽ መኮንን ይባል የነበረውን ሰው 1ኛ ተከሳሽ በድንጋይ ጭንቅላቱን መትቶ ከመሬት ላይ ሲጥለው 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ጭንቅላቱን በተለያየ ቦታ ላይ በድንጋይ በመምታት ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል በእጁ ገፍትሮ

በመወርወር፣ቀሪዎቹ ተከሳሾች ደግሞ ሟችን ከጥቃት ለማስጣል የመጡትን ሰዎች በመከላከል 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተከሳሾች ገላጋዮችን በድንጋይ ጭንቅላታቸውን በተለያዩ ቦታዎች እየፈነከቱ በማባረር፣6ኛ እና 7ኛ ተከሳሾች ደግሞ አባዲ ስዩም፣ብርሃነ አሰፋ እና ገዳሙ ገ/እግዚአብሔር የተባሉትን ሰዎች በድንጋይ በመምታት፣ልብሶቻቸውን በመጨምደድ እና እጆቻቸውን በመጠምዘዝ እንዳያገላግሉ በመከልከላቸው፤ሟችም በደረሰበት ጉዳት ምክንያት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በ25/09/2004 ዓ.ም. ሕይወቱ በማለፉ ተከሳሾቹ አባሪ ተባባሪ በመሆን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ አሰቃቂ የግድያ ወንጀል አድርገዋል የሚል ነው፡፡

አመልካቾቹ ያቀረቡት መቃወሚያ ውድቅ ተደርጎ የእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው ተጠሪ አራት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ፍ/ቤቱም የተጠሪን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ እንደክሱ አቀራረብ ያስረዳ መሆኑን ገልጾ 2ኛ አመልካች በክሱ በተጠቀሰበት ድንጋጌ ስር፤ቀሪዎቹ አመልካቾች ደግሞ በወ/ሕ/አ.32(3) እና 540 ስር እንዲከላከሉ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 142 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አመልካቾቹ ድርጊቱን ያልፈጸሙ መሆናቸውን እና ሟች የወደቁት በራሳቸው መሆኑን ያስረዱልናል በማለት በድምሩ ስምንት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የመከላከያ ምስክሮቹ ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት እና ከተፈጸመ በኂላ የነበረውን ሁኔታ ገልጸው ከመመስከራቸው በስተቀር ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ በቦታው ያልነበሩ በመሆኑ ምስክርነታቸው የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል የሚችል አይደለም በማለት ይከላከሉ በየተባሉበት ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኂላ በ2ኛ አመልካች ላይ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት፣በ1ኛ እና በ6ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአስራ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት፣በ3ኛ፣በ4ኛ እና በ5ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የስድስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት መነሻ አድርጎ ከወሰነ በኃላ የቀረበባቸው የቀድሞ ሪከርድ አለመኖሩን በማቅለያ ምክንያትነት ይዞ ቅጣቱን በማቅለል በ2ኛ አመልካች ላይ የሃያ ዓመት ጽኑ እስራት፤በ1ኛ እና በ6ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት፤በ3ኛ፣በ4ኛ እና በ5ኛ አመልካቾች በእያንዳንዳቸው ላይ የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት በመጣል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ይግባኝ እና አቤቱታ ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ለስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ከቀረበው ማስረጃ አንጻር 2ኛ አመልካች በወ/ሕ/አ. 539(1)(ሀ) ስር፤ቀሪዎቹ አመልካቾች ደግሞ በወ/ሕ/አ.32(3) እና 540 ስር ጥፋተኛ ልንሰኝ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ

ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በክሱ በተገለጸው ዝርዝር መሰረት ሟች ነጋሽ መኮንን ይባል የነበረውን ሰው 1ኛ አመልካች በድንጋይ ጭንቅላቱን መትቶ ከመሬት ላይ ሲጥለው 2ኛ አመልካች ደግሞ ጭንቅላቱን በተለያየ ቦታ ላይ በድንጋይ የመታው ከመሆኑም በላይ ቀጥሎም ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል በእጁ ገፍትሮ የወረወረው መሆኑ እና ተበዳዩም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በደረሰበት በዚሁ ጉዳት ምክንያት ለሞት የበቃ መሆኑ በተጠሪ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ መረጋገጡን እና አመልካቾቹ በመከላከያ ምስክሮቻቸው ከድርጊቱ መፈጸም በፊትና ከተፈጸመ በኃላ ስለነበረው ሁኔታ ከማስመስከር ውጪ ድርጊቱን ስላለመፈጸማቸው ያቀረቡት ቀጥተኛ መከላከያ አለመኖሩን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በ2ኛ አመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠው በወ/ሕ/አ.539(1)(ሀ) ስር መሆኑን በተመለከተም ቢሆን አመልካቹ በ1ኛ አመልካች በድንጋይ ከጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ ወድቆ የነበረውን ሟች በድንጋይ ከጭንቅላቱ ላይ ከመታው በኃላ ከሃያ ሜትር በላይ ርቀት ወዳለው ገደል የወረወረው መሆኑ እና ሟችም ለሞት የበቃው በዚሁ በሁለቱ አመልካቾች በደረሰበት ጉዳት ምክንያት እንደሆነ የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህ 2ኛው አመልካች የፈጸመው አድራጎት የአፈጻጸም ሁኔታ ደግሞ የአመልካቹን ጨካኝነት እና የአፈጻጸሙን አሰቃቂነት በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ ድርጊቱ የሚሸፈንበትን ድንጋጌ አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም በ1ኛ እና በ2ኛ አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ቀሪዎቹን ማለትም 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾችን በተመለከተ እነዚህ አመልካቾች የተከሰሱት በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 539(1)(ሀ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል ተብለው ሲሆን ይከላከሉ የተባሉትና የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው ደግሞ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር ነው፡፡እነዚህ አመልካቾች አድርገዋል ተብለው በክሱ የተጠቀሰባቸው ግዙፋዊ ድርጊት ሟችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ጥቃት ለማስጣል የመጡትን ሰዎች በመከላከል ልብሶቻቸውን እየጨመደዱና እጆቻቸውን እየጠመዘዙ እንዲሁም በድንጋይ ጭንቅላታቸውን በተለያየ ቦታዎች እየፈነከቱ አባረዋል የሚል ነው፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካቾቹ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለት የካዱ ቢሆንም ከበታች መሬት በኩል በስራ ላይ የነበሩትና ከላይኛው መሬት በኩል የድንጋይ ናዳ የወረደባቸው ሰዎች ከሟች ጋር ወደቦታው በመጡበት ጊዜ አመልካቾቹ በእነዚሁ ሰዎች ላይ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት መፈጸማቸው በተጠሪ ምስክሮች የተረጋገጠባቸው

መሆኑን እና ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር በተመሳሳይ ጭብጥ ያቀረቡት መከላከያ ከላይ ስለ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ከተገለጸው ጋር በተመሳሳይ ምክንያት ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ይሁን እንጂ በክስ ማመልከቻውም ሆነ በተጠሪ ምስክሮች በተገለጸው መሰረት በአንድ በኩል በ1ኛ እና በ2ኛ አመልካቾች፤በሌላ በኩል ደግሞ በቀሪዎቹ አመልካቾች መፈጸማቸው የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ድርጊቶች ከየተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል አንጻር ሲታዩ በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች መፈጸሙ የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ፍሬ ነገር በወ/ሕ/አ. 32 በተመለከተው መሰረት በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በግድያ ወንጀሉ መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ሟችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለማስጣል የመጡትን ሰዎች ደብድበው አባረዋል ከመባላቸው ውጪ እራሳቸው ሟችን በቀጥታ የመቱ ስለመሆኑ በክስ ማመልከቻው ላይ አልተገለጸም፡፡ይህ ፍሬ ነገር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.111(1)(ለ) እና 112 ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ ስርዓት መሰረት በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተ ወይም ክሱ እንዲሻሻል የተደረገ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ ሟችን የደበደቡት 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ጭምር ስለመሆናቸው በተጠሪ ምስክሮች የተገለጸው ፍሬ ነገር በእነዚህ አመልካቾች ላይ ውጤት እንዲኖረው ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፡፡በክስ ማመልከቻውም ሆነ በተጠሪ ምስክሮች በተገለጸው መሰረት እነዚህ አመልካቾች ሟችን ከ1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለማስጣል የመጡትን ሰዎች ደብድበው አባረዋል የተባሉት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በሟች ላይ በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ከፈጸሙ በኋላ በመሆኑ 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች መፈጸማቸው የተረጋገጠው ግዙፋዊ የወንጀል ፍሬ ነገር ራሱን የቻለ ሌላ ወንጀል የሚያቋቁም ነው ከሚባል በቀር ከ1ኛ እና ከ2ኛ አመልካቾች ጋር በየትኛውም ደረጃ ወይም ዓይነት የሚገለጽ የግድያ የወንጀል ሀሳብ በመጋራት ተጎጂዎቹ ሟችን ከጥቃት እንዳያስጥሉ ለመከላከል በማሰብ የተፈጸመ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ያስገኘው ሕግ በፍርዱ ውስጥ መገለጽ እንደሚገባው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 149 የተመለከተው ድንጋጌ የጥፋተኝት ውሳኔው የሚሰጥበት ድንጋጌ መፈጸሙ ከተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር ጋር በጥንቃቄ መነጻጸር እንደሚገባው የሚያስገነዝብ በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት 3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾችን በግድያ ወንጀል ጥፋተኛ በማድረግ የሰጠው ውሳኔም ሆነ ይህንኑ በማጽናት በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በመዝገቡ የተረጋጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለወንጀሉ ምክንያት የሆነው ግጭት የተፈጠረው በላይኛው የመሬት ክፍል በስራ ላይ የነበረው አመልካቾቹ የሚገኙበት ቡድን ከመሬቱ በታችኛው ክፍል በስራ ላይ በነበረው እና ተጎጂዎቹ በሚገኙበት ቡድን ላይ በተደጋጋሚ የድንጋይ ናዳ በማውረዱ ምክንያት ተጎጂዎቹ በዚሁ ድርጊት ተነሳስተው አመልካቾች ወደ ሚገኙበት አካባቢ በመምጣታቸው ምክንያት መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ይህም ግጭቱ የተከሰተው አመልካቾቹ ይገኙበት በነበረው ቡድን ጠብ አጫሪነት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ አመልካቾቹ ድንጋዮችን በመያዝ በዚህ ዓይነቱ ድርጊት ውስጥ በመሳተፍ በተጎጂዎቹ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውም በወ/ሕ/አ. 577(1) እና (3) ስር የተመለከተውን የአምባጓሮ ወንጀል ማድረጋቸውን የሚያመለክት በመሆኑ በአመልካቾቹ መፈጸሙ በፍሬ ነገር ደረጃ በተረጋገጠው መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ድንጋጌ ከወ/ሕ/አ.32(3) እና 540 ወደ ወ/ሕ/አ. 577(1) እና (3) ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ጥፋተኞች የተባሉበት የአምባጓሮ ወንጀል በወቅቱ በስራ ላይ በነበረው  የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ካልወጣላቸው ወንጀሎች መካከል የሚካተት ሲሆን ድርጊቱ የተፈጸመው በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ሰዎች በእርሻ ስራ ላይ ይገኙ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን ከግምት በማስገባት በመመሪያው አንቀጽ 13(2) በተመለከተው መሰረት በአፈጻጸሙና በክብደቱ ወንጀሉ በዝቅተኛ ደረጃ ሊመደብ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በድንጋጌው ስር በዝቅተኛ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተቀመጠው ፍቅደ ስልጣን  እስከ ሰባት ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ሲሆን ከዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው የቅጣት መጠን የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህ የቅጣት መጠን በቅጣት መመሪያው አባሪ አንድ በእርከን 20 ስር የሚወድቅ ሲሆን ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለው በተጠሪ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ የቅጣት ማቅለያን በተመለከተ 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች  የቀረበባቸው ሪከርድ አለመኖሩን ገልጸው አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ማስመዝገባቸውን እና 6ኛ አመልካች የሰባት ቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በመግለጽ  ተጨማሪ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ማስመዝገባቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡የቅጣት መነሻው ከአንድ ዓመት በላይ እና ከሰባት ዓመት በታች በሆነ ጊዜ በእያንዳንዱ የማቅለያ ምክንያት መነሻ ተደርጎ የተያዘው የቅጣት መጠን በሁለት እርከን እንደሚቀነስ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 16(6) በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ የሚደረገው የቅጣት መጠን ሊወሰን የሚገባው 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾችን በተመለከተ በእርከን 18 እንዲሁም 6ኛ አመልካችን በተመለከተ በእርከን 16 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአመልካቾቹ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በማዕከላዊ ዞን በአብይ ዓዲ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 01450 በ24/05/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ.57452 በ08/09/2005 ዓ.ም. እና በመ.ቁ. 59621 በ23/11/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾችን በተመለከተ የተሰጠው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በ3ኛ፣4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ አመልካቾች ላይ በወ/ሕ/አ. 32(3) እና 540 ስር ተሰጥቶ የነበረው የጥፋኝነት ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠቃሾቹ አመልካቾች ጥፋተኞች ሊባሉ የሚገባው በወ/ሕ/አ. 32(1) (ሀ) እና 577(1) እና (3) ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ከሰባት ወር ጽኑ እስራት፤6ኛው አመልካች ደግሞ በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ አመልካቾቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 95875

ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡-1.አቶ አዳሙ ዘለቀ
2.አቶ ሽባባው ወሂሶ
3.አቶ ኃይሉ ሽበት
የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-የአማራ ክልል አቃቤ ሕግ የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአንድ ወንጀል ጉዳይ በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ሰው ውሳኔውን እንዲነሳለት ለመጠየቅ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ አተገባበርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡አመልካቾች በዚህ ፍርድ ቤት በዞኑ አቃቤ ሕግ የተከሰሱት ታደሰ ግዛት ከተባለ ግለሰብ ጋር ሁነው ገበየሁ ጋው የተባለ ሰው በግፍ ገድለዋል ተብሎ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) እና 539(1/ሀ) ተጠቅሶባቸው ነው፡፡የአሁኑ አመልካቾች በበኩር ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ሊቀርቡ አልቻሉም ተብሎ ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን የስር 4ኛ ተከሳሽ የነበረው ታደሰ ግዛት ግን ቀርቦ ተከራክሯል፡፡ፍርድ ቤቱም በአቶ ታደሰ ግዛት የቀረበውን ክስ በተመለከተ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የምስክሮች ቃልና ተከሳሹ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 27(2) መሰረት ለፖሊስ የሰጠው ቃል የማይጣጣም፣ እርስ በእራሱ የሚጋጭ ሁኖ ተገኝቷል በሚል ምክንያት ተከሳሹን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 መሰረት በነጻ ያሰናበተው ሲሆን የአሁኑ አመልካቾችን በተመለከተ ግን በአቃቤ ሕግ ምስክሮች የሠው ግድያ ወንጀል የፈፀሙ መሆኑ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ለወንጀሉ ኃላፊ ያደረጋቸው ሲሆን አድራጎቱንም በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ሳይሆን ተራ በሆነ የሰው ግድያ ወንጀል የሚሸፈን ነው በማለት በክስ ማመልከቻው ላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሰረት ወደ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 540 ድንጋጌ

ለውጦ አመልካቾችን እያንዳንዳቸውን በ18 (አስራ ስምንት) አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ጥቅምት 08 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ፍርዱን መፈፀም መጀመራቸውንና በዋናው ጉዳይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በ01/08/2004 ዓ/ም ይግባኝ ጠይቀው እንደሚገኙ ገልጸውና ቀድሞ መፈፀም ያለበት ስርዓት በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማቅረብ መሆኑን መገንዘባቸውን ጠቅሰው በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ ሁኖ ክርክሩ ባሉበት እንደገና እንዲሰማ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአሁኑ አመልካቾች ጥያቄ ላይ የዞኑ አቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የተወሰነ መሆኑን ያወቁት ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን፣አንድ የወንጀል ጉዳይ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰንበት የተደረገ ሰው ደግሞ ውሳኔው ውድቅ እንዲሆን ጥያቄ ማቅረብ ያለበት ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሰላሳ ቀናት ውስጥ መሆኑን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተደነገገ መሆኑን እንዲሁም አመልካቾች ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስርዓቱን ባለማወቅ አቅርበናል የሚሉት ምክንያትም ሕጋዊ ያለመሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ከተጠሪ ጋር እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ሰኔ 08 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰላሳ ቀናት ጊዜ ለመቁጠር መነሻ ያደረጉት ሁኔታ የአመልካቾችን በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ቆይተው በስነ ስርዓት ተገቢውን ለመፈጸም ጥያቄውን ማቅረባቸውንና የመከራከር መብት መከበር ያለበት መሆኑን በአግባቡ ሳይገነዘቡ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካቾች ጥያቄ በሰላሳ ቀናት ያልቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎ የተወሰነባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መኖሩን ያወቁት መጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም

መሆኑን፣ሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም ደግሞ በዋናው ጉዳይ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረባቸውን፣ በዚህ ሂደት ውስጥ ከቆዩ በኂላ በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05102 ጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ/ም የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ስህተት ያልተገኘበት ነው ተብሎ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(1) ከመጽናቱ በፊት ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ውድቅ እንዲሆንላቸው አቤቱታቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 202 የተደነገገው ሥርዓት ጉዳዩን ተከሣሹ በሌለበት (default) በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተደነገገው መሠረት አይቶ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ ውድቅ ለማስደረግ የሚያገለግሉ ድንጋጌዎችን ያካተቱ ሲሆኑ ድንጋጌዎች ጥያቄ መቅረብ ያለበት እና የጊዜ ገደብ፣ የጥያቄ አቅራቢ ማመልከቻ ምክንያት መግለጽ ያለበት መሆኑን፣ በጊዜ ገደቡ ውስጥ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የማያገኝበትንና የሚያገኝበትን አግባብና በዚህ አግባብ በፍርድ ቤቱ የሚሰጡ ትዕዛዛት ያላቸውን ሕጋዊ ውጤቶቻቸውን በተመለከተ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 በተደነገገው መሰረት በሰላሳ ቀናት ውስጥ አመልካቾች በሌሉበት የተፈረደውን ፍርድ ውድቅ ለማስደረግ ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ማመልከቻቸውን አላቀረቡም፣ ፍርዱን ያወቁት ከመጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ሁኖ እያለ ጥያቄውን ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ማቅረባቸው ስነ ሥርዓታዊ አይደለም በማለት ነው፡፡ይህ መሆኑን አመልካቾችም የሚክዱት የፍሬ ጉዳይ ክርክር አይደለም፡፡አመልካቾች የሚከራከሩት በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ካሉ በኃላ ትክክለኛውን ስነ ስርዓት መከተል ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄያቸውን ማቅረባቸውን በመግለጽ ነው፡፡ በእርግጥ ትክክለኛውን የህግ ስነ ስርዓት አለማወቅ ለአቤቱታው አቀራረብ በሕጉ የተደረገውን የጊዜ ገደብ ለመተው የሚያስችል ምክንያት ባይሆንም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተመለከተው የጊዜ ገደብ ማቋረጫ ሕጋዊ ምክንያት በስነ ስርዓት ሕጉ በግልጽ ያለመመልከቱ ግን ይኼው ምክንያት መኖር ያለመኖሩን ከመከራከር አጠቃላይ መብትና ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 160 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ አንጻር ፍርድ ቤቱ ከማየት የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት የሌለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

የመከራከር መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 ድንጋጌ እና በሌሎች የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ጥበቃ ያገኘ መሰረታዊ መብት መሆኑ ይታወቃል፡፡የአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 በጠቅላላውና ንዑስ አንቀጽ 3/መ/ በልዩ ሁኔታ በአቀራረቡም ሆነ በይዘቱ የወንጀል ክስ ተከሣሽ

ባለበት መታየት ያለበት መሆኑን የሚደነግግና በወንጀል የተከሰሰ ሰው ሊከበርለት የሚችል ሰፊ መብት ያለው መሆኑን በዝርዝር ይደነግጋል፡፡ ይህ መብት ሊከበር የማይችለው በሕጉ የተዘረጋው ስርዓት መሰረት ተደርጐ ሲሆን ከእነዚህ በህግ ከተዘረጉ ስርዓቶች አንዱ የወንጀል ክስ ተከሣሹ በሌለበት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 160 እስከ አንቀጽ 163 በተመለከተው አግባብ እንዲታይ የተዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ከፍትህ ሸሽተው ተገቢውን ፍርድ ሳያገኙ እንዳይቀሩ ለማድረግ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ድንጋጌዎቹን ተፈፃሚ የሚያደርገው ተገቢውን የመጥሪያ አደራረስ ስርዓት ተከትሎ መሆኑንም ያስገነዝባሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የመጀመሪያው የወንጀል ክሱ በሌለበት የታየ ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ ውድቅ እንዲሆንለት ያቀረበው ማመልከቻ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 201 በተደነገገው ሥርዓት እንዲታይ መደረጉም የተከሳሽን የመከራከር መብት ከመጠበቅ አንጻር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ስርዓት ሕጋዊ ምክንያት ያለውና ጥሪውን ለመስማት ያልቻለ ሰው ባለመቅረቡ ብቻ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተሰጥቶ እንዳይቀር ታስቦ የተቀመጠ ስርዓት ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የሚቀርብ ጥያቄ ከመከራከር ህገ መንግስታዊ መብትና ከዝርዝር ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ፣ ይዘትና መንፈስ ጋር ተዛምዶ መታየት ያለበት ጉዳይ ሁኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 ስር የተቀመጠው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት የመከራከር መብትን በማያሣጣ ወይም በማያጣብብ መንገድ መሆን አለበት፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካቾች በዋናው ጉዳይ ላይ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ተቀብሎ በማየት ላይ እንዳለ ውጤቱን ሳይጠብቁ የመከራከር መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡበት ሁኔታ ጥያቄያቸውን በሰላሳ ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ አላቀረቡም ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ እንደዚህ አይነት ጥረት የነበረው ሰው በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥያቄውን አላቀረበም ተብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ የመከራከር መብትን በአግባቡ ለማስከበር የሚያስችል ነው ተብሎ የማይታሰብ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ሕግን አለማወቅ ጥያቄያቸውን ለመቀበል የሚያስችል አይደለም፣ ጊዜው መቆጠር ያለበት ፍርዱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው በማለት ያሰፈሩት ምክንያት ሕጋዊ ቢሆንም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 ስር የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ ሊቋረጥ የሚችልበትን ምክንያት ግን አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው ቆይተው ውጤቱን ሳይጠብቁ ትክክለኛውን ስነ ስርዓት ከመከተላቸውና ይህም ከመከራከር መብት ጋር አንፃር ሲታይ የሰላሳ ቀናት ጊዜውን ቀሪ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በሕገ መንግስቱ የተከበረው የመከራከር

መብት ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 198 ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ ጋር አጣጥሞ በመተርጎም ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የፈፀሙ ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01346 ሰኔ 08 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28404 መስከረም 28 ቀን 2006 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ የጸናው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 198 መሰረት በሰላሳ ቀናት ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ግንቦት 20 ቀን 2004 ዓ/ም ያቀረቡትን አቤቱታ የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ የማያግደው ነው ተብሎ መወሰኑን ተገንዝቦ ጥያቄያቸውን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 199 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በመመርመር አመልካቾች በሌሉበት የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ነጥብ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

የሰ/መ/ቁ. 96503

ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** መኮንን ወለላው ካሳ ጠበቃ ዘነበ አሰፋ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ህግ

ዋልተንጉስ ፍቅሬ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የአቤቱታው መነሻ የአሁኑ አመልካች የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ/ም ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ማመልከቻ ሲሆን ይዘቱም፡- በመ/ቁጥር 65858፣ 66882፣ 71671 እና በመ/ቁጥር 87280 በሆኑ መዛግብት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተለያዩ መጠን ያላቸው የእስራት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮዎች እንደተወሰኑባቸው ገልጸው ቅጣቶች እንደገና ተጣምረው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 186 መሰረት በአንድነት ተጠቃለው ይወሰኑልኝ በማለት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን ጥያቄ በኮ/መ/ቁጥር 87280 በመቀበል ከተመለከተው በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአራቱም መዝገቦች በአመልካቹ ላይ ተወስነውበት የነበሩት ቅጣቶች በአንድነት ተጠቃለው ተደምረው በ24 አመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 22,500 የገንዘብ መዋጮ እንዲቀጣ የሚል ውሳኔ በመስጠት ማረሚያ ቤቱንም በአንድነት ተጠቃሎ በተወሰነው ቅጣት መሰረት እንዲያስፈፅም አዟል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔን አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቹ የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የበታች ፍርድ ቤቶች አራቱን መዝገቦች በማሰባሰብና በማጣመር በወንጀል

ሕግ አንቀጽ 186(3) መሰረት አይቶ መወሰን ሲገባቸው ያለአግባብ በመደመር ቅጣቱን ከፍ አድርጎ የወሰኑባቸው ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ) ድንጋጌ ውጪ መሆኑንና ቅጣቱን በተመለከተውም በሕግ አግባብ ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግንዛቤ ውስጥ ገብተው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የቅጣት መጠኑ ያለመሰላቱን የሚገልፅ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የበታች ፍርድ ቤቶች ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) የሰጡት ትርጉም ተገቢ መሆን ያለመሆኑንና የቅጣት መጠኑ የተወሰነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያን መሰረት አድርጎ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) መሰረት የቅጣት ይጣመርልኝ ጥያቄ ከቀረበ በየመዝገቦቹ የተወሰኑትን ቅጣቶች መደመር ሳይሆን በአንድነት በማጠቃለል እንደገና በአዲስ መልክ ቅጣቱ ተሰልቶና ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው ጉዳዩ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ) ለአንድ የወንጀል ሐሳብ አንድ ቅጣት ከመሆኑ እና ከቅጣት መመሪያ ድንጋጌዎች አንፃር ታይቶ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው ነው በማለት ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአራት የክስ መዝገቦች ቀርበውባቸው እንደነበር፣ በወ/መ/ቁ 66882 ቀርበውበት በነበሩት 2 ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት የ9 ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 15,000 መቀጮ፣ በወ/መ/ቁ 71671 በቀረበበት አንድ ክስ ጥፋተኛ ተደረጎ የተወሰነበት የ5 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እና የብር 7000 መቀጮ እንዲሁም፣ በወ/መ/ቁ. 65858 በቀረቡበት ሁለት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ የተወሰነበት የ10 ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት እንዳለ የፀኑና ያለቀላቸው መሆኑን፣ በወ/መ/ቁ.87280 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቹ ላይ ቀርበው በነበሩ ሁለት ክሶች ጥፋተኛ አድርጓቸው የ2 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እና የብር 1000 መቀጮ ወስኖባቸው የነበረ ቢሆንም አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበው በአንዱ ክስ ብቻ ጥፋተኛ ተብለው የ6 ወር ቀላል እስራት ቅጣት እና የብር 500 መቀጮ የተወሰነባቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ

ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል ብሎ ከተጠቃሹ ድንጋጌ በላይ ወደ ተገለፁት ድንጋጌዎች የሚያጣቅስ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ በተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች ተወስነው በተገኙ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው መወሰን አለበት የሚል መንፈስ ያላቸው አይደሉም።ይልቁንም ሕጉ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ እንደሚወሰን የሚያስረዳ ነው። ስለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የሚመለከተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ)"ም" ሲታይም ጥፋተኛው ተደራራቢ ወንጀሎች ፈፅሞ በተገኘ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈፀሙ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢው የቅጣት መጠን ተወስኖ የሁሉም እንደሚደመር እና ቅጣቶችም ተደምረው ለወንጀሉ አይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ እንደማይችል ያስቀምጣል። በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የፅኑ እስራት ከፍተኛው ቅጣት ሃያ አምስት አመት ስለሆነ በጽኑ እስራት የሚያስቀጡት ተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣቶች ተደምረው ከሃያ አምስት አመት ሊበልጡ እንደማይችሉ ደግሞ ይሄው ድንጋጌ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 108(1) ድንጋጌ ይዘት ያሳያል። የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ይዘቱና መንፈሱ ደግሞ ቅጣቶቹ ተደምረው ከሃያ አምስት አመት በሚበልጡበት ጊዜም ሃያ አምስት አመት ላይ እንዲያቆም ፍርድ ቤቱ እንዲቆም የሚያስገድድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

እንግዲህ ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ጥፋተኛው ከፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ውስጥ የየትኛውም ወንጀል ቅጣት የቀሪዎችን ወንጀሎች ቅጣት የሚያጠቃልል ካልሆነና ወንጀሎቹ በእስራት የሚያስቀጡ ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ከሆኑ ለእያንዳንዱ በተደራራቢነት ለተፈፀመው ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ተወስኖ ሁሉም እንዲደመር የሚደረግ መሆኑን እና ምንጊዜም ቢሆን ለእስራቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ጣሪያ ቅጣት ማለፍ አይቻልም ተብሎ መደንገጉ ነው።ይህም መታየት ያለበት አጥፊው ጥፋተኛ የተባለበት ልዩ ድንጋጌ የሚያስቀምጠው የቅጣት ጣሪያ ሳይሆን በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ጣሪያ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። እንዲሁም አንድ ሰው የፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች ከፊሎቹ የሚያስቀጡት በቀላል እስራት፣ ከፊሎቹ ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሚሆኑበት ጊዜ የቅጣት አወሳሰኑ ቅጣቶችን ለመደመር እንዲያመች ሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት ይቆጠራል ተብሎ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል።
ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም ከላይ በተጠቀሱት አራት መዝገቦች በአመልካች ላይ በተለያየ ጊዜ ተነጣጥለው የተወሰኑበት የተለያዩ ቅጣቶች ተጣምረው ይወሰኑልኝ በሚል ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ

ሰሚው ፍ/ቤት የተወሰነበትን የ6 ወር ቀላል እስራት ወደ 3 ወር ጽኑ እስራት በመለወጥ የአራቱም መዝገቦች ቅጣቶች በአንድነት በማጠቃለል ደምሮ የ24 ዓመት ከ3 ወር ፅኑ እስራት ቅጣት እንዲፈፀም ከመወሰን ወጪ በሕጉ ስለጽኑ እስራት የተቀመጠውን ጣሪያ በማለፍ የወሰነው ቅጣት የለም፡፡ አመልካች በመጀመሪያ ይህንኑ የቅጣቶች ይጣመሩልኝ ጥያቄ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ አመልካቹን ጥያቄውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አለብህ ብሎ የመለሰው ወይም የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአራቱንም መዝገቦች ቅጣቶች አሰባስቦ እንደገና በመከለስ አዲስ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በተከተለ መንገድ እንዲያይ ስለመሆኑም የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ በግልጽ ያሳያል፡፡ አስቀድሞ በየመዝገቦቹ ቅጣቶቹ በተናጠል በሚወሰኑበት ጊዜ ሁሉም ነገሮች ታይተው ለፈፀማቸው ወንጀሎች ይመጥናሉ ተብለው የተወሰኑ መሆናቸው በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ሲሆን የቅጣቶች አፈጻጸምን በተመለከተም ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186(3)፣ 184(1(ለ)) እና 108(1) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ተደምረው እንዲፈፀም ማድረግ የድንጋጌዎቹን ትክክለኛ ትርጉም አተገባበር የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሊባል የሚችልበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩበትና ለዚህ ችሎት እንዲታይ የተያዘው ነጥብ የቅጣት አሰላሉን የሚመለከተው ነጥብ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት ተደርጎ ቅጣቱ ያለመሰላቱንና የቅጣት መጠኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ከፍ የተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች በተለያዩ ጊዜ ፣በተለያየ ሰነድና በተለያየ ቦታ ለፈጸሟቸው ተደራረቢ ወንጀሎች በተለያዩ መዛግብት ጥፋተኛ ተብለው ቅጣቱ ሲወሰን አለኝ የሚሏቸው ሕጋዊ የቅጣት ማቅለያ ምክያንቶች ተይዘውላቸው ቅጣቱ መሰላቱን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ቅጣቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186(3) ድንጋጌ አግባብ ታይቶ እንዲወሰን ሲደረግ ወይም መዝገቦቹ ተነጣጥለው ሲወሰኑ የተያዙት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች እንደገና የሚታዩበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በአመልካች ጥያቄ አግባብ ቅጣቱ እንዲሰላ ማድረግ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሁለት ጊዜ ዋጋ የመስጠት ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ በሕግ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን አመልካቹ መዝገቦቹ ተነጣጥለው ሲታይ ቅጣቱም ተነጣጥሎ ሲወሰን በተለያዩ መዝገቦች ተመሳሳይ የቅጣት ማቅለያ እንዲያዙ መደረጉ በውጤቱ አመልካችን ጠቅሟቸዋል ከሚባል በስተቀር የመብት መጣበብን አስከትሎባቸዋል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካቹ ቅሬታም የሕግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ሲጠቃለልም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87280 ሐምሌ 09 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 92594 ጥቅምት 04 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(መ) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በጉዳዩ ላይ የበታች ፍርድ ቤቶች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) ሲተርጉሙም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ ሲያደርጉ የፈፀሙት ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በአመልካች ላይ የተጣለው ቅጣት የጸና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለማረሚያ ቤቱ ትዕዛዝ ይድረስ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ታ/ተ

የሰ/መ/ቁ 98647

ሰኔ 02 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ፅጋቡ ወላይ ገብሩ- VC ስላልሰራ መቅረቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዐቃቤሕግ - VC ስላልሰራ መቅረቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ከሚሊኒየም ዴቨሎፐመንት ፐሮጀክት ጋር ከመቐሌ ወደ ሓውዜን ሲሚንቶ እንዲያጓጉዝላቸው የማጓጓዝ ሃላፊነት ተሰጥቶት በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት አጓጉዞ በጊዜው ሊያስረክባቸውና ለህዝብ ልማት ላይ ሊያውል የሚገባውን እምነት አጉድሎ ሲሚንቶውን ሸጦ ለግል ጥቅሙ በማዋሉ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ድንጋጌን ተላልፏል የሚል ሲሆን የአሁኑ አመልካች ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቅ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌለው መሆኑን ገልጾ የድርጊት አፈጻጸሙን በተመለከተ ግን በመጓጓዣ ዉሉ መሰረት ሲሚንቶውን መረከቡንና መሸጡን አምኖ ሆኖም አስጫኙ ያልከፈለው ገንዘብ ስለነበረ ይህንኑ ገንዘብ አስቀርተው ቀሪውን እንዲረከብ ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀባይነት ያጡ መሆኑን ገልፀው ጉዳዩ በፍትሐብሔር እንጂ በወንጀል ሊያስጠይቀኝ አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የክልተ በለሳ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩ የፍትሐ ብሔር እንጂ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም በማለት አመልካችን በነጻ አሰናብቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምስራቅ

ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ሲሚንቶውን የሸጠው በውሉ መሰረት ሳያስረክበው የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት አመልካችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(1) ስር ጥፋተኛ አድርጎታል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና ድንጋጌው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ቅጣቱን ከአሰላ በኋላ አመልካች  በሁለት አመት ከሶስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አድራጎቱ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው በማለት ድምዳሜ ላይ የደረሰው ከስልጣኑ ውጪ ማስረጃ መዝኖ ከመሆኑም በላይ በማስረጃ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተመለከቱትን የወንጀሉን ማቋቋሚያዎችን የሚያሟሉ አይደሉም የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(1) የሚያስጠይቅ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ  ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 (1) ድንጋጌ ስር ነው?  ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አመልካች አልፈጸምኩምበማለት ያልተከራከረ ሲሆን አጥብቆ የሚከራከረው በመኻንዣ ውሉ መሰረት ሊከፈለኝ የሚገባው ገንዘብ በሲሚንቶው አስጫኙ ድርጅት ስላልተከፈለ ሲሚንቶውን ሸጦ የመኻንዣውን ገንዘብ አመልካች ከቀነሰ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ ከሰሚንቶ አስጫኝ ድርጅት ለመመለስ ጥረት አድርጎ ድርጅቱ ቀሪውን ገንዘብ ሊቀበለው ያልቻለ መሆኑን በመጥቀስ ጉዳዩ ፍትሐ ብሔራዊ እንጂ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም በማለት ነው፡፡በርግጥ አመልካች ይህንኑ ቃሉን በመከላከያ ማስረጃዎቹም ያረጋገጠው ፍሬ ነገር መሆኑን  ክሱን የሰማው የወረዳው ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም እንደዚሁ የተሰማውን ማስረጃ በመመዘን ሲሚንቶው የተሸጠበትን ሁኔታ እርግጠኛ ሆኗል፡፡ የሲሚንቶው መሸጥ ድርጊት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው ፍሬ ነገር በአመልካች ካለመካዱም

በላይ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን በዚህ መልክ በመምራት መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡እነዚህ ፍርድ ቤቶች የአመልካች ድርጊት የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት አመልካች በመንገዣ ውሉ መሰረት ያልተከፈለውን ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሲሚንቶውን ሽጦ ከመንገዣ ዋጋ የተረፈውን ለሲሚንቶው አስጫኝ ድርጅት ለመመለስ አመልካች ጥረት ቢያደርግም ድርጅቱ ገንዘቡን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግን አመልካች ሲሚንቶውን እንዲሸጥ የውል ስምምነት የተደረገው መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ ከዚህ ቀን በፊት ያለው ውል ደግሞ ይህንኑ መብት እንደማይሰጠው፣ሲሚንቶውም የተሸጠው ከመጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ/ም በፊት ሁኖ የቀደመው ሕጋዊ ውል ባለበት ሁኔታ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአመልካች አድራጎት የእምነት ማጉደል ወንጀል ነው በማለት ደምድሟል፡፡ይህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድምዳሜ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃውን በመመዘን የተያዘ ሳይሆን በክርክሩ ሂደት የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጧቸው ፍሬ ነገሮችን በመለየት የተያዘ በመሆኑና በክርክሩ ሂደት የቀረቡት ማስረጃዎች ያረጋገጧቸውን ፍሬ ነገሮች የበታች ፍርድ ቤቶች ባግባቡ ሳይዙና ሳይመለከቱ ቀርተው በዚህ ረገድ ቅሬታው በስርዓቱ መሰረት ለሰበር ሰሚ ችሎት ቢቀርብና ችሎቱም ይህንኑ ቅሬታ ተቀብሎ በዚህ ረገድ የተፈፀመውን ስህተት ቢያርም የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም የሚል ቅሬታ የሚነሳበት ጉዳይ አይደለም፡፡ምክንያቱም የአንድ የህግ ድንጋጌ ትክክለኛ ትርጉም  እና አተገባበር የሚኖረው በህጉ አግባብ የተቆጠሩት ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ነገሮች  ከእነ ሙሉ ይዘታቸው ታይተውና  ተመዝነው እንጂ ማስረጃዎቹ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር በመተው ሊሆን አይገባምና፡፡ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ ያነሳው ቅሬታ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕግ ጥያቄ አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሰረት ሲሚንቶውን በሙሉ በጥንቃቄ በማጓጓዝ፣ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን አለመወጣቱ አመልካችን በፍታሐብሔር ተጠያቂ ከመሆን አልፎ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቃቸው ነው ወይስ በሌላ ድንጋጌ? የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀል ህጉ በንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝርበት ምእራፍ ሁለት በልዩ ሁኔታ በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በሚዘረዝረው ክፍል አንድ ሥር የተደነገገው የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሠረታዊ ባህሪ ይዘትና የሚያስከትለው ኃላፊነትን የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ ሲታይም፡

" ማንም ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ ግልጋሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ ፣ የወሰደ ፣የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለውን ማናቸውንም አድራጎት የፈጸመ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እስራት ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል" በማለት ያስቀምጣል፡፡ የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተከሣሹ ወንጀል ሃሣብ ግምት የሚደነግግ ሲሆን ይዘቱም ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ማዋል ሃሣብ እንዳለው ይቆጠራል የሚል ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይ አመልካች በገባው የእቃ ማጓጓዝ ውል መሠረት ሲሚንቶውን በማጓጓዝ በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡የድንጋጌው ይዘት አንድ ሰው አንድን ንብረት ለአንድ አገልግሎት ለማዋል በኃላፊነት ተረክቦት ንብረቱን ለተባለው አገልግሎት ሳያውል ሲቀር በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑን የሚመለከት እንጂ በማጓጓዝ ውል መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቂ አድርጐ እቃውን በማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ያልተወጣ አጓዥ በዕምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ የድንጋጌው ይዘትና መንፈስ የማያሣይ በመሆኑ በዚህ በኩል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል በማጓጓዝ ውል መሠረት በልምድ መሠረት የሚገባውን ሙሉ ጥንቃቄ በማድረግ እቃውን ማጓጓዝና በተወሰነው ጊዜና ሥፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታውን ሳይወጣ አመልካች ሲሚንቶውን መሸጡና የሸጠውም ያልተከፈለውን የማጓጓዣ ዋጋ ለራሱ ለማድረግ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ማንም ሰው በዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቀው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠውን ዋጋ ያለው ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገዉ የወንጀል ሃሣብ ግምት የማይሸፈን መሆኑን ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ እንዲሁም በአመልካችና በሲሚንቶው አስጫኝ ድርጅት መካከል ከነበረው የውል ግንኙነት ለመረዳት የሚቻል ሁኖ አግኝተናል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የመጓጓዣ ዋጋውን ሲሚንቶውን ሸጦ ለራሱ ማድረጉ ከስምምነት የመነጨ አድራጎት ያለመሆኑ

የተረጋገጠ ሲሆን ይህ የአመልካች መብት በሲሚንቶ አስጫኙ ድርጅት በውሉ መሰረት ካልተፈጸመም አመልካች ያላቸው መብት በሕግ አግባብ መብታቸውን ማስከበር ነው፡፡ከሕግ ውጪ መብት አለኝ በማለት የሌላውን ሰው መብት ለራስ ጥቅም ማዋል ደግሞ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መብትን ማስከበር ሲሆን ይህም የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል አድራጎት መሆኑን ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 436(ለ) ስር ከተደነገገው ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው የህግ፣ የግዙፍ ተግባርና የሞራል ሁኔታ በአንድነት ተጣምረው መገኘታቸው ሲረጋገጥ እንደሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር ሰፍሯል፡፡ በያዝነው ጉዳይም የአመልካች አድራጎት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ስር የተዘረዘሩት የህግ የሃሣብ ሁኔታዎች ያልተሟሉ ቢሆንም አድራጎቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436(ለ) ስር የሚሸፈን ሁኖ ስለአገኘነው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113(2) እና 195(2)(ለ)(2) ድንጋጌዎች አግባብ በማሻሻል አመልካች ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መብት ማስከበር ወንጀል የፈጸመ በመሆኑ ጥፋተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡

አመልካች መቀጣት ያለበት  በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ ስር ሲሆን ድንጋጌው የሚያስቀጣው ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት  ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ሲሆን እኛም የአመልካችን አድራጎትና የቅጣትን መሰረታዊ ዓላማ እንዲሁም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያስያዛቸውን ሪከርድ ያልቀረበበት መሆኑንና የቤተሰብ አስተዳዳሪነቱን የሚመለከቱትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተናል፡፡ቅጣቱን ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ መሰረት በማድረግ አስልተናል፡፡ይህን ሁሉ መሰረት ስናደርግ አመልካች የታሰረበት ጊዜ በቂ ሁኖ እንዲፈታ ማድረጉ አመልካችን የሚያርም ሌሎች መሰል ወንጀሎችን የሚያስጠነቅቅ ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የአመልካችን አድራጎት በሚሸፈነው ድንጋጌ ረገድ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 60228 ጥር 29 እና 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 195(2)(ለ(2)) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. የአመልካች አድራጎት በወንጀል የሚያስጠይቅ ሁኖ የሚሸፈነውም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 675(1) ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436(ለ) ስር ነው በማለት አመልካች ለዚሁ አድራጎቱ የታሰረው ጊዜ በቂ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የታሰረው ጊዜ ለአድራጎቱ በቂ ነው ተብሎ በዚህ ችሎት መወሰኑን አውቆ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታው ለመቐሌ ማረሚያ ቤት የመፍቻ ትዕዛዝ ይላክለት ብለናል፡፡ይፃፍ፡፤

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 94227

ቀን 05/09/2006 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች**፡- አቶ ገ/መድህን ኃ/ማሪያም - ቀረቡ(በV.c)

**ተጠሪ**፡- የትግራይ ክልል ዐ/ህግ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታ ያቀረቡት ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገው መጥሪያው በመደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው እንዲደርሳቸው ሳይደረግ በመሆኑ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ የቴሌኮምኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ኃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 4 ስር በ29/05/2005 ዓ/ም የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ እና ተጠሪው የሰጠውን መልስ ከመረመረ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ባለመቀበል የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.50320 በ19/11/2005 ዓ/ም. በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ.202 (2) መሰረት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ፍ/ቤት እንድቀርብ ባስመዘገብኩት አድራሻ የተላከ መጥሪያ የሌለ ከመሆኑም በተጨማሪ ለዋሴም በተመሳሳይ የደረሰ ነገር የለም በማለት በሌሉበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ላማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑ አለመሆኑ ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህ መሠረት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ያየው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ስልጣኑ ሲሆን ጉዳዩ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠውም በተደጋጋሚ በፓሊስ ተፈልገው አልተገኙም፣ በጋዜጣም ተጠርተው አልቀረቡም በማለት ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩላቸው በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳልኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩት መጥሪያው በምርመራ ጊዜ ቃሌን ስሰጥ በገለጽኩት እና በዚሁ መሠረት ተጠሪው በክስ ማመልከቻው ላይ በገለፀው መደበኛ መኖሪያ አድራሻዬ አልደረሰኝም፣ ተከሳሽን ማግኘት አልቻልኩም በማለት ለፍ/ቤቱ የገለፀው ከመደበኛ መኖሪያ ቦታዬ ውጪ የሚገኝ የሌላ ወረዳ ፓሊስ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ አንድ ከሳሽ በሌለበት የተሰጠበት ውሳኔ እንዲነሳለት የሚያቀርበውን ማመልከቻ ለመቀበል ከሚቻልባቸው ምክንያቶች አንዱ መጥሪያ ለተከሳሹ ያልደረሰው የመሆኑ ጉዳይ ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 199/ሀ/ ስር የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ለአመልካች መጥሪያው የተላከው የአመልካቹ መደበኛ መኖሪያ አድራሻ በሆነው ውቅሮ ወረዳ ፓሊስ በኩል ሳይሆን ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለበት ወረዳ በሚገኘው እና ምርመራውን አጣርቷል በተባለው አጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ በኩል ስለመሆኑ በክርክሩ ተረጋግጧል፡፡

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ተከሳሹን በጋዜጣ ሊያስጠራ የቻለው እና ቀጥሎም ጉዳዩን አመልካች በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ የሰጠው የአጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ ቁጥር 1008/8/34 በ07/09/2004 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ተከሳሹ ከአካባቢያችን ውጪ ስለሆነ እና ዋሱም ተነግሮት ላቀርበው አልችልም ስላለ ልናቀርበው አንችልም ሲል በሰጠው ምላሽ ሳቢያ ስለመሆኑ አመልካች ከስር ጀምሮ እየተከራከሩ ሲሆን መጥሪያው በአመልካቹ የተመዘገበ የመኖሪያ አድራሻ ተልኮ የነበረ ስለመሆኑ ወይም አመልካቹ ከዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ያልቻሉ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ የማያመለክት ከመሆኑም በላይ የአጽቢ ወንበርታ ወረዳ ፓሊስ በቁጥር 1008/8/34 በ07/09/2004 ዓ.ም የተሰጠውን ምላሽ አስመልክቶ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላቀረቡት ክርክር ተጠሪው ያቀረበው ግልፅ ማስተባበያ አለመኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በመሰረቱ ባስመዘገቡት አድራሻ መጥሪያው ለአመልካቹ የተላከ መሆኑ ወይም አመልካቹ በዚህ አድራሻቸው ተፈልገው ያልተገኙ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወደ ጋዜጣ ጥሪ አማራጭ የሚኬድበት አግባብ ስለማይኖር የጥሪ ማስታወቂያው በጋዜጣ መነገሩ ብቻውን መጥሪያው ለአመልካች በአግባቡ እንዲደርስ ተደርጓል ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ዋሱ ተከሳሹን ላቀርበው አልችልም ብለዋል መባሉም ኃላፊነት ሊያስከትል የሚችለው በዋሱ ላይ እንጂ በተከሳሹ ላይ አይደለም፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸው ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት እንዳላቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 20(4) ተደንግጎ የሚገኝ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ይህንን

ሕገ መንግስታዊ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ክስ የቀረበባቸው መሆኑን በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 123 በተመለከተው መሰረት በሚላክ መጥሪያ እንዲያውቁት ሲደረግ ነው፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ሆኖ እያለ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሌሉበት ታይቶ የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 50320 በ19/11/2005 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሌሉበት ታይቶ የጥፋተኝነት እና የአስር ዓመት ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠባቸው መጥሪያው ባስመዘገቡት የመኖሪያ አድራሻ እንዲደርሳቸው ሳይደረግ ወይም በዚሁ አድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ አለመቻላቸው ሳይረጋገጥ በመሆኑ እና ይህም በሌሉበት የተሰጠባቸውን ውሳኔ ለማንሳት በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 199(ሀ) ድንጋጌ መሰረት በቂ ምክንያት በመሆኑ ውሳኔው ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንደገና እንዲታይ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 202(1) በተደነገገው መሰረት ቀድሞ ጉዳዩን ያዩት ዳኞች በማይሰየሙበት ችሎት አመልካች ባሉበት ጉዳዩን እንደገና በማየት በስነ ስርዓት ሕጉ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ተገቢውን ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈፀም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እንዲሁም በሚገኙበት የመቀሌ ከተማ ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
5. ውሳኔው የተሰጠው በአብላጫ ድምጽ ነው፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተጠቀሰው ዳኞች በአብላጫ ድምጽ በተሰጠው ፍርድ ሰላልተስማማን የልዩነት ሀሳባችን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

በመሰረቱ ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል ሰርቆት ወንጀል ያጣራው የአፅቢ ወረዳ ፖሊስ ሳይሆን የትግራይ ብ/ክ/መ/ፖሊስ ኮሚሽን ስለመሆኑ የክልል ጠ/ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡እንዲሁም የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት አመልካችን የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን እንዲያቀርበው በተደጋጋሚ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ፖሊስ ከአድራሻው ፈልጎ ማጣቱን እና ማቅረብ አለመቻሉን ገልጾ ምላሽ የሰጠው የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን እንጂ የወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት አለመሆኑን የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የሠጠውና ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የትዕዛዙ ግልባጭ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት ለሰጠው ትዕዛዝ መነሻ ያደረገው አመልካች በሰበር አቤቱታው እንደገለጸው በወረዳ ፖሊስ የተሠጠውን ምላሽ ሳይሆን ከክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የተሰጠውን ምላሽ መሆኑን ነው፡፡የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ደግሞ አመልካችን ከአድራሻው ፈልጎ ማጣቱንና በዚህም ምክንያት ማቅረብ አለመቻሉን አረጋግጦ እስከገለጸ ድረስ ለአመልካች መጥሪያው በአድራሻው እንዲደርሰው ተገቢው ጥረት አልተደረገም ለማለት የሚቻል አይሆንም ፡፡

በአድራሻው ተፈልጎ ማግኘት ካልተቻለ ደግሞ የሚኖረው አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 162(1) ሥር እንደተመለከተው የጥሪ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ማድረግ ሲሆን በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት አመልካች ሊቀርብ አልቻለም፡፡እንዲሁም ዋሱም ተጠይቆ አመልካች በአድራሻው እንደሌለ እና ማቅረብ እንደማይችል ገልጿል፡፡ እነዚህም ጠቅላላ ሁኔታዎች አንድ ላይ ሲታዩም አመልካች በራሱ ምክንያት ፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር አለመፈለጉን መደምደም ከሚቻል በስተቀር ከመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት አንጻር የተፈጸመ ጉድለት የለም፡፡ በአጠቃላይ መጥሪያው በአድራሻ እንዲደርሰው ተገቢው ጥረት ተደርጎ ከታጣ በኋላ በጋዜጣም ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ የተነሳ ጉዳዩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ መጥሪያው በአድራሻው እንዲደርሰው አልተደረገም በሚል ምክንያት እንዲነሳ ማድረግ በክልሉ ጠ/ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ አብላጫው ድምጽ መጥሪያው በአግባብ ለአመልካች እንዳልደረሰው ቆጥሮ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ባለማግኘታችን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 94404

መጋቢት 09 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** የደቡብ ብሔር በሔረሰቦች ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል አቃቤ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ መኩሪያ ቡሎ - የቀረበ የለም

***መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ የእስር ቅጣት አፈፃፀሙ የሚገደብበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በ1996 ዓ/ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1) እና 540 ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ከሌላ ካልተያዘው ግብረ አበር ጋር በመሆን አቶ ላልሞ ላግዴ የተባለውን የግል ተበዳይ በክላሽ መሳሪያ አራት ጥይት ተኩሶ ስቷል፤ ከተሰወረ በኋላም ተይዟል በማለት ዘርዝሮ የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል የሚል ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ክደው ተከራክረው አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቶ ክሱን ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ ተጠሪ ክሱን እንዲከላከሉ መብታቸውን ተጠብቆላቸው የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አቅርበው አሰምተዋል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን መርምሮ ተጠሪ የአመልካችን ማስረጃዎች በመከላከያ ማስረጃዎቹ አላስተባበሉም በማለት ተጠሪን ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መመልከቱን ከጠቀሰ በኋላ በሶስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ሆኖም የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙን በተመለከተ ተጠሪ ታማሚ መሆናቸውን ሐኪም አረጋግጧል፤ በግል ተበዳይም የደረሰ ጉዳት የለም በሚል ምክንያት በሁለት አመት ገደብ እንዲሆን ወስኗል፡፡ በዚህ የእስራት ቅጣት እንዲገደብ ተብሎ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ

ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከሩ በኋላ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 34280 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ እንዲገደብ የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተጠሪ ላይ የተጣለው የሶስት አመት ፅኑ እስራት ቅጣት የተገደበው ሕጉ የሚጠይቃቸው መስፈርቶች ሳይሟሉና አግባብነት የሌለው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተጠቅሶ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ከድርጊቱ አፈፃፀም እና ተጠሪ የግል ተበዳይን ይቅርታን ያልጠየቁ፣ ካሳም ያልከፈሉ ከመሆናቸው አንጻር ሲታይ የእስራት ቅጣቱ መገደቡ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ድንጋጌ አንፃር ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት መልስ ድርጊቱን ያልፈፀሙ መሆኑን፣ ይግባኝ ያልጠየቁበት ምክንያትም በአቅመ ደካማነታቸው የተነሳ መሆኑንና የእስራት ቅጣቱ የተገደበው ባለባቸው በሽታ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ ነው በማለት ዘርዝረው ውሳኔው እንዲጸናላቸው ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በተከሳሽ ላይ የተወሰነ የቅጣት ውሳኔ ከመገደቡ ወይም የገደብ ውሳኔው ከመሻሩ በፊት የቅጣት ገደብ ስለሚከለከልበትና ስለሚሻርበት ሁኔታ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 እና 197 ስር የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ በተወሰነ ገደብ ቅጣትን ማቆም የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ከአንቀጽ 190 እስከ 200 ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡ የወንጀል ሕጉአንቀጽ 190 ሲታይም ከእስር በገደብ መለቀቅ ማለት ፍርድ ቤት አንድ ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታ የሚደረግበት አግባብ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሳሽ የቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የማይችሉባቸው ሁኔታዎችም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡በሌላ አገላለፅ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔውን በገደብ የሚያስቀመው የተለያዩ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን እነዚህም፡- ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት

እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፣ ጥፋቱ በመቀጮ፣ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኋላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ያመነበት እንደሆነ አስተያየት ከሰጠ በኋላ ቅጣት ሳይወስን የተወሰነ የፈተና ጊዜ ሊሰጠው የሚችልበት አግባብ መኖሩን ሕጉ ያሳያል፡፡ እንዲሁም ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ እንደሚችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192 ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን የገደብ አሰጣጥ ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ ግን ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ በማየት የተሟሉ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ የገደብ ውሳኔ ካልተሰጠ የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የማይቻል መሆኑ ይታመናል፡፡

የወንጀል ሕጉ በአንቀጽ 196 ስር እንደአስቀመጠው ፍርድ ቤቱ ለጥፋተኛው የሚሰጠውን የፈተና ጊዜ የሚወሰነው የወንጀሉን ከባድነት፣ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳትና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለውን እምነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ የተከሳሹን የገደብ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ከመቀበሉ በፊትም ተከሳሹ ቀድሞ የነበረውን ጠባይ ፣ የአኗኗርና የስራውን ሁኔታ ምን አይነት እንደነበር ፍርድ ቤቱ መረጃ መሰብሰብ እንደሚችልም ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197/1/ ሲታይም ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ እንዳይፈፀም ለማድረግ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች አስቀምጦ እናገኛለን፡፡ እነዚህም ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በመልካም ጠባይ እንደሚመራ ካመነ፣ ጥፋተኛው እንዲፈፀም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ካረጋገጠ ፣ ጥፋተኛው በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ስለመሆናቸው ሕጉ በግልጽ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ለገባበት ግዴታ አፈፃፀም መተማመኛ ዋስትና እዲያቀርብ እንደሚያደርግ ተጠቃሹ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስፍሮ ይገኛል፡፡

እንግዲህ ህግ አውጭው አንድ ሰው በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣት ሳይጣል ጥፋተኛ ነህ በማለት ብቻ ሊታለፍ የሚችልበትን እንዲሁም ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ቅጣቱ ከተጣለ በኋላ ደግሞ የእስራት ቅጣቱ ሳይፈፀም ተገድቦ የሚቆይበትን አግባብ በግልፅ የዘረጋ መሆኑን ከአንቀፅ 190 እስከ 200 ድረስ ያሉትን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን በማየት የምንረዳው ጉዳይ

ሲሆን አንድን ጥፋተኛ በተወሰነ ገደብ ከእስር ለመፍታት ግን በህጉ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የገደብ ውሳኔው በዘፈቀደ የሚሰጥ ሳይሆን ህጋዊ ሁኔታዎች መሟላታቸው በሚገባ ተረጋግጦ የሚሰጥ ነው፡፡ በህግ ተለይተው የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ደግሞ የዳኝነት አካሄድ የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሰር ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ የጣለውን የሶስት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት በሁለት አመት የገደበው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን መርምሮ ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ አያሣይም፡፡ ይልቁንም ፍርድ ቤቱ አጽንኦት የሰጠው የተጠሪን በሽተኛ መሆን በሐኪም መረጋገጡንና በግል ተበዳይ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመኖሩ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ተጠሪ መልካም ጠባይ እንደሚመራ ስለማመኑ፣ ተጠሪ እንዲፈጽም የተሰጠውን ግዴታ እንደሚቀበል ማረጋገጡን፣ ተጠሪ በሚቻለው መንገድ ሁሉ በጥፋቱ የደረሰውን ጉዳት እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍልና ለዚሁ ጉዳይ በተወሰነ ጊዜ ውሰጥ የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ስለመስጠቱ በቅጣት ፍርድ ላይ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 አግባብ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ የተጠሪ በሽተኛ መሆን ደግሞ ሕጉ ከአስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ በግልጽ ያልተጠቀሰ ሲሆን በግል ተበዳይ ላይ የደረሰ ጉዳት ያለመኖሩም ድርጊቱ ሙከራ ሁኖ አራት ጥይት ተተኩሶ የተሣተ እንደመሆኑ መጠን ለገደብ ውሣኔው የግድ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ምክንያት አይደለም፡፡ ተጠሪ ከግል ተበዳይ ጋር ይቅርታ ማውረዳቸውም ያልተረጋገጠ ሲሆን ይልቁንም እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገው ክርክር ስለአጥፊነታቸው አምነው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህም ተጠሪ የተጣለባቸው ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶላቸው አመላቸው ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግ የሚታገዱ ናቸው ብሎ ለመደምደም የማይቻል መሆኑን በግልጽ የሚያሣይ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ለማጽናት መሠረት የደረገው የዚህ ችሎት አስገዳጅ ትርጉም ሲታይም ከዚህ ጉዳይ በመሠረታዊ ነጥቦቹ ተመሣሣይነት የሌለው ነው፡፡ በሰ/መ/ቁ. 34280 የተሰጠው የሕግ ትርጉም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በገደብ አወሣሰን በሕጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች ባገናዘበ መልኩ ዳኝነት መስጠቱን የሰበር ሰሚ ችሎቱ በማረጋገጥ የሰጠው ከመሆኑ ውጪ በሕጉ የተመለከቱትን መሰፈርቶችን ሣይከተል የተሰጠ ውሣኔን የተቀበለ ባለመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች በተጠሪ ላይ የተጣለው የሶስት አመት ጽኑ እስራት በሁለት አመት የታገደው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ስር የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሣይሟሉ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቅጣት ገደብ የውሣኔ ክፍል ሕጉን ያልተከተለ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና የሰበር ችሎትም ይህንኑ የዞኑን

ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሣኔ ክፍል ማረም ሲገባቸው ማለፋቸውና ውሣኔውን ሙሉ በሙሉ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28009 መጋቢት 27 ቀን 2005 በተጠሪ ላይ የተወሰነው የሶስት አመት ጽኑ እስራት ቅጣት ውሣኔ ሊገደብ ይገባል ተብሎ ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59288 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁጥር 59939 ነሐሴ 23 ቀን 2005 ዓ.ም የፀናው የውሣኔ ክፍል ብቻ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195/2/መ/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ለፍርድ ቤቶቹ የውሣኔው ግልባጭ ይድረሣቸው ብለናል፡፡
2. በዚህ በኩል የእስራት ቅጣት ውሣኔው አፈፃፀም እንዲገደብ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ተጠሪ የሶስት አመት ጽኑ እስራት መፈጸም ያለባቸው በማረሚያ ቤት ነው ብለናል፡፡ የክፍሉ ፖሊስ ተጠሪን ይዞ ለሀዋሣ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ፣ የሀዋሣ ማረሚያ ቤትም ከክፍሉ ፖሊስ ተጠሪን ተረክቦ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ቀድሞ የታሰሩትን ጊዜ ታሣቢ በማድረግ የሶስት አመት ጽኑ እስራት ቅጣትን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 95438

ግንቦት 07 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሰለሞን ደሣለኝ ጠበቃ ግደይ ገድሉ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ክልል ዐ/ህግ አልቀረበም፡፡

**መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በቼክ የማጭበርበር ወንጀልን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በሀዋሳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰበር ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ወንጀል ክስ መነሻነት ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ በ3 መዝገቦች ያቀረበባቸው ክሶች ዝርዝር፤-

1. አመልካች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ወንጀል ህግ ቁ. 693(1) በመተላለፍ በ29/02/04 ዓ.ም ከጧቱ 4.00 ሰዓት ለግል ተበዳይ ጥላሁን ሰይድ የብር 12,786 ስንቅ የሌለው ቼክ ስለሰጠ፡
2. በቀን 5/03/2004 ዓ.ም ከቀኑ 5.00 ሰዓት ላይም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመተላለፍ ለግል ተበዳይ ጌቱ ተዋታን የብር 20,000 ስንቅ የሌለው ቼክ ስለሰጠና፡-
3. እንዲሁም አሁንም ተመሳሳይ የወንጀል ህጉን ድንጋጌ በመተላለፍ ለግል ተበዳይ ግርማ ፈንዲጋን እንደ ቅደም ተከተላቸው በቀን 30/02/2004 ዓ.ም እና በቀን 25/03/2004ዓ.ም የብር 20,624 እና 17,328 ስንቅ የሌላቸው ቼኮች ወይም የሚያዝበት ገንዘብ የሌለው መሆኑን እያወቀ ቼክ ስለሰጠ በቼክ የማጭበርበር ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ፍ/ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳ ከተደረገበኋላ ከክሱ ላይ የሚያቀርበው መቃወሚያ እንደሌለው ገለፆ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኗል፡፡ሆኖም ግን ድርጊቱን የፈፀምኩት የግል ተበዳዮቹን ለማጭበርበር አስቤ ሳይሆን ጨረታ አሸንፌ ስለነበር ገንዘብ ከመንግስት እስኪለቀቅልኝ ድረስ ቼኩን በዋስትና ይዘው ገንዘቡ ሲለቀቅ እንዲወስዱ ተብሎ ነበር በማለት የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል፡፡በመቀጠልም ፍ/ቤቱ የዐ/ህግን የሰነድና የሰው ምስክሮችን አድምጦ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ወንጀሉን እንዲከላከል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን

አመልካች የበኩሉን መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ወንጀሉን ባለመከላከሉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በሦስቱም ወንጀሎች ስር አመልካችን ጥፋተኛ ካደረገበኋላ ቅጣትን በተመለከተም ለእያንዳንዱ ወንጀል አመልካች በ5 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ ቅጣቶቹም በማረሚያ ቤት በኩል ተጀምረው እንዲፈጸሙ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ እና ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች አስቀርቦ በጉዳዩ ላይ እንዲከራከሩ ካደረጋ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍ/ቤቱን የጥፋተኝነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ካፀና በኋላ ቅጣትን በተመለከተ ግን በ2002 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሠረት በማድረግ ሦስቱም ወንጀሎች በተመሳሳይ በደረጃ 5፤የእስራት ቅጣት መነሻም እርከን 14 ስር ለእያንዳንዱ ወንጀል 2 ዓመት ከ6 ወር መነሻ ቅጣት ወስኖና እነዚህንም በአንድነት በመደመር ለሦስቱም ተደራራቢ ወንጀሎች 7 ዓመት ከ6 ወር የእስራት ቅጣት ወስኗል፡፡በመቀጠልም የቅጣት ማክበጃ አስተያየትን በተመለከተ ቅጣቱ እንዲከብድ ተብሎ በዓ/ህግ በኩል የቀረበ አስተያየት የለም በማለት ካለፈ በኋላ የቅጣትማቅለያን ምክንያትን በተመለከተ ደግሞ የቀረበው አስተያየት በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው አልፎ በመነሻ ቅጣቱ 7 ዓመት ከ6 ወር እስራት እንዲቀጣ ሲል በበታች ፍ/ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ወሰኗል ይህ ውሳኔም በክልሉ ሰበር ችሎትም መሠረታዊ የህግ ስህተት የለውም ተብሎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

አሁን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጡት ውሳኔዎች ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታልና ስህተቱ ይታረምልኝ የሚል ሲሆን አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰው የጉዳት መጠን እና በስር ፍ/ቤት የተወሰነው ቅጣት ተመጣጣኝነት፤እንዲሁም በአመልካች የቀረቡት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የመታለፋቸውን አግባብነት ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ 2/2006 አኳያ ለመመርምር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ዐ/ህግም ቀርቦ የበኩሉን መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዐ/ህግ በኩል የቀረበው መልስ ይዘትም ፤- በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሻሽሎ የተወሰነውና በክልሉ ሰበር ችሎትም ተቀባይነት አግኝቶ በትዕዛዝ እንዲፀና የተደረገው የቅጣት ውሳኔ ተገቢ እና የሚነቀፍ ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጐ እንዲወሰንለት ጠቅሶ መከራከሩን የሚያሳይ ሲሆን አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመ/መልሱን ሰጥቶበታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ሲደረግ ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አንፃር በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ብቻ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሠረቱ የቅጣት አወሳሰንን በተመለከተ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነት እና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥም ሆነ ስለመቆጣጠር እንዲቻል የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) ማውጣት ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 88(4) ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በዚህ መሠረት ከዚህ ቀደም የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.1/2002 አውጥቶ ከግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራበት የነበረ ስለመሆኑ ይታወቃል፡፡ሆኖም ግን በኂላ ላይ ይህን መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 በምትኩ ወጥቶ ከ1/2/2006ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ መዋሉም የሚታወቅ ነው፡፡ቅጣትን በሚመለከት ደግሞ አዲሱ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ወንጀል ከተፈረደበት እና ሆኖም ግን ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው ወንጀል ህግ ይልቅ አዲሱ ህግ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቀልለትና ተከሳሹን የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በአዲሱ ህግ ላይ ያለው ቅጣት የሚፈጽምበት ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ ቁ. 6 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም ምንም እንኳ አመልካች እነኝህን ወንጀሎች የፈጸመው የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 ዓ.ም ከመውጣቱ በፊት ቢሆንም ይህ ጉዳይ በዚህ ሰበር ችሎት ታይቶ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ከበፊቱ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 1/2002 ይልቅ በኂላ ተሻሽሎ ወጥቶ በአሁኑ ጊዜ ተፈፃሚነት ያለው የተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006 አመልካች የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ይሄው በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው ስለሚገባ በዚሁ መሠረት በአመልካች ላይ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ተመርምሯል፡፡

አመልካች በሦስቱም ቼኮች የሚያዝበትን ገንዘብ ከባንክ ሳይኖረው የተለያዩ ቼኮችን በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ ሦስት ግለሰቦች አውጥቶ ሰጥቷል ተብሎ ጥፋተኛ የተባለው የቼኮቹ ገንዘብ መጠን እንደቅደም ተከተላቸው ብር 12,786፤20,000 እና ብር 37,972 የያዙ ስለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ በግልፅ ያስረዳሉ፡፡ይህም በተሻሻለው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ መሠረት የእያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን እንደቅደም ተከተላቸው በ1ኛ ና 2ኛ ተደራራቢ ወንጀሎች የተገለፀው የገንዘብ መጠን በደረጃ 3 እና የእስራት መነሻ ቅጣቱም በእርከን 9 ስር የሚወድቁ ሲሆን በ3ኛ ተደራቢ ወንጀል የተገለጸው የገንዘብ መጠን ደግሞ በደረጃ 4 እና እርከን 11 ስር የሚወድቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመመሪያው አንቀጽ 22(1)(ሀ) መሠረት ደግሞ ለእያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ለብቻቸው ሊወሰን የሚገባው መነሻ ቅጣትም እንደቅደም ተከተላቸው 1 ዓመት ከ6ወር፤1 ዓመት ከ6 ወር እና 2 ዓመት እስራት ሆኖ ተወስኗል፡፡እነዚህ መነሻ የእስራት ቅጣቶችም በአንድ ላይ ሲደመር 5 ዓመት ሲሆን ይህም ከፍ ሲል በተገለፀው ተመሳሳይ የመመሪያው ድንጋጌ መሠረት በእርከን 20 ስር ይወድቃል፡፡

በሌላ በኩል የቅጣት ማክበጃ ምክንያትን በተመለከተ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ በዐ/ህግ አስተያየት አልቀረበም በሚል ምክንያት ሰላለፈ እና በዚህ ነጥብ ላይም በዐ/ህግ በኩል የቀረበ ቅሬታ ባለመኖሩ በዚሁ የሚታለፍ ይሆናል፡፡ የቅጣት ማቅለያን በተመለከተ ግን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው ያለፈው የቀረበው ምክንያት በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይሁን እንጂ አመልካች ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆኑትን ተደራራቢ ወንጀሎች ከመፈጸሙ በፊት የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበበት እና የዘወትር ፀባዩም መልካም ስለመሆኑና እንዲሁም ይሄንን ወንጀል ከፈፀመም በኂላ በመፀፀት ለግል ተበዳይ ገንዘብ መክፈል የጀመረ ስለመሆኑ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡እነዚህ በበታች ፍ/ቤት የተረጋገጡት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 82(1)(ሀ)፣5(ሠ) እንዲሁም በመመሪያው አንቀጽ 23 መሠረት መነሻ የቅጣት እርከኑን ከእርከን 20 ወደ እርከን 18 እንዲቀል ያደርጋሉ፡፡ በመመሪያው መሠረት የእርከን 18 መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ከ7 ወር ሲሆን መድረሻው ደግሞ 4 ዓመት ከ4 ወር በመሆኑ በዚሁ ፍቅደስልጣን ውስጥ ደግሞ የወንጀል አፈፃፀሙ ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ እንዲታይ ከተደረገ በኂላ አመልካች በ4 ዓመት እስራት ቅጣት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሲጠቃለልም የአመልካች ቅጣት ውሳኔ ሊመረመር የሚገባው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ወንጀል ህግ አንቀጽ 6 ስር እንደተመለከተው በ2006 ዓ.ም ከጥቅምት ወር ጀምሮ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት መሆን ስላለበት በዚህ መሠረት በስር ፍ/ቤቶች በአመልካች የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ብቻ አሻሽለን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ጉዳይ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 57677 በ07/09/05 ዓ.ም ተወስኖ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 58576 በ23/12/05 ዓ/ም በትዕዛዝ እንዲፀና የተደረገው የ7 ዓመት ከ6 ወር እስራት ወደ 4 ዓመት እስራት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ)(2) መሠረት ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
3. የቅጣት ውሳኔውም መሻሻሉ ታውቆ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶችና ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት የውሳኔ ግልባጭ እና ትዕዛዝ ይተላለፍ መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ 96954

ሚያዚያ 24 ቀን 2006 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ዘፈሩ ወልደ ትንሣኤ አብርሃ ጠበቃ ሽፈራው በላይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል ዐቃቤ ህግ አልቀረበም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል መፈጸም ጥፋተኛ በሆነ ሰው ላይ የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ህጋዊነት የሚመለከት ነው ከሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከሳሽ ተከሳሹ በወንጀል ህግ አንቀጽ543 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ የሰው ህይወት ጤናና ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ ያለበት ሆኖ እያለ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት 25/01/2006 ዓ.ም ከምሽቱ አራት ሠዓት በየካ/ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 ለም ሆቴል ፊት ለፊት አልኮል ጠጥቶ ሲያሽከረክር ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል ሲያሽከረክር ከፊት በነበረው የሰሌዳ ቁጥር 2-42769 ለጊዜው ማንነቱ ያልታወቀው ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት በመሆኑ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

ተከሳሽ የወንጀሉን ድርጊት ፈጽሜአለሁ ጥፋተኛ ነኝ፡፡ ሆኖም በወቅቱ መጠጥ አልጠጣሁም ነበር ሟችን የገጨሁት በላዳ መኪና ተከልሎ መንገድ ሲያቋርጥ ነው፡፡ ከዚያም ሟችን ወደ ሆስፒታል ወስጄው ነበር ሊተርፍ አልቻለም በማለት ተከራክሯል ፡፡ ዐቃቤ ህግ መጠጥ የመጠጣቱ ጉዳይ ወሳኝ ነጥብ አይደለም ፡፡ በእምነቱ መሠረት ፍርድ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል ፡፡ ፍርድ ቤቱ አመልካች /ተከሳሽ/ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 (2) የተመለከተውን በመተላላፍ ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ብሎ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ተከሳሽ አልኮል ጠጥቶ ሲያሽከረክር አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል ዕውቀት ያለው በመሆኑ የሞት አደጋውን ያደረሰው በታወቀ ቸልተኝነት ነው ብሎ በመደምደም በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በሁለት ዓመት ከስድስት ወር እስራትና ብር 3000 መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል ውሳኔውን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አጽንቶታል። አመልካች ጥር 19 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ እኔ አደጋው በደረሰበት ጊዜ አልኮል መጠጥ የጠጣሁ መሆኑን በማመን የስጠሁት የእምነት ቃል የለም። ዐቃቤ ህግም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም።ዐቃቤ ህጉ በዕምነት ቃሉ መሠረት ጥፋተኛ ይባልልኝ ብሏል ። ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት በክርክሩ ሂደት ያልታመነ ወይም በማስረጃ ያልተረጋገጠ ጉዳይ (አልኮል ጠጥቶ ያሽከረከረ ስለነበረ)በማለት ቸልተኝነቱ የሚታወቅ ቸልተኝነት ነው በማለት ያወጣው ደረጃና የሠጠው የቅጣት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል። ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል የሞት አደጋ ያደረሰ በመሆኑ የቅጣት ውሳኔው የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል ።

ከሥር የክርክር አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የቅጣት ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሻሽሎ ያወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ከምሽት አራት ሰዓት ሚች በላዳ መኪና ተከልሎ መንገድ ለማቋረጥ ሲሞክር የገጨው መሆኑን አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ከሰጠው የእምነት ቃል ይዘት ተረድተናል።አመልካች በወቅቱ የአልኮል መጠጥ ያልጠጣ መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት በግልጽ አስመዝግቧል።ተጠሪም አመልካች የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ አላሽከረከረኩም በማለት የሰጠውን ቃል በመቀበል ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልገኝ በእምነት ቃሉ መሠረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት እንዳሳሰበ ለመረዳት ችለናል፤ይህም አመልካች በዕምነት ቃሉ ያረጋገጠውን ወይም ዐቃቤ ህግ በማሰረጃ ያላስረዳውን ፍሬ ጉዳይ ማለትም አመልካች ሚችን ገጭቶ የሞት አደጋ ያደረሰበት የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ ሲያሽከረክር ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት በቅጣት ውሳኔው መግለጹ በዚህ ምክንያት ቸልተኛነቱም በግልጽ የታወቀ ቸልተኝነት በማለት መፈረጁ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 134(1) ድንጋጌ የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።

የአመልካች የወንጀል አድራጊነት የፈጸመው በወንጀልሕጉ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ (1)ሀ በተመለከተው ሁኔታ አይደለም። አመልካች በቸልተኝነት የሞት አደጋውን ያደረሰው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተው ሁኔታ መሆኑን ለጥፋተኝነት ውሳኔው መሠረት የሆነው አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የእምነት ቃል ያሳያል ። አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ የሚቀጣው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 134(1) መሠረት በሰጠው የእምነት ቃል

መሰረት ከሆነ የበታች ፍርድ ቤቶችአመልካች ከሰጠው የእምነት ቃል ውስጥ አመልካቹን የሚጠቅመውን ክፍል በመተው፤በአመልካች በዕምነት ቃሉ ያላስመዘገበውና ቅጣት የሚያከብድበትን ሁኔታ በቅጣት ውሳኔው በማስፈሩ ቅጣቱን መወሰናቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሻሽሎ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 134 (1) ድንጋጌ ይዘትና መሰረታዊ አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ነው፡፡ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው በወንጀል ህግ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተመለከተ ሁኔታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የአመልካች ቸልተኛነት የሚችአስተዋጾ በሌለበትና ባልታወቀ ቸልተኛነት የተፈጸመና በእስራት መቀጮ እርከን 8 በገንዘብ መቀጮ እርከን 4 ላይ የሚወድቅ ነው፡፡ ይህም ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ከስምንት ወር ባለው የቅጣት ሬንጅ ውስጥ የሚያስቀጣ ነው፡፡ በመቀጮም እስከ ብር 5000 የሚያስቀጣ ነው፡፡ አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል ፡፡ ይህም ሁለት እርከን ለመቀነስ የሚያስችል ነው፡፡ስለሆነም ነፃነትን በሚያሳጣ ቅጣት እርከን ስድስት ሥር እና ገንዘብ መቀጮን በሚያስቀምጠው እርከን ሁለት ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ወንጀል ውስጥ በተሰጠው እርከን ሁለት ሥር የሚወድቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሬንጅ ውስጥ በተሰጠው ፍቅደ ሥልጣን መሠረት አመልካች በአንድ ዓመት እስራትና በብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማፅናት የቅጣት ውሳኔውን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ(2))መሠረት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥተናል ፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 125698 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45874 የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ በማፅናት የቅጣት ውሳኔውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘችበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት እስራትና በብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር ) መቀጮ እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥተናል ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት የቅጣት ውሳኔው የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ፡፡

***መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 96078

መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- ረዳት ሳጂን አህመድ ለገሰ ---ጠበቃ አድምጠው በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ --- ዐ/ህግ መኩሪያ አለሙ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ ክሱም በስር ፍርድ ቤት በስድስት ምድብ ተከፍሎ የቀረበ ሆኖ አመልካች ጥፋተኛ የተባለው በአምስት ክሶች ነው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለባቸው ክሶችም እንደሚከተለው በአጭሩ የተገለጹ ናቸው፡፡

የ1ኛው ክስ አመልካች በ1996 ዓ.ም. የወጣውን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)እና 598(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያን ዜጎችን ወደ ውጪ ለመላክ የሚያስችል ምንም አይነት ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/06/07 ክልል ልዩ ቦታው ቂርቆስ ቴሌ አካባቢ ሚያዝያ 08 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ራቂያ አደም የተባለችውን ከሰሜን ጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ በማድረግ አመልካች በተከራየው ቤት ውስጥ ለሁለት ሳምንታት እንድትቀመጥ በማድረግ ወደ አረብ አገር እልክሻለሁ ብሎ ህክምና እንድትወስድ ከተደረገ በኋላ ከአመልካች ጋር በስር ፍርድ ቤት ተከሶ የነበረው 2ኛ ተከሳሽ የሕክምና ውጤቷን ፓስፖርትና የአሻራ ውጤት በመውሰድ ይኼው ተከሳሽ ቪዛውና የአየር ቲኬት በማምጣት ለመሄድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ብር 800.00 ለአሁኑ አመልካች ሰጥታ ለመሄድ በመዘጋጀት ላይ ሳለች ሚያዚያ 11 ቀን 2005 ዓ.ም በደረሰ ጥቆማ ሳትሄድ የቀረች በመሆኗ ተከሳሾች ወንጀል ለማድረግ ጀምረው የወንጀሉ ድርጊት እስከ መጨረሻው ለመከታተል ያልቻሉ በመሆናቸውና በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጲያዊን ለስራ ወደ ውጪ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ 2ኛው ክስ ደግሞ አመልካቹ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27(1)እና

598(1)ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ቀኑ በውል ባልታወቀበት መጋቢት ወር 2005 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 አካባቢ የግል ተበዳይ ናስራ መሐመድ ከትግራይ ክልል በማምጣት ወደ ውጪ አገር ለመሄድ እንደምትፈልግ ስትገልጽለት እኔ እልክሻለሁ በማለት በተከራየበት ቤት ውስጥ አንድ ወር ከአንድ ሳምንት አስቀምጧት የሜዲካል ውጤቷን ወስዶ ወደ ኦማን ነው የምትሄጂው ሲላት ወደዚያ አልሄድም ስትለዉ ቪዛው ለኦማን ነው የተሰራው በማለት የከለከላት እና ወደ ኦማን ለመሄድ በዝግጅት ላይ እንዳለች የአየር ትኬት ሲመጣ ብር 1000.00 እስከ 1500.00 እንድትከፈል በመግለጽ በመጠባበቅ ላይ እንዳለች በደረሰው ጥቆማ መሠረት ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ በመሆኑ አመልካቹ በፈጸመው በሕገ ወጥ መንገድ የኢትዮጵያዊያንን ለስራ ወደ ውጪ አገር መላክ ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ ሌላው አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት 4ኛ ክስ ሲሆን የክሱ ይዘት ሲታይም፡- በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ መጋቢት 28 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ እሸቱ ቱፋን ከሳውዲ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ በምትገባበት ወቅት አመልካቹ ወደ ተከራየበት ቤት በመውሰድና ከዚያም ወደ ሆስፒታል በመውሰድ እንድትመረመር ካደረገ በኋላ ኩዌት ላከኝ ስትለው ሕክምና ያደረግሽው ለሳውዲ አረቢያ ስለሆነ ኦማን ነው የምልክሽ በማለት ፓስፖርት እና ሜዲካል ውጤቱን ከተቀበላት በኋላ ሞገስ ለተባለው ግለሰብ በመስጠት ይህ ግለሰብም ከዚያው ስለመጣ ውል እንዋዋል ብሏት ውል ለመዋዋል ለመሄድ በዝግጅት ላይ ሳለ ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የተቋረጠ መሆኑን ጠቅሶ አመልካቹ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 27(1) 598/1 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፏል የሚል ነው፡፡ ሌላው አመልካች ተከሶ ጥፋተኛ የተባለበት ክስ ደግሞ በ5ኛ ምድብ የተጠቀሰው ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቹ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 27(1)እና 598(1) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ሚያዝያ 11 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ሕይወት ተስፋን ከሰሜን ጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ በማድረግ ወደ ውጪ ለስራ እልክልሻለሁ በማለት የአሻራና የህክምና ምርመራ እንድታደርግ አድርጎ፣ የአሻራ ውጤት፣የህክምና ውጤት እንዲሁም ፓስፖርት በመቀበል ወደ ውጪ እልክሻለሁ፣ ስትሄጂ ብር 1500.00 ትከፍያለሽ በማለት ለመሄድ በመጠባበቅ ላይ ሳለች ለፖሊስ በደረሰው ጥቆማ መሠረት ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ መሆኑን ተጠቅሶ አመልካቹ በሕገ ወጥ መንገድ ኢትዮጵያዊያን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሙከራ ወንጀል መፈፀሙን የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው ክስ በምድብ 6 ስር የተጠቀሰው ሆኖ አመልካቹ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 27 እና 598(1) የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቦታ ሚያዝያ 01 ቀን 2005 ዓ.ም. የግል ተበዳይ ሐጅራ ኡስማንን ከመተማ ከተማ ስትደውል ቪዛው መጥቶልሻል ነይ በማለት እንድትመጣ ካደረገ በኋላ ወደ ተከራየበት ቤት በመውሰድ ያለቀልሽ በመሆኑ ብር 800.00 ትከፍያለሽ በማለት ክፍያውን ለመክፈል በመስማማት ለመሄድ በዝግጅት ላይ ሳለች ለፖሊስ በደረሰው ጥቆማ ወንጀሉ ፍጻሜ ሳያገኝ የቀረ መሆኑ ተዘርዝሮ አመልካቹ በሕገ ወጥ መንገድ

ኢትዮጵያዊያንን ወደ ውጪ አገር የመላክ ሙከራ ወንጀል መፈፀሙን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም ክሶቹን ክዶ በመከራከሩ አቃቤ ሕግ አሉኝ ያላቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ከዚህም በኋላ አመልካች በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ወንጀሉን መፈፀሙ መረጋገጡን ፍርድ ቤቱ ገልጾ አመልካች እንዲከላከል መብቱን ጠብቆለት አመልካችም የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያስያዘው ጭብጥ እና የመከላከያ ማስረጃዎቹ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ያስያዘው ጭብጥ እና የመከላከያ ማስረጃዎቹ እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ናቸው በማለት የመከላከያ ማስረጃዎችን ክብደት ሳይሰጥ አልፎ አመልካችን በአምስቱ ክሶች ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ክስ ተገቢ ነው ያለውን የእስራት እና የገንዘብ መቀጮ ከአስቀመጠ በኋላ በድምሩ ደግሞ 25(ሃያ አምስት) አመት ፅኑ እስራት እና ብር 37,500.00 መምጣቱን ፣ ይህ የእስራት ቅጣት በእርከን 37፣ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ በእርከን 9 የሚመደብ ሆኖ ወንጀሉ ተደራራቢ በመሆኑ ምክንያትም አንድ እርከን ከፍ እንደሚል ተቀብሎና በዚህም ስሌት መሠረት የእስራት ቅጣቱ በእርከን 38፣የገንዘብ መቀጮ ደግሞ በእርከን 10 ስር እንደሚወድቅ ደምድሟል፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ አመልካች ሪከርድ የሌለበት፣የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ይዞ እያንዳንዳቸው ምክንያቶች ሁለት ሁለት እርከን እንደሚያስቀንሱለት እንዲሁም ወንጀሉ ሙከራ መሆኑም ሁለት እርከን እንደሚያስቀንስ ገልጾና በአጠቃላይ በስድስት እርከን መቀነስ ያለበት መሆኑን ደምድሞ የእስራት ቅጣቱን በእርከን 32 ስር ባለው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ በአስራ ሶስት አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ፣ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ ብር 2000.00 ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(1)መሠረት ተሰርዟል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ድርጊቱ ስለመፈፀሙም በአግባቡ አልተረጋገጠም፣ በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሣብ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ለተፈፀመ ድርጊት ስድስት ክሶች ቀርበው በአምስቱ ጥፋተኛ ተብሎ ለእያንዳንዱ ክስ ቅጣት ተጥሎ መደመሩ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ)እና (ሐ)ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ እንዲያገኝ ተብሎ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ክሱ በግል ተበዳዮች ቁጥር መቅረቡንና ቅጣቱ በተደራራቢ ወንጀሎች አንጻር ታይቶ ከብዶ የመወሰኑን አግባብነት የሚመለከት በመሆኑ ከዚሁ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተከሰሰው በአንድ መዝገብ ሆኖ ክሶቹ በስድስት ምድብ የተከፈሉ መሆኑንና የተጠቀሰበት የሕግ ድንጋጌም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32(1)(ሀ)፣27 እና 598(1)ሆኖ የክሱ ዝርዝር ይዘቱም ባጭሩ ሲታይ አመልካች ምንም ሕጋዊ የሆነ ፈቃድ ሳይኖረው የግል ተበዳዮችን ከተለያዩ ቦታዎች በማምጣት ወደ ውጪ አገር እልካችኋለሁ፣ ስራም አስቀጥራችኋለሁ በሚል ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡና ከተከራየበት ቤት እንዲቆዩ በማድረግ የተለያየ መጠን ያለውን ገንዘብ ለመቀበል ጠይቆ ወደ ውጪ ለመላክ በዝግጅት ላይ እያለ በፖሊስ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ አመልካች ክሱን የካደ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ አሉኝ ባላቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ማስረዳቱን የስር ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡

አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው በአንድ የወንጀል ሐሳብ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ለተፈፀመ ድርጊት በተለያዩ ክሶች ልጠየቅ አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ በርካታ ሰዎችን ጭኖ ወደ ውጪ አገር እልካችኋለሁ በማለት ማጓጓዝ ላይ እንዳለ መያዙን የክርክሩ ሂደት ያረጋግጣል፡፡

በመሠረቱ የተደራራቢ ወንጀሎች ትርጉም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሀ)እና (ለ)ስር የተቀመጠ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ፊደል "ሐ"ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይም አንድ ሰው በአንድ አይነት የወንጀል ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈጸመው ወንጀል አንድን የሕግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደተደራራቢ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚገባ መሆኑንያስገነዝባል፡፡ ሕግ አውጪው ይህንኑ ድንጋጌ በ1949 ዓ.ም. የወንጀል ሕግ ያስቀምጥ ከነበረው ሁኔታ በተለየ መልኩ እንዲገባ ያደረገበት ምክንያትም ነባሩ የወንጀል ሕግ በዚህ ረገድ የነበረው ይዘትና መንፈስ በሕግም ሆነ በፍትህ ረገድ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይገባው ፣በነባሩ ህግ ማብራሪያ የጻፉት ምሁራንም የሕጉን አቋም ያልደገፉት ሆኑን መሠረት አድርጎ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የተሻሻለው የወንጀል ሕግ ሐተታ ዘምክንያት ሰፍሮ የምናገኘው ጉዳይ ነው፣ ከዚህ ሕጉ ሲወጣ ከነበረው የሕግ አውጪ ሀሣብም ሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሐ)ድንጋጌ በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው ሕጉ ጥበቃ የሚያደርገው የእያንዳንዱን ሰው መብትና ጥቅም መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሳብ ተመሳሳይ ድንጋጌ ተጥሶ በበርካታ ሰዎች ላይ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳት

መድረሱ ከተረጋገጠ የድርጊቱ ፈጻሚ በተደራራቢ ወንጀሎች የሚጠየቅ ሲሆን ሕጉ በዚህ ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባ ያስቀመጠው በቅጣት አወሳሰን ጊዜ በጠቅላላው ሕግ ከተቀመጠው የቅጣት አይነት ጣሪያ ያለማለፍን ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184(1)(ሀ)ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 60(ሐ)ድንጋጌ ትርጉምና አተገባበሩ ከላይ በተመለከተው አግባብ ስለመሆኑም ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 83947 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1)መሠረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ሲጠቃለልም ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች አመልካች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን በበቂ ሁኔታ ያረጋገጡ መሆኑን በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር በተቀመጠው የማስረጃ ምዘና ስርዓት መሠረት መዝነው ከአረጋገጡና አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በግልጽ ከአስታወቀ ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አመልካችን ለወንጀል ድርጊቶቹ ኃላፊ ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት በግልጽ የሚያሳየው ጉዳይ ሆኖ ስለአገኘነውና አመልካቹ ለእያንዳንዱ ክስ ተጠያቂ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

ቅጣቱን በተመለከተም ለእያንዳንዱ ክስ በተናጠል ተወስኖ በጠቅላላው ተደምሮ ከ25/ሃያ አምስት አመት/ ጽኑ እስራት እና ብር 37,500.00ተደርጎ መወሰኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(2)፣58፣60፣(ሐ)፣92፣184(1)(ሀ)እና32(1)(ሀ)፣27(1)፣598(1)ድንጋጌዎችንይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሰው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተገቢ እንጂ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የቅጣት መጠኑ ከብዶ የተወሰነ መሆኑን በቅሬታ ነጥብነት የጠቀሰ መሆኑን ስለተገነዘብን የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች በቅጣት ማቅለያነት የያዛቸውን የሪከርድ ያለመኖርና የቤተሰብ አስተዳዳሪ የመሆኑ ምክንያቶች የሚያስቀንሱት የእርከን መጠን ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሠረቱ እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከግራ ቀኙ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ጥፋተኛ ከተባለበት ድንጋጌ እና ከአድራጐቱ አፈጻጸም አንጻር ሲታይ በቅጣት መመሪያው አንቀጽ 13 መሠረት የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ሆኖ ተደራራቢ በመሆኑ ምክንያት በእርከን 38 ላይ የሚወድቅ ሲሆን የስር ፍ/ቤቱ እንዳረጋገጠው የአሁን አመልካች ወንጀል ሪከርድ ያልቀረበበትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ሊያዝለት ስለሚገባውና ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ከሚያስከትለው ቅጣት ዓይነትና መጠን አኳያ በእነዚህ ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች መሠረት በድምሩ አራት እርከን እንደሚያስቀንስ የስር ፍርድ ቤት ገልጿል፡፡ ሆኖም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በአንቀጽ 16(7)እና16(8)ስር እንደሰፈረው የቅጣት

ዓይነትና መጠን ሬንጅ እድሜ ልክ በመሆኑ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ መቀነስ ያለበት እርከን ሶስት ነው፡፡ ይህ ስሌት ሲያዝ በሁለት የቅጣት ማቅለያዎች መቀነስ ያለበት ስድስት እርከን ሆኖ ሙከራ በመሆኑ ደግሞ ሁለት እርከን መቀነስ ያለበት በመሆኑ በጠቅላላው ስምንት እርከን ሲቀነስ ከእርከን 38 ወደ እርከን 30 መውረድ የግድ የሚል ነው ፡፡ በዚህ እርከን ለፍ/ቤቱ የተሰጠው ፍቅደ ስልጣን ደግሞ ከአስራ አንድ አመት እስከ 13 ዓመት ከሁለት ወር እስራት ስለሆነ በዚህ መሠረት የአሁን አመልካች ለፈፀመው ጥፋት በ11 ዓመት /በአስራ አንድ ዓመት/ ጽኑ እስራት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ ስላገኘነው የስር ፍ/ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዳለ በመቀበል በእስራት ቅጣት አጣጣል ረገድ የፈፀሙትን መሠረታዊ የህግ ስህተትን ግን አርመን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13370 ነሐሴ 8 እና 10 ቀን 2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 94212 ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጸናው ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች በአምስት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለዚህ ጥፋቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባወጣው ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንጻር ታይቶ ሊቀጣ የሚገባው በ11 ዓመት /በአስራ አንድ ዓመት/ጽኑ እስራት እና በብር 2000.00የገንዘብ መቀጮ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2)መሠረት አሻሽለን ወስነናል፡፡
4. በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለመ/ቤት ትዕዛዝ ይድረሰው ብለናል፡፡ ይጻፍ፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# የዳኝነት ስልጣን

የሰ/መ/ቁ. 93220

መጋቢት 8 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንገሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ግርማ አያሌው ዋልታንጉስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት

ነ/ፈጅ ቁምነገር ደጉ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ነሐሴ 28 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ሰለጠየቁ ነው፡፡ ጉዳዩም የመንግስትሠራተኞች የሰራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው በአ/አ/ከተማ አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍ/ቤት ነው በዚያ ደረጃ አመልካች ይግባኝ ባይ ተጠሪ ደግሞ መልስ ሰጪ በመሆን ተከራክሯል፡፡ አመልካች በ17/04/2005 ዓ.ም በተፃፈ ለአስተዳደር ፍ/ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ አመልካች ሠራተኞችን በስርዓት መምራት አልቻለም፣ የስራ ግዴታውን በአግባቡ አልተወጣም በሚል እና እንዲሁም ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሣልረከብ ተረክበሃል በሚል የተጠሪ መስሪያ ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያለምንም ማስረጃ ያለአግባብ ጥፋተኛ ካደረገኝ በኂላ ከስራ እንዲሰናበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት መሆኑን ጠቅሰው ውሣኔው ተሽሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ጠይቋል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የአስተዳደር ፍ/ቤቱም በበኩሉ በቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገና እንዲሁም በመስሪያ ቤቱ ዲስፕሊን ኮሚቴ ክርክር ደረጃ ተጠሪ አሰምቶ የነበረውን ምስክሮችም አስቀርቦ በድጋሚ ቃላቸውን ከተቀበለ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ማስረጃ ከመዘነ በኂላ አመልካች ፈጽመዋል ከተባሉት የዲስፕሊን ጥፋቶች ውስጥ ስለ ላፕቶፕ ኮምፒውተርን በተመለከተ አመልካች ኮምፒውተሩን ከመ/ቤቱ ተቀብሎ አለመመለሱ በበቂ ማስረጃ

ስላልተረጋገጠ በዚህ ረገድ ለቀረበበት የዲስፕሊን ክስ ተጠያቂ ሊሆን አይገባም በማለት ከወሰነ በኋላ ሌሎች ጥፋቶችን በተመለከተ ግን ማለትም አመልካች ከሰራተኞች ጋር ያለው መልካም ግንኙነት እናሣ ስለመሆኑና ከሰራተኞች ጋር ተባብሮ በስምምነት መሰራት አለመቻል በሚመለከት የቀረበበትን የዲስፕሊን ጥፋቶች መፈጸሙ በሚገባ በማስረጃ ተረጋግጦበታል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን ካሰፈረ በኋላ እና እነዚህን ጥፋቶች በተመለከተም በ2 ወር የደመወዝ ቅጣት እንዲቀጣ ሲል በተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን የሰንብት ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

በአሁኑ ተጠሪ ቅሬታ አቅራቢነት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ የአስተዳደር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል አሁንም ባአሁኑ ተጠሪ ሰበር አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩን የተመለከተው የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ እንዲከራከሩ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ላፕቶፕ ኮምፒዩተሩን ወስዶ አለመመለሱ የተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ በሰነድና በሰው ማስረጃ በበቂ ሁኔታ አረጋግጦ እያለ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ግን ይሄንን አላአግባብ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑንና እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይሄንኑ ስህተት ማረም ሲኖርበት ማጽናቱ እንዲሁ መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን ከገለፁ በኋላ የአስተዳደር ፍ/ቤቱንና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል በተጠሪ መ/ቤት ዲስፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ በማጽናት ወስኗል፡

አሁን የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም፡- የስር አስተዳደር ፍ/ቤቱ የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር እና በመመዘን አመልካች የመ/ቤቱን ላፕቶፕ መውሰዱ በማስረጃ በበቂ ሁኔታ አልተረጋገጠም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ የሰጠው ውሳኔ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት "አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ወስዶ አለመመለሱ ተረጋግጦበታል" በማለት የበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ መቀየሩ በህግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የማስረጃ ምዘናን ተግባር መሰረት በማድረግ ስለሆነና ውሳኔው ከዚህ አኳያ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተሽሮ በአስተዳደር ፍ/ቤቱ እና በከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ይፅናልኝ የሚል ነው፡፡ አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ባጭር ባጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም በበኩላችን የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት የአስተዳደር ፍ/ቤቱንና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱን ውሳኔ

የለወጠው በህግ ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ የማረም ስልጣን ውጭ በማውጣት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ካለ ይሄንኑን ለከተማ አስተዳደሩ ሰበር ችሎት ማቅረብ እንደሚችልና ሰበር ችሎቱም በበኩሉ የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ይሄንኑን አይቶና መርምሮ ለማረም ስልጣን እንደተሰጠው ከተሻሻለው የአ/አ/ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42(2) ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳዩ ነው፡፡

በሌላ በኩል በተያዘው ጉዳይ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የተጠሪ መስሪያ ቤት ዲስፕሊን ኮሚቴ ላፕቶፕ ኮምፒውተርን በሚመለከት የቀረበውን የዲስፕሊን ክስ በተመለከተ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በይግባኝ ስልጣኑ ተጠቅሞ ሊለውጥ የቻለው ግራ ቀኙ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር መሰረት በማድረግ በዲስፕሊን ኮሚቴ ክርክር ደረጃ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተው የነበሩ የተጠሪ መ/ቤት ሰራተኞች በድጋሚ አስቀርቦ ቃላቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኂላ አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ስለመውሰዱ በማስረጃ ተረጋግጦበታል? ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ የነገር ጭብጥ በማስረጃ በድጋሚ እንዲጣራ በማድረግ እና እነዚህ የቀረቡትን ማስረጃዎችም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር አገናዝቦ በመመርመርና በመመዘን ተገቢ ነው ያለውን ክብደት ለማስረጃዎቹም በመስጠትና በስተመጨረሻም አመልካቹ ላፕቶፑን ስለመውሰዱ በበቂ ማስረጃ አልተረጋገጠም የሚል የፍሬ-ነገር ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኂላ ስለመሆኑ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህ የፍሬ-ነገር ድምዳሜም በአ/አ/ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ሆኖም የአ/አበባ ከተማ አሰተዳደር ሰበር ችሎት በበኩሉ ይሄንን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር በአመልካች አለመወሰዱ በማስረጃ ተጣርቶና እንዲሁም ማስረጃውም ተመዝኖ የመጨረሻ ድምዳሜ ላይ የተደረሰበትን ፍሬ ነገር እንዳለ ተቀብሎ በህግ ረገድ ብቻ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ካለ ያንን ብቻ አይቶ ማረም ሲገባ በህግ ተወስኖ ከተሰጠው የስልጣን ገደብ ውጭ በመውጣትና የማስረጃ ምዘና ተግባር ውስጥ በመግባት አመልካች አከራካሪውን ላፕቶፕ ወስዶ አለመመለሱ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ተረጋግጦበታል በማለት የፍሬ ነገር ክርክርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን በህግ ስልጣን ከተሰጠው የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የተለየ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ለውጦ በተጠሪ መስሪያ ቤት ዲሲፕሊን ኮሚቴ የተሰጠውን የስንብት ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ በማፅናት የሰጠው ውሳኔ ከአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 42 (2) ድንጋጌ ይዘት ፣መንፈስና አላማ አኳያ ውሳኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአ/አ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 2005 በ7/12/2005 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1)መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአ/አ/ከ/አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍ/ቤት በመ/ቁ.643/05/ በ2/72005 ዓ.ም ተወስኖ በአ/አ/አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ.17945 በ7/8/2005 በሰጠው ውሳኔ እንዲፀና የተደረገው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348 (1) መሠረት ፀንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ የሰበር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የውሳኔ ግልባጩ ለሰር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 93358

መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማርች ፕሮጀክት፡- ነ/ፈጅ አላዮ አምበርብር ቀረቡ

ተጠሪ፣- 1. ቤተልሔም ሽፈራው
2. አሸናፊ ሀደራ
3. ሮማን ታደሰ
} ጠበቃ ግንቡ መኮንን ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት የሚገዛበትን የሕግና ዳኝነት የሚሰጠውን አካል በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች ባሁኑ አመልካችና በበሽታዎች መከላከል እና ቁጥጥር ማዕከል ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የክሳቸው ማመልከቻ ይዘትም ባጭሩ፡- በአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤቱ በተለያየ ጊዜና በተለያየ የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የበሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር ማዕከል የሰጠውን ውክልና በመጠቀም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የስራ ቅነሳ ያደረገባቸው መሆኑን ዘርዝረው እርምጃው ሕገ ወጥ ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁኑ አመልካች ለተጠሪዎች ክስ በሰጠው መልስም፡- አመልካች መስሪያ ቤት በአዋጅ የተቋቋመና በመንግስት በሚመደብለት አመታዊ በጀት የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ነው፣ የፌዴራል መንግስት የአስተዳደር መስሪያ ቤቶችና ሰራተኞች የስራ ግንኙነትን በተመለከተ ደግሞ ራሱን የቻለ የሠራተኞች ሕግ እና አስተዳደር ፍርድ ቤት ያለ በመሆኑ ጉዳዩ

በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው አካል ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካች መስሪያ ቤት በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት በመሆኑ ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚዳኝና በመደበኛ ፍርድ ቤትም የሚታይ አይደለም በማለት መዝገቡን የዘጋው ሲሆን ተጠሪዎች በዚህ የስር ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በኤች.አይ.ቪ. መከላከል ላይ ጥናት አድርጎ ባቀረበው የምርመራ ውጤት መሰረት በስር 1ኛ ተከሳሽ በነበረው አካል ፈንድ ተደርጎለት በራሱ ስራ የሚሰራ ተቋም እንጂ የአመልካች ወኪል አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች በመንግስት የተመደበለትን በጀት መሠረት አድርጎ መደበኛ የመማር ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ አካል አይደለም፣ አመልካች ተጠሪዎችን በመንግስት ሰራተኝነት የቀጠራቸው መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶችን አስፍሮ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የማይሸፈንበት እንደዚሁም ክርክር የተነሳ እንደሆነ በመደበኛ ፍርድ ቤት የማይዳኝበት ምክንያት አይኖርም ሲል ደምድሞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር መሠረታዊ ይዘትም፡- አመልካች የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ ሠራተኞቹን የሚያስተዳድረው በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 ተመልክቶ እያለ እንዲሁም ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሠረት መብቱን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ማቅረብ ሲገባቸው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው ትክክል ነው ተብሎ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው በመባሉ ምክንያት ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በሰጡት የጽሑፍ መልስ፤ የአመልካች አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፣ ተጠሪዎች የተቀጠሩት አመልካች በሚያከናውነው የፕሮጀክት ስራ በመሆኑ ጉዳዩ የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 377/1999 እንጂ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አይደለም፣ አመልካች በኮንትራት የተቀጠሩትን የመንግስት ሰራተኞችን ጉዳይ ለመግዛት በሚመለከተው አካል የወጣ መመሪያ ጉዳዩ ሊገዛ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ተጠሪዎች በመመሪያው መሠረት የተቀጠሩት መሆኑን የቅጥር ውሉ በማያመላክትበት ሁኔታ የቀረበ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጸው ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚታይ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው

ፍርድ ቤት መወሰኑ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀ ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ፡- የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን አመልካች ያነሳውን መቃወሚያ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ አድርጎ መወሰኑ ተገቢ ነው ? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሠረቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር በ214/2003 አንቀጽ 2(1) እና (3) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በፌዴራል ዩኒቨርስቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 210/2003 መሰረት የሚተዳደር መሆኑን ተጠቃሹ ደንብ በግልጽ የሚደነግገው ጉዳይ ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 5(1)ደግሞ ዩኒቨርሲቲው በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር መሆኑን፣ በአዋጁ አንቀጽ 29 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ደግሞ የተቋሙ ተቀጣሪ ሰራተኞች አይነትን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም ቅጥሩ ስለሚመራበት አግባብ የሚገልፁ ድንጋጌዎች ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከተቋቋመባቸው ተግባሮች አንዱ ምርምርና ጥናት ማካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ለማከናወን ደግሞ ፕሮጀክት ቀርጾ ሰራተኛን ከመቅጠር ጀምሮ ተገቢውን ሁሉ የሚፈጽም መሆኑ ይታመናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ፕሮጀክት በዩኒቨርሲቲው የሚተዳደር እንጂ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ፕሮጀክት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በደንብ ቁጥር 210/2003 አግባብ የሚተዳደር ሆኖ እያለ ለምርምር ስራ የሚቀጠሩ ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የመቀበልና ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ለዩኒቨርሲቲው በሕጉ አግባብ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ለማየት እንደህጋዊ ምክንያት አድርጎ ከወሰደባቸው ምክንያቶች አንዱ አመልካች ተጠሪዎች በኮንትራት የተቀጠሩ ሰራተኞች ስለመሆናቸው በማስረጃ አላስደገፈም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ነጥብም ቢሆን የተጠሪዎች ግንኙነት በመንግስት በጀት በሚተዳደር መስሪያ ቤት ስር ባለው አካል ጋር የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 እና በመንግስት የበጀት መስሪያ ቤቶች የቅጥር ሁኔታዎችን በሚደነግጉት ደንቦችና መመሪያዎች

አንጻር ስልጣን ባለው አካል እንዲታይ ከሚደረግ በስተቀር ጉዳዩን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ለመዳኘት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በመንግስት በጀት በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የተቀጠሩ ሰራተኞች ግንኙነታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ የማይገዛ መሆኑን የተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 3 (2)(ሠ) ድንጋጌ ጋር ከአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጋር አዛምደን ስንመለከተው የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመንግስት መስሪያ ቤት በኮንትራት የሚቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 22(3) የኮንትራት ሰራተኛ የቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ያወጣል ተብሎ የተደነገገ ሲሆን በሕጉ ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት "የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ" የሚል ርዕስ የተሰጠበትን ፣ በመግቢያውም ለፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ስለሚቀጠሩ ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞቹ አቀጣጠር፣ መብቶችና ግዴታዎች በግልጽ የሚያስቀምጥ መመሪያ ማውጣት ማስፈለጉን፣ የጊዜያዊ ሰራተኞች ምልመላና መረጣ በችሎታ፣ በግልጽነት ከአድሎ ነጻ በሆነ ውድድር ላይ እንዲመሠረት ለማድረግ፣ በቀጣሪና በተቀጣሪ መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ፍትህ ለመስጠት እንዲረዳ እና በሁሉም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ግልጽ የሆነ አፈጻጸም እንዲኖር ለማድረግ ተብሎ ዓላማው ተለይቶ የተቀመጠለት መመሪያን አውጥቶ ከህዳር ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ እንደሚውል አድርጓል፡፡ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በዚህ መመሪያ የሚገዛ መሆን ያለመሆኑን ሊለይ የሚችለው ደግሞ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ውጪ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ነው፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ጉዳዩ ሊታዩ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ሳይሆን በአዋጅ 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 214/2003 እና ደንብ ቁጥር 210/2003 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 130048 ሰኔ 13 ቀን 2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሠረት በተዘረጋው ስርዓት የሚታይ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት በስራ ክርክር ችሎት የሚታይ አይደለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጌ

የሰ/መ/ቁ. 96216

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-አቶ ተክለብርሃን ዘገየ /ጠበቃ መረሳ ፍስሐ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.አቶ ሸምሰዲን አክመል

2. አቶ ሬድዋን ኸይረዲን

3. አቶ መሐመድ አክመል

} 1ኛ ተጠሪ ከጠበቃ አበራ አንጃ

4. በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 8 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ፍጹም ካሳዩ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመንግስት የንግድ ቤት የተከራይነት መብትን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ06/10/2004 ዓ.ም በተጠሪዎቹ ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች በወረዳ 8 የሚገኘውን ቁጥሩ 144/495/145/516 የሆነውን የንግድ ቤት ከ4ኛ ተጠሪ ተከራይተው የንግድ ስራ ሲሰሩበት መቆየታቸውን እና ይሁን እንጂ 4ኛ ተጠሪ ውሉን አላግባብ ያቋረጠባቸው መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ 4ኛ ተጠሪ ውሉን ከአመልካች ጋር እንዲቀጥል እና ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ደግሞ የንግድ ቤቱን እና በሱቁ ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች ፍርድ ቤቱ ክሱን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍርድ ቤቱ ይህንኑ የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥብ መርምሮ ጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች የሚመለከት በመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አለመሆኑን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34428 በ23/03/2001 ዓ.ም የሰጠው አስገዳጅ የህግ

ትርጉምም ይህንኑ የሚያስገነዝብ መሆኑን ገልጾ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት አመልካች ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ መዝገቡ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ጉዳዩን ለማየት ለተመደበው ችሎት እንዲያስተላልፍ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን የብይን ክፍል ሲያጸናው ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ መዝገቡ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በኩል ጉዳዩን ለማየት ለተመደበው ችሎት እንዲመራ የተሰጠውን የብይኑን ክፍል ግን በመሻሩ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረቱት ክስ ተጠሪዎቹ በአመልካች የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ ላይ በግብረአበርነት እየፈጸሙት ያለው ሁከት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149(1) መሰረት ተወግዶ ሀብትና ንብረቴን ለቀው ያስረክቡኝ የሚል ሆኖ እያለ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህን መሰል ጉዳይ የማከራከር ስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ነው በማለት የመወሰኑን እና ውሳኔው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጽናቱን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡-

1. ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?
2. ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ከዋናው የዳኝነት ጥያቄ ተነጥሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ የሁከት ተግባር ፈጥረውብኛል በማለት አመልካች የሚከራከሩት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የንግድ ሱቃቸው ተቀጣሪዎች ሆነው እያለ መመሪያ ቁጥር 4/2004 መውጣቱን ምክንያት አድርገው የንግድ ሱቁን ከአመልካች የተከራዩ አስመስለው ለ4ኛ ተጠሪ በማቅረብ የተከራይነት መብቱ አላግባብ ወደ ራሳቸው

እንዲዛወር አድርገዋል፤4ኛ ተጠሪም በአመልካች እና በሌሎች ተጠሪዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ዓይነት በአግባቡ ሳያጣራ ከአመልካች ጋር የነበረውን ውል በማቋረጥ ውሉን ከ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ጋር አድርጓል፤3ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ወንድም በመሆን በሱቁ ውስጥ ተገኝቷል በማለት መሆኑን ከክርክራቸው ተገንዝበናል፡፡እንደሚታየው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በቀጥታ ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻፀም ጋር የተያያዘ ነው፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካች ነበር በተባለው የንግድ ሱቅ የገቡት አመልካች እንደሚከራከሩት በሰራተኝነት ነው ወይስ ተጠሪዎቹ እንደሚከራከሩት የንግድ ቤቱን ከአመልካች በመከራየታቸው ነው? የሚለው አከራካሪ ጭብጥ ጭምር ከመመሪያው አፈጻጸም ጋር ተያይዞ የሚታይ እና ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡የንግድ ቤቱ ተከራይ ከነበሩት ከአመልካች እና እንደ አመልካች አባባል በሰራተኛነት፤እንደ ተጠሪዎች አባባል ደግሞ በተከራይነት ወደ ንግድ ሱቁ ገብተዋል ከተባሉት ተጠሪዎች መካከል በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት የተከራይነት መብት ሊያገኝ የሚገባው ማነው? የሚለው ጥያቄ በመሰረቱ በመመሪያው ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መስፈርቶች መሰረት አድርጎ ምላሽ የሚያገኝ የመመሪያ አፈጻጸም ጉዳይ ከሚሆን ውጪ ከሁከት ድርጊት ጋር ግንኙነት ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡

መመሪያውን መሰረት አድርጎ የሚነሳ የንግድ ቤት የተከራይነት መብት ጥያቄ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣን እና ተግባር ጋር እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ጋር የተያያዘ እስከሆነ እና የከተማው አስተዳደር አካልም በተከሳሽነት የተሰየመ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ተቀብሎ የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር በአንቀጽ 41(1) (ለ) እና (ረ) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የዚህ ዓይነቱ ክስ የሁከት ስም ተሰጥቶት በመቅረቡ ብቻ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ሊወድቅ የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡አመልካች ጠቅሰው የሚከራከሩበት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 64703 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይም ከመመሪያ ቁጥር 4/2004 አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ባለመሆኑ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ የአመልካች ዋነኛው የዳኝነት ጥያቄ አላግባብ የተወሰደብኝ የንግድ ቤቱ የተከራይነት መብት ሊመለስልኝ ይገባል የሚል ሲሆን ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል የቀረበው ጥያቄ ዋናውን ጥያቄ ተከትሎ የቀረበ ተጨማሪ የዳኝነት ጥያቄ ነው፡፡ይህ ተጨማሪ የዳኝነት ጥያቄ በመሰረቱ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው፡፡ይሁን እንጂ የዳኝነት ጥያቄው የቀረበው ብቻውን ወይም ራሱን ችሎ ሳይሆን ዋነኛውን የዳኝነት ጥያቄ ተከትሎ ነው፡፡የዚህ ዓይነት ጉዳዮችን በተመለከተ በአንድ ክስ ውስጥ ብዙ አቤቱታዎች ቀርበው ከነዚሁ በከፊል ዋናውን ክስ የሚመለከቱ በከፊል ደግሞ ዋናውን ክስ መነሻ አድርገው ቅርንጫፍ ነገሮችን የሚመለከቱ በሆነ ጊዜ የፍርድ ቤቱ ስልጣን የሚወሰነው ከፍተኛ ግምት ያለውን አቤቱታ መሰረት አድርጎ በመከተል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17(2) ስር የተደነገገ በመሆኑ የአመልካች የንብረት ያስረክቡኝ ጥያቄ የንግድ ቤቱን የተከራይነት መብት ከሚመለከተው ዋነኛው የዳኝነት ጥያቄ ተነጥሎ ለብቻው ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የንብረት ያስረክቡኝ የዳኝነት ጥያቄ ጭምር ከዋናው ጉዳይ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ገልጾ መመለስ ሲገባው ተነጥሎ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ትዕዛዝ መስጠቱም ሆነ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ ግልጽ የሆነ ውሳኔ አለመስጠቱ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 190432 በ07/03/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128776 በ04/02/2006 ዓ.ም ተሻሽሎ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ክስ የቀረበበት ጉዳይ የሚወድቀው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር ነው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ

ከዋናው የክስ ምክንያት ተነጥሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

4. ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተመለከቱት ተጠሪዎች በሱቁ ውስጥ ያሉትን ንብረቶች ያስረክቡኝ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 17(2) በተመለከተው መሰረት የንግድ ቤቱን የተከራይነት መብት ከሚመለከተው ዋናው የዳኝነት ጥያቄ ጋር በአንድነት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ በአንድነት ሊስተናገድ የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
6. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 97372

ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ማም ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል/ማህበር አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ ሜሮን አንማው ቀረቡ

2. አፍሮ ግሎባል የንግድ ማዕከል ሊሚትድ አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በኮንቴነር ዲፖዚት ዋስትና የተያዘ ገንዘብ ይለቀቅልኝ ወይም ይከፈለኝ በሚል መንገድ የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ አንደኛ ተጠሪ /አንደኛ ተከሳሽ/ ሁለተኛ ተጠሪ /ሁለተኛ ተከሳሽ/ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸው ዕቃዎች የታሸጉበት ኮንቴነር ለመመለሰ ብር 22.836.32 /ሀያ ሁለት ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም/ የኮንቴነር ዲፖዚት ዋስትና መያዣ በማድረግ ለአንደኛው ተከሳሽ (አንደኛ ተጠሪ) በትራንዚተሩ ሁለተኛ ተከሳሽ (ሁለተኛ ተጠሪ) በኩል አስይዣለሁ፡፡ ኮንቴነሮቹ የተመለሱ ቢሆንም አንደኛ ተከሳሽ ገንዘቡን ያለ በቂ ምክንያት አለቅም በማለት ወስዷል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሾችም የትራንዚት ውል መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አቅርቦ ገንዘቡን እንዲመለስ ማድረግ ሲገባው፤ ሰነዶችን በአንደኛ ተከሳሽ አቅርቦ ገንዘብ እንዲመለስ በማድረጉ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ኪሳራ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ገንዘቡን በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ ቢሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2. በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛ ተጠሪ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት ቅሬታውን በሚመለከተው ኃላፊ /የስራ ክፍል/ አቅርቦ ማሳየት ሲገባው በህጉ መሰረት አቤቱታውን ሲያቀርብ ቀጥታ በፍርድ ቤት ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም፡፡ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ይህንን የአንደኛ ተከሳሽ የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 339 መሰረት ሰርዞታል፡፡
3. አመልካች የበታች ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ የተቀበለው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ከሚደነግገው ውጭ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ የማየት ስልጣን የለውም ቢባል እንኳን ሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ ነጥሎ የማያይበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት የፈፀሙት የህግ ስህተት ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ብይን አዋጅ ቁጥር 622/2001 መሰረት ያደረገ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው በመሆኑ፤ መዝገቡን መዝጋቱ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ባለማቅረቡ፤ የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡
4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የህግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረበበት ገንዘብ የመመለስ ኃላፊነት አለበት የሚለው አንደኛ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 ከሚደነግገው ውጭ ከኮንቴነር ዋስትና ያስያዝኩትን ገንዘብ አይመለስልህም ያለኝ በመሆኑ ገንዘቡን እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ይህም አመልካች አንደኛ ተጠሪ ዋስትና ያስያዝኩትን ገንዘብ የመመለስ ህጋዊ ግዴታ አለበት የሚልና የአንደኛው ተጠሪ ኃላፊነት የሚመነጨው ከሕግ መሆኑን አመልካች በግልፅ ጠቅሶ የተከራከረ መሆኑን ያሳያል፡፡
6. አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ዙሪያ የቀረበው ጥያቄ፤ ሁለተኛው ተጠሪ አስፈላጊ የግምሩክ ስርዓት እንዲፈጽምና የትራንዚት ሥራ እንዲሰራ ውክልና ተሰጥቶታል፡፡ በሁለተኛ ተጠሪ ለአመልካች ለመስጠት በተዋዋለው የትራንዚት አገልግሎት መሰረት

አስፈላጊ ሰነዶችን በአንደኛ ተጠሪ በማቅረብ ገንዘቡን በወቅቱ መጠየቅና ማስመለስ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ባለመፈጸም ገንዘቡን አንደኛ ተጠሪ ገቢ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ የደረሰብኝን ኪሳራ የመተካት ኃላፊነት አለበት በማለት የሁለተኛው ተጠሪ ኃላፊነት ምንጩ በሁለተኛ ተጠሪ በአመልካች መካከል ያለው የትራንዚት አገልግሎት ውል መሆኑን በመግለፅ ክስ ያቀረበ መሆኑን ተረድተናል፡፡

7. አንደኛ ተጠሪ አመልካች ዕቃ ላስገባባቸው ኮንቴነሮች በመያዝ እስከ ሚይዙ የነበረውን ገንዘብ መኖሩን የማይክድ አመልካች ተገቢውን የጉምሩክ ስርዓት በመፈፀም ኮንቴነሮቹን የመለሰ መሆኑን ገልፆ በወቅቱ ገንዘብ እንዲመለስለት ጥያቄ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ሆኗል፡፡ አመልካች ቢያንስ አስተዳደራዊ ውሳኔ ስህተት ነው የሚል ከሆነ በመጀመሪያ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያቋቋማቸው አቤቱታና ቅሬታ ሰሚ አካላት ማቅረብ አለበት በመሆኑ ይህ ስርዓት ሳይጠናቀቅ በፍርድ ቤት አይታይም በማለት መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

8. የአንደኛ ተጠሪን መቃወሚያ ስንመረምረው ጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ጋር በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ሰው ባለስልጣኑ አቤቱታ አጋር ቡድን ውሳኔው በተሰጠ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ማቅረብ እንደሚገባም ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3(ሐ) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 17 መሰረት የጉምሩክ ሥርዓት የሚለው ቃልና ወደ አገር የሚገባ፤ ወደ ውጭ አገር የሚላክ ወይም ተላላፊ ዕቃ ከጉምሩክ ወደብ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከጉምሩክ ቁጥጥርም እስከሚወጣ ድረስ የሚከናወን ማናቸውንም የጉምሩክ አፈፃፀም ሂደት የሚጨምር ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ዕቃ አስቦ ያስገባቸውና ወደ ውጭ የሚመልስ ስለመሆኑ የዋስትና ገንዘብ ያስያዘባቸው ኮንቴነሮች ከጉምሩክ ቁጥጥር ስር የሚወጡበትን የሚሄዱበትን አመልካች መያዣውን የሚጠይቅበትን ሂደት የሚያካትት መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

9. አመልካች የመያዣያ ገንዘቡን ለማስመለስ አስፈላጊውን ሥርዓት አሟልቶ ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት መጠየቂያና ባለስልጣኑ ለሚወስነው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ አቤቱታ አጣሪ ቡድን ቅሬታውን ማቅረብ እንዳለበት የአቤቱታ አጣሪ ቡድን የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ ተከትሎ ዳይሬክተሩ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር በተሰኘ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ እንደሚገባውና አመልካች በሰላሳ ቀናት ውስጥ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ካላቀረበ የዳይሬክተሩ ውሳኔ የመጨረሻ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 89 ንዑስ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) ንዑስ አንቀፅ 5 እና ንዑስ አንቀፅ 6 ድንጋጌዎችና ከባለስልጣን በቦንድ ወይም በዋስትና ስለተያዘ ገንዘብ አመላላሽ የወጣውን መመሪያ

ቁጥር 37/2002 አንቀፅ 9 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይም አመልካች በዋስትና ያስያዝኩት ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት የስር ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ያቀረበው በአዋጅ ቁጥር 622/2001 እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 37/2002 አንቀፅ መሰረት ሥልጣን ላላቸው አካላት ቅሬታውን ሳያቀርብና ሳይወሰን በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበውን የክስ በዳኝነትን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የዳኝነት ሥልጣን የሌለው መሆኑ፤ የስር ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ በመወሰን የሚገድበው አይደለም፡፡ አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ ሁለተኛው ተጠሪ የአመልካች ትራንዚተር ሆኖ ውክልና ወስዶ እያለ ተገቢውን የጉምሩክ ስርዓት ፈፅሞ በመያዣ የተሰጠውን ገንዘብ ባለማስመለሱ የደረሰብኝን ኪሳራ እንዲተካ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ በባህሪው አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተነጥሎ ሊታይና ሊወሰን የሚችል ዳኝነት የተጠየቀበት የገንዘብ መጠንም በስር ፍርድ ቤት የዳኝነት የስረ ነገረ ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ (ሀ) በአመልካች በሁለተኛው ተጠሪ መካከል የተደረገ የትራንዚት አገልግሎት ውል አለ ወይስ የለም (ለ) በሁለቱ መካከል የተደረገ የትራንዚት አገልግሎት ውል አለ ከተባለ ሁለተኛ ተጠሪ አመልካች ለኮንቴነሮች ያሰያዘው የዋስትና ገንዘብ እንዲመለስ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? ሁለተኛ ተጠሪ በዋስትና የተያዘውን ገንዘብ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት ቢባል፤ ሁለተኛ ተጠሪ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቷል ወይስ አልተወጣም? የሚሉትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች በመጨረሻም ሁለተኛ ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች የመተካት ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት መወሰን ሲገባው የስር ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛው ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስና አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የተለያዩ መሆናቸውን ሳያገናዝብ፤ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን የአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 14 ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 198134 ሰኔ 19 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 140746 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች በአንደኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ያቀረበውን ክስ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያለው በመሆኑ፤ የአመልካችንና የሁለተኛ ተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ተ

# ጉሙሩክ/ታክስ/

የሰ/መ/ቁ. 97409

ግንቦት 07 ቀን2006 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች:-** የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐቃቤ ህግ - ምህረት ቁምላቸው - ቀረቡ

**ተጠሪ:-** 1. ጋርዊች ዋንግ

2. ሽመልስ አየለ

3. ሰለሞን ተሾመ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሁኑ የሰበር አመልካች ከሳሽነት የተጀመረው በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ እንደ ቅደምተከተላቸው 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም:- ተከሳሾች የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመበትን እንዲሁም ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን ብር 250,759.16 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም) ለመንግስት መከፈል ሲገባው ይኼው ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበትን አርባ ስምንት በርሜል ነዳጅ እና አንድ መቶ ኩንታል ሲሚንቶ የታርጋ ኮድ ቁጥር 3-48079 ኢት በሆነ ኤርቴች የጭነት መኪና ላይ በመጫን ባሁኑ 2ኛ ተጠሪ አሽከርካሪነትና በአሁኑ ሶስተኛ ተጠሪ ረዳትነት የኢትዮጵያን መሬት ሙሉ በሙሉ ጨርሰው ሱዳን ሊገቡ ሲሉ በኢትዮጵያ ድንበር ላይ በምትገኘው ኩቡሪ ኬላ ላይ በፌዴራል ፓሊስ አባላትና በጉምሩክ ሰራተኞች ከእነ ሕገ ወጥ እቃዎቹ እጅ ከፍንጅ ሚያዚያ 07 ቀን 2005 ዓ.ም ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን መያዛቸውን ዘርዝሮ ተጠሪዎች የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾችም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጐላቸው የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ በክሱ የተጠቀሰውን ወንጀል ክደው በመከራከራቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን ምስክሮች በመስማት እና ማስረጃዎቹን በመመርመር የአሁኑን 1ኛ ተጠሪ እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪው ከኑዌር ዞን ላሬ ወረዳ የተፃፈ ደብዳቤ እንዲሁም ጥቅምት 06 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር 5/11/ ጋጉም የተፃፈ ደብዳቤ ሕጋዊ የጉምሩክ ክፍያ ከፍለው ሕጋዊ ደረሰኝ ያላቸው መሆኑና የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 764/38 የመቶ ኩንታል ሲሚንቶ ወደ ደቡብ ሱዳን የገባበት የጉምሩክ ገቢ ደረሰኝ ለመከላከያ ማስረጃነት ማቅረባቸውን ጠቅሶ ተጠሪው በእነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ማስተባበላቸውን ገልፆ ሁሉንም ተከሳሾች ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙ ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦት የአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው ጉዳያቸው በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ከሰጠና አመልካችንና የሁኑን 1ኛ ተጠሪን ግን አከራክሮ ጉዳዩን በመመርመር የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የነፃ መለቀቅ ውሳኔ ሙሉ በሙሉ በድምፅ ብለጫ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- እቃው ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ሌላ አገር ግዛት ሕጋዊ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ሲጓጓዝ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ሁኔታ በክልሉ በሚገኘው የወረዳው የገቢ ጽ/ቤት የተሰጠው ደረሰኝ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ያሳያል ተብሎ ተጠሪዎች በነፃ መሰናበታቸው በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሳኔው ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ፡-ተጠሪዎች ክስ የቀረበባቸውን የኮንትሮባንድ ወንጀል ስላለመፈፀማቸው በመከላከያ ማስረጃ አስረድተዋል ተብሎ በነፃ እንዲሰናበቱ መወሰኑ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል ፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ለክሱ መሰረት የሆኑትን እቃዎች ወደ ደቡብ ሱዳን ሊያስገቡ ሲሉ እቃዎቹ መያዛቸውን ሳይክዱ አጥብቀው ሲከራከሩ የነበሩት እቃዎቹ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈፀመባቸው ናቸው በሚል ምክንያት ሁኖ ይህንኑ ለማስረዳት በጋምቤላ ክልል የሚገኘው የላሬ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 600.00(ሰድስት መቶ ብር) የከፈሉ መሆኑን

የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑንና የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች ነፃ መለቀቅ መሰረት ያደረጉትም ይህንኑ የሰነድ ማስረጃ መሆኑን ነው፡፡አመልካች የሚከራከረው ደግሞ ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ውጪ አገር በሚወጡ እቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን የፌዴራል መንግስት ከመሆኑም በላይ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የቀረጥና ታክስ መጠን አይደለም፤ክልሎች በተለምዶ ለኮቴ ብለው የሚያስከፍሉ ነው በማለት መሆኑንም ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል

በመሰረቱ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህግ መንግስት በአንቀጽ 96፤97እና 98 ድንጋጌዎች ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም በእነዚህ የሕገ መንግስት ድንጋጌዎች አግባብ በፌዴራል መንግስት ስልጣን የሆኑትን የታክስ ጉዳዩችን በተመለከተ ስልጣን የተሰጠው አካል በሕግ ተቋቁሞ በሕጉ የተሰጠውን ስልጣንና ሐላፊነት በመውጣት ላይ የሚገኝ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 578/2000 በተለይ ሲታይም የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጣቸው ኃላፊነቶችና ተግባሮች በአንቀጽ6 ስር ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ ከኢትዮጵያ ግዛት ወደ ውጪ አገር በሚላኩ ወይም ከውጪ አገር ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 96(1) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህ አንጻር ስንመለከተውም በፌዴራል መንግስት ታክስና ቀረጥ እንዲያስከፍል በሕግ ስልጣን ከተሰጠው ተገቢው ቀረጥና ታክስ መከፈሉን መቆጣጠርና በሕጉ የተሰጠውን ኃላፊነት ሁሉ መወጣት ያለበት ይኼው አካል መሆኑ ከዚሁ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ እና ከአዋጅ ቁጥር 578/2000 አንቀጽ 6(8)፣9 እና 10 ድንጋጌዎች እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 15(1)፣ 82 (1(ሀ))((ለ)) ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለው አካል ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ እንደተከፈለ የሚቆጠርበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በሕጉ አግባብ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈፀመበትን እቃ ወደ ውጪ ማስወጣትም ሆነ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2(6)፣(2(11)፣2(17) እና 91 ድንጋጌዎች መሠረት የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው፡፡ ቀረጥና ታክሱን የከፈለው ሰው ከሐሣቡ በላይ የወንጀል ተጠያቂነት የሌለበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ወደዚህ ድምዳሜ የሚደረሰው ግን ተገቢው ቀረጥና ታክስ ከፋዩ ወገን መንግሥታዊ አካሉ ስልጣን ያለው መሆኑን በማመን ቀረጥና ታክሱን መክፈሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ እቃዎቹ ወደ ደቡብ ሱዳን ሊገቡ ሲሉ የተያዙ ሲሆን በእቃዎቹ ቀረጥና ታክስ የመሰብሰብ ሕጋዊ ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መንግሥት መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን ሊከፈል ይገባ የነበረው ቀረጥና ታክስ መጠንም ብር 250,759.16 ሣንቲም መሆኑን አመልካች ጠቅሶ የተከራከረበትና ማስተባበያ ማስረጃዎች ያልቀረቡበት

ጉዳይ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከፈሉ የተባለው ገንዘብ በጉዳዩ ላይ ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ ስልጣን በሌለው ለክልሉ የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ገቢ የሆነ ከመሆኑም በላይ መጠኑም ብር 600.00 /ስድስት መቶ ብር/ ብቻ መሆኑን ተጠሪው ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ይህ ደግሞ በእቃዎቹ ላይ ተገቢው ቀረጥና ታክስ በሕጉ ስልጣን በተሰጠው አካል ተሰብስቧል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተጠሪ እቃዎቹ ከውጪ አገር የገቡና የተከፈለባቸው ቀረጥና ታክስ ምን ያህል እንደሆነ የሚታወቅ እንደመሆኑ መጠን ወደ ውጪ ሲወጡ ሊከፈል ይችል የነበረውን የቀረጥና ታክስ መጠን እንዲሁም ስልጣን ያለውን አካል አያውቁም ለማለት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ታክስና ቀረጥ የመሰብሰብና ሕጉን የማስከበር ኃላፊነት ያለውን አካል አግባብነት ካላቸው ሕጎች አንፃር ሳይመለከቱና 1ኛ ተጠሪ ከፈልኩ የሚሉት የገንዘብ መጠን በእቃዎቹ ሊከፈል ይገባ የነበረውን የገንዘብ መጠን ያህል ያለመሆኑን በማስረጃዎቹ መረጋገጡን ሳያገናዝቡ ተጠሪዎችን ነፃ ማሰናበታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.05823 በቀን 10/03/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.01557 በቀን 08/05/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የፀናው ውሣኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/.ቁ. 195(2)(ሀ) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ከተባለ በኋላ አቃቤ ሕግ ስለቅጣት አስተያየት ተጠይቆ መንግስት በከፍተኛ ወጪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውንና ወደ ውጪ የማይላከውን እቃ ተጠሪዎች  ከወረዳው ገቢዎች ጽ/ቤት ጋር ተመሣጥረው ወደ ውጪ አገር መላካቸው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84/1/መ/ መሠረት ቅጣቱን የሚያከብድ ነው ወንጀሉም ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ መካከለኛ ተብሎ ተመድቦ ተገቢው ቅጣት በተጠሪዎች ላይ እንዲወሰን እናመለክታለን አሉ። ጉዳዩን መርምሮ የቅጣት ውሣኔ ለመስጠት ለ18/09/2006 ዓ.ም ተቀጠረ።

ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ ምህረት ቁምላቸው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ጋርዊች ዋንግ
2. ሽመልስ አየለ
3. ሰለሞን ተሾመ
} በሌሉበት የሚታይ ነው

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን የቅጣት ውሣኔ ሰጥተናል፡፡**

**ቅ ጣ ት**

ተጠሪዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91(1) ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ የተላለፉ ጥፋተኞች ናቸው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው ደግሞ ተገቢውን ቅጣት ሊያገኝ ይገባል፡፡

ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ወንጀሉ የተፈፀመባቸው እቃዎችና መሳሪያዎች እና የወንጀሉ ፍሬ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር በሚመጣጠን የገንዘብ መቀጫና ከሰባት እስከ አስራአምስት አመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ነው፡፡ድንጋጌው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የወንጀል ደረጃ እርከን ያልወጣለት በመሆኑ በመመሪያው መሰረት በድንጋጌው የመነሻ ቅጣት ሰባት አመት እና በጣሪያው፤በአስራ አምስት አመት መካከል ያለውን ልዩነት በአራት በማካፈል የምናገኘው የመጀመሪያውና ቀላል ተብሎ የሚታወቅ ደረጃ ቅጣት ፍቅድ ስልጣን ከሰባት አመት እስከ ዘጠኝ አመት ሲሆን መካከለኛው ደግሞ ከዘጠኝ አመት እስከ አስራ

አንድ አመት ነው፡፡ከባድ ተብሎ የሚለየው ደግሞ ከአስራ አንድ አመት እስከ አስራ ሶስት አመት ነው፡፡ በስሌቱ መሰረት የመጨረሻው ደግሞ ከአስራ ሶስት አመት እስከ አስራ አምስት አመት ይሆናል፡፡

ዓቃቤ ሕግ ደረጃው መካከለኛ ተብሎ እንዲመደብ ያመለከተ ሲሆን ለዚሁ ምክንያት ያደረገውም የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 84(1(ሐ)) ድንጋጌ ነው፡፡ይሁን እንጂ የወንጀሉ አፈጻጸም ዘዴ፣ጊዜ ቦታና የአፈጻጸሙ አኳኋን ሲሆን በዚህ ድንጋጌ በተመለከተው ይዘትና መንፈስ ነው ለማለት የሚቻል ያለመሆኑን ከድርጊቱ አጠቃላይ አፈፃጸም የተረዳን በመሆኑ የዓቃቤ ህጉን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡በመሆኑም ተጠሪዎች ስልጣን ከሌለው አካል ደረሰኝ በመያዝና ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ያህል ሳይከፍሉ እቃውን ወደ ውጪ አገር በማውጣት ላይ ሳሉ መያዛቸው የወንጀሉን ደረጃ ዝቅተኛ ሊያደርገው የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡በዝቅተኛ የወንጀል ደረጃ ስር የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ከሰባት አመት እስከ ዘጠኝ አመት ሲሆን ይህ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በእርከን 23 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ከዚሁ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ሰባት አመት ሊሆን እንደሚገባው ይዘናል፡፡ በዓቃቤ ሕግ በኩል በተጠሪዎች ላይ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን ተጠሪዎች ሪከርድ ያልቀረበባቸው በመሆኑ ከዚህ ወንጀል በፊት መልካም ባህርይ የነበራቸው መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፣ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 16(7) ደግሞ መነሻ ቅጣታቸው ሰባት አመት በላይ ለሆኑት ወንጀሎች አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሚያስቀንሰው ሶስት እርከን መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ከእርከን 23 ወደ እርከን 20 አውርደናል፡፡ በዚሁ እርከን ውስጥ የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ደግሞ ከአራት አመት ከአምስት ወር እስከ አምስት አመት ከአራት ወር ነው፡፡ ተጠሪዎች ስራቸው የተለያዩ ሲሆን በወንጀሉ የነበራቸው ሚናም ተመሳሳይ ነው ተብሎ አይገመትም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የእቃው ባለቤትና ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ላይም ከሌሎቹ ተጠሪዎች የላቀ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን 3ኛ ተጠሪ ደግሞ የመኪናው ረዳት በመሆኑ ከሌሎቹ ያነሰ ተሳትፎ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ቅጣት ደግሞ መወሰን ያለበት የአጥፊዎችን የተሳትፎ ደረጃም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 41 ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በተጠሪዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት በአንደኛ ተጠሪ ጋርዊች ዋንግ አምስት አመት ጽኑ እስራት፣ በሁለተኛ ተጠሪ፣ ሽመልስ አየለ አራት አመት ከሰባት ወር፣ በሶስተኛ ተጠሪ፣ ሰሎሞን ተሾመ አራት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት ሆኖ አግኝተናል፡፡ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተም እያንዳንዳቸው ብር 250,759.16 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከአስራ ስድስት ሳንቲም) እንዲከፍሉ፣ ለክሱ መሰረት የሆነው አርባ ስምንት በርሜል ነዳጅና አንድ መቶ ኩንታል ሲሚንቶ ደግሞ ለመንግስት ውርስ እንዲሆን ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. ተጠሪዎችን የፌዴራል ፖሊስ ከክፍሉ ፖሊስ ጋር በመተባበር ካሉበት በመያዝ ለጋምቤላ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር እንዲያስረክብ፣ ማረሚያ ቤቱም ተጠሪዎቹን ፖሊስ ይዞ ሲቀርብ በመረከብ በዚህ ችሎቱ በተወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሰረትና በጉዳዩ ላይ የታሰሩት ጊዜ ካለ በማሰብ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡
2. የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ይድረሳቸው ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ 88446

ግንቦት 22 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሤ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ሙሉ አሚን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር -ጠበቃ አቶ ገ/መድህን ረዳ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን -ዐ/ሕግ አቶ ኃይለመለኮት አበበ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

ለዚህ ለሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ተጠሪው በወሰነበት የገቢ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን ላይ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢያቀርብም ጉባኤው ቅሬታውን ውድቅ በማድረጉና ጉዳዩን በየደረጃው በይግባኝ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናታቸው ነው፡፡

አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታም፡- ይግባኝ ባይ የሚፈለግብኝን ግብር ከከፈልኩ ከ5 ዓመት በኋላ ያለአግባብ የተወሰነብኝ ግብር እና ታክስም በይርጋ የሚታገድ ነው፣የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን በይግባኝ ባይ ድርጅት ስም ገቢና ወጪ፣ትርፍና ኪሳራ በማስላት በሒሳብ መዝገብ መሰረት በማቅረብ ለግብር አስገቢ መስሪያ ቤት ካሳወቅሁ በኋላ ታህሳስ 23 ቀን 1998 ዓ/ም በድርጅቱ ላይ ባጋጠመው የእሳት አደጋ የሂሳብ እና መሰል ሰነዶች ተቃጥለው በመውደማቸው ይግባኝ ባይም ለሚመለከተው የመንግስት አካል አመልክቼ በክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ በኩል አደጋው ስለመጣራቱ ማስረጃ እያለኝ እና ግብር አስገቢው መ/ቤትም በዚሁ ምክንያት የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን በማገኘው 1.65% ኮሚሽን ሊገኝ የሚችለውን ትርፍ ማስላት ሲገባው በእሳት ቃጠሎው ንብረቱ እና ሰነዶቹ መውደማቸውን ቢቀበልም በእሳት አደጋው የወደመውን የሂሳብ መዝገብ ካላመጣህ በስተቀር በ1.65% አይሰላም በማለት ይግባኝ ባዩን በሚጎዳ መልኩ በ7.5% አማካይ የትርፍ መቶኛ በማስላት እጅግ የተጋነነ

ግብርና ታክስ መጠየቁ ተገቢነት የለውም፤ በሌላ በኩል ይግባኝ ባይ ድርጅት ከኬኬ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሚያገኘው የሱፍ ክር ሐምሌ 15 ቀን 1996 ዓ.ም በተፈራረምነው ውል አንቀጽ 5(5.3) መሰረት ማህበሩ ከሚሰጠው የጅምላ ዋጋ ላይ በፓኬት ከ1ብር እስከ 2 ብር ብቻ በመጨመር እንዲሸጥ የተስማማን ሲሆን ከተስማማነው በላይ የአገልግሎት ዋጋ በመጨመር ልሸጥ እንደማልችል፣ ሽጬ ብገኝም ለውሉ መፍረስ ምክንያት እንደሚሆን በተስማማነው መሰረት ይግባኝ ባይም ይህንኑ የውል ግዴታ በማክበር በኮሚሽን የሚሸጠው ክር የትርፍ መቶኛው 1.65 በማይበልጥበት ሁኔታ ግብር አስገቢው መ/ቤት ግብር እና ታክስ በግምት ሲወስን 7.5% የትርፍ ህዳግ መያዙ ተገቢ አይደለም፣እንዲሁም በ1996፣ከ1998 እስከ 2001 ዓ/ም ግብር ዘመን ግብሩ በተሰላበት በ1.65% መሰረት የ1997 ዓ/ም ግብርም መሰላት ሲገባው መስሪያ ቤቱ በተሳሳተ መንገድ ማስላቱ ተገቢ አይደለም፣የግብር አስገቢው መ/ቤት በግብር ማስታወቂያዎቹ ላይ አስመጪ በሚል በመጻፍ በተሳሳተ የስሌት መነሻ ወለድ፣ግብር አሳንሶ በመክፈል እና ክፍያ በማዘግየት እንድከፍል የወሰነብኝ መቀጫ ተቀባይነት የለውም ሲል የግብርና ታክስ ውሳኔው ተሰርዞ ኦዲት በተደረጉት የሂሳብ ሰነዶች መሰረት ሂሳብ ተስተካክሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጪው መ/ቤትም በሰጠው መልስ፡- ይግባኝ ባይ የግብር ውሳኔው መቅረብ ከሚገባው ጊዜ በላይ ቆይቶ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው ቢልም ውሳኔው የደረሰው በ25/02/2003 ዓ/ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ ከማለፉ በፊት የቀረበ ነው፤ጊዜው አልፏል ቢባል እንኳን ግብር ከፋይ የተጭበረበረ ገቢ ያቀረበ እንደሆነም በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 71(3) መሰረት በማናቸውም ጊዜ ግብሩን መወሰን እንደሚቻል በመደንገጉ የይርጋው ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ይግባኝ ባይ መስከረም 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የሂሳብ መዝገቡን እንዲያቀርብ ተጠይቆ በእሳት አደጋ ምክንያት ንብረቱ የወደመ መሆኑን በመግለጽ ምንም ዓይነት ሰነድ ማቅረብ ባለመቻሉ በአዋጁ መሰረት በይግባኝ ባይ ግብሩ የተወሰነበት ሲሆን ግብሩ በግምት በሚወሰንበት ጊዜም መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት የዘርፉን ዝቅተኛ ትርፍ 7.5% መሰረት በማድረግ ተወስኗል፡፡ ግብሩ በመመሪያው መሰረት የተወሰነበት ሆኖ ሳለም ይግባኝ ባዩ ከአምራች ድርጅት ጋር በተዋዋልኩት መሰረት በ1.65% ዝቅ ተደርጎ ሊሰላ ይገባል በማለት ያቀረበው ክርክርም የህግ መሰረት የለውም፤የ1996 ዓ/ም የግብር ዘመን ግብር የተሰላው ይግባኝ ባይ አምኖ በገለጸው መሰረት እንጂ በመልስ ሰጪው መ/ቤት ኦዲት ተደርጎ አይደለም፣የ1997 ዓ/ም ግብርም ሲወሰን በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ሲያተርፉ የነበረውን የትርፍ ህዳግ መሰረት አድርጎ በወጣው መመሪያ መሰረት ነው፡፡ መቀጫውን እና ወለድን በተመለከተም ማንኛውም ግብር ከፋይ በህጉ የተጣለበትን የግብርና ታክስ የመክፈል ግዴታ በአግባቡ ባልተወጣ ጊዜ ወለድም ሆነ መቀጫ በህጉ መሰረት የመክፈል ግዴታ ስላለበት መቀጫውንም ሆነ ወለዱን የማይከፍልበት ምክንያት የለም ሲል የግብር ውሳኔው እንዲጸናበት ጠይቋል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤውም ይግባኝ ባይ ያቀረበውን የይርጋ ክርክር በተመለከተ፡- መልስ ሰጪው የግብር ውሳኔውን ያስታወቀው በአዋጁ የተቀመጠው የ5 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ያለ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔ ደግሞ፡-በግብር ከፋዩ የሚቀርቡትን ሰነዶችና መዝገብ ግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በማናቸውም ምክንያት ያልተቀበለው እንደሆነ ግብሩን በግምት ሊወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) የተደነገገ ሲሆን መልስ ሰጪውም የይግባኝ ባይን የግብይት ሰነድ ውድቅ በማድረግ ግብሩን በግምት የወሰነው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው፤ እንዲሁም የግምቱን አወሳሰን በተመለከተም በአዋጁ አንቀጽ 69(2) ስሌቱ የመልስ ሰጪው መ/ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንደሚሆን በመደንገጉና መልስ ሰጪውም ግብሩን በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ የገቢዎች ሚኒስቴር በ1997 ዓ/ም ባወጣው መመሪያ በተቀመጠው ስሌት መሰረት ግብሩን ስለመወሰኑ ስለተረጋገጠ ይግባኝ ባይ ያቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የላቸውም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጓል፡፡ ከዚህ በላይ ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰውም ጉዳዩን በደረጃው ያሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ይግባኙን ውድቅ በማድረጋቸው አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የቅሬታ ነጥቦቹም፡- ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዝርዝር ያቀረባቸው ነጥቦች ሲሆኑ ተጠሪውም ለጉባኤው ያቀረበውን ተመሳሳይ ይዘት ያለውን መልስ ለዚህ ችሎትም አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- አመልካች የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን የሂሳብ መዝገብ እና ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች በድርጅቱ ባጋጠመው የእሳት አደጋ በመውደማቸው ለተጠሪው መ/ቤት ማቅረብ አልችልም ሲል ያቀረበውን ክርክር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና የሥር ፍርድ ቤቶች በማለፍ የዘመኑን ግብር ተጠሪው በግምት መወሰኑ አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) እና በ1997 ዓ/ም የገቢዎች ሚኒስቴር ያወጣውን የግብርና ታክስ ስሌት መሰረት ያደረገ ነው ሲሉ በመቀበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል የወሰኑት ይህንኑ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ በተረጋገጡበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች የ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን ገቢውን በማስታወቅ ግብሩን ለመክፈሉ በግራ ቀኙ የሚታመን ሲሆን ተጠሪው መስከረም 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አመልካች የሂሳብ መዝገቡን እንዲያቀርብ በመጠየቁ አመልካችም መስከረም 25 ቀን 2003 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በድርጅቱ በደረሰው የእሳት አደጋ ምክንያት ንብረቱና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን በመጥቀስ ማቅረብ እንደማይችል በማስታወቁ ተጠሪውም የግብሩን መጠን በግምት ስለመወሰኑ የግብር የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በውሳኔ ላይ ካሰፈረው መገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በእሳት አደጋው ንብረቱ እና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን ለመንግስት አካል አስታውቆ የአደጋው ሁኔታ

በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ እንዲጣራ ስለመደረጉ እና ማስረጃም እንደተሰጠው አመልካች ከሥር ጀምሮ እየተከራከረ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን አመልካች ያቀረበውን ምክንያት ተጠሪውም ሳይመረምር ግብሩን በግምት የወሰነ ሲሆን የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሳይመረምሩ ግብሩ በግምት መወሰኑ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) መሰረት ተገቢ ነው ሲሉ ተቀብለውታል፡፡ በእርግጥ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 69(1) ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሠነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ለመወሰን እንደሚችል የተደነገገ ቢሆንም ግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ግብሩን በግምት ከመወሰኑ በፊት ግብር ከፋዩ የሂሳብ ሰነዱን ያልያዘበትን ምክንያት፣ወይም በህጉ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢውን ያላታስወቀበት ምክንያት ከህጉ ጋር አገናዝቦ በመመርመር ምክንያቱ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም "...በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ..." በሚል በድንጋጌው የሰፈረው ሐረግም ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ባለመያዙ ወይም የሂሳብ መዝገቡንና ተያያዥነት ያላቸውን የሂሳብ ሰነዶች ማቅረብ ባለመቻሉ ብቻ በቀጥታ ግብሩ በግምት እንዲወሰን የሚያደርግ ሳይሆን በቅድሚያ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው ምክንያት በማስረጃ የተደገፈ መሆን አለመሆኑን፣ ምክንያቱ በማስረጃ የተደገፈ ሆኖ ቢቀርብ እንኳን ግብሩን በግምት ከመወሰን የማይከለክል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች በድርጅቱ ላይ በደረሰው የእሳት አደጋ ንብረቱና የሂሳብ ሰነዶቹ መውደማቸውን ገልጾ እስከተከራከረ ድረስም ተጠሪው አመልካች የሂሳብ መዝገብና ተያያዥነት ያላቸውን የሂሳብ ሰነዶቹ እንዲያቀርብ ታዞ አላቀረበም በሚል ግብሩን በግምት በአዋጁ አንቀጽ 69(1)መሰረት ከመወሰኑ አስቀድሞ የአመልካች ድርጅት በእሳት የተቃጠለ ስለመሆኑ፣ የእሳት ቃጠሎ ደርሶ ከሆነም ግብር እንዲከፈል በተጠየቀው ዘመን አመልካች የያዘው የሂሳብ መዝገብ እና የሂሳብ ሰነዶች መቃጠላቸውን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን አመልካች ካሉት ተቀብሎ በመመርመር እንዲሁም ተጠሪውም ከራሱ በኩል በሚኖረው የማጣሪያ መንገድ በማጣራት ማስረጃዎቹን መዝኖ ግብሩ በግምት ሊወሰን የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመለየት የአመልካችን ክርክር የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካለው ግብሩን በግምት መወሰን ሲገባው ክርክሩንና ማስረጃዎቹን ሳይመረምር በአዋጁ አንቀጽ 69(1)መሰረት ግብሩን በግምት መወሰኑ ተገቢነት የለውም፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም አመልካች ድርጅቱ በእሳት መቃጠሉንና የዘመኑ የሂሳብ መዝገቡም ሆነ ተያያዥነት ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች በቃጠሎው ምክንያት መውደማቸውን በመግለጽ ግብሩ

በግምት ሊወሰን አይገባም ሲል ያቀረበውን ቅሬታ በመመርመር አመልካች የጠቀሰው ምክንያት መኖር አለመኖሩን በማስረጃዎች በማጣራት መወሰን ሲገባው ተጠሪው በግምት ግብሩን የወሰነው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ሲል መቀበሉም ሆነ ጉዳዩን በየደረጃ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪው የሰጠውን የግብር ውሳኔ ተገቢ ነው ሲሉ ማጽናታቸው ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች በአግባቡ ባልተረጋገጡበት ሁኔታ ከመሆኑም ሌላ የአመልካችን መሰረታዊ የሆነ የመሰማት መብት ባልተጠበቀበት ሁኔታ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ስንል ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁ/706 በቀን 21/05/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ውሳኔ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/118346 በቀን 11/04/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/86148 በቀን 13/06/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሠጠውን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና የሥር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጡት ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችሉ ፍሬ ነገሮች ባልተሟሉበት፣ ባልተረጋገጡበት እና የአመልካች የመሰማት መብት ባልተከበረበት ሁኔታ ነው ብለናል፡፡
3. በአመልካች ድርጅት ታህሳስ 23 ቀን 1998 ዓ/ም የእሳት አደጋ መድረሱን እና በ1997 ዓ/ም የግብር ዘመን አመልካች የያዘው የሂሳብ መዝገብ እና ተያያዥነት ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች በቃጠሎው ምክንያት ስለመውደማቸው የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች እንዲሁም ተጠሪውም በተቃራኒው የሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ካሉ የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመስማት እና በመመዘን ግብሩ ስለሚወሰንበት ሁኔታ በግብር ህግ አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ህጎች አንጻር ጉዳዩን መርምሮ የበኩሉን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቁጥሩ 118346 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡
- መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 92537

ግንቦት 21 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሣ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች ፡- አዞ ግሎባል ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድማገኝ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን- ኃ/መለኮት አበበ ቀረበ

## መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ጉዳዩ የጉምሩክ ሥርዓት አልተፈጸመበትም ተብሎ ለተወረሰ ንብረት የተከፈለ ታክስ እንዲመለስ በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች ከቻይና አገር ኒግቦ ኦቪል ባትሪ ኮ/ሊሚትድ ከሚባል ኩባንያ 100,800 ደርዘን ካርቶኖች የያዘ ባትሪ ወደ አገር ውስጥ አስገብቻለሁ፡፡ዕቃውን ወደ አገር ውስጥ ሳስገባ በዴክላራሲዮን ቁጥር C/D22074 ብር 473,799.65 ቀረጥ ከፍለናል፡፡ነገር ግን ከዚህ በኋላ ህገ ወጥ ተግባር ተፈፅሟል ተብሎ በወንጀል ተከሰን ዕቃው ተወርሶ እኛ በነፃ ወጥተናል፡፡ስለዚህ የከፈልነውን ብር 473,799.65 እንዲመልስ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ውርሱ የተከፈለውንም የቀረጥ ገንዘብ የሚያካት ነው፡፡ስለዚህ የምመልስበት ምክንያት የለኝም የሚልና ሌሎች ዝርዝር መከራከሪያዎች አቅርቧል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የይግባኝ ማመልከቻ አቅርቧል፡፡ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡አመልካች ነሐሴ 3 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች እንዲመልስልኝ የጠየኩት ዕቃዎች የከፈልኩትን መደበኛ የቀረጥ ገንዘብ ነው፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንን በዋስትና እንደተያዘ ገንዘብ በመቁጠር የሰጡት የህግ ትርጉም መሰረታዊ ስህተት ያለበት ሰለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለትአመልክቷል፡፡ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 7 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ አመልካች ዕቃው ህገወጥ ተግባር ተፈፅሞበታል ተብሎ ሲወረስ ፣በህጋዊ መንገድ ዕቃው የተከፈለ ቀረጥ ውርሱ መጨመር የለበትም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቹ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

በሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራቀኙ በፅሑፍ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተወረሱ ዕቃ የተከፈለው የቀረጥ ገንዘብ እንዲመለስለት ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ህጋዊ የጉምሩክ ቀረጥ ከፍየበታለሁ የሚለው ዕቃ የተያዘውና የተወረሰው፣በአመልካች መጋዘን በተደረገ ብርበራ የጉምሩክ ህግን በመተላለፍ ከገቡ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅሎ በመገኘቱ እንደሆነ ይኸ ሰበር ችሎት መዝገብ ቁጥር 64115 ጥቅምት 8 ቀን 2004ዓ/ም በሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበት ዕቃ ህጋዊ የጉምሩክ ሥርዓት ካልተፈፀመበት ዕቃ ጋር ተቀላቅሎ በተያዘ ጊዜ፣በህጋዊ መንገድ ለገባው ዕቃ የተከፈለው ታክስ እንዲመለስለት የዕቃው ባለቤት የሚጠይቅበት ህጋዊ ሥርዓት የለም ፡፡የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 104(3)(ሀ) ድንጋጌም በዚህ መንገድ እንዲተረጎምለት አመልካች ያቀረበው ክርክር አዋጅ ሊያስፈፅመው የሚፈልገውን ጠቅላላ አላማና የድንጋጌውን ይዘትና ግብ ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁጥር 91622

መጋቢት 12 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አፍሪካ ታደሰ-

**ተጠሪ፡-** 1.ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ- ታልፏል

2.የጎባ ከተማ አስተዳደር ፅ/ቤት

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሚስትነትና በወራሽነት ድርሻ አለው ተብሎ ውሳኔ ያገኘ ሰው በንብረቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት በአፈጻጸም ማመልከቻ ዳኝነት ቢጠይቅ ጥያቄው በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በጎባ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍ/ቤት የአሁኗ አመልካች የፍርድ ባለመብት የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ሁነው ተከራክረው ነበር፡፡ አመልካች በአሁኑ ተጠሪና በወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ ላይ የከፈቱት የአፈጻጸም መዝገብ በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠ ውሳኔ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቅ ሲሆን አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤትም ጉዳዩ እንዲጣራ ትእዛዝ ሰጥቶ የጎባ ከተማ ማዘጋጃ ቤትም በቁጥር 1109/2/4/184 በ14/9/2004 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ በጻፈው ደብዳቤ አመልካች እንዲፈጸምላቸው የሚጠይቁት ቤት ከሚች ባለቤታቸው ኢንስፔክተር ጥላሁን መለሰ ስም ወደ ወ/ሮ ያለምወርቅ ታደሰ (1ኛ ተጠሪ) የተዛወረ ስለሆነ የሚፈፀም ነገር የለም በማለት ገልጿል፡፡ከዚህም በኋላ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ይህንኑ ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ የአፈፃጸም ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ለተጠሪዎች ጥሪ አድርጎ 1ኛዋ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ ያደረገ ሲሆን 2ኛው ተጠሪ ግን ቀርቦ ከአመልካች ጋር ከተከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውና በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ ይዘቱ አመልካችም ሆነ ህፃኑ ድርሻቸውን

እንዲያገኙ  የሚል እንጂ ስመ ሀብቱ እንዲዛወር የሚል አይደለም፣የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በሐሰተኛ የሚስትነት ማስረጃ ስመ ሃብቱ እንዲዞር ያደረጉ መሆኑ የተረጋገጠ ነው የሚል ክርክር ቢቀርብም ይህ ማስረጃ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 መሰረት እንዲሰረዝ አልተደረገም የሚሉትን ምክንያቶችን አስፍሮ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈጻጸም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠውን ውሳኔ የሚፈፀም አይደለም በማለት የአፈጻጸም መዝገብ መዝጋታቸው አንድ ውሳኔ የሚፈጸምበትን ስርዓት ባልተከተለ መንገድ መሆኑን ዘርዝረው አከራካሪው ቤት ስመ ሃብቱ እንዲዞርላቸው አድርገው ዋናውን ውሳኔ ያስፈጽሙ ዘንድ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው 1ኛዋ ተጠሪ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛው ተጠሪ ግን በመቅረቡ ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ አመልካች በመ/ቁጥር 10883 በ26/11/2003 በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላት መሆኑ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ ድርሻዋ እንዲሰጣት ውሳኔ ተሰጥቶ እያለና ውሳኔውም ባልተሻረበት ሁኔታ ባፈፃጸም ችሎቱም ቢሆን 1ኛ ተጠሪ ንብረቱ ላይ አፈጻጸም ሊቀጥል አይችልም በሚል ያቀረቡት ተቃውሞ ሳይኖር የበታች ፍርድ ቤቶች ሊፈጸም የሚችል ነገር የለም በሚል አቤቱታውን ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል በመሆኑ ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡ይህንኑ ጭብጥ ለመመለስም በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ አስቀርበን ይዘቱን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ጠቅሰውና ይኼው መብታቸው ተረጋግጦ ዳኝነት እንዲሰጥ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የወረዳው ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ያለውን ዳኝነት ከሰጠ በኋላ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ስመ ሃብቱን በስማቸው ያደረጉት ከቤቱ ባለቤት

ውል አድርገው መሆን ያለመሆኑን፣የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ስመ ሃብቱን ከሕግ ውጪ ካዛወረ መከሰስ አለበት? ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦችን ለይቶና የአሁኗን 1ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንድትገባ አድርጎ ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን ለወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሶለት ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን 1ኛ ተጠሪ በሌለችበት አይቶና አመልካችንና 2ኛ ተጠሪን ደግሞ በተገቢው መንገድ አከራክሮና ተገቢ ነው ያለውን ሁሉ ከአጣራ በኂላ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ የሟች ኢንስፔክተር ጥላሁን መለሰ ሚስትነትን በማሳወጅ በያዙት ማስረጃ መሰረት ቤቱን ሙሉ በሙሉ በግላቸው የሚያዛወሩበት ምክንያት እንደሌለ፣ተጠሪዋ ድርሻዋን ብቻ የምታገኝ መሆኑን፣የአሁኗ አመልካች ደግሞ የሟቹ ሚስት መሆናቸው መረጋጡንና እርሳቸውም ድርሻቸውን ማግኘት ያለባቸው መሆኑን እንዲሁም አመልካች ከሟቹ የወለዱት ልጅ(ይዲድያ ጥላሁን) ደግሞ የሟቹን ድርሻ ላይ ሙሉ የወራሽነት መብት ያለው መሆኑን ገልፆና ይህንኑ ድርሻውን የማግኘት መብት የተጠበቀ መሆኑን ጠቅሶ በመ/ቁጥር 10883 ሐምሌ 26 ቀን 2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ዳኝነት መስጠቱን፣ይህ ውሳኔ በየትኛውም እርከን ባለው ፍርድ ቤት ያልተለወጠ መሆኑንና ለአፈጻጸሙ መሰረት የሆነውም ይኼው የአመልካችና የልጃቸው ድርሻ ያለበት መሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠው ውሳኔ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠ ፍርድ እንደ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተዘረጋው ስርአት አግባብ በመመራት ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ ሕጋዊ ባልሆነ እና ውሳኔውን ውጤት አልባ በሚያደርግ መልኩ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡት አቢይ ነጥብ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር ወይም ውጤት የሚለውጥበት ስርአት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የድንጋጌዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ በጥንቃቄ ሲታይም የፍርድ አፈጻጸም ስለፍርድ አፈጻጸም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የአፈጻጸም ስርአቱ ህጉን መሰረት ማድረግ ያለበትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን መሰረታዊ ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአነስተኛ ወጪ ጊዜና ጉልበት በተፋጠነና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም በሚያስችል አግባብ ሕግ አውጪ ያስቀመጣቸው መሆኑን የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ውሳኔው የማይፈፀምበት ሕጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩም በፍርድ ቤቱ ታይቶ ተገቢው እልባት የሚሰጥበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ይህ ድንጋጌ አፈጻጸሙን የያዘው ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን ምቹ ሁኔታዎች ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ በተቻለ መጠን ፍርዱ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ሊከተል የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡ስለሆነም አንድን ፍርድ እንደፍርዱ ይዘትና መንፈስ ውጤት ባለው

መልኩ መፈጸም የግድ የሚል ሲሆን ይህ ደግሞ የፍርድ አፈጻጸምን በተመለከተ በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጉት ስርዓቶች በአግባቡ በማየትና ተፈፃሚ በማድረግ የሚከናወን መሆኑን የድንጋጌዎቹ ይዘት የሚያሳይን ጉዳይ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለአፈፃጸም ማመልከቻቸው መሰረት ያደረጉትና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አያይዘው ያቀረቡት የወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10883 የሰጠውን ፍርድ ሲሆን ከላይ እንደተገለጸው በአከራካሪው ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡በአፈፃጸም ማመልከቻቸው የጠየቁት ዳኝነትም የቤቱ ስመ ሃብተ በስማቸውና የሚቹ ወራሽ መሆኑ ተረጋግጦ የሚቹን ድርሻ እንዲወርስ ለተወሰነለት አመልካች ሞግዚት ለሆኑት ሕጻን ልጅ ስም ነው፤የበታች ፍርድ ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን የአፈጻጸም ዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት በመ/ቁጥር 10883 በተሰጠው ውሳኔ ስመ ሀብት እንዲኖር ለፍርድ ባለመብቶች አልተወሰነም በሚል ምክንያት መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የምንረዳው ጉዳይ ሲሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ግን ቤቱ ወደ አሁኗ 1ኛ ተጠሪ ስም ተዛውሯል ተብሎ በማዘጋጃ ቤት በመገለጹ ብቻ የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቷል፡፡ይሁን እንጂ አመልካችና ሕጻኑ በቤቱ ላይ መብት አላቸው የሚለው የዋናው ክርክር ውሳኔ ይዘትየሚያሳየው አመልካች እና ሕጻኑ በኢ/ፌ/ዲ/ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር የተከበረውን የንብረት ባለቤትነት ያረጋገጠ መሆኑን፣ በዚሁ ውሳኔ መሰረት የቤቱ ስመ ሃብት በአመልካችና በሕፃኑ ድርሻ መጠን ላይ እንዲመዘገብ የማይደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን ነው፡፡በዚህ አግባብ ውሳኔው እንዲፈፀም ካልተደረገ ደግሞ በዋናው ክርክር በሕጉ አግባብ ተጠርተው ያልቀረቡና ድርሻቸውን ብቻ እንዲያገኙ የተወሰነባቸው የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር እንዲፈፅሙ የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ የሚታመን ነው፡፡በመሆኑም አመልካች በቤቱ ላይ መብት እንዳላቸው በዋናው ውሳኔ ተረጋግጦላቸውና በ1ኛ ተጠሪም ስመ ሃብቱ ሙሉ በሙሉ የተመዘገበው ያላግባብ መሆኑን በመ/ቁጥር 10883 የተሰጠው ውሳኔ በግልጽ የሚያሳይ ሁኖ እያለና 1ኛዋ ተጠሪም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 386 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር በፍርድ ኃይል የተረጋገጠውን የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት ዋጋ የሚያሳጣ የአፈጻጸም ትእዛዝ መስጠት ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ 2ኛ ተጠሪም በዋናው ክርክር ተሳታፊ ሁኖ የአመልካችንና የህፃኑን ድርሻ በ1ኛ ተጠሪ ስም እንዲመዘገብ ማድረጉ ተገቢ ያለመሆኑን በሚያስገነዘብ መልኩ በዋናው ጉዳይ ተወስኖበት እያለ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ስመ ሃብቱ በ1ኛ ተጠሪ ተዛውሯል በማለት በአፈጻጸም ጊዜ ለፍርድ ቤቱ በመግለፁ ብቻ የአፈፃፀም መዝገብ የሚዘጋበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ምክንያቱም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና 1196 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ሲነበቡም የአስተዳደር አካል በባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አሰጣጥ ላይ

ፍጹም የሆነ አስተዳደራዊ ስልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሳዩም፡፡ይልቁንም ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከፍ/ሕ/ቁጥር 1198 ድንጋጌ ጋር ተዛምደው ሲታዩ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የሚሰረዘው በሕጉ በተመለከቱት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን ከሕጉ ውጪ ተግባሩ ተከናውኖ ከተገኘም መብቱ የተነካው ሰው በኢ/ፌ/ዲ/ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37፣78 እና 79 ድንጋጌዎች መሰረት ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ አቤቱታው እንዲታይለት የሚያደርግበት ጉዳይ እንጂ አስተዳደር አካሉ የሰጠው ውሣኔ በፍርድ ቤት እንዳይታይ የሚገደብበት ስርአት የሌለ መሆኑን የምንገነዘበው ነውና፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ በሚስትነታቸው ባገኙት ማስረጃ መሰረት የቤቱን ስመ ሃብት እንዲዞር ባደረጉበትና ይኼው ማስረጃ ባልተሰረዘበት ሁኔታ የስመ ሃብት ምዝገባ ጥያቄ በአመልካች መቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 998 ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የለውም በማለት በፍርድ ላይ ያሰፈረው ምክንያትም ቢሆን በዋናው ክርክር ጊዜ 1ኛ ተጠሪ ስመ ሃብት እንዲዞር ማድረግ የሚችሉት በሚስትነታቸው ባላቸው ድርሻ ብቻ ነው ተብሎ የተወሰነውን የውሳኔ ክፍል ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነው፡፡በመሆኑም የ1ኛ ተጠሪ የሚስትነት ማስረጃ ያለመሰረዝ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በድርሻቸው ብቻ እንጂ በአመልካችና በሟቹ ኢንስፔክተር ድርሻ ጭምር አይደለም፡፡አመልካችም ሆነ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ድርሻ አላቸው ከተባለም ድርሻቸው ምን ያህል ነው?፤በቤቱ ግማሽ ነው ወይስ ከሟቹ ጋር ሶስቱም እኩል? የሚለው የሟቹን ድርሻ ህፃኑ እንዲወርስ ተብሎ ከተወሰነው የውሳኔ ክፍል እና አግባብነት ካላቸው የህገ መንግስት እና ከክልሉ የቤተሰብ ህግ ድንጋጌዎች ጋር ተገናዝቦ በአፈፃፀሙ ጊዜም ቢሆንም ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥበት ጉዳይ ነው፡፡ይህም አካሄድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 392 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪዎች በዋናው ጉዳይ በፍርድ ቤት በነበረው ክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጎ 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ ተገቢ ነው ያለውን ክርክር አቅርቦ አመልካችና ሕጻኑ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ በተወሰነበት ሁኔታ በዋናው ጉዳይ ስመ ሃብቱ እንዲዞር አልተወሰነም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ መዘጋቱ ከላይ የተመለከቱትን ሕጋዊ ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ባላገናዘበ መንገድ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አፈፃጸሙ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በጎባ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 13408 ግንቦት 14 ቀን 2004ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝና ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት በባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14585 ጥቅምት 06 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች እና ህፃን ይዲድያ ጥላሁን መለሰ በዋናው ክርክር በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም በድርሻቸው ብቻ ስመ ሃብቱን ማስመዝገብ ሲገባቸው በቤቱ ላይ ሙሉ መብት እንዳላቸው ተደርጎ ስመ ሃብቱ መዞሩ ተገቢነት የሌለው መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በቤቱ ላይ 1ኛ ተጠሪ ስመ ሃብት ማዞራቸው አፈጻጸሙን ለማስቆም በቂ ምክንያት አይደለም ብለናል፡፡በዚህም ምክንያት አመልካች በራሳቸውና በህፃኑ ድርሻ ስመ ሃብቱ እንዲመዘግብላቸው ያቀረቡት የአፈጻጸም ጥያቄ ተገቢ በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት አፈጻጸሙን በመ/ቁጥር 13408 ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ እንዲያስፈፅም ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መዘገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 94571

ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ የልፍኝ መኮንን
2. ቄስ ደርሰህ መኮንን
} ጠበቃ አቶ ባንተአምላክ ብናልፈው ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአባ መኮንን እጅጉ ወራሽ አቶ ዘርሁን መኮንን ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ሆኖ አፈፃፀሙን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤትም የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካቾች የአፈፃፀምከሳሾች ደግሞ የአፈፃፀም ተከሳሽ ነበር፡፡

ለፍርድ አፈፃፀሙ ክርክር መነሻ የሆነው ፍርድ የተሰጠው በፌዴራሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 69209 የካቲት 27 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የወቅቱ የቤቱ ግንባታ ዋጋ በወራሾች መካከል የእኩልነት መብትን ስለሚያረጋግጥ የሚያከራክረው የውርስ ንብረት ወይም ቤት ለክፍፍል በሚቀርብበት ወቅት በሚኖረው የገበያ ዋጋ መሰረት ግምቱ ሲቀርብ አመልካቾች (የአሁኑ አመልካቾች)የግምቱን ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ የሚል ነው፡፡ይህ ውሳኔው በአሁኑ አመልካቾች አማካኝነት በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከ/ፍ/ቤት ለአፈፃፀም ቀርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ የአሁን ተጠሪን አስቀርቦ አስተያያቱን ከጠየቀ በኃላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረት ለማስፈፀም ይችል ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት ምን ያክል እንደሆነ ግምቱ በደብረ ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት በኩል በባለሙያ ተገምቶ ውጤቱ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት በብር 39,119.09 ተገምቶ መቅረቡን የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ግልባጭ የሚያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱም በበኩሉ የቤቱ

ጨረታ መነሻ ግምት ብር 39,119.09 መሆኑ ታውቋል በማለት ለአፈጻጸሙ መነሻ በሆነው ውሳኔ መሰረት የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ለማወቅ ይቻል ዘንድ የፍ/ቤቱ ተወካይ በተገኙበት ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ የጨረታ አሸናፊ የሆነው ዋጋ ታውቆ ለፍ/ቤቱ እንዲገለፅ የሚል ይዘት ያለው ትዕዛዝ ሰጥቶ ውጤቱን ለመጠባበቅም ቀጠሮ ለሐምሌ 2 ቀን 2004 ዓ/ም ይዟል፡፡

የአሁኑ ተጠሪም በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በበኩሉ ቅሬታውን መርምሮ በሰጠው ትዕዛዝ ፡- በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው እንጂ የጨረታው የመጨረሻ ውጤቱ የታወቀ ስላልሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሀ/ቁ 320(3) መሰረት የይግባኝ አቤቱታ ሊቀረብበት የሚችል አይደለም በማለት ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡ሆኖም ግን ቀጥሎ በአሁኑ ተጠሪ አመልካችነት ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአከራካሪው ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ መሰረት በደ/ማርቆስ ኢንዱስትሪ ልማት ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ብር 39,119.09 መሆኑ ተገምቶ ውጤቱ ቀርቦ እያለ የስር ፍ/ቤት ቤቱ በጨረታ ተሸጦ ክፍፍሉ እንዲፈፀም በማሰብ የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ መስጠቱ ለአፈፃፀም መነሻ የሆነውን ውሳኔ (በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን)ሙሉ ይዘት ያገናዘበ አይደለም የሚል ምክንያት ጠቅሶ የስር ፍ/ቤቱን ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሀ/ስ/ስ/ቁ 348(2) መሰረት በመሻር የአሁኑ ተጠሪ ተገምቶ በቀረበወ "የቤቱ ገበያ ዋጋ ግምት ብር 39,119.09" መሰረት ግማሹን ብር 19,559.55 ለአሁኑ አመልካቾች ይከፈል ሲል ወስኗል፡፡

አሁን በአመልካቾች የቀረበው የሰበር አቤቱታም ይሄንኑ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- የቤቱ ገበያ ዋጋ ግምት የሚታወቀው ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት በማድረግ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የጨረታ ማስታወቂያውን ያወጣው በዚሁ መሰረት የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ለማወቅ እንዲቻል እንጂ ቤቱ ተሸጦ ከተጠሪ እጅ እንዲወጣ በማሰብ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ትዕዛዝ ሽሮ የውርስ ንብረት ድርሻችንን በባለሙያ ግምት መሰረት ግማሹን ገንዘብ እንድንቀበል በማለት የሰጠው ውሳኔ ለአፈፃፀም መነሻ የሆነው ውሳኔ ይዘት በትክክል ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ መብታችንም በእጅጉ የጐዳ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ 3ኛ ወገን በሚያቀርበው የገበያ ዋጋ መሰረት ግማሹ እንዲከፈለን የሚያደርግ ውሳኔ ይሰጠን የሚል ነው፡፡

አቤቱታውም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 69209 ለክርክሩ መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት በወራሾች መካከል በእኩል ክፍፍሉ እንዲፈፀም

በሚያስችል መልኩ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግማሽ ድርሻ አመልካቾች እንዲያገኙ በማለት ከሰጠው ውሳኔ አንፃር የክልሉ ሰበር ችሎት ያሳለፈውን ውሳኔ ተገቢነተ ለማጣራት ሲባል አቤቱታው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጐ ተጠሪም ቀርቦ የበኩሉን መልስ በፅሁፍ ሰጥቷል፡፡ይዘቱም ባጭሩ፡- የክልሉ ሰበር ችሎት አመልቾች ድርሻቸውን እንዲያገኙ የወሰነው የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት መሰረት ባደረገ መልኩ ስለሆነ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን ሰጥተውበታል ፡፡

የጉዳይ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በበኩላችን የአንድ ንብረት የገበያ ዋጋ ግምቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚወሰነው ወይም የሚታወቀው በምን አግባብ ነው?የሚለውን በጭብጥነት ይዘን ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የውርስ ሀብት ወይም ቤት ግምት ግማሹን ድርሻ ለአመልካቾች ከፍሎ ቤቱን በቀዳሚነት ለራሱ እንዲያስቀር ተብሎ አስቀድሞ የተወሰነ በመሆኑ አመልካቾች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ የለም፡፡እንዲሁም ግምቱን በተመለከተም የውርስ ሀብቱን በወራሾች (በግራ ቀኙ )መካከል በእኩል ለማከፋፈል በሚያስችለው መልኩ በወቅቱ ገበያ የዋጋ መሰረት ግምቱ ሲቀርብ አመልካቾች የግምቱን ግማሽ ድርሻ እንዲያገኙ ተብሎም ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ 69209 በሆነው ላይ በግራ ቀኙ መካከል የስረ ነገር ክርክርን አስመልክቶ በቀረበው ጉዳይ ላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኗል፡፡ሆኖም ግን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ የውርስ ሀብቱ የገበያ ዋጋ በምን አግባብ ሊቆረጥ ወይም ተወስኖ ሊታወቅ እንደሚችል በግልፅ አለማመላከቱን ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ በተጠቀሰው ውሳኔ ይሄንን ጉዳይ በግልፅ ባያመለክትም በሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ ግን በተለይም በሰበር መ/ቁ 37297 እና 37298 ላይ የአንድ ንብረት ወይም ቤት የወቅቱ የገበያ ዋጋ ሊቆረጥ የሚችለው ከተቻለ በስምምነት ይህ ካልተቻለ ደግሞ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣው ከፍተኛ ዋጋ መሰረት መሆኑን በአዋጅ ቁ 454/97 አንቀጽ 2(1) ድንጋጌ መሰረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ይህ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔም ለዚህ ለተያዘው ጉዳይም አግባብነት ያለው ሆኖ ስላገኘን አመልካቾች የውርስ ሀብቱን ግማሽ ድርሻቸውን የወቅቱን የገበያ ዋጋ ግምት ተቆርጦ ወይም ታውቆ ሊከፈላቸው የሚገባው በዚህ መሰረት ሆኑ አግኝተነዋል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ተመልክቶ ውሳኔ መስጠት ሲገባ በደ/ማርቆስ ከተማ አገልግሎት ፅ/ቤት ባለሙያ ተገምቶ የቀረበውን የቤቱን ግምት የገበያ ዋጋ ግምት  እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ እና አመልካቾች በዚህ መሰረት ግማሽ ድርሻቸውን ብር 19,559.55 እንዲያገኙ በማለት የሰጠው ውሳኔ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. 1.የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 25073 በ5/02/06 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. 2.የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለአፈፃፀሙ መሰረት በሆነው ውሳኔ መሰረት ለማስፈፀም እንዲቻል የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት ተለይቶ እንዲታወቅ ይቻል ዘንድ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ አሸናፊ የሆነው ከፍተኛ ዋጋ ለፍ/ቤቱ ይገለፅ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የሚነቀፍ ባለመሆኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት የአፈፃፀም መ/ቁ 18328 በማይንቀሳቀስ እና ግራ ቀኙ ተጠይቀው የቤቱ የወቅቱ የገበያ ዋጋ ግምት በስምምነት ሊቆረጥ ካልተቻለ ቤቱ ለጨረታ ቀርቦ በሚያወጣ ከፍተኛ ዋጋ መነሻ በማድረግ ተጠሪ ግማሹን ለአመልካቾች እንዲከፍል እንዲደረግ ብለናል፡፡
4. 4.ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የ/ባ

የሰ/መ/ቁ. 92035

የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ.ማ. ዓድዋ ቅርንጫፍ - ነ/ፈጅ ጥላሁን ይህደጐ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ሐጎስ ተስፋይ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ክበይ ገ/ሊባኖስ - ተወካይ ሐጐስ ተስፋይ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለፍርድ ማስፈጸሚያ የቀረበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመጀመሪያ የሐራጅ ሽያጭ የሚቀርብበትን የዋጋ ግምት አስመልክቶ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አፈጻጸሙ በተጀመረበት የዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁኖቹ አመልካች እና ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸው የፍ/ባለመብት እና የፍ/ባለዕዳዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን አመጣጥ እና ሂደት በተመለከተ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የብድር ውል መሰረት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ለሰጠው የብር 275,165.73 ፍርድ የፍርድ ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ ለብድር ውሉ በመያዣነት የያዝኩት ነው ያለውን የተጠሪዎች ንብረት የሆነ ቤት(ሕንፃ) ለአፈጻጸም መምራቱን፣ ቤቱ አመልካች በጠየቀው መሰረት በከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲገመት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ግምቱ ብር 1,525,354.85 መሆኑ መገለጹን፣ ግምቱ በቀረበበት በ26/04/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት የቀረበው ግምት የተጋነነ በመሆኑ በገልተኛ መሐንዲስ እንደገና ተገምቶ እንዲቀርብ እንዲታዘዝለት አመልካች ጥያቄ ማቅረቡን፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ እስካልተስማሙ ድረስ ግምቱ በሌላ መሐንዲስ እንደገና እንዲከናወን ሊደረግ የሚችልበት አግባብ

አለመኖሩን እና በሌላ መሐንዲስ ተገምቶ የሚቀርበው ውጤት የተለየ ከሆነ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው ግምት የየትኛው መሀንዲስ ወይም ባለሙያ እንደሆነ መወሰኑ አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልጾ የዳግም ግምት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ፣ በሌላ በኩል ግን ሕንፃው በመንገድ ስራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑ መገለጹን ጠቅሶ የጉዳቱ መጠን በዓድዋ ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪና መሬት ልማት ጽ/ቤት ተገምቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን፣ በትዕዛዙ መሰረትም የጉዳቱ መጠን ብር 54,000.35 መሆኑ መገለጹን፣ ይህ ውጤት መቅረቡ በተመዘገበበት በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ተጠሪዎቹ ገንዘቡን ለመክፈል የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጣቸው፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀረበው ግምት መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን፣ አመልካች የተጨማሪ ጊዜ ይሰጠን ጥያቄውን በመቃወሙ ፍ/ቤቱ በመንገድ ስራ ምክንያት በሕንጻው ላይ ደርሷል የተባለውን ጉዳት የዋጋ ግምት ቀደም ሲል ከማዘጋጃ ቤት ከተገለጸው የሕንፃው የዋጋ ግምት ቀንሶ በተገኘው ውጤት መሰረት ሕንጻው በብር 1,471,354.40 የዋጋ ግምት በሐራጅ ሽያጭ እንዲቀርብ በዚያው በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ትዕዛዝ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ሕንጻው በገለልተኛ መሐንዲስ ወይም ባለሙያ በድጋሚ እንዲገመት አመልካች ያቀረበው ጥያቄ ውቅድ ተደርጎ የሐራጅ ሽያጩ የተጋነነ ነው በተባለው የዋጋ ግምት እንዲቀጥል በተሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት አመልካች ለክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ያቀረበው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ እንደቅደም ተከተሉ በፍርድ እና በትዕዛዝ ተቀባይነት በማጣቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች የንብረቱ የዋጋ ግምት የተጋነነ ነው በማለት ያቀረበው ተቃውሞ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በማዘጋጃ ቤት የቀረበው የሕንፃው ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ግምቱ በድጋሚ በሌላ ገለልተኛ መሐንዲስ ወይም ባለሙያ እንዲከናወን እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች ተቀባይነትን ያገኘው የዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ በትክክለኛ ሁኔታ መገለጽ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና የግምቱ ልክ መሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 423(2)(ሀ) ስር የተደነገገ ሲሆን የድንጋጌው ዓላማም የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛ የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በዚህ ሳቢያ በፍ/ባለገንዘቡም ሆነ

በፍ/ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመከላከል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍ/ቤቱ በማስታወቂያው ላይ የሚሰፍረውን የንብረቱን የዋጋ ግምት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚችል የሚሸጠውን ዓይነት ንብረት ለመገመት ልዩ ችሎታ ያለውን ኤክስፐርት በማዘዝ ንብረቱ እንዲገመት ለማድረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 424(2) ላይ የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሐራጅ ሽያጭ ትዕዛዝ የተሰጠበት የፍ/ባለዕዳዎች ቤት በፍ/ባለመብቱ ጥያቄ በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች በኩል በብር 1,525,354.85 የተገመተ ሲሆን አመልካች ይህ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት ይደረግ ዘንድ ያቀረበውን አቤቱታ የወረዳው ፍ/ቤት ሳይቀበለው የቀረው ከላይ እንደተገለጸው ሁለቱ ወገኖች እስካልተስማሙ ድረስ ቤቱ በድጋሚ ሊገመት የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን እና ይገመት ቢባል እንኳ የሚቀርበው ግምት ከበፊቱ የተለየ ከሆነ ተቀባይነት የሚኖረው የትኛው ግምት እንደሆነ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱ ወገኖች እስካልተስማሙ ድረስ ቤቱ በድጋሚ ሊገመት የሚችልበት አግባብ የለም በማለት በፍ/ቤቱ የተያዘው አቋም ሕጋዊ መሰረት የሌለው እና ፍ/ቤቱም የዚህ ዓይነት አቋም ለመያዝ ያስቻለውን ድንጋጌ በትዕዛዙ ላይ ያልጠቀሰ ከመሆኑም በላይ ቤቱ በድጋሚ በሌላ አካል ወይም ባለሙያ ተገምቶ የሚቀርበው ግምት ከበፊቱ የተለየ ከሆነ እንደየገማቹ አካል ወይም ባለሙያ ደረጃ እና ማንነት ከሁለቱ ግምቶች ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባው የትኛው ግምት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተገቢውን ትዕዛዝ ይሰጥበት የሚችል በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት አመልካች ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት ይደረግ ዘንድ ያቀረበውን አቤቱታ ላለመቀበል የሰጠው ምክንያት ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በማዘጋጃ ቤት በኩል ቤቱ እንዲገመት የጠየቀው የፍ/ባለመብቱ ራሱ በመሆኑ በጥያቄው መሰረት ተሰርቶ የቀረበውን ግምት መልሶ ሊቃወም አይችልም በማለት በይ/ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘውን አቋም በተመለከተ የቀረበው ግምት የተጋነነ ስለመሆኑ የፍ/ባለመብቱ ያቀረበው መከራከሪያ አሳማኝ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የግምቱ ስራ የተከናወነው የፍ/ባለመብቱ በጠየቀው አካል የመሆኑ ጉዳይ ብቻውን የፍ/ባለመብት ንብረቱ በሌላ ባለሙያ በድጋሚ እንዲገመት ጥያቄ ከማቅረብ ሊከለክለው የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡

በሌላ በኩል በወረዳው ፍ/ቤት በነበረው የአፈጻጸም ክርክር በ08/05/2005 ዓ.ም. በነበረው ችሎት ተጠሪዎቹ ገንዘቡን ለመክፈል የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጣቸው፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን በቀረበው ግምት መሰረት የሀራጅ ሽያጩ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን ተጠሪዎቹ አሁንም ድረስ የቤቱ ግምት የተጋነነ ስላልሆነ በግምቱ መሰረት

የሐራጅ ሽያጩ ሊቀጥል ይገባል በሚል ከመከራከር በስተቀር ግምቱ የተጋነነ አይደለም የሚሉ ከሆነ ጠይቀው በነበረው መሰረት ቤቱን በራሳቸው ሸጠው ከቀረበው የቤቱ ግምት አንፃር ሲታይ አነስተኛ የሆነውን ዕዳቸውን ለመክፈል ስላልቻሉበት ምክንያት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህም በማዘጋጃ ቤቱ ተሰርቶ የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ በመሆኑ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ አካል ወይም ባለሙያ ሊገመት ይገባል በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ምክንያታዊ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

ሲጠቃለል በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ካለበቂ ምክንያት ውድቅ በማድረግ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በከተማው ማዘጋጃ ቤት መሐንዲሶች የቀረበው የቤቱ ግምት የተጋነነ መሆኑን ገልጾ ቤቱ በሌላ ገለልተኛ ባለሙያ እንዲገመት እንዲደረግ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06471 በ08/05/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በዓድዋ ከተማ ከ/ፍ/ቤት እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመ.ቁ 03638 በ06/07/2005 ዓ.ም. እና በመ.ቁ 59337 በ13/10/2005 ዓ.ም. በውሳኔ እና በትዕዛዝ የፀናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለአፈጻጸሙ የተመራው የፍ/ባለዕዳዎች ቤት የግምት ስራ የማከናወን ስልጣን እና ሙያ ባለው የክልል ቢሮ ወይም የግምቱን ስራ የማከናወን በሚችል ሌላ ባለሙያ ወይም አካል አማካይነት በድጋሚ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የሚቀርብለትን ግምት ከቀዳሚው ግምት ጋር በማገናዘብ እና የግራ ቀኙን አስተያየት ጭምር በመቀበል በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ላይ መገለጽ የሚገባውን የቤቱን የዋጋ ግምት በተመለከተ ተገቢውን ትዕዛዝ በመስጠት የሐራጅ ሽያጩን እንዲያስቀጥል ጉዳዩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ለዓድዋ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
3. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለወረዳው ፍ/ቤት ይላክ፡፡ ለዓደዋ ከተማ ከ/ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስትዳኞችፊርማ አለበት

ዘቢ

የሰ/መ/ቁ. 97206

ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ አማረ መልካሙ ራሳቸው ቀረቡ በVC ከመቐለ

ተጠሪ፡- አቶ ካሌብ ሕሉፍ የቀረበ የለም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ በሰበር ችሎቱ ሊወሰን ይገባል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አመልካች የተጠሪ ንብረት የሆነውን በትግራይ ክልል ኮንስትራክሽንና መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ካላቸው ገንዘብ 612,2005.57 ብር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 154/ለ/ መሠረት ማሳገዳቸው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያረጋግጥላቸዋል ወይ? የሚለው ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ ተከትሎ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ በአመልካች ጠያቂነት ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ የነበረው ገንዘብም አሳግዷል፡፡ አመልካች ገንዘቡን ካሳገዱ በኋላ አሥራ ሰባት የፍርድ ባለገንዘቦች ከተወሰነ ቀን በኋላ በተመሳሳይ መንገድ የተጠሪ ገንዘብ ላይ ዕግድ እንዲሰጥ አመልክተው በፍርድ ቤት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አመልካች በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 14044 ባቀረቡት ክስ ያሳገዱትን ገንዘብ በቅድሚያ ለእሳቸው እንዲከፈል ጠይቋል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ለክርክር መነሻ የሆነውን ሀብት ገንዘብ መሆኑን መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ከመሆኑ አኳያ እንደማይንቀሳቀስ ንብረት የማይወሰድ ነው፡፡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደው ገንዘብ ለፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን (በሬሽዎ) እንዲከፋፈል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተፈጽሟል ያሉትን የሕግ አተረጓጐም ስሕተት በመዘርዘር የሰበር አቤቱታቸውን በ26-05-2006 ዓ.ም አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው መሠረታዊ ይዘት የፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው ማሳገዳቸውን መሠረት ተደርጐ የቀደምትነት መብት እንዲከበርላቸው፤ የቀደምትነት መብት በማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ ሳይሆን በሚንቀሳቀስ ንብረትም ማቋቋም እንደሚቻል፤ የሥር ፍርድ ቤቶችም ክፍያ ማስፈጸም ያለባቸው የፍርድ ባለገንዘቦች ገንዘቡን ባስከበሩበት ቅደም ተከተል ሊሆን እንደሚገባ በመጥቀስ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲታረም ጠይቋል፡፡ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸው ቢሆንም በአድራሻቸው ስላልተገኙ በፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ በሚለጠፍ መጥሪያ መሠረት እንዲቀርቡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባለ መቅረባቸው በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ገንዘብ ላይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማስከበራቸው የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረው ነገር ገንዘብ ነው፡፡ የፍርድ ባለገንዘብ በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ የቀደምትነት መብት በጋራ የንብረት ባለሀብቶች፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንደውሳኔውን ለማስፈጸም እንዲሁም ግራቀኙ ባደረጉት ስምምነት ሊቋቋም እንደሚችል ከፍ.ሕ.ቁ. 3043፣3044 እና 3045 ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት ሊቋቋም የሚችለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2825 በሚያዘው አግባብ የፍርድ ባለዕዳው ንብረቱን ለፍርድ ባለገንዘብ ማስረከቡ ሲረጋገጥ መሆኑን ከሕጉ ንባብ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች የቀደምትነት መብት እንዲሰጣቸው መሠረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154/ለ/ ነው፡፡ የዚህ ሕግ አንቀጽ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ ስንመለከተው በክርክር ላይ ባሉ ጉዳዮች የፍርድ ባለገንዘብ በመጨረሻ የረታ ከሆነ ፍርዱን ለማስፈጸም የሚያስችል ንብረት ወይም ገንዘብ እንዳይታጣ ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154 ርዕስ እንደምንረዳው የማገድ ትዕዛዙ የሚሰጠው ለጊዜው ስለመሆኑ፤ በፍርድ ባለዕዳ ሥር ያለው ንብረት በየትኛው መልኩ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ፤እንዳይበላሽ፤እንዳይጠፋ ፍርድ እስከሚሰጥ ተከብሮ እንዲቆይ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው፡፡ አመልካች ከላይ በተገለጸው አግባብ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ማሳገዳቸው በማይንቀሳቀስና በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋም በሚያስችል አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት አግኝቷል ወይ? የሚለውን የክርክር ነጥብ በአግባቡ መታየት

አለበት፡፡ ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ከፍርድ በፊት በማይንቀሳቀስ ሆነ በሚንቀሳቀስ ንብረት የቀደምትነት መብት ማቋቋማቸው የሚገልጽ ነገር አላቀረቡም፡፡ አመልካች በእጃችን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ነው በማለት የጠቀሱት የሕግ አንቀጽ 2860 ከላይ በጠቀስነው አግባብ መያዣ/Pledge/ ያቋቋሙ የፍርድ ባለገንዘቦች ያላቸው መብት የሚያመለክት እንጂ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች የቀደምትነት መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማቋቋማቸው የገለጹ ቢሆንም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.154/ለ/ ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ስንመለከተለው ከዚህ የተለየ ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ንብረት ለማስከበር የሚቀርብ ማመልከቻ ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 379 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ዓይነቱን በመለየት ማቅረብ ግዴታ መሆኑን፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ ንብረቱን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶች መገለጽ እንዳለባቸው ንብረቱ የሚለየው በአካባቢው ውስጥ ወይም ርስተመዝገብ ከሆነ በተራ ቁጥር በሆነ ጊዜ የወሰኑ ምልክት ወይም በመዝገብ ላይ የተሰጠው ቁጥር መግለጽ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ማድረጋቸው ከላይ በተገለጸው አግባብ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ አንድ የፍርድ ባለገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154/ለ/ መሠረት የንብረት ዕግድ ቢያሰጥ የቀደምትነት መብት የሚያቋቁም ስለመሆኑና አለመሆኑ ከአሁን በፊት የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 29269 እና 27808 የሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች ተመልክተናል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማድረግ ብድር በመስጠታቸው ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች የቀደምትነት መብታቸው የነፈገ ውሳኔ በመስጠታቸው የእነዚህ አበዳሪ ተቋማት መብት የሚያስጠብቅ ውሳኔ መስጠቱ የሚያስረዱ ናቸው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች በተናጠል ሲንመለከታቸው በሰ.መ.ቁ 27808 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ግለሰቦች ሲከራከሩ በመያዣ የያዘው ቤት በማሳገዳቸው ዕግዱ እንዲነሳ ሲጠይቅ ጣልቃ ገብተህ አልተከራከርክም ዕግዱ አይነሳም የሚል ውሳኔ በመስጠቱ በቀረበው አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በሌላ በኩል በሰ.መ.ቁ 29269 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አስቀድሞ ንብረት ማስከበሩ ብቻውን የቀደምትነት መብት አያሰጥም ማለታቸው ከሕግ የመነጨ የቀደምትነት መብት የነፈገ ነው ተብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ በእነዚህ ሁለት የሰበር ውሳኔዎች አሁን በእጃችን ካለው ጉዳይ ያላቸው ተመሳሳይነት እንደተመለከትነው ከላይ የተጠቀሱ ተቋማት የቀደምትነት መብታቸው በማይንቀሳቀስ ንብረት ያቋቋሙት የቀደምትነት መብት የነበረ መሆኑ የሚያሳይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ያቀረቡት ጉዳይ ግን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ

154/ለ/ መሠረት በአንድ የመንግሥት ተቋም የተያዘው የሚንቀሳቀስ ገንዘብ የሚመለከት በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የላቸውም።

የቀደምትነት መብት በሕግ፣ በውል ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ /ውሳኔ/ የሚቋቋም ስለመሆኑ ከላይ በተገለጸው የፍትሐብሄር ሕግ ተመልክቷል። አመልካች በፍርድ ባለዕዳ ላይ አስፈርደው ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ቀድመው የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ ማግኘታቸው ከሕግ፣ ውል ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ የመነጨ የቀደምትነት መብት አቋቁመዋል ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት የላቸውም።አመልካች በተጠሪ ገንዘብ የሰጡት የዕግድ ትዕዛዝ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የተሻለ መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ አይደለም ከተባለ፤ቀጥሎ የሚነሳውን ጥያቄ በተራ የፍርድ ባለመብቶች መካከል ያለው የክፍፍል ሥርዓት ምንመሆን አለበት የሚል ነው።ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው አመልካችን ጨምሮ በተጠሪ ገንዘብ ላይ 18 ግለሰቦች የዕግድ ትዕዛዝ አሰጥቷል።ከአንድ በላይ የፍርድ ባለመብቶች ባሉበት ጊዜ የሀብትና የንብረት ክፍፍል ሥርዓት ምን መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.403 ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ማየቱ ተገቢ ይሆናል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት የፍርድ ባለገንዘቦች ተቀማጭ የሆነውን ሀብት በውሳኔው መሰረት እንዲከፋፈሉ እንደሚደረግ ተመልክቷል። አመልካች በተጠሪ ገንዘብ ላይ ቀድመው የዕግድ ትዕዛዝ ማሰጠታቸው ግልጽ ቢሆንም ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦችም በተከታታይ ቀናት ይህንን የማሳገድ ተግባር አከናውነዋል።አመልካች ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች የቀደምትነት መብት ያልተሰጣቸው ከሆነ ሁሉም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ ገንዘብ ጠያቂዎች የሁሉም መብት እኩል እንደሆነ የሕግ ግምት ይወሰዳል።

ከላይ እንደተገለጸው አንድ የፍርድ ባለገንዘብ ከሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች አስቀድሞ የባለዕዳውን ንብረት በማስከበሩ ምክንያት ብቻ የቀደምትነት መብት አይሰጠውም።በመሆኑም የፍርድ ባለገንዘቦች እንደተራ የፍርድ ባለመብቶች ተወስደው ደረጃቸው(መብታቸው)እኩል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ ስሌት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ ማድረጉ የሕግ መሰረት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.403 ይዘት ዓላማና መንፈስ የምንረዳው ነው።ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ባለገንዘቦች በፍርድ ባለዕዳው ላይ ያላቸው የገንዘብ መጠን በሬሾዎ እንዲከፋፈሉ ትዕዛዝ መስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ባለመገኘቱ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

ው ሣ ኔ

1. የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.14044 በ25/04/2006 የሰጠው ብይን፤የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 6365 በ12/05/2006 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች እና ሌሎች የፍርድ ባለገንዘቦች ባስፈረዱት መጠን ገንዘብ መቶኛ ስሌት (ሬሾዎ)ድርሻ ድርሻቸውን ይከፋፈሉ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ 101271

ሐምሌ 30 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** መምህር ግዛቸው ጥሪት - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወሎ ዩንቨርስቲ አያና ስማቸው - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ወሎ ዩንቨርሲቲ ቦርድ የሰጠው የዲሲፕሊን ውሳኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ያቀረብኩትን የይግባኝ ቅሬታ በፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳዳር ፍርድ ቤት እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ወሎ ዩንቨርሲቲ ቦርድ የሰጠውን የዲስፕሊን ውሳኔ፣ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚታይና የሚታረም መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያለአግባብ የተማሪዎቹን ውጤት ቀይሯል ወይም ውጤት ሞልቷል በሚል መንገድ የቀረበውን የዲሲፕሊን ክስ፣ በዩኒቨርሲቲው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ከቀረበለት በኋላ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ አመልካች ከሥራ እንድሰናበት የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው፣ ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት በድምጽ ብልጫ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በሰጠው

ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበውን ይግባኝ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

2. አመልካች የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ድንጋጌዎች ያገናዘበ አይደለም፡፡ ውሳኔው አመልካች በሕገ መንግስት የተረጋገጠለትን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብ ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ መንግስት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት ለማረጋገጥ በአዋጅ የሰጣቸውን ሥልጣን ያገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይቀርብበት በመሆኑ፣ አመልካች የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይቀርብበት በመሆኑ አመልካች የዩኒቨርስቲው ቦርድ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ የሰበር አቤቱታውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ማቅረብ ሲገባው ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ለሌላቸው አካላት ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ይዘት ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

4. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለዚህ ሰበር ችሎት አከራካሪ ጭብጥ ሆኖ የቀረበውን የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው የሚለውን የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የሰጡት የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ኀ)የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ

መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመሥጠት ስልጣን ያለው መሆኑን በግልጽ ደንግጓል በማለት ነው፡፡

5. ይህም የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ኀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪው ከልካይና የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ሰራተኞች እንደማንኛውም መንግስት ሰራተኛ ፣ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የበላይ አመመራር አካል የሆነው የዩኒቨርስቲው ቦርድ፣ የሚሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤትና ደረጃውን ጠብቀው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የማይችሉ መሆኑን የሚደነግግ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ለድንጋጌው ትርጉም መስጠት የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ኀ) መሰረታዊ ባህሪና ዓላማ እንደዚሁም ድንጋጌው በአካዳሚክ ሰራተኞች የይግባኝ መብት ላይ የሚኖረውን ሕጋዊ ውጤት ለመረዳት የድንጋጌውን የተናጠል የቃል በቃል ንባብ ማየት ብቻዉን በቂ አይደለም፡፡

6. የአዋጁን አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ኀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪና ዓላማ እንደዚሁም፣ ድንጋጌው በአካዳሚክ ሰራተኞች የይግባኝ መብት ላይ የሚኖረው ሕጋዊ ውጤት ለመገንዘብ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሊያከብራቸውና ሊመሩባቸው የሚገቡ ቋሚና መሰረታዊ እሴቶች፣ በአዋጁ የተረጋገጠውን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ነጻነት ይዘትና የአካዳሚክ ሰራተኞች ስላላቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አደረጃጀትና የዩኒቨርሲቲው ቦርድና ሴኔት በአዋጁ የተሰጣቸውን ጥቅልና ዝርዝር ስልጣንና ኃላፊነትና ግዴታ አግባብነት ያላቸውን የፌደራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ድንጋጌዎች ጋር በጣምራ መታየትና መተርጎም ይኖርበታል፡፡

7. የመንግስት ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ አስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችና የቴክኒክ ሰራተኞች ሊኖራቸው እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2፣ ንዑስ አንቀጽ 3፣ንዑስ አንቀጽ 13 ፣ ንዑስ አንቀጽ 15 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 4 የከፍተኛ ተቋማት ዓላማዎችን ይዘረዝራል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች አንደኛው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ ነጻነት ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ እንደሆነና በከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንቅስቃሴ ፍትሕን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን ማራመድና መጠበቅ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 እና ንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማናቸውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም፣ እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለጽ ነጻነት፣ አሳታፊና የሕግ የበላይነት፣ፍትህንና ፍትሐዊነትንና ሌሎች በአዋጁ አንቀጽ 6 የተደነገጉ እሴቶች በቋሚነት የመያዝና ቋሚ እሴቶቹን ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ

አንቀጽ 1፣ ንዑስ አንቀጽ 5፣ እና ንዑስ አንቀጽ 6፣ ንዑስ አንቀጽ 11 እና በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡

8. ሕግ አውጭው የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና ቋሚ እሴቶች በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የደነገገው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ሕግ አውጭው የግልም ሆነ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚፈጽሟቸው ትምህርትና ምርምር ተግባራትና ተቋማቱ ከአካዳሚክ ሰራተኞች፣ ከአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች፣ከቴክኒክ ሰራተኞች እና ከተማሪዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትና የሚከተሉት አስተዳደር ጥበብ ከላይ የተገለጹትን የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና ቋሚ እሴቶች በሚያረጋግጥ መንገድ መሆን እንዳለበትና ተቋማቱ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችም ከላይ ከተገለጹት ዓላማዎችና እሴቶች አንጻር ሊመዘኑና ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ግልጽ ለማድረግ በማሰብ ከላይ የተገለጹት ድንጋጌዎች በማካተት አዋጁን ያወጀ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የዩኒቨርሲቲው በላይ አመራር የሆነው ቦርድ በዲስፕሊን ጉዳይ የሚሰጠው ውሳኔ በይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚታይበትንና ስህተትም ካለው የሚታረምበት እድል በሚያጣብብ ሁኔታ የአዋጁን አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ መተርጎም ዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና በቋሚነት ሊይዛቸው፣ ሊተገብራቸው የሚገባውን ቋሚ እሴቶች ለማስፈጸምና ለማጎልበት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ያለ መሆኑ መመዘን ይገባዋል፡፡

9. ከላይ የተገለጹትና ሕግ አውጭው በተቋማቱ ውስጥ ፍትህን የማስፈን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ዓላማና ቋሚ እሴት እንዲኖር የመድረግ መሰረታዊ ግብን ለማሳካት ከደነገጋቸው ድንጋጌዎች በተጨማሪ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነታቸው የተረጋገጠላቸው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 በጥቅሉ አገላለጽ ይደነግጋል፡፡ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአዋጁ የተረጋገጠላቸው አካዳሚክ ነጻነት አመላካች በሆነ መንገድ የሚዘረዝረው አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 የተቋማቱ የአካዳሚክ ነጻነት የአካዳሚክ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች የመቅጠርና በሥራ አፈጻጸም ውጤታቸው መሰረት መድቦ የማሰራትንና የሰው ኃይሉን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሰው ኃይሉን የማስተዳደርንና ሌሎች ነጥቦችን የሚያካትት መሆኑን ከአንቀጽ17 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እና (ሐ) ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. እዚህ ላይ በትኩረት መታየት ያለበት ሕግ አውጭው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት በሚደነግገው ድንጋጌ ሥር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጁና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የሰው ኃይሉን የማስተዳደር ነጻነት ያላቸው መሆኑን በአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) የደነገገበት ምክንያት ነው፡፡ ሕግ አውጭው ይህንን ድንጋጌ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ነጻነት

በሚያውጀው የአዋጁ ክፍልና ድንጋጌ ሥር ያካተተው ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የተረጋገጠላቸው አካዳሚክ ነጻነት በውስጡ ተነጻጻሪ ግዴታንም የያዘ በተለይም ተቋማቱ አዋጁንና አዋጅ ለማስፈጸም የወጣውን የፌደራል የዩንቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003 እና በአዋጅ ቁጥር 515/199 እንደ አግባብነቱ ሌሎች አግባብነትና ተፈፃሚነት ያላቸውን የፌደራል ሕጉች መሠረት በማድረግ የሰው ሀይላቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሚያካትት እና ይህንን ለተቋማቱ የተሰጠው አካዳሚክ ነጻነት ይህንን ተቋማቱን መሰረታዊ ግዴታ የማያስቀር ወይም የማይቀንስላቸው መሆኑን በግልጽ ለማስቀመጥ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

11. አከራካሪውን ጭብጥ ለመወሰን መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የአካዳሚክ ሰራተኞች የተረጋገጠላቸውን መብትና የተጣለባቸው አንጻራዊ ግዴታ ነው፡፡ በመንግስት ከፍተኛ ተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ የአካዳሚክ ሰራተኞች ያላቸውን መብት በአመላካች ሁኔታ የሚዘረዝረው የአዋጅ ቁጥር 650/2001፣ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) የአካዳሚክ ሰራተኞች ግልጽና ፍትሐዊ አስተዳደር የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በዲሲፕሊን ጉዳይ የመስማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላችው የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) በግልጽ ይደነግጋል ይህ ያአካዳሚ ሰራተኞች በአዋጅ ቁጥር 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) የተረጋገጠላቸው ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላቸው የሚጠይቅ እና ፍትሕ የማግኘት መብት እስከምን ድረስ ነው የሚለው ነጥብ ከሕገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆና ድንጋጌዎች አንፃር መታየት እና መተርጐም እንዳለበት ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባ ነው፡፡

12. ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲ ቦርድ በዩኒቨርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛውና የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ አካል መሆኑን ከአዋጅ አንቀጽ 43 ድንጋጌዎችና ከአንቀጽ 44 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም ቦርዱ የተቋሙ የላይ አመራር መሆኑ በአንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን ቦርዱም ቀዳሚ ኃላፊነት አዋጁ መከበሩንና መልካም አስተዳደር መሰፈኑን የማረጋገጥ እንደሆነ በአንቀጽ 44 ንዑስ አንቀት 1(ሀ) በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተቋሙ ውስጥ አዋጁ መከበሩንና መልካም አስተዳደር መስፈኑን ለማረጋገጥ የተቋሙ የሥራ ኃላፊዎች የዩኒቨርሲቲው አመራር አማካሪ አካላት፣ የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ የቴክኒክ ሰራተኞች፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች እና ተማሪዎች የከፍተኛ ክፍል ተቋማት አዋጅ የሚያከብሩና የሚተገብሩ መሆኑን መከታተልና መምራት ይጠበቅበታል፡፡ ቦርዱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ለማረጋገጥ በዩኒቨርሲቲው ተፈጽመዋል የሚባሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በበላይነት በማየት የመልካም

አስተዳደር ችግር አለበት የሚባለው አስተዳደራዊ ውሳኔ በማየት የማረም ሥልጣን ሊኖረው ይገባል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔም በተቋሙ በሌላ አካል ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ የማይችል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሆን ይገባል፡፡ የከፍተኛ ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ በመሰረታዊ ባህሪውና ይዘቱ ከላይ የገለጽነውንና ቦርዱ በተቋሙ ውስጥ አዋጁን ለማስከበርና ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ለማረጋገጥ የሚያስችለውን በዩኒቨርሲቲው መዋቅራዊ እርከን፣ የቦርዱን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭነት የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

13. የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ይህ በተለየ ሁኔታ አካዳሚክ ሰራተኞች የተሰጠ የዲሲኘሊን ውሳኔ ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የድንጋጌው አወቃቀር ጠቅላላና ሰፊ ነው፡፡ ድንጋጌው ማናቸውም የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች፣ የቴክኒክ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ጋር የአቅርቦት ወይም ሌላ የውል ግንኙነት ያላቸው ሶስተኛ ወገኖች በዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊ ወይም ሌላ አካል ደርሶብናል የሚሉትን የመልካም አስተዳደር በደል፣ በየደረጃው ባሉ የተቋሙ ኃላፊዎች ካልተፈታና ወይም ውሳኔያቸው ቅሬታ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ከሆነ፣ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ እንደሆነ የሚደነግግ ድንጋጌ ነው፡፡

14. ከዚህ አንጻር ሲታይ ቦርዱ ከፌደራል የመንግስት አዋጅ ቁጥር 515/199 አንቀጽ 2 ንዑስ 3 በሚሰጠው ትርጓሜ የዩኒቨርሲቲው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጭ አካል መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነዉ የሚለው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ ነጻነት ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንቅስቃሴ ፍትሕን፣ ፍትሐዊነትና የህግ የበላይነትን የማራመድና የመጠበቅ ዓላማዎች በማሳካት አንጻር ሲመዘን ተገቢነት የሌለው በመሆኑና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሊያዳብሩት የሚገባውን እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለጽ ነጻነት፣ አሳታፊና የሕግ የበላይነት፣ የፍትህንና ፍትሐዊነትን እሴቶች ለማረጋገጥ በጎ አስተዋጽኦ የማያበረክትና አዋጅ የደነገጋቸውን ቋሚና መሰረታዊ እሴቶች ግብና አላማ ጋር የማይሄድና አተረጓጎም መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

15. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ የአካዳሚክ ሰራተኞችን የይግባኝ መብት ከልካይና ገዳቢ እንደሆነ የተሰጠው ትርጉም ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 የተረጋገጠላቸው አካዳሚክ ነጻነት በውስጡ ተነጻጻሪ ግዴታንም የያዘ፣ በተለይም ተቋማቱ አዋጁንና አዋጅ ለማስፈጸም

የወጣውን የፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003 እና በአዋጅ ቁጥር 515/199 አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌደራል ሕጎች መሰረት በማድረግ የሰው ኃይላቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑንና ተቋማቱ ይህን ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ በሕግ አግባብ ሊጠየቁ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያካትት መሆኑን ያላገናዘበ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በአዋጁ ለተቋማቱ የተሰጠው የአካዳሚክ ነጻነት ተቋማቱን አዋጁንና ሌሎች ሕጎችን መሰረት በማድረግ የሰው ኃይላቸውን እንዲያስተዳድሩ የተጣለባቸውን መሰረታዊ ግዴታ የማያስቀር ወይም የማይቀንስላቸው መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

16. እንደሁም የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ የአካዳሚክ ሰራተኞችን የይግባኝ መብት ከልካይና ገዳቢ እንደሆነ የተሰጠው ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ) የአካዳሚክ ሰራተኞች ግልጽና ፍትሐዊ አስተዳደር የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑንና በዲስኘሊን ጉዳይ የመስማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳላቸው የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸዉ መሆኑ በግልጽ የሚደነግግ መሆኑን ያገናዘበ አይደለም፡፡ በመሰረቱ በአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1(ተ) የተገለጸው ፍትህ የማግኘት መብት፣ የአንድ ሰው ፍትህ የማግኘት መብት በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተሰጠው አካል አቅርቦ የማስወሰን መብትን የሚያካትት መሆኑን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተደነገገው ጋር በሚጣጣም ሁኔታ መተርጎምና ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

17. የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት የሚልና አግባብነት የተዋቀረ ድንጋጌ ነው ጥቅል የአካዳሚክ ስራተኞችን ጉዳይ ብቻ የማይመለከት ሌሎች ሠራተኞችና ሰዎች በዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊ ወይም አካል ደርሶብናል የሚሉትን የመልካም አስተዳደር በደል በየደረጃው ባሉ የተቋሙ ኃላፊዎች ካልተፈታና ቅሬታ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ከሆነ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ እንደሆነ የሚደነግግ ድንጋጌ መሆኑን ሣይመረምር የተሰጠ ትርጉምና ውሳኔ ነው፡፡

18. ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የዩኒቨርሲቲው ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ይኸ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 78945 በአካዳሚክ ሰራተኛ ላይ የተሰጠ የዲሲኘሊን የቅጣት ውሳኔ በዩኒቨርሲቲው ኘሬዝዳንት ከጸደቀ በኋላ፣

አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) መሠረት በቦርድ ቀርቦ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሳይሠጥበት በይግባኝም ሆነ በሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደማይገባው በመግለጽ የሰጠውን የሕግ ትርጉም በተዛባ ሁኔታ በመረዳት የሰበር ችሎት ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ እንደማይባልበት፣ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1(ጎ) ትርጉም እንደሰጠ አድርጎ በውሳኔው ማስፈሩ የተሳሳተና ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

19. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሲመለከቱ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያወጣውን አካዳሚክ ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ተግባራዊነት በሚያረጋግጥ መንገድ መሆን እንደሚገባው ግንዛቤ ሊያዝበተ የሚገባው ነው፡፡ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የዩኒቨርስቲው ቦርድ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ ሊቀርብበት የማይችል ነው በማለት የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉምና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት፣የአዋጅ ቁጥር 650/2001፣የፌደራል የዩኒቨርሲቲዎች ደንብ ቁጥር 210/2003፣ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያወጣውን የአካዳሚክ ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ እና የአዋጅ ቁጥር 515/1999 እንደ አግባብነቱ መሠረት በማድረግ በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341 (1) መሠረት መልስን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.99367

ሐምሌ 29 ቀን 2006ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ዶ/ር ሕሊና ፍቅሬ ጠበቃ ሶፊያ ክፍሌ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ፖሊስ ሆስፒታል ነገረ ፈጅ ረ/ኢንስፒክተር ወተቱ ተገኝ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የስራ መልቀቂያ ይሰጠኝ ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የአመልካች የይግባኝ አቤቱታቸው ይዘትም ባጭሩ፡- ከጥር 03 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ ባለመሆናቸው በገዛ ፈቃዳቸው ስራ ስለለቀቁ የሥራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸው የአሁኑን ተጠሪን ጠይቀው የተከለከሉ መሆኑን ገልጸው የስራ መልቀቂያ እንዲሰጣቸውና ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ ለደረሰባቸው ኪሳራ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለይግባኙ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያስቀደመ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት ከሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ በኮንስታብል ማእረግ በመለዩ ለባሽነት ቅጥር የፈፀሙ በመሆኑ የሚተዳደሩት በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ደንብ ሳይሆን በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 268/2005 ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡የአስተዳደር ፍርድ ቤቱም በዚህ መልክ የቀረበውን የተጠሪን መቃወሚያ መነሻ በማድረግና ከአዋጅ ቁጥር 720/2004 እና ደንብ ቁጥር 268/2005 ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤተ ተቀጥረው ለመስራት ማመልከታቸውን፣መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው

በፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር268/2005 መሰረት ሲጠበቁላቸው የነበረ መሆኑ መረጋገጡን፣የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት ለጡረታ ፈንድ መዋጮ ይዋጣላቸው የነበረው 20% መሆኑ መረጋገጡን፣አመልካች ሲቀጠሩ በሞሉት ፎርም ላይ በኮንስታብል ማዕረግ ለመስራት መፈረማቸውና በሕይወት ታሪክ ፎርሙም የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች ከሚሞሉበት ፎርም የተለየና በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 2(1) ስር ስለመንግስት ሰራተኛ የተመለከተውን ትርጉም የማያሟሉ መሆኑን መረዳቱን ገልፆ የአመልካች ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 መሰረት የሚታይ ሳይሆን በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚታይ ነው በማለት በድምፅ ብልጫ ውድቅ አድርጎታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-አመልካች አንድ ሰው የፌዴራል ፖሊስ አባል ለመሆን መሟላት ያለባቸው መስፈረቶች በሕጉ በግልጽ በተቀመጡበት ሁኔታ አመልካች ለደመወዝ አከፋፈል ሲባል እንዲሞሉ በተደረገው ፎርም ላይ ኮንስታብል ተብሎ በመገለፁና ለፖሊስ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ሲቀበሉ ስለቆዩ ብቻ የፌዴራል ፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ ጉዳዩ በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እንዲታይ ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1) እና ደንብ ቁጥር 268/2005 አንቀጽ 5(1)፣6(1)፣7(1) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተውን አግባብ የጣሰና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች ጉዳይ በፌዴራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች የፖሊስ አባላቱ የሚያገኙትን ማዕረግና ጥቅማ ጥቅም እያገኙ ሲሰሩ የቆዩ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶና አመልካች የፖሊስ መሰረታዊ ስልጠና ያልወሰዱት ለጊዜው መሆኑን ጠቅሶ አመልካች የፖሊስ አባል አይደሉም ተብሎ ሊወሰዱበት የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም ሲል የተከራከረ ሲሆን አመልካችም በመልስ መልሳቸውን ላይ የሰበር አቤቱታቸው አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር

በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም ሲቀጥረው የኮንስታብል ማዕረግ የተሰጣቸው መሆኑ፣ ሲቀጠሩ የሞሏቸው ቅጾች ፖሊሳዊ ባህርይ ያላቸው መሆኑን፣ለፖሊስ አባላት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች እና የጡረታ መዋጮ ለአመልካች ሲከፈልላቸው የነበረ መሆኑ በአስተዳደር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ከመሆናቸውም በላይ በግራ ቀኙ ያልተካዱ መሆኑን፣አመልካች እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት እነዚህ የተጠቀሱት ተግባሮች ሊፈፀሙ የቻሉት በጁኒየር ጄኔራል ሚዲካል ፕራክቲሽነር የስራ መደብ በተጠሪ መስሪያ ቤት ሲቀጠሩ የደመወዝ ቅጥራቸው ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የደመወዝ ስኬል ጋር አቻ እንዲሆን ታስቦና የአመልካችን ጥቅም ለመጠበቅ ታስቦ እንጂ ፖሊስ በመሆናቸው የተጠበቁላቸው ጥቅሞች ያለመሆናቸውን ጠቅሰው መሆኑን፣ተጠሪ በበኩሉ ይህንኑ የአመልካችን ክርክር የሚያስተባብል ማስረጃ ያለው ስለመሆኑ በግልጽ ሳይገልጽ አመልካች ወደውና ፈቅደው ፖሊስ ሁነው ስራቸውን መጀመራቸውንና የፖሊስ አባላቱ የሚያገኟቸውን ጥቅማ ጥቅሞችን ሲያገኙ የቆዩ በመሆኑ ፖሊስ ተብለው ሊወሰዱ ይገባል በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡

በዚህጉዳይበዋነኛነትየተያዘውጭብጥአንድ ሰው የፌዴራል ፖሊስ አባል ነው ተብሎ ጉዳዩ በዚህ ረገድ በተዘጋው የሕግ ስርዓት የሚታየው ምን ምን ሕጋዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው? የሚለው ነው፡፡ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ ይቻል ዘንድም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያላቸውን አዋጅ ቁጥር 720/2004 እና ደንብ ቁጥር 268/2005 ድንጋጌዎችን መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

አዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1) "የፖሊስ አባል" ማለት መሠረታዊ የሆነ የፖሊስ ሙያ ስልጠና ተሰጥቶት በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተቀጥሮ የሚሠራ የፌዴራል ፖሊስ አባል ነው በሚል ትርጉም የሰጠ ሲሆን በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 27(1) እና በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች መሰረት አዋጁን ለማስፈፀም ደንብ ቁጥር 268/2005 ወጥቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡ይህ ደንብ የፌዴራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 268/2005 ተብሎ የሚጠቀስ ሲሆን ደንቡ የተፈፃሚነት ወሰኑን በአንቀጽ 3 ስር በግልፅ አስቀምጧል፡፡በዚህም መሰረት ደንቡ ኮንስታብል እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ባላቸው የፌዴራል ፖሊስ አባት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን በተጠቃሹ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ ያስቀምጣል፡፡እንዲሁም የደንቡ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ስለፖሊስ ምልመላ፣ስልጠናና ምደባ የሚደነግግ ሲሆን የደንቡ አንቀጽ 5 ድንጋጌ በተለይ ሲታይም ማንኛውም ምልምል ፖሊስ በፖሊስ አባልነት ከመቀጠሩ በፊት መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና መውሰድና የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ አለበት በሚል በንዑስ ቁጥር አንድ ስር ሃይለ ቃል በያዘ አቀራረፅተቀምጦ ይገኛል፡፡በደንቡ

አንቀጽ 6(1) ደግሞ ማንኛውም ምልምል ፖሊስ መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና እንዳጠናቀቀ ስራ ከመጀመሩ በፊት ቃለመሐላ መፈፀም እንዳለበት እና ሊፈፀም የሚገባውን የቃለ መሓላ ይዘት አስፍሯል፡፡እንዲሁም የደንቡ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሲታይም የቅጥር ውል የሚደረግበትን አግባብ ይደነግጋል፡፡በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት ምልምል ፖሊስ የፖሊስ አባል የሚሆነው መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና አጠናቅቆ ቃለ መሃላ ፈፅሞ የቅጥር ውል ከፈረመ በኂላ መሆኑን አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚያስቀመጥ ሲሆን የተጠቃሹ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌም ውሉ ከተፈረመበት በኂላ ስለሚኖረው የአገልግሎት ዘመን ለይቶ የሚደነግግ ነው፡፡ደንቡ በትርጓሜ ክፍሉ አንቀጽ 2(2) በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለደንቡም ተፈፃሚ ይሆናል ሲል ያስቀመጠ ሲሆን በዚህ ደንብ አዋጅ ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር 720/2004 ስለመሆኑ በአንቀጽ 2(1) በግልፅ ያሳያል፡፡በዚህ አግባብ ሲታይ ደግሞ ፖሊስ ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(1) የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሁኖ በደንቡ አንቀጽ 4፣5፣6 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት በሕጉ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የተቀጠረ ሊሆን እንደሚገባው ከድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ይሆናል፡፡በመሆኑም በሕጉ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ አንድ ሰው የፖሊስ ቅጥር ፎርም የሚል ስያሜ የያዘ ሰነድ ስለሞላ ወይም በቅጥር ፎርሙ በሕጉ አግባብ የሚገኙት ማዕረጎች ተሰጥተውት የጥቅማ ጥቅሙ ተጋሪ መሆን እንደ ሕጉ አነጋገርና ይዘት ፖሊስ ነው ብሎ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው ጉዳዩን በተለይ እንዲገዙ የወጡ ሕጎች አያሳዩም፡፡

አዋጅ ቁጥር 720/2003 የወጣበት መሰረታዊ አላማ የፌዴራል ፖሊስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥትንና ሕገመንግሥቱን መሠረት አድርገው የሚወጡ ህጎችን የማስከበር ተልዕኮውን በብቃት በመወጣት የዲሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት፣ ሠላምን ለማስፈንና ልማትን ለማፋጠን በሚደረገው አገራዊ እንቅስቃሴ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት እንዲችል በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የፌዴራል ፖሊስ ተቋም ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ገለልተኛ የሆነ፣ ሕብረተሰቡን በእኩልነት የሚያገለግል፣ በፖሊሳዊ ሥነ-ምግባሩ የታነፀና ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ስለመሆኑ አዋጁ በመግቢያው ላይ የሚገልፅ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ በአግባቡ ለማስፈፀም ይቻል ዘንድ ደግሞ ደንቡ ወጥቷል፡፡በመሆኑም አዋጁ የራሱን አላማ እንዲያሳካ በአዋጁ የተቀመጡትና አዋጁን መሰረት አድርጎ በወጣው ደንብ ስር ያሉት ድንጋጌዎች በአግባቡ ሊከበሩና ሊተገበሩ ይገባል፡፡ከዚህ ውጪ ከአዋጁ የወጡ አሰራሮችና ልማዶች በአዋጁና በደንቡ ጥበቃ የሚያገኙበት አግባብእንዲኖር ማድረግ ጉዳዩን ለመግዛት ታስቦ ስልጣን ባለው አካል የወጣውን ሕግ ትርጉም የሚያሳጣ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰዱ፣በደንቡ መሰረትም ቃለ መሃላ ያልፈፀሙ ቅጥሩን የሞሉትም ምልምል ፖሊስ ሊወሰደው የሚገባውን መሰረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና አጠናቅቀው ሳይሆን ምንም ስልጠና ሳይወስዱ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጡ ነጥቦች ናቸው፡፡ የፌዴራል ፖሊስ የፖሊስ አባላቱን የሚመለምለው የሚያሰለጥነው የሚቀጥረውና የሚያስተዳድረው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 14 በግልፅ የተቀመጠ ሲሆን ደንቡን ለማውጣት በሕጉ ስልጣን የተሰጠው አካል ደግሞ ደንብ ቁጥር 268/2005 አውጥቶ ከህዳር 10 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ሁኗል፡፡በደንቡ አንቀጽ 96(2) ድንጋጌ ስር ደግሞ ከደንቡ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣መመሪያዎች ወይም የአሰራር ልማዶች በደንቡ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው አስገዳጅነት ባለው መልኩ አስቀምጧል፡፡በመሆኑም በአዋጁና በደንቡ ከተመለከቱት ሕጋዊ ስርዓቶች ውጪ የሚፈጸሙ የፖሊስ ቅጥሮች አንድን ሰው የፖሊስ አባል ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችሉ አይሆኑም፡፡

እንዲሁም ከጊዜ ቅደም ተከል አንፃር ይታይ ቢባል እንኳን አዋጅ ቁጥር 720/2004 ተፈፃሚ የሆነው ከሕዳር 18 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ነው፡፡አመልካች የቅጥር ፎርሙን የሞሉበት ጊዜ ሚያዚያ 01 ቀን 2002 ዓ/ም መነሻ ተደርጎ በጊዜው ተፈፃሚነት የነበራቸው ሕጎች አዋጅ ቁጥር 313/1995 እና ደንብ ቁጥር 86/1995 ድንጋጌዎች ሲታይም የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰደ ሰው የፖሊስ አባል ነው የሚለውን ትርጓሜ ሊያገኝ የሚችልበትን አግባብ የሚያሳዩ ድንጋጌዎችን ይዘው አይገኙም፡፡ስለሆነም ተጠሪ ለአመልካች የፖሊስ ማእረግ ሰጥቶ ቅጥሩ ላይም ማእረጉ ተጠቅሶ ፎርሙ መሞላቱም ሆነ አመልካች የአንድ ፖሊስ ጥቅማ ጥቅሞችን ሲያገኙ መቆየታቸው በአዋጁ ጥብቅ አነጋገር ስንነሳ በማናቸውም መመዘኛ አመልካች የፖሊስ አባል ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ለመውሰድ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ተጠሪ አመልካች የፖሊስ ትምህርትና ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን አምኖ ወደፊት የሚወስዱበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርም የአዋጁንና የደንቡን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች የፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ የሚደመደምበት አንዳችም የሕግ ምክንያትን በሌለበት ሁኔታ ማዕረጉ ተሠጥተው የፖሊስ አባል ጥቅማ ጥቅም ተጠቃሚ ነበሩ በሚሉ ምክንያቶች ብቻ ጉዳያቸው በፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ እንጂ በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው ስርዓት የሚታይ አይደለም ተብሎ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ መወሰኑም ሆነ ይኼው ውሳኔ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በድምጽ ብልጫ መጽናቱ ከላይ የተመለከቱትን የሕግ ማዕቀፎችን ጥብቅ ስርዓት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቭል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድቤት በይ/መ/ቁጥር 162/2006 ጳጉሜ 04 ቀን 2005 ተስጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 93890 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረትተሽሯል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 720/2004 አንቀጽ 2(1)፣14(1) እና በደንብ ቁጥር 268/2005 አንቀጽ 4፣5፣6 እና 7 ድንጋጌዎች መሰረት የፌዴራል ፖሊስ አባል ናቸው ተብሎ የሚወሰዱ አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት የነበራቸው ቅጥር ከፖሊስ አባልነት ውጪ የነበረ በመሆኑ ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 515/1999 በተዘረጋው አግባብ ነው በማለት በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ጉዳይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የአስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 162/2006 ክርክሩን ቀጥሎና በአግባቡ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ/ኢ

## የቅጽ 15 2005 እና 2006 ዓ.ም የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | | |
| 1. | • አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የደረሰበትን የአካል ጉዳት በተመለከተ የጉዳት ካሣ ክፍያ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚችለው በአማራጭ አንድም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት አሰሪውን ያለጥፋት በሥራ ክርክር ችሎት ከሶ በመጠየቅ ወይም የአሰሪውን ጥፋት መነሻ በማድረግ የጉዳት ካሣ ክፍያ ከውል ውጪ ኃላፊነትን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በፍ/ሔር ችሎት በአሠሪው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>• በሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የጉዳት ካሣን ለመጠየቅ በህጉ የተመለከቱትን መብቶች በአግባቡና በትክክል ተገንዝቦ እንደ ጉዳቱ ሁኔታ፣ አይነትና አግባብነት በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅመውን የመብት አድማስ አውቆ በመለየት ተገቢው መብቱ ከመነጨበት የህግ አግባብ አንፃር ክሱን ሊያቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ፣ | 80343 | ዋሊያ የቆዳ ማለስለሻ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ደረጀ ውለታው | ግንቦት 06/2005 | 2 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 ድንጋጌ ይዘት አድማሱ በግልጽ በተወሰኑ ጭብጦች ላይ ብቻ ሣይሆን በተከራካሪ ወገኖች ቢነሱ ኖሮ ሊወሰኑ ይችሉ የነበሩ ጭብጦችን ጭምር የሚያካትት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 96(1)¸97 109¸ 138(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 80(2) | | | | |
| 2. | አሠሪ ሠራተኛውን እንደ ሠራተኛ በመቀበል የሚሰራውን ሥራ ባልሰጠበት ሁኔታ ሠራተኛውን ከሥራ ገበታው ቀርቷል በሚል ያለ ማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1) ለ | 82091 | ኒው ጀኔሬሽን ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ ለገሠ ደሣለኝ | መጋቢት 25/2005 | 9 |
| 3. | የሥራ መሪ የሆነ ሠራተኛ ያለ አግባብ ከሥራ መሰናበቱ ተረጋግጦ ሲወሰንና የአሰሪው የመተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድለት ከሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት ኪሣራ ታስቦ ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2574(2)<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 43(4) (ሀ) | 84661 | አቶ ዳዊት ሸዋቀና<br>እና<br>ስኳር ኮርፖሬሽን | መጋቢት 27/2005 | 12 |
| 4. | ከሥራ ጋር በተገናኘ እንዲከፈል በሚል የሚቀርቡ የደመወዝ፣ የትርፍ | 79476 | ኢትዩ ቴሌኮም<br>እና | የካቲት 12/2005 | 17 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሰዓት እና ሌሎች ክፍያዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ሠራተኛው ክፍያዎቹን መጠየቅ ይችላል (ይገባዋል) ከሚባልበት ግዜ ጀምሮ እንጂ የሠራተኛው የሥራ ውል ከተቋረጠበት ግዜ ጀምሮ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(1-4) | | እነ<br>አቶ ዘሪሁን ታዬ (ዘጠና ስድስት ሰዎች) | | |
| 5. | የስራ ውል የሚመሠረተው ማንኛወም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሠነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት የተስማማ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2(3),4 | 81814 | እነ ወ/ት ፌቨን የሺጌታ (12 ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ አየር መንገድ | ሐምሌ 18/2005 | 24 |
| 6. | በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ ጉዳቱን ያደረስኩት በሥራ መደራረብ እና ከልምድ ማነስ ነው የሚል ምክንያት አቅርቦ የተከራከረ መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ ነው ለማለት የሚያበቃ (የሚያስችል) ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. | 86284 | ሆራይዞን አዲስ ጎማ (አ.ማ)<br>እና<br>አቶ መኮንን ዓለሙ | መጋቢት 13/2005 | 27 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሽ), 13(3) | | | | |
| 7. | አንድ ሠራተኛ የቅጥሩ ውል አይነት ቋሚም ይሁን ግዜያዊ ለሠራተኛ በህጉ በተፈቀዱ ጥቅሞች የመጠቀምና ህጉ የሰጣቸውን ከለላዎች የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 42(2) | 87338 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ገብሬ በላይነህ (አምስት ሰዎች) | ግንቦት 21/2005 | 30 |
| 8. | አንድ ሠራተኛ ከሥራ መቅረቱ በህመም ምክንያት መሆኑ እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በህጉ አግባብ፣ በህመሙ ምክንያት ስለመቅረቱ ለአሰሪው ያሳወቀና ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 85(4) | 87285 | ወ/ሮ የውብዳር ንጋቱ<br>እና<br>ገነት ሆቴል | መስከረም 23/2006 | 34 |
| 9. | የሥራ ኃላፊነቱን ባለመወጣት ተገቢነት የሌላቸው ሰዎችን ወደ አሰሪው ድርጅት ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ ጥፋት የፈፀመ የጥበቃ ሰራተኛ ወደ ድርጅቱ በገቡት ሰዎች ምክንያት የተፈጠረ የፀጥታና የደህንነት ችግር አልተከሰተም በሚል ምክንያት ብቻ አሰሪው በሰራተኛው ላይ የፈፀመውን የስራ ውል ማቋረጥ | 90389 | የኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በሪሁን በላይ | ጥቅምት 18/2006 | 38 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተግባር ህገ ወጥ ነው ሊያስብል የሚችል ስላለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሽ), 17(1)(ሽ)(ቀ), 14(2)(ሀ) | | | | |
| 10. | አንድን ሠራተኛ የሥራ መሪ ነው ለማለት የሚቻለው በህግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሰሪው በተሰጠ የውክልና ስልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም እንዲሁም በተጨማሪነት ወይም ይህንን ሣይጨምር ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ የማገድ፣ የመመደብ ወይም ሌሎች የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውን እንደሆነ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3(2)(ሐ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(1)(ሐ) | 92466 | ሳይግን ቴክስታይል ቢዩልዲንግ ኮንስትራክሽን ትሬድ ኢንዳሪኢንክ ኢትዮያ ብራንች እና አቶ ተስፋዬ ጥላሁን | ጥር 02/2006 | 41 |
| **ውል** | | | | | |
| 11. | የንግድ ቤትን ከመንግስት የተከራየ ተከራይ ከአከራዩ እውቅና ውጭ ለ3ኛ ወገን የንግድ ቤቱን ማስተላለፉ አከራዩ የመጀመሪያውን የኪራይ ውል ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ፣ በዚሁ መሠረትም አከራዩ ቤቱን ለማስለቀቅ የሚያደርግው | 82670 | እነ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 አስተዳደር ፅ/ቤት (ሁለት ሰዎች) እና | መጋቢት 09/2005 | 46 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንቅስቃሴ ሁከት ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 6<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1140, 1149 | | ዋጋዬ አሰፋ | | |
| 12. | • አንድን በጽሁፍ የተደረገ ውል ዋና ሰነድ ጠፍቷል በማለት ክርክር በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤት በማስረጃነት በቀረበው የውሉ ሰነድ ኮፒን ተቀብሎ በውሉ የተመለከቱትን ምስክሮች ሊሰማ የሚገባው ጠፍቷል የሚለው ወገን ዋናው ሰነድ ስለመጥፋቱ በተመለከተ በአግባቡ ያስረዳ እንደሆነና የውሉንም ኮፒ አግባብነት ያለው አካል ዋናው የውል ሰነድ ጋር ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• የምስክሮቹ ቃል ሊሰማ የሚገባውም የውሉ ቃል ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2011(1),2003 ,1730(1) | 84330 | አቶ መንግስቱ ኦሾ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እመቤት ጥላሁን (አምስት ሰዎች) | ሚያዝያ 10/2005 | 50 |
| 13. | አስቀድሞ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት አንድን የአከራይ ንብረት ይዞ ሲጠቀም የቆየ ተከራይ የኪራይ ውል ግዜው ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ አከራዩ የኪራዩን ዋጋ በመጨመር አዲስ የኪራይ ዋጋ እንዲከፈል ገልፆ | 81163 | አቶ ሲሳይ ረታ<br>እና<br>የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት | የካቲት 11/2005 | 55 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እያለ ተከራዩ በቀረበው አዲስ የኪራይ ዋጋ ሳይስማማ ወይም እየተቃወመ በንብረቱ መገልገሉን በቀጠለ ጊዜ ተከራይ ለአከራዩ ሊከፍለው የሚገባውን የኪራይ ዋጋ ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ፣<br><br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2950(1) (2), 1687 | | | | |
| 14. | • ከውል አፈፃፀም ሂደት ጋር በተገናኘ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኪሣራ ሊሰላ ስለሚችልበት አግባብ፣<br>• የኪሣራው ልክ ከውል ውጪ የሚደርስ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በርትዕ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 1800, 2102(1)(2) | 79794 | የማይክሮሊንክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ኃ.የተ.የግል ማህበር<br><br>እና<br><br>የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር | ሚያዝያ 22/2005 | 59 |
| 15. | አንድ ውል (ስምምነት) ህግ በጽሑፍ እንዲሆን ሲያስገድድ ውሉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት እና በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች ፊርማ ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑና መሀይማንና ማየት የተሳናቸው ሰዎች የሚያደርጉት ውል በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት የተደረገ ካልሆነ በቀር በውሉ የማይገደዱ ስለመሆኑ፣ | 83674 | ወ/ሮ እቴነሽ ካሳ<br><br>እና<br><br>ሀጂ ጀማል ይማም | ግንቦት 19/2005 | 65 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1727, 1728(3), 2005 | | | | |
| 16. | በመያዣ ውል መነሻነት አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከነይዞታው የያዘ ሰው በይዞታው ላይ የንብረቱ ባለቤት ሳይቃወመው ግንባታ የፈፀመ ከሆነ ተጠቃሹ የመያዣ ውል አይፀናም በሚል ተዋዋዬቹ ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ሲደረግ የንብረቱ ባለቤት በመያዣው ይዞታ ላይ የወጣውን የግንባታ ወጪ ግንባታውን ላካሄደው ወገን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1818, 2162 | 90862 | ወ/ሮ ተዋበች ኃይሌ<br>እና<br>ወ/ሮ አያንቱ በዬቻ | ታህሳስ 14/2006 | 69 |
| 17. | የማይንቀሣቀስ ንብረት ተከራይ የሆነ ሰው ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለ3ኛ ወገን በኪራይ ሊሰጥ የሚችለው ተከራዩ አስቀድሞ ለአከራዩ አሳውቆ አከራዩ የማይቃወም መሆኑ ሲታወቅ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2957(1)(2), 1731<br>በአ.አ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ ደንብ ቁጥር 3/2004, 4/2004 | 86847 | አቶ ፀጋዬ አማን<br>እና<br>እነ አቶ መሐመድ ነጋሽ (ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 18/2006 | 73 |
| 18. | ከሠራተኛ ቅጥር ውል ጋር በተገናኘ የዋስትና ግዴታ የገባ ሰው የሠራተኛው የቅጥር ውል እንዲሻሻል | 86813 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት | መስከረም 22/2006 | 77 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም እንዲለወጥ ከተደረገ በኋላ ሠራተኛው ከተሻሻለው ወይም ከተለወጠው የቅጥር ውል ጋር በተያያዘ ያለበትን ተጠያቂነት አስመልክቶ አስቀድሞ በገባበት የዋስትና ግዴታ መሰረት ተጠያቂ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1827(1) | | እና<br>እነ ሰሚር መላኩ (ሶስት ሰዎች) | | |
| 19. | • ተከራካሪ ወገኖች በአንድ የሰነድ ማስረጃ ላይ የተመለከተን ፊርማ የማን ስለመሆኑ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተጣርቶ ውጤቱ ከቀረበና ከታወቀ በኋላ ሰነዱ በውጭ አገር ተመርምሮ ውጤቱ እንዲታወቅ በማለት የሚያቀርቡት ጥያቄ በህግ አግባብ አጥጋቢና አሣማኝ ምክንያትን በመጥቀስና በማስረጃ አስደግፈው ያላቀረቡ እንደሆነ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ /ውሣኔ/ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት የሚቻለው በተከራካሪ ወገኖች ፍትህ የማግኘት መብት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2008, 2007, 2001, | 86187 | አቶ ዳንኤል ዘሚካኤል<br>እና<br>አቶ ቢሃሪ ባቡላል ሞዲ | ሰኔ 21/2005 | 80 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2005 | | | | |
| **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | |
| 20. | • በፍ/ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚሰማውና ፍሬ ነገሩ እንዲነጠር የሚደረገውም በማስረጃ የሚነጥረው ፍሬ ነገር ለዳኘነት አሰጣጡ እጅጉን አስፈላጊና የግድ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣<br>• ማስረጃ እንዲሠማ የሚፈልግ ወገን ማስረጃው የሚሰማበትን ነጥብ ለይቶ የማስረጃውን አይነትና የሚገኝበትን ቦታ ሁሉ በመጥቀስና በእጁ ላይ ያለውንም አያይዞ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.223፣234፣137(3)፣145፣256,136-138,246,248 | 77983 | እነ አቶ እንድሪስ አደም (አምስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች ጥላሁን | መጋቢት 24/2005 | 87 |
| 21. | አንድን ጉዳይ በተመለከተ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው በተለያዩ ፍ/ቤቶች (ችሎቶች) አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች ባቀረቡ ግዜ (የክርክሮቹ ደረጃ ምንም ይሁን ምን) ክሶቹ ተጣምረው ታይተው ሊወሠኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 8(1),11,244, | 81275 | ወ/ሮ ዘምዘም ወንድሙ<br>እና<br>አቶ አብዱሰቡር አብዱሰመድ | ሰኔ 05/2005 | 92 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 245 | | | | |
| 22. | • ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ ጋር በተገናኘ መብቱን ለማስፈፀም ጠይቆ በአፈፃፀም በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶ እያለ ባለመብት ነኝ የሚለው ወገን የሚያነሣው የመብት ጥያቄና ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሣኔ በህግ አግባብ እስካልተሻረ ድረስ የውሣኔው አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት በባለጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን በማናቸውም አስፈፃሚ አካላትና በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 79(2) | 83007 | እነ ወ/ሮ አልማዝ ገመቹ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ፋዩ ገመቹ | ሰኔ 03/2005 | 98 |
| 23. | በአንድ ጉዳይ ተከሣሽ የሆነ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ካቀረበ ፍ/ቤቱ ከቀረቡት ክሶች መካከል በሥረ-ነገር ስልጣኑ ሥር ያሉትን መርጦ ለማየትና ከሥረ-ነገር ስልጣኑ በላይ የሆነውን ጉዳይ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ይቅረብ በማለት የከሣሽን ክስና የተከሣሽን የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ተነጣጥለው እንዲታዩ በማድረግ | 83169 | ፕሮፌሰር አደም ዓሊ አህመድ<br>እና<br>አዳማ ጠቅላላ ሆስፒታልና ሜዲካል ኮሌጅ ኃ/የተ/የግል | መጋቢት 28/2005 | 103 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ስላለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 30(1)¸324(1)(ሀ),215(2)¸17(3) | | ማህበር | | |
| 24. | • አንድ ስምምነት በፍ/ቤት ሊፀድቅ የሚችለው ጉዳዩ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመታየት ሂደት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ መሆኑን ገልፀው ይኼው ስምምነት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ፣<br>• ከፍርድ ቤት ውጪ በሚደረግ እርቅ ወይም ግልግል መሰረት ያለመግባባትን ያስቀሩ ወይም ለጉዳያቸው እልባት ያገኙ ሰዎች የእርቁን ወይም የግልግሉን ስምምነት በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ወይም ማስፀደቅ የማያስፈልጋቸው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 እና 3324 | 85873 | እነ ወ/ሮ ኒኢማ አባድጋ አባዋጂ<br><br>እና<br><br>አቶ ጣሐ ጀማል አደም | መጋቢት 13/2005 | 108 |
| 25. | አንድን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የሚመለከት ፍ/ቤት በህጉ አግባብ ክስ ተሻሽሎ ከፍ ያለ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በግምት ላይ ተቃውሞ ቀርቦ ግምቱ እንዲጣራ ሲደረግ የንብረቱ ግምት ከፍ ማለቱ | 86551 | ወ/ሮ ብዙነሽ ወ/ሚካኤል<br><br>እና<br><br>እነ አቶ ሽመልስ | መጋቢት 25/2005 | 112 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመረጋገጡ ብቻ ቀድሞ ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) ,92, 225, 226, 250,136 | | ቦጋለ | | |
| 26. | ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ ላይ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተረጋግጦ የተሰጠውን ማስረጃ በሌላ ክርክር መቃወም የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 79871 | እነ ወ/ሮ የውብዳር ባንቱ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሎሚ ተሊላ (አምስት ሰዎች) | የካቲት 11/2005 | 116 |
| 27. | አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው እስከሆነና ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል እስከሌለ ድረስ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሣኔ ሊሰጥበት የሚችልና የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1), 79(1)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | 80202 | እነ አቶ ሐጎስ ሽጎዕ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የመሸነ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የካቲት12/ 2005 | 120 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | የክስ አቀራረብ ሥርዓቱን አሟልቶ ያልቀረበ ክስን ፍ/ቤቶች ሌላኛውን ወገን ሳይጠሩ ለመዘጋት ስለመቻላቸው፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 33, 80, 222, 225, 226 እና 231 | 83915 | አቶ ዩሐንስ በቀለ እና የቦንጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የካቲት 29/2005 | 123 |
| 29. | የማይንቀሳቀስ ንብረት የመፋለም ክስ ጋር በተያያዘ ክርክር ቀርቦ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ በክርክሩ ተሣታፊ የነበረ ወገን ንብረቱን አስመልክቶ ተሰጥቶ የነበረው የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መክኗል በሚል የሚያቀርበው አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑና በፍርዱ መሠረት የተጀመረው አፈፃፀም ሂደትን ለማስቆም የማይቻል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195,1196 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6,358,378 የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(1), 79(1)(4) , 37 | 42501 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና የአስር አለቃ ደምሴ ዳምጤ ወራሾች (ሶስት ሰዎች) | የካቲት 28 /2005 | 126 |
| 30. | የማይንቀሣቀስ ንብረት (ቤት) ሽያጭ ውል ጋር በተገናኘ ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ስመ-ንብረት የሚመለከተው አካል ወደ ገዢው ለማዞር እንዲችል በሚመለከተው ክፍል ቀርቦ ተገቢውን እንዲፈፀም | 82234 | አቶ አየለ መኮንን እና እነ ወ/ሮ ጦቢያው ወንድም ገዛው | የካቲት 26/2005 | 130 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማለት ገዥ የሚያቀርበው ክስ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1)(ሀ), 33(2-3), 222, 224 | | (ስድስት ሰዎች) | | |
| 31. | ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ አወሣሠን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን የተገነዘቡ ከሆነ ይሄው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያሉትን ማጣራት ሁሉ ለማድረግ ስለመቻላቸው፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 137, 272, 327(3), 345 | 72980 | ወ/ሮ ይርገዱ አዲሱ<br>እና<br>እነ ህጻን ምስጋናው ዘሪሁን (ሶስት ሰዎች) | ሐምሌ 06/2004 | 134 |
| 32. | ሚስትነትን በተመለከተ የአመልካችን ማስረጃ ብቻ በመቀበል ሚስትነትን በማረጋገጥ በፍ/ቤት የሚሰጥ ማስረጃ (Declaratory Judgment) በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበትና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ የሚችል እንጂ ማስረጃውን በተሰጠው ፍ/ቤት ተቃውም በማቅረብ ያልተሻረ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣ | 82679 | ወ/ሮ ከበቡሽ ሸዋረገድ<br>እና<br>ወ/ሮ እንዳገር ጌቱ | መጋቢት 27/2005 | 138 |
| 33. | በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ከነበረ ክርክር | 83582 | ወ/ሮ ወርቅነሽ | መጋቢት | 144 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጋር በተገናኘ በተከራካሪዎቹ ወገኖች አመልካችነት ጉዳይ በእርቅ በማለቁ የተከራካሪዎቹን የእርቅ ስምምነት ተቀብሎ በማጽደቅ እንዲመዘገብ በማለት በፍ/ቤት የተሰጠ ትእዛዝ ላይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚያቀርበው የመቃወሚያ አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ትእዛዙን የሠጠው ፍ/ቤት አቤቱታውን ተቀብሎ ሊያስተናግደው የሚገባ ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,360,277(1)(2) | | ውብነህ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አልማዝ ዓለሙ (ሶስት ሰዎች) | 27/2005 | |
| 34. | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች መካከል በዋናው ጉዳይ ላይ ከላይ ወደ ታች በተዋቀሩት ፍ/ቤቶች ከተደረገ ክርክርና ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተገናኘ እንጂ በአፈፃፀም ከተሰጠ ትእዛዝ (ውሣኔ) ጋር በተያያዘ ተፈፃሚ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5, 32 | 84446 | ጠበቃ አንበርብር ዓባይነህ<br>እና<br>ፍትህ ሚኒስቴር | ሚያዝያ 24/2005 | 149 |
| 35. | አንድን ጉዳይ ለማየት በህግ ስልጣን በሌለው ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ ታይቶ እንዲታረም ካልደተረገ በቀር በጉዳዩ ላይ | 85718 | አቶ ቴዎድሮስ አማረ<br>እና | ሰኔ 03/2005 | 153 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 212 | | አቶ አዲሱ ፍሰሃ | | |
| 36. | በአንድ የቀረበ ክስ በተከሣሽነት የተሰየመ ወገን በከሳሽ ከቀረበበት ክስ ጋር በተገናኘ ክስ በቀረበበት ንብረት (ጉዳይ) ጋር በተያያዘ የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ በህጉ አግባብ የተከሣሽ ከሣሽነት ክሱን ተገቢውን ዳኝነት በመክፈል ያቀረበ ካልሆነ በስተቀር ዳኝነት ሊሰጥ የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) (ረ)(ሠ), 215(2), 235(2) | 86454 | እሪ ወ/ት ፍሬወይኒ አለም (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አለም መሐሪ | ግንቦት 23/2005 | 156 |
| 37. | • ከሣሽ የሆነ ወገን የሚያቀርበውን የዳኝነት ጥያቄ አይነትና መጠኑን በክሱ ማመልከቻ በግልጽ በማስፈር ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በህግ የተፈቀደን መፍትሔ ለማግኘት በግልጽ ዳኝነት መጠየቅ የሚገባቸው ስለመሆኑ፣<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241 ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያቀረቡት ክርክር ለማብራራት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 246-248 መሠረት ጭብጥ ለመመስረት እንዲያግዝ እንጂ | 86510 | ሙሉ ኤሌክሮኒክስ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል /አ.አ/ | ሰኔ 18/2005 | 160 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በጽሁፍ ማመልከቻ ላይ ያልሰፈረን የዳኝነት ጥያቄ ተከራካሪዎች እንዲጠይቁ የሚያስችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 222, 234, 235, 236, 83, 224, 182, 241, 246-248, 251, 255 | | | | |
| 38. | በፍ/ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተመለከተው 60 ቀን የይግባኝ ማቅረቢያ ግዜ ታሳቢ የሚያደርገው እና ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት ውሣኔ መሰጠቱን ወይም ለውሣኔ የሚያበቃ ክርክር የተደረገ መሆኑን ተረድተው ቀርበው ለመከታተልና የዳኝነቱን ውጤት ለመስማትና ለማወቅ ያልፈለጉትን ወይም ደግሞ የተከራካሪዎችን የመደመጥ መብት ማክበር ይቻል ዘንድ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ጥሪ ተደርጉላቸው በጥሪው መሠረት ክርክራቸውን በአግባቡ ለመምራት ባልቻሉ ወገኖች ላይ ስለመሆኑ፣ | 87190 | ቄስ ዳንኤል አርኬ<br>እና<br>የኮልፌ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ | መስከረም 21/2006 | 164 |
| 39. | • የኑዛዜ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ በተካሄደ ክርክር ተሣታፊ ሆኖ ተቀባይነት ያጣና ኑዛዜው በፍርድ ቤት የፀደቀበት ሰው በሌላ ጊዜ | 85102 | አቶ ሰንደቁ አበበ<br>እና<br>አቶ ሐብታሙ | መስከረም 21/2006 | 168 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኑዛዜውን ህጋዊነት አስመልክቶ በመቃወሚያነት የሚያቀርበው ክርክር ወይም አዲስ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>• የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ዳኝነት መስጠት የሚገባው በስርዓቱ መሠረት የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ መሠረት በማድረግ እንጂ ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ተገቢ አልነበረም በሚል ምክንያት ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5,212<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | | ቃበቶ | | |
| 40. | • በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ መደበኛውን የሙግት ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ መከናወን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>• በፍርድ አፈፃፀም ደረጃ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር በሚል የመቃወሚያ አቤቱታ በቀረበ ግዜ ጉዳዩን የያዘው የአፈፃፀም ችሎት በንብረቱ ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ በሚል የቀረበውን የመቃወም አቤቱታ በመደበኛው የሙግት ሥነ-ሥርዓት ሂደት ክርክሩን በማስተናገድ ንብረቱ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የሚያደርግ ህጋዊና በቂ ምክንያት | 86133 | እነ አቶ ፍቅሩ ከበደ (አስራ አንድ ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አርአያ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2006 | 172 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መኖር ያለመኖሩን በማስረጃ በማጣራት ለጉዳዩ እልባት መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 419, 421 | | | | |
| 41. | የፍርድ ቤትን እገዛ በመጠየቅ ማስረጃ ማስቀረብ የሚቻለው ጠያቂው ተከራካሪ ወገን እንዲቀርብ የተጠየቀውን ማስረጃ ትክክለኛ ግልባጭ በቅርብ ግዜ ለማምጣት የማይችልበትን ወይም ለማስገልበጫ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመክፈል የማይቻል መሆኑን እንዲሁም ማስረጃው ለክርክሩ ምን ያህል ጠቃሚነት እንዳለውና ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያስችል ስለመሆኑ በጽሁፉ ገልፆ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145(1)(2), | 89494 | የኢትዩጵያመድን ድርጅት<br>እና<br>የሟች ዘካሪያ ኢብራሂም ባለቤት ሳዲያ ኢብሮሽ | ጥቅምት 19/2006 | 177 |
| 42. | • ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ አንድ ሰው ሟች በተውት ኑዛዜ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ክፍያ እንዲከፈለው ክስ አቅርቦ ገንዘቡ እንዲከፈል ዳኝነት ከተሰጠ በኋላ በሌላ ግዜ የሟቹ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ በማለት የሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 90543 | እነ አቶ ተሾመ አሰፋ (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሪት መስታወት አሰፋ | ጥቅምት 21/2006 | 183 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • ኑዛዜን መሠረት አድርጐ የሚቀርብ የኑዛዜ ተጠቃሚነት መብት ይረጋገጥልን ጥያቄና የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆነ የፍሬ ነገርና የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዬች ስለመሆናቸው፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(2) | | | | |
| 43. | በችሎት በመገኘት ስልክን ማስጮህ ብሎም ፍርድ በሚነበብበት ጊዜ በችሎት ዳኛው ሥነ-ሥርዓት እንዲይዝ ሲነገረው ችሎቱ በሥነ-ሥርዓት ያናግረኝ በማለት ያልተገባ ባህሪ ማሣየት በችሎት መድፈር ወንጀል ሊያስቀጣ የሚችል ተግባር ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 481<br><br>የወንጀል ህግ ቁጥር 449(1)(ሀ) | 92459 | አቶ ፍጽም ብርሃን ገ/ክርስቶስ<br><br>እና<br><br>ተጠሪ፡ የለም | ጥቅምት 19/2006 | 186 |
| 44. | • ከወጪና ኪሣራ አወሣሠን ጋር በተገናኘ ከቅን ልቦና ውጪ ለክርክር የተዳረገ ወገን የክርከሩ ረቺ መሆኑ እስከታወቀ ድረስ ቅን ልቦና ከሌላው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት በሚል ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• የወጪና ኪሣራ ጥያቄን | 91103 | ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር<br><br>እና<br><br>እነ የአቶ ፉአድ መሃመድ እናት ወራሽ ወ/ሮ | ታህሳስ 16/2006 | 188 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አስመልክቶ ፍ/ቤቶች በመጠኑ ላይ ለመወሰን በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑና ረቺ የሆነ ወገን ሁል ግዜ ወጪና ኪሣራ እንዲተካለት ሊወሰን ይገባል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 462-464 | | ማሪያም አብዱላሂ (ሁለት ) | | |
| 45. | በሌለበት የተሰጠ ውሣኔ እንዲነሣ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት ፍ/ቤቱ አስቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ ያነሳውና አቤቱታ አቅራቢው ክርክሩን እንዲያቀርብ በድጋሚ እድል ከተሰሠጠው በኂላ የጽሁፍ ክርክሩን ያላቀረበና ክሱ በሚሰማበት ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ክርክሩን እንደገና ለመስማት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የከሣሽ ክስና ማስረጃ እንደገና ተመርምሮ ተገቢው ውሣኔ ከሚሰጥበት በቀር እንዲነሣ ትእዛዝ የተሰጠበት የቀድሞው ውሣኔ በቀጥታ ተመልሶ እንደገና እንዲፀና ሊደረግ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፡<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78(2), 70(ሀ) | 90452 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br><br>እና<br><br>አቶ ገ/ሥላሴ በርሄ | ጥር 14/2006 | 191 |
| 46. | ሀሰተኛ ማስረጃ ለፍ/ቤት በመቅረቡ የተነሣ የተወሰነበት ተከራካሪ ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)ን መሠረት | 91968 | አቶ ግርማ ስንበት እና | ታህሳስ 15/2006 | 194 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማድረግ ፍርዱ በድጋሚ እንዲታይለት አቤቱታ ባቀረበ ጊዜ ሀሰተኛ ማስረጃውን የሰጠው አካል በምን ምክንያት በህገ ወጥ ተግባር ሀሰተኛውን ማስረጃ ሊሰጥ እንደቻለ የማስረዳት ግዴታ ጭምር አለበት ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 403፣405 | | ወ/ሮ አልማዝ ገብረየስ | | |
| 47. | • ተከራካሪ ወገኖች በቅድሚያ ሊያቀርቧቸው ሲችሉ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት ያላቀረቧቸውን ማስረጃዎች በክርክር ሂደት ሁሉ እያንጠባጠቡ ሊያቀረቡ ወይም የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ፍርድ ቤት እንዲያከናውን ሊጠይቁ የሚችሉበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>• በፍ/ቤት እገዛ ማስረጃ የሚቀርበው ተከራካሪ ወገን አጠቃቅሎ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ፍ/ቤቱ የተጠየቀው ማስረጃ ለተያዘው ጉዳይ ያለውን አግባብነት በተመለከተ የተቀበለው እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 234(1) | 85468 | ሣባኢንጂንሪንግኃ.የ ተ.የግልማህበር<br>እና<br>የፕራይቬታይዜሽ ንናየመንግስትልማ ትድርጅቶችተቆጣ ጣሪኤጂንሲ | መስከረም 24/2006 | 197 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 48. | • ተከራካሪ ወገኖች ለክርክራቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለውን ጉዳይ ወይም ያከራከራቸውን ጉዳይ በእርቅ ስምምነት የጨረሱ እንደሆነ የእርቅ ስምምነቱ ግብ ተከራካሪዎቹ (ታራቂዎቹ) በግላቸው ያላቸውን መብትና ግዴታ እንደሁኔታው በማስተካከል ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ጉዳይ በስምምነት ማስቀረት ስለመሆኑና የእርቅ ስምምነቱ ውጤትና ተፈፃሚነቱ እርቁን ባደረጉት ተከራካሪ ወገኖች መካከል ብቻ ተገድቦ የሚቀር እንጂ የሌሎች 3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታ ሁሉ በማካተት የ3ኛ ወገኖች መብትና ግዴታን አብሮ በእርቅ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ስላለመሆኑ፣<br>• የተከራካሪ ወገኖች የእርቅ ስምምነት በፍ/ቤት ትእዛዝ (ውሣኔ) መጽደቅና መመዝገብ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል 3ኛ ወገኖች የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3311<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | 87834 | በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የመሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ፀዳለ ካሣቀ (ሶስት ሰዎች) | መስከረም 21/2006 | 204 |
| 49. | አንድ ፍርድ ቤት ክርክርን በሚሰማበት ወቅት የሚሰጠው ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ | 89893 | ኮንቴክ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | መስከረም 24/2005 | 207 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | (Interlocutory order) ላይ በመነጠል ክርክር የሚካሄድበት ዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችለው የተሰጠው ትእዛዝ በባህሪው የሰውን መታሰር ወይም የንብረት ማስተላለፍን ወይም ስም ማዞርን ጉዳይ በተመለከተ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(3)(4) | | እና<br>አቶ ወልዱ ህሉፍ | | |
| 50. | • የዳግም ዳኝነት (Review of Judgement) ዓይነተኛ ዓላማ ተገቢ ሁኔታዎችና ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸው ሲረጋገጥ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በመደለያና በመሰል ወንጀል ጠቀስ ድርጊቶች ምክንያት የተዛነፈን ፍትህ ወደ ነበረበት መመለስ ስለመሆኑ፣<br>• የዳግም ዳኝነት ጥያቄ (አቤቱታ) ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ተግባራት የሚከናወንበት በመሆኑ ጥያቄው ለሰበር ችሎት በቀረበ ጊዜ ችሎት አቤቱታውን ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ላላቸው የስር ፍ/ቤቶች ሊመራውና ሊያስተላልፈው በሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1)(ሀ)(ለ) | 93137 | ወ/ሮ ብጥር ታገለ<br>እና<br>ወ/ሮ አገር ተሰማ | የካቲት 11/2006 | 210 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) | | | | |
| 51. | በተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚካሄድበት ወቅት በፍ/ቤት ትእዛዝ በተከራካሪ ወገን ስም በባንክ የሚገኝ ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ ተደርጐ ትእዛዙ ፀንቶ በነበረበት ግዜ በገንዘቡ ላይ ወለድ ሊታሰብ ይገባል ወይስ አይገባም በሚል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ ጋር በተገናኘ ፍ/ቤቶች የልዩ አዋቂ ምስክርነትና የባለሙያ ማብራሪያን አስቀርበው በማጣራት ሊወሰኑ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | 83771 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዘነበች አለማየሁ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 10/2005 | 214 |
| 52. | ባለ አምስት ዳኞች የሚሰየሙባቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች በአጣሪው ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል በሚል በተመለከተው ነጥብ (ጭብጥ) ሳይገደብ ሌላ (ሌሎች) ጭብጦችን በመመስረት ክርክሩ እንዲሰማ በማድረግ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣ | 90298 | አቶ ኃይሉ ዴሬሳ<br>እና<br>ወ/ሮ ሱፌ አለሙ | የካቲት 10/2006 | 217 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **የንግድ ህግ** | | | | | |
| 53. | • የንግድ መደብር ኪራይ ከንግድ ቤት ኪራይ የተለየ ስለመሆኑ፣<br>• የንግድ መደብር የተከራየ ሰው ያለአከራዩ እውቅና እና ፈቃድ መደብሩን ለ3ኛ ወገን በኪራይ አሳልፎ ለመስጠት ስለመቻሉ፣<br>የንግድ ህግ ቁ. 127 (ሐ),145(ለ), | 79561 | አቶ ፀጋዬ አማን ለጃ<br>እና<br>በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት | የካቲት 11/2005 | 221 |
| 54. | የንግድ ማህበር ሒሣብ ከተጣራና ትርፍና ኪሣራው ተለይቶ ከቀረበ በኂላ የማህበር አባል (ባለአክሲዮን) የሆነ ሰው ከትርፍ ሊደርሰው የሚገባውን የድርሻ ክፍያ በመለየት ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ፣<br>የንግድ ህግ ቁጥር 211, 517, 518, 532(1) | 82503 | እነ ወ/ሪት ቤዛ ዱጉማ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ዘሚሊ ቀለም ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 21/2005 | 224 |
| 55. | • የህብረት ሥራ ማህበራት ንብረት እንደ የአባለቱ የጋራ ሀብት (ንብረት) ተቆጥሮ ንብረቱን ለመሸጥ የሁሉም አባላት ስምምነት ያስፈልጋል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የህብረት ሥራ ማህበራት አሰራር ጋር በተያያዘ ውሣኔ ለማሳለፍ የሚችለው የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ | 85009 | ሃጅ ፈዩ ገመቹ ሄዳኦ<br>እና<br>እነ አቶ ዓለሙ በቀለ (አስራ አምስት ሰዎች) | መስከረም 21/2006 | 229 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 147/91 አንቀጽ 21, 18, 32, 19<br>ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 20(2) 123 | | | | |
| 56. | አበዳሪ የሆነ ባንክ ለተበዳሪው ላበደረው ገንዘብ በመያዣነት ለያዘው ንብረት የመድን ሽፋን የገባለት እና የአርቦን ክፍያን ለመክፈል የተስማማ እንደሆነ ለመድን አስገቢው ተቋም የአረቦን ክፍያውን ለመክፈል የሚገደድ ስለመሆኑ፣<br>• የንግድ ህግ ቁጥር 657, 675 | 83489 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | ግንቦት 19/2005 | 233 |
| **ቤተሠብ** | | | | | |
| 57. | ከሟች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠን ንብረት ወደ ውርስ መልሶ ማግባት (Collation) ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1065-1078 | 80920 | ወ/ሮ ውድነሽ እሸቱ<br>እና<br>አቶ ፍቅረማሪያም ወርቁ | የካቲት 25/2005 | 237 |
| 58. | ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ ክስ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973, 974 | 82585 | እነ ወ/ሮሱዛንሞንታልባን (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ ሙራድ | የካቲት 13/2005 | 240 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አሊ. (ስድስት ሰዎች) | | |
| 59. | ከውርስ ሀብት ክፍፍል ጋር በተገናኘ የውርስ ሀብት ተጣርቶና ሪፖርት ቀርቦ በመጽደቁ መነሻነት ሀብቱ ተከፋፍሎ ከተፈፀመ በኋላ ወራሾቹ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሣይኖራቸው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ አድርጓል በሚል እውነተኛ ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰዱበት የውርስ ንብረቶች እንዲመለሱለት በሚል ለመጠየቅ የሚችለው ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ በመክፈል አዲስ ክስ በመመስረት እንጂ ክፍፍሉ ተፈጽሞና ውሣኔ አግኝቶ የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ስላለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996(1), 998(1), 999<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91, 6 | 89641 | እነ ወ/ሮ ሐረገወይን ብርሃኑ(ሁለት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>እነ ወ/ሮ አዜብ ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 21/2006 | 243 |
| 60. | ተጋቢዎች የጋብቻቸውን ፍቺ አስመልክቶ ጉዳዩ በመደበኛው ፍ/ቤት ቀርቦና ክርክር ተካሄዶ ውሣኔ ከተሰጠበት በኋላ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጉዳይ ሀይማኖታዊ ስርዓትን በመጠቀም በሸሪአ ፍ/ቤት | 93779 | ወ/ሮ ጃእቶ ያሲን ሺበሺ<br><br>እና<br><br>አቶ ሐሰን | ታህሳስ 30/2005 | 247 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(1)(2), 244(2)(ለ), 245(2)<br><br>አዋጅ ቁጥር 188/92 አንቀጽ 5(4), 6(2)<br><br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 34(5) | | መሐመድ | | |
| 61. | • የአባት ስም እንዲስተካከልልኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የለውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አንድ ሰው አንድ የቤተዘመድ ስምና አንድ ወይም ብዙ የግል ስሞችና የአባት ስም ሊኖረው ስለመቻሉና የአንድ ልጅ የአባት ስም የሚሆነው የአባቱ የግል ስም ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231 (1)(ሀ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 32(1)፣ 36(1) | 95995 | ወ/ት ሞሚና ሡልጣን ኮርዋላ<br><br>እና<br><br>ተጠሪ፡- የለም | የካቲት 10/2006 | 251 |
| 62. | የቤተ ዘመድ ስም እንዲለወጥ በፍ/ቤት ጥያቄ ለማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 42 , 33(1) , (2) | 87420 | ወ/ሪት ማህሌት ልዑለቃል<br>እና<br>ተጠሪ የለም | ሚያዝያ 24/2005 | 254 |

# ጉምሩክ/ግብር/ታክስ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 63. | ግብርየተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማጽደቅ ስልጣን ያለው (የተሰጠው) የመንግስት አካል ግብሩ መከፈሉን ሣያረጋግጥ ዝውውሩን እንዲቀበል፣ እንዲመዘግብ ወይም እንዲያፀድቅ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 37(7) | 79189 | የኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>ጂ.ኤም.ቲ ኢንዱስትሪያል ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 9/2005 | 258 |
| 64. | • አንድ ሰው ለመንግስት ሊከፍል የሚገባውን ግብር ባለመክፈሉ በወንጀል ተግባር ሊጠየቅና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችለው ግብሩን ላለመክፈል በማሰብና ግብር አስገቢው መ/ቤትም ንብረቶቹን በመያዝና በመሸጥ የግብር ገንዘቡን ገቢ እንዳያደርግ ለማድረግና ግብር የመክፈል ኃላፊነቱን ለማምለጥ ንብረቶቹን ለማሸሽ፣ የመሰወር ወይም ሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ህገ ወጥ ተግባራትን በመፈፀም ግብርን ያልከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በሌሎች በህግ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች ግብሩን ለመክፈል ሳይችል የቀረ እንደሆነ ስላለመሆኑ፣ | 84623 | እነ ጅ. አግሪ ፖክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | ሰኔ 04/2005 | 261 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • ማንኛውም ሰው በፍ/ብሔር ጉዳይ ያለበትን እዳ ለመክፈል ባለመቻሉ ምክንያት ብቻ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የማይገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 285/94 አንቀጽ 49<br>አዋጅ ቁ. 286/94 አንቀጽ 96, 162<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 13(2)<br>ደንብ ቁጥር 78/94<br>ICCPR- አንቀጽ 11 | | | | |
| 65. | የንግድ ሥራ ፈቃድ ኖሮት ነገረ ግን በህግ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱ ሳይታደስ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ሰው የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሌለው ተቆጥሮ በወንጀል ኃላፊነት ጥፋተኛ ተደርጐ ሊያስቀጣው የሚችል ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 686/2002 አንቀጽ 2(10), 36, 60(1) | 86388 | አቶ ባዘዘው ይሁን<br>እና<br>የአ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ | ሰኔ 17/2005 | 268 |
| 66. | ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በተገናኘ ከሚመለከተው የገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ተገቢ ያልሆኑ ፓዶችን (የVAT ደረሰኞችን) ማሳተምና መገልገል በወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል | 86597 | ግሎሪ ኢትዩጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር | መስከረም 21/2006 | 271 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑና የድርጅቱ ባለሀብት (ሥራ አስኪያጅ) ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው ያልነበረ መሆኑን በመግለጽ የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ማንኛውም በጉ አሳቢ ሰው ሊያደርገው የሚችለውን ጥንቃቄ ያደረገና ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ድርጅቱን በመምራት ኃላፊነቱን የተወጣ መሆኑን ማስረዳት የቻለ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56(3),(ለ), 3(1)(ለ), 2(11), 3(1)(ሀ) አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 2, 19(50) (ሐ) | | እና<br>አቶ በርሀ ረዳ ኪዳኑ | | |
| 67. | አንድ በንግድ ሥራ የተሰማራ ሰው (ድርጅት) በተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት ለማለት የሚቻልበት እንዲሁም መመዝገብ ሲኖርበት ሳይመዘገብ ቀርቶ ግብር ሊጣልበት ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁ.285/94 አንቀጽ 3(1)(3), 16(1)(ለ) | 82061 | አቶአብዱልቀድር ሁሴን<br>እና<br>የአዲስከተማክፍለ ከተማአነስተኛግብ ርከፋይቅርንጫፍ ጽ/ቤት | መስከረም 20/2006 | 274 |
| 68. | የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ ነጋዴ (ሠው) ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭን አከናውኗል በሚል በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን | 86672 | የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ | መስከረም 22/2006 | 277 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለሚችልበት አግባብ፣<br>አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 11(1)(2)፣ 22(1)(3)<br>አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 11(1)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2)፣ 58(3)<br>ደንብ ቁጥር 139/1999 | | እና<br>አቶ በቀለ ተሰማ (ሁለት ሰዎች) | | |
| 69. | • ከጉምሩክ ህግና አፈፃፀም ጋር በተያያዘ በኮንትሮየባንድ ወንጀል ተጠርጥሮ በጉምሩክ ተቋም በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተደረገ የንግድ ተሸከርካሪን አስመልክቶ ለንብረቱ ባለቤት የተቋረጠ ጥቅም (ገቢ) እንዲከፈል ሲወሰን የካሣውን መጠን ለመወሰን የተሸከርካሪውን ዓመታዊ የተጣራ ገቢ በተመለከተ ባለንብረቱ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በህጉ አግባብ ያሳወቀውን የገቢ መጠን ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብና መሠረት በማድረግ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• በአንድ የመንግስት ባለስልጣን ተረጋግጦ የተሰጠ የሰነድ ማስረጃ በህጉ መሠረት ተቃውሞ ቀርቦበት ዋጋ የሌለው ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማስረጃው በማስረጃነት ዋጋ ሣይሰጠው ሊታለፍ የሚችልበት | 89640 | የገቢዎችናየጉምሩ ክባለስልጣን<br>እና<br>ሰይፈዲን አብዱልቃድር | መስከረም 23/2006 | 281 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አግባብ የሌለ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010, 2011, 2090, 2091, 2141, 2152, 2153<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136, 138, 180 (1) | | | | |
| **ንብረት** | | | | | |
| 70. | የአንድ እምነት ወይም ሐይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ በመሆን በሐይማኖታዊ ተቋሙ ውስጥ የመቃብር ቤት ገንብቻለሁና የቤቱን ግምት ይከፈለኝ በሚል ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር በተገናኘ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179 ድንጋጌ ተፈፃሚ ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1179<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 11,27 (1-3)<br>UDHR-Art. 18<br>ICCPR.Art. 18(1) | 85979 | የሐረር (ደ/ሳ) ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን<br>እና<br>ወ/ሮ ማንያህልሻል አበራ | መጋቢት 13/2005 | 286 |
| 71. | ከመንግስት የተከራየውን ቤት ከአከራዩ ፈቃድ ውጪ ለ3ኛ ወገኖች አከራይቶ ሲገለገል የነበረ ሰው በመንግስት መመሪያ መሠረት ቤቱ ተከራይቶ ሲሰራበት ለነበረው ሰው በመተላለፉ ምክንያት የመጀመሪያው ተከራይ በመመሪያው መሠረት ቤቱ የተላለፈለት ሰው ላይ የሚያቀርበው | 88798 | አቶ ሙሉ አብርሃ ገ/ሕይወት<br>እና<br>እነ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 አስተዳደር ጽ/ቤት | ሐምሌ 18/2005 | 291 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | | (ሶስት ሰዎች) | | |
| 72. | •የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚቻለው አቤቱታ አቅራቢው ለክርክሩ መነሻ በሆነው ነገር በቀጥታ ወይም በጥበቃ ሥር የሆነ ይዞታ ሲኖረው ስለመሆኑ፣ •የይዞታ ክስ የሚቀርበው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት በወቅቱ ለመያዝ ምንም አይነት መብት በሌለው ሰው ላይ ስለመሆኑ፣ •የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ንብረቱ በይዞታው ሥር የነበረና የሁከት ድርጊት ፈፃሚዉ የኃይል ተግባር በመጠቀም ወይም በሚስጥር ንብረቱን የወሰደበት መሆኑን ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ፣ •የሁከት ተግባር ተፈጥሯል ለማለት ባለይዞታ የሆነው ሰው በይዞታው ሥር በሚገኘው ንብረት እንዳይገለገልበት ሌላ ሰው ጣልቃ ገብቶበት መሰናክል ወይም ረብሻ የፈጠረበት ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ፣ •በህግ አግባብ በተደረገ የኪራይ ውል መነሻነት ይዞታን በእጁ ያደረገ ሰው (ተከራይ) ላይ አከራይ የሚያቀርበው | 80241 | ጽናት የሆቴል ቱሪዝም ስራዎች ኃ.የተ.የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ ዳመነ ነጋ (አምስት ሰዎች) | የካቲት 12/2005 | 295 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | | | | |
| 73. | የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተገናኘ ንብረትነቱ ከአገር የወጡ ኤርትራዊያን የሆነ ቤትን ለማስተዳደር ውክልና የተሰጠው ሰው የመሸጥ ውክልና በባለቤቱ ያልተሰጠ ቢሆንም እንኳን በሚመለከተው የመንግስት አካል በተሰጠ (በተላለፈ) መመሪያ መሠረት ከተወካዩ ቤቱን የገዛ ገዥ ተወካዩ ቤቱን የሸጠለት በሌለው የውክልና ስልጣን ነው በሚል ገዝቶ ስመ ንብረቱ ከተላለፈለት በኋላ የሽያጭ ውሉ ፈርሶ ቤቱ ለባለቤቱ ሊመልስ ይገባል ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 2(1), 4(1), 5(1)(ሀ) | 83060 | ገ/ማሪም ገ/መድህን<br>እና<br>ጣዕመ ወ/ስላሴ | ሰኔ 21/2005 | 300 |
| 74. | የውርስ ሀብትን እንዲያጣራ የተመደበ የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረትነቱ የሟች የግል ሀብት መሆን በተመለከተ በሪፖርቱ ገልጿል በሚል ምክንያት ከንብረቱ ጋር በተገናኘ የባለሀብትነት ክርክር ያቀረበውን ወገን ጥያቄ በአግባቡ ባለማስተናገድ ውሣኔ ላይ መድረስ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ | 83665 | ወ/ሮ እታፈራሁ ፀጋዬ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሰረት ግርማ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2005 | 305 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መግስት አንቀጽ 40(1), 37<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1206 | | | | |
| 75. | • አንድ ሰው ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚችለው በህግ ጥበቃ የሚደረግለትንና ያለውን መብት እንጂ የሌላውን መብት ስላለመሆኑ፣<br>• በህግ ጥበቃ የሚደረግለት መብት ሣይኖር በስሙ የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቅተ ከያዘ ሰው ንብረቱን በመንደር ውል የገዛ ገዢ ተገቢውን ማጣራት በማድረግና፣ በጥንቃቄ፣ የገዛና የቅን ልቦና ያለው ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ደንብና አሰራርን መሠረት ያላደረገ እንዲሁም ከስልጣን ውጪ የተሰጠና በህግ ፊት የማይፀና ስለመሆኑ በማናቸውም ማስረጃ ለማረጋገጥ የተቻለ እንደሆነ በተሰጠው የምስክር ወረቀት የተፈጠረውን የህጉን የህሊና ግምት ማፍረስ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, 1196, 2884, 2882-2884 | 88084 | ወ/ሮ ወጋየሁ ታምሩ<br>እና<br>እነ የወ/ሮ አስካለ ወሰኔ ወራሽ ፍሬዘውድ ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 19/2006 | 309 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(1)(2) | | | | |
| 76. | ፍርድ ቤቶች ከሣሽ በክሱ ገልፆ በትክክል ዳኝነት የጠየቀበት ጉዳይ በቤት ላይ ያለውን የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና የመፋለም ክስ ሆኖ እያለ ክሱ የቀረበው በአዋጅ የተወረሰ ቤት ወይም ከአዋጅ ውጪ በባለስልጣን ቃል ትእዛዝ ወይም በቀላጤ የተወሰደን ቤት ለማስመለስ ነው በሚል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሚሰጡት ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ፣ <br> አዋጅ ቁጥር 47/67 <br> የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2257 | 86049 | አቶ ሻፊ አብዱራህማን አብዱ <br> እና <br> ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ (ሶስት ሰዎች) | መስከረም 20/2006 | 313 |
| **ከውል ውጭ ኃላፊነት** | | | | | |
| 77. | ከውልውጪ በሆነ ግንኙነት አንድ ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ንብረት ባለቤት ለንብረቱ የመድን ዋስትና የገባ ሆኖ የመድን ተቋሙ በመድን ውሉ መሠረት ጉዳት ለደረሰበት ወገን የጉዳት ካሣ በመክፈል በጉዳት አድራሹ ንብረት ባለቤት ላይ ብቻ ክስ በመመስረትና ጉዳቱን በቀጥታ ያደረሰውን ሰው በመተው ጉዳቱ | 89504 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ <br> እና <br> እነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን (ሁለትት ሰዎች) | መስከረም 22/2006 | 317 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለደረሰበት ሰው የከፈለውን የጉዳት ካሣ ክፍያውን እንዲከፍለው ለመጠየቅ ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677, 1896, 2081, 18, 2156<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 36(2) | | | | |
| 78. | • ባለፎቶግራፍ ወይም ባለስዕሉ ካልፈቀደ በቀር የማንም ሰው ፎቶግራፍ ወይም ስዕል በህዝብ አደባባይ ሊለጠፍም ሆነ ሊባዛ ወይም ሊሸጥ የማይችል ስለመሆኑና ፎቶው ወይም ስዕሉ ጥቅም ላይ ለዋለበት የማስታወቂያ ሥራ ባለፎቶው ወይም ባለስዕሉ ካሣ ሊከፈለው የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>• ለባለ ፎቶው ወይም ለባለስዕሉ የሚከፈለውን የካሣ መጠን ድርጊቱን የፈፀመው ሰው በዚሁ ድርጊት ያገኘው ሀብት (ጥቅም) ተመዛዛኝ በሚሆንበት መጠን በዳኛች ሊወሰን ስለመቻሉ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 28 29(2), 2142 | 91710 | ሕጻን ሪያን ሚፍታህ<br>እና<br>ኤልሲውዲ ኤብልስ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር | ህዳር 16/2006 | 319 |
| 79. | • ጥቅምን መሠረት ባላደረገ ሁኔታ ህፃናትን (እድሜው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰውን) አሳፍሮ በመንዝ ወቅት በደረሰ አደጋ ምክንያት በህፃናቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ | 92020 | እነ የኢ.ፌ.ዲ.ፌ ፌዴሬሽን ምክር ቤት (ሁለት ሰዎች) | ታህሳስ 15/2005 | 323 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተሽከርካሪው ባለቤትና በወቅቱ በተሽከርካሪው ሲገለገል የነበረ ወይም ሹፌሩ የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርባቸው ስለመሆኑ፣<br>• የተሽከርካሪ ባለቤት የሆነ ሰው ጥቅም በሌላው ግንኙነት መነሻ በተሽከርካሪው ተሳፍሮ ሲጓዝ በነበረ ሰው ላይ ለሚደርስ የአደጋ ጉዳት ካሣ ለመክፈል የማይገደድ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ሊደረግላቸው በሚገባ ህፃናት ላይ በሆነ ጊዜና ህፃናቱም ጥንቃቄ ባልተሞላበት ሁኔታ በተሽከርካሪው ላይ የተጫኑ (የተሣፈሩ) እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(2), 15, 25<br>የህፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 3, 6(1)<br>የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4(1), 5(1)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126(2), 2127, 2130 2131, 2089(2), 2081(1) | | እና<br>ቄስ ማሞ ይታፈሩ | | |
| 80. | አንድ ሠው በሰራው ሥራ ወይም በፈፀመው ድርጊትና ድርጊቱ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል | 88432 | ወጣት ደሣለኝ ወንታ | መስከረም 22/2006 | 327 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት በ3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በፍ/ብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆን ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2069 | | እና<br>አቶ ኡስማን መሐመድ | | |
| 81. | •አንድ የመንግስት መ/ቤት በሠራተኛው ተግባር በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችለው በሠራተኛው የተፈፀመው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ፣<br>•አንድ ጥፋት የሥራ ጥፋት ነው ተብሎ የሚወሰደው ጥፋት አድራጊው በጥፋቱ ላይ የወደቀው በቅን ልቦና በስልጣኑ ለሥራው ክፍል መልካም ያደረገ መስሎት የፈፀመው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑና ከዚህ ውጪ በሆነ ጉዳይ ግን ጥፋቱ እንደ ግል ጥፋት የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2126, 2127 (1)(2)(3) | 82154 | አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ<br>እና<br>ተጠሪ፡ አቶ ፍቅሩ ኃይሌ | መጋቢት 24/2005 | 330 |
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | |
| 82. | ከንግድ ምዝገባ ፈቃድ ጋር በተገናኘ የሚነሱ የፍሬ ነገር ክርክሮችን የመደበኛ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ፣ | 81934 | የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ንግድና ኢንዱስትሪ | የካቲት 28/2005 | |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁ. 686/2002 አንቀጽ 61 | | ጽ/ቤት<br>እና<br>50 አለቃ ታምራት ከበደ | | 336 |
| 83. | ከአስጉብኚና የጉዞ ወኪል የንግድ ሥራ ፈቃድ ጋር በተያያዘ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ መኪኖችን በተመለከተ የሚቀርብ ክርክርን መደበኛ ፍ/ቤቶች በቀጥታ ክስ ለማስተናገድ የሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 87(1), (5), (9), (10),<br>ደንብ ቁጥር 146/2000 | 86817 | የኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን<br>እና<br>ግሎሪ ኢትዩጵያ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ኃ.የተ.የግል ማህበር | መስከረም 22/2006 | 338 |
| 84. | የክርክሩ ገንዘብ መጠን ከአምስት ሺህ ብር በታች በመሆኑ ምክንያት ብቻ ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ጋር በተገናኘ የሚቀርብን ክርክር የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አይተው ለመወሰን ስልጣን አላቸው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 138, 142<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(1), 231(1)(ለ),<br>አዋጅ ቁ. 416/96 አንቀጽ 41(1), | 89530 | ቲኤንቲ ኮንስትራክሽንና የንግድ ስራዎች ድርጅት<br>እና<br>አቶ እያዩ ደጀኔ | ጥቅምት 21/2006 | 341 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 85. | ከህብረት ሥራ ማህበራት ጋር በተገናኘ የማህበር የሥራ ኃላፊዎችን በተመለከተ ገንዘብ አጉድለዋል በማለት ገንዘቡ እንዲከፈል ማህበሩ በኃላፊዎቹ ላይ የሚያቀርበው ክስ አስቀድሞ በእርቅ ካልተቻለ ደግሞ በሽምግልና ሊታይ የሚገባው እንጂ በቀጥታ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ ሊቀርብበት አይችልም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑና መደበኛ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 49(1-4), 47(1), 26(2), 39(1)(ለ)(ሐ), 152<br>አዋጅ ቁጥር 402/96 አንቀጽ 46<br>ደንብ ቁጥር 106/96 አንቀጽ 14(ሀ)(ሐ)(መ) | 90737 | የንጋት ኮከብ ሸማቾች ኃ/የተ የግል ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ የሴፍ እንድሪስ (አስር ሰዎች) | ህዳር 16/2006 | 344 |
| 86. | አንድን ክርክር በማስተናገድ ላይ ያለ የክልል ፍ/ቤት በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ተቋም (ድርጅት) አግባብነት ያለው የጣልቃ ገብ አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ጉዳዩን ጣልቃ ገቡን ወደ ክርክሩ በማስገባት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክርክሩ ጣልቃ ገብን ባካተተ መልኩ ለማየት ወደሚችለውና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዩ ቀርቦ | 90920 | ዓባይ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>አቶ አለማየሁ አሰፋ | ህዳር 06/2006 | 347 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊታይ የሚገባ መሆኑን ገልፆ መዝገቡን መዝጋትና ተከራካሪዎችን ማሰናበት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(6),14<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4)<br>የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(4)<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9, 231(1)(ለ) | | | | |
| **ወንጀል** | | | | | |
| 87. | አንድ ሠው በፍ/ብሔር ጉዳይ ተከስሶ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኂላ በተመሳሳይ ማስረጃ በወንጀል ጉዳይ ተከስሶ ተጠያቂ ነው (ኃላፊነት አለበት) ለማለት የሚያስችል የህግ አግባብ ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2149<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 141 | 78470 | አቶ ታሪኩ ጫኔ<br>እና<br>የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | ሚያዝያ 07/2005 | 351 |
| 88. | አንድ ሠው በአንድ ወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ የሆነ ውሣኔ ተሰጥቷል በማለት በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ከዚህ ቀደም ተጣርቶ ክስ የቀረበበትና የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት የወንጀል ድርጊትን በድጋሚ (ለሁለተኛ ጊዜ) ክስ | 85237 | ዘካሪያስ ገ/ጻዲቅ<br>እና<br>የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ | መጋቢት 27/2005 | 355 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቀርቦበታል ከተባለው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2(5), 678, 696(ሐ) እና 378<br>ህገ መንግስት አንቀጽ 23 | | | | |
| 89. | በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ተከሣሽ ላይ የሚወሰነው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም እንዲገደብ ለማድረግ ስለማይችልባቸው ሁኔታዎች፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 194(1) እና (2)¸190¸192 | 85596 | እነ ሰይፉ ደስታ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ | መጋቢት 25/2005 | 359 |
| 90. | ህጋዊ መከላከል (Legitimate self-defense) በወንጀል የማያስቀጣው የራስን ወይም የሌላን ሰው መብት ህገ ወጥ ከሆነ ጥቃት ወይም በቅርብ ከሚደርስ ህገ ወጥ ጥቃት ለማዳንና ጥቃቱ እንዳይደርስ ከማድረግ ሌላ አማራጭ (መንገድ) ሣይኖር ከሁኔታው መጠን ባለማለፍ የተፈፀመ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 78 ,79 | 86570 | ጌታቸው ገላዬ ፈረደ<br>እና<br>የደቡብ ክልል ዐቃቤ ሕግ | ሚያዝያ 07/2005 | 363 |
| 91. | • አንድ ሠው የአራጣ ወንጀል ድርጊት ፈጽሟል በሚል በወንጀል | 80119 | አቶ ተድላ ተገኘ | የካቲት 11/2005 | 367 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>• በወር 10% ወለድ ታስቦ እንዲከፈል በመስማማት ገንዘብ ማበደር በአራጣ የወንጀል ድርጊት የሚያስጠይቅ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ 667(1) | | እና<br>የአማራብሔራዊክ ልላዊመንግስትፍ ትህቢሮ | | |
| 92. | • በሌላ ሰው ጥቅም የሥራ አመራር ላይ ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• በተከታታይ ለተፈፀመ ወንጀል ይርጋ ስለሚቆጠርበት አገባብ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/፣702/3/፣219/2/ | 79389 | እነ ዶ/ር ታጀዲን ያህያ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የአማራ ክልል ዐ/ሕግ | መጋቢት 12/2005 | 371 |
| 93. | አንድ ሰው በስራው ስልጣን መሠረት በአደራ የተሰጠውን ወይም ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የህዝብ ወይም የመንግስት ጥቅም የሚጐዳ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ በወንጀል ህግ አንቀጽ 411 መሠረት በወንጀል ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ፣<br><br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 411(ሐ), 407 | 86845 | የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ህግ<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ዩሐንስ | መስከረም 22/2006 | 374 |
| 94. | • የአንድ ደርጊት ወይም ግድፈት ወንጀልነት በህግ በግልጽ ተደንግጐ በማይገኝበት ሁኔታ | 81178 | የኢዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ | መስከረም 21/2006 | 380 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የድርጊቱን ወይም የግድፈቱን ፈፃሚ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>• በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለ ድርጊቱና አፈፃፀሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር በጣም የተቀራረበ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>• በንግድ ሥራ ለተሰማሩ ወይም ሌሎች ሰዎች በግለሰብ ደረጃ መጠኑ በርካታ የሆነ ገንዘብን በተደጋጋሚ በብድር የመስጠት ተግባር በህግ የተከለከለ ወይም በወንጀል የሚያስቀጣ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2, 23(2), 3, 61<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 112<br>አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 59(1), (ሸ), 2(ሀ), | | እና<br>እነ አቶ ከበደ ተሰራ (ሁለት ሰዎች) | | |
| 95. | ነፍሰጡር (እርጉዝ) የሆነች ሴትን ሆዷ ላይ በመምታት ጽንሱ እንዲሞት ማድረግ ድርጊቱን በፈፀመው ሰው ላይ በግድያ ሙከራ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 27(1), | 90089 | ዘኒት አባቡ<br>እና<br>የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ዐ/ህግ | ጥቅምት 20/2006 | 384 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | 581(ለ), 540 | | | | |
| 96. | • አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሟል ሊባል የሚችለው የድርጊቱን ውጤት እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ድርጊቱ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ማወቅ ይችል ነበረ ለማለት የሚቻል እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>• አንድ ሰው የፈፀመው ድርጊት በቸልተኛነት ነው ለማለት በመስፈርትነት ሊወሰድ የሚገባው የድርጊቱ ፈፃሚ በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ስለመሆኑና ይህም የድርጊቱ ፈፃሚ የነበረው እውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባውን እውቀትና ግንዛቤ መመዘን ያለበት ከግለሰቡ እድሜ፣ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 59(1), 543(2), 57 | 93741 | አቶ አብነት ዋቆ ብሩ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ዐቃቤ ህግ | ታህሳስ 14/2005 | 387 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 97. | ፈቃድ የሌላቸው የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶችን በቤቱ ውስጥ አከማችቶ የተገኘ ሰው መሣሪያዎቹን ለመነገድ በሚል ሀሳብ የያዘ መሆኑ የተረጋገጠ ካልሆነ በስተቀር ግለሰቡ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ) ሣይሆን በአንቀጽ 809(ሀ) ሥር በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ስለመሆኑ፣<br><br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 481(1)(ሀ), 809(ሀ) | 93173 | እነ አቶ ተዋበ እስጢፋኖስ (ሁለት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ | ታህሳስ 17/2006 | 391 |
| 98. | አንድ ሠው የአንድን ጉዳይ መከሰት በምክንያትነት በመግለጽ ከሌላ ሰው ገንዘብን ተበድሮ መውሰድ ተከስቷል የተባለው ጉዳይ ካለመከሰት ጋር በተገናኘ ተበዳሪው በእምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችል ስላለመሆኑ፣<br><br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 675 | 89276 | ተፈሪ ሚናሞ<br><br>እና<br><br>የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ዐቃቤ ሕግ | መስከረም 23/2006 | 395 |
| 99. | • አንድ ሠው ወንጀል አደረገ የሚባለው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ስለመሆኑና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች | 91535 | አቶ አህመድ አደም በሽር<br><br>እና<br><br>የአማራ ብ/ክ/መንግስት | የካቲት 12/2006 | 400 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ስለመሆኑ፣<br>• ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በሙላ አሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆኑ ድርጊቱን የራሱ ያደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 2፣23(1)፣ 32(1)<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣112፣141፣142 | | ዐ/ሕግ | | |
| **ባንክ እና ኢንሹራንስ** | | | | | |
| 100. | የመድን ዋስትና ሽፋን ውል ተደርጓል እንዲሁም ውሉ ተሻሽሏል ለማለት ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>የንግድ ህግ፡ 657 | 78180 | አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር ንጉሴ | መጋቢት 09/2005 | 405 |
| 101. | • አንድ ውል በቂ የሆነ እርግጠኛነት ያለውና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ ለማከናወን ሊደረግ የሚገባ | 90793 | ግሎባል ኢንሹራንስ | ታህሳስ 04/2006 | 410 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፣<br>• የመድን ዋስትና ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ከትራንስፖርት ጋር በተገናኘ በወጡ ህጎች ከተፈቀደው የመጫን አቅም በላይ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ አደጋ የደረሰበት እንደሆነ መድን ሰጪው የዋስትናውን ሽፋን ገንዘብ ለመድን ገቢው የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) | | እና<br>እነ አቶ ፍጹም ላቀው (ሁለት ሰዎች) | | |
| **አፈፃፀም** | | | | | |
| 102. | • በውጭ አገር የተሰጠን ፍርድ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለማስፈፀም ስለሚቻልበት አግባብ፣<br>• በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድን በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ከማስፈፀም ጋር በተያያዘ በአፈፃፀም ሂደቱ ክርክር በተነሣ ግዜ የፍርድ አፈፃፀሙን በያዘው ፍ/ቤት ክርክሩ ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 458-460 | 78206 | እነ ወ/ሮ ዩስራ አብዱልመኢን (ሶስት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ አብዱልቀኒ አብዱልሙኢን | ሰኔ 20/2005 | 415 |
| 103. | • በአንድ የፍርድ ባለእዳ ንብረት ላይ ፍርድ እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁ የፍርድ ባለገንዘቦች ያሉ እንደሆነ አፈፃፀሙ | 88867 | ሪዩስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር<br>እና | ታህሳስ 28/2006 | 423 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 መሠረት ሊስተናገድ የሚገባ እንጂ በሌላ የፍ/ባለመብት ምክንያት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ የአፈፃፀም ጥያቄው ካልቀረበ በስተቀር ሊቀጥል አይችልም ለማለት የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አፈፃፀሙ በሚካሄድበት ወቅት በንብረቱ ላይ የመያዣ ውልን መነሻ በማድረግ የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖች ያሉ እንደሆነም ጥያቄው በቀረበ ጊዜ እንደየአግባብነቱ ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ስለመሆኑ፣<br>• አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በንብረቱ ባለቤት ላይ የገንዘብ ክፍያ ፍርድ አሰጥተው እና ገንዘቡም እንዲከፈላቸው ጥያቄ ያቀረቡ የፍርድ ባለገንዘቦችን አስቀርቦ ጥያቄያቸውን በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አኳያ አገናዝቦ በመመልከት አፈፃፀሙ ሊመራ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403, 378 | | የአክሱም ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ጌታሁን ሁሴን | | |
| 104. | ለፍርድ አፈፃፀም ከተያዘ የሀራጅ ጨረታ ሽያጭ ጋር በተገናኘ ለሁለተኛ ጊዜ በወጣው ጨረታ | 89088 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ታህሳስ 17/2006 | 426 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተያዘው ንብረት ሊሸጥ የሚገባው ባለሙያ ካቀረበው የንብረቱ ግምት ዋጋ በላይ በተገኘ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ብቻ ሣይሆን የባለሙያው ግምት ሳይጠበቅ በሁለተኛው ጨረታ ከተወዳዳሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነውን ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 428(1) | | እና<br><br>አቶ ሞላ እርቂ | | |
| 105. | አንድን የተሰጠ ፍርድ ከማስፈፀም ጋር በተገናኘ የአፈፃፀም ስልጣን መሰረቱ ፍርዱን መስጠት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችል ውክልና ማግኘት እንጂ የፍርድ ባለዕዳውን ወይም ባለመብቱ የሚኖርበት ክልል (ከተማ) ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | 85764 | እነ አቶ ኃ/ሚካኤል ታደሰ (አራት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>አቶ ተስፉ ታደሰ | መስከረም 21/2006 | 429 |
| | **ልዩ ልዩ** | | | | |
| 106. | የመሬት አስተዳዳር ጽ/ቤት ቀድሞ የተሰጠን የቤትና ቦታ ካርታና ፕላን ጠፍቷል በሚል ሲጠየቅ በምትኩ ሌላ ሊሠጥ የሚገባው በ3ኛ ወገኖች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት | 81023 | አቶ ገላና ኦልጅራ<br><br>እና<br><br>እነ አቶ ገዛኸኝ ፋይስ (ሶስት | ግንቦት 5/2005 | 433 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለማስወገድ በቅድሚያ ጠያቂው በቂ ዋስትና እንዲሰጥ በማድረግ ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1197(2) | | ሰዎች) | | |
| 107. | •አንድ የመንግስት ሠራተኛ መ/ቤቱን በመወከል ተቋሙ ከ3ኛ ወገን ጋር ካለው አለመግባባት ጋር በተገናኘ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት በዳኝነት ተሰይሞ ለጉባኤው የሚከፈለውን አበል ክፍያ መወሰኑ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ሊያስብለው የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>•በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ዳኝነት የተሰየመ ዳኛ በህግ ስላለበት ኃላፊነት፣<br>•የግልግል ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰው በግልግል ዳኝነቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ በወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 351(2)(መ), 317, 318(መ)<br>የወንጀል ህግ አንቀጽ 399<br>የአ.አ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አዋጅ ቁ. 6/2000 አንቀጽ 31 | 80301 | አቶ አንተነህ ሲሳይ<br>እና<br>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ | ሚያዝያ 24/2005 | 440 |
| 108. | የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታነት፣ ወይም ወደ አክስዮን | 88060 | የኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አ/ማህበር | መስከረም 23/2006 | 444 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ማህበር፣ በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለሀብቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ ሒሣቦችን ለመሰብሰብ ዕዳዎችን ለመረከብና የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ለመከታተል ስልጣን የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 208/92 አንቀጽ 5፣6 | | እና<br>አቶ ምስጋናው ጥሩነህ | | |
| 109. | • የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማስተዳደር ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>• የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በህግ የተሰጠውን የማስተዳደር ስልጣን መሠረት በማድረግ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬት በተመለከተ የከተማዋን መሪ ፕላን እንዲሁም የከተማውን ማህበረሰብ ፀጥታና ደህንነት ታሣቢ በማድረግ በከተማው የሚገኝ ቦታ (መሬት) ለምን ለምን አገልግሎት መዋል እንዳለበት የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት ያለው ስለመሆኑና ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደ የሁከት ተግባር | 88959 | የልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ደብረ አማን ተክለኃማኖት ቤተክርስቲያን | ህዳር 17/2006 | 447 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊቆጠር የማይችል ስለመሆኑ፣<br>• አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 11(2)(ለ)(ሰ), 38 | | | | |
| 110. | በአቃብያነ ህግ ሙያ የተሰማሩ ሠዎች ላይ ከዲሲፒሊን ጉዳዬች ጋር በተያያዘ ክስ በቀረበ ጊዜ ጉዳዩ በተዋረድ በተቋቋሙትና ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ታይቶ ሊወሰን ስለሚችልበት አግባብ፣<br>የአቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁ. 44/1991 አንቀጽ 78, 79, 82(1)(2), 83(1)(3), 84(ሀ), 85, 86(ሀ)<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 25, 37 | 92546 | አቶ አብዱራዛቅ ኢብራሒም<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ህግ | ታህሳስ 18/2006 | 450 |
| 111. | አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ከውጭ ምንጭ በህጉ ከተመለከው የገንዘብ መጠን በላይ እንዲሰበሰብ ሊፈቅድ የማይችል ስለመሆኑ፡-<br>አዋጅቁ.621/2001<br>አንቀጽ2/2/፣3/4/፣14/5/፣14/2/፣6፣90፣111/2/፣112፣108፣110<br>ደንብ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 18/3/፣10/2/፣36 | 75877 | የኢትዮጲያ የህግ ባለሙያ ሴቶችማህበር<br>እና<br>የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ | መስከረም 23/2005 | 454 |